# ትንቢተ ኤርምያስ

ከቀደምት አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ
የመጣው ንባቡና ትርጓሜው
(በአንድምታ)

በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ
ለመጀመሪያ ጊዜ ታተመ

አሳታሚ፡- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

## መግለጫ

እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ ነቢያት፣ ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት፣ አሠረ ሐዋርያትን ለተከተሉት ሊቃውንት አዝዞ ያጻፋ ቸውና ምእመናን በቤተ ክርስቲያን የተቀበሏቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ሰማንያ አንድ መሆኑ ፍትሐ መንፈሳዊ (ፍትሐ ነገሥት) በተሰኘው መጽሐፍ አንቀጽ ፪ ላይ ተደንግጓል።

እነርሱም መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት (ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን) በመባል የሚታወቁ ሲሆን፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት፣ ሕግና ሥርዓት፣ ታሪክና ባህል መሠረት በመሆናቸው በምእመናን ሕይወት ጸንተውና ተጠብቀው እስከ አሁን ድረስ የኖሩና ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው።

ብሉይ ኪዳን፣ ልዑል እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ለነበሩት አበው በሕገ ልቡና፣ ከሙሴ እስከ ልደተ ክርስቶስ ለነበሩት ሕዝበ እስራኤል፣ በሕገ ኦሪት የተነገረው ተስፋ እንደሚ ፈጸም የገባው ቃል ኪዳን ነው። (ገላ. ፫: ፲፮ - ፲፯)

ሐዲስ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝቡ የሰጠውን የድኅነት ተስፋ በጊዜው ጊዜ መፈጸሙን ያረጋገጠ አማናዊና ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ነው። (ዕብ. ፱:፲፮)

«እስመ ብዝኀ ጠበብት መድኃኒተ ዓለም ውእቱ» እንደተባለው ሊቃውንት ያሉት ሀገርና ሕዝብ አዋቂ እንደሚሆን የታመነ ነው፤ ምክንያቱም ሊቃውንት ያሉት ሕዝብ ችግር አይኖርበትምና ነው ።

«ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ተብሎ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የተሰጣት እናት ሀገራችን፣

www.ethiopianorthodox.org

በብሉይ ኪዳን፣ ሕገ ኦሪት፣ በሐዲስ ኪዳን፣ ሕገ ወንጌል ተሰብኮ ላታል:: ለትምህርት፣ ለሥርዓት፣ ለታሪክና ለሕግ ምንጭ የሆኗት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕ ፍት፣ ኑፋቄ በዓለም ላይ ከመዘራቱ አስቀድሞ የገቡላትና የተቀበ ለቻቸው በመሆኑ ትምህርቷም ሆነ እምነቷ በጌታችንና በመድ ኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በነቢ ያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የጸና ነው::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ብሔራዊት፣ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት እንደመሆኗ መጠን ጥንታውያን የሆኑ ጥበባትና ልዩ ልዩ የትምህርት ዓይነቶች አሏት፤ ከእነዚህም ውስጥ ሊቃውንቱን ዐራት ዓይና የሚያሰኛቸው የቅዱሳት መጻሕፍት የትርጓሜ ስልትና ትምህርት ነው:: ሥርዓተ ትምህርቱም በዐራት ዐበይት ጉባዔያት የተከፈለ ሲሆን ዐራቱ ጉባኤያት በመባል የሚታወቁትም መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት፣ መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው::

ቤተ ክርስቲያናችን ከተቀበለቻቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕ ፍትም ውስጥ አንዱ ትንቢተ ኤርምያስ ነው :: ነቢዩ ኤርምያስ ከዐራቱ ዓበይት ነቢያት አንዱ ሲሆን የነበረበትም ዘመን ከ626 እስከ 560 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው::

ስለሆነም የእምነቱ ግለት ያልበረደበት ማንኛውም የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በምታስተምረው እምነት መሠረት ለሚቀ ርብለት ጥያቄ መልስ ይሰጥበት፣ እምነቱን በትክክል ይመሰ ክርበት ዘንድ በብሉይና ሐዲስ ኪዳን ማዕከልነት በጥንታውያን ሊቃውንት በትርጉም ተቀነባብረው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስፈልጉት እሙን ነው::

በመሆኑም ቀደም ሲል በዳግማዊ አፄ ምኒልክ መታሰቢያ በአታ ለማርያም ገዳም የመጻሕፍተ ብሉያት መምህር የነበሩት መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ ያስተምሩበት የነበረው ትንቢተ ኢሳይያስ አንድምታ ትርጓሜ ታትሞ ፣ ለሚያስተምሩ መምህራን፣ ለሚማሩ ደቀ መዛሙርትና ለመላው ሕዝበ ክርስ ቲያን ጠቃሚ እንደሚሆን ታምኖበት በዚሁ ዓመት ታትሞ በመሰራጨት ላይ በመሆኑ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል::

በቀጣይም የመጻሕፍተ ብሉያትን አንድምታ ትርጓሜ ለማሳተም ካለን ዕቅድ አኳያ የትንቢተ ኤርምያስ አንድምታ ትርጓሜ በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ፣ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅታችን አሳታሚነት በአስቸኳይ ታትሞ ለሊቃ ውንቱ፣ ለደቀ መዛሙርቱና ለምእመናኑ እንዲደርስ አድርገናል:: በተከታታይም ሌሎቹ የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ በቅደም ተከተል እየታተሙ ብሥራ ላይ እንደሚውሉ ጽኑ እምነት አለን ::

«በረከተ አምላኩ ለዝንቱ ነቢይ የሀሉ ምስሌነ»

አባ ጳውሎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ፤፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም፤
## ዘኤርምያስ፡ነቢይ፤

ኤርምያስ፡ማለት፡ብርሃን፡ዘተፈነወ፡ እምነበ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ ኦሪት፡ማለት፡ብርሃን፡እግዚአብሔር፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፤ ኤር ፡ ትርያሬስ ፡ ማለትም፡ብርሃን፡ማለት፡እንደሆነ፤ ወወረደ ፡ ኤር ፡ ቅዱስ ፤ ያለውን ፡ ብርሃን፡ ቅዱስ ፡ ብለው፡ እንዲተ ረጕሙ፤ትውልዱም፡ከቤተ፡ክህነት፡ ነው፤ አገሩ ፡ አናቶት ፡ ይባላል፤ መንፈስ፡ ቅዱስን ፡ መቀበሉ ፡ በማኅፀን፡ ነው፤ኤርምያስና፡ዮሐንስ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መቀበላቸው ፡ በማኅፀን ፡ ነውና፤ ወናሁ ፡ ቀደስኩከ፡ እንበለ ፡ ትፃእ ፡ እምከርሠ፡ እምከ ፤ እንዲል፡፩፡፭፤

ወነቢየ፡ረሰይኩከ፡ከመ፡ትኩን፡መምሀረ፡
ለአሕዛብ ፡ መምህር ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ነቢይ፡አደረግሁህ፡አለው፤

ወእቤ፡አሌ፡ሊተ፡እስመ፡ሕፃን፡አነ፡
ሕፃን፡ነኝና፤አንድም፡ሕፃነ፡አእምሮ፡ ነኝና፡ወዮልኝ፡አለ፤

ወኢትበል ፡ ወሬዛ ፡ አነ ፡ እኔ ፡ ሕፃን ፡ ነኝ፤ አንድም ፡ ሕፃነ ፡ አእምሮ ፡ ነኝ ፡ አትበል፤

እስመ፡ተሐውር፡ኀበ፡ኵሉ፡ኀበ፡ፈነውኩከ፡
አሕዛብን ፡ ታስተምር ፡ ዘንድ ፡ ትሄዳለህና ፤ ትንስት ፡ ወትሕንፅ ፡ ትትክል ፡ ወትሥሩ፤

እስራኤልን ፡ በሕንፃ ፡ ይመስላቸ ዋልና፤ትንስት፡ወትሕንፅ፡ትትክል፡ ይመስላቸዋልና፤ትትክል፡ወትሥሩ፡

አለ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ትትክል ፡ ወትሕንፅ ፡ ማለት፡ ከአምልኮተ፡ ጣዖት ፡ ወደአም ልኮተ ፡ እግዚአብሔር፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ቢመለሱ፡እየጸለየ፡ጸጋ፡ክብር፡ያሰጣ ቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ትንስት ፡ ወትሥሩ ፡ ማለት ፡ ከገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደገቢረ፡ኃጢአት፡ከአምልኮተ፡እግ ዚአብሔር ፡ ወደአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ቢሄዱ፡እየጸለየ፡አባር፡ቸነፈር፡ያመ ጣባቸዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ፤ ይህም ፡ ኤርምያስ ፡ በአሕዛብ ፡ ስለ፡ አራት ፡ ነገር፤በእስራኤል፡ስለ፡ሦስት፡ነገር፡ ተናግሯል፤

በአሕዛብ ፡ ስለ ፡ አራት ፡ ነገር ፡ እንደ ምነው ፡ ቢሉ ፡ አሕዛብ ፡ አምላክ ፡ ሕዝብ፡ነው፡እንጂ፡አምላክ፡አሕዛብ፡ አይደለም ፡ ይላሉ ፤ ግድ ፡ አምላክ ፡ አሕዛብ፡ወሕዝብ፡እንደሆነ፡ተናግሮ ባቸዋል፤እንደ፡ኢሳይያስ፡ተርጕም፤ በእስራኤል፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ እንደ ምነው፡ቢሉ፡በደብረ፡ሲና፡የተሠራላ ቸውን፡ ሕግ፡ ቢያፈርሱ ፤ አባር ፡ ቸነ ፈር፡እንዲመጣባቸው፤ ፄዋዌ፡እንዲደ ረግባቸው ፤ ሚጠት፡ እንዲደረግ ላቸው፡ ተናግሯል፤ ጨርስ፤ አንድም፡ በእስራኤል ፡ ቅሉ ፡ ስለአራት ፡ ነገር ፡ ተናግሯል፤ ዘሂ ፡ ውስተ፡ ኩናት ፡ ለኩናት ፤ ወዘሂ ፡ ውስተ ፡ ረኃብ ፡ ለረኃብ፤ ወዘሂ፡ውስተ፡ሞት፡ለሞት፡

www.ethiopianorthodox.org

ኤር፡ ፴፫፡ ፲፩፡ ብሎ፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ናቡ
ከደነፆር፡ በነገሠ፡ በዓሥራ፡ ስምንት፡
ዘመን ፡ ወአመ ፡ ራብዕት ፡ አመተ ፡
መንግሥቱ፡ ለኢዮአቄም፡ ኢዮአቄም፡
በነገሠ፡ በአራት፡ ዘመን፡ ኤርምያስ፡
ባሮክን፡ ጠርቶ ፡ ኢዮስያስ ፡ ከነገሠ፡
ካስራ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡
የሆነውን ፡ ጽፈህ ፡ ወስደህ፡ አንብብ
ላቸው ፡ አለው፤ ኤርምያስ ፡ በነቢ
ይነት፡ መነሣቱ፡ ኢዮስያስ፡ በነገሠ፡
ባስራ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፡
እሥራኤል፡ ታኅሣሥ፡ ፲፱፡ ቀን፡ ጾመ፡
አስተሥርዮን፡ ይጾማሉ፤ ከዚያ፡ ጽፎ፡
ወስዶ፡ አነበበላቸው፤ ይህንማ፡ እኛ፡
ብቻ፡ ሰምተነው፡ ይቀራል? ንጉሡም፡
ይስማው፡ እንጂ፡ አንተና፡ ኤርምያስ፡
ተሠወሩ፡ ብለው፡ ወስደው፤

ወአንበርዎ፡ ውስተ ፡ ህዋረ ፡
ኤልስማስ፡ ጸሐፊ ፡ ወስደው ፡
ከጸሐፊው፡ መደብ፡ አኑረውት፡ ገቡ፤
ንጉሡ፡ ኤልያቄም፡ ነው፤ ወይነብር፡
ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ቤተ፡ ምክራም ፡
ይላል፤ ቤተ፡ ምክራም፡ የሚለው፡ የእ
ሥራኤል፡ ነገሥታት ፡ በክረምት ፡
ከቈላ ፤ በበጋ ፡ ከደጋ ፡ ይከርማሉ ፤
አንድም፡ በክረምት፡ ከምድር፡ ቤት፤
በበጋ፡ ከደርብ፡ ይቀመጣሉ፤

ወአፍሐመ ፡ እሳት ፡ ይነድድ ፡
ቅድሜሁ፡ ይላል፤ ኤር፡ ፴፮፡ ፳፪፤
እሳት፡ በብረት፡ ማንደጃ፡ ሆኖ፡ በፊቱ፡
ይነድ፡ ነበር ፤ ይሁዳም ፡ ይለዋል፤
ይሁዲም ፡ ይለዋል፤ የእኅቱም፡ ልጅ፡
ነው፡ ይላሉ፤ ጋሻ፡ ጃግሬው፡ ነውም፡
ይላሉ፤ እሱን፡ አምጣ፡ ብሎ፡ ሦስት፡
ቅጠል ፡ አራት ፡ ቅጠል ፡ እንዳነበ
በለት፤ አንድም ፡ ሦስት ፡ ጥራዝ ፡
አራት፡ ጥራዝ፡ እንዳነበበለት፤

ወመተሮ፡ በመጥባሕተ፡ ኤልስማስ፡
ጸሐፊ፡ በጸሐፊው፡ ወቅለምት፡ ካርያ፡
እያረፈ፡ እያረፈ፡ (እየቆረጠ)፡ ከእሳት፡
ላይ ፡ ጥሎታል ፤ ከዚያ፡ በኋላ ፡
ባሮክንና፡ ኤርምያስን፡ አምጧቸው፡
አለ ፤ ጌታ ፡ ሠወራቸው ፤ ሴዴቅያስ፡
በነገሠ ፡ በስምንት ፡ ዓመት ፡ በእስ
ራኤል፡ የለ፡ ግብር፡ በሰማይ፡ የለ፡ ዱር፡
ብሎ፡ አዋጅ፡ ነገረ፤ የባቢሎን፡ ሰዎች፡
ዘመቱ፤ ኤርምያስ ፡ የነሱ ፡ ዳፋ፡
በቅቶኝ፡ እማረክ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡
ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ አናቶት ፡ ሲሄድ ፡
በጥሬው ፡ ኤርምያስ፡ ግን ፡ ተርቦ ፡
ምግብ ፡ ለመሻት ፡ ሲሄድ ፡ ሱራስ ፡
ሶርሒያ፡ ይለዋል፤ በአንቀጸ፡ ኤፍሬም፡
አገኘው፤ ይህ ፡ ቀጣፊ ፡ ነቢይ ፡ የተና
ገረው ፡ ባይሆንለት ፡ ከለዳውያንን፡
አምጥቶ፡ ሊያስማርካቸው፡ ይሄዳል፡
ብሎ ፡ ወስዶ ፡ ሰጣቸው ፤ ገርፈው ፡
አሥረው፡ ከጸሐፊው፡ ከናታን፡ ደጅ፡
ካለው፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ አኑረውታል ፤
በኋላ፡ ኢልያቄም፡ ወስዶ፡ ጠይቆታል፤
የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ንገረኝ፡
አለው፤ ምንም፡ አላይ፡ አለው፤ በግድ፡
ዘበዘበው፤ እስራኤል፡ ይማረካሉ፤ ኢየ
ሩሳሌም፡ ትጠፋለች፡ አለው፤

ወአዕቀቦ፤ የሚናገረውን፡ ስሙት፡ አለ፤
ለናቡከደነፆር ፡ የተገዛ ፡ የሕይወት፡
መገኛ፡ ይሆናል ፤ ለናቡከደነፆር ፡
ያልተገዛ፡ ይሞታል ፡ እያለ ፡ ሲናገር ፡
ሰምተው ፡ የኛን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡
ተድላ ፡ ደስታችንን፡ አይናገርም ፤ ዘወ
ትር፡ መከራችንን ፡ ነው፤ የእስራኤልን ፡
ቃላቸውን ፡ ከመምከር፡ እጃቸውን፡ ከመ
ወርወር፡ አደከመው፡ አሉት፤ እኔን፡ ምን፡
[illegible]



እንደወደዳችሁ፡ አድርጉት፡ አላቸው፤
ወስደው፡ ከአዘቅተ፡ ኰስሕ፤ ጣሉት፤
መልአኩ፡ እንዳይሸተው፡ ዕፀ፡ ፊላስን፡
(ፒላሳን) ፡ ከገነት ፡ አምጥቶ ፡
ሰጥቶታል ፤ በኋላ ፡ ከወደአገራችን ፡
አቤሜሌክ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ሄደ፤ ኤርም
ያስን፡ ከዚህ፡ ጥለውት፡ ሊሞት፡ ነው፤
አራት ፡ ሰዎች፡ ይዘህ ፡ ሂደህ ፡
አውጣው፡ አለው፤ ሂዶ ፤ በዘያሜንዩ ፡
ሎቱ ፡ አፍራስ ፤ ፈረስ፡ የሚወለውሉ
በትን፡ ጨርቁን ፡ ከዚያ ፡ አግኝቶ ፡
ጨርቁን፡ ጣለለት፤ ከእጅህ፡ እሠረው፡
አለው ፤ በኋላ ፡ ገመዱን ፡ ሰድዶ ፡
አወጣው፤ ከከተማ፡ ሂዶ ፡ ተቀመጠ ፤
ከዚህ ፡ በኋላ፡ በሰባተኛው ፡ ሰዓተ ፡
ሌሊት፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤ ከኤርምያስ፡ ዘንድ፡ ቃለ፡
እግዚአብሔር ፡ መጣ ፤ ተነገረ ፤
አንተና፡ ባሮክ፡ ወደቤተ፡ መቅደስ፡ ኑ፡
የምነግርህ ፡ አለና ፡ አለው ፤
ተነሥተው፡ ሲሄዱ ፡ መላእክት ፡
ባጭር፡ ባጭር ፡ ታጥቀው ፡ ቲሃ ፡
ቲሃቸውን ፡ ይዘው፡ አገኛቸው ፤
ደነገጠ፤ ትሜጡኑ፡ ዛተ፡ ሀገረ፡ ውስተ፡
እደ፡ ጸላዕታ፤ አለው፤ (ተረፈ፡ ኤር)፡
አዎን፡ አለው፤ እስከ፡ ዛሬም፡ ድረስ፡
ያልጣልኋት ፡ ያንተ ፡ ጸሎት ፡ ቀን ፡
እንደ፡ ግርግዳ፤ ሌሊት፡ እንደ፡ ተራዳ፡
ሆኖ፡ እየጠበቃት፡ ነው፡ አለው፤

ኤርምያስ፤ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ የምነጋ
ገረው ፡ አለኝና ፡ ቆዩ ፡ ብሎ ፡ መላእ
ክትን፡ ለመነ፤ ጌታም፡ ከወዳጄ፡ ከኤር
ምያስ፡ ጋራ፡ የምነጋገረው፡ አለና፡ ቆዩ፡
[illegible]

ምንተ ፡ ንግበር ፡ በእንተ ፡ ንዋየ ፡
ቅድሳቲነ ፤ ዘንትቀነይ ፡ በኀቡዕ ፡
አለው፡ ዘንትጌበርም፡ ይላል፤
አወፍዮ፡ መራኁተ፡ ለፀሐይ፤ ፀሐይ፤
ለበላው ፡ መሬት ፡ አደራ ፡ ስጠው ፡
አለው ፡ (ተረፈ ፡ ኤር)፤ በቋንቋው፡
መሬቱን፡ ፀሐይ፡ ይለዋል፤

ወስዶ ፡ ምድር ፡ ተመጠዊ ፡ ስነኪ ፤
አላት፤ መሬት ፡ ተከፍቶ፡ ዋጠው ፤
ከሰባ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በሚጠት ፡
ቢያወጡት ፡ መብራቱ ፡ ሳይጠፋ ፡
ልብሰ፡ ተክህኖው፡ ሳይበላሽ፡ ዕጣኑ፡
ሲጤስ፡ አግኝተውታል፤

አርእየኒ፡ ዘእገብር ፡ በእንተ ፡
አቤሜሌክ ፡ ኢትዮጵያዊ ፤ አለው፤
ባሮክና ፡ አቤሜሌክ ፤ ኢታርእየኒ፡
ሙስናሃ ፤ ለኢየሩሳሌም ፡ እያሉ ፡
ይጸልዩ፡ ነበርና፡ ባሮክን፡ ዓፅመ፡ ነገሥ
ታትን ፡ አስጠብቀው፤ አቤሜሌክን፡
ድውይ፡ የምንፈውስበት፡ ዕፀ፡ በለስን፡
አምጣ፡ በለው ፡ አለው፤ ቍራንቀ
ሬውን ፡ ይዞ ፡ ተነሥቷል፤ ከዚህ ፡
ያቆዩታል፤ ወነፍሐ፡ ዓቢይ፡ መልአክ፡
ቀርነ፡ ዓቢየ፤ ይላል፡ መልአኩ፡ ቅዱስ፡
ሚካኤል፡ ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል ፡
የነጋሪት፡ ድምፅ፡ አሰማ፤ ከዚህ፡ በኋላ፤
ባኡ፡ ከለዳውያን፡ ወዔውውዎሙ፡ ለዕ
ብራውያን፤ ብሎ፡ መልአኩ፡ ቅዱስ፡
ሚካኤል፡ በሩን፡ ከፍቶ፡ አስገባቸው፤
እስራኤል ፡ ተማረኩ ፤ ናቡከደነፆር ፡
ዲብላታንን፡ ከተማ፡ አድርጎ፡ ተቀምጦ፡
ሳለ፡ በነሐሴ፡ በ፳፡ ቀን፡ ናቡዛርዳንን፡

www.ethiopianorthodox.org

ሂደህ፡ ቤተ፡ መቅደስን ፡ አፍርሰህ ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ ይዘህ፡ ሕዝቡን ፡ ማርከህ ፡ ና፡ አለው፤ ታሪክ ፡ እንደ ፡ ኢሳይያስ ፡ ድውይ ፡ የምንፈውስበት ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፡ ብለን ፡ ነበርና ፡ ዕፀ ፡ በለሱን ፡ ይዞ ፡ ሲመለስ፡በጊዜ፡ቀትር፡ዋዕየ፡ፀሐይ፡ ተሰማው፤ ወርእየ ፡ ዕፀ ፡ ጽፍቅተ ፤ እንዲል ፡ (ተረፈ ፡ ኤር) ጽፍቅ ፡ ዱር ፡ አይቶ ፡ ሂዶ ፡ ተኛ ፤ ታሪክ፡ እንደ ፡ ዳዊት፡ከመቃብሩ፡አምጥተው፡ገጥመ ውታል ፡ እስከሚለው ፡ ተርክ፤ የኤር ምያስ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም፤ እስክንድር ፡ የሚባል ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነበር፤ መንግሥት ፡ ለማዳረስ፡ ወደሀገ ራቸው፡ መጣ፤ ይቺ ፡ እስክንድርያ ፤ ማይ ፡ ሐጹራ ፡ ማይ ፡ ጽንፋ፣ ይላታል፤

የብረት ፡ ምሰሶ ፡ እያቆመ፡ መረባ ፡ እየጣለ ፡ ልማደ፡ ሰብእ ፡ ግብረ ፡ ሰብእ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ እንዲሄድ ፡ እያደረገ፡ ሠርቶታል፤ ኋላ ፡ አዞ፡ ጉማሬ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ መጥቶ ፡ አነዋወጠው፤ ከተማው ፡ ተነዋወጠ፤ ምን ፡ ባደርግ፡ ይሻለኛል ፡ አለ፤ ኤርምያስ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ የሱን፡ አጥንት፡አምጥተህ፡ከመካከሉ፡አኑር፡ አሉት፤ አምጥቶ ፡ ቢያኖረው ፡ ጸጥ ፡ ብሏል፤ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ነው፤ ይህም ፡ ተጽፎ ፡ ሲነበብ ፡ ጨርስ፤ ይህ ፡ አርእስት ፡ ነው፤ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ለመ ጻሕፍት ፡ አርእስት ፡ ሲሰጡ ፡ አርእስት፡ ሰጥተውታል፤ እሱ ፡ ግን፡ ነገሩን ፤ ወኮነ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ያመጣዋል።



## ምዕራፍ ፡ ፩

፩፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ ወልደ ፡ ኬልቅዩ ፡ ዘእምካህናት ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ አናቶት ፡ በብሔረ ፡ ብንያም፡

ወልደ ፡ ኬልቅዩና ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ አናቶት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ከካህናት፡ ወገን ፡ ከሚሆን ፡ ከኬልቅዩ፡ ተወልዶ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ባለች ፡ በአናቶት ፡ ወደሚኖር ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል፤ ዘመጽአ ፡ ዘተነግረ ፤ ሲል ፡ ነው፤ መጥቶ፡ ተነገረ፤ አንድም ፤ ዘይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አናቶት ፤ ይላል፤ በብንያም፡ አገር ፡ ከሚኖሩ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ከተወለደ ፡ ከኬልቅዩ፡ ወደ ፡ ተወለደ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር፡ የእግዚአብሔር፡ ቃሉ ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ፤ አንድም፤ ወዘይነብር ፡ ውስተ፡ አናቶት፡ ይላል፤ ከካህናት ፡ ወገን፡ ከሚሆን ፡ ከኬልቅዩ ፡ ወደተወለደ ፤ ተወልዶም ፡ በብንያም፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ባለች፡ በአናቶት ፡ ወደሚኖር ፡ ወደኤር ምያስ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ፤ መጽአ፡ ተነግረ ፡ ዘመጽአ ፡ ዘተነግረ ፤ ሲል ፡ ነው፡ የመጣ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ መጥቶ፡ የተነገረ፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው፤

፪፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤየ ፡ በመዋዕለ ፡ ኢዮስያስ ፡ ወልደ ፡ አሞፅ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ እምአመ ፡ ፲ወ፫ዓመተ ፡ መንግሥቱ፤

ኀቤየ፡ ለኤርምያስ ፡ ነው ፤ ንጉሡ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም ፡ ይቀጣል፤

ኢዮስያስ ፡ ከነገሠ ፡ ካሥራ ፡ ሦስተኛው፡ ዘመን ፡ ጀምሮ፡ የሚሆነውን፡ ንገረው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደኤር ምያስ ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ፤ አንድም ፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤየ ፤ ይላል ፡ ዘኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ ያለውን ፡ ሠለቱ ፡ ምዕት ፡ ለመጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ አርእስት ፡ ሲሰጡ ፡ ሰጥተውታል ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ ወልደ፡ ኬልቅዩ፤ ያለውን ፡ የኋላ ፡ ሰዎች፡ የአርእስት ፡ አርእስት ፡ ሰጥተዋል ፤ ወኮነ፡ ቃለ ፤ እግዚአ ብሔር፡ ኀቤየ ፡ ያለውን ፡ እሱው ፡ ራሱ፡ ተናግሮታል፤ ኢዮስያስ ፡ ከነገሠ ፡ ካሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ አስተምር ፡ የሚል፡ ቃል ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ ፡ አለ፤

፫፤ ወኮነ ፡ በመዋዕለ ፡ ኢዮአቄም ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ እስከ፡ ተፈጸመ ፡ ፲ወ፩ ፡ ዓመተ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ፤

የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮስያስ፡ ልጅ ፡ የሴ ዴቅያስ ፡ ዓሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የሚሆነውን ፡ በይ ሁዳው፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ ዘመን ፡ የሚደረገውን፡ ነገር፡ ንገረው ፡ የሚል፤

እስከ ፡ አመ፡ ተፄወወት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በሐምስ፡ ወርኀ፤

ባምስተኛው ፡ ወር ፡ በነሐሴ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ እስክትማረክ፡ ድረስ ፡ የሚሆ ነውን ፡ ንገረው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ መጥቶ፡ ተነገረ፤ ምንው ፡ የተማረኩ ፡ በሐምሌ ፡

www.ethiopianorthodox.org

መቅደስን ፡ ያቃጠለ ፡ ያፈረሰ ፡ በሐምሌ፡ ነውና፤ አንድም ፡ ፍጹም፡ ጺዋዌም፡የተደረገ፡በሐምሌ፡ነውና፤

፬፤ ወኮነ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኀቤየ፡
ከላይ፡ የተናገረውን ፡ ከዚህ ፡ ደግሞ፡ ተናገረው፤ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ነገሩን ለማጽናት ፡ ለማስረዳት ፡ ነው፤ አንድም፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ፡ ወደፊት ፡ ለሚያመጣው፡ነው፤

ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤

፭፤ ዘእንበለ ፡ እፍጥርከ ፡ እምከርሠ ፡ እምከ፡አእመርኩከ፡
በናትህ ፡ ማኅፀን ፡ ደሙን ፡ አርግቼ፡ ሳልፈጥርህ ፤ አንድም ፡ ከመፍጠሬ፡ አስቀድሞ ፡ አወቅሁህ፤ አንድም፡ ወደድኩህ ፡ አለኝ ፤ አእመርኩከ ፡ ሙሴ፡ወልደ፡እንበረም፡እንዲል፤

ወዘእንበለ፡ትጻእ፡እማኅፀን፡ቀደስኩከ፡
ከናትህም ፡ ማኅፀን ፡ ከመውጣትህ፡ አስቀድሞ፡ገና፡ሳትወጣ፡አከበርሁህ፤ ሾምኩህ ፤ ኤርምያስ ፡ ዮሐንስ ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን ፡ በማኅፀን ፡ አግኝ ተዋል፤

ወነቢየ፡ረሰይኩከ፡ለአሕዛብ፡
ለእስራኤልም፡መምህር፡አደረግሁህ፤ አሕዛብ፡ያላቸው፡እስራኤል፡ናቸው፤ ግብረ፡አሕዛብ፡ይሠራሉና፤አንድም፡ በጸያፍ፡የገባ፡ነው፤አንድም፡ስለብዛ ታቸው፡አሕዛብ፡ብሏቸዋል፤ይህንንም፡ ይዘው፡የወዲያ፡ሰዎች፡ ይነቅፉናል፤ ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፤ ነቀጥንና ፡ ነጥብን ፡ ሲራኩንና መሥመሩን ፡ ለይተው ፡ አያውቁም ፡ ብለው ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ መምህር፡አደረግሁህ፤

፮፤ ወእቤሎ ፡ አሌ ፡ሊተ ፡ እግዚአ ፡ እግዚእየ፡
እኔም ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ወዮልኝ ፤ አንድም ፡ ወዮታ ፡ ለኔ ፡ ይገባኛል ፡ አልኩት፤

ናሁኬ፡ኢይክል፡ተናግሮ፡
ወነቢየ ፡ ረሰይኩከ፡ ለአሕዛብ ፤ ብሎት፡ ነበረና ፡ እነሆ ፡ እስራኤልን፡ ማስተማር አይቻለኝም፤ አንድም ፡ ኢይክል፡ተናጽሮ፡ይላል፤ስንኳንስ፡ እስራኤልን፡ማስተማር፡ፊታቸውን፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ማየት ፡ አይቻለኝም ፡ አልኩት፤

እስመ፡ንዑስ፡አነ፡
ሕፃን ፡ አእምሮ ፡ ነኝና ፤ አንድም ፡ በቁሙ፡ሕፃን፡ነኝና፤

፯፡ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡ኢትበል፡ ወሬዛ፡አነ፡
እግዚአብሔርም፡ሕፃን፡አእምሮ፡ነኝ፡ አትበል፤ አንድም ፡ ሕፃን ፡ ነኝ ፡ አትበል፡አለኝ፤

እስመ፡ተሐውር፡ኀበ፡ኵሉ፡ፈነውኩከ፡
አስተምር፡ብዬ፡ወደምሰድህ፡አገር፡ ሁሉ፡ትሄዳለህና፤

ወትነግር፡ኵሎ፡ዘአዘዝኩከ፡
አስተምር፡ብዬ፡ያዘዝሁህንም፡ታስተ ምራለህና፤አንድም፡የምታስተምር፡ [illegible]



፰፡ ወኢትፍራኅ፡እምገጾሙ፡
ከፊታቸውም፡የተነሣ፡አትፍራ፤

እስመ፡ሀለውኩ፡ምስሌከ፡
እኔ፡ካንተ፡ጋራ፡በረድኤት፡አለሁና፤

ወአድኅነከ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ከእስራኤልም፡እጅ፡አድንሃለሁ፡አለ፡ እግዚአብሔር ፤ አንድም ፡ እግዚአ ብሔር፡ ከእስራኤል ፡ እጅ ፡ አድን ሃለሁ፡ ብሏልና፡ አለ፤ ራሱን ፡ አርቆ ፡ ይናገራል፤

፱፤ ወሰፍሐ ፡ እዴሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤየ፡
እግዚአብሔርም፡እጁን፡ዘርግቶ፡በአ ንበሮተ፡እድ፡ሾመኝ፤

ወገሠሠኒ፡አፉየ፡
አፌን ፡ዳሰሰኝ ፤ ሀብተ ፡ ትንቢትም፡ አሳደረብኝ፤ አንድም፡ትንቢቱን፡እን ድናገረው፡አደረገኝ፤

ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤

ናሁ፡ወደይኩ፡ቃልየ፡ውስተ፡አፉከ፡
እነሆ፡ትንቢቱን፡እንድትናገር፡አደረ ግሁህ፤

፲፤ ወናሁ ፡ ሤምኩከ ፡ዮም ፡ ለአሕዛብ ፡ ወለነገሥት ፡ ትሥርዎሙ ፡ ወትንስቶሙ ፡ ወታጥፍዖሙ፡ወትሕንፅ፡ወትትክል፡
ትተክላቸው ፣ ትነቅላቸው ፣ ትሠራ ቸው፣ታፈርሳቸው፡ዘንድ፡ከዚያም፡ በኋላ፡ጨርሰህ፡ታጠፋቸው፡ዘንድ፡ ለሠራዊቱ ፣ ለነገሥታቱ ፡ እነሆ ፡ [illegible] አለኝ፤

ሐተታ፡እስራኤልን፡በተክል፡ይመስ ላቸዋልና ፣ ትትክል ፡ ትሥሩ ፤ አለ ፡ በሕንፃ ፡ ይመስላቸዋልና ፡ ትሕንፅ ፡ ትንስት ፡ አለ ፣ ታጥፍዖሙ ፡ የወል ፡ ነው፤

፲፩፤ ወነበበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳግመ ፡ ወይቤለኒ፡
ዳግመኛም፡እግዚአብሔር፡ተናገረኝ፤ እንዲህ ፡ አለኝ፤ ሐተታ ፡ ከላይ ፡ ይቤለኒ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ለዚያ፡ ዳግመ ይቤለኒ፡አለ፤

ምንተ፡ትሬኢ፡ኤርምያስ፡
ኤርምያስ ፡ ምን ፡ ታያለህ ፡ አለኝ፤ ሐተታ ፡ ምንተ ፡ ትሬኢ ፡ ማለቱ ፡ ያየው፡ ጠፍቶት ፡ አይደለም ፤ ሊያና ግረው፡ነው፤

ወእቤ፡ቀስታመ፡ከርካዕ፡እሬኢ፡
የለውዝ ፡ መንደርዮ ፡ አያለሁ ፡ አልኩት፤

፲፪፤ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናየ ፡ ርኢከ፡
እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አይተሃል ፡ አለኝ፤ የለውዚ ፡ በሎታ ፡ ማየትህ፡ደግ፡ነው፡አለኝ፤

እስመ፡እትጋህ፡አነ፡ከመ፡እግበር፡ዘነበብኩ፣
አደርገዋለሁ ፡ ብዬ ፡ የተናገርኩትን፣ ሳደርገው ፡ እተጋለሁና፤ ሐተታ ፡ ይህ ሎሚ ፡ ለትጋት ፡ አብነት ፡ ነው፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ፡ ዛሬ ፡ ባሕታ ውያን ፡ ለትጋት ፡ አብነት ፡ ይሆናል ፡ እያሉ ፡ መስቀል ፡ መቍጠሪያ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እያደረጉ ፡ ይይዙታል፡ አንድም ፡ ወእቤ፡ ቀስታመ ፡ ከርካዕ ፡ ናቡከደነ ፆርን ፡ አያለሁ ፡ አልሁት፡ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናየ ፡ ርኢከ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አይተሃል ፡ አለኝ፤ማርያምን ፡ማየትህ ፡ደግ ፡ ነው፤ እስመ ፡ እተግህ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ እግበር፡ ዘነበብኩ፡

በእስራኤል ፡ አደርገዋለሁ፡ ብዬ ፡ የተናገርኩትን ፡ ፈዋፄ ፡ ላደርገው ፡ እተጋለሁና ፤ አንድም ፡ ወእቤ ፡ ቀስታመ ፡ ከርካዕ፡

ወልድን ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ አየሁት ፡ አልኩት ፤ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናየ ፡ ርኢከ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አይተሃል ፡ አለኝ ፤ እስመ ፡ እተግህ ፡ አነ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ዘነበብኩ፤

አደርገዋለሁ፡ ብዬ ፡ የተናገርኩትን ፡ ሥጋዊ፡ ላደርገው ፡ እተጋለሁና፤ አንድም ፡ ወእቤ ፡ በአጋንንት ፡ መንደርቶ፡ የሚሆንባቸው ፡ መስቀልን፡ አየሁ ፡ አልሁት ፤ ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ነገር፡ አይተሃል ፡ አለኝ፤ መስቀልን ፡ ማየትህ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ አለኝ፤ እስመ ፡ እተግህ ፡ በቀራንዮ ፡ እሰቀልበ ታለሁ ፡ ብዬ ፡ የተናገርኩትን ፡ መስቀልን ፡ ላደርገው ፡ እተጋለሁና፤

፲፫፡ ወነበበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳግመ፤
እግዚአብሔርም ፡ ዳግመኛ ፡ ተናገረኝ፤ ሐተታ ፡ ከላይ ፡ ነበበኒ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ለዚያ ፡ ዳግመ ፡ አለ፤

ወይቤለኒ ፡ ምንተ ፡ ትሬኢ፡
ምን ፡ ታያለህ ፡ አለኝ፤ ሐተታ ፡ አሁን ፡ ያየው ፡ ጠፍቶት ፡ አይደለም፤ ሊያና ግረው ፡ ሊተረጉምለት ፡ ነው፤

ወእቤ ፡ ጽሕርት ፡ ይነድድ ፡ ወገጹ ፡ መንገለ፡ ሰሜን፡
ፊቱ ፡ ወደሰሜን ፡ ዞሮ ፡ ድስት ፡ ተጥዶ፡ ሲፈላ ፡ አየሁ ፡ አልሁት፤ ይኸውም ፡ ምሳሌ ፡ ነው፤ ድስቱ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ነው፤ ውሃው ፡ እስራኤል ፡ ናቸው፤ እሳት በባቢሎን ፡ የሚቀበሉት ፡ መከራ፡ ነው፤ ፊቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ዞሯል ፡ አለ፤ ሰሜን፡ ባቢሎን ፡ ናት፤ እስራኤል፡ ተማርከው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የመውረዳቸው ፡ ምሳሌ፡ ነው፤ አንድም፡ ወእቤ ፡ ጽሕርት ፡ ይነድድ ፡ ወገጹ ፡ እመንገለ ፡ ሰሜን ፡ ይላል፤ ድስት ፡ ተጥዶ ፡ ሲፈላ ፡ ፊቱ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዞሮ ፡ አየሁት ፡ አልሁት፤ ጽሕርት ፡ ናቡከደ ነፆር ፡ ነው ፤ ውሃው ፡ ፳ኤል ፡ ናቸው ፡ እሳቱ፡ በባቢሎን ፡ የሚቀበሉት ፡ መከራ ፡ ወገጹ ፡ እመንገለ ፡ ሰሜን ፡ አለ፤ ናቡከደነፆርን፡ በፄዋዌ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ፳ኤልን ፡ ለማጥፋት፡ ሲመጣ ፡ ያየዋል፤ አንድም ፡ ወእቤ ፡ ጽሕርት ፡ ይነድድ ፡ ወገጹ ፡ መንገለ ፡ ሰሜን፤ ፊቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ዞሮ ፡ ድስት፡ ተጥዶ፡ ሲፈላ ፡ አየሁ ፡ አልሁት፤ ድስቱ፡ ጥጦስ ፡ ነው ፤ በውስጡ ፡ ያለው፡ ውሀ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው፤ እሳቱ ፡ ባርባ ፡ ዘመን ፡ በጥጦስ ፡ የሚቀበሉት ፡ መከራ ፡ ነው፤ ወገጹ ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ፡ ...
ፊቱን ፡ ወደሰሜን ፡ አዙረው ፡ በሰቀሉ ፡



በአይሁድ ፡ መከራ፡ ሲመጣባቸው ፡ ያያል፤ አንድም ፡ ወገጹ ፡ እመንገለ ፡ ሰሜን፡ ይላል፤ ፊቱ ፡ ከሮም ፡ ወደ ፡ ኢየ ሩሳሌም፡ ተመልሷል ፡ አለ፤ ሰሜን ፡ ያላት፡ ሮም ፡ ናት፤ ባርባ ፡ ዘመን ፡ ጥጦስ፡ አስፋስያኖስ ፡ አይሁድን ፡ ለማጥፋት ፡ ከሮም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲመጡ ፡ ያያል፤

፲፬፡ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ፤

እምገጸ ፡ ሰሜን ፡ ትትረኃው ፡ እኪት ፡ ላዕለ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር፡
በኢየሩሳሌም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ በሚኖሩ ፡ በ፳ኤል ፡ ላይ ፡ ከባቢሎን ፡ መከራ ፡ ታዝዛባቸው ፡ ትመጣለች፤ አንድም ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ፡ ትትረኃው ፡ እኬት ፡ ይላል፤ በፄዋዌ ፡ ተማርከው ፡ ወደባቢሎን፡ በሚሄዱ ፡ በ፳ኤል ፡ መከራይቱ፡ ታዝዛ ፡ ትመጣባቸዋለች፤ አንድም ፡ እምገጸ ፡ ሰሜን ፡ ትትረኃው ፡ እኪት ፡ ላዕለ፡ እለ፡ ይነብሩ ፡ በኢየሩ ሳሌም ፤ በተድላ ፡ በደስታ ፡ በሚኖሩ ፡ በአይሁድ ፡ በዐርባ ፡ ዘመን ፡ መከራዩቱ፡ ከሮም ፡ ታዝዛ ፡ ትመጣባ ቸዋለች፤ አንድም ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ፡ ትትረኃው ፡ እኪት ፡ ይላል፤ ፊቱን ፡ ወደሰሜን ፡ አዙረው ፡ ጌታን ፡ በሰቀሉ ፡ በአይሁድ ፡ በዐርባ ፡ ዘመን ፡ መከራ ዩቱ ፡ ታዝዛ ፡ ትመጣባቸዋለች ፡ አለኝ፤

፲፭፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እጼውዕ ፡ ነገሥተ ፡
...

ታት ፡ እስራኤልን ፡ ሊያጠፉልኝ፡ በፄዋዌ ፡ ከባቢሎን ፡ ጠሮቹ፡ አመጣቸ ዋለሁ ፡ አለ፡ አንድም ፡ በዐርባ ፡ ዘመን ፡ አይሁድን ፡ ሊያጠፉልኝ ፡ ጥጦስ ፡ አስ ፋስያኖስን ፡ ከሮም፡ ጠሮቹ፡ ወደኢየሩ ሳሌም ፡ አመጣቸዋለሁ ፡ አለ፡

ይመጽኡ ፡ ወያነብሩ ፡ መናብርቲሆሙ ፡ ወነቲሎሙ ፡ ቅድመ ፡ ዶዶያተ ፡ አናቅጸ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡
እጼውዕ ፡ ነሎ ፡ ነገሥተ ፡ ምድረ ፡ ሰሜን ፡ ብሎ፡ ነበረና ፡ ጦሮቻቸው ፡ መጥተውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ ደጃፍ ፡ ሁሉም ፡ ዙፋናቸውን ፡ ዘር ግተው ፡ ይቀመጣሉ፤

ወላዕለ ፡ ነሉ ፡ አረፋቲሃ ፡ ዘጥቅም፡
ግምቡን ፡ በሚከቡ ፡ አጥር ፡ ቅጥሮችም ፡ ሁሉ፤

ወላዕለ ፡ ነሉ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ፡
በይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ባሉ ፡ በጥቃቅኑ፡ አገሮችም ፡ ሁሉ ፡ ዙፋናቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ይቀመጣሉ፤

፲፮፡ ወእትናገሮሙ ፡ በነኔየ፡
ሕጌን ፡ በማፍረሳቸው ፤ አንድም ፡ በም ፈርድባት ፡ ቀን ፡ እናገራቸዋለሁ፤

በእንተ ፡ ነሉ ፡ እከዮሙ ፡ ዘኀደጉኒ፡
በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እኔን ፡ ስለተ ዉበት ፡ ክፋታቸው ፡ ሁሉ፤

ወሦዑ ፡ ለአማልክተ ፡ ነኪር፡
ልዩ ፡ ለሆኑ ፡ ለአሕዛብ ፡ ጣዖታትም፡ ስለሠዉ፡ አንድም ፡ ለአማልክት ፡ ነኪራን ፡ ይላል፡ ልዩ ፡ ለሆኑ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሰገዱ፡ለግብረ፡እደዊሆሙ፡
በእጃቸው ፡ በቃላቸውም ፡ ሥራ ፡
ለጣዖት፡ ምስል ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፡ እናገርባ
ቸዋለሁ፡

፲፯፡ ወአንተሰ፡ቅንት፡ሐቌከ፡
ኤርምያስ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እነሱ ፡
አይደለህምና ፡ ወገብህን ፡ አጽንተህ ፡
ታጠቅ፡ አለው፤ ሐተታ ፡ በዐርበኛ ፡
ግሥ፡ ይናገረዋል ፤ አንድም ፡ ወገብ ፡
ልቡናህን ፡ በንጽሕና፡ ዝናር ፡ ታጠቅ፤
አንድም ፡ ሐቌ፡ ልቡናህን ፡ በአእምሮ ፡
አጽናው፤

ወተንሥእ፡በሎሙ፡ኵሎ፡ዘአዘዝኩከ፡
ተነሥተህ ፡ ሂደህ ፡ ንገራቸው ፡ ብዬ ፡
ያዘዝኩህን፡ቃል፡ሁሉ፡ንገራቸው፤

ወኢትፍራኅ፡እምገጾሙ፡ወኢትደንግፅ፡እም
ቅድሚሆሙ፡
እምገጾሙና ፡ እምቅድሚሆሙ ፡
አንድ፡ ወገን፡ ከፊታቸው ፡ የተነሣ ፡
አንድም ፡ ከገጸ ፡ መዓታቸው ፡ የተነሣ ፤
አትፍራ ፡ አትደንግጥ፤

እስመ፡ሀለውኩ፡ምስሌከ፡ከመ፡አድኅንከ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ከእስራኤል፡እጅ፡አድንህ፡ዘንድ፡እግ
ዚአብሔር ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡
አለሁ፡ብሎታልና፤

፲፰፡ ናሁ፡ረሰይኩከ፡ዮም፡በዛቲ፡ዕለት፡
ከመ፡ሀገር፡ጽንዕት፡
ዮምና ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
ነው፤ አንተንስ ፡ ወዳጄ ፡ ኤርምያስን ፡
በዚች፡ቀን፡ለጠላቶችህ፡ለ፳ኤል፡እን
ደባልያ፡እንደ፡ቀብቲያ፡አደረግሁህ፡
ሐተታ ፡ ባልያና፡ ቀብቲያ ፡ ለጠላት ፡
እንዳይመቹ፡ አንተንም፡ ለጠላቶችህ፡
ለ፳ኤል ፡ እንዳትመቻቸው ፡ አደረ
ግሁህ፡ሲለው፡ነው፤

ወከመ ፡ ዓምደ ፡ ሐፂን ፡ ወከመ ፡ አረፍተ ፡
ብርት፡ጽኑዕ፡ለኵሉ፡ምድር፡
ለኵሉ ፡ ምድር ፡ ለሠራዊቱ ፡ እንደ
ብረት ፡ ምሰሶ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ እንደ ፡
ብርት ፡ ግድግዳም ፡ አደረግሁህ ፡
ቢገኝ፡ ጽኑ ፡ ነው፤ አንድም ፡ እስክ
ንድር፡ የብረት ፡ መረባ ፡ እየጣለ ፡
አሠርቶ፡ነበረና፡እንዲህ፡አለ፤

ወለነገሥት፡ይሁዳ፡ወለመላእክቲሆሙ፡ወለ
ካህናት፡ወለሕዝበ፡ምድር፡
ለነገሥታቱና ፡ ለመኳንንቱ ፡ ለካህ
ናቱና ፡ ለ፳ኤል ፡ ይጸብዑከ ፡ ማንሻ፤
አንድም ፡ ለን ፡ ትቶ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡
ወነገሥት ፡ ይሁዳ ፡ ወመላእክቲሆሙ፡
ወካህናት ፡ ወሕዝበ ፡ ምድር ፤ ይላል፡
ሠራዊቱና ፡ ነገሥታቱ ፤ መኳንንቱና ፡
ካህናቱ፡ ፳ኤልም፡ ሁሉ፤

፲፱፡ ወይጸብዑከ፡ወኢይክሉከ፡
ይጣሉሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንተን ፡ ድል ፡
መንሣት፡አይቻላቸውም፤

እስመ፡አነ፡ሀሎኩ፡ምስሌከ፡
እኔ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ አለሁና፤
አይክሉከ፡ብለህ፡እሠር፤
ወአድኅነከ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔርም ፡ ከጠላቶችህ ፡ ከእስ
ራኤል፡አድንሃለሁ፡አለው።

## ምዕራፍ፡፪

፩፡ ወኮነ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኀቤየ፡
[illegible]



ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡ የመጣ
የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው፡ አንድም፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡
መጥቶ፡የተነገረ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፡ ወይቤለኒ ፡ ሑር ፡ ወስብክ፡ ውስተ ፡
ዕዘኒሃ፡ለኢየሩሳሌም፡እንዘ፡ትብል፡
ቤተ፡እስራኤል፡በጆሮዋ፡ስትሰማህ፡
እንዲህ ፡ ብለህ ፡ አስተምራት ፡ አለኝ፤
ሐተታ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያላት ፡ ቤተ ፡
እስራኤል ፡ ናት፤ በሀገሪቱ ፡ ሰዎቹን ፡
መናገር፡ ነው፡፤ ያማራ ፡ ልጅ ፡ የጐጃም ፡
እንዲሉ፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

እስመ፡ተዘከርኩ፡ምሕረተኪ፡ዘእምንዕስኪ፡
ከጥቂትነትሽ ፡ ከግብፅ ፡ ከወጣሽ ፡
ጀምሮ፡በሕፃንነትሽ፡ታደርጊልኝ፡የነ
በረውን ፡ በጎነትሽን፤ አንድም፡ እኔ ፡
አደርግልሽ ፡ የነበረውን፡ በጎነቴን ፡
አሰብኩት፤

ወፍቅረኪ፡ዘአመ፡ልሕቂ፡
በአእምሮ ፡ በጐለመስሽ ፡ ጊዜ ፡
ትወጅኝ ፡ የነበረውን ፡ መውደድ፤
አንድም፡እኔ፡አንቺን፡እወድሽ፡የነበ
ረውን፡መውደድ፤

ዘተለውኪ፡ድኅሬየ፡በገዳም፡ውስተ፡ምድር፡
ዘኢይዘራዕ፡
ወዘተለውኪ፤ሲል፡ነው፤ተክል፡በማ
ይተከልበት ፤ ዘርም ፡ በማይዘራበት ፡
በምድረ፡በዳው፡ሳለሽ፡አንቺ፡እኔን፡
በሕግ፡በአምልኮት፡የተከተልሽውን፡
መከተል፤ አንድም ፡ ወዘተለውኩ ፡
[illegible] ፡ በማ
ይተከልበት ፡ ዘር ፡ በማይዘራበት ፡
በምድረ ፡ በዳውም ፡ ሳለሽ ፡ በዋል
ሽበት፡ እየዋልኩ ፡ ባደርሽበት ፡
እያደርኩ ፡ እኔ ፡ አንቺን ፡ በረድኤት፡
እጠብቅሽ ፡ የነበረውን፡ መጠበቅ ፡
አሰብኩት፤ እኮን ፡ አላት ፤ ሐተታ ፡
የወዳጅ፡ጠቡ፡ጥኑ፡ነውና፤

፫፡ ቅዱስ ፡ ፳ኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ቀዳሚ፡ማዕረሩ፡
፳ኤል ፡ ከገንዘባቸው፡ ለይተው ፡
ያመጡት፡አሥራቱ፡በኵራቱ፡ቀዳም
ያቱም፡የእግዚአብሔር፡ገንዘብ፡ነው፤

ወኵሎሙ፡እለ፡ይበልዕዎ፡ይኄስሑ፡
አሥራቱን፡በኵራቱን፡አስቀርተው፡
የበሉ፡ሰዎች፡መከራ፡መጥቶባቸው፡
ያዝናሉ፤ አንድም ፡ ቅዱስ ፡ ፳ኤል ፡
ጽኑ፡ ክቡር ፡ ልዩ ፡ የሚሆን ፡ ፳ኤል ፡
ቀዳሚ ፡ ማዕረሩ ፡ ኋላ ፡ በሐዲስ ፡
ተፈጥሮ፡ከምፈጥራቸው፡አስቀድሞ፡
ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡ ያልኋቸው ፡
፳ኤል፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡
ናቸው፤ ወኵሎሙ ፡ ፳ኤልን ፡ የሚ
ጠሉ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ መጥቶባቸው፡
ያዝናሉ፤

ወትመጽእ፡እኪት፡ላዕሌሆሙ፡ይቤ፡እግዚ
አብሐር፡
መከራዪቱም ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ታዝዛ ፡
ትመጣባቸዋለች ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

፬፡ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡
ያዕቆብ፡ወኵሉ፡በሐውርት፡ዘቤተ፡፳ኤል፡
ቤተ፡ያዕቆብ፡ሁለቱ፡ነገድ፤ወኵሉ፡
በሐውርት ፡ ዘቤተ ፡ ፳ኤል፡ ዓሥሩ ፡
ነገድ፡ አንድም ፡ ቤተ ፡ ያዕቆብ ፡
በከተማ፡ያላችሁ፤
ወኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ዘቤተ ፡ ፳ኤል፤

www.ethiopianorthodox.org

ከከተማ ፡ በአፍአ ፡ በገጠር፡ ያላችሁ፡ ሁሉ፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስሙ፡

፭፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡

ምንተ ፡ ረከቡ ፡ አበዊክሙ ፡ ላዕሌየ ፡ በዘይግ ዕዙኒ፡ከመ፡ይርኀቁ፡እምኔየ፡ነዋኀ፡
ከኔ ፡ ፈጽመው ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ እኔን፡ በሚነቅፉ ፡ ገንዘብ ፡ እኔን ፡ የሚነቅ ፉበት ፡ አባቶቻችሁ ፡ በኔ ፡ ምን፡ ተዋርዶ፡ምን፡ነቀፋ፡አገኙብኝ?

ወሖሩ፡ወተለዉ፡ከንቶ፡
ሔደው ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ተከተሉ፡ አለ፤ከንቱ፡ጣዖቱን፡አመለኩ፤

ወከንቶ፡ኮኑ፡
ከንቱ ፡ ጣዖትንም ፡ ተከትለው ፡ አልቀሩ፤እነሱም፡ከንቱ፡ሆኑ፤

፮፡ ወኢይቤሉ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ዘአውጽአነ ፡ እምድረ ፡ ግብፅ ፡ ወመርሐነ፡
ከግብፅ፡አገር፡መርቶ፡ያወጣን፡እግዚ አብሔር ፡ የት ፡ ነው ፡ አላሉም፤ አንድም፡ከግብፅ፡አገር፡ያወጣን፤

ወመርሐነ፡ውስተ፡በድው፡በብሔረ፡ዓጽ፡ ወበምድር፡ኀበ፡አልቦ፡ዕፅ፡ዘአልቦ፡ፍሬ፡ ብሔረ፡ኀበ፡ኢኬዶ፡ሰብእ፡ወኢይነብሮ፡ ዕጓለ፡እመሕያው፡
ተክል ፡ በማይተከልበት ፡ ውሀ ፡ በሌለበት፡ዘር፡በማይዘራበት፡ሰው፡ በማይረግጠው ፡ ሰውም ፡ በማይኖ ርበት ፡ በረኃ ፡ መካከል ፡ ወዳለው፡ ምድረ፡በዳ፡የመራን፤

፯፡ ወአብአነ ፡ ውስተ ፡ ከነዓን ፡ ወቀር ሜሎስ፡ከመ፡ንብላዕ፡ፍሬሁ፡ወበረከቶ፡
ፍሬሁ፡አዲሱን፡በረከቶ፡ድልቡን፤ አንድም ፡ ፍሬሁ ፡ ወርቁን ፡ ብሩን፤ ወበረከቶ ፡ ማምጃውን ፡ ልብሱን፤ እንወስድ ፡ ዘንድ ፡ ወደቀርሜሎስና፤ ወደከነዓን ፡ ያገባን ፡ እግዚአብሔር ፡ የት፡ሔዶ፡ነው፡አላሉም፤

ወቦእክሙ ፡ ወአርኰስክምዋ ፡ ለምድርየ፤ ገብታችሁ፡ከነዓንን፡ኢየሩሳሌምን፡ አረከሳችኋት፡አለ፤ኃጢአት፡ሠራች ሁባት፡ጣዖት፡አመለካችሁባት፤

ወአሕሰርክሙ፡ርስትየ፡
ነቢያትንም ፡ አጕሰቈላችኋቸው ፤ ማለት፡አልተቀበላችኋቸውም፤

፰፡ ወካህናትኒ ፡ ኢይቤሉ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ፡እግዚአብሔር፡
ስንኳንስ፡እናንተ፡ካህናት፡ስንኳ፡እግ ዚአብሔር፡የት፡ሄዶ፡ነው፡አላሉም፤

ወእለሂ፡ተምህሩ፡ሕግየ፡ኢሐለዩኒ፡
ሕጌንም፡የተማሩ፡ወገኖቼም፡ሁሉ፡ በሕግ፡በአምልኮት፡አላሰቡኝም፤

ወኖሎትኒ፡ዐለዉኒ፡
ወትሮ ፡ ለልማዱ ፡ ሕዝቡ ፡ ቢያጠፉ ፡ ነገሥታቱ፡ይሠሩ፡ይቀጡ፡ነበር፤ነገ ሥታቱም፡ወነጀሉኝ፤

ወነቢያትኒ፡ይትኔበዩ፡ለበዓል፡
ለኔ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩልኝ ፡ የነበሩ ፡ ነቢያት ፡ ከቤተ ፡ ጣዖቱ ፡ ገብተው ፡ የሆነውን፡ያልሆነውን፡ይለፈልፉሉ፤

ወሖሩ፡ወተለዉ፡ዘኢይበቍዖሙ፡
ሄደው ፡ የማይረባቸው ፡ የማይጠቅማ ቸውን፡ጣዖቱን፡ተከተሉ፤



፱ ፡ ወበበይነዝ ፡ ዓዲ ፡ እትዋቀሰሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ቀጥዬ ፡ ቀጥዬ ፡ እወቅሳ ቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፡

ወእሳነኖሙ፡ለደቂቀ፡ደቂቆሙ፡
ልጆቻቸውን ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸ ውንም፡እከራከራቸዋለሁ፤

፲፡ ዕድዉ፡ውስተ፡ደስያተ፡ኬጥኤም፡
ይኸንንስ፡ትታችሁ፡በሮም፡ወዳሉ፡ ደሴቶች፡ወንዙን፡ተሻግራችሁ፡ሂዱ፤ አንድም ፡ ይህንንስ ፡ ትታችሁ ፡ የሮ ምን፡ ደሴቶች ፡ ተሻግራችሁ ፡ ወደ ፡ ሮም፡ከተማ፡ሂዱ፤

ወፈንዉ፡ውስተ፡ቄዳር፡
ወደኤሳውም ፡ ልጆች ፡ እስኪ ፡ መላክተኛ፡ላኩ፤

ወጠይቁ፡በሕቁ፡
በሮም ፡ ከተማ ፡ የሚደረገውን ፡ ነገር ፡ ጠይቃችሁ፡ተረዱ፤

ወርእዩ፡እመ፡ኮነ፡ከመዝ፡
አሁን ፡ እንደተናገርኩት ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ፡አይታችሁ፡እወቁ፤

፲፩፡ እመ ፡ ይዌልጡ ፡ አሕዛብ ፡ አማልክ ቲሆሙ፡እንዘኪ፡ኢኮኑ፡አማልክተ፡
አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ሳይሆኑ ፡ አማልክት ፡ የሚባሉ ፡ አማልክቶቻ ቸውን ፡ ይለውጡዋቸው ፡ እንደሆነ፤ አንድም ፡ ዘኪ ፡ ኢኮኑ ፡ አማልክተ ፡ ይላል፤ እመ ፡ ኮነ ፡ ከመዝ ፡ ያለውን አመጣ፤ አማልክት ፡ ስንኳ ፡ ያይደሉ፡ ጣዖታቱን ፡ አሕዛብ ፡ ይለውጡ ዋቸው፡ እንደሆነ ፡ እነሆ ፡ እዩ ፤ ተአምልክቱ ፡ እነሱስ ፡ ከወርቁ ፡

ወደብሩ፤ ከብሩ ፡ ወደወርቁ ፡ ከደን ጊያው ፡ ወደእንጨቱ ፡ ይሄዱ ፡ የለም?፤ ቢሉ ፡ እነሱ ፡ የቀደመውን ፡ ሳይተዉ ፡ ነው፡ እነዚህ ፡ ግን ፡ እሱን ፡ ትተው ፡ ነውና፤

ወሕዝብየሰ ፡ ወለጡ ፡ ክብሮሙ ፡ በዘኢይበ ቍዖሙ፡
በማይረባቸው ፡ በማይጠቅማቸው ፡ ጣዖት ፡ ወገኖቼ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ለወጡ፤አንድም፡ክብራቸው፡እኔን፡ ካዱ፤

፲፪፡ ደንገፀት፡ሰማይ፡በበይነዝ፡
ስለዚህ፡ልዑላኑ፡በመከራ፡ተይዘው፡ ደነገጡ፤

ወአንሦጠጠት ፡ በሕቁ ፡ ጥቀ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡
ትሑታኑም ፡ በመከራው ፡ ተይዘው ፡ ስቅጥጥ፡ስቅጥጥ፡አሉ፡አለ፡እግዚአ ብሔር፤ አንድም ፡ ደንገፀት ፡ ሰማይ ፡ ሰማይ ፡ በቁሙ ፡ በድርቅ ፡ ተይዛ ፡ ደነገጠች፤ ወአንሦጠጠት ፡ በሕቁ፡ በድርቁም ፡ ምክንያት ፡ ስቅጥጥ ፡ ስቅጥጥ ፡ አለች፤ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር፡የማትሰጥ፡ሆነች፤

፲፫፡ እስመ ፡ ክልዔተ ፡ እከያተ ፡ ገብሩ ፡ ሕዝብየ፡
ወገኖቼ፡፳ኤል፡ሁለት፡ክፉ፡ሥራ፡ ሠርተዋልና፡ክልዔተ፡እከያተ፡ብሎ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሮለታል ፤ ለሁለቱም፡ያመጣለታል፤
ኪያየ ፡ ኀደጉኒ ፡ ነቅዓ ፡ ማየ ፡ ሕይወት፡ ኀደጉኒ፡ ኪያየ፡ነቅዓ፡ማየ፡ሕይወት፡ ሲል ፡ ነው ፤ የሕይወት ፡ የረድዔት ፡ መገኛ ፡ እኔን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ተዉኝ፡አለ፤ክልዔተ፡እከያተ፡ካለው፡

www.ethiopianorthodox.org

አንዱ፡ይህ፡ነው፡
ወከረዩ፡ለሙ፡እዘቀተ፡ንጹፋተ፡ዘአልቦ፡ማይ፡
እኔን፡ትተው፡ሕይወት፡ረድኤት፡የማ
ይገኝበት ፡ ጣዖቱን ፡ አመለኩ ፡ አለ፡
ክልዔተ፡እኪያተ፡ካለው፡ሁለተኛው፡
ይህ ፡ ነው፤ እሱን፡ ከተው ፡ እንደምን ፡
ሁነው፡ቢኖሩ፡ይወድ፡ኖሯል፡ቢሉ፡
እንደ፡አረሚ፡አረሚ፡ማን፡ፈጠረህ፡
ያሉት፡እንደሆነ፡አባቱ፡አባትህንስ፡
አባቱ ፡ ይላል፤ ይኄይስ ፡ ብእሲ ፡
ዘአልቦ፡ጣዖት፡ወርኀቀ፡እምጽዕለት፡
ብሎ ፡ አሁን ፡ ወደፊት ፡ እንዲያ
መጣው፤ አንድም፡የልጅነት፡መገኛ፡
እኔን፡ተዉኝ፡አንድም፡ዘርዓ፡ዳዊት፡
አምላክ፡ብለው፡አመኑ፤
፲፬፤ ቦኑ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ ያዕቆብ ፡ አው
ልደ፡ቤት፡ውእቱ፡ለምንት፡ኮነ፡ዜዋ፤
ያዕቆብ፡በውኑ፡ባሪያን፡ነው?ወላጅ፤
ነው ? ለምን ፡ ለምርኮ ፡ ሆነ ፡ ባሪያን ፡
ነበር?ወላጅ፡ነበር?ለምርኮ፡ሆኗልና፤
፲፭፤ ወጥህሩ፡ላዕሌሁ፡አናብስት፡
አናብስት፡ከልሁ፡ብሎ፡ጥኀሩ፡አለ፡
እንጂ፡ወውዑ፡ሲል፡ነው፡የባቢሎን፡
ነገሥታት ፡ አገረሩበት ፡ ደነፉበት ፡
ወወውዑ ፡ ላዕሌሁ ፡ እለ ፡ አማሰንዋ ፡
ለብሔሩ፤
ጥኀሩ፡ያለውን፡ወውዑ፤አናብስት፡
ያለውን፡እለ፡አማሰንዋ፡ለብሔሩ፡
ብሎ፡ገለጠው፤ አንድም፡አናብስት፡
ያላቸው፡ነገሥታቱ፤እለ፡አማሰንዋ፡
ለብሔሩ ፡ ያላቸው ፡ ኃያላኑ፡ ናቸው፤
ጥኀሩ ፡ ወውዑ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡
ነገሥታቱ ፡ ሲደነፉ ፡ ኃያላኑ ፡ እኔ ፡
አሸከርህ፡ከፊትህ፡እሞታለሁ፡እያሉ፡
መደንፋት፡ልማድ፡ነውና፤
ወነሥትዎን፡ለአህጉሪሁ፡ወረሰይዎን፡ከመ፡
አልቦ፡ዘይነብሮን፡
የያዕቆብንም ፡ አገሮች ፡ አጥፍተው፡
ሰው፡እንዳይኖርባቸው፡አደረጓቸው፤
፲፮፤ ወአእመሩኪ ፡ ደቂቀ ፡ ኖፍ ፡
ወጣፍናስ፡
የኖፍ ፡ የጣፍናስ ፡ ልጆች ፡ ቤተ ፡
መቅደስ፡በመግባት፡አወቁሽ፤ወተቀ
ነዩኪ ፡ ዛቲኑ ፡ አክሊሉ ፡ ወምክሁ ፡
ብለው ፡ ዘበቱብሽ፤ አንድም ፡ ወአእ
መሩኪ ፡ በሩካቤ ፡ አወቁሽ ፤ ወተቀ
ነዩኪ ፡ እሪና፡ አደሩብሽ ፤ አንድም ፡
የኖፍ፡የጣፍናስ፡ኃያላን፡በመማረክ፡
አወቁሽ፤ ወተቀነዩኪ ፡ ማርከው ፡
ወስደው፡ዘበቱብሽ፤ዛሬ፡ምርኮኛን፡
ማርከው፡እንደ፡ሀገርህ፡አጫውተን፡
እንዲሉት ፡ እነሱንም ፡ ማርከው ፡
ወስደው ፡ እንደ ፡ ሀገራችሁ ፡
አጫውቱን ፡ እያሉ ፡ ዘብተውባቸ
ዋልና፤ አንድም ፡ የኖፍ ፡ የጣፍናስ፡
ኃያላን ፡ በድካም ፡ አወቁሽ ፡ ወተቀ
ነዩኪ፡ድንኂ፡ወንትዓደውኪ፡አሉሽ፤
፲፯፤ ናሁ፡ርእዩ፡ዘረሰየኪ፡ኀዲገ፡ዚአየ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላክኪ፡
ፈጣሪሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔን ፡
መተውሽ ፡ ያደረገሽን ፡ ማድረግ ፡
እነሆ፡ እዩ ፡ ተመልከቱ ፡ አለሽ ፤
፲፰፤ ወይእዜኒ፡ምንት፡ብኪ፡በፍኖተ፡
ግብፅ፡ከመ፡ትስተዪ፡ማየ፡ሕሙግ፡
ወደ፡ግብፅ፡ርዱኝ፡ብለሽ፡ስትወርጂ፡
ደፍራሳውን፡ውሀ፡ትጠጪ፡ዘንድ፡
በግብፅ፡ምን፡ነበረሽ፤
ወምንት ፡ ብኪ ፡ በፍኖተ ፡ ፋርስ ፡ ከመ ፡
ትስተዪ፡ማየ፡ፈለግ፤
ተማርከሽ ፡ ስትሔጂ ፡ ፈሳሹን ፡
ትጠጪ፡ዘንድ፡በፋርስ፡ምን፡ነበረሽ?



በፍኖተ፡ግብፅ፡ከመ፡ትስተዪ፡ማየ፡
ሕሙግ ፡ በግብፅ ፡ ሥርዓት ፡ ደፍራ
ሳውን፡ ውሀ ፡ ታመልኪ ፡ ዘንድ፤
ምንት፡ብኪ፡ከጣዖቱ፡ምን፡ነበረሽ፡
ወምንት ፡ ብኪ ፡ በፍኖተ ፡ ፋርስ ፡
ተማርከሽ ፡ ሂደሽ ፡ ጣዖቱን ፡
ልታመልኪ፡በፋርስ፡ሕግ፡ሥርዓት፡
ጸንተሽ፡ትኖሪ፡ዘንድ፡ምን፡አለሽ?፡
ይህን ፡ ባለው ፡ አኮኑ ፡ ዘነሣእኪ ፡
ሥርዓተ፡ግብፅ፡ይላል፤እንደዚሁ፡ያስ
ተረጉማል፤
፲፱፤ ወይገሥጽኪ፡ተራኀቆትኪ፡
በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ከኔ ፡ ራቅሽ ፤
ይገሥጽሽ ፡ ማለት ፡ ይሥራሽ ፡
ይቅጣሽ፤
ወይዝልፍኪ፡እከይኪ፡
ክፋትሽ ፡ መከራውን ፡ አምጥቶ ፡
ይዝለፍሽ፤
ተአምሪ ፡ ወትጠይቂ ፡ ከመ ፡ ይመርረኪ ፡
ኀዲገ ፡ ዚአየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፤
አምላክኪ፤
ፈጣሪሽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እኔን ፡
በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ መተውሽ ፡
መከራውን ፡ እንዲያመጣብሽ ፡ ኋላ ፡
ታውቂያለሽ፡ትረጂዋለሽ፡አለሽ፤
፳ ፤ እስመ ፡ እምዓለም ፡ ቀጥቀጥኩ ፡
አርዑተኪ፤
ከጥንት፡ጀምሮ፡ቀምበርሽን፡ቀጥቅ
ጬልሽ፡ነበርኩና፡አለ፤አሕዛብ፡በሠ
ራዊቶቻቸው ፡ ይገዙሽ ፡ የነበረውን ፡
ጽኑ፡አገዛዝ፤
ወሰበርኩ፡መዋቅሕተኪ፡
እግር ፡ ብረትሽን ፡ ሰንሰለትሽን ፡
ሰብሬልሽ ፡ ነበርኩና ፡ አለ፡ የአሕዛብ ፡
ነገሥታት ፡ የሚገዙሽን ፡ ጽኑ ፡ አገዛዝ፡
አጥፍቶልሽ ፡ ነበረና፡ አንድም ፡ ቀጥ
ቀጥኩ፡አርዑተኪ፡ዛሬ፡ሠራዊቶችሽ፡

ወሰበርኩ፡መዋቅሕተኪ፡
አንቺ፡የምትገዥውን፡አገዛዝ፡አጥፍ
ቼብሻለሁና፡
ወትቤሊ፡ኢይገብር፡
አንቺ፡ግን፡ኃጢአት፡ሠርተሽ፡አልሠ
ራሁም፡ትይኛለሽ፤
ዳዕሙ፡ተሐውሪ፡ውስተ፡አድባር፡ነዋኃት፡
ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ ጣዖት ፡
ለማምለክ ፡ ወደረጃጅሙ ፡ ተራራ ፡
ትሄጃለሽ፡ እንጂ ፤ ተራራውን ፡ ያመል
ካሉና፤አንድም፡በተራራ፡የቆመውን፡
ጣዖት፡ያመልካሉና፤ አንድም፡ዐሐይ፡
ጨረቃን ፡ ያመልካሉና ፡ እንዲቀር
ባቸው ፡ በተራራው ፡ መሥዋዕት ፡
ሠውተው ፡ በልተው ፡ ጠጥተው ፡
መብራቱን፡አጥፍተው፡ደይ፡እዴከ፡
ኀበ፡ዘፈቀድከ፡ብለው፡ወንድ፡ልጅ፡
ከናቱ፤ሴት፡ልጅ፡ከአባቷ፡ይደርሳሉ፤
ምነው ፡ ቢሏቸው ፡ ባናውቅ ፡ ምን ፡
እናድርግ፡ይላሉ፤
ወታሕተ፡ኵሉ፡ዖም፡ዘቦ፡ጽላሎት፡
ጥላ፡ወዳለው፡ዛፍ፡ትሄጃለሽ፤ሐተታ፡
እንደ፡ኢሳይያስ፤
ወበህየ፡ከዓውኪ፡ዝሙተኪ፡
ከዚያውም ፡ ቦታ ፡ ዝሙትሽን ፡
አብዝተሽ ፡ ሠራሽው ፡ አለ፤ ሐልዮ ፡
ነቢብ፤ገቢር፡አለና።
፳፩፤ አንሰ፡ተከልኩኪ፡ሴሬቀ፤
እኔስ ፡ የሴሬቅን ፡ ወይን ፡ አድርጌ ፡
ተክየሽ፡ነበር፤ ሐተታ፡የሴሬቅ፡ወይን፡
ካመት፡ሦስት፡ጊዜ፡ያፈራል፤ላንቺም፡
ካመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ገቢረ ፡ በዓል ፡
ሠርቼልሽ ፡ነበር ፤ አንድም፡ አንሰ ፡
ተከልኩኪ፡ሴሬቀ፡ወኵሎ፡አቅማሐ፡
ጽድቅ፤ እኔስ ፡ የምግባር ፡ ቅመም ፡
ያለው፡የአብርሃም፡ልጅ፡ብየሽ፡ነበር፤
አንድም፡አንሰ፡ተከልኩኪ፡እምወይነ፡
ነኪር፡ይላል፡እኔስ፡ከርስቱ፡ከነገዱ፡
የተለየ፡የአብርሃም፡ልጅ፡ብየሽ፡ነበር፡

www.ethiopianorthodox.org

እፎ፡ኮንኪ፡ሃኪ፡
ግመሮ፡ጋቢሎ፡
ወወይነ፡ነኪረ፡
ሬት ፡ እንጀሪ ፡ እንዴት ፡ ሆንሽ ፡
ሐተታ፡ ይህ፡እንጨት፡እሾሃም፡ነው፡
አንቺስ ፡ የአባትሽ ፡ የአብርሃምን ፡
ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ ትተሽ ፡
ኃጢአቱን ፡ ጣዖቱን ፡ እንደምን ፡
አጽንተሽ ፡ ያዝሽ ፤ አንድም ፡ እፎ ፡
ኮንኪ ፡ ሃኪ ፡ ወወይነ ፡ ነኪር፡ ይላል፡
የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ አንቺ ፡ በምግባር ፡
በሃይማኖት ፡ የተለየ ፡ የከነዓን ፡ ልጅ ፡
እንደምን፡ሆንሽ?

፳፪፤ እመ፡ተሐዘብኪ፡በአፍላግ፡
በፈሳሽ ፡ ውሀ ፡ ብትጠራጠሪ ፡ አለ፤
ፈሳሹን፡ውሀ፡አምላክ፡ነው፡ብትዪ፤
ወተካየድኪ፡ኪዳነ፡
ከፈሳሽ ፡ ውሀ ፡ ጋራም ፡ ብትማማይ ፡
አለ፤ የተማማለ ፡ እንዳይለያይ ፡ እንዳ
ይካዳ ፡ እንዲዋደድ ፡ ፈሳሹን ፡ ውሀ ፡
አምላክ፡ነው፡ብለሽ፡ብትወጂው፤
ወይትነተም፡ኃጢአትኪ፡በቅድሜየ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡
ኃጢአትሽ ፡ በፊቱ ፡ ይቆጠራል ፡
ማለት፡ በልበ ፡ ሥላሴ ፡ ይቆጠራል፤
አለ፡ እግዚአብሔር፤ ሐተታ ፡
በቅድሜየ ፡ አለ፤ በፊት ፡ ያለ ፡እንዲ
ታሰብ ፡ ዘወትር፡ ኃጢአትሽን ፡ አስብ
ብሻለሁ፡ሲል፡ነው፤

፳፫፤ ወእፎ፡ትብሊ፡ኢረኰስኩ፡
በኃጢአት፡በጣዖት፡ከረከስሽ፡በኋላ፡
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ አረከስኩም ፡
እንደምን፡ትያለሽ፤
ወኢተለውክዎ፡ለበዓል፡
ጣዖቱን፡ካመለክሽ፡በኋላ፡ጣዖት፡አላ
መለኩም፡እንደምን፡ትያለሽ፤
ርእዪ፡ፍኖተኪ፡ዘውስተ፡አፍላግ፡
በፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ ዳር ፡ የምትሠሪውን ፡
ሥራሽን፡እዪ፤ተመልከች፤

ወእእምሪ፡ዘገበርኪ፡
የሠራሽውን ፡ ሥራሽን ፡ መርምሪሽ ፡
እወቂ፡
በበሠርክ፡ትየብቢ፡ውስተ፡ፍናዊሃ፡
በባቢሎን ፡ በጎዳናዋ ፤ አንድም ፡
በመንደሯ፡ ትሠያለሽ፤ (ትቀልጫለሽ)፤
ፍናዊሃ ፡ ለጽዮን ፡ ይላህዋ፡ እንዲል፤
አንድም፡በበሠርክ፡ትየብብ፡ውስተ፡
ፍናዊሃ ፡ ይላል ፤ ያርቃል፤ ያቀርባል፤
በባቢሎን፡በጎዳናዋ፤አንድም፡በመን
ደሩዋ፡ትሠያለች፤(ትቀልጣለች)፤

፳፬፤ ወተርኅበት ፡ በውስተ ፡ ማያተ ፡
አሕቃላት፡
ከውሀው ፡ ዳርም ፡ ስትደርስ ፡ ተንሰ
ራፋች፤ ተንዘራጋች ፤ ሐተታ ፡
ጠጥቿው ፡ ልሙት ፡ አለች፤ አንድም ፡
በውሀው ፡ ዳር ፡ ታጠፈች ፡ ተዘረጋች ፡
ሐተታ፡አምላኬ፡ነው፡ብላ፤
በፍትወተ፡ነፍሳ፡ትትዌረድ፡
ልቡናዋ ፡ በወደደው ፡ በጣዖቱም ፡
ከቤተ፡ጣዖቱ፡ገብታ፡ትለፈልፋለች፤
ወአኃዝዋ፡ወአልቦ፡ዘያገብአ፡
በዌዋዌ ፡ ጠላቶቿ ፡ የባቢሎን ፡
ሰዎችም፡ ከብበው ፡ ያዝዋት፤ ባጭር ፡
ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ ተዋግቶ ፡
የመለሳት፡የለም፤
ኵሎሙ፡እለ፡ኃሥሥዋ፡ኢይፃምዉ፡
የሚፈልጓት ፡ ጠላቶቿ ፡ ሁሉ ፡ አይደ
ክሙም ፡ ማለት ፡ አይወጡም፤ አይወ
ርዱም፤ ይረክብዋ ፡ ዘእንበለ ፡ አሣዕን፡
እሱዋ ፡ ጫማ ፡ ሳታዝብ፤ አንድም፡
እነሱ ፡ ጫማ፡ ሳይዝቡ ፡ በቅርብ ፡
ያገኟታል።

፳፭፡ ሚጢ ፡ እግረኪ ፡ እምነ ፡ ፍኖት ፡
ሙብእስ፤
እግርሽን ፡ ከጕጸጉጹ ፡ ጎዳና ፡
መልሽው ፡ አለ ፤ ተማርከሽ ፡
በጕጸጉጹ፡ጎዳና፡እንዳትሔጂ፡ሁኚ፤



ተማርከሽም፡ ስትሔጂ ፡ ከውሀ ፡ ጥም ፡
ጉሮሮሽን ፡ መልሽው ፡ አለ፡ ይህማ ፡
በምክርን፡ ይሆናል ፡ ብሎ፡ ተማርከሽ ፡
በጕጸጉጽ፡ ጎዳና ፡ የምትሄጂበትን ፡
ሥራ፡አትሥሪ፡ሲል፡ነው፤
ወትቤ፡አጥባዕኩ፡አንስ፡ወአፍቀርኩ፡ነኪረ፡
ብመክራት፡ባስተምራት፡እኔስ፡ልዩ፡
ጣዖትን ፡ ወድጄ ፡ አምልኪያለሁ ፡
በዚህም፡ጨክኛለሁ፡አለችኝ፤
ወተለወቶሙ፡
ይህንም ፡ ብላ ፡ አልቀረች ፡ ተጨልጣ ፡
ተገርኝታ፡ጣዖታቱን፡ተከትላ፡ሔደች፤

፳፮፤ ከመ ፡ ሐፍረተ ፡ ሰራቂ ፡ ሶበ ፡
ይእኀዝዎ፡
ሌባ ፡ ሲሰርቅ ፡ አግኝተው ፡ በያዙት ፡
ጊዜ፡እንዲያፍር፡እንዲደነግጥ፤
ከማሁ፡የሐፍሩ፡ደቂቀ፡፳ኤል፡
የ፳ኤልም፡ ልጆች ፡ ኃጢአት ፡
ሠርተው፡ጣዖት፡አምልከው፡መከራ፡
መጥቶባቸው፡ያፍራሉ፤
እሙንቱኒ፡
እነሱም፡ያፍራሉ፤
ነገሥቶሙኒ፡ወመላእክቲሆሙኒ፡
ነገሥታቱና፡መኳንንቱም፤
ወካህናቲሆሙኒ፡ወነቢያቲሆሙኒ፡
ካህናትና ፡ ነቢያትም ፡ በመከራው ፡
ተይዘው፡ያፍራሉ፤

፳፯፤ እስመ ፡ ይቤልዎ ፡ ለዕፅ ፡ አቡነ ፡
አንተ፡ወለዕብንኒ፡ወለድከነ፡አንተ፡
እንጨቱን ፡ አባታችን ፡ አንተ ፡ ነህ ፤
ደንጊያውንም፡አንተ፡ወለድኸን፡ብለ
ውታልና፤
ወሜጡ፡ዘባኖሙ፡ኀቤየ፡
ዘባኑ፡ልቡናቸውን፡ወደኔ፡መለሱ፤
ወአኮ፡ገጾሙ፡
ገጸ ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደኔ ፡ የመለሱት ፡
አይደለም፤ አንድም ፡ ሜጡ ፡ ዘባኖሙ ፡
አሕዛብ ፡ በመጡባቸው ፡ ጊዜ ፡ ባጭር ፡
ታጥቀን ፡ ዘገር ፡ ነጥቀን ፡ እንዋጋ ፡
[illegible] ፡ ጀርባ

ባቸውን፡ቀልሰው፡ሸሹ፡
ወአኮ፡ገጾሙ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመው ፡ የተዋጉ ፡
አይደለም፤
ወአመሰ፡ምንዳቤሆሙ፡ይብሉኒ፡ተንሥእ፡
ወአድኅነነ፡
መከራው ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን፡
በረድኤት ፡ ተነሥተህ ፡ አድነን ፡
ይሉኛል፤

፳፰፤አይቴኑመ፡አማልክቲከ፡ዘገበርከ፡ለከ፡
ሠርተህ፡ያቆምሃቸው፡ጣዖታቱ፡የት፡
አሉ?
ኢይትነሥኡ ፡ እንከ ፡ ኢያድኅኑከ ፡ አመ ፡
ምንዳቤከ፡
በመከራህ ፡ ጊዜ ፡ ሊያድኑህ ፡ አይነሡ
ልህምን፤ አንድም ፡ ኢይትነሥኡ
ወኢያድኅኑከኑ ፡ ይላል፤ ወዳጅ ፡
ዘመድ፡ ለመቼ፡ነው፡በመከራህ፡ጊዜ፡
ተነሥተው፡አያድኑህምን፤
እስመ ፡ በኍልቈ ፡ አህጉሪከ ፡ አማልክቲከ ፡
ይሁዳ፤
ይሁዳ ፡ ብሎ ፡ ያሰማዋል ፡ የጣዖታ
ቶችህ ፡ ቍጥር ፡ ባገሮችህ ፡ ቍጥር፡
ልክ፡ነውና፤
ወበኍልቈ፡ፍናዊሃ፡ለኢየሩሳሌም፡
በኢየሩሳሌምም ፡ በጎዳናዋ ፡ በመን
ደሩዋ ፡ ቍጥር ፡ ልክ ፡ ነውና፤ ሐተታ ፡
አገር፡አስፍቶ፡አብዝቶ፡ማቅናቱን፡አይ
ጠላበትም ፡ ጣዖት ፡ ማምለኩን ፡ ነው ፡
እንጂ፤ ሦዐ ፡ ለበዓል ፡ ማንሻ ፡ ነው፤
አንድም፡በኢየሩሳሌም፡በጎዳናዋ፡በመ
ንደሩዋ፡ልክ፡ጣዖት፡አቁመው፤
ሦዑ፡ለበዓል፤
ለጣዖቱ፡መሥዋዕት፡ሠዉ፤

፳፱፤ ለምንት፡ትነብቡኒ፤
ኃጢአት፡እየሠራችሁ፡ጣዖት፡እያመ
ለካችሁ፤ ማረን ፡ አድነን ፡ እያላችሁ ፡
ለምን ፡ ትለምኑኛላችሁ፤ አንድም ፡
እኔን ፡ እየበደላችሁ ፡ ማረን ፡ አድነን ፡
እያላችሁ፡ትለምኑኛላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ናሁ ፡ ኮልክሙ ፡ ዓለውክሙኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡

እነሆ ፡ ለነበርነው ፡ ሁላችሁ ፡ ወነጀላ ችሁኝ፡አለ፡እግዚአብሔር፡

፴ ፡ በከ ፡ ለከንቱ ፡ ቀተልክምዎሙ ፡ ለደቂ ቅክሙ፡

ላይረባችሁ ፡ ላይጠቅማችሁ ፡ በከንቱ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢአት ፡ ልጆቻ ችሁን፡አጠፋችኋቸው ፡ አለ፤ አባቶች ፡ የሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ያው ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ልጆችን ፡ ጭምር ፡ አጥፍቷልና፤ አንድም ፡ በከ ፡ ለከንቱ ፡ ቀተልኩ ፡ ደቂቀክሙ ፡ ይላል ፡ ላይረባችሁ ፡ ላይ ጠቅማችሁ ፡ እናንተ ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢአት ፡ እኔ ፡ ልጆቻችሁን ፡ አጠፋሁ፤

ወኢተወከፍክሙ፡ተግሣጽየ፡

እናንተ ፡ ግን ፡ የኔን ፡ ምክር ፡ እዝናት ፡ ወድዳችሁ፡አልተቀበላችሁም፤

ወለነቢያቲክሙኒ ፡ በልዐቶሙ ፡ መጥባ ሕትየ፡ከመ፡አንበሳ፡ዘይሜሩ፡

አንበሳ፡ሊያጠፋ፡ሲል፡በማስፈራት፡ አናፍቶ ፡ እንዲነሣ ፡ እንደዚያ ፡ በማስ ፈራት ፡ መጥታ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ እያሉ ፡ የሚያስተምሯችሁ ፡ ነቢያት ፡ ሐሰትን ፡ አጠፋቻቸው፤ አንድም፡ የስልምናሶር ፡ የናቡከደ ነፆር፡ ሾተል ፡ አጠፋቻቸው ፤ ሐተታ ፡ መጥባሕትየ፡አላት፡በተፈጥሮ፤

ወበዝኒ ፡ ኢፈራህክሙኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡

በዚህም ፡ ሁሉ ፡ አልፈራችሁኝም፤ አላ መለካችሁኝም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፴፩፤ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤

አሁንም፡የእግዚአብሔርን፡ትእዛዝ፡ስሙ፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ጉባኤ፤

መዝበረኑ፡ኮንክዎሙ፡ለደቂቀ፡ፀኤል፡

ለፀኤል፡ልጆች፡ፍራሽ፡ሆንሁባቸው፡ ፍራሽ ፡ እንዳያድን ፡ የማላድን ፡ ሆንሁ ባቸው፤

አው፡ምድረ፡በድው፡

ምድረ ፡ በዳውን ፡ ሆንሁባቸው፤ ያ፡እን ዲያስፈራ፡የማስፈራ፡ሆንሁባቸውን፤

እስመ፡ይቤሉ፡ሕዝብየ፡ኢንትቀነይ፡ለከ፡

ወገኖቼ፡እስራኤል፡ላንተ፡አንገዛልህም፡ ብለውኛልና፤አንድም፡ፍራሽ፡በሆንሁ ባቸው ፡ ነበር ፤ ፍራሽ ፡ እንዳያድን ፡ የማላድን፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ በሆንሁ ባቸው ፡ ነበር፤ ያ ፡ እንዲያስፈራ ፡ የማ ስፈራ ፡ በሆንሁባቸው ፡ ነበር፤ አንገዛም፡ ብለውኛልና፡ስለዚህነው፡እንጂ፤

ወኢንመጽእ፡እንከ፡ኀቤከ፡

በሕግ ፡ በአምልኮትም ፡ ወዳንተ ፡ አንመጣም ፡ ብለዋልና፤ አንድም ፡ ስላሉኝ፤

፴፪፤ትረሥዕኑ፡መርዓት፡ሠርጓ፡

የተዳረች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብትዘነጋው ፡ ብትዘነጋው፡አባት፡እናቷ፡የሰጧትን፡ አንድም፤ባሏ፡የሰጣትን፡ጌጧን፤

ወድንግል፡ባዝግናሃ፡

ያልተዳረች፡ሴት፡ልጅ፡ናት፡እናት፡ አባቷ ፡ የሰጧት ፡ ዝርግፏን ፡ (የወርቅ ማገርዳ)፡ትዘነጋዋለችን፤

ሕዝብየሰ ፡ ረሥዑኒ ፡ መዋዕለ ፡ ዘአልቦ ፡ ኊልቈ፡

ወገኖቼ፡እሥራኤል፡ግን፡እነሱ፡ከተዳረ ችው፡ ሴት፡ ልጅና፡ ካልተዳረችው፡ ድን ግል፡ ሴት፡ ልጅ፡ ብሰው፡ አንሰው፡ እኔን፡ ከዝርግፏ፡ ከጌጧ፡ አሳንሰው፡ ስፍር፡ ቁጥር፡የሌለው፡ብዙ፡ዘመን፡ዘነጉኝ፤

፴፫፤ ምንት ፡ እንከ ፡ ዓዲ ፡ ሠናይ፡ ዘትፈቅድ፡ በፍናዊከ፡ ከመ፡ ትኅሥሥ፡ ተፋቅሮ፡

ኃጢአት፡ እየሠራህ ፤ ጣዖት፡ እያመ ለክህ፡ ከጣዖቱ፡ ፍቅርን፡ ትሻ፡ ዘንድ፡ ምን፡አለህ፡

አኮ፡ከመዝ፡

[illegible]



አንድም፡ኃጢአት፡እየሠራህ፡ጣዖት፡ እያመለክህ ፡ ከኔ ፡ የምታገኘው ፡ ፍቅር፡ምንድር፡ነው?አኮ፡ከኔ፡የምታ ገኘው፡አይደለም፡

ዓዲ፡ አንተሂ፡ አሕሰምከ፡ ከመ፡ ታርኮስ፡ ፍናዊከ፡

ሥራህን፡ ታረክስ፡ ዘንድ፡ ክፉ፡ ሥራ፡ ሠራህ፤

፴፬፤ ወተረክበ ፡ ውስተ፡ እደዊከ፡ ደመ፡ ዕጓለ፡ማውታ፡ወደመ፡ነፍስ፡ንጹሕ፤

ከመ፡ ታርኮስ፡ ፍናዊከ ፡ ብሎት ፡ ነበረና፡ ሥራዬን፡ ማርከሴ፡ እንደምን ድነዋ፡ ትለኝ፡ እንደሆነ፡ ይኸውም፡ ሊታወቅ፡ እናት፡ አባት፡ የሌለው፡ የድኃ፡ አደጉ፡ ልጅ፡ ደምና፡ የንጹሑ፡ የነቢዩና፡ የካህኑ፡ ደም ፡ በእጆችህ፡ መልቶ፡ ተገኘ፤ አንድም፡ የደሀው፡ ደመወዝ፡ በእጅህ፡ ተገኘ፡ ወዙ፡ ይፈስ በታልና፡ደም፡አለው፤

ወአኮ፡ ውስተ፡ ግብ፡ ዘረከብክዎሙ ፡ ዳዕሙ፡ ውስተ፡ያም፡

በረድኤት፡ ተጠብቀው፡ ያገኘኋቸው፡ አይደለም፤ ከረድኤት፡ በአፍአ፡ ሁነው፡ ነው፡ እንጂ፤ አንድም፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ ማዕጠንት፡ ሲያጥኑ፡ መሥ ዋዕት፡ ሲሠዉ፡ ያገኘኋቸው፡ አይደለም፤በዛፍ፡ሥር፡ለቆመ፡ጣዖት፡ ዕጣን፡ ሲያጥኑ፡ መሥዋዕት ሲሠዉ፡ ነው፡ እንጂ፤ ግብ፡ አላት፤ ቤተ፡ መቅደስን ፡ ሱሳን ፡ ወርድ ፡ ይቀረጽ ባታል ፤ ዓረግ ፡ ይሳብባታልና ፤ አንድም፡ ጉድጓድ ፡ እንዲሠውር ፡ ቤተ፡መቅደስም፡ከመከራ፡ትሠውራ ለችና፤ አንድም ፡ በጉድጓድ ፡ ያለ ፡ ለቀሥት ፡ ለጦር ፡ እንዳይመች ፤ ለጠላት ፡ የማይመቹ ፡ ሁነው ፡ ያገኘ ኋቸው ፡ አይደለም ፤ ከዛፍ ፡ ያለ ፡ [illegible]፡ለጠላት፡

የማይመቹ ፡ ሁነው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድም፡ በሕግ፡ ጣዖት፡ ጸንተው፡ አገ ኘኋቸው ፡ እንጂ ፡ በሕገ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ጸንተው ፡ ያገኘኋቸው ፡ አይደለም ፤ ግብ ፡ አለው ፡ ሕጉን ፡ ጉድጓድ፡ወዲያና፡ወዲህ፡እንዳያስተ ላልፍ ፡ ሕጉም ፡ ከዚህ ፡ አትውጣ ፤ ከዚህ ፡ አትለፉ ፡ ብሎ ፡ ያስተላል ፍምና፤

፴፭፤ ወትብሊ፡ ንጹሕ፡ አነ፡ ዳዕሙ፡ ይትመየጥ፡መዓቱ፡እምኔየ፡

ወተረክበ፡ ውስተ፡ እደዊከ ፡ ደመ፡ ዕጓለ፡ ማውታ፡ ወደመ፡ ነፍስ፡ ንጹሕ፤ ብለህ ፡ ቍጣው ፡ ከኔ ፡ ይመለስልኝ ፡ እንጂ፡እኔስ፡ከዚህ፡ሁሉ፡ንጹሕ፡ነኝ፡ ትያለሽ፤

ናሁ፡አነ፡እትዋቀሰኪ፡

እኔስ፡እነሆ፡እወቅሻለሁ፤

፴፮፤ እስመ፡ ትቤሊ፡ ኢአበስኩ፡ እስመ፡ አስተአበድክኒ፡ጥቀ፡

ፈጽመሽ፡ አላዋቂ፡ ስላደረግሽኝ፡ በድ ለሽ፡ አልበደልሁም፡ ብለሻልና፤ አንድም፡ በድለሽ፡ አልበደልሁም፡ ስላልሽ፡እኔን፡ፈጽመሽ፡አላዋቂ፡አድ ርገሽኛልና፤አንድም፡እስመና፡እስመ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ እስመ፡ ትቤሊ፡ ኢአበስኩ፡

አንቺ በድለሽ፡ አልበደልሁም፡ ብለሻልና ፤ ወአስተአበድክኒ፡ ጥቀ ፤ እኔንም፡ ፈጽመሽ፡ አላዋቂ፡ አድርገሽ ኛልና፤

ወአመክዓብኪ፡ፍናወኪ፤

ክፉ፡ሥራሽንም፡እጥፍ፡ድርብ፡አድር ገሽዋልና፡ አለ፤ ኃጢአት፡ ሠርቶ፡ ንሥሓ፡አለመግባት፡ነው፤

ወበግብዕ፡ ተሐፈርኪ፡ በከመ፡ ተሐፈርኪ፡ በአሦር፡

www.ethiopianorthodox.org

በከመ ፡ ተሐፈርኪ ፡ በአሦር ፡ ተሐፈርኪ፡ በግብፅ ሲል ነው ፡ በሙሴ፡ በአሮን ጊዜ፡ በግብፅ፡ እንደአፈርሽ፡ በሀገርሽ፡ ሳለሽ፡ በስልምናሶር፡ ጊዜ ፡ አፈርሽ፤

፴፯፤ እምዝየኒ፡ትወጽኢ፡

ከሀገርሽም፡ ተማርከሽ፡ ወጥተሽ፡ ትሄጃለሽ፤ አንድም ፡ እንዳለም ፡ ይሆናል፤ ቀድሞ፡ በሀገርሽ፡ ሳለሽ ፡ በናቡከደናዖር ፡ ጊዜ ፡ እንዳፈርሽ ፡ ኋላም ፡ በግብፅ፡ በናቡከነዖር፡ ጊዜ፡ አፈርሽ፤ ሐተታ፡ ናቡከደነዖር፡ ኢየሩሳሌምን፡ ካጠፋ፡ በኋላ፡ ግብፅ፡ ወርዶ፡ ባቢሎን፡ ዘግብፅ፡አሰኝቷታልና፡እንዲህ፡አለ፤ ወእምዝየኒ፡ ትወጽኢ፡ ከግብፅ፡ ተማርከሽ፡ ትሔጃለሽ፡ አንድም፡ ቀድሞ፡ በናቡከደነዖር፡ጊዜ፡እንዳፈርሽ፡ኋላም፡ በፈርዖን፡ኒካው፡ጊዜ፡በግብፅ፡አፈርሽ፤ አንድም፡ ቀድሞ፡ በስልምናሶር፡ ጊዜ፡ በሰጎል፡ ንጉሡ፡ ግብፅ፡ እንዳፈርሽ ኋላም፡ በናቡከደነዖር፡ ጊዜ በፈርዖን፡ አውፍር፡አደባባይ፡አፈርሽ፤

እምዝየኒ፡ትወጽኢ፡

ከዚያም፡ ከግብፅ፡ ወጥተሽ፡ ሒደሽ፡ ባቢሎን፡ትገቢያለሽ፤

ወእደውኪ፡ዲበ፡ርእስኪ፤

ይህም፡ ሁሉ፡ መከራ፡ በመጣብሽ፡ ጊዜ፡እጅሽን፡ከራስሽ፡ላይ፡አድርገሽ፡ ታለቅሻለሽ፤ አንድም፡ በእጅሽ፡ መግደል ፡ በቃልሽ ፡ ተንኮል ፡ የሠራሽው፡ ግፍ፡ ሁሉ፡ በራስሽ፡ ይደረግብሻል፤

እስመ፡አቅበጸኪ፡እግዚአብሔር፡ተስፋኪ፡

እግዚአብሔርም ፡ ከመከራው ፡ እድናለሁ፡የምትይውን፡አለኝታ፡አጥፍቶብሻልና፤

ወኢትረክቢ፡

አለኝታሽን፡ አታገኝውም፡ አንድም፡ ይህን ሁሉ፡ መከራ፡ ስትቀበይ፡ የሚረዳሽ፡ወዳጅ፡ዘመድ፡አታገኚም።

## ምዕራፍ፡፫፡

፩፤ አመ፡ሰደዳ፡ብእሲ፡ለብእሲቱ፡

አንዱም፡አንዱ፡ሰው፡በነውር፡ፈትቶ፡ ሚስቱን፡አስወጥቶ፡ቢሰዳት፤

ወወጽአት፡እምኅቤሁ፡

እሷም፡ በነውር፡ ተፈትታ፡ ከባሏ፡ ወጥታ፡ብትሄድ፤

ወአውሰበት፡ካልአ፡ብእሴ፡

በነውር፡ ከተፈታች፡ በኋላ፡ ሔዳ፡ ሌላ፡ ሰው፡ብታገባ፤

ትገብእኑ፡ኀቤሁ፡እንከ፡ዳግመ፤

ወደጥንተ፡ ባሏ፡ ዳግመኛ፡ ትመለሳለችን፤

አኮኑ፡እንከ፡ትረኵስ፡ይእቲ፡ብእሲት፡

ይቺ፡ በነውር፡ የተፈታች፡ ሴት፡ የምትረክስ፡አይደለችምን፤

ወአንቲኒ፡ዘመውኪ፡በብዙኃን፡ኖሎት፡

አንቺም ፡ በነበር ፡ ነው ፤ በብዙ ፡ ነገሥታት ፡ በብዙ ፡ መምህራን፡ ምክንያት ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሰሰንሽ ፤ አንድም ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት፡ምክንያት፡ከኔ፡ተለየሽ፤

ወተመየጢ፡ኅቤየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

እኔ፡ግን፡እንደ፡አንቺ፡አይደለሁም፤ በንስሐ፡በሕግ፡በአምልኮት፡ወደኔ፡ ተመለሽ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአንሥኢ፡አዕይንተኪ፡ርቱዐ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ምን ፡ ያደክምሻል ፡ አንገትሽን ፡ አቅንተሽ ፡ ዓይንሽንም ፡ ቀና ፡ አድርገሽ ፡ እኔ ፡ የፈጠርኩትን ፡ ሰማይ ፡ እዪው ፡ አለ፡እግዚአብሔር...



ሐተታ፡ ሥነ፡ ፍጥረቱን፡ ማየት፡ ፈጣሪውን ፡ መመርመር፡ ነውና፡ ከዚህ፡ቀድሞ፡እነአብርሃም፡እነሙሴ፡ ጸሊም፡ ሥነ፡ ፍጥረቱን፡ አይተው፡ እንዳመኑ፤ አንድም፡ ዓይነ፡ ልቡናሽን፡ ቀና፡ አድርገሽ፡ የቀና፡ ሕጌን፡ ተመልከችው፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፪፤ ወነጽሪ፡ወርእዪ፡ኵሎ፡ፍናወኪ፡

እኔንም ፡ የበደልሽበትን ፡ ክፉ ፡ ሥራሽን፡ሁሉ፡እዪው፡ተመልከችው፤

እስመ፡ነበርኪ፡ከመ፡ቋዓት፡በድው፤

በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቁራ ፡ ሁነሽ ፡ ኑረሻልና፡በሕዋው፡እንዲኖር፡በሕገ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳትሆኚ ፡ በሕገ ፡ ጣዖት፡ሳትሆኚ፡በመካከል፡ኑረሻልና፤ አንድም፡ እግሩ፡ ቀይ፡ ነው፤ አንቺም፡ ለጣዖት፡ ደም፡ ታፈሻለሽና፤ አንድም፡ ወደ፡ ውዱቃኑ፡ እንዲሄድ፡ አንቺም፡ ወደጣዖት፡ትሄጃለሽና፤

ወአርኰስኪያ፡ ለምድር፡ በዝሙትኪ፡ ወበእከይኪ፡

በኃጢአት፡ በጣዖት፡ ከነዓንን፡ አረከስሻት፤

፫፤ ወነበርኪ፡ ምስለ፡ ብዙኃን፡ ኖሎት፡ ለኃሣርኪ፡

ሐሣር፡ ጕስቁልናሽ፡ ሊገለጥብሽ፡ ከብዙ፡ነገሥታት፡ከብዙ፡መምህራን፡ ጋራ፡ በኃጢአት፡ በጣዖት፡ ጸንተሽ፡ ኖርሽ፤

ገጸ፡ዘማ፡ኮንኪ፤

አንቺስ ፡ ይልማ ፡ ይስማ ፡ ብላ ፡ ኃጢአቷን ፡ ገልጣ ፡ የምትሠራ ፡ አመንዝራ፡ሆንሽ፤ሐተታ፡ያቺ፡ዘማ፡ ... ፡ እንድ

ትሄድ ፡ እሷም ፡ ተኩላ ፡ ተቀብታ ፡ ወደጣዖት፡ትሄዳለችና፤አንድም፡ያቺ፡ ዘማ፡ ቀይ፡ ስታይ፡ ቀይ፤ ጥቁር፡ ስታይ፡ ጥቁር፡ ትሆናለች፤ እሷም፡ ከደንጊያው፡ ወደ፡ እንጨቱ፡ ከእንጨቱ፡ ወደብሩ፤ከብሩ፡ወደወርቁ ጣዖት፡ትሄዳለችና፤

ወተኃፈርኪ፡በኀበ፡ኵሉ፡

እንዲህም፡ አድርገሽ፡ ፈጣሪሽን ብትበድዪ ፡ መከራ ፡ መጥቶብሽ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አፈርሽ ፤ አንድም ፡ እንዲህ ፡ አድርገሽ፡ ፈጣሪሽን፡ ብትበድዪ፡ በሁሉ፡ ዘንድ፡ አፈርሽ፡ አለ፤ በእግዚአብሔርም፡ በጣዖቱም፡ ዘንድ፡ መከራ፡ መጥቶብሽ፡ አፈርሽ፡ ሲል፡ ነው፤ ሐተታ፡ እግዚአብሔርን፡ ክዳ ፡ ጠልታ፡ ጣዖቱን፡ ብታመልክ፡ ብትወድ፡ ጣዖቱ፡ እኔን፡ ወደደችኝ፤ አመለከችኝ፡ ብሎ፡ አልተራዳትም፤ አላዳናትምና፤ ይትነሥኡኬ፡ ወይርድኡክሙ፡ወይኩኑክሙ፡መድኃኒክሙ፡ ብሎ፡ ጌታ፡ በዳግም፡ ሕግ፡ እንደተናገረ፤ዘዳግ፡፴፪፡፴፰፤

ወተከልዐ፡ጠል፡ወተወን፡በእንተዝ፤

ስለዚህ ፡ በበልጉም ፡ በመከሩም ፡ ዝናም፡ ለዘር፤ ጠል፡ ለመከር፡ ተከለከለብሽ፤

፬፤አኮ፡ከመ፡እግዚእኪ፤

ምነዋ፡ ጌታዬ፡ አይደለህምን፡ ትዪኝ፡ እንደሆነ ፡ ጌታሽን ፡ እንድትፈሪ ፡ የፈራሽኝ፡አይደለሽም፤

ወአቡኪ፡ዘጸዋዕክኒ፡

ይህስ፡ ባይሆን፡ አባቴ፡ አይደለህምን፡ ትይኝ፡ እንደሆነ፡ አባትሽን፡ እንድታከብሪ፡ያከበርሽኝ፡አይደለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢከመ፡ምትኪ፡ዘንእስኪ፡
ይህስ፡ ባይሆን፡ ከሕፃንነቴ፡ ጀምሮ፡ የምወድህ፡ የማመልክህ፡ አይደለ ህምን፡ ትይኝ፡ እንደሆነ፡ የሕፃንነ ትሽን፡ ባልሽን፡ እንድትወጅው፡ እኔ ንም፡ እንደዚያ፡ የምትወጅኝ፡ የምታ መልኪኝ፡አይደለሽም፤

፭፡ወኢትነብሪ፡ለዓለም፡
እንዲህ፡አድርገሽ፡ከበደልሽኝ፡በኋላ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት፡ ጸንተሽ፡ አት ኖሪም፡ተማርከሽ፡ትሄጃለሽ፤
ናሁ፡ነበብኪ፡
ክፉውን፡ ነገር፡ እነሆ፡ እሠራዋለሁ፡ ብለሽ፡ተናገርሽ፤
ወገበርኪ፡ዘንተ፡እኩየ፡
ክፉውን፡ ነገር፡ ይልማ፡ ይስማ፡ ብለሽ ደፍረሽ፡ሠራሽው፤
ወክህልኪ፤
ክፉውን፡ነገር፡ማድረግ፡ተቻለሽ፤

፮፡ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡በመዋዕለ፡ ኢዮስያስ፡ንጉሥ፡
በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤
ርኢከኑ፡ዘረሰየተኒ፡ዕሉተ፡፳ኤል፡
ያሥሩ፡ ነገድ፡ ወንጀለኛ፡ ዐሥሩ፡ ነገድ፤ አንድም፡ ዕሉት፡ እስራኤል፡ ይላል፤ ወንጀለኛ፡ ዓሥሩ፡ ነገድ፡ እኔን ያደረጉኝን፡ነገር፡አየኸውን፡አለኝ፤
ሖረት፡ውስተ፡ኵሉ፡ደብር፡ነዋህ፤
ወደረጅሙ፡ተራራ፤
ወታሕተ፡ኵሉ፡ዕፀው፡ወፆም፤
ወደእንጨቱ፡ ሁሉ፤ ሐተታ ዕፀው፡ ጥቅቅኑ፤ ፆም፡ ታላላቁ፡ ነው፤ ወደዚህ፡ ሁሉ፡ሄዳ፤
ወዘመወት፡በህየ፡
በዚያ፡ ቦታ፡ የማይገባ፡ ሥራ፡ ሠራች ፤ ጣዖት፡አመለከች፤

፯ ወእቤላ፡ እምድኅረ፡ ዘንተ፡ ኵሎ፡ ገብረት፡ግብዒ፡ኀቤየ፡
ይህን፡ሁሉ፡ደፍራ፡ከሠራችው፡በኋላ፡ በንሥሐ፡ወደኔ፡ተመለሽ፡አልኋት፤
ወዓበየት፡ገቢዓ፡ኀቤየ፡
እሱዋ፡ ግን፡ በንሥሐ፡ ወደኔ፡ መመ ለሱን፡እምቢ፡አለች፤
ወርእየት፡እኅታ፡ምርዕተ፡ይሁዳ፤
የይሁዳ፡ ድራተኛ፡ ደረሞኛ፡ እኅቷ፡ ይሁዳ፤ አንድም፡ ምርዕት፡ ይሁዳ፡ ይላል፤ ድራተኛ ደረሞኛ፡ የምትሆን፡ እኅቷ፡ ይሁዳ፡ ይኸንን፡ ነገር፡ ሰማች፤ ርእየን፡ ሰማ፡ ሲል፡ ነው፤ አጽንን፡ ጨርስ፤
ይኸስ ፡ አይደለም ፤ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ የተማረኩ፡ ሕዝቅያስ፡በሁለቱ፡ ነገድ፡ በነገሠ፡ በስድስት፡ ዓመት፡ ነውና፡ ብሎ፡ ይኸ፡ ነገር፡ ባሥሩ፡ ነገድ፡ ተደር ጎባት፡ሁለቱን፡ነገድ፡አየች፤አንድም፡ ርእየት፡ ያለውን፡ አሁን፡ ከሙ፡ ኃደ ግዋ፡ብሎ፡ያመጣዋል፤
ከመ፡ ኃደግዋ፡ ኵሎሙ፡ መሐዛኒሃ፡ እለ፡ ዘመወት፡ምስሌሆሙ፤
ርእየት፡ ያለውን፡ አመጣ፤ ከነሱ፡ ጋራ፡ እንደነሱ፡በኃጢአት፡የሰሰነችባቸው፡ ካህናቱ፡ ጣዖታቱ ፤ አንድም፡ እለ፡ ዘመዉ፡ ምስሌሃ፡ ይላል፤ ከሱዋ፡ ጋራ፡ ሁነው፡ ኃጢአት፡ ያሠሩዋት፡ ጣዖት፡ ያስመለኩዋት፤አንድም፡እለ፡ዘመዉ፡ ኪያሃ፡ ይላል፤እሷን፡ከእግዚአብሔር፡ አንድነት ፡ የለዩዋት ፡ ጣዖታቱ ፡ ካህናቱ፡ትተዋት፡እንደሔዱ፡አየች፤

፰፡ ወርኢኩ፡ ከመ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ዘመወት፡ ዕሉት፡፳ኤል፤
እኔም ፡ ያሥሩ ፡ ነገድ ፡ ወንጀለኛ ፡
[illegible]
ይላል ፡ ወንጀለኛ ፡ [illegible]



በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ እንደሰሰነች ፡ አየሁ፡
ወሰደድክዋ፡
አይቼም ፡ አልቀረሁ ፤ አስማርኬ ፡ ከሀ ገሩዋ ፡ አስወጥቼ ፡ ሰደድኋት ፤ አን ድም፡ በኃጢአት፡ በጣዖት፡ እንደሰ ሰነች፡ አይቼ ፡ አስማርኬ ፡ ከሀገርዋ ፡ አስወጥቼ፡ሰደድኋት፤
ወወሀብክዋ፡ መጽሐፈ፡ ኅዳጋቲሃ፡ ውስተ፡ ዕዴሃ፡
የምትፈታበትን፡ ነውር፡ የሚናገር፡ ደብዳቤ፡ጽፌ፡በእጅዋ፡ሰጠኋት፡አለ፤ የምትማረክበትን፡ የኃጢአቷን፡ ፍዳ፡ በራሱዋ፡ አመጣሁባት፡ ሲል፡ ነው፤ ሐተታ፡ ወኢከመ፡ ምትኪ፡ ዘንእስኪ፡ ያለውን፡ገለጸው፤
ወኢሐፈረት፡ኅሥርተ፡ይሁዳ፡እኅታ፤
የይሁዳ፡ ጐስቋላ፡ ይሁዳ፤ አንድም፡ ይሁዳ፡ስመ፡ሀገር፡ነው፤በይሁዳ፡የጐ ሰቆለች፡ ይሁዳ ፤ አንድም ፡ ኅሥርት ፡ ይሁዳ፡ እኅታ፡ ይላል፤ የጐሰቈለች፡ እኅቱዋ፡ ይሁዳም፡ አላፈረችም፡ አለ፤ ዓሥሩን፡ ነገድ፡ ያገኘ፡ መከራ፡ እኔን፡ ያገኘኛል፡አላለችም፤
ሖረት፡ወዘመወት፤
ወደ፡ ቤተ፡ ጣዖት፡ ሒዳ፡ በኃጢአት፡ በጣዖት ፡ ሰሰነች ፤ አንድም ፡ በኃ ጢአት ፡ በጣዖት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለየች፤

፱፡ ወከንቶ፡ኮነ፡ዝሙታ፡
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ መሰሰኗም ፡ ከንቱ ፡ ሆነባት ፡ አለ ፤ ከመጣባት ፡ መከራ፡አላዳናትም፤
ወዘመወት፡በዕፀው፡ወበአዕባን፡
በእንጨቱና፡ በድንጊያው፡ ሰሰነች፡
[illegible] ምላክ፡
[illegible]

፲፡ ወምስለ፡ ዝንቱ፡ ኵሉ፡ ኢተመይጠት፡ ኀቤየ፡ኅሥርተ፡ይሁዳ፡እኅታ፡በኵሉ፡ልባ፡
ይህም፡ ይህ፡ ነው፤ ከዚህም፡ ጋራ፡ በይሁዳ፡ የጐሰቈለች፡ ያሥሩ፡ ነገድ፡ እኅት፡ይሁዳ፡በፍጹም፡ልቡናዋ፡ሁና፡ በንሥሐ፡ወደኔ፡አልተመለሰችም፤
ዳዕሙ፡ውስተ፡ሐሰት፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
በጣዖት፡ጸንታ፡ኖረች፡እንጂ፡አለ፡እግ ዚአብሔር፤

፲፩፡ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤
አጽደቀት፡ ነፍሳ፡ ዕሉት፡ ፳ኤል፡ እምነ፡ ኅሥርት፡ይሁዳ፡
ከጐሰቆለች፡ ከይሁዳ፡ ያሥሩ፡ ነገድ፡ ወንጀለኛ፡ ዓሥሩ፡ ነገድ፡ ራሱዋን፡ አከበረች፤ አንድም፡ ዕሉት፡ ፳ኤል፡ ወንጀለኛ፡ ዓሥሩ፡ ነገድ፡ ከሁለቱ፡ ነገድ፡ ይልቅ፡ ራሱዋን፡ አሻለች፤ አሥሩ ነገድ፡ሕግ፡ተሠርቶለት፡ሕግ፡ አፍርሶ ፡ የተማረከ ፡ አብነት ፡ የላ ቸውም፤ሁለቱ፡ነገድ፡ግን፡ሕግ፡ተሠ ርቶላቸው ፡ ሕግ ፡ አፍርሰው ፡ የተማረኩ ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡ አብነት ፡ አሏቸውና ፤ አንድም ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁለቱ፡ነገድ፡ራሷን፡አከበረች፤

፲፪፡ ሖር፡ ወአንብብ፡ ዘ፡ ነገረ፡ ለመንገለ፡ ሰሜን፡
ሰሜን ፡ ያላት፡ ባቢሎን፡ ናት፤ ተማ ርከው ፡ ወደባቢሎን ፡ ለሚሄዱ ፡ ለ፳ኤል፡ ይህንን፡ ነገር፡ ጽፈህ፡ ሂደህ፡ አንብብላቸው፤
ወበል፡ተመየጢ፡ኀቤየ፡ዕሉት፡፳ኤል፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
ያሥሩ፡ነገድ፡ወንጀለኛ፡ሁለቱ፡ነገድ አንድም፡እንደ፡ዓሥሩ፡ነገድ፡የወንጀ

www.ethiopianorthodox.org

ነገድ፡ ጋራ፡ የወነጀልሽኝ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ በንሥሓ፡ ወደኔ፡ ተመለሽ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፡ ብለህ፡ አስተምራት፡ ሐተታ፡ካሥሩ፡ነገድ፡ ጋራ፡አለ፤ መች፡ ተገናኝተዋልና፡ እንዲህ፡ አለ፡ ቢሉ፡ ጊዜው፡ባያስተባብራቸው፡ግብሩ፡ያስተባብራቸዋልና፡እንዲህ፡አለ፤

ወኢያጸንዕ፡ገጽየ፡ላዕሌክሙ፡

በንሥሓ፡ ወደኔ፡ ከተመለሳችሁ፡ ግን፡ እኔም፡በናንተ፡ ገጼ፡ መዓቴን፡ አላጸናባችሁም፡አለ፤

እስመ፡መሓሪ፡አነ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እኔ፡ ፈጣሪያችሁ፡ እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ ባይ፡ ነኝና፡ እንደሰው፡ ጨካኝ፡ አይደለሁምና፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወኢይትመአዓክሙ፡እስከ፡ለዓለም፡

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብፈርድባችሁ ፡ ለዘላለሙ፡አልፈርድባችሁም፤

፲፫፡ ዳዕሙ፡ አእምሪ፡ ዓመፃኪ፡ ዘዓለውክኪ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላክኪ፤

ቤተ፡ ይሁዳ፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ትተሽ፡ እኔን፡ የወነጀልሽበትን፡ ክፉ፡ ሥራሽን፡ ብቻ፡ መርምረሽ፡ እወቂው፤ አንድም፡ ዳዕሙ፡ አእምሪ፡ ዓመፃኪ፡ ዘከመ፡ ዐለውክኪ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክኪ፡ ይላል፤ ቤተ፡ ይሁዳ፡ እኔን፡ እንደወነጀልሽ፡ ክፉ፡ ሥራሽን፡ መርምረሽ፡ እወቂው፡ አለ፡ ፈጣሪሽ፡እግዚአብሔር፤

ወዘረውኪ፡ፍናወኪ፡ኀበ፡ነኪራን፡

ክፉ፡ ሥራሽን፡ አበዛሽ፤ አንድም፡ ዘረውኩ፡ብኪ፡ይላል፤መከራሽን፡አበዛሁብሽ፤

ወታሕተ፡ኵሉ፡ዕፀው፡ወአዕዋም፡

ዘረውኩ፡ ያለውን፡ አመጣ፤ ወደዕንጨቱና ፡ ወደዛፉ ፡ በታች ፡ እንድትመ

ላለሽ፡አደረግሁሽ፤

ወኢሰማዕኪ፡ቃልየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ቀድሞ፡ እኔው፡ ራሴ፡ በደብረ፡ ሲና፡ ኋላም፡በነቢያት፡አድሬ፡የነገርኩሽን፡ ቃሌን፡ አልሰማሽም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፲፬፡ ተመየጡ፡ ኀቤየ፡ ደቂቅ፡ ዐላውያን፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፤

ወንጀለኞች ፡ ቤተ ፡ እስራኤል፤ አንድም፡ደቂቀ፡ዐላውያን፡ይላል፤የወንጀለኞች፡ ልጆች፡ ወንጀለኞች፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ግዱን፡ በንሥሓ፡ ወደኔ፡ ተመለሱ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡አነ፡እቀንየክሙ፡

ይኸን፡ ያደረጋችሁ፡ እንደሆነ፡ እኔ፡ በፍቅር፡ በሃይማኖት፡ አንድ፡ አድርጌ፡ እገዛችኋለሁና፤

ወእነሥአክሙ፡፲ተ፡ወ፩ደ፡እምሀገር፡ወ፪ተ፡እምብሔር፤

አሐደ ፡ እምሀገር ፡ አሥሩን ፡ ነገድ ፤ ወ፪ተ፡ እምብሔር፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ አንድ፡አድርጌ፡አወጣችኋለሁና፤

ወእወስደክሙ፡ውስተ፡ጽዮን፡

ከባቢሎንም፡ አውጥቼ፡ ወደጥንተ ዐገራችሁ፡ ወደጽዮን፡ እወስዳችኋለሁ፤

፲፭፡ ወእሁበክሙ፡ኖሎተ፡ዘከመ፡ልብየ፡

የሚመክሯችሁ ፡ የሚያስተምሯችሁ፡ ካህናትን ፤ የሚሠሯችሁ ፡ የሚቀጧችሁ ፡ ነገሥታትን ፡ እሰጣችኋለሁ ፤ አንድም ብእሴ፡ ምዕመኑ፡ ዘከመ፡ ልብየ፡ ያልሁት፡ ዳዊትን፤ አንድም፡ ዮሴዕንና ፡ ዘሩባቤልን ፡ እሾምላችኋለሁ፤

ወይርዕዩክሙ፡በጥበብ፡ወበአእምሮ፡

[illegible]

፳፭ ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፫

እኔ፡ በባሕርይ፡ ጥበቤ፡ በባሕርይ፡ እውቀቴ፡ እንዲጠብቋችሁ፡ አደርጋለሁ፤

፲፮፤ ወእምዝ፡ አመ፡ በዛኀክሙ፡ ውስተ፡ ምድር፡እንተ፡ወሀብክዋ፡ለአበዊክሙ፡

ከግብፅ ፡ ከወጣችሁ ፡ በኋላ ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ ባወረስኋት ፡ ሀገር ፡ በከነዓን ፡ ሁናችሁ፡በበዛችሁ፡ጊዜ፤

ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይብሉ፡እንከ፡ነያ፡ታቦተ፡ሥርዓቱ፡ለእግዚአብሔር፡ቅዱስ፡፳ኤል፡

ያንጊዜ ፡ ጽንዓ ፡ እስራኤል ፡ ክብረ ፡ እስራኤል ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር፡ የሕጉ፡ማደሪያ፡ታቦት፡ይህች፡ናት፡ አይሉም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወኢይሔልይዋ፡በልቦሙ፡

በልቡናቸውም፡አያስቧትም፤

ወኢይሰምይዋ፡በአፉሆሙ፡

በአፋቸውም ፡ የሕጉ ፡ ማደሪያ ፡ ናት ፡ ብለው፡አይጠሩዋትም፤

ወኢየኀሥሥዋ፡እንከ፡ውእተ፡አሚረ፡

ይእተ ፡ አሚረና ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ አንድ፡ወገን፡ነው፤ያንጊዜም፡የሕጉ፡ ማደሪያ፡ናት፡ብለው፡አይፈልጓትም፡ አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፯፤ወበውእቱ፡መዋዕል፡ይሰምይዋ፡ለኢየሩሳሌም፡መንበረ፡እግዚአብሔር፤

ድኅረ ፡ ሚጠት ፡ ግን ፡ ሚጠቱን ፡ አዝዝላቸዋለሁና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አገራችን ፡ ናት ፡ ብለው ፤ አንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ይጠሯታል፤አንድም፡ወእምዝ፡አመ፡ በዛኀክሙ ፤ ከባቢሎን ከወጣችሁ ፡ … ባወረስኋት ፡

በከነዓን ፡ ሁናችሁ ፡ በበዛችሁ ፡ ጊዜ ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይብሉ ፡ ጽንዓ ፡ ፳ኤል ፡ ክብረ ፡ እስራኤል፡የሚሆን፡የእግዚአብሔር፡ የሕጉ፡ማደሪያ፡ታቦት፡ይህች፡ናት፡ አይሉም፤

ወኢይሔልይዋ፡በልቦሙ፡

በልቡናቸውም፡አያስቧትም፤ ወኢይሰምይዋ፡በአፉሆሙ፡

የሕጉ፡ማደሪያ፡ታቦት፡ይህቺ፡ናት፡ ብለውም ፡ አይጠሯትም ፤ ወኢየኃሥሥዋ ፡ እንከ ፡ ውእተ ፡ አሚረ፤ ከጽርዕ፡በወጡ፡ጊዜ፡ግን፡ያን፡ጊዜ፡ የሕጉ፡ማደሪያ፡ይህች፡ናት፡ብለው፡ አይፈልጓትም፡አለ፡እግዚአብሔር፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ከጽርዕ ፡ በወጡበት ፡ ወራት ፡ ግን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ናት፡ብለው፡ስሟን፡ይጠሯታል፤

ወይትጋብኡ፡ኵሉ፡አሕዛብ፡በስመ፡እግዚአብሔር፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም፡

ዓሥሩ፡ነገድና፡ሁለቱ፡ነገድ፡በፈጣሪያቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ተሰብስበው ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ይመጣሉ ፡ አሕዛብ፤ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ አሕዛብ ፡ ናቸው፤ አምነው ፡ ተጋብተው ፡ የመጡ ፡ አሕዛብ ፡ በሰባው ፡ ዘመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም፡ አምነው ፡ ተሰብስበው፡ ከ፳ኤል ፡ ጋራ ፡ ሁነው፡ወደኢየሩሳሌም፡ይመጣሉ፤

ወኢይተልዉ፡እንከ፡ሕሊና፡ልቦሙ፡እኩየ፡

እንግዲህ፡ወዲህ፡ልቡናቸው፡የሚወደውን፡ክፉውን፡ነገር፡አይከተሉም፤ አንድም፡ወኢይተሉ፡እንከ፡ሕሊና፡

www.ethiopianorthodox.org

ልቦሙ፡እኩየ፡ይላል፤በዚያ፡ወራት፡
ልቡናቸው ፡ የወደደውን ፡ ክፋውን ፡
ነገር፤ አንድም ፡ የወደደው፡ ክፋውን ፡
ጣዖት፡ልቡናቸው፡አይከተልም፤

፲፰፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ይመጽኡ ፡
ቤተ፡ይሁዳ፡ምስለ፡ቤተ፡፳ኤል፡

በዚያ፡ወራት፡ሁለቱ፡ነገድ፡ካሥሩ፡
ነገድ ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ ከባቢሎን ፡
ይመጣሉ፡ይኸስ፡አይደለም፤ዓሥሩ፡
ነገድ፡የወጡ፡በሁለቱ፡ነገድ፡ተስፋ፡
ነው፤ መደበኞች ፡ ሁለቱ ነገድ ፡
ናቸውና፡ብሎ፡ወበውእቱ፡መዋዕል፡
ይመጽኡ፡ቤተ፡፳ኤል፡ምስለ፡ቤተ፡
ይሁዳ፡ይላል፤በዚያስ፡ወራት፡ዓሥሩ፡
ነገድ፡ከሁለቱ፡ነገድ፡ጋራ፡ሁነው፡
ይመጣሉ፤

ወይመጽኡ ፡ ኅቡረ ፡ እምብሔረ ፡ ሰሜን፡
ሲመጡም ፡ ከባቢሎን፤ አንድም ፡
ከጽርዕ ፡ ወእምኵሉ ፡ በሐውርት ፡
ውስተ፡ምድር፡እንተ፡ወሀብክዋ፡ለአ
በዊሆሙ፤

ከሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለአባቶ
ቻቸው ፡ ወደሰጠኋት ፡ አገር ፡ ወደ፡ከ
ነዓን ፡ ተሰብስበው፡ አንድ ፡ ሁነው ፡
ይመጣሉ፤

፲፱፡ወአነሂ፡እቤ፡ይኩን፡እግዚእ፡
እኔም፡ይኸን፡ሰምቼ፡አቤቱ፡ይበጅ፡
ያድርግ፡አልኩ፤

እስመ ፡ አዘዝከ ፡ ላዕለ ፡ ውሉዶሙ ፡
እሁበክሙ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ርስተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ዘአሕዛብ፤
የሰብዓ ፡ ከነዓንን ፡ አገር ፡ ሁሉን ፡
የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡
ያደረጋት ፡ ምድረ፡ ርስትን ፡ ለልጆ
ቻችሁ ፡ አወርሳለሁ ፡ ብለህ፡ አዝዘ
ሃልና፡ይሁን፡ይበጅ፡አልሁ፤

እመሰ፡አቡየ፡ትብለኒ፡
አባት፡እንዲከበር፡አባቴስ፡ብላ፡ብታ
ከብረኝ፤

ወትትመየጥ፡ኀቤየ፡
በንሥሓም ፡ ወደኔ ፡ ብትመለስ ፡
እሰጣለሁ፡ብለህ፡አዝዘሃልና፤

፳፤ ወባሕቱ ፡ ከመ ፡ ተአልዎ ፡ ብእሲት፡
ለምታ፡ከማሁ፡ክህዱኒ፡ቤተ፡፳ኤል፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡

ነገር ፡ ግን ፡ ሴት ፡ ባሉዋን ፡ እንድት
ክደው፡እንድትወነጅለው፡የ፳ኤልም፡
ወገኖች ፡ ካዱኝ ፤ ወነጀሉኝ ፡ አለ ፡
እንጂ፡ እግዚአብሔር ፤ በንሥሓ ፡
ብትመለስ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለህ ፡ አዝዘ
ሃልና፤

፳፩፡ቃል፡በአዕላፍ፡ተሰምዐ፡
በ፳ኤል፡ከተማ፡በዝቶ፡ቃል፡ተሰማ፤
አንድም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡
በዝቶ፡ቃል፡ተሰማ፤

ብካየ፡ገዓሮሙ፡ለደቂቀ፡፳ኤል፡
ቃል፡በአዕላፍ፡ተሰምዓ፡ያልሁትም፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጦር ፡
ተወግተው፡ጨኸው፡የሚያለቅሱት፡
ልቅሶ፡ነው፤

እስመ፡ዓመፁኒ፡በፍናዊሆሙ፤
በሥራቸው ፡ በድለውኛልና ፡ (አሳዝነ
ውኛልና)፤

ወረስዕዎ ፡ ለአምላኮሙ ፡ ወለቅዱሶሙ ፡
ጽንዓቸው፡ክብራቸው፡የሚሆን፡ፈጣ
ሪያቸውንም፡ዘንግተውታልና፤

፳፪፤ተመየጡ፡ደቂቅ፡ዓላውያን፡
ደቂቅ ፡ ዓላውያን ፡ ደቂቀ ፡ ዓላውያን ፡
ይላል ፤ ወንጀለኞች ፡ የምትሆኑ ፡
እስራኤል፡በንሥሓ፡ወደኔ፡ተመለሱ፤

ወእፌውሰክሙ፡ቀኑስለክሙ፤
በንሥሓ ፡ ብትመለሱ ፡ ከቍስለ ፡
መከራችሁ፡አድናችኋለሁ፤



ናሁ፡ንህነ፡ንከውን፡አግብርቲከ፡
ይኸንስ፡ካደረግክልን፡ላንተ፡እነሆ፡
ተገዦች፡እንሆናለን፤

እስመ፡አንተ፡አምላክነ፡
ፈጣሪያችን ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ይቅር ፡
በለን፤ አንድም ፡ አንተ ፡ አምላካችን ፡
ስለሆንክ፤

፳፫፤ ወአማን ፡ ሐሰት ፡ ውእቱ ፡ አውግሪን፡
ወኃይለ፡አድባሪነ፡
ተራራውን፡ኮረብታውን፡አምልከን፡
ኀያል፡ማለታችን፡በእውነት፡ሐሰት፡
ነው፤

ወዳዕሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡
መድኃኒተ፡፳ኤል፡
የኛ፡የወዳጆችህ፡የ፳ኤል፡ደህንነት፡
ከፈጣሪያችን፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ
ታዝዞ ፡ ይደረግልን ፡ እንጂ፤ ኮረብ
ታውና፡ተራራው፡በእውነት፡ሐሰት፡
ነው፡አሉ፤ሐተታ፡በዚያ፡ወራት፡
ተራራውንና፡ኮረብታውን፡ያመልኩ፡
ነበረና፤አንድም፡ዘላዕለ፡አውግሪነ፡
ወኃይለ ፡ አድባሪነ ፡ ይላል፤ በኮረ
ብታው ፡ የቆመ ፡ ጣዖት ፡ በተራ
ራውም፡የቆመ፡ጣዖት፡በኛስ፡ዘንድ፡
በእውነቱ ፡ ሐሰት ፡ ነው፤ ወዳዕሙ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የኛ ፡ የወዳጆችህ ፡ የእስ
ራኤል፡ድህነት፡በፈጣሪያችን፡በእግ
ዚአብሔር፡ዘንድ፡ይደረግልን፡እንጅ፤

፳፬፤ ወሐፍረቶሙ ፡ አኀለቀት ፡ ተግባ
ሮሙ፡ለአበዊነ፡እምንእሶሙ፡
ሐፍረቶሙ፡ለአበዊነ፡እምንእሶሙ፡
አህለቀት፡ተግባሮሙ፡እምንእሶሙ፡
ብለው ፡ ይገጥሙታል፤ አባቶቻችን ፡
ከጥንት፡ጀምረው፡የሠሩዋት፡ክፋ፡
ሥራቸው ፡ ኃጢአታቸው ፤ ከጥንት ፡
ጀምሮ፡ያጠራቀሙት፡ገንዘባቸውን፡
ሁሉ፡አጠፋባቸው፤ሐተታ፡ሐፍረት፡
አላት፡ኃጢአቲቱን፡በሰውም፡በእግ
ዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ የምታሳፍራ
ቸው፡ስለሆነ፤

አባግዒሆሙ፡ወአልሕምቲሆሙ፡
ተግባሮሙ ፡ ያለውን ፡ ይተረትራል ፡
በጎቻቸውንና፡ላሞቻቸውን፤

ወአዋልዲሆሙ፡ወደቂቆሙ፡
ሴቶች፡ልጆቻቸውንና፡ወንዶች፡ልጆ
ቻቸውን፡አጠፋችባቸው፤

፳፭፤ ወኖምነ፡በሐፍረትነ፡
በጕስቍልና ፡ ሳለን ፡ የሞት ፡ እን
ቅልፍ፡አንቀላፋን፤

ወተከደነ፡በሐሣርነ፡
በመከራውም ፡ ፈጽመን ፡ ተያዝን፤
አንድም ፡ ከጕስቍልናው ፡ ጋራ ፡
በመከራው ፡ ተይዘን ፡ የሞት ፡
እንቅልፍ ፡ አንቀላፋን፤ ወተዋሐደ ፡
ቃል፡በሥጋ፡እንዲል፤ሐተታ፡ነቢዩ፡
በነሱ ፡ ተገብቶ ፡ ኖምነ ፡ በሐሣርነ ፡
አለ፤ አንድም ፡ ኖምነ ፡ በሐፍረትነ ፡
በሉ፡ይላቸዋል፤

እስመ ፡ አበስነ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፡ ንሕነ ፡ ወአበዊነ ፡ እምንእስነ ፡
እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡
እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡አለ፤ እስኪጽፍ፡
ድረስ፡ከጥንት፡ጀምሮ፡እስከ፡ዛሬ፡
ድረስ፡እኛም፡አባቶቻችንም፡ፈጣሪ
ያችን፡እግዚአብሔር፡ባወቀው፡በድ
ለናልና፤

ወኢሰማዕነ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡
እኛም፡አባቶቻችንም፡የፈጣሪያችን፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማ
ንምና።

## ምዕራፍ፡፬

፩፤ ለእመ፡ገብአ፡፳ኤል፡ኀቤየ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡ወተመይጠ፡

www.ethiopianorthodox.org

ገብአ፡ ወተመይጠ፡ አንድ፡ ወገን፡ ነው፤ እስራኤል፡ በንሥሓ፡ ፈጽሞ፡ ወደኔ፡ቢመለስ፤

ለእመ፡አዕተተ፡ርኵሰ፡እምአፉሁ፡

ኃጢአት፡ ልሥራ፡ ማለትን፡ ካን ደበቱ፡ ቢያርቅ፤ አንድም፡ ለእመ፡ አስተተ፡ ርኵሰ፡ እምአፉሁ፡ ይላል፤ የጣዖቱን፡ምስጋና፡ባንደበቱ፡ቢንቅ፡ ቢያቃልል፤

ወፈርኀ፡እምገጽየ፡

ከገጸ፡ መዓቴም፡ የተነሣ፡ ቢፈራኝ፡ ቢያመልከኝ፤

፪፡ ወመሐለ፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ በርትዕ፡ወፍትሕ፡ወጽድቅ፡

ፍትሕ፡ ርትዕ፡ አንድ፡ ወገን፡ ነው፤ ሕያው፡ እግዚአብሔርን፡ ብሎ፡ በእውነቱ፡በሚገባ፡ቢምል፤

ወይትባረኩ፡ቦቱ፡አሕዛብ፡

ሕዝቡ፡ አሕዛቡ፡ እስራኤል፡ በዚህ፡ ይከብራሉ፤

ወይሴብሑ፡ ቦቱ፡ በኢየሩሳሌም፡ ዘእግዚአ ብሔር፡

ቦቱን፡ ኪያሁ፡ ሲል፡ ነው፤ በእግዚአ ብሔር፡ መዲና፡ በኢየሩሳሌምም፡ እሱን፡ ያመሰግናሉ፡ አለ፡ እግዚአ ብሔር፤ አንድም፡ ለእመ፡ ገብአ፡ ፳ኤል፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ወተመይጠ፡ እስራኤል፡ በንስሓ፡ ፈጽሞ፡ ወደኔ፡ ከተመለሰ፡ ለእመ፡ አስተተ፡ ርኵሰ፡ እምአፉሁ፡ ባንደ በቱም፡ ጣዖቱን፡ ቢንቅ፡ ቢያቃልል፤ አንድም፡ለእመ፡ አዕተተ፡ ርኵሰ፡ እምአፉሁ፡ እምኔሁ፡ ሲል፡ ነው፤ ኃጢአቱንም፡ ከሱ፡ ካራቀ፡ ቢያ ርቅ፡ ወፈርኀ፡ ከገጸ፡ መዓቴም፡

የተነሣ፡ ያጠፋኛል፡ ብሎ፡ እኔን፡ ከፈራ፡ ካመለከ፡ ወመሐለ፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ በርትዕ፡ ወፍትህ፡ ወጽድቅ፡ መሐላ፡ እግዚአብሔርን፡ ጠብቀው፤ ወይትባረኩ፡ ቦቱ፡ አሕዛብ፡ ሕዝቡ፡ አሕዛቡ፡ በዚህ፡ እን ዲከብሩ፡ ሕያውየ፡ አማንየ፡ ብሎ፡ በእውነቱ፡ ማለ፤ እግዚአብሔር፡ ወይሴብሑ፡ ቦቱ፡ ይሴብሑን፡ አጥብቅ፤ በኢየሩሳሌም፡ ዘእግዚአ ብሔር፡በእግዚአብሔር፡መዲና፡በኢ የሩሳሌምም፡ ሁነው፡ በነሱ፡ እንዲ ከበሩ፡ ሕያውየ፡ አማንየ፡ ብሎ፡ በሚገባ፡ማለ፡እግዚአብሔር፤

፫፡ እስመ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ለእደወ፡ይሁዳ፡እለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፡

በኢየሩሳሌም፡ የሚኖሩ፡ የይሁዳን፡ ሰዎች፤እግዚአብሔር፡ነገር፡አድርጎ፡ ተናገራቸው፤ አንድም፡ በኢየሩ ሳሌም፡ለሚኖሩ፡ለይሁዳ፡ሰዎች፡እግ ዚአብሔር፡ የሚያደርጉትን፡ ነገር፡ አውጥቶ፡ነገራቸው፤

ሐድሱ፡ልበክሙ፡ሐድሶተ፡

ልቡናችሁን፡በእውቀት፡አጽኑ፤

ወአኀትዉ፡ማኀቶተ፡ጥበብ፡

አኀትዉ፡ ማኀቶተ፡ ግሥ፡ ነው፤ ጥበብንም፡ ያዙ፤ አንድም፡ በጥበብ፡ የተገኘውንም፡ዕውቀት፡አጽኑ፤

ወኢትዝርኡ፡ውስተ፡ሦክ፡

ኃጢአት፡ በሚስማማው፡ ሰውነት፡ ኃጢአት፡ አትሥሩ፤ አንድም፡ ሦክ፡ ኃጢአት፡አትሥሩ፤

፬፡ወ[illegible]

ፈጣሪያችሁን፡ [illegible]



አንድም፡ ፈጣሪያችሁን፡ ደስ፡ ለማሰኘት፡ ቍልፈተ፡ ልቡናችሁን፡ ከናንተ፡አርቁ፤

ወግዝሩ፡ እከዮ፡ ለልብክሙ፡ እደወ፡ ይሁዳ፡ እለ፡ትነብሩ፡ኢየሩሳሌም፡

በኢየሩሳሌም፡ አገር፡ የምትኖሩ፡ የይሁዳ፡ ሰዎች፤ አንድም፡ ዕደወ፡ ይሁዳ፡ የይሁዳ፡ ሰዎች፡ ወእለ፡ ትነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፤ በኢየሩሳሌም፡ የምትኖሩ፡ሰዎችም፡ሁሉ፡ተገዘሩም፡ ማለቴ፡የአባለ፡ዘራችሁን፡ቍልፈት፡ አይደለም፤ የልቡናችሁን ቍልፈት፡ ከናንተ፡አርቁ፤

ወኢይፃእ፡ከመ፡እሳት፡መዓትየ፡

ቁጣዬ፡እንደ፡እሳት፡ተናዶ፡እንዳይ መጣባችሁ፡ነው፤

ወትነድድ፡

መጽሐፍ፡ምሥጢር፡እንጂ፡ዘይቤ፡ አይጠነቀቅምና፡ ኢይጻእ፡ መዓትየ፡ ብሎ፡ ወትነድድ፡ አለ፤ ይኸንን፡ ሰምታችሁ፡ባትመለሱ፡ግን፡ቍጣዬ፡ እንደ፡እሳት፡ትናደድባችኋለች፤

ወአልቦ፡ ዘያጠፍአ፡ እምገጸ፡ ጌጋየ፡ እከይክሙ፤

መቅሠፍቲቱንም፡ በክፋታችሁ፡ ከበ ደላችሁኝ፡ በደል፡ የተነሣ፡ መዓትን፡ መቅሠፍትን፡ የሚያጠፋት፡ የለም፤ አንድም፡ እምገጸ፡ እከየ፡ ጌጋይክሙ፡ ይላል፤ ከበደላችሁኝ፡ በደል፡ ጽናት፡ የተነሣ፡ቍጣዬን፡በዚያ፡ወራት፡የሚ መልሳት፡ የለም፤ ሐተታ፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ በብዙ፡ ወገን ይመለ ሳልና፡ሐተታ፡እንደ፡ኢሳይያስ፤

፭፡ ዜንዉ፡ በይሁዳ፡ ወአስምዑ፡ በኢየሩ ሳሌም፡

ይኸንንም፡ ነገር፡ በኢየሩሳሌምና፡ በይሁዳ፡ ሁናችሁ፡ ለእስራኤል፡ ንገሯቸው፤ እምቢ፡ አንሰማም፡ ቢሉ፡ ግን፡ አዳኙባቸው፤ አንድም፡ ዜንዉ፡ ለይሁዳ፡ ወአስምዑ፡ ለኢየሩሳሌም፡ ይላል፤ ይኸንንም፡ ነገር፡ ለኢየሩሳ ሌምና፡ ለይሁዳ፡ ሰዎች፡ ንገሩዋቸው፡ አስተምሩዋቸው፤ እምቢ፡ ቢሉ፡ ግን፡ አዳኙባቸው፤

ወበሉ፡፡ተአመሩ፡በቃለ፡ቀርን፡

ዜንዉ፡ያለውን፡አመጣ፤ነጋሪቱንም፡ እየመታችሁ፡ ተገልጣችሁ፡ ታወቁ፡ በኋቸው፤

ወንፍሑ፡ቀርነ፡ውስተ፡ብሔር፡

በሀገራችሁም፡ ውጋ፡ ውጋ፡ የሚል፡ ነጋሪቱን፡ ምቱ፤ ጦር፡ ለመሰብሰብ፡ አንበጣ፡ለማባረር፤

ወስብኩ፡ምህላ፡ዓቢየ፡

ምህላ፡ ለመያዝ፡ ምህላ፡ እንያዝ፡ ብላችሁ፡አዋጅ፡ንገሩ፤

ተጋብኡ፡ወባኡ፡አህጉረ፡ጥቅም፡

ተሰብስባችሁ፡ አጥር፡ ቅጥር፡ ወዳለበት፡ ከተማ፡ ግቡ፤ ሐተታ፡ – ባጥር፡በቅጥር፡ሁኖ፡የሚዋጋ፡ጦር፡ ፈጥኖ፡ድል፡አይነሣምና፤

፮፡ወንሥኡ፡ጽዮነ፡

አምባውን፡ያዙ፤

ወአምሥጡ፡ውስተ፡ጽዮን፡

አምባውን፡ ይዛችሁ፡ ዳኑ፤ አንድም፡ ጽዮንን፡ እመኑባት፤ በጽዮን፡ አምናችሁ፡ዳኑ፤አንድም፡ሕገ፡እግዚ አብሔርን፡ ያዙ፡ ሕገ፡ እግዚአብ ሔርን፡ይዛችሁ፡ዳኑ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሩጹ፡ወኢትቁሙ፡
ይህ ፡ ባይሆንላችሁ ፡ ግን ፡ ፈጥናችሁ፡
ሽሹ፡አትቁሙ፤

እስመ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ እምደቡብ ፡
ወዓቢየ፡ቅጥቃጤ፡
ከባቢሎን ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ አመጣባችኋ
ለሁና፤ ሐተታ ፡ ባቢሎንን ከታች
ሰሜን፡ ብሏት ፡ አልነበረምን ፡ ከዚህ፡
ስለምን ፡ ደቡብ ፡ አላት ፡ ቢሉ ፡ ላንድ፡
ሀገር፡ ሁለት፡ ስም፡ አለውና፤ አንድም፡
ዓራት፡ማዕዘን፡የሌለውን፡አገር፡አለ?
ላንዱ፡ሰሜን፡ብትሆን፡ላንዱ፡ደቡብ፡
ትሆናለችና፤

፯፡ አንበሳ፡ወጽአ፡እምግቡ፡ወሠረዎሙ፡
ለአሕዛብ፡
አንበሳ ፡ ናቡከደነጿር ፡ ነው ፤ ከከተ
ማው፡ወጥቶ፡አሕዛብን፤አጠፋቸው፡
አለ ፡ በቁሙ ፤ አንድም ፡ አሕዛብ ፡
ያላቸው፡እስራኤል፡ናቸው፤ሐተታ፡
እንዳለፈው፤

ተንሥአ፡ወወጽአ፡እምድሩ፡ከመ፡ያማስን፡
ብሔረከ ፡ ወያንሕሎን ፡ ለአህጉሪከ፡ ከመ ፡
አልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴቶን፡
ቤተ ፡ እስራኤል ፡ በሀገሮችህ ፡ ሰው ፡
እንዳይኖርባቸው፡ አገርህን ፡ ፈጽሞ ፡
ሊያጠፋ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ከከተማው ፡
ተነሥቶ ፡ መጣ፤ ሐተታ ፡ – ናቡከደነ
ፆርን ፡ አንበሳ አለው፤ አንበሳ ፡
ከዓራዊት ፡ ሁሉ ፡ ተለይቶ ፡ ገናና ፡
ኃይለኛ ፡ እንደሆነ ፡ እሱም ፡ ከሱ ፡
አስቀድሞ ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ ከነገሡ ፡
ነገሥታት ፡ ተለይቶ ፡ ገናና ፡ ኃይለኛ ፡
ነውና፤

፰፡ ወበበይነ፡ዝንቱ፡ቅንቱ፡ሠቀ፡ብከዩ፡
ወአውይዉ፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ
ታጥቃችሁ ፡ ጩኹችሁ ፡ አልቅሱ፤
አንድም፡አልቅሳችሁ፡ጩኹ፤

እስመ፡ኢተመይጠ፡መዓተ፡እግዚአብሔር፡
ወመቅሠፍቱ፡እምኔክሙ፡
እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ያመጣው ፡
ፍጹም ፡ መቅሠፍቱ ፡ ከናንተ ፡ አልተ
መለሰምና፤ ሐተታ ፡ መዓት ፡ የልብ ፡
ነው፤ መቅሠፍት ፡ በሥራ ፡ የሚገለጽ
ነው፤

፱፡ ወውእቱ ፡ አሚረ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ይጠፍዕ ፡ ልበ ፡ ንጉሥ ፡ ወልበሙ ፡
ለመላእክት፡
የመኳንንቱና ፡ የንጉሡ ፡ አእምሮ ፡
በዚያ፡ወራት፡ይጠፋል፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤ አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡
በዚያ ፡ ወራት ፡ የንጉሡና ፡ የመኳ
ንንቱ፡አእምሮ፡ይጠፋል፡አለ፤
ወካህናትኒ ፡ ይትኃበኡ ፤ ካህናተ ፡
ጣዖቱም፡ መከራውን ፡ ፈርተው ፤
አንድም ፡ የተናገራችሁት ፡ ሐሰት ፡
ሐሰት ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ይጣሉናል ፡
ብለው ፡ ፈርተው ፡ ይህን ፡ ባለው ፡
ይኀብኡ ፡ ይላል፤ ይፈርሁ ፡ ይደነግፁ፡
ሲል፡ነው፤

፲፡ ወእቤ ፡ እግዚእ ፡ በከኑ ፡ ትየውሆሙ ፡
ለአሕዛብ ፡ ወለኢየሩሳሌም ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡
ሰላም፡ሰላም፤
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት ፡
አንደበት ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ እያልክ ፡
አገርህ፡ኢየሩሳሌምን፤ወገኖችህ፡እስ
ራኤልን ፡ በከንቱ ፡ ታታልላቸዋለህ ፡
ይሆን፡አልሁ፤

ወትረክቦሙ፡በመጥባሕት፡እስከ፡ነፍሶሙ፤
ለኔ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ጨርሳ ፡ እስክ
ታጠፋ ፡ ድረስ ፡ ወር ፡ መቅሠፍቱቱ ፡
ታገኛቸዋለች፡ትለኛለህ፡

፲፩፡ ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ይቤልዎሙ ፡ ለዝ፡
እዝብ ፡ እለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ጋኔን ፡ መስሕት፡
ውስተ፡ገዳመ፡ፍኖተ፡ወለተ፡ሕዝብየ፡
ላእሉ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ሲል፡ነው፤
የንጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡
እነዚህን ፡ ወገኖች ፡ ነቢያተ ፡ ጽድቅ ፡
የወገኔ ፡ ልጅ ፡ በምትሄድበት ፡ ጎዳና ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ የሚያስት፡
ጋኔን፡አለ፡አሉዋቸው፤

እኮ፡ለዘረው፡ወእኮ፡ለአስተጋብኦ፡
ይህም፡ጧት፡ማታ፡የሚያስት፡ጋኔን፡
ጼዋዌን ፡ ተናግሮ ፡ ለማስማረክ፡
ሚጠትን ፡ ተናግሮ ፡ ለመመለስ ፡
አይደለም፤

፲፪፡ዳዕሙ፡ጋኔን፡መስሕት፡ይመጽእ፡
ጧት ፡ ማታ ፡ የሚያስታቸው ፡ ጋኔን ፡
ያስቀባጥራቸዋል ፡ እንጂ፤ አንድም ፡
የሚያስታቸው ፡ ጋኔን ፡ ጧት ፡ ማታ ፡
ያስቀባጥራቸዋል፡እንጂ፤

ወይእዜኒ፡አነ፡እነግር፡ቅስትየ፡ሎሙ፡
ቦሙ ፡ ሲል ፡ ነው፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ በነሱ፡
ያገኘኝን ፡ ወቀሳ ፡ ላንተ ፡ ለፈጣሪዬ ፡
እናገራለሁ፤አንድም፡ሎሙ፡እነሱን፡
ሊረባቸው፡ሊጠቅማቸው፡ብዬ፤

፲፫፡ ናሁ፡ከመ፡ደመና፡ወከመ፡ዓውሎ፡
ሠረገላሁ፡
እነሆ ፡ የናቡከደነፆርስ ፡ ሠረገላው ፡
እንደ ፡ ደመና ፤ እንደ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡
በዝቶ፡ፈጥኖ፡ይመጣል፤

ይበድሩ፡እምአንሥርት፡ሰማይ፡አፍራሲሁ፡
ፈረሶቹም ፡ ከሰማይ ፡ ንሥሮች ፡
ፈጥነው፡ቀድመው፡ይገኛሉ፤

አሌ፡ለነ፡እስመ፡ኃሠርነ፡
በመከራው፡ጕስቍለናልና፡ወዮልን፡
አለ ፤ በነሱ ፡ ተገብቶ ፡ ነቢዩ ፡ እንዲህ ፡
አለ፤ አንድም ፡ በሉ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤
በመከራው፡ ጕስቍለናልና ፡ ወዮልን ፡
በሉ፡ አሏቸው፡

፲፬፡ ሕፅቢ ፡ እከየ ፡ ልብኪ ፡ ኢየሩሳሌም፡
ከመ፡ትድኅኒ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ብሎ ፡ ያሰማታል ፤ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ከመከራው ፡ ትድኚ ፡ ዘንድ ፡
የልቡናሽን፡ክፋት፡ካንቺ፡አርቂው፤

እስከ፡ማዕዜኑ፡የኀድር፡ላዕሌኪ፡ሕሊና፡ዘየ
ኃሥረኪ፤
ጣዖት ፡ አምልኪ ፤ ኃጢአት ፡ ሥሪ ፡
የሚል፡ ሕሊና ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡
ያድርብሻል?

፲፭፡ እስመ፡መጽአ፡ቃል፡ዘይዜንወኪ፡
እምዳን፡
ከዳርቻ፤አንድም፡ከነገደ፡ዳን፡ነቢይ፡
መጥቷልና ፡ ንሥሒ ፡ ግቢ ፡ እንጂ ፤
አንድም ፡ ሽሺ ፡ አትዋጊ ፡ የሚል ፡
ሕሊና ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ያድር
ብሻል ፡ ከጽንፍ፤ አንድም ፡ ከዳን ፡ ዕፃ፡
ናቡከደነፆር ፡ መጥቷልና ፡ ወጥተሽ ፡
ተዋጊ፡እንጂ፤

ወደሰማዕ፡ሕማም፡እምአድባረ፡ኤፍሬም፡
ካሥሩ፡ነገድ፡አገር፡ጀምሮ፡እስከኛ፡
ድረስ ፡ መከራው ፡ ሲነገር ፡ ተሰማ ፤
አንድም ፡ ባሥሩ ፡ ነገድ ፡ የመጣ ፡
መከራ ፡ በኛም ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ተደረገ፤



www.ethiopianorthodox.org

፲፮፤ አዘክሩ፡ለአሕዛብ፡ወአስምዑ፡ ላዕለ፡ኢየሩሳሌም፤

ይኸንንም ነገር፡በገጠር፡ላሉ፡ለእስ ራኤል፡ንገሯቸው፤በመዲናይቱ፡በኢ የሩሳሌም፡ላሉ፡ ሰዎችም፡አዳኙ ባቸው፤

ወዜንዉ፡መጽኡ፡እምርኁቅ፡ብሔር፤

አዘክሩ፡ያለውን፡አመጣ፤እነናቡከደ ነፆር፡ከፋርስ፡ከባቢሎን፡ከጽርዕ፡ ከሜዶን፡ተሰብስበው፡መጡ፡ ብላችሁ፡ንገሩዋቸው፤

ወይሁቡ፡ቃሎሙ፡ውስተ፡አህጉረ፡ይሁዳ፤

ተሰብስበው፡መጥተውም፡በይሁዳ፡ አውራጃ፡ባሉ፡አገሮች፡ቃላቸውን፡ ይሰጣሉ፤አለ፤አገረሩ፤ደነፉ፤

፲፯፤ ከመ፡መዓቅበ፡ሐቅለ፡ዘርእ፡ኮኑ፡ ላዕሌሃ፡እምዓውዳ፤

በዙሪያዋም፡ሁነው፡እንደ፡መት፡ ጠባቂ፡ሆኑባት፤ሐተታ፡ይህ፡መት፡ ጠባቂ፡አንዱ፡መጀመሪያ፡ኻይ፡ ብሎ፡ የጮኸ፡እንደሆነ፡ቀጥሎ፡ ቀጥሎ፡ያለውም፡ኻይ፡ኻይ፡እያለ፡ ይጮኻልና፤

፲፰፤ እስመ፡ተሐየይክኒ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፡ፍናውኪ፡ወምግባርኪ፡ገብረ፡ዘንተ፤

በምግባር፡በሃይማኖት፡ቸል፡ብለሽ ኛልና፡ፍጹም፡ክፉ፡ሥራሽ፡ይኸን፡ ሁሉ፡አደረገብሽ፡አለ፡እግዚአ ብሔር፤

ወዝንቱ፡ኵሉ፡በእከይኪ፤

ይህም፡ሁሉ፡መከራ፡የታዘዘብሽ፡ በክፉ፡ሥራሽ፡ነው፤

እስመ፡መሪር፡ረከባ፡ለነፍስኪ፤

ሰውነትሽን፡ጽኑ፡መከራ፡አግኝ ታልና፤

አሕመመኒ፡ማንሻ፡ነው፤አንድም ሰውነትሽን፡ጽኑ፡መከራ፡ጽኑ፡ኃዘን አግኝቷታልና፤

፲፱፤ ከርሥየ፡ወሥርወ፡ልብየ አሕመመኒ፤

ከርሥየ፡በቁሙ፡የልቡናዬም፡ሥር፡ አዘነብኝ፤

ወነፍስየ፡ተአነብዝ፤

ልቡናዬም፡አእምሮዋን፡ታጣለች፤

ወተአይስ፤

ወዲያውም፡ትዛብራለች፤

ወልብየኒ፡ኢያረምም፤

ነፍስየ፡ተአነብዝ፡ያለውን፡አመጣ፤ ልቡናዬም፡ላንቺ፡ከማዘን፡አያርፍም፤ ዝም፡አይልም፡አለ፤ነቢይ፡ርኅሩኅ፡ ነውና፤ አንድም፡ርኅሩኅ፡እግዚአ ብሔር፡ቢያድርበት፤

እስመ፡ሰምዐት፡ነፍስየ፡ቃለ፡ቀርን፡ ወውውዓ፡ቀትል፤

ይህንም፡ሁሉ፡ማድረጌ፡አሕዛብ፡ተሰ ብስበው፡መጥተው፡ውጋ፡ውጋ፡ የሚል፡የነጋሪቱን፡ድምፅ፡እልል ታውን፤ግርግርታውን፡ልቡናዬ፡ ስለሰማች፡ስለአወቀች፡ነው፤

፳፤ ወሕርትምና፤

ጕስቍልናውም፡ከእግዚአብሔር፡ ታዝዞ፡ስለመጣባት፡ነው፤አንድም፡ በኔ፡ታዝዞ፡ስለመጣብኝ፡ነው፤

ቅጥቃጤ፡በዲበ፡ቅጥቃጤ፡ተጸውአ፤

በቤተ፡እስራኤልስ፡መከራው፡ ከመከራው፡ጋራ፡ተጣርቶ፡መጠበቅ



እስመ፡ኅሥረት፡ኵላ፡ምድር፡ግብተ፡ ድንገት፡መከራው፡መጥቶባት፡ ምድር፡ሁሉ፡ጐስቍላለችና፤ሐተታ፡ በምድር፡ሰዎቹን፡መናገር፡ነው፤

ወሐርተሙ፡ተዓይንየ፤

በረድዔት፡የማድርበት፡ከተማዬም፡ ጐሰቈለ፤ይኸስ፡አይደለምና፡ብሎ፡ ነቢዩ፡የምመክረው፡የማስተምረው፡ ከተማዬ፡ጐሰቈለ፡አለ፤ይኸን፡ ባለው፡ወተነሥተ፡ደብተራየ፡ይላል፡ እንደዚሁ፡ያስተረጕማል፤በዚህም፡ ሰዎቹን፡መናገር፡ነው፤

፳፩፤ እስከ፡ማዕዜኑ፡እሬኢ፡ትእምርተ፡ ወእሰምዕ፡ቃለ፡ቀርን፤

ምነው፡ነቢይ፡እንዲህ፡ትለናለህ?አን ዋጋምና፡ነውን፡ትሉኝ፡እንደሆነ፡ እንዲህ፡ከሆነ፤አንድም፡ከተዋጋ ችሁማ፡የአሕዛብ፡ሰንደቅ፡ዓላማ ቸውን፡እስከመቼ፡ድረስ፡ተተክሎ፡ አየዋለሁ፤ውጋ፡ውጋ፡የሚል፡የነጋሪ ታቸውንስ፡ድምፅ፡እስከ፡መቼ፡ ድረስ፡እሰማለሁ፡አለ፤

፳፪፤ እስመ፡ኢያእመሩኒ፡መኳንንተ፡ ሕዝብየ፤

በወገኖቼ፡እስራኤል፡ላይ፡የተሾሙ፡ መኳንንቱ፡በሕግ፡በአምልኮት፡አላወ ቁኝምና፤አንድም፡መኳንንት፡ ሕዝብየ፡ይላል፤ወገኖቼ፡ሹማምንቱ፡ አላወቁኝምና፡አለ፡እግዚአብሔር፤ ሐተታ፡ ወገኖቼ፡አላቸው፡ሹማም ንቱን፡ፍርድ፡ጠንቅቁ፤ድኃ፡ጠብቁ፡ ብሎ፡ ሾሟቸዋልና፤አንድም፡ መኳንንት፡ሕዝብየ፡ያላቸው፡ነቢዩ፡ ኤርምያስ፡ነው፤ትውልዱ፡ከእስ

ራኤል፡ነውና፤አንድም፡እነሱ፡እስራ ኤልን፡ቢሠሩ፡ቢቀጡ፡እሱም፡እስራ ኤልን፡ይመክራል፤ያስተምራልና፡ በሹመት፡ሕዝብየ፡አላቸው፤አንድም፡ እስመ፡ኢያእመሩኒ፡መኳንንት፡ ወሕዝብየ፡ይላል፤ሹማምንቱና፡ ወገኖቼ፡፳ኤል፡አላወቁኝምና፡ ደቂቅ፡አብዳን፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡ ሹማምንቱና፡ወገኖቼ፡እስራኤል፡ በሕግ፡በአምልኮት፡አላወቁኝምና፤

ደቂቅ፡አብዳን፡እሙንቱ፡፡

አላዋቆች፡ልጆች፡ናቸው፤

ወኢያእመሩ፤

ሕጉን፡አምልኮቱን፡አላወቁም፤

ለእከይሰ፡ጠቢባን፡እሙንቱ፡፡

አብዳን፡እሙንቱ፡ብሏቸው፡ነበረና፡ አብዳን፡እሙንቱም፡ማለቴ፡ለበጎ፡ ሥራ፡ነው፡እንጂ፡ለክፉውስ፡ነገር፡ ብልሆች፡አዋቆች፡ናቸው፤ነቅተው፡ ተግተው፡ከዚህ፡ይህ፡ቀረ፡ብለው፡ ይሠሩታል፤

እስመ፡ኢያእመሩ፡ገቢረ፡ሠናይ፤

በጎውን፡ሥራ፡መርምሮ፡መሥራት፡ አይወዱምና፡ለእከይሰ፡ጠቢባን፡ እሙንቱ፡ላለው፤አንድም፡በጎውን፡ ሥራ፡መርምሮ፡መሥራት፡አያው ቁምና፡አብዳን፡እሙንቱ፡ላለው፡ ይሰጧል።

## ጉባዔ፤

፳፫፤ነጸርኩ፡ምድረ፡አልቦ፡ወኢምንትኒ፤

በዚያ፡ወራት፡ልምላሜ፡ለማየት፡ አንገቴን፡ደፍቼ፡ወደምድር፡ተመለ ከትኩ፤ምንም፡ምን፡ልምላሜ፡ የለውም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአንቃዕጹኩ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወኢሀሎ ፡ ብርሃን፡
ሰማዩንም ፡ አቅንቼ ፡ አየሁ ፡ ዝናም ፡ የያዘ፡ደመና፡የለም፤

፳፬፡ ወርኢኩ ፡ አድባረ ፡ ወናሁ ፡ ይርዕዱ፡
ተራሮችንም ፡ አየሁ ፤ በድርቅ ፡ ተይዘው፡ይንቀጠቀጣሉ፤

ወኵሉ፡አውግር፡ያንቀለቅሉ፡
ኮረብታዎችም ፡ ሁሉ ፡ በድርቅ ፡ ተይዘው ፡ ይነዋወጣሉ ፤ ሐተታ ፡ በድርቅ ፡ ዘመን ፡ ተራራውም ፡ ኮረብታውም፡ይናዳልና፤
አንድም ፡ ነጸርኩ ፡ ምድረ ፡ ምድርን ፡ አየሁ፤

ወአልቦ፡ወኢምንትኒ፤
ምንም፡ምን፡ቡቃያ፡ልምላሜ፡የለም፤

ወአንቃዕዶኩ፡ውስተ፡ሰማይ፡
ወደ፡ሰማይ፡አቅንቼ፡አየሁ፤

ወኢሀሎ፡ብርሃን፡
ዝናም፡የያዘ፡ደመና፡የለም፤አንድም፡ ስንኳን፡ዝናም፡የያዘ፡ደመና፡ዝናም፡ ያልያዘ፡ብሩህ፡ደመና፡የለም፤

ወርኢኩ፡አድባረ፡
ተራራውን፡አየሁ፤

ወናሁ፡ይርዕዱ፡
እነሆ፡ይርዳሉ፡ይንቀጠቀጣሉ፤

ወአውግር፡ያንቀለቅሉ፡
ተራራዎችም፡ይነዋወጣሉ፤

፳፭፡ነጸርኩ፡ወአልቦ፡ሰብእ፡
አየሁ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የለም ፤ ወደንገጹ፡አዕዋፈ፡ሰማይ፡ ድርቅ ፡ የማያስተባብረው ፡ የለምና አዕዋፍ ፡ ደነገጡ ፤ አንድም ፡ ኃያላኑ ጠፉ፤

ወነጸርኩ ፡ ወርኢክዎ ፡ ለቀርሜሎስ መዝበረ፡
ምዝቡረ፡ሲል፡ነው፤
ደጋውን፡ተፈትቶ፡አየሁት፤

ወኵሉ፡አህጉር፡ውዕዩ፡በእሳት፡
አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በድርቅ ፡ ተቃጠሉ
አንድም፡ነጸርኩ፡ብለህ፡መልስ፤
ነጸርኩ ፡ ምድረ ፡ ወአልቦ ፡ ወኢምንትኒ፡ወአንቃዕዶኩ፡ውስተ፡ሰማይ ወኢሀሎ፡ብርሃን፡
ልዑላኑ፡ ትሑታኑ ፡ አዝነው ፡ አየሁ
ምንም፡ምን፡ደስ፡ያለው፡የለም፤
ወርኢኩ፡አድባረ፡
ነገሥታቱን፡ካህናቱን፡አየሁ፤
ወናሁ፡ይርዕዱ፡
እነሆ፡ይርዳሉ፡ይንቀጠቀጣሉ፤
ወአውግር፡ያንቀለቅሉ፡
መኳንንቱ፡ካህናቱ፡ይነዋወጣሉ፤
ነጸርኩ፡ወአልቦ፡ሰብእ፤
አየሁ፡ባለአእምሮ፡የለም፤
ወደንገጹ፡ኵሉ፡አዕዋፈ፡ሰማይ፡
ኃያላኑ፡ደነገጡ፤

፳፮፡ ወነጸርኩ፡ወርኢክዎ፡ለቀርሜሎስ፡ መዝበረ፤
ንጉሡን፡አዝኖ፡አየሁት፤

ወኵሉ፡አህጉር፡ውዕዩ፡በእሳት፡
አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በጦር ፡ ጠፉ ፤
እምገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ...
...



እግዚአብሔር ፡ ከገጸ ፡ መዓቱ ፡ ...ተነሣ፡ጠፉ፤

፳፯፡እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ...ድወ፡ትከውን፡ኵላ፡ምድር፡
...ግዚአብሔር፡አገሩ፡ሁሉ፡ምድረ፡ ...ጻ፡ይሆናል፡ብሏልና፤

...ኢይገብር፡ማኅለቅተ፡ለእሉ፡
...እስራኤል፡የመከራ፡ፍጻሜን፡አላደ...ርግም፡ብሏልና፤

፳፰፡በእንተ፡ዝንቱ፡ትላሁ፡ምድር፡
ምድር ፡ ታለቅሳለች ፡ ማለት ፡ የዘሩ ...ትን ፡ አታበቅልም ፤ የተከሉባትን ፡ አታጸድቅም፤

ወይጸልም፡ሰማይ፡በላዕሉ፤
ሰማይ ፡ ይጠቍራል ፡ ማለት ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ አይሰጥም ፤
አንድም፡ልዑላኑ፡ትሑታኑ፡ያዝናሉ፤

እስመ፡ነበብኩ፡ወኢይኔሥሕ፡
መቅሠፍቱን፡አመጣባቸዋለሁ፡ብዬ፡ ተናግሬአለሁና፤ከተናገርኩም፡በኋላ፡ ከመዓት፡ወደምህረት፡አልመለስላቸ ውምና ፡ አውረድክዋ ፡ ማንሻ ፡ ነው ፤
አንድም፡ጦር፡መቅሠፍቱን፡አመጣ ባቸዋለሁ፡ብዬ፡ተናግሬአለሁና፤ከተ ናገርኩም ፡ በኋላ ፡ ከመዓት ፡ ወደም ህረት፡አልመለስላቸውምና፤

አውረድክዋ፡
ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ አስማርኬ ፡ ወደባ ቢሎን፡አወረድኳት፤

ወኢይትመየጥ፡መዓትየ፡እምኔሃ፡
ቍጣዬም፡ከሱዋ፡ወደኋላ፡አይመለስ ሳትም ፤ አንድም ፡ አውረድክዋ ፡ ... ወ...ዋ ፡

ወኢይትመየጥ፡እምኔሃ፤
እኔ፡እሷን፡ከማጥፋት፡አልመለስም፤
አንድም ፡ አውረድክዋ ፡ መቅሠፍ ቲቱን፡ወደሱዋ፡አወረድኩባት፤
ወኢትትመየጥ፡መዓትየ፡ድኅሬሃ፤
ቍጣዬ፡መቅሠፍቴ፡እሷን፡ሳታጠፋ፡ ወደኋላዋ፡አትመለስላትም፤

፳፱፡ እምነ ፡ ውውዓሆሙ ፡ ለሰብዓ ፡ አፍራስ፡
በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ከተቀመጡ ፡ ሰዎች፡እልልታ፡ግርግርታ፡የተነሣ፤

ወለእለ፡ወሰቁ፡አቅስስቲሆሙ፤
አርበኞችም ፡ ቀስታቸውን ፡ ከመቀፈ ራቸው፡ከመሳባቸው፡የተነሣ፤

ወተጉ፡ኵሉ፡በሐውርት፡ወተጸወኑ፡ውስተ፡ በዓታት፤
ያገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰዎች ፡ ሸሽተው ፡ ወደአ ንበሳ፡መደብ፡ሒደው፡ተጠጉ፤

ወተኀብኡ፡ውስተ፡ፆም፡
ቢጨንቃቸው ፡ በታላቁም ፡ ዛፍ ፡ ተሠወሩ፤

ወዐርጉ፡ውስተ፡ጸዋልዕት፡
በገደሉ፡መካከል፡ወዳለ፡ዋሻ፡ወጡ፤

ወዐርቁ፡ኵሉ፡አህጉር፡ወአልቦ፡ዘይነብር፡ ውስቴቶሙ፡ሰብእ፡
በዚህም ፡ ምክንያት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፤ ከከብት ፡ ተለይተው ፡ ባድዋ ቸውን፡ሁነው፡በነሱ፡የሚኖርባቸው፡ ሰው፡የለም፤

፴፡ምንተ፡ትሬስዩ፡አንቲ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስታደርጊ ፡ ኑረሽ ፡ መከራው፡በመጣብሽ፡ጊዜ፡ያንጊዜ፡

www.ethiopianorthodox.org

እመሂ፡ለበስኪ፡ለየ፡
ቀይ፡ግምጃ፡ብትለብሺ፤

ወተሠርገውኪ፡ሠርጐ፡ወርቅ፡
ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ ለብሰሺም ፡ ብታጊጪ፤

ወእመኒ፡ተኰሀልኪ፡ኰሀለ፡አዕይንተኪ፡
አእምሪ፡ከመ፡ከንቶ፡ተሠርገውኪ፡
ዓይንሽንም ፡ ብትኳይ ፡ ብትቀቢ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ በከንቱ ፡ እንዳጌጥሽ ፡ ዕወቂ፤

ወከንቱ፡ላህይኪ፡
መልክሽም ፡ ውበትሺም ፡ በከንቱ ፡ ነው፤

ጸልዑኪ፡መሐዛንኪ፡
ስንኳንስ፡እኔ፡ውሽሞችሽ፡ጣዖታቱ፤ አንድም ፡ ካህናቱ ፡ ጠሉሽ ፤ ሐተታ፡– ውሽሞችሽ ፡ አላቸው ፤ ጣዖታቱን ፡ ውሽማ ፡ ሠርቆ ፡ እንዲወደድ ፡ እነሱም፡ በሥርቆት ፡ ይመለካሉ ፡ ይወደዳሉና፤

ወየኃሥሥዋ፡ለነፍስኪ፡
ሰውነትሽንም፡ለጥፋት፡ፈለጓት፤

እስመ፡ቃሉ፡ለዘይጽዕለኪ፡
ተሰምየ፡ያለበት፡ነው፤
የሚመክርሽ ፡ የሚያስተምርሽ ፡ የነቢዩ ፡ የካህኑ ፡ ቃል ፡ ባንቺ ፡ ተሰምቷልና ፤ (አላደረግምና) ፤ አንድም ፡ ማርኮ፡ ወስዶ፤ገዶ፡ገብሮ፡እያለ፡የሚሰድብሽ፡የናቡከደነፆር፡ቃል፡ቃሉ፡ባንቺ፡ተሰምቷልና፤(ታገዢብሻልና)

ወሰማዕኩ፡ገዓረኪ፡ከመ፡እንተ፡ትወልድ፡
በኰራ፡
የምትወልድ፡ሴት፡ስትጮኽ፡እን ተሰማ ፡ ጩኸትሽን ፡ ሰማሁ ፤ ቃመ

ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ደክመ ፡ ማንሻ አንድም፡ የምትወልድ ፡ ሴት ፡ ጮኻ ጮኻ፡እንድትደክም፤

ቃለ፡ወለተ፡ጽዮን፡ደክመ፡
የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ተማርካ ፡ ስትሄድ ቃሏ፡በጩኸት፡ደከመ፤(ሰለለ)፤

ወትሰፍሕ፡ዕደዊሃ፡
በዜዋዌም፡ጊዜ፡ባጭር፡ታጥቃ፡ዘገ ነጥቃ ፡ ሳትዋጋ ፡ እጇን ፡ ዘርግታ ተማረከች፤አንድም፡እጇን፡እያርገ ገበች፡ተማርካ፡ትሄዳለች፤

አሌ፡ሊተ፡እስመ፡ሐልቀት፡ነፍስየ፡በእንተ
እለ፡ተቀትሉ፡
በግፍዕ ፡ ስለሞቱት ፡ ዘመዶቼ ሰውነቴ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ብላለችና ወዮልኝ፤አንድም፡በግፍዕ፡በሞቱት ዘመዶቼ ፡ ነፍሴ ፡ ከሥጋዬ ፡ እለይ እለይ፡ብላለችና፡ወዮልኝ።

## ምዕራፍ፡፭

፩፥ሩጹ፡ውስተ፡ፍናዊሃ፡ለኢየሩሳሌም፡
ይህ፡ሁሉ፡መከራ፡እንጅ፡የተደረገ ፍርድ፡ባይጠነቀቅ፤አንድም፡ሕጉ ባይጠበቅ ፡ ነውና ፡ በኢየሩሳሌም ወዳለው ፡ ጎዳና ፤ አንድም ፡ ወደመ ንደሯ፡እስኪ፡ፈጥናችሁ፡ሂዱ።

ወርእዩ ፡ ወአእምሩ ፡ ወኅሥሡ ፡ ውስተ
መርኅባ፡
ሂዳችሁም ፡ በአደባባይዋ ፡ የሚፈረ ደውን ፡ ፍርድ ፤ አንድም ፡ በአደባ ባዩዋ፡ የሚጠበቀውን ፡ ሕግ ፡ መርም ራችሁ፡እወቁ፤



ቃመ ፡ ዘይገብር ፡ ፍትሐ ፡ ወየኃሥሥ ፡
ማንሻ.ድቀ፡
ውነት፡ፍርድ፡የሚፈርድ፡እውነት፡
ገር ፡ የሚናገር ፡ ባደባባይዋ ፡ አለ ፡
ንደሆነ፡መርምራችሁ፡ዕወቁ፤

፪፥ ወእመሂ ሎሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
መ፡ይቤሉ፡ሕያው፡እግዚአብሔር፡ዳዕሙ፡
ሐሰት፡ይምሕሉ፡
ሐሰት ፡ ነገር ፡ ይምላሉ ፡ እንጂ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብለው ፡ ይምሉ፤ አንድም፡ በሐሰት፡ በጣዖቱ፡ ም፡ይምላሉ፡እንጅ፡በሕያው፡እግዚ አብሔር፡ስምስ፡ቢምሉ፡ይቅር፡እላቸ ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፫፥ እግዚኦ ፡ አዕይንቲከሰ ፡ አኮኑ ፡ ለሃይ
ማኖት፡
አቤቱ ፡ ዓይኖችህ ፡ ግን ፡ ሃይማኖት ፡ ያየዘ ፡ ሰውን ፡ የሚመለከቱ ፡ አይደሉም? ቀሠፍኮሙ ፡ ማንሻ ፤ አንድም፡ዓይኖችህ፡ነቢያት፡ካህናት፡ ለሃይማኖት፡አጋዥ፡ጠበቃ፡ናቸውና፤

ቀሠፍኮሙ፡
ቢመክሯቸው፡ቢያስተምሯቸው፡አን ቀበላቸው፡ያሉ፡እስራኤልን፡አጠፋ ኻቸው፤

ወኢሐሙ፡
እስራኤል፡በዚህ፡ንስሐ፡አልገቡም፤ አንድም አቤቱ ምክሩ ፡ አስተምሩ ያልካቸው ፡ ነቢያት ፡ ለሃይማኖት ፡ ዋስ፡ ጠበቃ ፡ ናቸውና ፡ እስራኤልን ፡ ሊመክሩ ፡ ሊያስተምሩ ፡ በሔዱበት ፡ አገር፡ነቢያትን፡በሃይማኖት መከራ፡ እንዲቀበሉ፡አደረግሃቸው፤ወኢሐሙ፤

ነቢያትም ፡ በዚህ መከራ ፡ በመቀበ ላቸው ፡ አላዘኑበትም ፤ ወደው ፡ ተቀበሉት፡እንጂ፤

አኅለቆሙሂ፡
ነቢያት ፡ ቢመክሯቸው ፡ ቢያስተም ሯቸው ፡ ትምህርታቸውን ምክራ ቸውን ፡ አንቀበልም ፡ ያሉ ፡ እስራ ኤልን ፡ ከአሕዛብ ፡ ለይተህ ፡ አጠፋ ሀቸው፤

ወአበዩ፡ተምህሮ፡
ከዚህ፡አስቀድሞ፡ግን፡ነቢያት፡ቢመ ክሯቸው ፡ ቢያስተምሯቸው ፡ አንመ ለስም ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ እምቢ ፡ አንማርም፡አሉ፤

ወአጽንዑ፡ገጾሙ፡እምኰኵሕ፡ወኢፈቀዱ፡
ይትመየጡ፤
ገጸ፡ልቡናቸውንም፡ከአለት፡ደንጊያ፡ ይልቅ ፡ አጽንተው ፡ በሕግ ፡ በአም ልኮት ፡ በንስሓ ፡ ወደፈጣሪያቸው ፡ ወደእግዚአብሔር፡ሊመለሱ፡አልወ ደዱም፤

፬፥ ወአነሂ፡እቤ፡አኮኑ፡ነዳያን፡እሙንቱ፡
እስመ ፡ ስዕኑ ፡ አእምሮ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአ ብሔር፡ወፍትሐ፡አምላኮሙ፡አሐውር፡ኀበ፡
ዐቢያን፡
ዘጠኙ ፡ ቃላትንና ፡ የፈጣሪያቸው ፡ እውነተኛ ፡ ሕጉ ፡ ኢታምልክን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ስለተሳናቸው ፡ ነዳያነ ፡ አእምሮ ፡ ናቸውና ፡ ወደባለ ጸጎች፡እሄዳለሁ፡አልሁ፤

ወእነግሮሙ፡
ለባለጸጎች፡ዘጠኙ፡ቃላትንና፡ኢታም ልክን፡እነግራቸዋለሁ፡አልሁ፤

፭፥ ወባሕቱ፡እሙንቱ፡ቀጥቀጡ፡ኀቡረ፡
አርዑተ፡ወበተኩ፡ማዕሠረ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ፡ ግን ፡ እኒህ ፡ ባለጸጎች ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ አርዑተ ፡ ዘጠኙ ፡ ቃላትን ፡ ማዕሠረ ፡ ኢታምልክን ፡ አፈረሱ ፤ እንድም ፡ እስመ ፡ ስዕኑ ፡ አእምሮ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላቸዋልና ፡ ድኆችንም ፡ ብሎ ፡ ነዳያን ፡ ነዳያኑ ፡ አእምሮ ፡ ናቸው ፡ ያልኋቸው ፡ ድኆች ፡ ብዑላን ፡ ብዑላኑ ፡ አእምሮ ፡ ናቸው ፡ ያልኋቸው ፡ ባለጸጎችም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ዘጠኙ ፡ ቃላትንና ፡ ኢታምልክን አፈረሱ ፤ አንድም ፡ አርዑተ ፡ ሕገ፡ ኦሪትን ፤ ማዕሠረ ፤ ዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ በተኩ ፡ ኀቡረ ፡ አንድ ፡ አድርገው፡አፈረሱ፤

፮፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽአሙ ፡ አንበሳ፡እምውስተ፡ዖም፤

ባለጸጎችም ፡ ድኆችም ፡ አንድ ፡ ሁነው፡ ሕግጋቱን ፡ ስላፈረሱ ፤ አንድም ፡ ሕግጋቱን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ስላፈረሱ ፤ ናቡከደነፆር ፡ ከባቢሎን ፡ ክተት ፡ ሠራዊት ፤ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብሎ ፡ መጣባቸው ፤ ሐተታ ፡ አንበሳ ፡ አለው ፤ ናቡከደነፆርን ፡ አንበሳ ፡ ገድሎ ፡ ደሙን ፡ ጠጥቶ ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ከሄደ በኋላ ፡ ዳግመኛ፡ አይመለስም ፤ ናቡከደነ ፆርም ፡ አንድ፡ ጊዜ ፡ ከማረካቸው ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ መጥቶ ፡ አልማረካቸ ውምና፤

ወተኵላ፡እምገዳም፡ይሚርዎሙ፤

ንጉሠ ፡ ሜዶን ፤ አንድም ፡ ተኵላ ፡ ያልታወቀ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ከሀገሩ ፡ ከሕንደኬ፡ ክተት፡ሠራዊት፡ምታ፡ነጋሪት፡ብሎ፡ መጥቶ፡ያጠፋቸዋል፤

ወነምርኒ፡ተግሀ፡ላዕለ፡አህጉሪሆሙ፤

ስልምናሶርም ፡ አገራቸውን ፡ ለማ[illegible] ፋት፡ተጋ፤ሐተታ፡ነምር፡አለው፤ስል ምናሶርን ፤ ነምር ፡ ገድሎ ፡ አውሎ አሳድሮ ፡ አትልቶ ፡ ይበላል ፡ እነ[illegible] ህንም ፡ ቀድሞ፡ (አያቱ)፡ ፎሐ ፡ እስ[illegible] ኤልን ፡ ሽህ ፡ መክሊት ፡ አስገብ[illegible] ቸዋል ፤ ኋላም ፡ ቴልጌል ፡ መጥቶ ሰባት፡አህጉር፡ወግቶባቸዋል፤ኋላም ስልምናሶር፡መጥቶ፡ዓሥሩን፡ነገድ ማርኳቸዋልና፤

ኵሉ ፡ ዘወጽአ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይትመሰጥ፤

በዚያ ፡ ወራት ፡ ከእስራኤል ፡ ተለይቶ ከከተማ ፡ የወጣ ፡ ሰው ፡ በሞት ፡ ይነጠቃል፤

እስመ፡በዝኃ፡ጌጋዮሙ፤

ክፋታቸው፡በዝቷልና፤

ወጸንዐ፡በጣዖቶሙ፤

በጣዖታቸውም፡ጸንተው፡ኑረዋልና፤

፯፤ በአይ ፡ እምእላንቱ ፡ እሠሃሎሙ ፡ ለደቂቅኪ ፡ እለ ፡ ኀደጉኒ ፡ ወይምሕሉ ፡ በእለ፡ ኢኮኑ፡አማልክተ፤

እኔን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ የተዉኝ፡ አማልክት ፡ ባይደሉ ፡ በጣዖታቱ ፡ የሚ ምሉ ፡ ልጆችሽን ፡ በማናቸው ፡ በጎ ፡ ሥራቸው፡ይቅር፡ልበላቸው?

ወአጽገብክዎሙ፤

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ መናውን ፡ አጠገብ ኋቸው ፤ አንድም ፡ ተድላውን ፡ ደስታውን፡አጠገብኋቸው፤

ወዘመዉ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሰዕኑ፤ እንዲሁም ፡ [illegible] በሬ፡ተለዩ፤



ወኃደሩ፡ቤተ፡ዘማት፡

ይልማ ፡ ይስማም ፡ ብለው ፡ በዘማት ፡ ቤት ፡ አደሩ ፤ አንድም ፡ በቤተ ፡ ጣዖት ፡ አደሩ፤

፰፤ አፍራስ፡ዘማውያን፡ኮኑ፡

አለሌ ፡ ፈረስ ፡ ሆኑ ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ አፍራስ ፡ ዘማውያን ፡ ኮኑ ፤ እንዳለሌ ፡ ፈረስ፡ሆኑ፤አንድም፡አፍራስ፡ዘኢ.ተ ረየጹ፡ኮኑ፡ያልተገሩ፡ፈረሶችን፡ሆኑ፡ አንድም፡ከመ፡አፍራስ፡ዘኢተረየፁ፡ ኮኑ፤እንዳልተገሩ፡ፈረሶች፡ሆኑ፤

አሐዱ፡አሐዱ፡ያረኵስ፡ብእሲተ፡ቢጹ፤

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ኢትሐር ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ ያለውን ፡ አፍርሶ ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ የባልንጀራውን ፡ ሚስት ፡ ያረክሳል ፤ አንድም፡ የባልንጀ ራውን፡ሕግ፡ያስነቅፋል፤

፱፤ በዝሂ ፡ ኢይኴንንሁ ፡ ይቤ ፤ እግዚአ ብሔር፤

በዚህ ፡ ነገር ፡ አልፈርድባቸሁምን ፤ አንድም ፡ ኢይኴንንሁ ፡ በዚህ ፡ አልፈ ርድምን፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወበዝሂ፡ኢትትቤቀልሁ፡ነፍስየ፡

በዚህ ፡ ልቡናዬ ፤ አንድም ፡ ሕይወቴ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አትበቀላቸውም ፡ አትበቀላቸው፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፤ ዕርጉ ፡ ውስተ ፡ አሕቃላቲሃ ፡ ወአ ማስኑ፤

አሕዛብ ፡ ይኸንስ ፡ ትታችሁ ፡ ወደ ፡ አውራጃዋ፡ዘምታችሁ፡አውራጃዋን፡ ሁሉ ፡ አጥፉ ፤ አንድም ፡ ዕርጉ ፡ ወአማስኑ፡አሕቃላቲሃ፡ይላል፤ አሕዛብ ፡ ዘምታችሁ ፡ አውራጃዋን ፡ [illegible]

የመከራውንም ፡ ፍጻሜ ፡ አታድር ጉላት፡

ወአሰስሉ፡ትራፋቲሃ፤

ክፉ፡ክፉዎቹን፡ለይታችሁ፡አጥፉ፤

እስመ፡ኢኮኑ፡ዘእግዚአብሔር፡እሙንቱ፡

የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ (ገንዘቦች) አይደሉምና ፤ አንድም ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ወገኖች ፡ አይደሉምና ፡ ክፉ ፡ ክፉዎቹን፡ለይታችሁ፡አጥፉ፤

ወአትርፉ፡ምስማካቲሃ፤

በጎ፡በጎዎቹን፡ግን፡ለይታችሁ፡አስቀ ሩዋቸው፤

እስመ፡ዘእግዚአብሔር፡እሙንቱ፤

የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ ናቸውና ፤ አንድም፡ስለሆኑ፤አንድም፡የእግዚአ ብሔር ፡ ወገኖች ፡ ናቸውና ፡ በጎዎች ፡ በጎዎቹን ፡ ለይታችሁ ፡ ተዉአቸው ፤ ሐተታ ፡ አሁን ፡ እነሱ ፡ ክፉዎቹን ፡ ለይተው ፡ የሚያጠፉ ፤ በጎዎቹን ፡ ለይ ተው ፡ የሚተዉ ፡ ሆነው ፡ አይደለም ፤ ክፉዎቹም ፡ በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ የሚ ጠፉ ፤ በጎዎቹም ፡ በበጎ ፡ ሥራቸው ፡ የሚድኑ፡ስለሆነ፡እንዲህ፡አለ፡እንጂ፤

፲፩፤ እስመ ፡ ዓሊወ ፡ ዓለዉኒ ፡ ቤተ እስራኤል፡ወቤተ፡ይሁዳ፤

ዓሥሩ፡ነገድና፡ሁለቱ፡ነገድ፡አንድ፡ ሁነው፡ወንጅለውኛልና፤

ወከህዱኒ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

ወንጅለውኝም ፡ አልቀሩ ፡ ክደው ኛልና ፤ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የማደ ርግባቸው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አለ ፡ እግ ዚአብሔር፤

፲፪፤ ወሐሠዉ ፡ ቤተ ፡ ይሁዳ ፡ በእግዚአ ብሔር፡

www.ethiopianorthodox.org

ሐሰት፡ ተናገሩበት ፡ አንድም ፡ ወሐ
ሰውዎ፡ለእግዚአብሔር፡ቤተ፡ይሁዳ፡
ይላል ፤ ሕዝብየ ፡ የሚላቸው ፡ ሁለቱ ፡
ነገድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሐሰተኛ፡
ነው፡አሉት፤

ወይቤሉ፡ኢኮነ፡ከመዝ፡
ሐሰውዎ ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤ ኃጢ
አት ፡ አትሥሩ ፤ ጣዖት ፡ አታምልኩ ፤
እኔን ፡ አትበድሉ ፤ ትጠፋላችሁ ፡ ቢላ
ቸው ፡ አሁን ፡ እንደተናገርከው ፡ አይ
ደረግብንም ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ እኔን ፡
አትበድሉ ፤ ከኃጢአታችሁ ፡ ተመ
ለሱ ፡ ቢላቸው ፡ አሁን ፡ እንደተናገ
ርከው፡ከኃጢአታችን፡አንመለስም፡
አሉ፤

ወኢይረክበነ፡እኩይ፡
ክፉውም ፡ ነገር ፡ ያገኛችኋል ፡ ቢላ
ቸው፡ክፉ፡ነገር፡አያገኘንም፡አሉ፤

ወኢይመጽአነ፡መጥባሕት፡ወረኃብ፡
ተወ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍት ፡ ይመጣባች
ኋል ፤ ቀጠናውም ፡ ያገኛችኋል ፡ ቢላ
ቸው ፡ ጦሩ ፡ መቅሠፍቱም ፡ አይመ
ጣብንም ፤ ቀጠናውም ፡ አያገኘንም ፡
አሉት፡

፲፫፡ ነቢያቲክሙኒ፡ነፋሳት፡እሙንቱ፤
ሰላም ፡ ሰላም ፡ እያሉ ፡ የሚያስተም
ሯችሁ፡ነቢያቶቻችሁ፡ነቢያተ፡ሐሰ
ትም ፡ ነፋሳት ፡ ናቸው ፡ አለ ፤
ሐሰተኞች፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ሐተታ፡እገሌ፡ነፋስ፡ነው፡እንዲባል፤
ሐሰተኛ፡ነው፡ሲሉት፤

ወአልቦሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
ላዕሌሆሙ፡

በተናገሩት ፡ ትንቢታቸውም ፡ ፍሬ ፡
ቃል፡አይገኝባቸውም፤

ወከመዝ፡ይከውን፡በበይነዝ፤
እግዚአብሔር ፡ መቅሠፍቱን ፡ አብ
ዝቶ ፡ ስላመጣባቸው ፡ መከራው ፡
እንዲህ፡ይደረግባቸዋል፤አንድም፡
ወከመዝ ፡ ይከውኑ ፡ በበይነዝ ፤ እነሱ ፡
አብዝተው ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ስለበ
ደሉት፡እንደዚህ፡ነው፡ይጠፋሉ፤

፲፬፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘኵሎ፡ይመልክ፡
ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤

እስመ፡ይቤሉ፡
ኃጢአት ፡ ብንሠራ ፡ ጣዖት ፡
ብናመልክ፡ እግዚአብሔር ፡ አያውቅ
ብንም ፤ አይፈርድብንም ፡ ብለው ፡
ስላሉ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ ወደይኩ ፡ ቃልየ ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡
እሳተ፡
ቃሌን ፡ እሳት ፡ አድርጌ ፡ ወደአፍህ ፡
ጨመርኩት ፡ አለ ፤ ትንቢቱን ፡ ነው ፤
ሐተታ ፡ የተናገርከውን ፡ ትንቢት ፡
አጥፊ፡አደረግሁት፡ሲል፡ነው፤

ወዝ፡ሕዝብ፡ዕፀው፡
ትምህርትህንም ፡ ያልተቀበሉ ፡
እነዚህ፡ ወገኖች፡እንጨቶች፡ናቸው፡
አለ፤ጠፊዎች፡ናቸው፤

ወትበልዖሙ፤
የተናገርካትም፡ትንቢት፡እሳት፡ሁና፡
ሕዝቡን ፡ ታጠፋቸዋለች ፤ ሐተታ ፡
[illegible]



፲፭፡ ናሁ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ ላዕሌክሙ ፡
ሕዝበ ፡ ዘእምርኁቅ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ይቤ፡
እግዚአብሔር፡
የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ እኔስ ፡ በኃጢአ
ታችሁ ፡ በክፋታችሁ፡ ከፋርስ ፡
ከባቢሎን ፡ ከጽርዕ ፡ ከሜዶን ፡
አሕዛብን ፡ ጠርቼ ፡ ፈጥኜ ፡ አመጣባች
ኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወሕዝብ፡እኩይ፡ውእቱ፤
ይህም ፡ ከሩቅ ፡ የሚመጣ ፡ ወገን ፡ ክፉ፡
ወገን፡ነው፤

ሕዝብ፡ዘኢተአምር፡ልሳኖ፡
እኩይ ፡ ያለውን ፡ ይተረትራል ፤ ይኸ
ውም፡ ቋንቋውን ፡ የማታውቅለት፡
ነገሩን ፡ የማትሰማው ፡ ክፉ ፡ ወገን ፡
ነው፤

ወኢትሰምዕ፡ቃሎ፡
ቋንቋውንም ፡ የማትሰማው ፡ ክፉ ፡
ወገን፡ነው፡አለ፤ውሪ፡ውሪ፡ሲል፤

፲፮፡ ወከናፍሪሁ ፡ ከመ ፡ መቃብር ፡
ክሡት፡
ክሡት ፤ ከናፍሪሁ ፡ ከመ ፡ መቃብር ፡
ሲል ፡ ነው ፤ የተከፈተ ፡ አንደበቱም ፡
እንደ፡ መቃብር ፡ ነው ፡ አለ ፤ ሞት ፡
ቢገድል ፡ ቢገድል ፤ መቃብር ፡
ቢቀበል፡ ቢቀበል ፡ በቃኝ ፡ አይልም ፤
እነሱም ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡
በቃን ፡ አይሉምና ፤ አንድም ፡ እንዳለ ፡
ይሆናል ፤ አንደበቱ ፡ እንደተከፈተ ፡
መቃብር ፡ ነው ፡ አለ ፤ ይህ ፡ የተከፈተ ፡
መቃብር ፡ ሲያዩት ፡ መቃብሩ ፡
ተከፍቶ፡ መግነዙ፡ ተፈትቶ፡ ጅማቱ ፡
ተፈትቶ ፤ እዝኑ ፡ ፈስሶ ፡ አጥንቱ፡ ተል
ከስክሶ ፡ ለዓይን ፡ የሚከፋ፡ ለአፍንጫ፡
[illegible] እነሱም ፡

የሚያጸይፍ ፡ የሚያጸይፍ ፡ ነገር ፡ ይናገ
ራሉና፤

፲፯፡ ወኵሎሙ ፡ ጽኑዓን ፡ ይበልዑ፡
ማዕረረከ፡ወእክለከ፡
የአሕዛብ ፡ አርበኞችም ፡ ሁሉ ፡
ማዕረረከ ፡ አዲሱን ፡ ወእክለከ ፡
ድልቡን ፡ ይበሉብሃል ፤ አንድም ፡
ማዕረረከ ፡ በዱር ፡ ያለውን ፡ ወእክለከ ፡
ወደቤት ፡ የገባውን ፡ ይበሉብሃል፤

ወይበልዕዎሙ፡ለውሉድከ፡ወለአዋልዲከ፡
ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ልጆችህ ፡ ያጠራቀ
ሙትን ፡ ገንዘባቸውንም ፡ ይበሉባ
ቸዋል ፤ ኤፍሬም ፡ ይበልዖ ፡ ለምናሴ ፡
እንዲል ፤ ኢሳ ፱ ፡ ፳፤

ወይበልዑ፡ዓባግዒከ፡ወአልሕምቲከ፤
ገዝተህ፡አዋልደህ፡ያረባሃቸው፡በጎች
ህንና፡ላሞችህንም፡ይበሉብሃል፤

ወይበልዑ፡ወይነከ፡ወበለሰከኒ፡ወዘይተከኒ፡
ተክለህ ፡ ውሀ ፡ አጠጥተህ ፡ አርመህ ፡
ኮትኩተህ ፡ ያሳደግኸው ፡ ወይንህንና ፡
በለስህን ፡ ዘይትህንም ፡ ይበሉብሃል፤

ወይከይድዎን ፡ ለአህጉሪከ ፡ ጽኑዓት ፡
በኵናት፡እለ፡ቦቱ፡ትትአመኑ፤
እለ፡ቦሙ፡ትትአመኑ፡ሲል፡ነው፤
በጦራችን አንደበት ፡ በጋሻችን ፡
እንብርት ፡ በአምባዎቻችን ፡ ጽናት ፡
እንዋጋባቸዋለን ፡ ብላችሁ ፡ የምትታ
መኑባቸውን ፡ አገሮቻችሁንም ፡ ገብ
ተው፡ይረጋግጧቸዋል፤

፲፰፡ ወይከውን ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኢይሬስየክሙ ፡
ማኅለቅተ፡
ያንጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፤ ፈጣሪህ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የመከ

www.ethiopianorthodox.org

ራውን ፡ ፍጻሜ ፡ አላደርግላችሁም ፡
አለ፤ይከውን፡ያለውን፡አመጣ፤

፲፱፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ይብሉ ፡ በእንተ ፡
ምንት ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡
ዘንተ፡ኵሎ፡ላዕሌነ፡
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከመከራው ፡ ጽናት ፡
የተነሣ ፡ የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡
ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ፈጣሪያችን ፡
እግዚአብሐር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡
በኛ ፡ ያመጣብን ፡ ስለምንድነው ?
ቢሉህ፤

ወትብሎሙ ፡ እስመ ፡ ኅደግሙኒ ፡ ወተቀነ
ይክሙ ፡ ለአማልክተ ፡ ነኪር ፡ በብሔርክሙ ፡
ከማሁ ፡ ትትቀነዩ ፡ ለዐር ፡ በብሔረ ፡ ባዕድ ፡
ዘኢኮነ፡ለክሙ፤
አንተም ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፤ በሕግ ፡
በአምልኮት ፡ ትታችሁኛልና ፡ ለአማ
ልክት ፡ ነኪራን ፡ ለአማልክተ ፡ ነኪር፡
ይላል ፤ ባገራችሁ ፡ ሳላችሁ ፤ አንድም፡
ባገራችሁ ፡ ለቆሙ ፡ ጣዖታት ፡ ተገዝታ
ችኋልና ፡ አሁን ፡ እንደተናገርኩት ፡
ለናንተ ፡ ባይደለ ፡ በጠላቶቻችሁ ፡
አገር ፡ ለጠላቶቻችሁም ፡ ትገዛላችሁ ፡
በላቸው፤

፳፡ ዜንውዎሙ ፡ ዘንተ፡ ለቤተ፡
ያዕቆብ፡
ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡
ለያዕቆብ ፡ ወገኖች ፡ ለዓሥሩ ፡ ነገድ ፡
ንገሩዋቸው፤

ወይስምዕዎ፡ቤተ፡ይሁዳ፡
ይህንንም ፡ ነገር ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ይስሙት፡አለ፤

፳፩፡ ስምዑ ፡ ዘንተ ፡ ሕዝብ ፡ ዘአልቦ ፡
አእምሮ ፡ የሌላቸሁ ፡ ወገኖች ፡ ዓሥሩ ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ከነቢያት ፡ ከካህናት ፡
ይህነን፡ነገር፡ስሙ፤

አዕይንት፡በሙ፡ወኢይሬእዩ፡
ዓይንስ ፡ አላቸው ፤ አንድም ፡ ዓይንስ፡
ነበራቸው፤አንድም፡ዓይን፡ሳላቸው፡
አያዩም፡የምትባሉ፤

ዕዝን፡በሙ፡ወኢይሰምዑ፤
ጆሮ ፡ እያላቸው ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡
አይሰሙም ፡ የምትባሉ ፡ እናንተ ፡
ይህንን፡ነገር፡ስሙ፤

፳፪፡ ቦኑ፡ኪያየ፡ኢትፈርሁ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡
መፈራትስ ፡ እንዳይፈራ ፡ የለም ፤
ፈጥሬ፡የምገዛችሁ፡እኔን፡በውኑ፡አት
ፈሩኝምን፡አታመልኩኝምን፤

አው፡እምቅድመ፡ገጽየ፡ኢትደንግፁኑ፡
ከኔ ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ የተነሣ ፡ አትደነግ
ጡምን፤

ሠራዕኩ ፡ ኆፃ ፡ ወሰነ ፡ ለባሕር ፡ ሥርዓተ ፡
ዘለዓለም፡
ለውቅያኖስ ፡ ስንኳ ፡ በወዲያ ፡ አድማ
ስን ፡ በወዲህ ፡ ናጌብን ፡ ለዘላለም ፡ ሥር
ዓት ፡ አድርጌ ፡ ድንበር ፡ ወሰን ፡ ሠራሁ
ላት፤አንድም፡እስከ፡ዝየ፡ብጽሒ፡ወኢ
ትትአደዊ፡እምወሰንኪ፡ብዬ፡ቃሌን፡
ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ የሚሆን ፡ ወሰን ፡
ድምበር፡አድርጌ፡ሠራሁላት፤

ወኢይትዓደው፡ወኢይትነኀናኅ፡
ከወሰኑ፡ከድምበሩ፡እልፍ፡አይልም፤
አንድም ፡ ወይትነኀናኅ ፡ ይላል ፤
በወሰኑ፡ይወጣል፡ይወርዳል፡



ለወገኖቼ ፡ ፳ኤል ፡ ግን ፡ እነሱ ፡
ከማዕበሉ ፡ ከሞገዱ ፡ ብሰው ፡ አንሰው ፡
እኔን ፡ ከናጌብ ፡ ከአድማስ ፡ ስንኳ ፡
አሳንሰው ፡ ለእሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው፤
የማያውቅ ፡ የማይሰማ ፡ ልቡና ፡
ተሰጣቸው፤

ወክህዱኒ፡
በዚህም ፡ በተሰጣቸው ፡ ልቡና ፡ እኔን፡
ካዱኝ፤

ወተመይጡ፡ወሖሩ፤
ከኔም ፡ ተመልሰው ፡ ወደቤተ ፡ ጣዖቱ ፡
ተጨልጠው ፡ ተገርኝተው ፡ ሔዱ፤ አን
ድም ፡ ወኢተመይጡ ፡ ወሖሩ ፡ ይላል፤
ወደቤተ ፡ ጣዖቱ ፡ ተጨልጠው ፡ ተገር
ኝተው ፡ ሔዱ ፡ እንጂ ፤ በሕግ ፡ በአም
ልኮት፡ወደኔ፡አልተመለሱም፤

፳፬፡ ወኢይብሉ ፡ በልቦሙ ፡ ንፈርሆ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ዘይሁበነ ፡ ዝናመ ፡
ተወን፡ወመፀው፤
ይህነንም ፡ ሁሉ ፡ ሲያደርጉ ፡ በልቡ
ናቸው ፡ አስበው ፡ የበልጉንና ፡ የመከ
ሩን ፡ ዝናም ፡ የሚሰጠን ፡ ፈጣሪያችን ፡
እግዚአብሔርን፡እንፈራዋለን፤እናመ
ልከዋለን፡አላሉም፤

ወይፌጽም፡ለነ፡በበዕድሜሁ፡
የመከሩን የበልጉን ፡ ዝናም ፡
በየጊዜው፡ በየሰዓቱ ፡ ጀምሮ ፡ የሚጨ
ርስልን፤

ወማዕረረ፡ዘበሕጉ፡ዐቀበ፡ለነ፡
በሕጉ ፡ በሥርዓቱ ፡ የሚያደርግልን ፡
መከሩንም ፡ ያጸናልን ፡ እግዚአብ
ሔርን፡ እናመልከዋለን ፤ እንፈራ

ታቸው ፡ ከታኅሣሥ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
መጋቢት፡ ነውና ፤ የኛ ፡ ክረምታችን ፡
ከሰኔ ፡ ፳፭ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡
፳፭ ፡ ነውና፤

፳፭፡ ኃጢአትክሙ፡ከልዓ፡እሎንተ፤
ምነዋ፡ዛሬስ፡አያደርግልንም፡ትሉኝ፡
እንደሆነ፡ዛሬስ፡ፈጣሪያችሁን፡የበደ
ላችሁበት ፡ ኃጢአታችሁ ፡ እነዚህን፡
ሁሉ፡ከለከለባችሁ፤ሐተታ፡እሎንተ፡
ያላቸው ፡ ተወን ፤ መፀው ፤ ማዕረር ፡
ናቸው፤

ወጌጋይክሙ፡አርሐቀ፡ሠናያተ፡እምኔክሙ፤
ፈጣሪያችሁንም ፡ የበደላችሁበት ፡
በደል ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ከናንተ ፡
አራቀባችሁ፤

፳፮፡ እስመ ፡ ተረክቡ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ ፡
ዓማዕያን፡
በናንተ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡
በደለኞች፡ተገኝተዋልና፤

ወሠርዑ ፡ መሣግረ ፡ ይቅትሉ ፡ ሰብአ ፡
ወየአኀዙ፡
ሰውን ፡ በሞት ፡ ሊያጠፉት ፡ በፍዳ ፡
ሊያሲዙት ፡ ወጥመዳቸውን ፡ ዘረጉ ፡
አለ ፤ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡
እያሉ፡አስተማሩ፤

፳፯፡ ከመ ፡ ዔረግ ፡ ዘምሉዕ ፡ አዕዋፈ ፡
ከማሁ፡
እናንተስ፡በጸብታ፡በፃግታ፡ተይዘው፡
እንደመሉ፡አዕዋፍ፡ናችሁ፤ሐተታ፡
በሀገራቸው ፡ መት ፡ ጠባቂ ፡ ጸብታ ፡
ፃግታ ፡ የሚባል ፡ አለ ፤ ያነን ፡ ፈልጎ ፡
አምጥቶ፡ወይኑን፡ይቀባዋል፤አዕዋፍ፡
መጥተው፡በዚያ፡ላይ፡ይሰፍራሉ፤እግ
ራቸውን ፡ ጨምዶ ፡ ይይዛቸዋል፤
የንጉዚ ፡ በጭራሮ ፡ በጭራንፎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ደብድበው ፡ ይገድሏቸዋል ፤ ይኸ
ውም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ አዕዋፍ ፡ የእስ
ራኤል ፡ወይኑ ፡ የኢየሩሳሌም ፡
የሰማርያ፤ ጸብታ ፡ ፃግታ ፡ የኃጢአ
ታቸው ፡ የፍዳ ፡ ጭራሮ ፡ ጭራንፎ ፡ የስ
ልምናሶር ፡ የናቡከደነፆር ፤ ጸብታ ፡
ፃግታው ፡ ይዟቸው ፡ አዕዋፍ ፡ እንዳለቁ፡
እስራኤልም ፡ በኃጢአታቸው ፡ በፍዳ ፡
ተይዘው ፡ ስልምናሶር ፡ ናቡከደነፆር ፡
የማጥፋታቸው፡ምሳሌ፡ነው፤

ኦብያቲሆሙኒ፡ምሉዕ፡ጉህሉት፤
ልቡናሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ልቡና
ቸውም፡ ክዳት ፡ ተንኮልን ፡ የተመላ ፡
ነው፤

በበይነዝ፡ዐበዩ፡ወብዕሉ፡ወገዘፉ፤
ስለዚህ፡ነገር፡ፈጽመው፡ከበሩ፤ገነኑ፤
በድንቁርናውም፡ተያዙ፤

፳፰፤ ወተዐደዉ ፡ ነገርየ ፡ ወዐለዉ ፡
ፍትሐ፤
ነገርየ ፤ ዘጠኙን ፤ ፍትሐ ፡ ኢ.ታም
ልክን፡አልጠበቁም፤

ወኢፈትሑ፡ለዕጓለ፡ማውታ፤
እናት ፡ አባት ፡ ለሌለው ፡ ለድኃ ፡
አደጉም ፡ ልጅ ፡ እውነት ፡ ፍርድ ፡ አል
ፈረዱለትም፤

ወኢኰነኑ፡ኵነኔ፡ዕቤር፤
ቀንዋ ፡ ለገፋውም ፡ ባልቴት ፡ እውነት ፡
ፍርድ፡አልፈረዱላትም፤

፳፱፤ በዝሂ ፡ ኢይኴንንሁ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ቤተ ፡ እስራኤል ፤ በዚህ ፡ በደላችሁ ፡
አልፈርድባችሁምን፤

ወኢትትቤቀሎሙኑ፡ነፍስየ፡ለሕዝብየ፡
ወገኖቼ፡እስራኤልንስ፡ልቡናዬ፡አት
በቀላቸውምን ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር
አንድም ፡ በዝሂ፡ ኢይኴንንሁ ፡ ይቤ
እግዚአብሔር ፡ ወኢትትቤቀሎሙኑ
ነፍስየ ፡ ለሕዝብየ ፡ ይላል ፤ ቤተ፳ኤል
በዚህ ፡ በበደላችሁኝ ፡ በደል ፡ አልፍ
ረድን ፡ ልቡናዬስ ፡ እናንተን ፡
ወገኖቼን፡ አትበቀላችሁምን ፡ አለ ፡
እግዚአብሔር፤

፴፤ ዘከመዝ ፡ ድንጋፄ ፡ ወነሣጣ
መጽአ፡ውስተ፡ብሔር፤
አሁን ፡ እንደተናገርኩት ፡ ድንጋፄ ፡
ጽኑዕ ፡ ድንጋፄ ፡ ወነሣጣ ፡ ስቅጥጥ ፡
ስቅጥጥ ፡ የሚያደርግ ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡
ወዳለበት፡አገር፡ታዞ፡መጣባቸው፤

፴፩፤ ነቢያትኒ፡ይትኔበዩ፡ሐሰተ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትም ፡
ሰላም ፡ ሰላም ፡ እያሉ ፡ የሐሰት ፡
ትንቢት፡ይናገራሉ፤

ወካህናትኒ፡ይጠፍሑ፡እደዊሆሙ፤
ካህናተ ፡ ጣዖቱም ፡ ይበጅ ፡ ያድርግ ፡
እያሉ፡በእጃቸው፡ያጨበጭባሉ፤

ወሕዝብኒ፡ዘንተ፡አፍቀሩ፤
ሕዝቡም ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ሰላም ፡
ሰላም፡ብለው፡የተናገሩትን፡የሐሰት፡
ትንቢት ፡ ካህናተ ፡ ጣዖቱም ፡ ይበጅ ፡
ያድርግ ፡ ብለው ፡ በእጃቸው ፡ ያጨበ
ጨቡትን፡ማጨብጨብ፡ወደዱ፤

ወምንተ፡ይሬስዩ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፤
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ኃጢአ
ታቸው ፡ ፍዳውን ፡ ይዞ ፡ በመጣባቸው ፡
ጊዜ፡ምን፡ያደርጉ፡ዘንድ፡አላቸው።



## ምዕራፍ፡፮፤

፩፤ ጽንዑ ፡ ደቂቀ ፡ ብንያም ፡ ዘማዕከለ ፡
ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ መካከል ፡ የምትኖሩ ፡
የብንያም ፡ ልጆች ፡ ይሆንላችሁ ፡
እንደሆነ ፡ ባጭር ፡ ታጥቃችሁ ፡ ዘገር ፡
ነጥቃችሁ፡ለመዋጋት፡ጽኑ፤

### ጉባዔ፤

ወበቴቁሔ፡ንፍሑ፡ቀርነ፤
በቴቁሔም ፡ ሁናችሁ ፡ ነጋሪቱን ፡
ምቱ፡ አለ ፡ ጦር ፡ ለመሰብሰብ ፤
አንድም፡ አንበጣውን ፡ ለማራቅ ፤
አንድም፡ምህላውን፡ለመያዝ፡ነው፤

ወንሥኡ፡ትእምርተ፡በቤተ፡ካሬም፤
ካሬም፡የነገደ፡ብንያም፡አለቃ፡ነው፤
አንድም ፡ የነገደ ፡ ዛብሎን ፡ አለቃ ፡
ነው፤ አንድም ፡ ከነገደ ፡ ብንያም ፡
ተወልዶ ፡ በቴቁሔ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡
ነው ፤ በካሬም ፡ ቤትም ፡ አጠገብ ፡
ሁናችሁ፡ሰንድቅ፡ዓላማውን፡አንሡ፤

እስመ፡ሐወፀት፡እኪት፡እምነ፡መስዕ፤
መከራ ፡ ከባቢሎን ፡ ታዝዛ ፡ መጥታ
ለችና፡ስለመጣች፤

ወይከውን፡ዓቢይ፡ቅጥቃጤ፤
ያንጊዜም ፡ በቤተ ፡ እስራኤል ፡ ጽኑ ፡
መከራ፡ይደረግባታል፤

፪፤ ወያሐሥረኪ፡ወለተ፡ጽዮን፤
ወይከውን ፡ ዓቢይ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ብሎ ፡
ነበርና ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
መከራው ፡ ያጐሰቍልሻል ፤ አንድም ፡
ናቡከደነፆር፡ያጐሰቍልሻል፤

ኮንኪ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ድልድል ፡ ቅም
ጥል ፡ ሁነሽ ፡ ኖርሽ ፤ አንድም ፡
እንዳለም ፡ ይሆናል ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡
ዛሬ፡ በዌዋዌ፡ ድልድል ፡ ቅምጥል ፡
መስለሽ ፡ አለ ፤ ያቺ ፡ ድልድል ፡
ቅምጥል ፡መውጣት ፡ መውረዱን፡
አትችልም ፤ ቤተ ፡ እስራኤልም ፡
መከራውን፡የማትችል፡ሁናለችና፤

፫፤ ወይመጽኡ፡ላዕሌሃ፡ኖሎት፤
ነገሥታቱም፡ከተት፡ሠራዊት፡ምታ፡
ነጋሪት፡ብለው፡ይመጡባታል፤

ወመራዕይሆሙ፤
ሠራዊቶቻቸውም፡አብረው፡ይመጣሉ፤

ወይተክሉ፡ምጽላሎሙ፡በዓውዳ፤
በዙሪያዋም፡ድንኳናቸውን፡ይተክላሉ፤

ወይርእዩ፡ኵሎሙ፡በእደዊሆሙ፤
በእጃቸው ፡ በቃላቸው ፡ ይጠብቃሉ ፡
አለ ፤ ከዚህ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ያመነ ፡
አገር ፡ ይገብር ፤ ይቀቅል ፡ እንጂ ፡
አትውጉት ፤ አትዝረፉት ፡ ይላሉ ፤
አንድም ፡ ወይሬእዩ ፡ ኵሎ ፡ በእደ
ዊሆሙ ፡ ይላል ፤ በእጃቸው ፡
በቃላቸው፡ ያያሉ ፡ አለ ፤ የእገሌን ፡
አገር፡ ለእገሌ ፡ ሰጥቼዋለሁ ፡ ይላሉ ፤
ሐተታ ፡ ይሬእዩ ፡ በእደዊሆሙ፡ አለ ፤
እጅም፡ ለነገር ፡ አጋዥ ፡ ነውና ፤
አንድም፡ ወይመጽኡ ፡ ላዕሌሃ ፡
ኖሎት፤ አገሪቱ ፡ ተፈትታ ፡ ጠፍታ ፡
ዘላኖች፡ተሰብስበው፡ይመጡባታል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወመራዕይሆሙ ፤ መንጋቸውንም ፡ ይዘው ፡ ይመጣሉ ፤ ወይተክሉ ፡ ምጽላሎሙ ፡ በዓውዳ ፤ ደረባ ፡ ይሠሩ ባታል ፤ ወይሬእዩ ፡ ኵሎሙ ፡ በእደዊሆሙ ፤ ሁሉም ፡ በእጃቸው ፡ ያያሉ ፡ ያመለክታሉ ፡ አለ ፤ ከዚህ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የኔ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ አገሪቱን ፡ በዓይነ ፡ ገመድ፡ ይካፈሏታል ፤ አንድም፡ ወይርእዩ ፡ ኵሎ ፡ በእደዊሆሙ ፡ በእጃቸው ፡ በቃላቸው ፡ ይጠብቋታል ፡ አለ ፤ ከዚህ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ፡ ያቀናሁት ፡ አገሬ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ እየተከራከሩ፡ይጠብቋታል፤

፬፤ ቀደሱ፡ቀትለ፡ላዕሌሃ፡

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ሰልፍ ፡ አጸኑባት አፍሪ፡መለሱባት፤

ወይቤሉ፡ተንሥኡ፡ንዕርግ፡ዲቤሃ፡ቀትረ፡

ተነሡ፡እንዝመትባት፡ሌሊቱን፡ስንገሠግሥ ፡ አድረን ፡ በቀትር ፡ አደጋ ፡ ጥለን ፡ እናጥፋት ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ ባፍላ ፡ ባለፀግነቷ ፡ ሳለች፡ ገሥግሠን ፡ ዘምተን፡እናጥፋት፡አሉ፤

አሌ፡ለነ፡

ወዮልን ፡ አለ ፡ ነቢዩ ፡ በእስራኤል ፡ ተገብቶ ፤ አንድም ፡ ወዮልን ፡ በሉ ፡ አላቸው፡እነሱን፤

እስመ ፡ ተቈልቈለ ፡ ፀሐይ ፡ ወሐለፈ ፡ ጽላሎተ፡መዓልት፡

ፀሐዩ ፡ ገብቷልና ፡ ጥላውም ፡ ድንግዝግዝ ፡ ብሏልና ፤ ሐተታ ፡ ሌሊት ፡ አሕዛብ ፡ አደጋ ፡ እየጣሉ ፡ ያጠፉዋቸው ፡ ነበረና፡ በዚያ ፡ ልማድ ፡ አሌ ፡ ለነ፡አለ፤አንድም፡እስመ፡ተቈልቈ ፀሐይ ፡ ተድላ ፡ ደስታው ፡ ቀርቶ ናልና፤ወሐለፈ፡ጽላሎተ፡መዓልት፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ የምናደርግበት ወራት፡አልፎብናልና፡ወዮልን፡አለ

፭፤ ተንሥኡ፡ንዕርግ፡በሌሊት፡

ጠላቶቿዋም ፡ ቀን ፡ ስንገሠግሥ ውለን ፡ ሌሊት ፡ አደጋ ፡ ጥለን እናጥፋት ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ በሌሊት መከራ ፡ ተይዛ ፡ ሳለች ፡ ገሥግሠን ዘምተን፡እናጥፋት፡አሉ፤

ወናማስን፡መሠረታቲሃ፡

ሌሊት ፡ አደጋ ፡ ጥለን ፤ አንድም በሌሊት፡መከራ፡ተይዛ፡ሳለች፡ሥ መሠረቷን ፡ እናጥፋው ፡ አሉ አንድም፡ ኃያላኖቿን ፡ ነገሥታቷን እናጥፋ፡አሉ፤

፮፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር ኃያል፤

አምጻኤ፡ዓለማት፡ወላዴ፡ፍጥረታት እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናግ ባታልና፤

ግዝሙ፡ዕፀዊሃ፡

አስቀድማችሁ ፡ እንጨቶቿን ፡ (እን ጨቱን) ቈረጡባት፤አንድም፡አስቀደ ማችሁ ፡ ሠራዊቶቿን ፡ አጥፉባት ፡ ብሎ፡ተናግሯልና፤

ወከዓዉ፡ኃይለ፡ላዕለ፡ኢየሩሳሌም፡አህጉረ ሐሰት፡

መጽሐፍ፡ምሥጢር፡እንጂ፡ዘይቤ፡ አይጠነቅቅምና ፤ ለኢየሩሳሌም ፡ አህጉረ፡ ሐሰት ፡ ብሎ ፡ ቀጸለላት ፤



ሐሰት ፡ በሚነገርባት ፤ አንድም ፡ ሐሰት፡ ጣዖት ፡ በቆመባት ፡ በሚመለክባት፤

ወኵሉ፡ትዕግልት፡ውስቴታ፡

ቅሚያውም ፡ ሁሉ ፡ በሚደረግባት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ የሱዋን ፡ ሠራዊት፡ አጥፍታችሁ ፡ የናንተን ፡ ሠራዊት፡አብዝታችሁ፡አፍሱባት፤

፯፤ ከመ፡ቍረ፡አዘቅተ፡ማይ፡ከማሁ፡ ቆሪር፡እከያ፡

በጥልቅ፡ጕድጓድ፡ውስጥ፡ባለ፡ውሀ፡ ያለ ፡ ቅዝቃዜ ፡ ብዙ ፡ እንደሆነ ፡ በሱዋም፡ያለ፡ክፋት፡እንደዚያ፡ብዙ፡ ነው፤አንድም፡ያ፡በውሃ፡ያለ፡ቍረት፡ እንዲያሰቅቅ ፡ በሱዋም ፡ ያለ ፡ ክፋት፡ እጅግ፡ያሰቅቃል፤

ዓመፃ፡ወግፍዕ፡ተሰምዐ፡በውስቴታ፡

በዚያም ፡ ወራት ፡ ኃጢአት ፡ ግፍዕ ፡ በሷ፡ተደረገ፡ሲሉ፡ተሰማ፤

ወውስተ ፡ ገጻ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ሕማም ፡ መከራውም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይመጣባታል ፤ አንድም ፡ ገና ፡ ወደፊቱዋ ፡ ነው፤

፰፤ ወበመቅሠፍት ፡ ትትቀሠፍ ፡ ኢየሩሳሌም፡

ኢየሩሳሌምም ፡ እኔ ፡ ያመጣሁባትን፡ መከራ፡ትቀበላለች፤(በመከራ፡ትገረፋለች)፤

ከመ፡ትርኀቅ፡ነፍስየ፡እምኔሃ፡

ልቡናዬም፡በፍቅር፡በረድዔት፡ከሷ፡ ትርቅ ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ ወበመቅሠፍት፡ትትቀሠፍ፡ኢየሩሳሌም፤ኢየሩሳሌም፡እኔ፡ያመጣሁባትን፡መከራ፡ ትቀበላለች፤

ወትርኀቅ፡እምኔየ፡በባለሟልነትም፡ ከኔ ፡ ትርቃለች፤ አንድም ፡ ወበመቅሠፍት፡ትትቀሠፊ፡ኢየሩሳሌም፤ኢየሩሳሌም፡እኔ፡ያመጣሁብሽን፡መከራ፡ ትቀበያለሽ ፤ ወትርኀቅ ፡ ነፍስየ ፡ እምኔኪ ፤ ልቡናዬም ፡ በፍቅር ፡ በረድዔት ፡ ካንቺ፡ ትርቃለች ፤ አንድም፡ወበመቅሠፍት፡ትትቀሠፊ፡ ኢየሩሳሌም ፤ ወትርኀቂ፡ እምኔየ ፤ አንቺም ፡ ከኔ ፡ ባለሟልነት ፡ ትርቂ ያለሽ ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ትትረኀቂ ፡ እምኔየ ፤ ወበመቅሠፍት ፡ ትትቀሠፊ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይላል ፤ እንደዚህም ፡ ያስተረጕማል፤

ወእሬስየኪ ፡ ምድረ ፡ በድው ፡ ዘአልቦ ፡ ዘይነብሮ፡

እኔም ፡ አንቺ ፡ ተፈትተሽ ፡ ጠፍተሽ ፡ ሰው፡ የማይኖርበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደርግሻለሁ፤

፱፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ጸባዖት፡

አቸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ፡ተናግሯልና፤

ተቅራመ ፡ ይትቄረምዎሙ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ለተረፈ፡እስራኤል፤

ወይን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ዐይነታውን ፡ ከለቀሙ ፡ በኋላ ፡ ቃርሚያውን ፡ አጥርተው ፡ እንዲለቅሙት ፤ የእስራኤልንም ፡ ወገኖች ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ በስልምናሶር ፡ ከማረኳቸው ፡ በኋላ ፡ ሁለቱን፡ ነገድ ፡ በናቡከደነፆር ፡ ይማርኳቸዋል ፤ አንድም ፡ በናቡከደነፆር ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ከማረኳቸው ፡ በኋላ፡ በናቡዛርዳን ፡ የቀሩትን ፡ ይለቅሚ

www.ethiopianorthodox.org

ቸዋል ፤ አንድም ፡ ዐሥሩን ፤ ሁለቱን ፡
ነገድ ፡ ከማረኳቸው ፡ በኋላ ፡ መቃብ
ያንን፡በጽርዓውያን፡ያጠፏቸዋል፤

ሚጥ ፡ እዴከ ፡ ከመ ፡ ዘይቀሥም ፡ ውስተ ፡
ከረቦ፡

ያ፡ቃርሚያ፡የሚለቅም፡ሰው፡ወደት
ራንትራው፡ወደ፡ቅምብቻው፡እጁን፡
መላልሶ፡እንዲያገባ፡ነቢይ፡አንተም፡
መልሰህ፡መላልሰህ፡አስተምራቸው፤
አንድም፡ናቡከደነፆር፡አንመለስም፡
ካሉ፡መላልሰህ፡ውጋቸው፤

፲፡ ለመኑ፡እነግር፡ወአሰምዕ፡

ሚጥ ፡ እዴከ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡
ምከራቸው ፤ አስተምራቸው ፡ ትለ
ኛለህ፡እንጂ፡ለማን፡እመክራለሁ፡አስ
ተምራለሁ፤

ወኢይሰምዑኒ፡

እኔስ ፡ ብመክራቸውም ፡ ባስተምራ
ቸውም፡አይሰሙኝም፤

ናሁ፡ጽሉል፡ልቦሙ፡ወዕዘኒሆሙ፡

እነሱስ ፡ ዓይነ ፡ ልቦናቸው ፡ ዕዝነ ፡
ልቡናቸው፡በድንቍርና፡ተይዟል፤

ወኢይክሉ፡ሰሚዐ፡

ስለዚህ፡ነገር፡ብመክራቸው፡ባስተም
ራቸውም ፡ እኔን ፡ መስማት ፡ አይቻላ
ቸውም፤

ወናሁ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮኖሙ ፡
ለጽዕለት፡

ትምህርቱንስ ፡ አንማረው ፡ ብለው ፡
ነቀፉት ፤ አንድም ፡ እኔን ፡ ምከር ፡
አስተምር ፡ ትለኛለህ ፡ እንጂ ፡
ትምርቱስ ፡ እኔን ፡ የሚነቅፉበት ፡
እኔን፡ የሚሰድቡበት ፡ ሆናቸው ፤
አንድም፡ወናሁ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
ኮኖሙ ፡ ለጽዕለት ፡ ትምርቱንስ ፡
አንማረውም ፡ ብለው ፡ ተማርከው
ሄደው፡ገዶ ፡ ገብሮ ፡ ተብለው ፡ እን
ሰደቡ፡አደረጋቸው፤

እስመ፡ኢፈቀዱ፡ይስምዕዎ፤

ስንኳንስ ፡ ሊማሩት ፡ በጆሮዋቸው
ሊሰሙት፡አልወደዱምና፤

፲፩፡ ወመላዕክዎሙ ፡ መዓትየ ፡ ወአሐ
ቅዎሙ፤

በዚህ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ቍጣዬንም
አብዝቼ፡አምጥቼ፡አጠፋኋቸው፤

ወዕክዕዎ፡ላዕለ፡ሕፃናት፡ኅቡረ፡በአፍዓ፡

ልጆቻቸው ፡ ከቤታቸው ፡ ደጃፍ
አንድ፡ሁነው፡እንዲጠፉ፤

ወላዕለ፡ማኅበረ፡ወራዙት፡ኅቡረ፡

ጐልማሶቻቸውም፡በአደባባይ፡አንድ
ሆነው፡ እንዲጠፉ ፡ መቀሠፍቴን ፡
አብዝቼ፡አመጣዋለሁ፤አንድም፡ልጆ
ቻቸውና ፡ ጐልማሶቻቸው ፡ አንድ ፡
ሆነው፡ባደባባይ፡እንዲጠፉ፡አደርጋ
ቸዋለሁ፤

እስመ፡ያሠግሩ፡ብእሴ፡ምስለ፡ብእሲቱ፡

ሰውዬውን፡ከሚስቱ፡ጋራ፡ያጠምዱ
ታልና ፡ አለ ፤ ፊት ፡ ሚስቱን ፡
ይቀሙታል ፤ ሚስቴን ፡ ሲል ፡ እሱን፡
ይደግሙታልና ፤ አንድም ፡ ባልና ፡
ሚስቱን፡አንድ፡አድርገው፡ያጠፏች
ዋልና ፤ አንድም ፡ ሚስቱን ከመቀማ
ታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ እሱን ፡ ያጠ
ፉታል ፤ እሱን ፡ ካጠፉት ፡ በኋላ ፡
ሚስቱን፡ይወስዱታልና፤

ወልሒቀ፡ምስለ፡ወሬዛ፡

አባትየውን ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ አጥፍተ
ውታልና ፡ አለ ፤ ፊት ፡ ልጁን ፡
[illegible]



እሱን ፡ ይደግሙታልና ፤ አንድም ፡
አባትና፡ልጁን፡ያጠፏቸዋልና፤

፲፪፡ ወይትዌለጥ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ለነ
ኪራን፤

ቤታቸውም ፡ ተለውጦ ፡ ለአሕዛብ ፡
ይሆናል፡(ይሰጣል)፤

ገራኅቶሙ፡ወአንስቶሙኒ፡ኅቡረ፡

እርሻቸውም ፡ ሚስቶቻቸውም፡ተለ
ውጠው ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ለአሕዛብ ፡
ይሆናሉ፡(ይሰጣሉ)፤

እስመ፡አነሥእ፡እደውየ፡ላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡
ውስተ፡ዛቲ፡ምድር፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

በዚያች ፡ አገር ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ፡እደ ፡ መዓቴን ፤ አንድም ፡ እደ ፡
ቃሌን፤አንድም፡ነቢያት፡ካህናትን፡
አመጣባቸዋለሁ ፡ ብሏልና ፡ እግዚአ
ብሔር ፤ ሐተታ ፡ እደውየ ፡ አላቸው ፡
ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ እጅ ፡ ለነገር ፡
አጋዥ ፡ ረዳት ፡ እንደሆነ ፡ እነሱም ፡
ለነገሩ ፡ አጋዥ ፡ ረዳት ፡ ናቸውና ፤
አንድም ፡ በእጅ ፡ በእግር ፡ እንዲያ
ዙበት፡በነሱም፡ያዝባቸዋልና፤

፲፫ እስመ ፡ ንዑሶሙኒ ፡ ወዐቢዮሙኒ ፡
ገብሩ፡ኃጢአተ፡

እንዲህም ፡ ማድረጌ ፡ ትንሹም ፡
ትልቁም ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ኃጢአት፡
ሠርተው ፡ በድለውኛልና ፡ ስለዚህ ፡
ነው ፤ ንዑሶሙ ፡ ዐቢዮሙ ፡ ብሎ ፡
ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሮአል ፤
ለሁለቱም፡ያመጣለታል፤

እምካህን ፡ እስከ ፡ ሐሳዊ ፡ ነቢይ ፡ ኵሎሙ ፡
ገብሩ፡ሐሰተ፡

[illegible]

ዐቢዮሙ ፡ ያለውን ፡ ሐሳዊ ፡ ነቢይ ፡
ብሎ ፡ አመጣው ፤ ከካህነ ፡ ጣዖቱ ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ድረስ ፡
ሁሉም፡አንድ፡ሆነው፡ነበቡ፡ሐሰተ፡
ሲል፡ነው፤ሐሰት፡ተናገሩ፤አንድም፡
እንዳለ ፡ ይሆናል ፤ ሁሉም፡ አንድ ፡
ሆነው ፡ ሐሰት ፡ ጣዖቱን ፡ ሠርተው ፡
አመለኩ፤

፲፬ ወይፌውሱ ፡ ቅጥቃጤሆሙ ፡
ለሕዝብየ፡

በሕዝቡ፡የመጣውንም፡መከራ፡እናር
ቃለን፡ይላሉ፤

ወይቤሉ፡ሰላም፡ሰላም፡

ሰላም፡ሰላም፡ይላሉ፤

ወአልቦ፡ሰላም፡

ሰላም፡የለም፤

፲፭፡ ወተሐፍሩ፡እስመ፡ርኵሰ፡ገብሩ፡

ኃጢአቱን፡ሠርተውታልና፤አንድም፡
ጣዖት ፡ ሠርተው ፡ አምልከዋልና ፡
በዚህ፡መከራ፡መጥቶባቸው፡አፈሩ፤

ወሐፊረኒ፡ኢየኃፍሩ፡

ንሥሓ፡ግን፡አይገቡም፤

ወኢ የአምሩ፡ኃሣሮሙ፡

ወደፊት፡የሚመጣባቸውንም፡መከራ፡
አያውቁትም፤

በእንተ፡ዝንቱ፡ይወድቁ፡

ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ንሥሐ ፡
ስላልገቡ፡ይጠፋሉ፤

ወአመ፡እሔውፆሙ፡ይደክሙ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡

እነሱንም ፡ በመዓት ፡ በጐበኘኋቸው፡
ጊዜ ፡ በእጃቸው ፡ ከመወርወር ፡
በቃላቸው ፡ ከመምከር ፡ ይደክማሉ ፡
አለ፡እግዚአብሔር፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ቁሙ፡ውስተ፡ፍናው፤
ሂዳችሁ ፡ በተመሳቀለው ፡ ጎዳና ፡ መካከል፡ቁሙ፤

ወርእዩ ፡ ወተሰአሉ ፡ ፍኖተ ፡ ቃለ ፡ እግዘአብሔር፡ዘለዓለም፤
ዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ የእግዚአብሔር፡ ሕጉን፡ጠይቃችሁ፡እወቁ፤

ወአእምሩ፡አይ፡ፍኖት፡ሠናይ፤
ከሕገ፡እግዚአብሔርና፡ከሕገ፡ጣዖት፡ በጎው ፡ ሕግ ፡ ማናቸውም ፡ እንደሆነ ፡ ለይታችሁ፡እወቁ፤

ወሑሩ፡ባቲ፤
በበጎ፡ሥራ፡ጸንታችሁ፡ኑሩ፤

ወትረክቡ፡መድኃኒተ፡ነፍስክሙ፤
ይኸን፡ያደረጋችሁ፡እንደሆነ፡ለሰውነታችሁ ፡ ድኅነትን ፡ ታገኛላችሁ ፡ አልኳቸው፤

ወይቤሉ፡ኢነሐውር።
በሕገ ፡ ጣዖት ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፡ እንጂ፡በሕገ፡እግዚአብሔር፡ጸንተን፡ አንኖርም፡አሉ፤

፲፯፤ ወሤምኩ፡ላዕሌሆሙ፡ሰብአ፡ዐይን፡
ጦር ፡ መጣ ፡ የሚል ፡ ጉበኛ ፡ አኖርኩባቸው፤

ወሰምዑ፡ቃለ፡ቀርን፤
ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል ፡ የነጋሪቱን ፡ ድምፅ፡ ሰሙ ፤ አንድም ፡ ወይቤሉ ፡ ኢነሐውር፤
በሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንተን ፡ አንኖርም ፡ አሉ ፤ ወሤምኩ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ዓይን ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምክሯቸው ፡ አስተምሯቸው፡ብዬ፡ነቢያትን፡ወደነሱ፡ሰደድኩላቸው፤

ወሰምዑ፡ቃለ፡ቀርን፤
የእነኢሳይያስን፡ የእነኤርምያስን ፡ ቃል፡ሲያስተምሩ፡ሰሙ፤ሐተታ፡ኢሳይያስን፡ልዑለ፡ቃል፡ልዑለ፡ቀርን፡ የሚያሰኘው፡ይህ፡ነው፤

ወይቤሉ፡ኢንሰምዕ፤
ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል ፡ የነጋሪቱንም ፡ ድምፅ ፡ አንሰማም ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ ቢመክሯቸው፡ቢያስተምሯቸው፡የነኢሳይያስን ፡ የነኤርምያስን ፡ ቃል፡ አንሰማም፡አሉ፤

፲፰፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ስምዑ፡አሕዛብ፤
ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ ስለበደሉኝ ፡ አሕዛብ፡ስሙኝ፤አንድም፡እኔን፡የበደሉበትን ፡ የበደላቸውን ፡ ነገር ፡ አሕዛብ፡እናንተ፡ስሙኝ፤

ወኖሎተ፡መራዕይ፤
መንጋውን፡የምትጠብቁ፡ዘላኖችም፡ ስሙ ፤ አንድም ፡ ወመራዕየ ፡ ኖሎት ፡ ይላል፤ዘላኖች፡የሚጠብቋችሁ፡መንጋዎቹም፡ስሙኝ፤

፲፱፤ ወስምዒ፡ምድር፤
ምድርም ፡ ስሚ ፤ ሐተታ ፡ የሰዎቹን ፡ ለመንጋዎች ፤ ለምድር ፡ ሰጥቶ ፡ መናገር፡ ነው ፤ አንድም ፡ ወኖሎተ ፡ መራዕይ ፡ ሠራዊት ፡ ያሏችሁ ፡ ነገሥታቱ ፤ አንድም ወመራዕየ ፡ ኖሎት ፡ ነገሥታት ፡ ያሏችሁ ፡ ሠራዊቱ፤ወስምዒ፡ምድር፡ትሑታኑ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ ስሙ ፤ አንድም ፡ በእንተ፡ ዝንቱ ፡ ስምዑ ፡ አሕዛብ ፡ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡ የተባሉ ፡ እስራኤል፡እኔን፡የበደሉበትን፡ነገር፡ ሕዝቡ ፡ አሕዛቡ ፡ ስሙ ፤ ወኖሎተ ፡ መራዕይ፡ደቀ፡መዛሙርት፡ያሏችሁ፡ መምህራኑ ፤ አንድም ፡ ወመራዕየ ፡ ኖሎት፡መምህራን፡ያሏችሁ፡ደቀመዛሙርቱ፡ስሙ፤

ወስምዒ ፡ ምድር ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ልቡናም፡ይኸን፡ሰምታ፡ትወቅ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብ፡ በከመ፡ፍሬ፡ምግባሮሙ፤
ፍሬ፡ግሥ፡ነው፤እንደክፉ፡ሥራቸው፡ መጠን ፤ አንድም ፡ ፍሬ ፡ ፍዳ ፡ ነው ፡ ምግባር፡ኃጢአት፡ነው፤እንደኃጢአታቸው፡ፍዳ፡መጠን፡በወገኖቼ፡በእስራኤል፡መከራውን፡እነሆ፡አመጣባቸዋለሁ፤

እስመ፡ኢያጽምዑ፡ነገርየ፡ወዐለዉ፡ሕግየ፡
የነገርኳቸውን፡ነገር፡አልሰሙኝምና፡ ሕጌን ፡ ሥርዓቴንም ፡ ወንጅለዋልና ፡ አለ ፡ በቁሙ ፤ አንድም ፡ ነገርየ ፡ ዘጠኙን፡ሕግየ፡ኢታምልክን፡ነው፤

ወመነኑ፡ኪያየ
በዚህም ፡ ላይ ፡ እኔን ፡ ንቀዋል ፡ አቃለዋልና፤

፳፤ለምንት ፡ ታመጽኡ ፡ ሊተ ፡ ስሂነ ፡ እምሳባ፤
እኔን ፡ እየበደላችሁ ፡ ሳባ ፡ ከሚባል ፡ አገር፤አንድም፡ከፋስቆሎ፡ነግዳችሁ፡ ነጩን ፡ ዕጣን ፡ ለምን ፡ ታመጡልኛላችሁ፤



ወቀናንሞስ፡ሠናየ፡እምርኁቅ፡ብሔር፡
ስኂን ፡ ያለውን ፡ ቀናንሞስ ፤ ሳባ ፡ ያለውን ፡ እምርኁቅ ፡ ብሔር ፡ ብሎ ፡ ገለጠው፤ አንድም ፡ ነጩን ፡ ዕጣን ፡ ከሳባ ፡ ዶርሲኒ ፡ የሚባለውንም ፡ ሽቱ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ነግዳችሁ ፡ ለምን ፡ ታመጡልኛችሁ፤

መሥዋዕቲክሙኒ፡ኢኮነ፡ኅሩየ፤
በኃጢአት ፡ ሁናችሁ ፡ የምታቀርቡልኝም ፡ መሥዋዕት ፡ የተመረጠ ፡ አይደለም ፤ አንድም ፡ ዕሩየ ፡ ይላል፤ ቀድሞ፡ንጹሐን፡ሁናችሁ፡ከምታቀርቡልኝ፡መሥዋዕት፡ጋራ፡የተካከለ፡ አይደለም፤

ወቍርባንክሙኒ ፡ ኢይኤድመኒ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ፤
አብዝታችሁም ፡ ስለበደላችሁኝ ፡ በኃጢአት ፡ ሁናችሁ ፡ የምታቀርቡልኝ፡ቁርባናችሁ፡ደስ፡አያሰኘኝም፡ አለ፤ ወድጄ ፡ አልቀበለውም ፡ ሲል ፡ ነው፤

፳፩፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ስለዚህ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እሁብ፡ደዌ፡ላዕለ፡ዝንቱ፡ሕዝብ፤
ስለበደሉኝ ፡ በወገኖቼ ፡ በእስራኤል ፡ መከራውን ፡ አብዝቼ ፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ወይደውዩ ፡ ውስቴታ ፤ አበው ፡ ምስለ ፡ ደቂቆሙ፡ኅቡረ፤
እሁብ ፡ ደዌ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ውስቴታ ፡ ባቲ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዚያች ፡ ባመጣሁባቸው ፡ መከራ፤ አንድም ፡ ውስቴታ ፡ ስምዒ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ በሚኖ

www.ethiopianorthodox.org

ሩባት፡አገር፡አባቶች፡ከልጆች፡ጋራ፡
አንድ፡ሁነው፡መከራ፡ይቀበላሉ፤

ወይትኀጐሉ፡ኅር፡ምስለ፡ቢጾሙ፤

ጎረቤቶችም፡ከጎረቤቶቻቸው፡ጋራ፡
መከራ፡ይቀበላሉ፡አለ፤ያልበደሉት፡
ከበደሉት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡
ይጠፋሉ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ከጎረቤት ፡
የመጣ ፡ መከራ ፡ ለጎረቤቱ ፡ ይተር
ፋልና ፤ ጎረቤትህ ፡ ደኅና ፡ ይዋል ፡
አንተም ፡ ደኅና ፡ እንድትውል ፡
እንዲሉ፤ አንድም ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡
ሁነው ፡ ኃጢአቱን ፡ ሠርተው ፡
ይጠፋሉ፡ሲል፡ነው፤

፳፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡ይመጽኡ፡ሕዝብ፡እምሰሜን፡
እነሆ፡እናንተን፡ሊያጠፉ፡አሕዛብ፡
ከባቢሎን፡ይመጣሉ፤

ወሕዝብ፡ዐቢይ፤
እሊህም ፡ ይመጣሉ ፡ ያልኳቸው ፡
ወገኖች፡ብዙ፡ናቸው፤

ወነገሥትኒ ፡ ብዙኃን ፡ ይትነሥኡ ፡ እምአ
ጽናፈ፡ምድር፤

ብዙ ፡ ነገሥታትም ፡ ከባቢሎን ፡
ተነሥተው ፡ ይመጣሉ ፤ ሐተታ ፡
እምሰሜን ፡ ያለውን ፡ እምአጽናፈ ፡
ምድር ፡ ብሎ ፡ ገለጠው ፤ ያውስ ፡
ቢሆን፡ስለምን፡ነገሥት፡ብሎ፡አበዛ፡
አንድ፡ናቡከደነፆር፡አይደለም፡ቢሉ፡
መጽሐፍ፡ስም፡ካልጠራ፡ማብዛት፡
ልማድ ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ብዙ ፡
ተወራጅ ፡ ነገሥታት ፡ አሉና ፤
አንድም፡ ናሁ ፡ ይመጽኡ ፡ ሕዝብ ፡
እምሰሜን ፤ ከባቢሎን ፡ እነናቡከደ
ነፆር፡ይመጣሉ፤

ወነገሥትኒ ፡ ብዙኃን ፡ ይትነሥኡ ፡ እም
ጽናፈ፡ምድር፤
ሌሎችም፡ብዙ፡ረዳት፡ነገሥታት፡ከ
ሀገራቸው፡ተሰብስበው፡ይመጣሉ፤

፳፫፤ ወይፀውሩ፡ቀስተ፡ወኲናተ፤
ቀስታቸውን ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው
ይመጣሉ፤

ወይነድፉ፤
እንዳገኙ፡ይወጋሉ፤

ወኢይምህኩ፤
ለሰውም ፡ ለከብትም ፡ አይራሩም ፡
አያዝኑም፤

ወውውዓሆሙ፡ከመ፡ድምፀ፡ማዕበለ፡ባሕር
እልልታቸውም ፡ ግርግርታቸውም ፡
እንደ ፡ መጣያ ፡ ውሀ ፡ ድምጥ ፡ ነው፤
አንድም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደተነሣ፡
እንደ፡ማዕበል፡ድምፅ፡ነው፤ ሐተታ፡
ያ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማል፤ የነሱም ፡ እልል
ታቸው ፡ ግርግርታቸው ፡ ከሩቅ ፡
ይሰማልና፤አንድም፡ያ፡እንዲያስፈራ፡
የነሱም ፡ እልልታቸውም ፡ ግርግርታ
ቸውም፡ያስፈራልና፤

በአፍራስ፡ወበሠረገላት፡ይፄዓኑ፤
ይመጽኡ፡ብሎ፡ነበረና፡ሲመጡም፡
በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡
ይመጣሉ፤

ወይፀብኡኪ፡ከመ፡እሳት፡ወለተ፡ጽዮን፤
የጽዮን ፡ ልጅ ፡ እሳት ፡ ሁሉን ፡ እንዲ
ያጠፋ ፡ ጠላቶችሽ ፡ አሕዛብም ፡
እንደዚያ ፡ መጥተው ፡ ይወጉሻል፤
(ያጠፉሻል)፤

፳፬፤ ወሰሚዐነ ፡ ውውዓሆሙ ፡ ደክማ ፡
እደዊነ፤



እልልታ፡(ድንፋታቸውን)፡ግርግርታ
ቸውንም ፡ ሰምተን ፡ ቃላችን
ከመምከር ፡ እጃችን ፡ ከመወርወር ፡
ደከመ፤

ወአኀዘነ፡ምንዳቤ፡ወሕማም፡ከመ፡እንተ፡
ትወልድ፤
ምጥ፡የያዛት፡በምጡ፡ተይዛ፡እንድት
ጨነቅ፤ እኛንም ፡ እንደሱዋ ፡ የሚያስ
ጨንቅ፡ፍጹም፡መከራ፡ያዘን፤

፳፭፤ ኢትግፁ ፡ ሐቅለ ፡ ወኢትሑሩ ፡
መንገደ፤
በዚያ፡ወራት፡ወደ፡ምድረ፡በዳው፡
አትውጡ፤ ጉዳይም ፡ ቢያገኛችሁ ፡
ጎዳና፡አትሒዱ፤

እስመ፡አገተክሙ፡ኲናተ፡ፀርክሙ፤
የጠላቶቻችሁ፡ጦር፡ከቧችኋልና፤

፳፮፤ አዋልደ ፡ ሕዝብየ ፡ ቅንታ ፡ ሠቀ ፡
ወደያ፡ሐመደ፡ውስተ፡ርእስክን፤
የወገኖቼ ፡ የእስራኤል ፡ ሴቶች ፡
ልጆች፡ማቅ፡ምንጣፍ፡ታጠቁ፤ማቅ፡
ምንጣፍ፡ልበሱ፤(እመት)፡ትቢያም፡
በራሳችሁ፡ነስንሱ፤

ወላህዋ፡ላሀ፡ፍቁር፤
ወዳጅ ፡ ለወዳጁ ፡ እንዲያለቅስ ፡
እናንተም ፡ ለቤተ ፡ ፰ ኤል ፡ አልቅ
ሱላት፤

እስመ፡ግብተ፡ይመጽአክሙ፡ኃሣር፤
ድንገት፡ያላሰባችሁት፡መከራ፡ይመ
ጣባችኋልና፤

፳፯፤ ወመከራ ፡ ረሰይኩከ ፡ በሕዝብየ ፡
ምኩራን፤
መከራ ፡ ብሎ ፡ ያሰማል፤ በአባር ፡
በቸነፈር፡በተፈተኑ፡በወገኖቼ፡ላይ፡
[illegible] ፡ መከራ ፡ ረገሃህ ፤

አንድም ፡ ኤርምያስ ፡ በአባር ፡ በቸ
ነፈር፡ በተፈተኑ ፡ በወገኖቼ ፡ በእስ
ራኤል ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አድርጌ ፡
አመጣሁህ፤ ሐተታ ፡ ነቢያት ፡ ትንቢ
ታቸውን ፡ ባይሰሟቸው ፤ ትምህርታ
ቸውን፡ባይቀበሏቸው፡እየጸለዩ፡በእስ
ራኤል፡አባር፡ቸነፈር፡ያመጡባቸው፡
ነበረና፤ አንድም ፡ ናቡከደነፆር ፡
በመከራ ፡ በተፈተኑ ፡ በእስራኤል ፡
መከራ፡አድርጌ፡አመጣሁህ፤ሐተታ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ቢበድሉ ፡ ከባቢሎን ፡
እግዚአብሔር፡አምጥቶታልና፤

ወተአምር፡ሶበ፡አመከርከ፡ፍኖቶሙ፤
ልቡናቸውንም ፡ በተፈታተንኸው ፡
ጊዜ ፡ በመከራው ፡ እንደ ፤ ተፈተኑ ፡
ያንጊዜ፡ታውቃቸዋለህ፤

፳፰፤ኵሎሙ፡ጽሙማን፡እሙንቱ፤
ምንም፡በመከራው፡ቢፈተኑ፡መላው፡
አያውቁም፤ደናቁርት፡ናቸው፤

ወየሐውሩ፡መብእሰ፤
በጐጻጕዕ ፡ ጎዳና ፡ ይሄዳሉ ፡ ማለት ፡
በሕገ ፡ ጣዖት ፡ በገቢረ ፡ ኃጢአት ፡
ጸንተው፡ይኖራሉ፤

ከመ፡ብርት፡ወሐፂን፡ኵሎሙ፡ዝኑላን፤
የብርት፡ወገን፡ብረት፣የብረት፡ወገን፡
ብርት ፡ ከነዚህ ፡ ዝገት ፡ እንዳይጠፋ ፡
ከነሱም ፡ ልቡና ፡ ክፋት ፡ ክህደት ፡
አይጠፋም፤አንድም፡የብርት፡ወገን፡
ብረት፣የብረት፡ወገን፡ብርት፡እነዚህ፡
ጽኑዓን ፡ እንደሆኑ ፡ እስራኤልም ፡
በዚያ ፡ ወራት ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡
የጸኑ፡ናቸው፤

፳፱፤ ደክመ ፡ ዘያመበኵሕ ፡ ምብኳሐ ፡
እሳት፤
ገባሬ ፡ ጣዖት ፡ ነው፤ ወናፍ ፡ የሚያ

www.ethiopianorthodox.org

ናፋው፡ሰው፡በዚያ፡ወራት፡እሳቱን፡
በማናፋት፡ደከመ፤

ወተክዕወ፡አረርኒ፤
አረሩ፡(እርሳሱ)፡ቀለጠ፤

ነሃቢ፡ነሀቦ፡ለእከየሙ፤
ጃን ፡ ሸላሚ ፡ አንጥረኛ ፡ ጣዖቱን ፡
ሠራው፤

ኢጸርየ፡ወኢተመስወ፤
አልጠራም ፡ አልቀለጠም ፡ ማለት፤
ተመትቶ ፡ የተሠራው ፡ ጣዖት ፡
የባሕርይ፡አምላክ፡አልሆነም፤

፴፤ብሩር፡ምኑን፡በልዎሙ፤
እናንተስ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ማለቱን ፡
ትታችሁ ፡ የተናቀ ፡ ብር ፡ ነው ፡
በሏቸው፤

እስመ፡መነኖሙ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ ንቋቸዋል፤ አቃሏቸ
ዋልና፤አንድም፡ደከመ፡ዘያመበኵህ፡
ምብኳሀ ፡ እሳት ፤ ኃጢአት ፡
ለመሥራት ፡ የሚናደድ ፡ ልቡና
ቸውን፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡
የሚመልስ ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፡ ደከመ ፤
ወተክዕወ ፡ አረርኒ፤ አእምሯቸው ፡
ጠፋ፤ ነሃቢ፡ ነሀቦ ፡ ለእከየሙ ፤ ክፋታ
ቸውን ፡ ለማራቅ ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፡
ደከመ፤ኢጸርየ፡ወኢተመስወ፤ነገር፡
ግን ፡ አእምሯቸው ፡ አልተመለሰም፤
ብሩር፡ምኑን፡በልዎሙ፤ይህንንስ፡
ትታችሁ፡የተናቁ፡ወገኖች፡በሏቸው፤
እስመ፡እግዚአብሔር፡መነኖሙ፤
እግዚአብሔር፡ንቋቸዋል፤አቃልሏቸ
ዋልና።

## ምዕራፍ፡፯

፩፤ ቃል፡ዘኮነ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡ኀበ፡
ኤርምያስ፤

ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ወደ
ነቢዩ ፡ ወደኤርምያስ ፡ የመጣ
የተነገረ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው፤ አንድም
መጥቶ፡የተነገረ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፤ ወይቤ ፡ ቁም ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ቤተ ፡
እግዚአብሔር፤
ይኸውም ፡ ቃል ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በቤተ ፡
መቅደስ ፡ በሮች ፡ በአምስቱ ፡ በስ
ድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ሔደህ ፡ ቁም ፡
አለው፤

ወአንብብ፡ህየ፡ዘንተ፡ነገረ፤
በዚያም ፡ ቁመህ ፡ ይኸንን ፡ ነገር ፡
አንብበህ ፡ ተርጕመህ ፡ ንገራቸው ፤
ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡
ስምዑ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡
ያመጣዋል፤

ወበል ፡ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሉ ፡
ይሁዳ ፡ እለ ፡ ትበውዑ ፡ ውስተ ፡ አንቀጽ ፡
ውስቴታ፡ትስግዱ፡ለእግዚአብሔር፤
ለእግዚአብሔር ፡ ልትሰግዱ ፡ በቤተ ፡
እግዚአብሔር ፡ በር ፡ የምትወጡ ፡
የምትገቡ ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ይኸንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ፡በላቸው፤

፫፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃያል ፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አምጻኤ ፡
ዓለማት፤ ወላዴ ፡ ፍጥረታት ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
አርትዑ፡ፍናዊከሙ፡ወምግባሪከሙ፡
ፍጹም ፡ ጠማማ ፡ ሥራችሁን ፡ ግዱን ፡
የቀና፡አድርጉ፡አቅኑት፤



አኀድር፡ኀቤከሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ቤት፤
ኸን፡ያደረጋችሁ፡እንደሆነ፡በዚህ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሳላችሁ ፡ በናንተ ፡
ይ፡በረድዔት፡አድራለሁ፤
ንድም ፡ አኀድር ፡ ኀቤከሙ ፡ ወው
ተ፡ዝንቱ፡ቤት፡ይላል፤ይኸን፡ያደረ
ጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ አስቀድሜ ፡
ናንተ፤ኋላም፡በዚህ፡ቤተ፡መቅደስ፡
ረድዔት፡አድርበታለሁ፤

፬፤ ኢትትአመኑ ፡ ርእሰከሙ ፡ በነገረ ፡
ሐሰት ፡ እንዘ ፡ ትብሉ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር፡
ሕነ፡ውእቱ፤
በረድዔት ፡ ሳላድርባችሁ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አድሮብናል ፡ እያላችሁ ፡
በሐሰት ፡ ነገራችሁ ፡ ራሳችሁን ፡
አትታመኑ፤
እስመ፡ኢይበቍዓከሙ፤
ይህ ፡ ሐሰቱ ፡ ነገራችሁ ፡ አይረባ
ችሁም ፤ አይጠቅማችሁምና ፤ አን
ድም ፡ ኢትትአመኑ ፡ ርእሰከሙ ፡
በነገረ ፡ ሐሰት ፡ ዘኢይበቍዐከሙ ፡
እንዘ ፡ ትብሉ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ውእቱ፤
በረድዔት ፡ ሳላድርባችሁ፤ የእግዚአ
ብሔር፡ማደሪያ፡ነን፡እያላችሁ፡በማ
ይረባችሁ፡በማይጠቅማችሁ፡ሐሰት፡
ነገራችሁ፡ራሳችሁን፡አትታመኑ፤

፭፤ለእመ፡አርታዕከሙ፡ፍናዊከሙ፡ወም
ግባሪከሙኒ፡ርቱዐ፤
የቀናውን ፡ ፍጹም ፡ ሥራችሁን ፡
ብታቀኑት ፡ አለ፤ የቀናውን ፡ ፍጹም ፡
ሥራችሁን፡ብታጠሙት፡ግን፤
ወለእመ፡ገበርከሙ፡ፍትሐ፡ማዕከለ፡ብእሲ፡
ወማዕከለ፡ቢፁ፤
በወንድማማች፡መካከልና፡በባልንጀ
ራሞች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡
ጠንቅቃችሁ ፡ ብትፈርዱ፤ አንድም ፡

በባልና፡በሚስት፡መካከል፡እውነት፡
ብትፈርዱ፤ ሐተታ ፡ ቢፅ ፡ ያላት ፡
ሚስት፡ናት፡

ንግበር ፡ ሎቱ ፡ ቢፀ ፡ ዘትረድኦ ፡
እንዲል፤

፮፤ ወኢተአገልከሙ ፡ ዕቤረ ፡ ወዕጓለ ፡
ማውታ፡ወፈላሴ፤
ቀኗ ፡ (ዕድሜዋ) ፡ የገፋውን ፡
ባልቴትና፡እናት፡አባቱ፡የሞቱበት፡
ድኃ፡አደጉን፡ልጅ፡መጻተኛውንም፡
ባትቀሙ፤

ወኢከዐውከሙ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ፡ ውስተ ፡
ዝንቱ፡ቤት፤
በዚህም፡ቤተ፡መቅደስ፡ንጹሕ፡ደም፡
ባታፈስሱ፤

ወኢሖርከሙ፡ወኢተለውከሙ፡አማልክተ፡
ነኪር፡ለእኪትክሙ፤
ክፋታችሁም ፡ ሊገለጥባችሁ ፡ የከነ
ዓንን፡ጣዖት፡ብትከተሉት፤
አንድም፡አማልክተ፡ነኪራነ፡በእኪ
ትክሙ፡ይላል፤ክፋታችሁን፡በምት
ሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡
ጣዖታቱን፡ተከትላችሁ፡ባትሔዱ፤

፯፤ አነብረከሙ ፡ ውስተ ፡ ብሔርከሙ ፡
ውስተ፡ምድር፡እንተ፡ወሀብክዎሙ፡ለአበ
ዊከሙ፡እምዓለም፡ወእስከ፡ለዓለም፤
ይኸን፡ሁሉ፡ባታደርጉ፡ቀድሞ፡ለአ
ባቶቻችሁ፡ዛሬም፡ለናንተ፡ከጥንት፡
ጀምሮ፡ለዘላለሙ፡ልትኖሩባት፡በሰ
ጠኋችሁ፡አገር፡በከንዓን፡አኖራች
ኋለሁ፤ ሐተታ ፡ ብሔርከሙ ፡ አላት፤
ከነዓንን ፡ ቀድሞም ፡የሌም ፡ ዕጣ ፡
ናትና ፡ ኋላም ፡ በኢያሱ ፡ ወርሰዋ
ታልና፡ውስተ፡ብሔርከሙ፡ያለውን፡

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ስለምን ፡
ደገመው ፡ ቢሉ፤ ፍጹመ ፡ ለማለት ፡
ነው፤ አንድም ፡ ብሔርክሙ ፡ መላዋ ፡
ከነዓን ፡ ናት ፤ ምድር ፡ ተካፍለው ፡
የያዟት፡ምድረ፡ርስታቸው፡ናት፤

፰፤ ወእመሰ ፡ ተወከልክሙ ፡ ላዕለ ፡ ነገረ ፡
ሐሰት፡ዘለምንትኒ፡ኢይበቍዓክሙ፡

ለምንም ፡ ለምን ፡ በማይረባችሁ ፡ በማ
ይጠቅማችሁ ፡ በሐሰተኛው ፡ ነገር ፡
ብትታመኑ፡ግን፡አለ፤እኔ፡በረድዔት፡
ሳላድርባችሁ ፡ እናንተ ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ማደሪያ፡ነን፡ብትሉ፡ግን፤

፱፤ወቀተልክሙ፤

ነፍስ፡ብትገድሉ፤

ወሰረቅሙኒ፤

የሰው፡ገንዘብ፡ብትሰርቁ፤

ወዘመውክሙ፤

ብትሰስኑ፤

ወመሐልክሙ፡በዓመፃ፡

በሐሰት፡ነገርም፡ብትምሉ፤

ወዐጠንክሙ፡ለበዓል፡

ለጣዖቱ ፡ ብታጥኑ ፤ ሐተታ ፡ በዓል ፡
የሚለው፡የሰው፡ምስል፡ነው፤

ወሖርክሙ ፡ ወተለውክሙ ፡ አማልክተ ፡
ነኪር፡ዘኢተአምሩ፤

ዘኢተአምሩ ፡ በማለት ፡ ደግሞታል፤
አንድም ፡ ቀድሞ ፡ የማታውቋቸው ፡
የከነዓንን፤ አንድም ፡ አማልክተ ፡
ነኪራነ ፡ ዘኢየአምሩ ፡ ይላል፤ ምንም
ምን ፡ የማያውቁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡
ጣዖታቱን ፡ ተከትላችሁ ፡ ብትሔዱ ፡
ግን፤

በዝ፡ይረከበክሙ፡እኩይ፡

በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ክፉው ፡
ነገር፡ያገኛችኋል፤

፲፤ ወመጻእክሙ ፡ ወቆምክሙ ፡ ቅድሜየ ፡
ውስተ፡ዝንቱ፡ቤት፡ኀበ፡ተሰምየ፡ውስቴቱ፡
ስምየ፡ህየ፡

ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤትና ፡ ህየ ፡ አንድ
ወገን፡ነው፤ይኸን፡ሁሉ፡በደል፡በደ
ችሁኝ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ በቤተ
መቅደስ ፡ መጥታችሁ ፡ ከፊቴ
ቆማችሁ፡ብትለምኑኝ፤

ወትቤሉ ፡ ሥልጣን ፡ ብነ ፡ ለገቢረ ፡ ኵሉ
ርኵስ፡

ጣዖቱን ፡ ሠርቶ ፡ ለማቆም፤ አንድም
ለገቢረ ፡ ኵሉ ፡ ርኵስ ፡ ይላል
ኃጢአትን ፡ ለመሥራት ፡ ሥልጣን
አለን፡ትሉኛ፡እንደሆነ፤

፲፩፤ ቦኑ ፡ በዓተ ፡ ፈያት ፡ ውእቱ ፡ ቤትየ
ኀበ፡ተሰምየ፡ስምየ፡ውስቴቱ፡ህየ፤

ስሜ ፡ የተጠራበት ፡ ቤቴ ፤ ቤተ
መቅደስ፡በውኑ፡የሌባ፡ዋሻ፡የቀማኛ
ጋሻ፡ነውን፤

ወናሁ ፡ ርኢክሙ ፡ አንትሙ ፡ በአዕይን
ቲክሙ፡ ወአነሂ ፡ ርኢኩ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡

እነሆ ፡ እናንተ ፡ በዓይነ ፡ ልቡናችሁ፤
አንድም ፡ በዓይነ ፡ ሥጋችሁ ፡ ወደ ፡
ኃጢአቱ፤ ወደጣዖቱ ፡ አያችሁ፤ ተመለ
ከታችሁ፤ እኔም ፡ በዓይነ ፡ መዓቴ ፡
ወደናንተ ፡ አየሁ፤ ተመለከትሁ፤ አለ ፡
እግዚአብሔር ፤ የፍየል ፡ ዓይን ፡ ወደ ፡
ቅጠል ፤ የነብር ፡ ዓይን ፡ ወደ ፡ ፍየል ፡
እንዲሉ፤

፲፪፤ ሑሩ ፡ ወርእዩ ፡ ውስተ ፡ ቤትየ ፡ ዘሴሎ፡
ኀበ፡ኀደረ፡ስምየ፡ህየ፡ቀዲሙ፤

እኛም፡እንደፈርም፡ቤተ፡መቅደስም፡



ድሞ ፡ ስሜ ፡ ይጠራባት ፡ የነበረ ፡
ሴሎ ፡ የነበረች ፡ ቤቴ ፤ ቤተ ፡
ቅደስን ፡ ሒዳችሁ ፡ እዩ ፤ ተመ
ከቱ፤

ርእዩ፡ዘገበርክዎ፡ሎቱ፡እምገጸ፡እከዮሙ፡
ሕዝብየ፡እስራኤል፡

ቱ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡
ልጁቻው ፡ ከእስራኤል ፡ በደል ፡
ተነሣ፡ያደረግሁበትን፡ነገር፡ሁሉ፡
ዳችሁ፡እዩ፤

፲፫፤ ወይእዜኒ፡እስመ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ዘገበ
ክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ናንተ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡ ስለሠ
ራችሁ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

በብኩክሙ፡ወኢሰማዕክሙኒ፡

ቀድሞ ፡ በዐበይት ፡ ነቢያት ፡ አድሬ ፡
አስተማርኋችሁ፤ በዐበይት ፡ ነቢያት ፡
አድሬ፡ያስተማርኋችሁን ፡ ቃል ፡ አል
ሰማችሁም፤

ጸዋዕኩክሙ፡ወኢያውሣእክሙኒ፡

ኋላም ፡ በደቂቅ ፡ ነቢያት ፡ አድሬ ፡ አስ
ተማርኋችሁ፤ በደቂቅ ፡ ነቢያት ፡
አድሬ፡ያስተማርኳችሁን፡ትምህርት፡
አልተቀበላችሁም፤ አንድም ፡ ነበብ
ኩክሙ፤ ቀድሞ ፡ በዐበይት ፡ ነቢያት ፡
በደቂቅ ፡ ነቢያት ፡ አድረ ፡ አስተማር
ኋችሁ፤ ወኢሰማዕክሙኒ ፡ በዐበይት ፡
ነቢያት፡በደቂቅ፡ነቢያት፡አድሬ፡ያስ
ተማርኋችሁን፡ ትምህርት ፡ አልተቀበ
ላችሁኝም፤ጸዋዕኩክሙ ፡ ኋላም ፡ እኔ ፡

፲፬፤ ወአነሂ ፡ እሬስዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ፡ ኀበ ፡
ተሰምየ ፡ ስምየ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘቦቱ ፡ ትትዌከሉ
አንትሙ፤

ቀድሞ ፡ በዐበይት ፡ ነቢያት ፡ በደቂቅ ፡
ነቢያት ፡ አድሬ ፡ አስተምሬያችሁ ፡
ካልተመለሳችሁስ፤እናንተ፡አይፈርስ
ብንም ፡ ብላችሁ፡ የምትታመኑበት ፡
ስሜም ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የተጠራበት፡
ቤቴ፡ቤተ፡መቅደስን፡በሴሎም፡እንደ
ፈረሰ፡ቤተ፡መቅደስ፡አደርገዋለሁ፤

ወብሔረኒ ፡ ዘወሀብክዎሙ ፡ ለአበዊክሙ ፡
በከመ፡ረሰይክዋ፡ለሴሎ፡

ሴሎን፡እንዳጠፋሁ፡ላባቶቻችሁ፡የሰ
ጠኋትን፡አገር፡አጠፋታለሁ፤

፲፭፤ ወእገድፈክሙ ፡ እምቅድመ ፡
ገጽየ፡ ከመ ፡ ገደፍክዎሙ ፡ ለአኃዊክሙ ፡
ለኵሉ፡ዘርዐ፡ኤፍሬም፡

ለኵሉ ፡ ዘርዐ ፡ ኤፍሬምና ፡ ለአኃ
ዊክሙ ፤ አንድ ፡ ወገን ፤ ከነገደ ፡
ኤፍሬም፡የተወለዱ፡ወንድሞቻችሁ፡
ዓሥሩን ፡ ነገድ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ከባለ
ሟልነት ፡ እንዳወጣኋቸው ፡ ዛሬም ፡
እናንተን፡ወንድሞቻቸውን፡ሁለቱን፡
ነገድ፡ከባልሟልነት፡አወጣችኋለሁ፤

፲፮፤ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡አንተሂ፡
ኢትጸሊ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ሕዝብ፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡ አለኝ ፤ ስለነዚህ ፡ ወገኖች ፤
አንድም፡ለዝ፡ሕዝብ፡ይላል፡ለነዚህ፡
ወገኖች፡አትለምንላቸው፤

ወኢታስተብቍዕ፡ከመ፡እሣሃሎሙ፡

ይቅርም ፡ እንድላቸው ፡ አታማል

www.ethiopianorthodox.org

እንዲነሳ፡ለማጠየቅ፤አንድም፡እሱን፡
ሲበድሉ ፡ ኑረው ፡ መከራ ፡ በመጣ
ባቸው፡ጊዜ፡ቢለምኑት፤

ወኢትጸሊ፡
ኢትጸሊና፡ወኢትጸሊ፡አንድ፡ወገን፤
ወኢትምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ በእንቲአሆሙ ፡
ወኢይሰምዐከ፤እስመ፡ኢይሰምዐከ፡
ሲል ፡ ነው ፤ ብትማልደኝ ፡ ብትለም
ነኝም ፡ አልሰማህምና፤ እነሱን ፡
ለማማለድ ፡ ወደኔ ፡ አትምጣ ፤
አንድም፡ ወኢይሰምዐከ ፡ እንዳለም ፡
ይሆናል፤አንተ፡እነሱን፡ለማማለድ፡
ወደኔ፡አትምጣ፡እኔም፡አልሰማህም፡
አለኝ፤

፲፯፡ ኢትሬኢኑ ፡ ዘገብሩ ፡ በአህጉረ ፡
ይሁዳ፡ወበፍናዊሃ፡ለኢየሩሳሌም፡
ኢይሰምዐከ፡ብሎት፡ነበረና፡ምነዋ፡
ስለምንህ ፡ የማትሰማኝ ፡ ትለኝ፡
እንደሆነ ፡ በይሁዳ ፡ አገርና ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ በጎዳናዋ ፤ አንድም ፡ በመን
ደሩዋ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አታ
ይምን፡አትመለከትምን፤

፲፰፡ ደቂቆሙ፡ያመጽኡ፡ዕፀወ፡
ዘገብሩ ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤ ልጆቻ
ቸው ፡ ለጣዖቱ ፡ አምባሻ ፡ የሚጋግ
ሩበት፡እንጨቱን፡እየሰበሩ፡ያመጣሉ፤

ወአበዊሆሙኒ፡ያነድዱ፡እሳተ፤
አባቶቻቸውም ፡ ያመጡትን ፡ እን
ጨት ፡ እየፈለጡ ፡ እሳት ፡ ያነድዳሉ ፡
ኃጢአት፡ይሠራሉ፤

ወአንስቲያሆሙኒ፡የሐርፃ፡ከመ፡ይግበሩ፡
ዳፍንተ፡ለንግሥተ፡ሰማይ፡
ሚስቶቻቸውም፡ለሰማይ፡እመቤት፡
ለፀሐይ ፡ ለጨረቃ ፡ አምባሻው

ሊጋግሩ ፡ዱቄቱን ፡ ይፈጫሉ ፡ አ
ከሆነ፡በኋላ፡እንዲህ፡አለ፤አንድ
እንደ ፡ ትግሬ ፡ ገርድፈው ፡ ይሰል
ታልና፤

፲፱፡ ወሞፃሕተ ፡ ያወጽሑ ፡ ለአማ
ቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ያምዕዑኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚ
ብሔር፡
እኔን፡ያሳዝኑ፡ዘንድ፡ለጣዖታቸው
ወይኑን ፡ ፍልቅ ፡ አድርገው
ያፈስሳሉ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር
አንድም፡ለጣዖታቱ፡ወይኑን፡ፍል
እያደረጉ፡ያፈስሳሉ፤

ከመ፡ያምዕዑኒ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ይኸንም ፡ ማድረጋቸው ፡ እኔን
ያሳዝኑ፡ መስሏቸው ፡ ነው ፤ አንድም
እኔን፡የጎዱ፡መስሏቸው፡ነው፤

ኪያየ፡ያምዕዑኒ፡
ይኸን፡ሁሉ፡የሚያደርጉ፡እኔን፡ይ
ዱኛልን፡እኔን፡ያሳዝኑኛልን፤

አኮኑ፡ለርእሶሙ፡ከመ፡ይትኃፈር፡ገጸሙ፤
ፊታቸው ፡ ገጸ ፡ ረድዔቴን ፡ አጥቶ
ያፍር፡ዘንድ፡ራሳቸውን፡የሚያሳዝ
ራሳቸውን፡የሚጎዱ፡አይደለምን፤

፳፡ወባሕቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር
ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ
አለ፤

ናሁ ፡ መዓትየ ፡ ወመቅሠፍትየ ፡ ተከዐወ
ላዕለ፡ዝ፡ብሔር፡
እነሆ ፡ ፍጹም ፡ ቍጣዬ ፡ መቅሠፍቴ
ባሉበት ፡ አገር ፡ በዝቶ ፡ ተደረገ
አንድም ፡ መዓት ፡ የጊዜው ፤ መቅ
ሠፍት ፡ የዘገየው ፡ ነው ፤ አንድም
መዓት፡የልብ፡የሐልዮ፡መቅሠፍት
የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሁሉ



ላዕለ፡ሰብእ፡ወላዕለ፡እንስሳ፡
በሰው፡በከብቱ፡ጦር፡መቅሠፍት፤

ወላዕለ፡ዕፀው፡ዘገዳም፡
በምድረ፡በዳ፡ባሉ፡እንጨቶችም፤

ወላዕለ፡ኵሉ፡ፍሬያተ፡ምድር፡
በአዝመራውም፡ሁሉ፡ድርቅ፡በዝቶ፡
ተደረገበት፤

ትነድድ፡ወኢትጠፍዕ፡
መቅሠፍቲቱ ፡ በዝታ ፡ ትነድዳለች ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አትጠፋም ፤ ሐተታ፡—
መቅሠፍት ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ይጠ
ፋልና፤

፳፩፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጸባዖት፡አምላከ፡፳ኤል፡
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡በዚያ፡ወራት፡እንዲህ፡አለ፤

አስተጋብኡ ፡ መባዓክሙ ፡ ላዕለ ፡ ምሥዋ
ዒክሙ ፡ ወብልዑ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡
ኢይቤሎሙ፡ለአበዊክሙ፡
ጥንቱንም ፡ አባቶቻችሁን ፡ መሥዋ
ዕቱን ፡ በምትሠዉበት ፡ በምሥዋዑ ፡
ላይ፡መባዓችሁን፡ሰብስባችሁ፡ሠዉ፤
ተረፈ፡መሥዋዕቱንም፡ተመገቡ፡አላ
ልኋቸውም፤

፳፪፡ ወኢአዘዝክዎሙ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡
አውጻእክዎሙ ፡ እምድረ ፡ ግብፅ ፡ በእንተ ፡
መሥዋዕት፡ወበእንተ፡ቍርባን፡
ከግብፅ፡አገርም፡ባወጣኋቸው፡ቀን፡
ተረፉን፡የሚጤሰውን፡አቅርቡልኝ፡
ብዬ፡አላዘዝኋቸውም?

፳፫፡ ዳዕሙ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ አዘዝክዎሙ ፡
ወእቤሎሙ፡
ለአባቶቻችሁስ ፡ ይኸንን ፡ ነገር ፡
...አዘዝኋቸው... እንጂ፤

ስምዑኒ፡ቃልየ፡
አዘዝክዎሙ ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤
ግዱን፡የነገርኋችሁን፡ቃል፡ስሙኝ፤

ወእከውነክሙ፡አምላከክሙ፡
ይኸን ፡ ያደረጋችሁልኝ ፡ እንደሆነ ፡
እኔ፡ ለናንተ ፡ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡
አባት፡እሆናችኋለሁ፤

ወአንትሙኒ፡ትከውኑኒ፡ሕዝብየ፡
እናንተም፡ለኔ፡የፍቅር፡የሃይማኖት፡
ልጆች ፡ ትሆኑኛላችሁ ፡ ብዬ ፡ አዘዝ
ኋቸው፤

ወሑሩ፡በኵሉ፡ፍናውየ፡ዘአዘዝኩክሙ፤
ይኸንንስ፡ትታችሁ፡እኔ፡ባዘዝኋችሁ፡
ሕግ፡ሥርዓት፡ጸንታችሁ፡ኑሩ፤

ከመ፡ይኩን፡ሠናይ፡ለክሙ፡
በጎ ፡ ረድዔት ፡ ይደረግላችሁ ፡ ዘንድ ፤
አንድም፡ሠናየ፡ረድዔቱ፤በጎ፡ሁኖ፡
ይደረግላችሁ ፡ ዘንድ ፡ በሕጌ ፡
በሥርዓቴ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡
አልኋቸው፤

፳፬፡ ወኢሰምዑኒ ፡ ወኢያጽምዑኒ ፡
በዕዝኖሙ፡
በዕዝነ፡ሥጋቸው፤አንድም፡በዕዝነ፡
ልቡናቸው፡ፈጽመው፡አልሰሙኝም፤
አላደመጡኝም፤

ዳዕሙ ፡ ሖሩ ፡ በግዕዘሙ ፡ በከመ ፡ እከየ ፡
ልቦሙ፡
እንደልቡናቸው ፡ ክፋት ፡ መጠን ፡
በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ጸንተው ፡ ኖሩ ፡
እንጂ፤

ወገብዑ፡ድኅሬሆሙ፡
ወደኋላቸው ፡ ተመለሱ ፡ አለ ፤
ወደገቢረ፡ኃጢአት፡ወደ፡አምልኮ፡
ጣዖት፡ተመለሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢአመልዑ፡ቅድሚሆሙ፤
ወደፊታቸው፡አልገሠገሡም፤በሕገ፡
ኦሪት ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡
አልጸኑም፤

፳፭፤ እምአመ ፡ ወጽኡ ፡ አበዊሆሙ ፡
እምድረ፡ግብፅ፡ወእስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡
አባቶቻቸው ፡ ቀድሞ ፡ ከግብፅ ፡
ከወጡ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡
ድረስ፤

ወፈነውኩ፡ኀቢሆሙ፡ኵሎሙ፡አግብርትየ፡
ነቢያተ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፡እፌንዎሙ፤
ፈነውኩና፡እፌንዎሙ፡አንድ፡ወገን፤
በመዓልትም፡በሌሊትም፡ተግተው፡
ነቅተው፡የሚያስተምሯቸው፡አገል
ጋዮቼ፡ነቢያትን፡ሁሉ፡ምክሯቸው፡
አስተምሯቸው ፡ ብዬ ፡ ወደነሱ ፡
ላክኋቸው፤

፳፮፤ ወኢሰምዑኒ ፡ ወኢያጽምዑኒ ፡
በዕዝኖሙ፤
በዕዝነ፡ሥጋቸው፤አንድም፡በዕዝነ፡
ልቡናቸው ፡ ነቢያትን ፡ ካህናትን ፡
ፈጽመው፡አልሰሙልኝም፤

ወአግዘፉ፡ክሣዶሙ፡እምነ፡አበዊሆሙ፤
ከአባቶቻቸውም ፡ ይልቅ ፤ አንድም ፡
ከአባቶቻቸው፡የተነሣ፤አንድም፡ከአ
ባቶቻቸው፡ተለይተው፡ክሣደ፡ልቡና
ቸውን፡አጸኑ፤

፳፯፤ ወበሎሙ፡ዘ፡ነገረ፡ለሕዝብ፡ወኢይ
ሰምዑከ፤
ይኽንን፡ነገር፡ለሕዝቡ፡ንገራቸው፡
ወኢይሰምዑከ፤
እነሱ፡ግን፡አይሰሙህም፤አንድም፡
አይሰሙህም ፡ እንጂ ፡ አንተ፡ ግን ፡
ይኽንን፡ነገር፡ለሕዝቡ፡ንገራቸው፤
ወትሰብኮ፡ሎሙ፡ወኢይሰጠዉከ፡
አንተ ፡ ለነሱ ፡ ምክራቸው ፤ አስተም
ራቸው፡እነሱ፡ግን፡አይቀበሉህም፤

፳፰፤ ወበሎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እለ
ኢይሰምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አምላኮሙ፡
የፈጣሪያቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ሕግ፡የማይሰሙ፤

ወኢተምህሩ፡ሥርዓቶ፡
ሥርዓቱንም ፡ ሕጉንም ፡ ላልተማሩ፡
ለነዚህ፡ወገኖች፡እንዲህ፡በላቸው፤
ጠፍዓት፡ሃይማኖት፡
ሃይማኖት ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ እልም፡
ድርግም፡ብላ፡ጠፋች፤

ወተመትረ፡እምአፉሆሙ፤
ሕጉም፡ሥርዓቱም፡ከአንደበታቸው፡
ተመተረ ፡ አለ ፤ ሕጉም ፡ ሥርዓቱም፡
በአንደበታቸው፡አልተነገረም፡ብለህ፡
ንገራቸው፤

፳፱፤ቅርጺ፡ርእሰኪ፡ወግድፊ፡
ቤተ ፡ እስራኤል ፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ፡
እንደዱሮው ፡ (እንደቀድሞው) ፡
መደላደል ፡ መቀማጠል ፡ የለምና ፡
ጠጉርሽን፡ቈርጠሽ፡ጣዪው፤

ወንሥኢ፡በከናፍርኪ፡ሰቆቃወ፤
በአንደበትሽም፡ሙሾውን፡አውጪ፤
እስመ፡መነኖሙ፡እግዚአብሔር፡
ወገኖችሽ፡እስራኤልን፡ፈጣሪያቸው፡
እግዚአብሔር ፡ ንቋቸዋል ፤ አቃሏቸ
ዋልና፤

ወገደፈ፡ትውልደ፡መዓት፡
ቍጣ ፡ (የተመሉ) ፡ የሚስማማቸው ፡
እስራኤልን ፡ በመከራው ፡ ጣላቸው ፤
አንድም ፡ መዓት ፡ ያለው ፡ ጣዖቱን ፡
ነው፤መዓተ፡አረሚ፡መዓተ፡ዳርዮስ፡



ኤልን ፤ አንድም ፡ መዓቱ ፡ የታዘዘ
ባቸው ፡ እስራኤልን ፡ በመከራው ፡
ጣላቸው፤

ወኢኀለቆሙ፡ለመሐዛት፡
(ጐልማሶችን) ፡ ደቦሎቻቸውንም ፡
ካሉ፡ከሌሉ፡አልቈጠራቸውም፤

፴፤ እስመ ፡ ገብሩ ፡ እኩየ ፡ ደቂቀ ፡ ይሁዳ ፡
በቅድሜየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ይልማ፡ ይስማ ፡ ብለው ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡
ሥራ፡ሠርተዋልና፡ካሉ፡ከሌሉ፡አል
ቆጠራቸውም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአንበሩ ፡ ርኵሶሙ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ኀበ ፡
ተሰምየ፡ስምየ፡ከመ፡ያርኵስዎ፡
ገብሩ፡እኩየ፡ደቂቀ፡ይሁዳ፡ያለውን፡
አመጣ፤ይኽውም ፡ ሊታወቅ ፡ ቤተ ፡
መቅደስን ፡ ሊያረክሱ ፡ ስሜ ፡ በሚጠ
ራበት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ኃጢአታ
ቸውን ፡ ሠሩ ፤ አንድም ፡ ጣዖቱን ፡
አቆሙ ፡ አለ ፤ ምናሴ ፡ ባምስቱ ፡
በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ሥዕለ፡
ንሥር፡አቁሞ፡ነበረና፤

፴፩፤ ወሐነፁ ፡ ምሥዋዐ ፡ ለጣፌጥ ፡
በውስተ ፡ ቈላተ ፡ ወልደ ፡ ሔኖም ፡ ከመ ፡
ያውዕዩ፡ደቂቆሙ፡ወአዋልዲሆሙ፡በእሳት፡
ዘኢአዘዝክዎሙ፡ወዘኢሐለይኩ፡በልብየ፤
ያደርጉታል ፡ ብዬ ፡ በልቤ ፡ ያላሰብ
ሁትን፤አንድም፡ይተዉታል፡ብዬ፡
በልቤ ፡ ያላሰብሁትን ፡ ከዚህ ፡ አስቀ
ድሞም ፡ አድርጉት ፡ ብዬ ፡ ያላዘዝኋ
ቸውን ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻቸውንና ፡
ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡
ሊያቃጥሉ፡በነገደ፡ዛብሎን፡አለቃ፡
ርስት ፡ ጉልት ፡ ለቆመ ፡ ጣፌጥ ፡
ለበዓል፡ጣዖት፡ምሥዋዕ፡ጸፈጸፉ፤
አንድም፡ሐነፁ፡ምሥዋዐ፡በጣፌጥ፡
ይላል፤በነገደ፡ዛብሎን፡አለቃ፡ርስተ፡
ጉልት ፡ በቆመ ፡ መቅደስ ፡ ጣዖት ፡
ምሥዋዑን፡ጸፈጸፉ፤

፴፪፤ በበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡
መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እንዲህ ፡ አድርገው ፡ አብዝተው ፡
ስለበደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እነሆ ፡
እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፡አለ፤
ወኢይብሉ፡እንከ፡ጣፌጥ፡
በዚያ፡ወራት፡ጣዖቱ፡ይህ፡ነው፤
ወቈላተ፡ወልደ፡ሔኖም፡
የነገደ ፡ ዛብሎን ፡ አለቃም ፡ ርስተ ፡
ጉልት፡ይህ፡ነው፡አይሉም፤ሐተታ፡
ጠፍቶ፡ተፈቶ፡ነው፤
ዳዕሙ፡ቈላተ፡ቅቱላን፡
የእስራኤል ፡ አርበኞች ፡ የሞቱበት ፡
ቈላ፡ነው፡ይሉታል፡እንጂ፤

ወይቀብርዎሙ፡በጣፌጥ፡
ሙተው፡አልቀው፡በጣፌጥ፡ይቀብሯ
ቸዋል ፡ አለ ፤ በኀሡር ፡ ቦታ ፡ ይቀብሯ
ቸዋል፤

እስመ፡አልቦሙ፡መካን፡
የሚቀበሩበት፡ክቡር፡ቦታ፡የለምና፤
አንድም፡ወይቀብርዎሙ፡በጣፌጥ፡
በጣፌጥ፡አልቀው፡የሚቀብራቸው፡
አጥተው ፡ በከርሠ ፡ አራዊት ፡
ይቀበራሉ፤

እስመ፡አልቦሙ፡መካን፡ኀበ፡ይትቀበሩ፡
የሚቀበሩበት፡ክቡር፡ቦታ፡የለምና፤

፴፫፤ ወይከውን ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ለዝ ፡
ሕዝብ ፡ መብልዐ ፡ ለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወለአ
ራዊተ፡ገዳም፡
በዚያ ፡ ወራት ፡ የኒህ ፡ ወገኖች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሬሳቸው ፡ ቀን ፡ ለአዕዋፍ ፡ ሌሊት ፡
ለአራዊት፡ምግብ፡ይሆናል፤

ወአልቦ፡ዘይቀብሮሙ፡

ከአዕዋፍ፡ከአራዊት፡የተረፉትንም፡
የሚቀብራቸው ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡
የለም፤

፴፬፤ ወእሥዕር፡እምአህጉረ፡ይሁዳ፡ወእ
ምፍናወ፡ኢየሩሳሌም፡ቃለ፡ኃሤት፡ወቃለ፡
ፍሥሓ፡ቃለ፡መርዓዊ፡ወቃለ፡መርዓት፡

ከይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ጎዳናዎች ፤ አንድም ፡ ከመንደሮቹ ፡
የተድላ ፡ የደስታውን ፡ ቃል ፡ እገሌ ፡
እገሊትን ፡ አጨ ፤ እገሊት ፡ እገሌን ፡
አጨች፡ብለው፡የሚናገሩትን፡ቃል፤
አንድም ፡ ባሦርቱ ፡ የሚዘፍኑት ፡
ዘፈን፡ ጨዋታ ፡ አለና ፡ ያንን ፡
አጠፋለሁ፤

እስመ፡ይማስን፡ኵሉ፡በሐውርት፡

አውራጃው፡ሁሉ፡እልም፡ድርግም፡
ብሎ፡ይጠፋልና፤አንድም፡የሚጠፋ፡
ስለሆነ።

## ምዕራፍ፡፰

፩፤ ይእተ፡አሚረ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡
አለ፤

ያወጽኡ፡አዕጽምተ፡ነገሥተ፡ይሁዳ፡ወአዕ
ጽምተ፡መላእክቲሆሙ፡

በጼዋዌ ፤ አንድም ፡ በኢዮስያስ ፡
ዘመን፡የይሁዳ፡ነገሥታትንና፡የመኳ
ንንቱን፡አጥንት፡ያወጡታል፤

ወአዕጽምተ፡ነቢያት፡ወአዕጽምተ፡ካህናት፡

የነቢያትንና፡የካህናቱን፡አጥንት፤

ወአዕጽምቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ፡
ኢየሩሳሌም፡እምነ፡መቃብሪሆሙ፡

በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ የሕ
ቡንም ፡ አጥንት ፡ ከመቃብራቸው
ያወጡታል ፤ ኢዮስያስ ፡ የቆሙትን
እያረደ፡የተቀበሩትን፡እያወጣ፡እን
ቃጠላቸው ፤ አንድም ፡ በዳዊት
በሰሎሞን፡መቃብር፡ወርቅ፡ብር፡እ
ደተገኘ፡ወርቅ፡ብር፡ይገኝባቸዋል
ብለው፤

፪፤ ወይሰጥሕዎ ፡ ለፀሐይ ፡ ወለወርኅ
ወለኵሉ፡ከዋክብት፡

ይኸንንም ፡ አጥንቱን ፡ ከመቃብሩ
አውጥተው፡ለፀሐይና፡ለጨረቃ፡ለ
ዋክብት፡ያሰጡታል፤

ወለኵሉ፡ሠርጓተ፡ሰማይ፡ዘአፍቀሩ፡

ለወደዱት ፡ ለሰማይም ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ
ያሰጡታል፤

ወዘሎሙ፡ተቀንዩ፡

ለተገዙላቸው፤

ወዘተለዉ፡ድኅሬሆሙ፡

በአምልኮት፡ለተከተሏቸው፤

ወዘፈቀዱ፡

ዘአፍቅሩ፡ያለውን፡ወዘፈቀዱ፡ብሎ፡
ደገመው፤ለሚወዱት፡ለሰማይ፡ጌጥ፡
ሁሉ፡ለፀሐይ፡ለጨረቃ፡ለከዋክብት፡
ያሰጡታል፤ አንድም ፡ ስንኳን ፡ የነ
ቢያት፡የካህናት፡የነገሥታት፡የመኳ
ንንቱን፡የሰዎቹን፡አጥንት፡የሰማይ፡
ጌጥ፡የሚሆን፡የፀሐይ፡የጨረቃ፡የከ
ዋክብት ፡ ምስል ፡ ካለበት ፡ አው
ጥተው፡ይጥሉታል፤

ኢይበከይዎሙ፡

እኩሌቶች፡ [illegible]
ተውም፤



ኢይቀብርዎሙ፡

መዶች ፡ ዘመዶቻቸውን ፤ ልጆች ፡
ናት፡አባታቸውን፡አክብረው፡አይ
ብሩዋቸውም፤

ብልያ፡ይከውኑ፡ውስተ፡ገጸ፡ምድር፡

ላ ፡ ያለበት ፡ ነው፤ በአደባባይ ፡
ልቀው፡ወድቀው፡ቀን፡ለአዕዋፍ፤
ሌሊት፡ለአራዊት፡ብዝበዛ፡ይሆናሉ፡
ንጂ፤

ኢይቀብርዎሙ፤ይህን፡ባለው፡ወይከ
ድዎሙ ፡ ከመ ፡ ድኵዕ ፡ ውስተ ፡
ምድር ፡ ይላል ፤ አስማርኬ ፡ በወሰድ
ቸው ፡ ቦታ ፡ እንደፋንድያ ፡ ይረጋግ
ቿቸዋል፤

፫፤ እስመ ፡ አብደሩ ፡ ሞተ ፡ እምነ ፡
ሕይወት፡

ቁሙ ፡ ከሕይወት ፡ ሞትን ፡ ወደ
ዋልና፤አንድም፡ከሕይወት፡ከእግዚአ
ብሔር ፡ ሞት ፡ ጣዖቱን ፡ ወደ
ዋል ፡ መርጠዋልና ፤ ሐተታ ፡ ሞት፡
አለው፤ጣዖቱን፡በግብሩ፡ሞተ፡ሥጋ፡
ሞተ ፡ ነፍስ ፡ የሚያመጣባቸው ፡
ስለሆነ፡ነው፤ሕይወት፡ያለው፡አያሳ
ትትም፤

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ዘአትረፉ ፡
ምይእቲ፡ ትውልድ ፡ እኪት ፡ በኵሉ ፡
ሐውርት፡ኅበ፡እወስዶሙ፡ህየ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡

ዚች ፡ ከክፉ ፡ ወገን ፡ ከቤተ ፡
እስራኤል፡አሕዛብ፡ያስቀሩዋቸው፡
ዘአትረፉ ፡ አለ፤ ከብዛት ፡ ቀርተው፤
አንድም ፡ ጦር ፡ መጣ ፡ መጣ ፡
ሲሉዋቸው፡ሸሽተው፡የቀሩ፡ናቸው፤
ከሞት ፡ የቀሩ ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡
[illegible] አገር ፡
ሁሉ፡ሆየ፡ይመውቱ፡የለበት፡ነጡ፤

በዚያ፡ቦታ፡ይሞታሉ፡አለ፤እግዚአ
ብሔር፤

ሐተታ፡ቤተ፡እስራኤልን፡ተማርከ፡
በሄደችበት ፡ አገር ፡ ድንኒ ፡ ወንት
ዓዶኪ፡ብለዋታልና፤

፬፤ ወበሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በላ
ቸው፤

ዘወድቀአ፡ኢይትነሣእኑ፡

የወደቀ፡ሰው፡አይነሣምን፤

ወዘስሕተአ፡ኢይትመየጥኑ፡

የሳተስ፡የበደለስ፡ሰው፡በንስሐ፡አይ
መለስምን፤

ወዘወጽአ፡አፍአ፡ኢይገብእኑ፡

ወደ፡ውጭ፡የወጣ፡ሰው፡ወደ፡ቤቱ፡
አይመለስምን፤

በእንተ፡ምንት፡ማንኛ፤አንድም፡እን
ደዚህም ፡ ሁሉ ፡ እኒህ ፡ እስራኤል ፡
እኔን፡ከበደሉ፡በኋላ፡በንስሓ፡አይመ
ለሱምን ፡ አለመመለሳቸው ፡ ስለምን
ድነው፡አለ፡በላቸው፤

፭፤ በእንተ፡ምንት፡ዐለዉ፡ሕዝብ፡በኢየ
ሩሳሌም፡ማዕሌተ፡እኩየ።

ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ማዘን ፡ መጠጠት ፡ የሌለበት ፡ ክፉ ፡
ወንጀልን፡ስለምን፡ወነጀሉኝ፡አለ፡
በላቸው፤

ወአጽንዑ፡ምክሮሙ፡

ክፉ ፡ ምክራቸውን ፡ አጽንተው ፡
መከሩ፤

ወአበዩ፡ኀዲገ፤

አጽንዑ ፡ ምክሮሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡
[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ፡ ማዕሌተ ፡ እኩየ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ክፉ ፡ ወንጀልን ፡ መተው ፡ እምቢ፡አሉ፤

፮፤ አጽማዕኩ፡ወሰማዕኩ፡ይእዜኒ፤
ይህንንም፡ከነሱ፡አንደበት፡ፈጽሜ፡ሰማሁት፤

አኮ፡ከመዝ፡ይቤሉ፤
እንመከራለን፡እንመለሳለን፡አላሉም፤

እስመ፡አልቦ፡ሰብእ፡ዘይኔስሕ፡እምእከዩ፤ ወይብል፡ምንተ፡ገበርኩ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ ከክፉ ፡ ሥራው ፡ በንስሐ፡የሚመለስ፡ይህን፡መከራ፡ያመጣብኝ፡ምን፡አድርጌ፡በድየው፡ይሆን፡የሚል፡ባለ፡አእምሮ፡ሰው፡የለምና፤

ዘይሜርድሂ፡ደክመ፡እንዘ፡ይረውጽ፡ከመ፡ፈረስ፡ውስተ፡ፀብዕ፤
በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ ተጭኖ ፡ የሚሮጥ ፡ ፈረስ፡ እንዲደክም ፡ ጅአት ፡ እንጅ ሞንን፡በመፈለግ፤አንድም፡ተማርኮ፡የሚሄድ፡እስራኤል፡ደከመ፤አንድም፡እነሱን፡የሚመክር፡የሚያስተምር፡ነቢይ፡ካህን፡የሚጠበጥብ፡ፈረስ፡እንዲደክም፡ደከመ፤አንድም፡አሕዛብ፡እስራኤልን ፡ ሊወጓቸው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ፡ ከእስራኤል ፡ እንገብር ፡ እንቀቅል፡ ተመለሱልን ፡ ብሎ ፡ ሊነግር ፡ ጎዳናውን ፡ የሚጠበጥብ ፡ ሰው፡ደከመ፤

፯፤ ወሄሮድያኖስ ፡ በሰማይ ፡ የአምር ፡ ዕድሜሁ፤
በአየር፡የሚወረወር፡እባብ፡የ[illegible]
[illegible]

ቀይ ፡ መሬት ፡ ሲበላ ፡ ቀይ፤ ጥቁ
መሬት፡ሲበላ፡ጥቁር፤ነጭ፡ሲ
ነጭ ፡ ይሆናል ፤ ሲያረጅ ፡ ፵ ቀ
ከምግቡ ፡ ተከልክሎ ፡ ይሰነብታ
በ፵ኛው ፡ ቀን ፡ በስቍረተ ፡ነ
(በሰንጣቃ፡መሬት)፡ቢሉ፡በስቍ
ኰኵህም ፡ ቢሉ ፡ አልፎ ፡ እሄዳለ
ሲል ፡ ተገልፎ ፡ ይወድቅለታ
ይታደሳል፤አንድም፡በአየር፡የሚ
ንሥር ፡ የሚታደስበትን ፡ ያውቃ
እንደፎገራ፡አሞራ፤ሲያረጅ፡አን
ከንፈሩ፡ይረዝማል፤አንዱ፡ከን
ያጥራል ፡ የረዘመውን፡ በአጥንት
በደንጊያም፡ቢሉ፡እየኰረኰመ
ተካክለዋል ፡ ይታደሳል ፤ አንድ
ይህ፡ንሥር፡ከባሕር፡ወርዶ፡ሦስ
ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ይወጣ
ይታደሳል፤እንደዚህም፡ሁሉ፡እኛ
በሦስቱ ፡ ሥላሴ ፡ ስም ፡ አምነ
ተጠምቀን፡የመታደሳችን፡አምሳ

ማዕነቅኒ፡ወርግበ፡ገዳም፡ወአዕዋፍኒ፤
የአምሩ ፡ ጊዜ ፡ ይወጽኡ ፡ ወይበው
አዕዋፍ፤ርግብ፤ዋኖስም፡የሚወ
ትንና፡የሚገቡበትን፡ጊዜ፡ያውቃ
ጊዜ፡ይገብኡ፡ወየሐውሩ፡ይላል፤
ከመስኮቶቻቸው፡ወጥተው፡የሚ
በትን ፡ ወደመስኮቶቻቸው ፡ የሚ
ሱበትን፡ጊዜውን፡ያውቁታል፤

ወሕዝብየሰ ፡ ኢየአምሩ ፡ ኵነኔ ፡ እግ ብሔር፤
ወገኖቼ፡እስራኤል፡ግን፡እነሱ፡እ
አሳንሰው ፡ እኔ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ የ
[illegible]



እንዴህ ፡ ከሆነ ፡ እኛ ፡ አዋቆች ፡ ብልሆች ፡ ነን ፤ አንድም ፡ አዋቆች ፡ ብልሆች፡እኛ፡ነን፤

ወሕገ፡እግዚአብሔር፡ምስሌነ፤
ከእኛ፡ጋራ፡ያለው፡ሕጉም፤አንድም፡የእግዚአብሔርም ፡ ሕጉ ፡ ለነ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ተጠብቆልናል፡ ለምን ፡ ትላላችሁ፤

ከንቶ፡ኮኑ፡መጻሕፍቲክሙ፤
የተማራችኋቸው፡መጻሕፍቶቻችሁ፡ከንቱ፡ሆኑ፤

ወሐሰት፤
የተማራችሁትም፡ትምህርት፡ሐሰት፡ሆነ፤በሐሰት፡ነው፤

፱፤ ወተኀፍሩ ጠቢባን፤
አዋቆች ፡ ብልሖች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች፤አንድም፡አዋቆች፡ብልኆች፡የሚሆኑ ፡ መምህሮቻቸው ፡ ስንኳ ፡ በዚያ፡ወራት፡በመከራው፡አፈሩ፤

ተሰብሩ፡ወተአስሩ፤
በጦር ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ ታሥረው፡ተግዘው፡ሔዱ፤አንድም፡በጦር፡ጊዜ፡ድል፡ተነሡ፤
ወተአስሩ፤ለጥፋትም፡ተቀጠሩ፤

ወደንገጹ፤
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ አፈሩ ፤ ደነገጡ ፤

እስመ፡መነኑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔርን፡ሕጉን፡አንማረው፡ብለው፡ንቀዋል፤አቃለዋልና፤ምንት፡ውእቱ፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡እስመ፡[illegible]፡የእግዚአ

ምንት፡ውእቱ፡ጥበቦሙ፤
ጥበባቸው፡ምንድነው፤

፲፤ በእንተ፡ዝንቱ፡እሁብ፡አንስቲያሆሙ፡ለካልዓን፤
ሕጉን፡ንቀው፡አቃለው፡ስለበደሉኝ፡ሚስቶቻቸውን ፡ ዓይናቸው ፡ እያየ ፡ ለአሕዛብ፡አሳልፌ፡እሰጥባቸዋለሁ፤

ወገራውሂሆሙ፡ለመዋርሥት
እርሻቸውንም ፡ ዓይናቸው ፡ እያየ ፡ ለሚወርሷቸው ፡ ለአሕዛብ፡ እሰጥባቸዋለሁ፤

እስመ፡ንዑስ፡ወዓቢይ፡ኵሉ፡ይትዔገል፤
ትልቁም፡ትንሹም፡ሁሉ፡የድኃውን፡ከብት ፡ ይቀማልና ፤ አንድም ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀምቶ ፡ ለጣዖቱ፡ይሰጣልና፤አንድም፡እስመ፡ንኡስ፡ወዐቢይ፡ወኵሉ፡ይትሌገል፡ይላል ፤ ሐተታ ፡ ንዑስ ፡ ወዓቢይ፡የዕድሜ፡የማዕርግ፤ወኵሉ፡በዕድሜ፡በመዓርግ፡የማይቆጠር፡ነው፤

እምነቢይ፡እስከ፡ካህን፡ይትጌበሩ፡ሐሰተ፤
ንዑስ ፡ ወዓቢይ ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤ ይኸውም፡ሊታወቅ፡ከነቢየ፡ሐሰቱ፡ጀምሮ፡እስከ፡ካህኑ፡ጣዖቱ፡ድረስ፡ሐሰት፡ጣዖቱን፡ጠርበው፡አለዝበው፡ያመልካሉ፤አንድም፡ሐሰቱን፡ነገር፡ተግባር፡ያደርጋሉ፤

፲፩፤ ወይፌውሱ፡ቅጥቃጤሃ፡ለወለተ፡ሕዝብየ፡ለአስትቶ፤
ይትጌበሩ፡ሐሰተ፡ያለውን፡አመጣ፤ሕገ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመናቅ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ለማሳት ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፤ ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ የቤተ ፡ እስራኤልን ፡ መከራ፡እናርቅላታለን፡ይላሉ፤

ወይብሉ፡ሰላም፡ሰላም፡

በቤተ እስራኤል ፡ መከራ ፡ አይመጣ ባትም ፤ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይደረግ ላታል፡እንጂ፡ይላሉ፤

ወአልቦ፡ሰላም፡

መከራው ፡ ይደረግባታል ፡ እንጂ ፡ ፍቅር፡አንድነቱ፡አይደረግላትም፤

፲፱፡ ወተሐፍሩ፡እስመ፡ሰቄራረ፡ገብሩ፡

በሰው፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የሚያ ጸይፍ፡ሥራ፡ሠርተዋልና፡አለ፤ገቢረ፡ ኃጢአት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ሠርተ ዋልና፡በመከራ፡ተይዘው፡አፈሩ፤

ወሐፍረተሰ፡ኢየኀፍሩ፡

በመከራው፡አላፈሩም፡አልሁ፡እንጂ፡ ንስሐ፡ግን፡አልገቡም፤

እስመ፡ኢየአምሩ፡ሐፍረተ፡

ንስሐ ፡ መግባትን ፡ አያውቁምና፤ አንድም ፡ ንስሐ ፡ መግባት ፡ አይወ ዱምና ፤ አእመርኩከ ፡ ሙሴ ፡ ወልደ ፡ እንበረም፡እንዲል፤

በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይወድቁ ፡ በድቀቶሙ፡ ሶበ ፡ ይሔውጽዎሙ፤

በድለው ፡ ንስሐ ፡ ስለ ፡ አልገቡ ፡ አሕዛብ ፡ በጦር ፤ አንድም ፡ ሥላሴ ፡ በመዓት ፡ በኀበኛቸው ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ጥፋታቸው ፡ ተይዘው ፡ ይወድቃሉ፤ ወይደውዩ ፡ ማንሻ ፤ አንድም፡ ሥላሴ ፡ በመዓት፡በጐበኛቸው፡ጊዜ፤

ይደውዩ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ያንጊዜ፡ እስራኤል ፡ መከራ ይቀበላሉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፡ አስተጋብኡ ፡ እለ ፡ ያስተጋብኡ፡ በማዕረር፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

መከር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ወራት፡ መከር ፡ የሚሰበስቡ ፡ ሰዎች ፡ መከር፡ እንሰበስባለን፡አሉ፤

አልቦ፡አስካል፡ውስተ፡ወይን፡

በወይኑ፡ዘለላ፡አልተገኘበትም፡አለ፡ እግዚአብሔር፤

ወአልቦ፡በለስ፡በውስተ፡ሰግላ፡

በሾላውም ፡ ፍሬ ፡ የለም ፡ ወአልቦ ሰግላ፡ በውስተ ፡ በለስ ፡ ይላል ፤ ወአልቦ፡ ፍሬም ፡ ይላል፤ በበለሱም፡ ፍሬ፡የለም፤

ወተነግፈ፡ቈጽሉሂ፡

ቅጠሉ፡ሳይቀር፡ደርቆ፡ረግፎ፡ተገኘ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤ አንድም ፡ አስተ ጋብኡ ፡ እለ ፡ ያስተጋብኡ ፤ በምግባር፡ በሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ ሕጉን ፡ እንጠብ ቃለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች፡ በዚያ ፡ ወራት፡ የሚደረገውን ፡ ክፋውንና ፡ መል ካሙን ፡ እናስተውለዋለን ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ እስራኤልን፡ የሚመክሩ ፡ የሚያስተምሩ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ እንመክራለን ፡ እናስተም ራለን፡አሉ፤

አልቦ፡አስካል፡በውስተ፡ወይን፡

በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ምግባር ፡ ጸንቶ አልተገኘም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤ ሐተታ ፡ ወይን ፡ ያላቸው ፡ እስራኤል ፡ ናቸው፤ ወአፀደ ፡ ወይኑሰ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ውእቱ ፡ እንዲል፤



ስ፤በእስራኤልም፡ዘንድ፡ምግባር፡
ተገኘም ፤ በለስም፡ ያላቸው ፡
ራኤል፡ናቸው፤በለስ፡ዘይቤ፡ቤተ፡
ራኤል ፡ እሙንቱ ፡ እንዲል ፤
ተነግፈ ፡ ቈጽሉሂ ፤ ሃይማኖትም ፡
ቀር፡ጠፋባቸው፤ሐተታ፡አስካል፡
፡ ያለው ፡ምግባር ፡ ነው፤ ቈጽል ፡
ው ፡ ሃይማኖት ፡ ነው፤ ከፍሬ፡
ል፡ እንዲቀድም ፡ ከምግባርም ፡
ማኖት ፡ ይቀድማልና፤ አሚንስ ፡
ሠረት፡ይእቲ፤ወካልዓኒሃኒ፡ሕንፃ፡
ድቅ ፡ እሙንቱ ፡ እንዲል፤ ዮሐ ፡
፡ወርቅ፤

ሀብክዎሙ፡

ህ፡አስቀድሞ፡ተድላ፡ደስታውን፡
ኋቸው፤

ለፎሙ፤

ጢአታቸው ፡ በክፋታቸው ፡ ይህ ፡
ሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አለፈባቸው ፡
፡እግዚአብሔር፤

፲፬፡ ለምንት ፡ እንከ ፡ ንነብር ፡ ንሕነ ፡
ብኡ፡ወንባእ፡ውስተ፡አህጉር፡ጽኑዓት፡
ትወረው፡ህየ፤

፡ ትርፍ ፡ ነው ፤ ምልዓተ ፡ ጸሐፊ ፡
ው፤

ሙ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡ገደፈነ፡
ባሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመከ
ው፡ጥሎናልና፤

ስተየነ፡ማየ፡ሕምዝ፡

ዪውን ፡ ጥሶ ፡ መርዝ ፡ ያለበትን ፡
ሀ፡አጠጣን፤ሐተታ፡ማየ፡ሕምዝ፡

ያሰኘ ፡ ጠጥተውት ፡ ደስ ፡ ስላላሰ ኛቸው፡ እንዲህ ፡ አለ፤ አንድም ፡ የድርቅ ፡ ውሀ ፡ አጠጣን፤ ሐተታ ፡ ሕምዝ ፡ ያለው ፡ ድርቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በቋንቋው፤

እስመ፡አበስነ፡ለእግዚአብሔር፡

ይህም፡የተደረገብን፡ፈጣሪያችን፡እግ ዚአብሔርን፡ስለበደልን፡ነው፤

፳፩፡ ተሰፈውነ፡ሰላመ፡

ፍቅር፡አንድነትን፡እናገኛለን፡ብለን፡ ተስፋ ፡ አደረግን፤ ተሰፈውነ ፡ ባለው ፡ ተሰፌወነ፡ይላል፤

ወነጣእነ፡ሠናይተ፡ለጊዜ፡ሣህል፡

በይቅርታው ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገውን ፡ በጎውን፡ነገር፡ሁሉ፡አጣን፤

፳፪፡ ናሁ፡ይመጽእ፡እምነ፡ዳን፡

እምጽንፍ ፡ ሲል ፡ ነው፤ የአሕዛብ ፡ ጦር፡ ከዳን ፡ ዕፃ፤ አንድም ፡ ከዳርቻ ፡ እነሆ፡ይመጣል፤

ናጽምዕ ፡ ድምፀ ፡ ሩጸተ ፡ አፍራሲሆሙ፤

ናጸምዕ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ያንጊዜ ፡ እኛም ፡ የፈረሶቻቸውን ፡ ሩጫ ፡ ድምጽ ፡ እንሰ ማለን፤

እምቃለ ፡ ሠራዊቱ ፡ አድለቅለቀት ፡ ምድር ፡ በምልዓ፡

ታድለቀልቅ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ከናቡከደነ ፆርም ፡ ሠራዊት ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ መላዋ፡ኢየሩሳሌም፡ትነዋወጣለች፤

ወይመጽኡ ፡ ወይበልዕዋ ፡ ለዙላ ፡ ምድር፤

ከተት ፡ ሠራዊት ፤ ምታ ፡ ነገረት ፡ ብለው፡መጥተውም፡ኢየሩሳሌምን፤

ወለሀገር፡

ከተማዪቱን፡ያጠፉዋታል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለእለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡

በሱዋ፡የሚኖሩ፡ሰዎቹንም፡ይዘርፉዋ ቸዋል፤ይገፍፋዋቸዋል፤

፲፯፤ እስመ፡ናሁ፡አነ፡እፌኑ፡ለክሙ፡ አራዊተ፡ምድር፡ዘይቀትል፡

ዘይቀትሉ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እየነደፉ ፡ እየወጉ ፡ የሚጥሏችሁ ፡ የምድር ፡ አራዊትን፡አመጣባችኋለሁና፤

ዘአልቦ፡ዘይረቅዮ፡

ዘይረቅዮሙ ፡ ሲል ፡ ነው፤ እነሱንም ፡ ጠበል ፡ ረጭቶ ፡ መድኃኒት ፡ ቀብቶ ፡ የሚያድናቸው፡ሰው፡የለም፤

ወይነስኩክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እየወጉ ፡ እየነደፉ ፡ ይጥሏችኋል ፡ እንጂ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤ አንድም፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እፌኑ ፡ ለክሙ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ዘይቀትሉ፤ የሚወ ጓችሁ ፡ አሕዛብን ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢ ሎን፡ አመጣባችኋለሁና ፤ ዘአልቦ ፡ ዘይረቅዮ ፤ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ፡ዘገር፡ነጥቆ፡ተዋግቶ፡የሚመ ልሳቸው ፡ የለም ፤ ወይነስኩክሙ ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እነሱ፡እየወጉ፡እየወጉ፡ይጥሏችኋል፡ እንጂ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፰፤ እንዘ ፡ ተሐምሙ ፡ ልባክሙ ፡ ታንጎግዉ፤

እናንተም፡በልቦናችሁ፡እያዘናችሁ፡ እየተቆረቆራችሁ፡ትቅበዘበዛላችሁ፡ አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፱፤ ናሁ ፡ ቃለ ፡ አውያቲሃ ፡ ለወለተ ፡ ሕዝብየ፡እምርኁቅ፡ብሔር፡

እነሆ ፡ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ የቤ

እስራኤል፡ጩኸቷ፡ከሩቅ፡ይሰ

አለ፤ ጣዖቱን ፡ አምልካ ፡ ስም

በዓል፡ ስምዓነ ፡ ዳጎን ፡ ስት

አንድም፡በጦር፡ተወግታ፡ስታለ

ከሩቅ፡ይሰማል፤

ኢሀሎኑ፡እግዚአብሔር፡ውስተ፡ጽዮን

ቤተ፡እስራኤል፡ኃጢአት፡መሥ

ጣዖት ፡ ማምለኳ ፡ የሚፈርድ ፡

ያዊ፡እግዚአብሔር፡በጽዮን፡የለ

ወአልቦኑ፡ንጉሥ፡ህየ፡

በዚያ ፡ የሚሠራት ፡ የሚቀጣ

ምድራዊ፡ንጉሥስ፡በጽዮን፡የለም

እስመ ፡ አምዕዑኒ ፡ በከንቱ ፡ በግልፎ

ዘነኪር፡

ሳልበድላቸው ፡ በግፍ ፡ ልዩ ፡ በ

ዓይን ፡ እጅ ፡ እግር ፡ በተቀረፀ

ጣዖት ፤ አንድም ፡ ልዩ ፡ በሀ

በከነዓን፡ ጣዖት ፡ አሳዝነውኛል

አንድም፡ኢሀሎኑ፡በጽዮን፡እ

አብሔር፡የለም፡ነበርን፡

፳፤ ኀለፈ፡ቀስም፡

እንዲህ ፡ የምትለን ፡ ምን ፡ ሰም

ብናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ የዘይ

የወይኑ፡ፍሬ፡የሚለቀምበት፡ወ

አለፈ፤

ወሐልቀ፡ማዕረር፡

ስንዴው፡ገብሱ፡የሚታጨድበት

ወራት፡አለቀ፤

፳፩፤ ወንሕነኒ፡ኢድኅነ፡እምቀትል፤

እኛም ፡ ከጠላቶቻችን ፡ ሰልፍ ፡ ጦ

አልዳንም፤

ለወለተ፡ሕዝብየ፡ተንተንኩ፡ወተቀጥቀጥ

ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ ለወ



ጅ፡ለቤተ፡እስራኤል፡በመከራው፡

ጉመገምኩ፤

ነዘኒ፡ነኩላል፡

ን፡ደም፡ማዞር፡ያዘኝ፤

ሐምም፡ከመ፡እንተ፡ትወልድ፡

ጥ ፡ የያዛት ፡ ሴት ፡ በምጡ ፡ ተይዛ ፡

ድትጨነቅ ፡ እንደዚያ ፡ በመከ

ው፡ተይገዥ፡እጨነቃለሁ፤

፳፪፤ አልቦኑ፡ርጢን፡ውስተ፡ገለዓድ፡

ዓድ፡የወል፡ስም፡ነው፤በገለዓድ፡

ድኃኒት፡የለምን?

ኢሀሎኑ፡ህየ፡ዓቃቢ፡ሥራይ፡

ያስ ፡ አገር ፡ አግሞ ፤ ተኩሶ ፡

ሚያድን ፡ ባለመድኃኒት ፡ የለምን ፤

ምንት፡ኢዐርገ፡ከመ፡ይፈውሳ፡ለወለተ፡

ዝብየ፡

ማ ፡ የወገኔ ፡ ልጅ፡ ቤተ ፡ እስራ

ልን፡ሊያድናት፡ለምን፡አልወጣም፤

ንድም ፡ አልቦኑ ፡ ርጢን፡ ውስተ ፡

ለዐድ ፤ በገለዓድ ፡ ጦር፡ ሰልፍ ፡

ለምን ፤ ወኢሀሎኑ ፡ ህየ ፡ አቃቢ ፡

ራይ፤ባጭር፡ታጥቆ፡ዘገር፡ነጥቆ፡

ሚዋጋ፡አርበኛ፡የለምን፤ለምንት፡

ዐርገ ፡ ከመ ፡ ይፈውሳ ፡ ለወለተ፡

ዝብየ፤ካለማ፡ባጭር፡ታጥቆ፡ዘገር፡

ጥቆ ፡ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ቤተ ፡ እስራ

ልን፡ ሊያድናት ፡ ለምን ፡ አልወጣ ፡

ንድም፡ አልቦኑ ፡ ርጢን ፡ በገለዓድ ፤

ጦር፡መድኃኒት፡የለም?ወኢሀሎኑ፤

ለቃ፡የጦር፡መድኃኒት፡የሚያውቅ፡

ለም ፤ ለምንት ፡ ኢዐርገ ፡

ድናት ፡ ዘንድ ፤ ለምን ፡ አልወጣም ፤

ንድም ፡ ፈውሷ ፡ ድኅነቷ ፡ ለምን ፡

አልተደረገም ፤ አንድም ፡ አልቦኑ ፡ ትንቢት፡ ትምህርት ፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ የለም፤ ወኢሀሎኑ ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፤ ሐዋርያ ፡ የለም ፤ ለምንት ፡ ኢዐርገ ፡ ያድናት ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ አልወጣም፤ አንድም ፡ ፈውሷ ፡ ድኅነቷ ፡ ለምን ፡ አልተደረገም።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ፡
### ጉባኤ፤

፩፤ መኑ፡ይሁበኒ፡ማየ፡ለርእስየ፡

ራሴን ፡ ልታጠብበት ፡ ውሀ ፡ ማን ፡ በሰጠኝ፤

ወፈልፈለ፡አንብዕ፡ለአዕይንትየ፤

ካይኔም ፡ የሚፈስ ፡ የዕንባ ፡ ጐርፍን ፡ ማን፡በሰጠኝ፤

ወእብክዮሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ፡ለቅቱላነ፡ወለተ፡ሕዝብየ፡

ወእብክዮሙ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ለሕዝብየ ፡ ቅቱላነ ፡ ወለተ ፡ ሕዝብየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ከወገኔ ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ ለሞቱ ፡ ወገኖቼ፡ በመዓ ልትም ፡ በሌሊትም ፡ አለቅስላቸው ፡ ዘንድ ፡ ማልቀሱን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፤ አንድም፡እንዳለም፡ይሆናል፤ከወገኔ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ በመዓ ልትም፡ በሌሊትም ፡ ለሞቱ ፡ ለወገኖቼ፡ አለቅስላቸው ፡ ዘንድ ፡ ማልቀሱን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፤ ሐተታ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ለሞቱ ፡ አለ፤ቀን፡ተሰልፈው፡ሲዋጉ፡ይገድሉ ዋቸዋል፤ ሌሊትም ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ይገድሉዋቸዋልና፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ማኅደረ ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ ወእኅድጎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ወእሑር፡ እምኔሆሙ፡

ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ትቻቸው ፡ ወደምድረ ፡ በዳው ፡ እሔድ ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ ጎጆ፡ ሠርቶ ፡ ማን ፡ በሰጠኝ፡አለ፡ነቢይ፤ሐተታ፡ነቢዩት፡ ሳያጡ ፡ መመኘት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው፤ ከዚያ ፡ ኄኖክ ፡ መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ አዕይንትየ ፡ ደመናተ ፡ ማይ፡ ብሏል ፤ ከዚያም ፡ ኢሳይያስ ፡ መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ሕለተ ፡ ወሣዕረ ፡ በእንተ ፡ ዑበእ፡ አውዕዮ ፡ በእሳት ፡ ብሏል ፤ ከዚህም ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ማየ፡ ለርእስየ ፡ ወፈልፈለ ፡ አንብዕ፡ለአዕይንትየ፡አለ፡

እስመ፡ኵሎሙ፡ዓላውያን፡

እንዲህም ፡ ማለቴ ፡ መላው ፡ እስራኤል ፡ ሰውን ፡ ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወነጅላሉና ፡ ስለዚህ ፡ ነው፤

ወየሐውሩ፡በእሲተ፡ብእሲ፡

ዓላውያን ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፡ መጅ መሪያ ፡ ወደ ፡ ጉልማሳ ፡ ሚስት፡ ይሄዳሉ፤

፫፤ ወወሰቁ ፡ ልሳኖሙ ፡ ለሐሰት ፡ ከመ ፡ ቀስት፡

ቀስትን ፡ አነጣጥሮ ፡ እንዲቀፍሩት ፡ እንዲስቡት ፡ እንደበታቸውንም ፡ ለሐሰት ፡ ነገር ፡ አነጣጥረው ፡ ሳቡት፡ ቀፈሩት፤

ወአኮ፡እሙነ፡ዘፀንዑ፡ውስተ፡ምድር፡

በታመነ ፡ ረድዔቱ ፡ ተጠብቀው ፡ ጸንተው፡የኖሩ፡አይደለም፤

እስመ፡እምእኪት፡ኀበ፡እኪት፡የሐውሩ፡

ካንዱ ፡ መከራ ፡ ወዳንዱ ፡ መ
ይሔዳሉ፡እንጂ፤አንድም፡ይሄዳ
አንድም ፡ አኮ ፤ እሙነ ፡ ዘጸን
በታመነ ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ የኖ
አይደለም ፤ እስመ ፡ እምእኪት ፡
እኪት፡የሐውሩ፡አላ፡ያለበት፡
ካንዱ ፡ ሕግ፡ ጣዖት ፡ ወዳንዱ ፡
ጣዖት፡ይላሉ፡እንጂ፤አንድም፡
እሙነ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ጣ
አምልከው፤ፈጣሪያቸውን፡በድለ
በሀገራቸው ፡ ጸንተው ፡ የኖሩ ፡
ደሉም፤ እስመ ፡ እምእኪት ፡
እኪት፡የሐውሩ፡በዌዋዌ፡ተማርከ
ካንዱ ፡ አገር ፡ ወዳንዱ ፡ አገ
ይሔዳሉ፡እንጂ፤አንድም፡ይሔዳ

ወሊተሰ፡ኢየአምኑኒ፡ይቤ፡እግዚአብሔ
እኔን፡ግን፡አያምኑብኝም፡አለ፡እ
አብሔር ፤ አንድም ፡ ኢያእመ
ይላል፤እኔን፡ግን፡አይወዱኝም፡
ውቁኝም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፬፡ዑቁ፡ተዐቀብዎሙ፡ለቢጽክ
በዚያስ ፡ ወራት ፡ ባልንጀሮቻችሁ
ስንኳ፡ተጠበቋቸው፡አለ፤ኃጢአ
እንዳያሠሩዋችሁ፡ጣዖት፡እንዳያ
ልኳችሁ፡እወቋባቸው፤

ወኢትእመንዎሙ፡ለአኃዊክሙ፡
ስንኳን፡ባዕዶቹን፡የሥጋ፡ወንድ
ችሁን፡አትመኑዋቸው፤

እስመ፡ኵሉ፡እኍ፡አዕቅጾ፡የአቅጽ፡
ስንኳን ፡ ሌላው ፡ ወንድም ፡
ድሙን ፡ ኃጢአት ፡ እንሥራ ፡ ጣዖ



ወኵሉ፡አርክ፡ጠዋየ፡የሐውር፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ የታመነ ፡ ወዳጅ ፡ ከታመነ ፡ ወዳጁ ፡ ጋር ፡ በጠማማ ፡ ሥራ፡ጸንቶ፡ይኖራል፤

፭፤አሐዱ፡አሐዱ፡ይሣለቅ፡ላዕለ፡ካልኡ፡

ነሣሣለትና፡አንዱም፡አንዱም፡ሰው፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ በዋዛ ፡ በፈዛዛ ፡ ነገር፡ይዘብትበታል፤

ወኢይትናገሩ፡ጽድቀ፡

ባልንጀሮች ፡ ከባልንጀሮቻቸው ፤ ወን ድማማቾች ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ፡ እውነት፡ነገር፡አይነጋገሩም፤

ወልሳኖሙ፡ለመደ፡ተናግሮ፡ሐሰት፡

አንደበታቸውም ፡ ሐሰት ፡ ነገር ፡ መናገርን ፡ ለመደ ፡ አለ ፤ ኢይትናገሩ፡ ጽድቀ፡ያለውን፡አመጣ፤

ዐመፁ፡

ሳቱ፤በደሉ፤

፮፤ወኢኅደጉ፡ነሢአ፡ርደ፡

አራጣ፡መቀበልንም፡አልተዉም፤

ወይትሜየኑ፡

እኩሌቶች ፡ እኩሌቶችን ፡ ይተነኳኰሉዋቸዋል፤

ወይገብሩ፡ትምይንተ፡

እኩሌቶች ፡ በእኩሌቶች ፡ ተንኰል፡ ያደርጋሉ ፤ አንድም ፡ ወይትሜነዩ ፡ ይላል ፤ ባልንጀሮች ፡ የባልንጀሮቻቸውን ፤ ወንድሞች ፡ የወንድሞቻቸውን፡ሚስቶች፡ከብቶች፡ይመኛሉ፤

ወይገብሩ፡ተምኔተ፡

ባልንጀሮች ፡ የባልንጀሮቻቸውን ፡ ወንድሞች ፡ የወንድሞቻቸውን ፡ ...ትን ፡ ገል

ጠው፡ይመኛሉ፤ያደርጋሉ፤

ወኢፈቀዱ፡ያእምሩኒ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ኃያል፡

አምጻኤ፡ዓለማት፡ወላዴ፡ፍጥረታት፡ እግዚአብሔርም ፡ እኔን ፡ ሊያውቁኝ ፡ ሊያመልኩኝ፡አልወደዱም፡አለ፤

፯፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ጸባዖት፡

አቻናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡አረስኖሙ፡ወእፈትኖሙ፡

እነሱ ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ስለበደሉኝ፡ እኔም ፡ በመከራው ፡ አግላቸዋለሁ ፤ እየመረመርኩም ፡ አጠፋቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ ፡ እገብር ፡ እምቅድመ ፡ ገጸ ፡ ወለተ ፡ ሕዝብየ፡

ከወገኔ ፡ ልጅ ፡ ከገጸ ፡ ኃጢአቷም ፡ የተነሣ፡የመከራውን፡ፍጻሜ፡አደርግ ባታለሁና ፤ አንድም ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ወለተ፡ሕዝብየ፡ይላል፤በወገኔ፡ልጅ፡ በቤተ ፡ እስራኤል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የመከራ፡ፍጻሜ፡አደርግባታለሁና፡

፰፤ማዕበል፡በሊህ፡ልሳኖሙ፡

አንደበታቸውም ፡ የተሳለ ፡ ዓረብ ፡ ቃራ፡ ጮሖ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ያ ፡ እንዲያ ስፈራ፡የሚያስፈራ፡ነው፤

ወጕሕሉት፡ቃለ፡አፉሆሙ፡

ካንደበታቸውም ፡ የሚወጣው ፡ ነገር፡ ክህደት፡ተንኰል፡ነው፤

ዳኅነ፡ይትናገሩ፡ለቢጾሙ፡

ለባልንጀሮቻቸው ፡ ደኅና ፡ ደኅና ፡ ነገርን፡ይናገራሉ፤

ወበልቦሙ፡ይሠይሙ፡ጽልዐ፡

በልቡናቸው ፡ ግን ፡ ቂም ፡ ተንኰልን ፡ ይይዛሉ፡

www.ethiopianorthodox.org

አሐዱ፡አሐዱ፡ምስለ፡ካልዑ፡
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ ተንኰልን፡ይይዛሉ።

፱፡በዝንቱ፡ኢይዋሂኑ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
በዚህ፡ክፋታቸው፡በመዓት፡አልጐበኛቸውምን።

ወለሕዝብኒ፡ዘከመዝ፡ኢትትቤቀለሙኑ፡
ነፍስየ፡
እንደዚህ፡ያሉ፡ክፉዎች፡ወገኖቼንስ፡ልቡናዬ ፡ በክፋታቸው ፡ አትበቀላቸውምን፡አለ፡እግዚአብሔር።አንድም፡
በዝኒ ፡ ኢይዋሂኑ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ይላል። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ክፋታቸው ፡ በመዓት ፡ አልጐበኛቸውምን ። ወለሕዝብኒ ፡ ዘከመዝ ፡ ኢትትበቀለሙኑ፡ነፍስየ።እንደዚህ፡ያሉ ፡ ክፉዎች ፡ ወገኖቼንስ ፡ በዚህ ፡ ክፋታቸው ፡ ልቡናዬ፡ አትበቀላቸውምን፡አለ፡እግዚአብሔር።

፲፡ ወላህዉ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወበክዩ ፡
በውስተ፡ፍና፡በድው፡
ይህንስ ፡ ትታችሁ ፡ ወደተራራው ፡ ወጥታችሁ፡ወደምድረ፡በዳ፡በሚያስኬደውም ፡ ጎዳና ፡ ሁናችሁ ፡ እዘኑ ፡ አልቅሱ።

ወአስቆቅዉ፡
ሙሾውንም፡እያወጣችሁ፡አልቅሱ፡
እስመ፡ነልቀ፡ሰብእ፡
ሰው ፡ እልም ፡ ድርግም ፡ ብሎ ፡ ጠፍቷልና።

ወአልቦ፡ዘያንሶሱ፡
በዚያውም፡ወራት፡ከቤቱ፡የሚወ... ወደቤቱ፡የማገባ፡ሰው፡ያለመር...

ወኢይሰምዑ፡ቃለ፡የፊ፡ሰማይ፡
ባገር ፡ ኑረው ፡ በሰማይና ፡ በምድር፡ መካከል ፡ የሚበር ፡ የወፍ ፡ ድምፅ፡ ጭው፡ሲል፡አይሰሙም።

ወእስከ፡እንስሳ፡ሐለፉ፡ድንጉፃኒሆሙ፡
እስከን፡ታገሠው፡ከብቶችም፡ባገር፡ ተገኝተው ፡ እምቡዋ ፡ እምቡዋ ፡ እያሉ፡ ሲጮሁ ፡ አይሰሙም ። ኀለፉ፡ ድንጉፃኒሆሙ፡ማንሻ፡ነው።አንድም፡ ከሰው፡ጀምሮ፡እስከ፡እንስሳ፡ድረስ፡ የደነገጡ፡ሁነው፡ተማርከው፡ሂዱ።

፲፩፡ወእሬስያ፡ለኢየሩሳሌም፡ለፍልሰት፡
ኢየሩሳሌምንም ፡ ለጥፋት ፡ አድርጋታለሁ።

ወለግበበ፡አራዊት፡
ወግበበ ፡ ለአራዊት ፡ ሲል ፡ ነው ። ተፈታ፡ ጠፍታ ፡ ለአራዊት ፡ ሁሉ ፡ ጉድጓድ፡አድርጋታለሁ።

ወማኀደረ፡ሰገኖ፡
ወማኅደረ ፡ ለሰገኖ ፡ ሲል ፡ ነው ። ለሰገኖም፡ማደሪያ፡አድርጋታለሁ።

ወለአህጉረ፡ይሁዳ፡አማስኖን፡ከመ፡ኢይንበርዎን፡
የይሁዳ ፡ አውራጃዎች ፡ አገሮችንም፡ ሁሉ፡ሰው፡ከብት፡እንዳይኖርባቸው፡ አጠፋቸዋለሁ።

፲፪፡ መኑ ፡ ብእሲ ፡ ጠቢብ ፡ ዘይሌብዎ ፡
ለዝንቱ፡
ዝንቱ ፡ ሲናገረው ፡ የመጣውን ፡ ነው። ይኸነን ፡ ነገር ፡ ልብ ፡ የሚያደርግ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አለ ። ሰውን ፡ ያነቃቃል።



እግዚአብሔር ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ተናግሮ፡የሠራው፡ሕጉ፡በሱ፡ዘንድ፡ ተጠብቆለት ፡ ያለ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አለ ። ሕጉን ፡ የጠበቀ ፡ ሲል ፡ ነው።ይንግርከሙ፡ቃለ፡አፉሁ፡ብሎ፡ ነበርና፡ሕጉን፡ያስተምራችሁ፡ዘንድ። አንድም፡መኑ፡ጠቢብ፡ብሎ፡ነበርና፡ ብልህ፡አዋቂ፡እኔ፡ነኝ፡ብሎ፡ይነግራችሁ፡ዘንድ።አንድም፡ይንግርከሙ፡ በእንተ፡ምንት፡ተሐጕለት፡ምድር፡ መኑ፡ብእሲ፡ጠቢብ፡ብሎ፡ነበርና፡ ብልህ፡አዋቂስ፡ሰው፡ካለ፡ኢየሩሳሌም፡የጠፋችበት፡በምን፡በምን፡ ነገር፡እንደሆነ፡ይንገራችሁ።

ወጠፍዐት፡ከመ፡ምድረ፡በድው፡
ምድረ፡በዳ፡ሁና፡ጠፋች።አንድም፡ እንደ፡ምድረ፡በዳ፡ጠፋች።

እስመ፡አልቦ፡ዘየሐውራ፡
የሚኖርባት፡ሰው፡የለምና፡ስላልኖረ።

፲፫፡ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ።

እስመ ፡ ኀደጉ ፡ ሕዝብየ ፡ ሕግየ ፡ ዘወሀብክዎሙ፡በቅድመ፡ገጾሙ፡
በደብረ፡ሲና፡ፊት፡ለፊት፡የሠራሁላቸው፡ሕጌን፡ወገኖቼ፡እስራኤል፡ ትተውታልና።

ወኢሰምዑኒ፡ቃልየ፡
ቃሌንም ፡ አልሰሙትምና ። ሐተታ ፡ ሕግየ ፡ ያለው ፡ ፫፻፸ ፡ ወነበቦ ፡ ዘጠኙን፡ ቃላት ፡ ነው ። ቃልየ ፡ ኢታምልክ ፡ ነው ። አንድም ፡ ሕግየ ፡ መላው፡ቃልየ፡ዓሠርቱ፡ቃላት፡ነው።

...ተ፡ልቦሙ፡

ተከትለዉ ፡ ሔደዋልና ። ሐተታ ፡ ፍትወት ፡ አለው ። ወደው ፡ ስላመለኩት፡ነው።

ወተለዉ፡ጣዖተ፡ዘመሀርዎሙ፡አበዊሆሙ፡
ፍትወተ ፡ ልቦሙ ፡ ያለውን ፡ ጣዖት ፡ ብሎ ፡ ገለጠው ። አንድም ፡ ፍትወተ ፡ ልቦሙ ፡ ያለው ፡ ለጊዜው ፡ ልጆች ፡ ወደው ፡ ያመለኩት ፡ ጣዖታቸው ፡ ነው።ወተለዉ፡ጣዖተ፡ዘመሀርዎሙ። አበዊሆሙ ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጀምሮ ፡ ሲመለክ ፡ የቆየ ፡ ጣዖት ፡ ነው ። አንድም፡ ፍትወተ ፡ ልቦሙ ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። ወተለዉ ፡ ጣዖተ ፡ አምልኮ፡ጣዖት፡ነው።

፲፬፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ጸባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፡
ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ አድርገው ፡ በድለውኛልና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአብሐር፡እንዲህ፡አለ።ይቤለኒ፡ ያለውና፡ይቤ፡ያለው፡አንድ፡ወገን፡ ነው።

ናሁ፡አነ፡አበልዖሙ፡ፃዕረ፡
አበልዖሙ ፡ ግሥ ፡ ነው ። ጭንቅ ፡ መከራ፡አመጣባቸዋለሁ።

ወአሰትዮሙ፡ሐሞተ፡
የድርቅ ፡ ውሀ ፡ አጠጣቸዋለሁ ። አሰትዮሙ ፡ ግሥ ፡ ነው ። ሐሞት ፡ መራራ፡ነው።መራራ፡መከራ፡አመጣባቸዋለሁ።አንድም፡እንዳለ፡ይሆናል። አበልዖሙ፡ፃዕረ።ሰርቀው፡ቀምተው፡ በልተው ፡ በዚያ ፡ ኃጢአት ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ስላመጣባቸው ፡ አበልዖሙ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የድኃውን ፡ ወይን ፡ ሰርቀው ፡ ቀም
ተው፡ጠጥተው፡መረረ፡መከረ፡ስላ
መጣባቸው፡አስትዮሙ፡ሐሞተ፡አለ፤

፲፮ ፡ወእዘርዎሙ ፡ ውስተ ፡ በሐውርት ፡
ኀበ ፡ ኢየአምሩ ፡ ኢእሙንቱ ፡ ወኢአበ
ዊሆሙ፤
ዛሬ፡እነሱ፡ቀድሞ፡አባቶቻቸው፡በማ
ያውቋት ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ አስ
ማርኬ፡እበትናቸዋለሁ፤

ወእፌኑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መጥባሕተ ፡ እስከ ፡
አኅልቆሙ፡ባቲ፤
በጦር፡በመቅሠፍት፡ጨርሼ፡እስካጠ
ፋቸው፡ድረስ፡ጦር፡መቅሠፍት፡አመ
ጣባቸዋለሁ፤

፲፯ ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ጸባዖት፤
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡

ተደለዉ፡ወጸውዕዎን፡ለመስቆቅዋት፤
ተዘጋጅታችሁ፡ሙሾ፡እያወጡ፡የሚ
ያላቅሷችሁን ፡ ሴቶች ፡ ጥሩዋቸው ፤
ሐተታ ፡ ተዘጋጅታችሁ፡ ጥሩዋቸው፡
አለ፤ዛሬ፡ወዮባይ፡ስትጠራ፡ስንቋን፡
ዋጋዋን፡ አዘጋጅተው ፡ ነውና ፡
የሚጠሯት ፡ ተዘጋጅታችሁ ፡ ጥሩዋ
ቸው፡አለ፤

ወይምጽአ፤
እነሱም፡ተጠርተው፡ይምጡ፤

ወኀበ፡ጠቢባት፡ለአኩ፤
ከዚያም ፡ ዘንድ ፡ ካዋቆች ፡ ካዋቆች ፡
ሴቶች፡ላኩ፤

ወይምጽአ ፡ ወይንግራክሙ ፡ ፍጡነ ፤
ይምጽአ ፡ ፍጡነ ፡ ወይንግራክሙ ፡
ፍጡነ ሲል ፡ ነው ፤ ፈጥነው ፡ መጥ
ተውም ፡ የሙሾውን ፡ ወጉን ፡ ሥር
ዓቱን፡ፈጥነው፡ይንገሯችሁ፤

፲፰፡ወያስቆቅዋክሙ፤
ፈጥነው ፡ መጥተውም ፡ ሙሾውን ፡
እያወጡ፡ያላቅሷችሁ፤

ወያንብዓ ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ወየኃዝ ፡ ማይ ፡
እምነ፡ቀራንብቲክሙ፤
ያን፡ጊዜ፡ዓይኖቻችሁ፡ያልቅሱ፤ከቅ
ንድባችሁም፡የዕንባ፡ጐርፍ፡ይፍሰስ፤

፲፱፡ እስመ ፡ ተሰምዐ ፡ ቃለ ፡ ብካይ ፡
ውስተ፡ጽዮን፤
በጽዮን፡ከተማ፡የልቅሶ፡ቃል፡ተሰም
ቷልና ፡ አለ ፤ በአሕዛብ ፡ ጦር ፡
ተወግታ፡ስታለቅስ፤

እፎ፡ሐሠርነ፡ወተሐፈርነ፡ጥቀ፤
በአሕዛብ፡ጦር፡ተወግተን፡እንዴት፡
ጐሰቈልን ፤ ፈጽመንስ ፡ እንደምን ፡
አፈርን ፡ አለ ፤ ነቢዩ ፡ በእስራኤል ፡
ተገብቶ፤አንድም፡እፎ፡ሐሠርነ፡ወተ
ሐፈርነ፡ጥቀ፡በሉ፡አላቸው፤

እስመ ፡ ኀደግነ ፡ ብሔረነ ፡ ወገደፍነ ፡
አብያቲነ፤
የተወለድንበት ፡ የኖርንበት ፡ አገራ
ችንን፡የኖርንበት፡ቤታችንን፡ጥለን፡
ተማርከን፡ሂደናልና፤

፳፡ስምዓ፡አንስት፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤
የእስራኤል፡ሴቶች፡ግዱን፡የእግዚአ
ብሔርን፡ትእዛዝ፡ስሙ፤

ወይትወከፍ፡ዕዝንክን፡ቃለ፡አፉሁ፤
ካንደበቱ ፡ የወጣውንም ፡ ነገር ፡
ጆሮአችሁ፡ይቀበለው፤

ወመህራሆን፡ለአዋልዲክን፡ሰቆቃወ፤
እንደወትሮው ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡
መኖር፡የለምና፡እንግዲህስ፡ወዲህ፡



ለሴቶች፡ልጆቻችሁ፡ሙሾውን፡አስ
ተምሯቸው፤

ወብእሲትኒ፡ለካልዕታ፡ላሀ፤
ስንኳን፡እናት፡ለልጇዋ፡ጎረቤት፡ለጎ
ረቤትዋ፡ወዳጅ፡ለወዳጇ፡ልቅሶውን፡
ታስተምራት፤

፳፩፡ እስመ ፡ ዐርገ ፡ ሞት ፡ ውስተ ፡
ብሔርነ፤
አባር ፡ ቸነፈር ፡ በቂሙ ፡ ሞት ፡
አንድም፡ናቡከደነፆር፡ወደሀገራችን፡
ዘምቶብናልና፤

ወቦአ፡እንተ፡መሳክዊነ፡ከመ፡ይቀጥቅጥ፡
ሕፃናተ ፡ በአፍአ ፡ ወወራዙተኒ ፡ በመራኅ
ብቲነ፤
ሕፃናቱን ፡ ከቤት ፡ በአፍአ ፡ ጐልማ
ሶችን፡ባደባባይ፡ሊያጠፋ፡በመስኮት፡
እየዘለለ ፡ ገብቷልና ፤ ሐተታ ፡ ቦአ ፡
እንተ ፡ መሳክዊነ ፡ ማለቱ ፡ የፍርሃት ፡
አይደለም፤የብዛት፡ነው፤

፳፪፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ወይከውን፡አብድንተ፡ሰብእክሙ፤
ይከውን፡ያለውን፡ወደፊት፡ይሰጣሕ፡
ብሎ፡ያመጣዋል፤የሰዎቻችሁ፡ሬሳ፡

ወይሰጣሕ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ገዳም ፡ ከመ ፡
ተቅራም፤
ቃርሚያን፡ገና፡አልደረቀም፡ብለው፡
እንዲያሰጡት፤

ወከመ፡ከላስስት፡ድኅረ፡ዘየዓፅድ፤
ካጫጅ ፡ በኋላ ፡ ተረስቶ ፡ የቀረ ፡
ነዶንም፡ ገና ፡ አልደረቀም ፡ ብለው ፡
እንዲያሰጡት ፡ የሰዎቻችሁም ፡ ሬሳ፡
እንደዚያ ፡ ሰጣ ፡ ብሎ ፡ ይወድቃል፤
ወአልቦ፡ዘያስተጋብእ፡ማንሻ፡ነው፤
አንድም ፡ ቃርሚያን ፡ ካይነታው ፡
ጋራ፡ እንዳይሰበስቡት ፡ ካጫጅም ፡
በኋላ ፡ ተረስቶ ፡ የወደቀ ፡ ነዶን ፡
ካይነታው፡ጋራ፡እንዳይሰበስቡት፤

ወአልቦ፡ዘያስተጋብእ፡
የሰዎቻችሁም ፡ ሬሳ ፡ ባደባባይ ፡
ወድቆ፡ የሚቀብረው ፡ አጥቶ ፡ ጅብ፡
ይገትነዋል ፡ አሞራ ፡ ይበትነዋል ፡
እንጂ ፡ ሰብስቦ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡
ከዘመዶቹ፡ጋራ፡የሚቀብረው፡የለም፡

፳፫፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ኢይትመካህ፡ጠቢብ፡በጥበቡ፡
ጥበበኛ ፡ በጥበቡ ፡ አይመካ ፡ ማለት ፡
ዕመቀ ፡ ዕመቃትን ፡ አየረ ፡ አየራትን፡
ፈለከ ፡ ፈለካትን ፡ ሙዓአ ፡ ነፋሳትን ፡
ምሕዋረ ፡ ከዋክብትን ፡ ምሕዋረ ፡
ደመናትን፡አውቃለሁ፡ብሎ፡አንድ፡
አርእስት፤

ወኢይዘኀር፡ኀያል፡በኃይሉ፤
ኃይለኛም፡በኃይሉ፡አይመካ፤ባሥር፡
አጡብቃለሁ ፤ ብመታ ፡ አደቀለሁ ፤
ብሮጥ ፡ እቀድማለሁ ፤ ብወርውር ፡
አርቃለሁ፡ብሎ፡ሁለት፡አርእስት፤

ወኢይዘኀር፡ባዕል፡በብዕሉ፤
ባለጸጋ ፡ በብዕሉ ፡ አይመካ ፡ ወርቅ ፡
ብር ፡ በማጥኔ ፤ እህል ፡ በጎታ ፡
በጎተራዬ፤ከብት፡በበረቴ፡አለ፡ብሎ፡
ሦስቱም፡አርእስት፡ነው፡ለሦስቱም፡
ያመጣል፤

፳፬፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ በዝንቱ ፡
ይትመካህ፡ዘይትሜካህ፤
የሚመካስ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ይመካ ፡
እንጂ፤ ዝንቱ ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡
ያመጣዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ጠቢብ ፡ ወየአምር ፡ ኪያየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እኔን፡በሕግ፡በአምልኮት፡የሚያውቅ
ብልህ፡ሰው፡ይመካ፡እንጂ፡አለ፤ኢይ
ትመካህ፡ጠቢብ፡በጥበቡ፡ላለው፤

ዘይገብር፡ፍትሐ፡
የተቀማ ፡ የሚያስመልስ ፡ የተበደለ ፡
የሚያስክስ ፡ ይመካ ፡ እንጂ ፡ አለው ፤
ኢይዘኀር ፡ ኃያል ፡ በኃይሉ ፡ ላለው ፤

ወጽድቀ፤
የሚሰጥ ፡ የሚመጸውት ፡ ይመካ ፡
እንጂ፡ ባዕል ፡ በብዕሉ ፡ ላለው ፡ ይህ፡
ቅሉ ፡ ይመካ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤
ተስፋ፡ያድርግ፤

እስመ፡አነ፡እግዚአብሔር፡ዘእገብር፡ሣህለ፡
ወጽድቀ፡ወፍትሐ፡በዲበ፡ምድር፡
ጠቢብ፡ኃያል፡ባዕል፡ላላቸው፡ነው፤
በኒህ ፡ በሦስቱ ፡ አድሬ ፡ ይቅርታዬን፡
ቸርነቴን ፡ እውነተኛ ፡ ፍርዴን ፡
የማደርግ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ነኝና፤

እስመ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ፈቃድየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡
ይህ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ፈቃድ ፡ ስለሆነ ፡ አለ፡
እግዚአብሔር፤

፳፭፤ ናሁ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፤
እንዲህ ፡ ያል ፡ (ያለ) ፡ ወራት ፡ እነሆ ፡
ይመጣል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እዋህዮሙ ፡ ወእቤይኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ፡
ግዙራን፡ወቈላፋን፡ነፍስቶሙ፤
ይመጽእ፡መዋዕል፡ያለውን፡አመጣ፤
በመዓትም ፡ በምሕረትም ፡ እጐበኛቸ
ዋለሁ ፤ በጐዎቹን ፡ ከክፉዎች ፡
ክፉዎቹን፡ከበጐዎች፡እለያቸዋለሁ፤
አንድም፡እዋህዮሙ፡በመዓትም፡በም
ሕረትም ፡ እጐበኛቸዋለሁ፤ ወእቤ
ይኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ግዙራን ፡
ግዙራኑ ፡ ሥጋ ፡ እስራኤልን ፡
ከአሕዛብ፡ እለያቸዋለሁ ፤ ወቈላፋን ፡
ነፍስቶሙ ፡ ቈላፋኑ ፡ ሥጋ ፡ አሕዛ
ብንም ፡ ከእስራኤል ፡ እለያቸዋለሁ ፤
ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፤
ለሁለቱ፡ያመጣል፤

፳፮፤ ዘውስተ፡ግብፅ፡
በግብፅ፡ያሉ፡አሕዛብን፡ለይቼ፡አጠ
ፋቸዋለሁ ፡ ወቈላፋን ፡ ነፍስቶሙ ፡
ላለው፤

ወዘውስተ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ፡ያሉ፡እስራኤልን፡አጠፋቸ
ዋለሁ ፡ ግዙራኑ ፡ ሥጋ ፡ ቈላፋኑ ፡
ልቡና፡ላለው፤

ወዘውስተ፡ኤዶም፤
በኤዶም፡ያሉ፡አሕዛብ፤

ወዘውስተ፡አሞን፤
በአሞን፡ያሉ፤

ወዘደቂቀ፡ሞዓብ፤
በሞዓብ ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡
አሕዛብ፡ቈላፋኑ፡ሥጋ፡ናቸው፤

ወኵሎሙ፡እለ፡ቅሩጻን፡ገጾሙ፤
ሁሉም ፡ ፊታቸውን ፡ የተከተቡ፡
ናቸው፡አለ፤ይህን፡ባለው፡ልጹያን፡
አጽሐም፡ ወቅሩፃን ፡ ፀጉረ ፡ ከናፍር፡
ይላል ፤ ሁሉም ፡ ጢማቸውን ፡
የተላጩ፡ የከንፈራቸውን ፡ ጠጉሩን፡
የተቆረጡ፡ናቸው፤

እለ፡ይነብሩ፡ሐቅለ፤
በምድረ፡በዳ፡የሚኖሩ፤

እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ቈላፍያን፡
ነፍስቶሙ፤



ቈላፋን ፡ ሥጋ ፡ ናቸውና ፡ ወእስራ
ኤልሰ፡ ቈላፍ ፡ ልቦሙ ፡ እስራኤል ፡
ግን፡ግዙራን፡ሥጋ፡ቈላፋን፡ልቡና፡
ናቸውና።

## ምዕራፍ ፡ ፲

፩፤ ስምዑ፡ቃለ፡ዘነበበ፡እግዚአብሔር፡
ላዕሌክሙ፡ቤተ፡እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ የምትሆኑ ፡
ዓሥሩም ፡ ሁለቱም ፡ ነገድ ፡ እግዚአ
ብሔር፡በናንተ፡የተናገረውን፡ቃል፡
ስሙ፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ኢትትመሀሩ፡ፍኖተ፡አረማውያን፤
ዘነበበ፡ላዕሌክሙ፡ያለውን፡አመጣ፤
የአረማውያንን ፡ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡
አትማሩ፡ፍኖተ፡አረማውያን፡ባለው፡
ፍኖተ፡የናናውያን፡ይላል፤

ወኢትፍርሁ፡እምትእምርተ፡ሰማይ፤
ከሰማይም ፡ ምልክት ፡ የተነሣ ፡
አትፍሩ፡አለ፤ሰማይ፡ደም፡መስሏል፤
ጨረቃ፡በደም፡ተከትራለች፤አዘንብ
ላለች ፤ ፀሐይ ፡ በቀስተ ፡ ደመና ፡
ተከባለች፡እያሉ፡ይኸን፡ምልክት፡
እያደረጉ ፡ አሕዛብ ፡ ይፈራሉና ፤
ይኸንንም፡ጌታ፡በወንጌል፡እመ፡ይቀ
የሐይሕ ፡ ሰማይ ፡ ድሙነ ፡ ብሎ ፡
ለዘለፋ፡ወስዶታል፤

እስመ፡ይፈርሁ፡አሕዛብ፡እምኔሆሙ፤
እምኔሆሙ ፡ ያላቸው ፡ አረማውያን
ናቸው ፡ ከነሱ ፡ ይልቅ ፤ አንድም ፡
ከነሱ፡ አብነት ፡ ነሥተው ፤ አንድም ፡
ከማሆሙ ፡ እንደነሱ ፤ አንድም ፡
እምኔሁ ፡ ይላል፡ ትእምርተ ፡ ሰማይ ፡
ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከሱ ፡ የተነሣ ፡
ይፈራሉና፤

፫፤ እስመ፡ከንቱ፡ውእቱ፡ሕገ፡አማልክ
ቲሆሙ፡
በአማልክት ፡ ስም ፡ የሚሠራ ፡ ሕግ ፡
ከንቱ ፡ ነውና ፡ የአሕዛብ ፡ ሕጋቸው ፡
ሥርዓታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፤
አንድም፡ ከንቱ ፡ ስለሆነ፤ አንድም ፡
እስመ ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሕገ ፡ አስማ
ቲሆሙ፡ለአሕዛብ፡ ይላል፤የአሕዛብ፡
የስማቸው ፡ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ከንቱ ፡
ነውና ፡ አለ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡
ከአሕዛብ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡
እገሌ፡ፈርዖን፡ነበር፤እገሌ፡ኀልያድ፡
ነበር ፡ እያሉ ፡ ቁርበቱን ፡ ቀደው ፡
ቀደው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጋሻ ፤ ሸንበ
ቆውን፡አገዳውን፡ሰብስበው፡ይህን፡
ያህል፡ጦር፡ማርኮ፡ነበር፡ለማለት፡
ከመቃብሩ፡አጠገብ፡ባለ፡ዛፍ፡ይሰቅ
ላሉና፤ አንድም ፡ እስመ ፡ ከንቱ፡
ውእቱ፡ ሕገ፡አማልክቲሆሙ፡ይላል፤
ይህ፡ኢየሳትትም፡የተመቸ፡ነው፤

፬፤እስመ፡ዕፀ፡ዘገዘሙ፡እምገዳም፡ግብረ፡
ዕደ፡ፀራቢ፡በማኅፄ፡ዘገዘሞ፤
ከዱር ፡ የቆረጡት ፡ የብልህ ፡ ሥራ ፡
የሚሆን፤

በብሩር፡ወበወርቅ፡ቀፈልዎ፤
ከዱር ፡ ገብተው ፡ የቀና ፡ እንጨት ፡
ቆርጠው ፡ ፈልጠው ፡ አምጥተው ፡
ሰጥተውት፡የጃን፡ሸላሚ፡እጅ፡በመጥ
ረቢያ፡ጠርቦ፡አለዝቦ፡አንፆ፡ቀርፆ፡
የሠራላቸውን ፡ ጣዖት ፡ በብርና ፡
በወርቅ፡ለብጠውታልና፤

www.ethiopianorthodox.org

በሰፌልያ፡ወበቀኖት፡አጽንዕዎ፡ከመ፡ኢይ
ተሐወስ፤
ወዲያ፡ወዲህ፡ብሎ፡እንዳይንቀሳቀስ፡
በመዶሻ፡መትተው፡በችንካር፡አጽን
ተውታልና ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሕገ ፡
አሕዛብ፡ሳለው፤

፭፤ ብሩር፡ዘፍሕቆ፡እሙንቱ፤
ወዲያ፡ወዲህ፡ብሎ፡እንዳይንቀሳቀስ፡
በመዶሻ፡መትተው፡በችንካር፡አጽን
ተውታልና ፡ ጣዖታቱን ፡ የለዘቡ ፡
ብር ፡ ናቸው ፡ በሉዋቸው፤ አንድም ፡
ነቢዩ ፡ ጣዖታቱ ፡ የለዘቡ ፡ ብሮች ፡
ናቸው፡ብሎ፡ይናገራል፤

ወኢይትናገሩ፤
ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡
ሲነግሯቸው ፡ ጣዖታቱ ፡ መልሰው ፡
አንድ፡ቃል፡አይናገሩም፤

ፀዊረ፡ይፀውርዎሙ፤
ሰዎቹ፡ጣዖታቱን፡ይሸከሟቸዋል፤

ወኢየሐውሩ፤
ጣዖታቱ ፡ ግን ፡ በፈቃዳቸው ፡ አንድ ፡
እርምጃ፡መንገድ፡አይሄዱም፤

ኢትፍርሁ፡እምኔሆሙ፤
ከእንዲህ ፡ ያሉ ፡ ጣዖታት ፡ የተነሣ ፡
አትፍሩ፤

ኢየሐሥሙ፡ወኢያሤንዩ፤
እነሱስ ፡ ጠላታቸውን ፡ አይጐዱም፤
ወዳጃቸውን፡አይጠቅሙም፤ አንድም፡
እነሱስ፡አይሾሙም፡አይሽሩም፤

፮፤ አልቦ፡ከማከ፡እግዚአ፡
አቤቱ ፡ እንዳንተ ፡ ግን ፡ ፈጥሮ ፡
የሚገዛ፡የለም፤

ዐቢይ፡አንተ፤
ተአምራትም፡በማድረግ፤ገናና፡ነህ
ወዐቢይ፡ስምከ፡በኃይል፤
ስምህም፡ኃይል፡በማድረግ፤አንድ
ተአምራት፡በማድረግ፡ገናና፡ነው፤

፯፤ ወመኑ፡ዘኢይፈርሀከ፤
እንዲህ፡የምታደርግ፡አንተን፡የ
ፈራህ፡የማያመልክህ፡ማነው፤

ወነገሥታተ ፡ አሕዛብ ፡ ኵሎሙ ፡ እስ
ኀቤከ፡ይመጽኡ፤
የእስራኤልም፡የአሕዛብም፡ነገሥታ
አንተን ፡ በመፍራት ፡ በማምለ
ወዳንተ፡ይመጣሉና፤

እስመ፡በኵሉ፡ጠቢባን፡አሕዛብ፡ወበ
መንግሥቶሙ፡አልቦ፡ከማከ፤
አዋቆች፡በሚሆኑ፡በሠራዊቶቻቸ
ዘንድና፡በነገሥታቱ፡ሁሉ፡እንዳን
ያለ፡ገናና፡ፈጣሪ፡የለምና፤

፰፤ ምዕረ፡ይነድዱ፤
በተቆጣህባቸው ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነው
ይጠፋሉ፤

ወየአብዱ፡ትምህርተ፡ከንቱ፤
ከንቱ ፡ ትምህርትንም ፡ ተምረ
ሰዎች ፡ አላዋቂነታቸው ፡ ይገለ
ቸዋል፤ አንድም፡ከንቱ፡ዕፅ፡ውእ
ይላል፤እንዲህ፡እንዲህ፡ነውና፡የ
መልከት ፡ እንጨት ፡ ከንቱ ፡ ነ
አንድም፡ከንቶ፡ዕፅ፡ይላል፤አምላ
ነው፡ብላችሁ፡የምታመልኩት፡
እንጨት፡በከንቱ፡ነው፤

፱፤ ብሩረ ፡ ሜሮቃስ ፡ እምተርሴ
ይመጽእ፤
ይኸውም ፡ የምታመልኩት ፡ ጣ



ከተርሴስ፡ተነግዶ፡የሚመጣ፡ብሩረ፡
ፅዕዳዌ፡ሲል፡ነው፤ ነጭነት፡ያለው፡
ብር ፡ ነው፤ አንድም ፡ ከተርሴስ ፡
ተነግዶ ፡ የሚመጣ ፡ ሜሮቃስ ፡
ከምትባል ፡ አገር ፡ የተነጠረ ፡ ብር ፡
ነው፤

ወወርቅ፡እምአፌር፤
አፌር ፡ አፌዝ ፡ ይላል፤ ይኸውም ፡
ከህንደኬ ፡ ተነግዶ ፡ የመጣ ፡ ወርቅ ፡
ነው፤

ግብረ፡ኬንያ፡ወእደ፡ነሃቢ፤
ግብረ ፡ ኬንያና ፡ ወእደ ፡ ነሃቢ ፡
አንድ፡ወገን፤ይኸውም፡የብልህ፡ጅን፡
ሸላሚ፡እጅ፡የሠራው፡ጣዖት፡ነው፤

ደርከኖ ፡ ወሜላት ፡ አልባሲሆሙ ፡ ግብረ ፡
ጠቢባን፡ወኵሎሙ፤
ሰማያዊ፡ሐርና፡ነጭ፡ሐር፡የሚሆኑ፡
የጣዖታቱ፡ልብሳቸው፡እነዚህ፡ሁሉ፡
የብልሆች፡ሰዎች፡ሥራዎች፡ናቸው፤
አንድም ፡ ደርከኖ ፡ ሰማያዊ ፡ ሐር ፡
ወሜላት፡ነጭ፡ሐር፡የጣዖታቱ፡ልብ
ሶቻቸው፡ወለሲሆሙ፡ያለበት፡ነው፤
እነሱም፡ጣዖታቱ፡ሁሉም፡የብልሆች፡
ሰዎች፡ሥራ፡ናቸው፤

፲፤ ወእግዚአብሔርሰ፡አምላክ፡ጻድቅ፡
ውእቱ፤
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔርስ ፡ እን
ደነሱ፡አይደለም ፤ የቸርነት፡ፈጣሪ፡
ነው፤

አምላክ፡ሕያዋን፤
የሕያዋኑም ፡ የሙታኑም ፡ ፈጣሪ ፡
ነው፤

ወንጉሠ፡ዓለማት፤
ዓራቱን ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡ የፈጠረ፤
አንድም ፡ ዓራቱን ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡
አዙሮ ፡ ያሳየኝ፤ አንድም ፡ ዓራቱን ፡
መዓዝነ ፡ ዓለም ፡ የሠራ ፡ ፈጥሮ ፡
የሚገዛ፡ንጉሥ፡እሱ፡ነው፤

እመዓቱ፡ታድለቀልቅ፡ምድር፡
ከቁጣውም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ትነዋወጣለች፤

ወኢይክሉ፡አሕዛብ፡መዓቶ፤
ሕዝቡ ፡ አሕዛቡም ፡ እሱ ፡ ተቆጥቶ ፡
ያመጣባቸውን ፡ መዓቱን ፡ መመለስ ፡
አይቻላቸውም፤

፲፩፤ ከመዝ፡በልዎሙ፡ለአማልክት፡እለ፡
ኢገብሩ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ለይደምሰሱ ፡
ወይጥፍዑ፡እምድር፡ወእምታሕተ፡ሰማይ፡
ሰማይና፡ምድርን፡ያልፈጠሩ፡ጣዖታ
ቱንስ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡
በላይ፡ከዚህ፡ዓለም፡እልም፡ድርግም፡
ብለው ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይጥፉ ፡
በሏቸው፤

፲፪፤ እግዚአብሔርሰ ፡ ገብረ ፡ ምድረ ፡
በኃይሉ፡
እግዚአብሔር፡ግን፡በአምጻኤ፡ዓለሚ
ትነቱ ፡ በወላዴ ፡ ፍጥረትነቱ ፡
ምድርን፡በውሀው፡ላይ፡ፈጠረ፤

ወአርትዐ፡ዓለመ፡በጥበቡ፤
በባሕርይ፡ጥበቡም፡ዓለምን፡አቅንቶ፡
ፈጠረ፤

ወሰፍሐ፡ሰማየ፡በምክሩ፤
በባሕርይ፡ምክሩም፡ምድርን፡ዘረጋ፡
ሰማይን፡አረጋ፤

፲፫፤ ወመልዓ፡ማየ፡ውስተ፡ሰማይ፡ላዕለ፡
ከጠፈርም፡በላይ፡ሐኖስን፡መልቶ፡
አኖረው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአዕረገ ፡ ደመናተ ፡ አምአጽናፈ ፡ ምድር፡
ከጽንፈ ፡ ምድር ፡ ከአድማስም ፡ ደመናትን፡ያወጣ፡እሱ፡ነው፤

ወገብረ፡መባርቅተ፡ለጊዜ፡ዝናም፡
በጊዜ ፡ ዝናም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዝናም ፡ ጊዜ ፡ ሊሰማ ፡ መብረቅን ፡ የፈጠረ ፡ እሱ፡ ነው ፤ ወይበርቁ ፡ መባርቅት ፡ ለጽጋብ፡ወለበረከት፡እንዲል፤

ወአውጽአ፡ነፋሳተ፡እመዛግብቲሆሙ፡
ነፋሳትንም ፡ መጥኖ ፡ መጥኖ ፡ ከቦታቸው ፡ የሚያወጣቸው ፡ እሱ ፡ ነው፤

፲፬፡ ወለስሐ ፡ ኵሉ ፡ ምክረ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው፡
እንደዚህ ፡ ባለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ምክር ፡ አልጫ፡ነው፡አለ፤አልጫ፡እንዲጠላ፡እንዲነቀፍ፡ይጠላል፤ይነቀፋል፤

ወተኀፍሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ነሃብት ፡ በእንተ ፡ ግልፎሆሙ፤
ዓይን ፡ እጅ ፡ እግር ፡ የተቀረፀለት ፡ ጣዖቱን ፡ ስለሠሩ ፡ ጃን ፡ ሸላሚዎች ፡ ሁሉ፡በዚያ፡ወራት፡አፈሩ፤

እስመ፡ሐሰተ፡ሰበኩ፡
ሐሰት፡ጣዖቱን፡መትተው፡ሠርተው፡አምልከዋልና፤ አንድም ፡ ሐሰት ፡ ጣዖቱን፡መትተው፡ሠርተው፡አስመልከዋልና፤

ወአልቦሙ፡መንፈስ፡ውስቴቶሙ፤
እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ለሚሠሩ ፡ ለጃን ፡ ሸላሚዎች ፡ አእምሮ ፡ የላቸውም፤ አንድም፡እንዲህ፡አድርገው፡የሠሯቸው፡ጣዖታቱ፡ነፍስ፡እስትንፋስ፡የላቸውም፤

፲፭፡ ከንቱ፡ውእቱ፡ግብር፡ዘያስተጣብቅ
ይህም ፡ ጣዖቱ ፡ አጠባብቀው አጣብቀው ፡ ጠጋግነው ፡ የሚሠሩት ከንቱ፡ሥራ፡ነው፤

እንተ፡አመ፡ሐወፆሙ፡ይትሐጐሉ፡
እግዚአብሔርም ፡ በመዓት ፡ በጐ ኛቸው፡ጊዜ፡ሰዎቹ፤አንድም፡ጣዖታ ይጠፋሉ፤

፲፮፡ ኢኮነ፡ከማሁ፡መክፈልተ፡ያዕቆብ፤
የያዕቆብ፡እድል፡ፈንታ፡ጽዋ፡ተርታ እግዚአብሔር፡ግን፡አሁን፡እንደተና ርኩት፡የሚጠፋ፡አይደለም፤አንድም እንደ፡ጣዖቱ፡አይደለም፤

እስመ፡ዘኵሎ፡ፈጠረ፡ውእቱ፤
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የፈጠረ እሱ ፡ ነውና፤ አንድም ፡ እስመዝ ፡ ኵለ ፈጠራ፡ውእቱ፡ይላል፤ዝ፡ኵሉ፡ያለው ሲናገረው፡የመጣውን፡ነው፤ይህ፡ሁሉ ልብ ፡ ወለድ ፡ ፈጠራ ፡ ነገር ፡ ነውና ተሐፍሩ፡ነሃብት፡ይትኃጐሉ፡ላለው፤

ወእስራኤልሰ፡በትረ፡ርስቱ፡እግዚአ፡ኃይ ስሙ፤
እስራኤል፡የርስቱ፡ነገድ፡የሆነለት፡እ ዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ እግዚአ ፡ ኃይል ይባላል፤

፲፯፡ አስተጋብዒ ፡ እምአፍአ ፡ ኃይለኪ እንተ፡ትነብሪ፡ውስተ፡ፀወን፤
እድናለሁ ፡ መስሎሽ ፡ ወደአምባ የገባሽ፡ ቤተ ፡ እስራኤል፤ አንድም እንተ፡ ትነብሪ ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ፡ ይላል በጽዮን ፡ ከተማ ፡ ተደላድለሽ ፡ ተቀ ጥለሽ ፡ ትኖሪ ፡ የነበርሽ ፡ ቤተ እስራኤል፤አንድም፡በሕጉ፡ተጠብቀ



ትኖሪ ፡ የነበርሽ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ይሆንልሽ፡እንደሁ፡ከእዳሪ፡የደከምሽ በትን፡አዝርእትሽን፡አትክልትሽን፡ሰብስቢ፤

፲፰፡ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ናሁ፡አነ፡አዐቅጾሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ ዛቲ፡ምድር፡
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ያስቀየምሽው ፡ ፈጣሪሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሩ ሳሌም፡ የሚኖሩ ፡ እስራኤልን ፡ በመከራው ፡ አሰነካክላቸዋለሁ ፡ ብሏልና፤ከመዝ፡ያለውን፡አዐቅጾሙ፡ ብሎ፡ገለጠው፤

በሕማም ፡ አመነደቦሙ ፡ ከመ ፡ ይትረከቡ ፡ መቅሠፍቶሙ፤
የታዘዘባችው ፡ መቅሠፍት ፡ በነሱ ፡ በዝቶ ፡ ይገኝባቸው ፡ ዘንድ ፡ በመከራው ፡ አስጨንቃቸዋለሁ፤ አንድም፡ወኢይትረከቡ፡ይላል፤እንደ ቀድሞው፡በተድላ፡በደስታ፡ሁነው፡ አይገኙም፤አንድም፡በሕማም፡አመነ ድቦሙ ፡ አስማርኬ ፡ ወስጄ ፡ በባቢሎን፡ በመከራው ፡ አስጨንቃቸ ዋለሁ፤ ወኢይትረከቡ ፡ በሀገራቸው ፡ ግን፡አይገኙም፤ጥቂትም፡ቢገኙ፡ኋላ፡ ናቡዛርዳን፡መጥቶ፡ጨርሶ፡ወስዷቸ ዋልና፡ኢይትረከቡ፡አለ፤

፲፱፡ በሊ፡ወይሌ፡ለቅጥቃጤየ፡
በእስራኤል ፡ ለመጣ ፡ መከራ ፡ ወዮልኝ፤

ጸልዐ፡ደዌየ፡
ቍስለ፡መከራዬም፡ሰፋ፡አለ፡ነቢዩ፡ ኤርምያስ ፡ በእስራኤል ፡ ተገብቶ ፤ አንድም ፡ ወይሌ ፡ ለቅጥቃጤየ ፡ ለመከራዬ ፡ ወዮልኝ ፡ ጸልዐ ፡ ደዌየ ፡ ቍስለ ፡ መከራዬም ፡ ሰፋ ፡ በዪ ፤ ይላታል፡ቤተ፡እስራኤልን፤

ወአነሂ፡እቤ፡አማን፡ዝንቱ፡
እኔም ፡ ይህን ፡ ሰምቼ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይበጅ ፡ ያድርግ ፡ አልሁ፤ አንድም ፡ ዝንቱ ፡ ቍስልየ ፡ ረከበኒ፡ይላል፤ይህ፡ቍስለ፡መከራዬ፡ በሚገባ ፡ አገኘኝ ፡ አለ ፡ ነቢዩ፤ አንድም፡በዪ፡ይላታል፤

፳፡ ደብተራየ፡ኀሥረ፡
ባለድንኳን፡ጠፋብኝ፡ ይህን፡ባለው፡ ተዓይንየ፡ኀሥረ፡ይላል፤እንደዚሁ፡ ያስተረጕማል፤

ወኵሉ፡አኀባልየ፡ተበትከ፡
ደብተራየ ፡ ኀሥረ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የድንኳኑ፡መዘርጊያ፡ገመዱ፡ተቆረ ጠብኝ ፡ አለ ፡ በቁሙ፤ አንድም ፡ አኀባልየ፡ ተበትኩ ፡ ወገኖቼ ፡ ጥለውኝ፡ሄዱ፤

ወኢሀለዉ፡ደቂቅየ፡
ወገኖቼ፡ቢቀሩ፡ልጆቼ፡ያረጋጉኝ፡ ነበር፤ ልጆቼም፡ተማርከው፡ሄደው፡ ከኔ፡ጋር፡የሉም፡አያረጋጉኝም፤

ወአባግዕየ፡
ልጆቼም ፡ ቢቀሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ ያረጋጋ ፡ ነበር ፤ በጎቼም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሉም፡አያረጋጉኝም፤

ወአልቦ ፡ እንከ ፡ ማኀደር ፡ ለትዕይንትየ ፡
ተዓይንየ፡ኃሥረ፡ብሎ፡ነበርና፤ለከተ ማዬም ፡ የሚያድርበት ፡ ቦታ ፡ የለውም፤ አንድም ፡ ለደብተራየ ፡ ይላል፡ ድንኳኔን ፡ ስንኳ ፡ የምተከ ልበት፡ቦታ፡የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢብሔር፡ለመራዕይየ፡
ጥቂት ፡ ስንኳ ፡ መንጋዎች ፡ ቢኖሩ ፡ እነዚያን፡የማሰማሪበት፡ቦታ፡የለም፤

፳፩፤ እስመ፡አብዱ፡ካህናት፡
ካህናት ፡ አልመከሩም ፤ አላስተማሩምና ፤ አንድም ፡ ኖሎት ፡ ይላል ፤ ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡ አልሠሩም፤ አልቀጡምና፤

ወኢኃሠሥዎ፡ለእግዚአብሔር፡
እግዚአብሔርንም ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት፡አልፈለጉትምና፡አለ፡ሕዝቡ፤ አንድም ፡ ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፤ አንድም፡ነቢያት፡ካህናት፡ናቸው፤

በእንተ፡ዝንቱ፡ኢያእመሩ፡ኵሎ፤
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስላደረጉ ፡ የሚመጣባቸውን፡መከራ፡አላወቁም፤

ወኢዐቀቡ፡ኵሎ፡መራዕየ፡
ከዚህ፡አስቀድሞ፡በተድላ፡በደስታ፡ ስለኖሩ፡ዘላኖች፡መንጎቻቸውን፡አልጠበቁም፤

ወተዘርዉ፡
መንጋዎችም ፡ ተበተኑ ፤ ከጥጋብ ፡ የተነሣ ፡ የመጣው ፡ ይምጣ ፤ የተረፈው፡ ይቅር ፡ ብለዋልና ፤ አንድም፡ ወኢዐቀቡ፡ኵሎ፡መራዕየ፡ መኳንንቱ፤ነገሥታቱ፡እሥራኤልን፡ አልሠሩም ፡ አልቀጡምና ፤ አንድም፡ ነቢያት፡ካህናት፡እስራኤልን፡አልመከሩም፤አላስተማሩምና፤

ወተዘርዉ፡
እስራኤል ፡ በበደሉት ፡ በደል ፡ ተማርከው፡ሄዱ፤

፳፪፤ ቃል፡ተሰምዓ፡
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በሀገራቸው ፡ ጣዖት ፡ አቁመው ፡ ስምዓኒ ፡ ስምዓኒ፡ዳኅን፤እያሉ፡ጣዖቱን፡ ሰግኑ ፡ ቃላቸው ፡ ከሩቅ ፡ ተ አንድም ፡ በጦር ፡ ተወግተ ሲላቀሱ፡ቃላቸው፡ከሩቅ፡ተሰማ

ናሁ፡ይመጽእ፡ድልቅልቅ፡ዓቢይ፡እ ሰሜን፡ከመ፡ያማስኖን፡ለአህጉረ፡ ወይረስይዎን፡ቤተ፡ሰገኖ፡
የይሁዳን፡አገሮች፡እልም፡ድር አድርገው፡አጥፍተዋቸው፡የሰ ማደሪያ ፡ ሊያደርጉዋቸው ፡ እ ከባቢሎን ፡ አገር ፡ ታላቅ ፡ ን ውጽታ፡ይመጣል፡አለ፤ናቡከደ ነው ፤ አንድም ፡ እምድኅረ ፡ ሰ ይላል ፤ ከባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ በ የባቢሎን፡ሰዎች፡ይመጣሉ፡አለ ቡከደነፆር ፡ በኋላ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ቷልና ፤ ሐተታ ፡ ሰሜን ፡ አላ ባቢሎንን ፡ በሀገሩ ፡ ቋንቋ ፤ አንድ ዓራት፡ማዕዘን፡የሌለውን፡አገር፡ ላንዱ ፡ ደቡብ ፡ ብትሆን ፡ ላን ሰሜን፡ናትና፤

፳፫፤ ናሁ ፡ አእመርኩ ፡ እግዚእ ፡ ከ ኢኮነ፡ፍኖቱ፡ለእግዚአብሔር፡ከመ፡ፍ ሰብእ፤
የሰው ፡ ሕጉ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔ ሕግ፡ እንዳይደለ ፡ አቤቱ ፡ እነ አወቅሁ፤

ወኢየሐውራ፡ብእሲ፡
በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ሰው ጸንቶባት፡አይኖርም፡



ወኢጼሐ፡መንገዶ፡
ሕጉንም ፡ ሥርዓቷንም ፡ ሰው ፡ አይፈጽምም፤

፳፬፤ መሐረነ፡እግዚእ፡
አቤቱ፡አሁንም፡ይቅር፡በለን፤

ወባሕቱ፡በፍትሕ፡ወአኮ፡በመዓትከ፡ከመ፡ ኢታኅልቀነ፡
የሰይጣንን ፡ ብርታት ፡ የኛን ፡ ደካማነት ፡ ታውቃለህና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተቆጥተህ ፡ ጨርሰህ ፡ እንዳታጠፋን ፡ በፍርድ ፡ ይሁን ፤ አንድም ፡ ናሁ ፡ አእመርኩ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ፍኖቱ፡ለእግዚአብሔር፡ከመ፡ፍናወ፡ ሰብእ ፡ አቤቱ ፡ ያንተ ፡ ባሕርይና ፡ የሰው፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ እንዳይደለ ፡ አወቅሁ፤ወኢየሐውራ፡ብእሲ፤ሰው፡ ያንተን፡ባሕርይ፡አይመረምራትም፤ ወኢጼሐ፡መንገዶ፤ጥቂት፡ስንኳ፡ባሕ ርይህን፤አይመረምራትም፤መሐረነ፡ እግዚእ፡አቤቱ፡በቸርነትህ፡ይቅር፡ በለን ፤ ወባሕቱ ፡ በፍትሕ ፤ ወአኮ ፡ በመዓትከ፡ከመ፡ኢታሕልቀነ፤የኛ፡ ባሕርይ ፡ ጸናኒ ፡ ያንተ ፡ ባሕርይ ፡ ኢጸናኒ፤ ነውና ፡ በተቆጣህበት ፡ ቀን ፡ ጨርሰህ፡እንዳታጠፋን፤ነገር፡ግን፡ በፍርድ፡ይሁን፤

፳፭፤ ከዓው ፡ መዓተከ ፡ ላዕለ ፡ አሕዛብ ፡ እለ፡ኢየአምሩከ፡
በማያውቁህ ፡ በማያመልኩህ ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ቊጣህን ፡ አብዝተህ ፡ አምጣባት፤

ወላዕለ፡መንግሥት፡እንተ፡ኢትጼውዓከ፤
ስምህን ፡ በማትጠራ ፡ በመንግሥት ፡ ብልጣሶርም ፡ ቊጣህን ፡ አብዝተህ ፡ አምጣባት፤

እስመ ፡ በልዕዎ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወአማሰኑ ፡ ብሔሮ፤
የሁለቱን፡ነገድ፡ገንዘቡን፡የባቢሎን፡ ሰዎች ፡ ዘርፈውታል ፤ ገፈውታልና ፡ አገሩንም ፡ አጥፍተውበታልና ፤ ኤፍሬም፡ይበልዖ፡ለምናሴ፡ወምናሴ፡ ይበልዖ፡ለኤፍሬም፡እንዲል፡ሐተታ፡ ምነዋ ፤ ይኸንማ ፡ ያደረገ ፡ ናቡከደ ነፆር፡ አይደለም ፤ ብልጣሶር፡ ወዴት፡ አለና፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ናቡከደ ነፆር፡ ዮልማሮዴቅን ፡ ዮልማሮዴቅ ፡ ብልጣሶርን ፡ ይወልዳል ፤ ያያቱን ፡ ሥራ ፡ ለልጅ ፡ ልጁ ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ ፤ ስለከፋቱ፡ጽናት፡ያባት፡ዕዳ፡ለልጅ፤ ያፍንጫ ፡ ዕድፍ ፡ ለእጅ ፡ እንዲሉ ፤ ያውስ ፡ ቢሆን ፡ ከቡር ፡ ዳዊት፡ ይህን ፡ የተናገረው ፡ በዕርዓውያን ፡ ነው ፤ ስለምን ፡ ኤርምያስ ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች፡ ተናገረው ፡ ቢሉ ፡ ጠፊዎች ፡ ትሩፋንም ፡ መቃብያንም ፡ ናቸው ፤ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ አጥፊዎች ፤ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ጽርአውያን ፡ ናቸውና፤ ምሥጢር ፡ ለምሥጢር፡ አያይዞ፡ተናገረው፤አንድም፡ሀብተ፡ ትንቢት ፡ እየራሱ ፡ ነው ፤ ቀድሞ ፡ አባቱ፡ዳዊት፡ትንቢት፡ተገልጦለት፡ በጽርዓውያን፡ተናገረው፤ኋላ፡ልጁ፡ ግን ፡ ኤርምያስ ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ተገልጦለት፡ተናግሮታል፤አንድም፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዓው፡መዓተከ፡ላዕለ፡አሕዛብ፡እለ፡ ኢየአምሩከ ፤ በማያውቁህ ፡ በማያመ ልኩህ ፡ በአጋንንት ፡ በመናፍቃን ፡ ቍጣህን ፡ አብዝተህ ፡ አምጣባቸው፤ አሕዛብ፦አላቸው፡አጋንንትን፡በማደ ሪያቸው፤ ወላዕለ፡መንግሥት፡እንተ፡ ኢጸውአት ፡ ስመከ ፡ ስምህንም ፡ በማትጠራ፡በመንግሥት፡ዲያብሎስ፡ ቍጣህን ፡ አብዝተህ ፡ አምጣባት ፤ እስመ፡በልዕዎ፤ለያዕቆብ፡ወአማሰኑ፡ ብሔሮ ፤ የያቆብ ፡ ዘነፍስን ፡ ሃይማ ኖቱን፡አጥፍተውበታል፡ምግባሩን፡ አሰነካክለውበታልና ፡ ገነት ፡ መን ግሥተ፡ሰማያት፡እንዳይገባ፡አድርገ ውታል ፤ ሐተታ ፡ በልዕዎ ፡ አለ ፤ የበሉት፡የጠጡት፡ደስ፡እንዲያሰኝ፡ እነሱም ፡ ሃይማኖት ፡ ሲያስክዱ ፡ ምግባር፡ሲያሰነካክሉ፡ሲያጠፉ፡ደስ፡ ይላቸዋልና።

## ምዕራፍ፡፲፩፡

### ጉባዔ

፩፤ ቃል፡ዘኮነ፡ኀበ፡ኤርምያስ፡እምኀበ፡ እግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ወደ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ፡ነው፤አንድም፡ከእግዚአብሔር፡ መጥቶ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው፤ አንድም፡በኤርምያስ፡ቃል፡የተነገረ፡ ይህ፡ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ነገረ፡ዝ፡ኪዳን፤

የዚህን፡የዳግም፡ሕግን፡ነገር፡ስሙ፤ አንድም፡የመሐላን፡ነገር፡ስሙ፤

ወንግሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ይሁዳ ፡ ወለእለ ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ለሚኖሩ ሰዎች፡ይህንንም፡ነገር፡ንገራቸው፤

፫፤ ወትብሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚ ብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፡ርጉም፡ውእቱ ሰብእ፡ዘኢይሰምዕ፡ነገረ፡ዝ፡ኪዳን፡ዘአዘ ዝክዎሙ፡ለአበዊክሙ፡አመ፡ዕለተ፡አውፃ ክዎሙ፡እምድረ፡ግብፅ፡ወእምዕቶን፡ሐፂን ከግብፅ፡አገር፡ከጽኑ፡አገዛዝ፡ባወ ኋቸው ፡ ቀን ፡ አባቶቻችሁን ፡ ጠ ቁት ፡ ብዬ ፡ ያዝዝኋቸው ፤ የዳግም ሕግን፡ነገር፡የሚይሰማ፡ሰው፡ርጉም ነው ፤ አንድም ፡ የመሐላን ፡ ነገር የማይሰማ ፡ ርጉም ፡ ነው ፡ አለ ፡ የእ ራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡ብለህ ንገራቸው፤

፬፤ወእቤ፡ስምዑኒ፡ቃልየ፤

የነገርኳችሁንም፡ነገር፡ስሙኝ፤

ወግበሩ፡ኵሎ፡ዘአዘዝኩክሙ፤

ያዘዝኋችሁንም፡ነገር፡ሁሉ፡ሥሩት፤

ወትከውኑኒ፡ሕዝብየ፤

ይህን ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ እናንተ፡የፍቅር፡የሃይማኖት፡ልጆች፡ ወገን፡ትሆኑኛላችሁ፤

ወአነሂ፡እከውነክሙ፡አምላከክሙ፤

እኔም፡የፍቅር፡አባት፡እሆናችኋለሁ፤

፭፤ከመ፡ዓቅም፡መሐላየ፡ዘመሐልኩ፡ለአ በዊክሙ ፡ ከመ ፡ አህቦሙ ፡ ምድረ ፡እንተ ታውኅዝ ፡ ሀሊበ ፡ ወመዓረ ፡ በከመ ፡ ዛቲ ዕለት፤



ዛሬ፡ለናንተ፡እንደሰጠኋት፡ተድላ፡ ደስታ ፡ የማይታጣባት ፡ ከነዓንን ፡ ልሰጣቸው ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ የማል ኩትን ፡ መሐላ ፡ እንዳጸናላችሁ ፡ የፍቅር፡የሃይማኖት፡አባት፡እሆናች ኋላሁ፡ብዬ፡አልኳችሁ፤እንዲህ፡ብዬ፡ የተናገርኩት፡የዳግም፡ሕግን፡ነገር፡ ያልሰማ፡ሰው፡ርጉም፡ነው፡አለ፡የእስ ራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡ብለህ፡ ንገራቸው፤

ወአውሣእኩ ፡ ወእቤ ፡ ለይኩን ፡ እግዚኦ ፤ ይህንንም፡ቃል፡ከሱ፡ሰምቼ፡አቤቱ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይበጅ ፡ ይደረግ፡አልሁ፤

፮፤ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡አንብብ፡ዘ፡ ነገረ፡በአህጉረ፡ይሁዳ፡ወበአፍአሃ፡ለኢየሩ ሳሌም፤

እግዚአብሔርም፡በኢየሩሳሌም፡አደ ባባይና ፡ በይሁዳ ፡ አውራጃዎች ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ወስደህ ፡ አንብብ ላቸው፡አለኝ፤

ወበሎሙ፡ስምዑ፡ነገረ፡ዝ፡ኪዳን፤

የዚህን ፡ የዳግም ፡ ሕግን ፡ ነገር ፡ ስሙት፤ አንድም ፡ የመሐላን ፡ ነገር ፡ ስሙት፤

ወግበርዎ፤

ሰምታችሁትም፡የሚቀር፡አይደለም፤ አሁንም ፡ ሥሩት ፤ አድርጉት ፡ በላቸው፡አለኝ፤

፯፤ እስመ ፡ አስምዖ ፡ አስማዕኩ ፡ ለአበ ዊክሙ ፡ በዕለተ፡ አውጻእክዎሙ፡ እምድረ ፡ ግብፅ፡ወእስከ፡ዛቲ፡ዕለት፤

ከዚህ፡ቀድሞ፡ከግብፅ፡አገር፡ካወጣ ሁባቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚች ፡ ቀን፡ድረስ፡ለአባቶቻችሁ፡ስምዕዎ፡ ወግበርዎ ፡ ብዬ ፡ አዳኝቼባቸው ፡ ነበርና፤

ጊሥ፡ወአስምዕ፤

አሁንም ፡ ገሥግሠህ ፡ ሄደህ ፡ በእስ ራኤል፡አዳኝባቸው፤

ወበል፡ስምዑ፡ቃልየ፤

ሂደህም፡ቃሌን፡ስሙ፡በላቸው፤

፰፤ ወኢይሰምዑ ፡ ወኢያጽምኡ ፡ በዕዝኖሙ፤

እኔ ፡ ምከር ፡ አስተምር ፡ አልኩህ ፡ እንጂ፡ እነሱስ ፡ ያስተማርካቸውን ፡ ትምህርት ፡ በዕዝነ ፡ ሥጋቸው፤ አንድም ፡ በዕዝነ ፡ ልቡናቸው ፡ ፈጽመው፡አይሰሙህም፤

ወየሐውሩ፡ሰብእ፡በፈቃደ፡ልቦሙ፡እኩይ፤

በዚያ፡ወራት፡ሰዎች፡ሁሉ፡ያስተማር ኋቸውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራሁላ ቸውን፡ ሥርዓት ፡ ትተው ፡ በልቡ ናቸው ፡ ክፉ፡ ፈቃድ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ፤

ወአምጻእኩ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዝ ፡ ኪዳን፡ዘአዘዝኩ፡ይግበሩ፡ወኢገብሩ፤

በነቢያት፡በካህናት፡አድሬ፡ይሠሩት፡ ዘንድ፡ያዘዝኋቸውን፡ባይሠሩ፡በዚህ፡ በዳግም ፡ ሕግ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አመጣሁባቸው፡አለ፤እስመ፡እሳት፡ ትነድድ፡እመዓትየ፤ወታውዒ፡እስከ፡ ሲኦል፡ታሕተ፡ተብሎ፡የተጻፈውን፡ አመጣሁባቸው፤

፱፤ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተረክበ ፡ ማዕሌት ፡ ውስተ ፡ ዕደው ፡ ይሁዳ ፡ ወእለ ፡ ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤

እግዚአብሔርም ፡ በኢየሩሳሌምና ፡

www.ethiopianorthodox.org

በይሁዳ ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወንጀል ፡
በዝቶ ፡ ተሠርቶ ፡ ተገኘ ፡ አለኝ ፤ የድሀ ፡
ገንዘብ ፡ መቀማት ፤ እንድም ፡ የሰው ፡
ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ተገኝቷልና ፤

፲፤ ተመይጡ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአተ ፡
አበዊሆሙ ፡ ዘቀዲሙ ፡ እለ ፡ አበዩ ፡ ሰሚዐ ፡
ቃልየ ፤
ተረክበ ፡ ማዕሌት ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤
ቃሌን ፡ መስማት ፡ እምቢ ፡ ያሉበት ፡
ወደቀደሙ ፡ አባቶቻቸው ፡ ኃጢአት ፡
ተመለሱ ፤

ወናሁ ፡ እሙንቱ ፡ የሐውሩ ፡ ወይተልዉ ፡
አማልክተ ፡ ነኪር ፡ ከመ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎሙ ፤
ተመይጡ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአተ ፡
አበዊሆሙ ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤ እነሱስ ፡
እነሆ ፡ ሊገዙላቸው ፡ የከነዓንን ፡
ጣዖታት ፡ ተከትለው ፡ ሄዱ ፤

ወዐለዉ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ወቤተ ፡ ይሁዳ ፡
ሕግየ ፡ ዘሠራዕኩ ፡ ለአበዊሆሙ ፤
የሐውሩ ፡ ወይተልዉ ፡ አማልክተ ፡
ነኪር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፤ በኒህም ፡
በጣዖታቱ ፡ ዓሥሩና ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ቀድሞ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የሠራሁላ
ቸውን ፡ ሕግ ፡ ወነጀሉ ፤

፲፩፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚ
አብሔር ፤
እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ስለበደሉት ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብየ ፡
ዘኢይክሉ ፡ ወጺአ ፡ እምኔሁ ፤
እነሆ ፡ እኔም ፡ በወገኖቼ ፡ በእስራኤል ፡
ከመከራው ፡ መዳን ፡ የማይቻላቸውን ፡
ጽኑ ፡ መከራ ፡ አመጣባቸዋለሁ ፤

ወይጸርሑ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢይሰምአሙ ፤
ከመከራው ፡ ጽናትም ፡ የተነሣ ፡ ወደኔ ፡
ይጮሃሉ ፤ ይለምናሉ ፤ እኔም ፡ አልሰማ
ቸውም ፤

፲፪፤ ወየሐውሩ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ፡ ወእለ ፡
ይነብሩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወይጸርሁ ፡ ኀበ ፡ አማል
ክቲሆሙ ፡ እለ ፡ የዓጥኑ ፡ ሎሙ ፤
በይሁዳ ፡ አገሮችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡
ሄደው ፡ ወደሚያጥኑላቸው ፡ ወደ ፡
ጣዖታቱ ፡ አድኑን ፡ እያሉ ፡ ይጮሃሉ ፤
ይለምናሉ ፤

ወአድኅኖ ፡ ኢያድኅንዎሙ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡
ምንዳቤሆሙ ፤
ጣዖታቱም ፡ በመከራቸው ፡ ቀን ፡ አያድ
ኗቸውም ፤

፲፫፤ እስመ ፡ በኍልቈ ፡ አህጉሪክሙ ፡
ከማሁ ፡ አማልክቲክሙ ፤
ይጸርሑ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢይሰምአሙ ፡
ብሎዋቸው ፡ ነበርና ፡ እኛ ፡ እየለመንህ ፡
አንተ ፡ የማትሰማን ፡ በምን ፡ ነገር ፡
ነው ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ አሁን ፡ እንደተ
ናገርኩት ፡ አማልክቶቻችሁ ፡ ባገሮ
ቻችሁ ፡ ቍጥር ፡ ናቸውና ፡ ስለዚህ ፡
ነው ፤ አንድም ፡ ከማሆሙ ፡ አማልክ
ቲክሙ ፡ ይላል ፡ ያገሮቻችሁ ፡ ቍጥሮ
ቻቸው ፡ ብዙ ፡ እንደሆኑ ፡ ጣዖቶቻ
ችሁም ፡ እንደነዚያ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡
ስለዚህ ፡ ነው ፤

ወበኍልቈ ፡ ፍናዊሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡
ገበርክሙ ፡ ምሥዋዓ ፡ ለሐፍረት ፡ ከመ ፡ ት
ዕጥኑ ፡ ለበዓል ፤
በኢየሩሳሌም ፡ በጐዳናዎቿ ፤ አንድም ፡
በመንደሮቿ ፡ ቍጥር ፡ ለጣዖቱ ፡ ልታጥኑ ፡
ጣዖቱ ፡ ምሥዋዕ ፡ ጸፈጸፋችሁ ፡
ዊሃ ፡ ለጽዮን ፡ ይላህዋ ፡ እንዲል ፤
ተታ ፡ ሐፍረት ፡ አለው ፡ ጣዖቱን ፤
ብሩ ፡ ሐፍረት ፡ ያለውንም ፡ በዓል ፡
ሎ ፡ ገለጠው ፤ አንድም ፡ ገበርክሙ ፡
ሥዋዓ ፡ ከመ ፡ ትዕጥኑ ፡ ለበዓል ፡ ለሐ
ረትክሙ ፡ ይላል ፤ ኋላ ፡ ሐፍረት ፡ ጕስ
ልናችሁ ፡ ሊገለጥባችሁ ፡ ከዚህ ፡
ቀድሞ ፡ ለጣዖቱ ፡ ልታጥኑ ፡
ትሠዉ ፡ ምሥዋዕ ፡ ጸፈጸፋችሁለት ፤

፲፬፤ ወአንተሂ ፡ ኢትጸሊ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፤
ሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ግን
ህ ፡ ወገኖች ፡ አትለምንላቸው ፡ አለ ፤
ት ፡ ሰውን ፡ በተጣላበት ፡ ወራት ፡
ማላጅ ፡ ይነሣል ፤

ኢታስተብቍዕ ፡ ወኢትስአል ፡ በጸሎት ፡
ሙ ፤
እነዚህ ፡ ወገኖች ፡ በልመናህ ፡ አትለ
ምንላቸው ፤ አታማልዳቸው ፤

ስመ ፡ ኢይሰምእ ፤
ትለምነኝ ፡ ብትማልደኝ ፡ አልሰማ
ምና ፤ አመ ፡ ምንዳቤሆሙ ፡ ሶበ ፡
ጼውዑኒ ፡ ማገሻ ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ስመ ፡ ኢይሰምአሙ ፡ አመ ፡ ምንዳ
ሆሙ ፡ ሶበ ፡ ይጼውዑኒ ፡ እነሱም ፡
ኔን ፡ በድለው ፡ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡
ለምኑኝ ፡ አልሰማቸውም ፡ እኮን ፤

፲፭፤ ለምንት ፡ ሊተ ፡ ለፍቅርትየ ፡ ውስተ ፡
ትየ ፡ ገቢረ ፡ ምሥዋዕ ፡ ብዙኀ ፤
ኔ ፡ እወዳት ፡ ለነበረ ፡ ለቤተ ፡
ስራኤል ፡ በኃጢአት ፡ ሁና ፡ በቤተ ፡
መቅደስ ፡ ብዙ ፡ መሥዋዕት ፡ የምታቀ
ብልኝ ፡ ለምኔ ፡ ነው ፤ አልቀበላትም ፤
አንድም ፡ ለፍቅርትየ ፡ እሱዋ ፡ በሕግ ፡
በአምልኮት ፡ ትወደኝ ፡ ለነበረ ፡ ለቤተ ፡
እስራኤል ፤ ገቢረ ፡ ምሥዋዕ ፡ ብዙኀ ፡
ሊተ ፡ ለምንት ፤ በኃጢአት ፡ ሁና
በቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሥዋዕቱን ፡
አብዝታ ፡ ለኔ ፡ የምታቀርብልኝ ፡
ማቅረብ ፡ ለምኑዋ ፡ ነው ፤ ላይረባት ፡
ላይጠቅማት ፡ የወዳጅ ፡ ጠቡ ፡ ጽኑ ፡
ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

ወሥጋ ፡ ቅዱስ ፡ የዓትት ፡ እምላዕሌኪ ፡
በእከይኪ ፤
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሁነሽ ፡ ያቀረብ
ሽውን ፡ መሥዋዕት ፡ ካንቺ ፡ ያርቃልና ፤
አንድም ፡ ተአተተ ፡ ከአንቺ ፤ ርቋልና ፤
አንድም ፡ የዓትቶ ፡ ለእከይኪ ፡ መቅሠ
ፍቱን ፡ ያርቅልሻል ፡ አለ ፤ መቅሠ
ፍቱን ፡ እከይ ፡ አለው ፤ በክፋቷ ፡ ስለመ
ጣባት ፤

ወበዝኒ ፡ ኢትድኅኒ ፤
በዚህም ፡ አትድኚም ፤

እስመ ፡ እከይኪ ፡ አሜሃ ፡ ያፈርሃኪ ፤
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሁነሽ ፡ ሳለ ፡
የመጣብሽ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ያንጊዜ ፡ ያስ
ፈራሻልና ፤ አንድም ፡ እንዳለ ፡
ይሆናል ፤ የሠራሽው ፡ ክፋትሽ ፡ መቅሠ
ፍቱን ፡ አምጥቶ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስ
ፈራሽ ፡ ስለሆነ ፤

፲፮፤ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ሠናይተ ፡ ራእይ ፡
ወፍሬሃኒ ፡ ወአዕጹቂሃኒ ፡ ብዙኀ ፡ ጸውዓ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ስመኪ ፤
ቅጠሏ ፡ አበባዋ ፡ ያማረ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡
ብሎ ፡ ጠራሽ ፤ አንድም ፡ ምግባርሽ ፡
ሃይማኖትሽ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ የአብ
ርሃም ፡ ልጅ ፡ ብሎ ፡ ጠራሽ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እምቃለ፡ምረታ፡ዓቢይ፡ነደ፡እሳት፡ላዕሌሃ፡
ነዳዲትም ፡ ይላል ፤ ተቆጥታ ፡ ከመ
ናገሯ ፡ የተነሣ ፤ አንድም ፡ እምቃለ፡
ምትረታ ፡ ይላል ፤ ከእግዚአብሔር ፡
የሚለይ ፡ ነገር ፡ ከመናገሯ ፡ የተነሣ ፡
ጦር፡መቅሠፍት፡በዝታ፡መጣችባት፤

ወማሰኑ፡አዕፁቂሃ፡
ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ብሎዋት ፡ ነበረና ፡
አዕፁቂሃ፡አለ፡እንጂ፤ልጆቹዋ፡የልጅ፡
ልጆቹዋም፡ከሱዋ፡ተለይተው፡ጠፉ፤

፲፯፤ ወእግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ኃይል ፡
ዘተከለኪ ፡ ነበበ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌኪ ፡ በእንተ ፡
ኃጢአተ፡እስራኤል፡ወቤተ፡ይሁዳ፤
ኃይል ፡ የሚያደርግ ፡ ፈጣሪሽ ፡ እግዚአ
ብሔርም ፡ በዓሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ኃጢአት ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ተናገረብሽ፤

እስመ፡ገብሩ፡በዘያምዕዑኒ፤
እኔን፡በሚያሳዝኑ፡ገንዘብ፡እኔን፡የሚ
ያሳዝኑበትን፡ሥራ፡ሠርተዋልና፤

ወዓጠኑ፡ለበዓል፤
እኔን ፡ ትተው ፡ ለጣዖቱ ፡ መሥዋዕት ፡
አቀረቡ፤ዕጣን፡አጠኑ፤

፲፰፤ እግዚኦ፡አርዕየኒ፤
አቤቱ ፡ የእስራኤልን ፡ ነገር ፡ ግብራ
ቸውን፡ግለጥልኝ፤(አሳየኝ፤)

ወአእምር፤
እኔም ፡ የእስራኤልን ፡ ግብራቸውን ፡
መርምሬ፡ልወቅ፤

አሜሃ፡አርአይከኒ፡ምግባሮሙ፤
አንተ፡ከዚህ፡ቀድሞ፡የእስራኤልን፡
ግብራቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ገልጠ

ህልኝ፡ነበር፤

፲፱፤ ወአንሰ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ የዋህ ፡ ዘ
ስድዎ፡ይጥብሕዎ፤
እኔስ፡ሊያርዱት፡ሊያወራርዱት፡
ወስዱት ፡ በግ ፡ እንዲታረድ ፡ እን
ራረድ ፡ ሳያውቅ ፡ እንዲሄድ
እስራኤል፡ ሊገርፉኝ ፡ ሊገድሉ
ሲወስዱኝ፡ሳላውቅ፡እሄዳለሁ፤

ወኢያእመርኩ፤
የምገረፍበትን ፡ መከራዬን ፡ አ
ቅሁም፡አለ፤ዕውቀቱ፡የጸጋ፡ነው

ተማከሩ፡ላዕሌየ፡እኩየ፡ምክረ፤
እንግደለው፡ብለው፡በኔ፡ክፉ፡ም
መከሩብኝ፤

ወይቤሉ፡ንዑ፡ንደይ፡ዕፀ፡ውስተ፡ኅብስ
በሚበላው ፡ በሚጠጣው ፡ መር
ጨምረን፡ሰጥተን፡እንግደለው፡አ

ወንቀጥቅጦ፡እምድረ፡ሕያዋን፤
እሱንም ፡ ገድለን ፡ ከአብርሃም
ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ አገር
እናጥፋው፡ አሉኝ ፤ ሐተታ፡ ሕያዋ
አላቸው ፤ በነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ናቸው
አንድም፡ኋላም፡ያሥነሳቸዋልና፤

፳፤ ወኢይዝክሩ፡እንከ፡ስሞ፤
እንግዲህ፡ወዲህ፡ኤርምያስ፡ብለ
ስሙን፡እንዳይጠሩት፤

እግዚአብሔር፡መኰንነ፡ጽድቅ፡ዘይፈት
ልበ፡ወኵልያተ፤
እንዲህም ፡ ማድረጋቸው ፡ ልብ
ያጤሰውን፡ኵላሊት፡ያመላለሰው
መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ ፈታሂ
በጽድቅ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ እውነተኛ
ዳኛ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔርን



፡ እሱ ፡ ያስተማራቸው ፡ እስራ
፡ እንዳይጠሩ ፡ ነው ፤ አንድም፡
ር፡ ይላል ፡ ነቢዩ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ፡
አብሔር ፡ እያለ ፡ የእግዚአብ
ን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ እንዳያስተምር፡
፤ አንድም ፡ ኢይዝክር ፡ ይላል ፤
፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤
፡ ካስተማራቸው ፡ ከእስራኤል ፡
ም፡አንዱ፡የፈጣሪው፡የእግዚአ
ርን ፡ ስም ፡ እንዳይጠራ ፡ ነው፤
ድም ፡ እግዚኦ ፡ አርእየኒ ፤ አቤቱ ፡
ይሁድን፡ግብራቸውን፡ግለጥልኝ፡
ል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤
እምር፤ እኔም ፡ ግብራቸውን ፡
ምሬ፡ልወቅ፡አለ፡ስለ፡ሥጋ፡እን
ነት፤ አሜሃ ፡ አርአይከኒ ፡ ምግ
ሙ፤ከዚህ፡ቀድሞ፡ግብራቸውን፡
ምረህ ፡ አሳይተኸኝ ፡ ነበር፤
ንሰ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ የዋህ ፡ ዘይወ
ዎ ፡ ይጥብሕዎ ፡ እኔስ ፡ ያመት ፡
ል ፡ በግ ፡ ሊያርዱት ፡ ሊያወራ
ት፡ አሥረው ፡ ስበው ፡ ጐትተው ፡
ወስዱት ፡ ጨው ፡ ሊያልሱኝ ፡ ሣር ፡
ጐርሱኝ ፡ ነው ፡ መስሎት ፡ ሳያ
ቅ፡ተከትሏቸው፡እንዲሄድ፡እኔም፡
ለተ ፡ ዓርብ ፡ ሊሰቅሉኝ፣ ሊቸነ
ኝ፣ ሊገድሉኝ ፡ አሥረው ፡ ጐት
ው፣ ከሊቶስጥራ ፡ ወደቀራንዮ ፡
ወስዱኝ ፡ ሞቴን ፡ በባሕርይ ፡ ዕው
ቴ፡እያወቅሁ፡በኀዳጌ፡በቀልነቴ፡ተከ
ቸው ፡ እሄዳለሁ ፤ ወኢያእመርኩ ፤
ሰቀልበትን፡የምገረፍበትን፡ግብር፡

አላውቀውም ፡ አለ ፤ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡
ነውና፤ ወተማከሩ ፡ ላዕሌየ ፡ እኩየ
ምክረ ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ሰቅለን ፡ እንግ
ደለው ፡ ብለው ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡
ተማከሩ ፤ ወይቤሉ ፡ ንዑ ፡ ንደይ ፡ ዕፀ ፡
ውስተ ፡ ኅብስቱ ፡ ውስተ ፡ ትስብእቱ ፡
ሲል ፡ ነው ፤ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ሥጋ ፡
በመልበሱ ፡ ሰቅለን ፡ እንግደለው ፡
አሉ፤ወንቀጥቅጦ፡እምድረ፡ሕያዋን፤
ከአብርሃም፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡
አገር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ገድለን ፡
እናጥፋው፡አሉ፤
ወኢይዝክሩ ፡ እንከ ፡ ስሞ ፤ ክርስቶስ ፡
ያስተማራቸው ፡ ምዕመናን ፡ ነአምን ፡
ሞቶ ፡ ወትንሣኤሁ ፡ ብለው ፡ የክርስ
ቶስን ፡ ስም ፡ እንዳይጠሩ ፤ አንድም ፡
ወኢይዝክር ፡ የእግዚአብሔርነቱን ፡
ስም፡እንዳይጠራ፡አለ፤አቡየ፡ፈነወኒ፡
ወአነ፡ተፈኖኩ፡ብሎ፤አንድም፡ወኢ
ይዝክር ፡ እንከ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፤
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ሐዋርያ ፡ ወረደ ፡
ተወለደ ፡ ሞተ ፤ ተነሣ፡ ብሎ ፡ የፈጣ
ሪው፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እንዳይ
ጠራ፤እግዚአብሔር፡መኰንነ፡ጽድቅ፡
ዘይፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ ልቡና ፡
ያመላለሰውን ፡ ኩላሊት ፡ ያጤሰውን ፡
መርምሮ፡የሚያውቅ፡እግዚአብሔር፡
ፈታሂ፡በጽድቅ፡ኰናኒ፡በርትዕ፡ነው፡
ፍታሕ፡ ማንሻ ፡ አንድም ፡ ዘትፈትን ፡
ይላል፡ልቡና፡ያመላለሰውን፡ኩላሊት፡
ያጤሰውን ፡ መርምረህ ፡ የምታወቅ ፡
ኰናኒ፡በጽድቅ፡ፈታሂ፡በርትዕ፡ፍታህ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሊተ፡እምኔሆሙ፡ፍረድልኝ፤እስመ፡
ለከ ፡ ነገርኩ ፡ ቅስትየ ፡ ወቀሳዬን ፡
ነገሬን ፡ ላንተ ፡ ተናግሬያለሁና ፤
አንድም ፡ ኢዮብ ፡ ድኃ ፡ ግፉን ፡
በደሉን፡ ለዳኛ ፡ ያመልክት ፡ ከዚያ ፡
በኋላ ፡ ዳኛ ፡ ይከራከርለት፤ ይሟገ
ትለት ፡ እንዳለ ፡ መኰንን ፡ ጽድቅ ፡
ብሎት፡ነበርና፡ነገርኩ፡ቅስትየ፡አለ፤

፳፩፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብዬ፡ባስ
ተምራቸው፡አንሰማም፡አንቀበልም፡
ስላሉኝ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ላዕለ ፡ ሰብአ ፡ አናቶት ፡ እለ ፡ የኃሥሥዋ ፡
ለነፍስየ፡
ሰውነቴን፡ለጥፋት፡በሚፈልጓት፤
እለ ፡ ይብሉ ፡ ኢትትነበይ ፡ በስመ ፡ እግዚአ
ብሔር፡
ከመዝ ፡ ይቤ፤ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡
ትንቢት፡አትናገር፤
እመ፡አኮ፡ትመውት፡በእደዊነ፡
እምቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፡ በእጃችን ፡
ትሞታለህ፤ ትጠፋለህ ፡ በሚሉ ፡
በአናቶት ፡ ሰዎች ፡ በመዓት ፡ አለሁ
ባቸው፡አለ፤

፳፪፤ወበበይነ፡ዝንቱ፡ከመ፡ዝ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡ኃያል፡
ስላልተመለሱ ፡ አምጻኤ ፡ ዓለማት ፡
ወላዴ ፡ ፍጥረት ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤
ናሁ፡አነ፡እዋህዮሙ፤
እነሆ፡እኔ፡በመዓት፡እጐበኛቸዋለሁ፡
አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዋህ
ያለውን፡ይተረትራል፤
ወራዙቶሙኒ፡ይመውቱ፡በኲናት፤
ለጦር፡ለጋሻ፡የበቁ፡ጐልማሶቻ
ዘመቻ ፡ ሒደው ፡ ተዋግተው ፡ በ
ይሞታሉ፤
ወደቂቆሙኒ ፡ ወአዋልዲሆሙኒ ፡ የ
በረኃብ፡
ለጦር፡ለጋሻ፡ያልበቁ፡ወንዶች
ቻቸውና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው፡
በከተማ ፡ ቀርተው ፡ በቀ
ያልቃሉ፤

፳፫፤ወአልቦ፡ዘይተርፍ፡እምኔሆሙ
ከነሳቸው ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰ
የሚቀር፡የለም፤
እስመ፡አመጽእ፡እኪተ፡ላዕለ፡እለ፡ይ
በአናቶት፡በዓመተ፡እሔውፆሙ፤
እነሱን ፡ በመዓት ፡ በጐበኝሁ
ዘመን ፡ አንተን ፡ በበደሉ ፡ በአና
ሰዎች ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ አመጣ
ለሁና።

## ምዕራፍ፡፲፪፤

፩፡ጻድቅ፡አንተ፡እግዚአ፡
አቤቱ ፡ አንተስ ፡ ፈታሒ ፡ በጽ
ኵናኒ፡በርትዕ፡እውነተኛ፡ዳኛ፡ነ
እስመ፡እትዋቀስ፡በኀቤከ፤
ባንተ፡ዘንድ፡እከራከራለሁና፤
ወባሕቱ፡ፍትሐ፡እትናገር፤
እሴአል፡ሲል፡ነው፤ነገር፡ግን፡ፍ
እጠይቅሃለሁ፤
ለምንት፡ፍኖተ፡ኃጥአን፡ድሉት፡ይእቲ
ጠላቶችህ፡ኃጥአን፡በተድላ፡በደስ
ለምን፡ተዘጋጅተው፡ይኖራሉ?



ወተፈሥሑ፡ኵሎሙ፡ዓላውያን፡በማዕሌት፡
አንተን፡የሚወነጅሉ፡ጠላቶችህ፡በወ
ንጀላቸው ፡ ሳሉ ፡ ለምን ፡ ደስ ፡
ብሏቸው፡ይኖራሉ፤

፪፡ወተከልከሙ፡ወሰፍሐ፡ሥርዎሙ፤
አንተም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ለምን ፡
አጸናሃቸው፤አባትነታቸውም፡ለምን፡
ጸንቶ፡ይኖራል፤
ወገብሩ፡ፍሬ፡
ለምን፡ልጅ፡ወለዱ፤አንድም፡ወተከ
ልከሙ ፡ በተድላ ፡ በደስታው ፡ አጸና
ሃቸው፤
ወሰፍሐ፡ሥርዎሙ፡
ልጃቸው፡በዛ፤ሐተታ፡ሥር፡አለው፡
ልጁን ፡ ለሚመጣው ፡ ሥር ፡ ነውና ፤
ወገብረ፡ፍሬ፡ልጃቸው፡የልጅ፡ልጅ፡
ወለደ፤
ቅሩብ፡አንተ፡ውስተ፡አፉሆሙ፡ወርኁቅ፡
እምነ፡ኵልያቲሆሙ፤
ቢወዱኝ ፡ እንጂ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡
በአፋቸው፡ወደድንህ፡እናመልክሃለን፡
ይሉሃል ፤ በልባቸው ፡ ግን ፡ ሩቅ ፡ ነህ ፡
ማለት፡አያምኑብህም፡ይጠሉሃል፤

፫፤ ወለሊከ ፡ እግዚአ ፡ ተአምረኒ ፡ ወትሌ
ብወኒ፡
ኤርምያስ፡አንተስ፡ከነሱ፡ሌላን፡ነህ?
ትለኝ ፡ እንደሆነ፤ አቤቱ ፡ እኔ ፡ እንደ
ነሱ፡እንዳይደለሁ፡አንተ፡ፈጽመህ፡
መርምረህ፡ታውቀኛለህ፤
ወፈተንኮ፡ለልብየ፡በቅድሜከ፡
ቅሩብ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡
ወርኁቅ ፡ እምነ ፡ ኵልያቲሆሙ ፡
ብሎት፡ነበርና፤
አንተስ ፡ በአፍህ ፡ ትወደኝ፤ በልብህ ፡
ትከዳኝ፡እንደሆነ፡ማን፡ያውቅልሀል፡
ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ የኔንስ ፡ ልቤ ፡
ያጤሰውን፡ኵላሊቴ፡ያመላለሰውን፡
መርምረህ ፡ ታውቀዋለህ፤ ዘወትር ፡
በፊትህ ፡ ነው፤ በፊት ፡ ያለ ፡ እንዳይ
ሠወር፡አይሠወርህም፤
ትጸንሖሙ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ለተጠብሖ፡
ወተፈሥሖ ፡ ኵሎሙ ፡ ዓላውያን ፡
በማዕሌት ፡ ወሰፍሐ ፡ ሥርዎሙ፡
አሏሁ፡እንጂ፡ኋላስ፡በግን፡እንዲያ
ርዱት ፡ እንዲጠብቁት ፡ ትጠብቃቸ
ዋለህ፤
ወትቄድሶሙ፡ለዕለተ፡ቀትል፡
የሚታረዱ ፡ በጎችን ፡ ከመንጋ ፡
ለይተው፡እንዲወስዷቸው፡እነሱንም፡
በሚጠፉበት ፡ ቀን ፡ ከወገኖቻቸው ፡
እየለየህ፡ለጥፋት፡ትወስዳቸዋለህ፤

፬፡እስከ፡ማዕዜኑ፡ትላሁ፡ምድር፡ወየብሰ፡
ሣዕረ ፡ ገዳም ፡ በእከየሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስቴታ፡
ውስቴታ ፡ ለሀገር ፡ ነው ፤ በሀገሪቱ ፡
በሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡ ክፋት ፡ ምድር ፡
የምታለቅስ ፡ የምድረ ፡ በዳው ፡ ሣር ፡
የሚደርቅ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡
አለ፤ ትላሁን ፡ አይሻውም ፡ የብሰ ፡
ሣዕረ ፡ ገዳም ፡ ያለውን ፡ ነው፤ ይህ ፡
በቁሙ ፡ ነው፤ አንድም ፡ የሰዎቹን ፡
ማልቀስ ፡ የሰዎቹን ፡ መጐስቈል ፡
ለምድር ፡ ለሣዕር ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ፤
አንድም ፡ ለምንት ፡ ይላል፤ በሀገሪቱ፤
በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ክፋት፡ ምድር ፡
ትሑታኑ ፤ ሣዕር ፡ ሠራዊቱ ፡
የተማረኩ፡ ስለምንድነው፤ አንድም ፡
እንዳለ ፡ ይሆናል፤ እነዚያ ፡ በበደሉ ፡
እነዚህ ፡ የሚማረኩ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ድረስ፡ነው፤ሐተታ፡ባንዱ፡ኃጢአት፡
አንዱ ፡ ተጨምሮ ፡ መጥፋቱ ፡ እስከ ፡
ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ነውና፤ እስከ ፡
ማዕዜኑ፡አለ፤
ኢያመሥጥ ፡ ጸድቅ ፡ እምነ ፡ ጸሐፉ ፡
ለኃጥእ ፡ እንዳለ ፡ ነቢዩ ፡ ሚራክ፤
የኃጥአን ፡ ዳፋ ፡ ጻድቃንን ፡ ይጋፋ ፡
ሲል፤ነው፤

ወኅልቁ፡እንስሳ፡ወአዕዋፍ፤

በሰው ፡ ኃጢአት ፡ እንስሳትም ፡
አዕዋፍም ፡ አለቁ ፡ አለ፤ ድርቁ ፡
ሰውንም፡እንስሳትንም፡አዕዋፍንም፡
ያስተባብራልና፤ አንድም ፡ እንስሳ ፡
አዕዋፍ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው፤
እንስሳ፡ያላቸው፡በሀገር፡ያሉ፡ሰዎች፡
ናቸው ፤ አዕዋፍ ፡ ያላቸው ፡ ዘማቾች ፡
ናቸው፤እነዚህ፡ሁሉ፡አንድ፡ሁነው፡
ጠፉ፤

እስመ፡ይቤሉ፡አልቦ፡ዘይሬኢ፡ደኅራተነ፡

ፍጻሜ ፡ ነገራችነን፤ አንድም ፡ የነገራ
ችነን ፡ ፍጻሜ ፡ መርምሮ ፡ የሚያ
ውቀው፡የለም፤አይኑር፡ብለዋልና፤

፭፤አዕጋሪከ፡ይረውጹ፡ወይደክሙከ፡

የሰው ፡ ሁሉ ፡ እግር ፡ ጣዖት ፡
ለመፈለግ፡ ይፋጠናል ፤ ጣዖት ፡
ለመፈለግ፡የሚፋጠን፡የሰው፡ሁሉ፡
እግር፡ይደክማል፤

ለምንት ፡ ታስተሬሲ ፡ አፍራስ ፡ በብሔረ ፡
ስንዕ፡እንተ፡ትትአመን፤

፬ኤል ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተህ፡ ጣዖት ፡
አምልከህ ፤ ጠላት ፡ ጠፍቶላት፡ ተዘ
ልላ ፡ ተስማምታ ፡ በምትኖር ፡ አገር
ኢየሩሳሌም ፡ አባር ፡ ቸነፈር ፡ ጦ...

እንዲመጣ ፡ ለምን ፡ ታደርጋለህ
አንድም ፡ ዝዋት ፡ እንጅሞን
የሚፈልግ፡እግር፡ይሮጣል፤ ዝዋት
እንጅሞን ፡ በመፈለግ ፡ ይደክማል
የቀረው፡አይለወጥም፤አንድም፡እስ
ራኤልን፡የሚመክር፡የሚያስተምር
ነቢይ ፡ ካህን ፡ ይሮጣል፤ ለመምከር
ለማስተማር፡የሚሮጥ፡ነቢይ፡ካህን
ይደክማል ፤ ለምንት ፡ ታስተሬሲ
ጠላት ፡ ጠፍቶላት ፡ ተዘልላ
ተስማምታ፡በምትኖር፡ኢየሩሳሌም
ጦር፡እንዲመጣ፡ለምን፡ታደርጋለህ
ይሉታል፡ነቢዩን፤አንድም፡ወባሕቱ
ፍትሐ ፡ እነግር ፡ ለምንት ፡ ፍኖተ
ኃጥአን ፡ ድሉት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፤ አ
ነቢይ ፡ አዕጋሪከ ፡ ይረውፃ ፡ ወይደ
ክማከ ፡ ይላል፤ ነቢይ ፡ የኔን ፡ ፍርድ
የኔን ፡ ባሕርይ ፡ ለመመርመር
ልቡናህ፡ይፋጠናል፤
ወይደክማከ፡ የኔን ፡ ፍርድ ፡ የኔን
ባሕርይ ፡ ለመመርመር ፡ የሚፋጠን
እግረ፡ልቡናህ፡ይደክማል፤ለምንት
ታስተሬሲ ፤ የማይመረመር ፡ እንደፈ
ረሰኛ፡ካለ፡ከኔ፡ባሕርይ፡ጋራ፡የሚመ
ረመር ፡ ያንተን ፡ ባሕርይ ፡ ለምን
አንድ ፡ ታደርጋለህ ፤ እግረኛ ፡ በፈ
ረሰኛ ፡ ቢሮጥ ፡ ይደርስበታልን ፤ አን
ተስ ፡ የኔን ፡ ባሕርይ ፡ መመርመር
ይቻልሀል?

ወእፎ፡ትገብር፡በኃሣረ፡ዮርዳኖስ፡

በታሕተ፡ዮርዳኖስ፡ሲል፡ነው፤ከዮር
ዳኖስ ፡ በታች ፡ በዕበየ ፡ ዮርዳኖስ



ከዮርዳኖስ፡በላይ፡ኃጢአት፡ሠርተህ፡
ጣዖት፡አምልከህ፡እስራኤል፡ጦር፡
እንዲመጣ ፡ ለምን ፡ ታደርጋለህ ?
ይላል፡ ነቢዩ ፤ አንድም ፡ ከዮርዳኖስ ፡
በላይ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ በታች ፡ ጦር ፡
ይመጣል ፡ ለምን ፡ ትላለህ ፡ ይሉታል ፡
ነቢዩን፤

፮፤እስመ፡አኃዊከ፡

የናትህ፡ወገኖች፤

ወቤተ፡አቡከ፡እሙንቱ፡ክህዱከ፡

ያባትህ ፡ ወገኖች ፤ አንድም ፡ እስመ ፡
አኃዊከ ፤ በትውልድ ፡ የራቁ ፡
ወገኖችህ፡ ወቤተ ፡ አቡከ፡ የቀረቡ ፡
ወገኖችህ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ክደው
ሀልና፤

ወወውዑ፡ወአንገለጉ፡በድኅሬከ፡ብዙኃን፡

ብዙ ፡ ወገኖችህም ፡ ባንተ ፡ ዶለቱ ፡
አገረሩ፤ደነፉ፤

ኢትእመኖሙ፡እመ፡ሠናየ፡ነበቡ፡ላዕሌከ፡

ወንድማችን ፡ ወዳጃችን ፡ መምህ
ራችን፡ ብለው ፡ በጎ ፡ በጎ ፡ ነገርም ፡
ቢናገሩህ፡አትመናቸው፤

፯፤ኀደጉ፡ቤትየ፡

ቤቴን፡ተውኩ፡አለ፡በቁሙ፤

ወኅደጉ፡ርስትየ፤

እናቶትን፤አንድም፡ኅደጉ፡ቤትየ፡እስ
ራኤልን ፤ ወኅደጉ ፡ ርስትየ ፡ ቤተ ፡
መቅደስን፡ተውሁ፤

ወወሀብክዋ፡ለፍቅርተ፡ነፍስየ፡ውስተ፡እደ፡
ፀሬ፤

ልቡናዬ፡ይወዳት፡የነበረ፡እናቶትን፡
በጠላቷዋ ፡ እጅ ፡ ጣልሁዋት ፡ አለ ፤
ላገር፡ጠላቷ፡ባላባቷ፡ነውና፤

፰፤ወከነተኒ፡ሊተ፡ርስትየ፡ከመ፡አንበሳ፡

ርስቴ፡እናቶት፤አንድም፡ርስቴ፡ቤተ፡
መቅደስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡
አንበሳ፡ሆነችብኝ፡አለ፤ያ፡እንዲያ
ስፈራ፡አስፈራችኝ፤ጥሕረት፡ማገሻ፤
አንድም ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ በገዳም ፡
ጥሕረት ፡ ላዕሌየ፤ ያ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡
ያለ፡ አንበሳ ፡ ሰው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እንዲ
ያናፋ፤ እንዲጮህ ፡ እሱዋም ፡ እኔን ፡
ባየችኝ ፡ ጊዜ ፡ አገረረችብኝ ፡ ደነፋ
ችብኝ፤

በእንተ፡ዝንቱ፡ጸላእክዋ፡

እኔን ፡ ባየችኝ ፡ ጊዜ ፡ ስላገረረችብኝ፤
ስለደነፋችብኝ ፡ የተወለድኩባት ፡
አገሬ ፡ እናቶትን ፤ አንድም ፡ ቤተ ፡
መቅደስን፡ጠላኋት፤

ጉባዔ፤

፱፤ ግበ፡ዝዕብኑ፡ቤትየ፡ወሚመ፡በዓተ፡
ፈያት፡ይእቲ፡ርስትየ፤

ቤቴ፡ቤተ፡መቅደስ፡የጅብ፡ጉድጓድን፡
ናት ? ወይስ ፡ ርስቴ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡
የወምበዴ፡የቀማኛ፡ዋሻ፡ናት፤

ዘየዓውዱ፡ዓውዳ፤

የጅብን ፡ ጉድጓድ ፡ የሌባን ፡ ዋሻ ፡
ከበው ፡ እንዲደበድቧት ፡ እሱዋንም ፡
ዳር፡ዳር፡የሚሉዋት፤አንድም፡ያቺን፡
ዙሪያዋን ፡ እንዲከቧት ፡ ይህቺንም ፡
አሕዛብ፡የሚከቧት፤አንድም፡የጅብ፡
ጉድጓድ፡ነበረች ? ወይስ፡የወንበዴ፤
የቀማኛ ፡ ዋሻ ፡ ነበረች ፤ የጅብ ፡
ጉድጓድ፤የቀማኛ፡ዋሻ፡እንዲከበብ፡
አሕዛብ፡ከበዋት፡የሚቆሙ፡በኃጢአ
ታቸው፡አይደለም፡ለማለት፤

ወይትጋብኡ፡ኵሎሙ፡አራዊተ፡ገዳም፡

ተፈታ፡ጠፍታ፡አራዊት፡ሁሉ፡ይሰበ
ሰቡባታል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይመጽኡ፡ይብልዕዋ፡
እነሱ ፡ ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ከጽርዕ ፡
ከሜዶን ፡ ከተት ፡ ሠራዊት ፡ ምታ ፡
ነጋሪት፡ብለው፡ይመጣሉ፤

፲፡ ኖሎት ፡ ብዙኃን ፡ አማሰኑ ፡ ዐፀደ ፡
ወይንየ፡
ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡ እንሥራ ፡
እንቀጣ፡ ብለው፤ እንድም ፡ ነቢያት ፡
ካህናት ፡ እንመክር ፡ እናስተምር ፡
ብለው ፡ የሕጌ ፡ ማደሪያ ፡ ቤተ ፡ እስራ
ኤልን፡አጠፉ፤

ወአርከሱ፡መክፈልትየ፡
እድል ፡ ፈንታዬ ፡ ጽዋ ፡ ተርታዬ ፡
አናቶትን፤እንድም፡ቤተ፡መቅደስን፡
ገብተው፡አረከሱዋት፡አለ፡አሕዛብ፤
እንድም ፡ ነገሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡
ኃጢአት፡እየሠሩባት፡ጣዖት፡እያመ
ለኩባት፤

ወረሰይዋ፡ለመክፈልትየ፡እንተ፡አፈቅር፡
በድወ፡ወዐፀ፡
ቀድሞ ፡ እኔ ፡ የምወዳት ፤ እንድም ፡
እንተ ፡ ታፈቅር ፡ እሱዋ ፡ እኔን ፡
ትወደኝ፡ የነበረች ፤ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡
ጽዋ ፡ ተርታዬ ፡ አናቶትን፤ እንድም ፡
ቤተ መቅደስን ፡ ኢየሩሳሌምን፡ ነገ
ሥታቱ ፡ መኳንንቱ ፡ ኃጢአት፡ እየሠ
ሩባት፡ጣዖት፡እያመለኩባት፤እንድም፡
አሕዛብ፡ገንዘቧን፡ዘርፈው፡ገፍፈው፡
ምድረ፡በዳ፡በረት፡አደረጓት፤

፲፩፡ ወኮነት ፡ ለሙስና ፡ ወለኀጕል ፡
በላዕሌሃ፡
በሱዋ ፡ ኃጢአት ፡ በሱዋ ፡ ክፋት፤
እንድም፡በላዕሌየ፡በኔ፡ፈቃድ፡በኔ፡
ትእዛዝ፡ለፍጹም፡ጥፋት፡ሆነች፤

ወበእንቲአየ ፡ ኀልቀት ፡ ኵላ ፡ ምድር
ወማሰነት፡
ኃጢአት ፡ በመሥራት ፡ ጣዖት
በማምለክ፡እኔን፡ስለበደለች፡ምድር
ኢየሩሳሌም፡ፈጽማ፡ጠፋች፤

እስመ ፡ አልቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘይሠይም ፡ ጽድቀ
በልቡ፡
ይህ ፡ መከራው ፡ የመጣብኝ
ፈጣሪዬን፡በበደልኩበት፡ነው፡ብሎ
በልቡናው ፡ እውነቱን ፡ ነገር
የሚያስብ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሰው
የለምና፤

፲፪፡ኀበ፡ኵሉ፡ገዳም፡ባኡ፡ወሐሩ፡ገዳመ
ኀሠራን፡
እናንተ ፡ ጐስቋሎች ፡ እስቲ ፡ ይሆን
ላችሁ፡እንደሆነ፡ወደ፡ምድረ፡በዳው
ገብታችሁም፡ በምድረ፡ በዳው ፡
ሽሽታችሁ፡ሂዳችሁ፡አምልጡ፤

እስመ ፡ መጥባሕቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ትበልዕ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡
አጽናፈሃ፡
ባኡ ፡ ወሑሩ ፡ ብሎዋቸው ፡ ነበርና ፡
ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሽሽተን፡ መግባ
ታችን ፡ ስለምንድነው ፡ ትሉኝ ፡
እንደሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅ
ሠፍቱ ፤ እንድም ፡ የናቡከደነ ፆር ፡
ሾተል በተፈጥሮ ፡ ገንዘቡ ፡ ናትና ፡
ጽንፍ፡እስከ፡ጽንፍ፡ሒዳ፡ሰውንም፡
ከብትንም ፡ ታጠፋለችና ፡ ስለዚህ፡
ነው፤

ወአልቦ፡ሰላም፡ለኵሉ፡ዘሥጋ፡
በዚያ ፡ ወራትስ ፡ ለሥጋዊ ፡ ለደማዊ ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡
...ም ፡ አለ ፤ እርስ ፡ በርሱ ፡ አይፋ
...ም፡ሲል፡ነው፤እንድም፡ለሥጋዊ፡
...ማዊ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡
...፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ አይታዘዝ
...ም፤

...፤ትዘርዑ፡ሥርናየ፡ወተዓርሩ፡አሥዋከ፡
...ተስ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ስንዴ
...ታችሁ ፡ እሾህ ፡ ትለቅማላችሁ ፡
...ስንዴ ፡ ዘርታችሁ ፡ እንክርዳድ ፡
...ዳላችሁ፤

...ይበቍዓክሙ፡መክፈልትክሙ፡
...የ ፡ ወራትም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ
...፡ጽዋ፡ተርታችሁ፡ለናንተ፡አይረ
...ችሁም ፡ አይጠቅማችሁም ፤
...ድም፡ወኢይበቍዓክሙ ፡ መክፈ
...ክሙ ፡ ይላል ፤ በርሻችሁ ፡ የተ
...ው፡አዝመራው፡አይረባችሁም፡
...ጠቅማችሁም፤

...ፈርክሙ፡እማዕረርክሙ፡
...ከማችሁበት ፡ መከር ፡ ተለይታ
...፡አፈራችሁ፤እንድም፡ከደከማች
...ት፡መከር፡ጋራ፡አፈራችሁ፡አለ፤
...ከማችህ በትን ፡ መከር ፡ እነሱ ፡
...ደው፡ወቅተው፡ይበሉባችኋል፤
...ንተንም ፡ ማርከው ፡ ይወስዷ
...ል፡ሲል፡ነው፤

...ሥርክሙ፡እመዓተ፡መቅሠፍቱ፡ለእግዚ
...ሔር፤
...ዚአብሔር ፡ ካመጣው ፡ መቅ
...ት ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፤ እንድም ፡
...ዓቱ ፡ ወመቅሠፍቱ፡ ለእግዚአብ
...ር ፡ ይላል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከቍ
...ው፡ከመቅሠፍቱ፡የተነሣ፡ጐሰቈላ
...፤ሐተታ፡መዓት፡የልብ፡የሐልዮ፡
...ቅሠፍት፡የነቢብ፡የገቢር፡ነው፤



፲፬፡እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናግ
ሯልና፤

በእንተ ኵሉ ጎር ፡ እኩይ ፡ እለ ፡ ይገሥሱ፡
ርስትየ ፡ ዘከፈልክዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡
እስራኤል፡
ለወገኖቼ፡ለእስራኤል፡አካፍዬ፡የሰ
ጠኋቸው ፡ ርስቴ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡
ስላጠፉ፡በጎረቤት፡ጠላት፡በሞዓብ፡
በአሞን፡በመዓት፡አለሁባቸው፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እመልሐሙ፡እምነ፡ምድሮሙ፡
የሞዓብ ፡ የአሞንን ፡ ሰዎች ፡ እነሆ፡
ካገራቸው ፡ አስወጥቼ ፡ አስማርካቸ
ዋለሁ፤

ወአወጽአሙ ፡ ለቤተ ፡ ይሁዳ ፡ እምነ ፡
ማዕከሎሙ፡
የይሁዳንም ፡ ወገኖች ፡ ብየ ፡ ከእኩ
ሌቶች ፡ ለይቼ ፡ እኩሌቶችን፡ አስ
ወጥቼ፡እሰዳቸዋለሁ፤
እንድም ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እመልሐሙ፡
እምነ ፡ ምድሮሙ ፤ የሞዓብ ፡ የአሞን
ሰዎች፡ከጠፉ፡በኋላ፡የይሁዳን ሰዎች
ከሞዓብ ፡ ከአሞን፡ አገር ፡ አወጣቸ
ዋለሁ፤ወአወጽአሙ፡ለቤተ፡ይሁዳ፡
እምነ ፡ ማዕከሎሙ ፡ እመልሐሙ፡
ያለውን ፡ አወጽአሙ ፤ እምነ ፡ ምድ
ሮሙ፡ያለውን፡እምነ፡ማዕከሎሙ፡
ብሎ፡ደገመው፤

፲፭፡ወእምድኅረ፡አውፃእክዎሙ፡እትመ
የጠሙ፡ወእሠሃሎሙ፡
ከሞዓብ ፡ ከአሞንም ፡ አገር ፡ ካወጣ
ኋቸው ፡ በኋላ ፡ እመይጠሙ፡ ሲል ፡
ነው፤ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ እመልሳቸ
ዋለሁ ፤ እንድም ፡ እንዳለ፡ ይሆናል ፤
እትመየጠሙ ፡ ከመዓት፡ ወደ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምህረት ፡ እመለስላቸዋለሁ ፤ ይቅር፡ እላቸዋለሁ፤

ወአነብሮሙ፡ለኵሎሙ፡ውስተ፡ርስቶሙ፤
ወዳገራቸውም ፡ ካገባኋቸው ፡ በኋላ፡ በየርስታቸው፡አኖራቸዋለሁ፤

ወለለ፩ዱ፡ውስተ፡ምድሮሙ፤
እያንዳንዱንም ፡ በየምድራቸው ፡ አኖ ራቸዋለሁ ፤ ሐተታ ፡ ርስቶሙ፡ የሚ ለው፡በየነገዱ፡በየነገዱ፡የተካፈሉት፡ ርስታቸው ፡ ነው ፤ ምድሮሙ ፡ የሚ ለው፡ቤት፡ሥርተው፡ጎመን፡ዘርተው፡ አጥር ፡ አጥረው፡ አርሰው ፡ ቆፍረው ፡ አዝርዕት ፡ አትክልት ፡ አብቅለው ፡ የሚኖሩበት፡ነው፤

፲፮፤ ወእምዝ ፡ ለእመ ፡ ተምህሮ ፡ ተምህሩ ፡ ፍኖትየ ፡ ሕዝብየ ፡ ከመ ፡ ይምሀሉ ፡ በስምየ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ መሀርዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ መሀላ ፡ በበዓል ፡ ይትሐነጹ ፡ በማዕከለ፡ሕዝብየ፤
ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ለወገኖቼ ፡ ለእስ ራኤል፡በበዓል፡ቀን፡መሀላን፡እንዳስ ተማሯቸው ፡ ሕያው ፡ በሆነ ፡ በስሜ ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ ይምሉበት ፡ ዘንድ፡ ወገኖቼ ፡ ሕጌን ፡ ቢማሩት ፡ እኩሌቶች ፡ ወገኖቼ ፡ በእኩሌቶች ፡ ወገኖቼ ፡ መካከል ፡ ይታነጻሉ ፤ አንድም ፡ ሕያውን ፡ ጠብቀው ፡ ነቢያት፡ ካህናት ፡ ለወገኖቼ ፡ ለእስ ራኤል፡በበዓል፡ቀን፡መሀላን፡እንዳስ ተማሯቸው ፤ ስሜን ፡ ጠርተው ፡ ሲምሉበት ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ ሕጌን ፡ ቢማሩ ፡ ከመ ፡ ይትሐነፁ ፡ እኩሌቶች ፡ ወገኖቼ ፡ በእኩሌቶች ፡ ወገኖቼ ፡ መካከል ፡ እንዲታነፁ ፡

ሕያው፡ነኝ፡አለ፡እግዚአብሔ

፲፯፤ ወእመሰ ፡ ኢተመይጡ ፡ ዕሥ
ለእሙንቱ፡ሕዝብ፤
ከክፋታቸው ፡ ካልተመለሱ
እኒህን፡ወገኖቼን፡አጠፋቸዋለ

ወዓእትቶሙ ፡ ወአጠፍአሙ ፡ ይቤ ፡
ብሔር፤
ሳጠፋቸውም፡ካገራቸው፡አስ
አርቄ ፡ ወስጄ ፡ በሰው፡ አገር ፡ አ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር።

## ምዕራፍ፡፲፫፤

፩፤ከመዝ፡ይቤለኒ፡እግዚአብሔር፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ እግዚአብ
እንዲህ፡አለኝ፤

ሑር፡ተሣየጥ፡ለከ፡ሞራዐ፡አጌ፤
ሒደህ ፡ የነጭ ፡ ሀር ፡ ዳኮ ፡ ግ
ጉለሻ፡አንቀልባ፡ግዛ፡አለኝ፤ሐ
ለከ፡አለ፤አንተ፡ልትታጠቀው፤

ወዕጥቆ፡ውስተ፡ሐቌከ፤
ገዝተህም ፡ በወገብህ ፡ ታጠቀ
አለኝ፤

ወኢትጥምዮ፡ውስተ፡ማይ፤
ነገር፡ግን፡ከውሀ፡አትንከረው፡አ

፪፤ ወተሣየጥኩ፡ሞራዐ፡በከመ፡ይ
እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔርም ፡ ሑር ፡ ተ
ብሎ፡እንደነገረኝ፡ሒጄ፡ዳኮ፡ጉ
አንቀልባውን፡ገዛሁ፤

ወአጠቁ፡ውስተ፡ሐቌየ፤
ገዝቼም፡በወገቤ፡ታጠቅሁት፤

፫፤ ወነበበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳግ



ይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሑር ፡ ተሣየጥ፡ ላለው ፡ ነበበኒ ፡ እግዚአ ብሔር፡ዳግመ፡አለ፤ዳግመኛም፡እግ ዚአብሔር፡ተናገረኝ፡እንዲህ፡አለኝ፤

፬፤ ንሣእ ፡ ዝኰ ፡ ሞራዐ ፡ ዘተሣየጥከ፡ ለሐቌከ፤
በወገብህ ፡ ልትታጠቀው ፡ የገዛ ኸውን፡ ዳኮ ፤ ጉለሻ ፤ አንቀልባውን ፡ ይዘህ፤

ተንሥእ፡ወሑር፡ኤፍራጥስ፤
ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ሒድ፤

ወኅብዮ፡ህየ፡ውስተ፡አዘቅተ፡ኰኵሕ፤
ሒደህም ፡ በዋሻው ፡ ጥግ ፡ ባለው፡ ጕድጓድ፡ቆፍረህ፡ቅበረው፡አለኝ፤

፭፤ ወሖርኩ ወኀባዕክዎ ፡ ውስተ ፡ ኤፍራጥስ ፡ በከመ ፡ አዘዘኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ፤
ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሑር ፡ ወኅብዮ ፡ ውስተ ፡ አዘቅተ ፡ ኰኵሕ ፡ ብሎ፡እንዳዘዘኝ፡ሒጄ፡በኤፍራጥስ፡ ወንዝ፡ቀበርኩት፤አንድም፡ሖርኩን፡ ታገሥ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኅብዮ፡ ውስተ ፡ አዘቅተ ፡ ኰኵሕ ፡ ብሎ፡እንዳዘዘኝ፡በኤፍራጥስ፡ወንዝ፡ ዋሻ ፡ ቀብሬው ፡ ሖርኩ ፤ ተነሥቼ ፡ ሔድሁ፤

፮፤ ወእምድኅረ ፡ ጕንዱይ ፡ መዋዕል ፡ ይቤለኒ፡እግዚአብሔር፤
ከዚህ፡ቀጥሎ፡ከብዙ፡ቀን፡በኋላ፡እግ ዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤

ተንሥእ፡ወሑር፡ኤፍራጥስ፤
ተነሥተህ ፡ ወደኤፍራጥስ ፡ ወንዝ፡
...እ፡ ትሖር ፡

ኤፍራጥስ ፡ ይላል ፤ ወደ፡ ኤፍራጥስ ፡ ወንዝ፡ልትሔድ፡ተነሥ፤

ወንሣእ፡እምህየ፡ዝኰ፡ሞራዐ፡ዘአዘዝኩከ፡ ትኅባዕ፡ህየ፤
በዚያ ፡ ልትቀብረው ፡ ቅበረው ፡ ብየ ፡ ያዘዝኩህን ፡ ዳኮ ፡ ጉለሻውን ፡ አንቀል ባውን ፡ ሒደህ ፡ ከዚያ ፡ ከቀበርክበት ፡ ከዋሻው፡አውጣው፡አለኝ፤

፯፤ ወሖርኩ፡ኤፍራጥስ፤
ተነሥቼ ፡ ወደኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ሄድሁ፤

ወከረይኩ ፡ ወነሣእኩ ፡ ዝኰ ፡ ሞራዐ ፡ እምኀበ፡ደፈንክዎ፤
ሒጄም ፡ ከቀበርኩበት ፡ ቦታ ፡ ዳኮውን፤ ጉለሻውን ፡ አንቀልባውን ፡ ቆፍሬ፡አወጣሁት፤

ወረከብኩ፡ብጹላቲሃ፤
ቡጭቅጫቂዋን፡ብጥስጣሽዋን፤

ወአጽርቅተ፡ዘለምንትኒ፡ኢይበቍዕ፤
ለምንም ፡ ለምን ፡ የማይረባ ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ፡መሆንዋን፡ቆፍሬ፡ባወጣው፡ ይኸን፡አገኘሁ፤

፰፤ ወኮነ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኀቤየ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ የፈጣሪየ ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፡ ወደኔ ፡ መጣ ፤ ተነገረ ፤ አንድም፡ወደኔ፡መጥቶ፡ተነገረ፤

፱፤ ወይቤለኒ ፡ ከመዝ ፡ አኀሥራ ፡ ለጽዕለተ፡ይሁዳ፤
ያ፡ያማረ፡የተወደደ፡የነጭ፡ሐር፡ዳኮ፡ ጉለሻ ፡ አንቀልባ ፡ እንደጐሰቈለ ፡ እንደሰ ፤ አንድም፡ አሁን ፡ እንደተናገ ርኩት፡በሁለቱ፡ነገድ፡ስድብ፤

ወለጽዕለተ፡ኢየሩሳሌም፡ብዝኀት፡
ኢየሩሳሌምም ፡ አብዝታ ፡ ትሳደብ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በነበረው ፡ መሳደብ ፡ አጐሰቍላ
ታለሁ፤ አንድም ፡ ለፀዓሊት ፡ ይሁዳ ፡
ይላል፤ከፍና፡ዝቅ፡አድርጋ፡ትሳደብ፡
የነበረች፡ይሁዳን፡ወለፀዓሊት፡ኢየሩ
ሳሌም፡ከፍና፡ዝቅ፡አድርጋ፡ትሳደብ፡
የነበረች፡ኢየሩሳሌምንም፤አጐሰቍላ
ታለሁ፤ አንድም ፡ ለፅዕልት ፡ ይሁዳ ፡
ኃጢአት ፡ ሠርታ ፡ ጣዖት፡ አምልካ ፡
ከፈጣሪዋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተ
ጣላች ፡ ይሁዳን ፤ ወለፅዕልት ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ኃጢአት ፡ ሠርታ ፡ ጣዖት፡
አምልካ፡ከፈጣሪዋ፡ከእግዚአብሔር፡
የተጣላች ፤ የተናቀች ፡ ኢየሩሳሌ
ምንም፡ተማርካ፡ስትሄድ፡አጐሰቍላ
ታለሁ፤ አንድም ፡ ለፅዕልተ ፡ ይሁዳ ፡
ወለፅዕልተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ብዝኀት ፡
ይላል፤በኢየሩሳሌምና፡በይሁዳ፡የተነ
ቀፈች፡ቤተ፡እስራኤልን፡አጐሰቍላ
ታለሁ፤

፲፥ ወለዝኒ ፡ ሕዝብ ፡ እኩይ ፡ እለ ፡
ኢይፈቅዱ፡ይሰምዑ፡ቃልየ፡
ወለእሉኒ ፡ ሕዝብ ፡ እኩያን ፡ ሲል፡
ነው፤ ቃሌን፡ ሊሰሙ፡ የማይወዱ፡ እነ
ዚህንም ፡ ክፉዎች፡ ወገኖች ፡ አጎ
ሥሮሙ፡ ያለበት፡ ነው፤ በመከራው፡
አጐሰቍላቸዋለሁ፤
ወየሐውሩ፡በግዕዘ፡ልቦሙ፡እኩይ፤
ኢይፈቅዱ ፡ ይስምዑ ፡ ቃልየ ፡ ብሎ ፡
ነበርና ፡ ቃሌን ፡ ሊሰሙ ፡ አይወዱም ፤
እነሱስ ፡ በክፉ ፡ ልቡናቸው ፡ ሥራ ፤
አንድም ፡ በልቡናቸው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ጸንተው፡ይኖራሉ፤
ወየሐውሩ፡ወይትልዉ፡አማልክተ፡ነኪር፡
ከመ፡ይትቀነዩ፡ሎሙ፡ወያመልክዎሙ፡
ለእነሱ፡ተገዝተው፡ሊያመልኳቸው፡

የከነዓንን ፡ ጣዖት ፡ ተከትለው
ይሔዳሉ ፤ አንድም ፡ ወየሐውሩ
ይትልዉ፡አማልክተ፡ነኪራን፡ይላ
እነሱን፡አምልከው፡እንዲገዙላቸ
ልዩ ልዩ ፡ ጣዖታቱን ፡ ሊከተሉ
ተነሥተው፡ይሄዳሉ፡
ወይከውኑ፡ከመ፡ዝንቱ፡ሞራዕ፡ዘለምንት
ኢይበቍዕ፡
ያ፡የነጭ፡ሐር፡ዳኮ፤ጉለሻ፤አንቀል
ከተቀበረበት፡ወጥቶ፡ለምንም፡ለም
እንዳይረባ፤እንዳይጠቅም፡ቤተ፡እስ
ኤልም፡ተማርከው፡ሒደው፡ባቢሎ
ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥተው
ለምንም፡ ለምን ፡ አይረቡም ፤ አይ
ቅሙም፤

፲፩፥ በከመ ፡ ይጠግዕ ፡ ዝ ፡ ሞራዕ ፡ ውስ
ሐቌ፡ብእሲ፤
ያ፡የነጭ፡ሐር፡ዳኮ፡ጉለሻ፤አንቀል
ወደ ፡ ሰው ፡ ወገብ ፡ እንዲጠጋ ፡ እን
ቀርብ፤
ከማሁ ፡ አቅረብክዎሙ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል
ኀቤየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እኔም፡ዓሥሩን፡ነገድ፡ሁለቱን፡ነገድ
በፍቅር፡ በረድኤት ፡ ወደኔ ፡ አቅር
ያቸው፡ነበር፡አለ፡እግዚአብሔር፤
ወለኵሎሙ ፡ ቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ
ሕዝበ፡ለክብር፡ወለምክህ፡ወለስምዕ፡ወእ
ምዑኒ፤
ብመከራቸው ፡ ባስተምራቸው ፡ አል
ሙኝም ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ስሜ፡ ሊጠ
ባቸው፡ልመካባቸው፤አንድም፡እነሱ
በኔ፡ሊመኩብኝ፤ክብሬ፡ሊገለጥባቸው
አንድም ፡ እኔ ፡ እነሱን ፡ ላከብራቸው



ልቁንም፡ሁለቱን፡ነገድ፡ወደኔ፡አቅ
ቤያቸው ፡ ነበር ፤ ይኸውም ፡ ምሳሌ፡
ው፤ሞራዐ፡አጌ፡የቤተ፡እስራኤል፤
ደህ ፡ የነጭ ፡ ሐር ፡ ዳኮ ፤ ጉለሻ ፤
ንቀልባ፡ግዛ፡አለኝ፡አለ፤ሒደህ፡
ተ፡እስራኤልን፡ምከራቸው፡አስተ
ራቸው ፡ አለኝ ፤ ለከ ፡ ሊረባህ ፡
ጠቅምህ፡አለ፤መምህር፡ከመከረ፡
ስተማረ፡ይረባዋል፡ይጠቅመዋል፡
ጋውን፡አያጣምና፤ወዕጥቆ፡ውስተ፡
ቌከ ፤ እኔ ፡ በልቡናዬ ፡ እንድወ
ቸው፡ አንተም ፡ በልቡናህ ፡ ውደ
ቸው፡አለኝ፤ወኢትጥምዮ፡ውስተ፡
ይ፤ነገር፡ግን፡ውሀ፡አትንከረው፡
ለው፤ረድዔት፡መንሣቱን፡መናገር፡
ው፤ ወተሣየጥኩ ፡ ሞራዐ ፡ በከመ ፡
ቤለኒ፡እግዚአብሔር፤ሒደህ፡ቤተ፡
ስራኤልን ፡ ምከ
ራቸው ፡ አስተምራቸው ፡ እንዳለኝ፡
ሒጄ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ መከር
ኳቸው፤ አስተማርኳቸው ፤ ወአጠቌ ፡
ውስተ ፡ ሐቌየ፡ በልቡናህ ፡ አጽንተህ ፡
ውደዳቸው፡ እንዳለኝ ፡ በልቡናዬ፡
አጽንቼ፡ወደድኳቸው፤
ወነበበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳግመ ፡
ወይቤለኒ፡ንሣእ፡ዝኰ፡ሞራዐ፡ዘተሣ
የጥከ፡ለሐቌከ፤
እኔ ፡ በልቡናዬ ፡ እንደወደድኳቸው ፡
አንተም ፡ በልቡናህ፡ ልትወዳቸው ፡
የመከርካቸው፡ ያስተማርካቸው ፡ እስ
ራኤልን ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡ ኤፍ
ራጥስ ፡ እነሱን ፡ ይዘህ ፡ አብረህ ፡
ተማርከህ፡ወደባቢሎን፡ሒድ፡አለኝ፤
ወኅብኦ ፡ ህየ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፤
...ለ፡ ዋሻ ፡

ቅበረው፡አለኝ፡አለ፤እስራኤልንም፡
ወስደህ ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ ባለበት ፡
በባቢሎን፡እንዲኖሩ፡አድርጋቸው፡
አለኝ፤ወሖርኩ፡ወኅባዕክዎ፡ውስተ፡
ኤፍራጥስ ፡ በከመ ፡ አዘዘኒ ፡ እግዚአ
ብሔር ፤ አምላክ ፡ ፈጣሪዬ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ቅበረው ፡ ብሎ፡ እንዳዘዘኝ ፡
የነጩን ፡ ሐር ፡ ዳኮ ፤ ጉለሻ፤ አንቀል
ባውን ፡ ሒጄ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡
ቀበርኩት ፡ አለ ፤ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እስራኤል፡ይማረካሉ፡ብሎ፡
እንደነገረኝ ፡ እኔም ፡ እስራኤልን፡
ተማርከው፡ሂደው፡በባቢሎን፡ወንዝ፡
ሰባ፡ዘመን፡እንዲኖሩ፡አደረግኋቸው፤
ወእምድኅረ ፡ ጕንዱይ፡ መዋዕል ፡
ከብዙ፡ቀን፡በኋላ፡አለ፡ከሰባ፡ዘመን፡
በኋላ ፡ ይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡
ተንሥእ፡ ወሑር ፡ ኤፍራጥስ ፡
ተነሥተህ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ሂድ ፤
ወንሣእ፡እምህየ፡ዝኰ፡ሞራዐ፡ዘአዘ
ዝኩከ ፡ ትኅባዕ ፡ ህየ ፤ ትቀብረው፡
ዘንድ፡ቅበረው፡ብዬ፡ያዘዝኩህ፡ዳኮ፡
ጉለሻ፡አንቀልባውን፡ከዚያ፡ከቀበር
ክበት ፡ ከዋሻው ፡ አውጣው ፡ አለኝ ፡
አለ፤ ተማርከው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡
በባቢሎን፡ ይኖራሉ፡ ብዬ የነገርኩህ፡
ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡
በኋላ፡ ከባቢሎን፡ አውጣቸው ፡ አለኝ፤
እኩሌቶች ፡ እስራኤልን ፡ ኤርምያስ ፡
ይዟቸው፡ወጥቷልና፤
ወሖርኩ ፡ ኤፌፍራጥስ ፡ ወከረይኩ፡
ወነሣእኩ ፡ ዝኰ ፡ ሞራዐ ፡ እምኅበ ፡
ደፈንክዎ ፡ ወደ፡ ኤፍራጥስ ፡ ሒጄ ፡
ያነን ፡ ዳኮ ፤ ጉለሻ ፤ አንቀልባውን ፡ ከቀ
በርኩበት ፡ ቦታ ፡ ቆፍሬ ፡ አወጣሁት፡

www.ethiopianorthodox.org

እኔ ፡ መክሬአችሁ ፡ አስተምሬያችሁ ፡
እናንተ ፡ ባትሰሙኝ ፡ ግን ፡ መከራው ፡
ሳይመጣባችሁ ፡ ከመምጣቱ ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ልቡናዬ ፤ አንድም ፡ ሰውነቴ ፡
ከቤቷ ፡ ገብታ ፡ ደጇን ፡ ዘግታ ፤ አንድም ፡
በኀቡዕ ፡ በልቡና ፡ ታለቅስላችኋለች ፡
ታዝንላችኋለች ፤

ወአንብዓ ፡ ታነብዕ ፡ ዓይንየ ፡
ዓይኔም ፡ ዕንባዋን ፡ ታፈስላችኋለች ፤

ወይውኅዝ ፡ አንብዕ ፡
ከፊቴም ፡ የእንባ ፡ ጐርፍ ፡ ይፈስሳል ፤

እስመ ፡ ተረሥዓ ፡ መርዔተ ፡ እግዚአብሔር ፡
እስራኤል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡
መሆናቸው ፤ አንድም ፡ መርዔተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ይላል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አን
ድነታቸው ፡ ተዘንግቶባቸዋልና ፡ ይው
ኅዝ ፡ ብለህ ፡ እሥር ፤ አንድም ፡ እስመ ፡
ተረስዓ ፡ መርዔተ ፡ እግዚአብሔር ፤ የእግ
ዚአብሔር ፡ ወገንነታቸው ፤ አንድም ፡
አንድነታቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልቡና ፡
ተዘንግቶባቸዋልና ፤

፲፰፤ በሎሙ ፡ ለነገሥቶሙ ፡ ወለዐበ
ይቶሙ ፡ አትሕቱ ፡ ርእስክሙ ፡ ወንበሩ ፡
ነገሥታቱን ፡ ሹማምቱንም ፤ አንገታ
ችሁን ፡ ደፍታችሁ ፡ ተቀመጡ ፡
በላቸው ፤

እስመ ፡ ይሰልቡክሙ ፡ አክሊለ ፡ ምክህክሙ ፡
እምነ ፡ ርእስክሙ ፡
እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ የምትመኩበት ፡
ዘውዳችሁን ፤ ከራሳችሁ ፡ አውርደው ፡
የሚጥሉት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፤

፲፱፤ ወይትአፀዉ ፡ አህጉር ፡ ዘመንገለ ፡
ናጌብ ፡
ዘመንገለ ፡ ሆለሄ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዐራቱ ፡
ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ አህጉር ፡ ይዘጋሉ ፤

ወአልቦ ፡ ዘየርኅዎን ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚ
ታቸው ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡ የለም ፤

ወይሁዳኒ ፡ ፈለሰ ፡ ፍጹመ ፡ ፍልሰተ ፡
ይሁዳም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ፍጹ
ዜዋዌ ፡ አድርጎ ፡ ተሰደደ ፡ አለ ፤ በሀ
ሰዎቹን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ባታቸው ፡ በይሁዳ ፡ ልጆቹን ፡ ተና
ዋቸዋል ፤

፳፤ አንሥኡ ፡ አዕይንቲክሙ ፡
ይዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይመጽኡ ፡ እምሰሜን ፤
ምን ፡ ያደክማችኋል ፤ እናንተስ ፡ ዓ
ልቡናችሁን ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡
ናችሁን ፡ አቅንታችሁ ፡ ክተ
ሠራዊት ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብለ
ከባቢሎን ፡ የሚመጡ ፡ ጠላቶቻችሁ
እዩ ፤ ተመልከቱ ፤

አይቴኑ ፡ መርዔት ፡ ዘወሀቡ ፡ ለኪ ፡ አባ
ክብርኪ ፡
መርዓትም ፡ ይላል ፡ ቤተ ፡ እስራኤል
እንዲያስከብር ፡ የሚያስከብሩ ፡ በጎች
አንድም ፡ ልትከብሪባቸው ፡ ክብ
ሲሆኑሽ ፡ በጎችን ፡ የሰጡሽ ፡ አለ ፡ ሥ
አንድም ፡ ዘወሀበኪ ፡ ይላል ፤ እግ
ብሔር ፡ በአንድነቱ ፤ አንድም
ዘወሁበኩ ፡ ለኪ ፡ ይላል ፤ እኔ ፡ የሰጠሁ
ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ አይቴ
መርዔተ ፡ አባግዓ ፡ ክብርኪ ፡ ይላ
አብነት ፡ ያ ፡ እንዲያስከብር ፡ የሚያ
ብሩሽ ፡ የበጎዎችሽ ፡ መንጋዎች
ወዴት ፡ አሉ ፡ አልጠፉም ፡ ወይ ፤

፳፩ ፤ ምንተ ፡ ትብሊ ፡ አመ ፡ ይዋህዩኪ ፤
ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ስታደርጊ ፡ ኑረሽ ፡ ሥ
በመዓት ፡ በጐበኙሽ ፡ ጊዜ ፤ አንድ



አሕዛብ ፡ በጦር ፡ በጐበኙሽ ፡ ጊዜ ፤
አንድም ፡ ከሞት ፡ የተረፉ ፡ ከጥላ ፡
ያረፉ ፤ ዘመዶችሽ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጽኑ ፡
መከራ ፡ በምን ፡ አገኘሽ ፡ ብለው
በጐበኙሽ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ትናገሪ ፡ ይሆን ፤

ወአንቲኒ ፡ መሀርኪዮሙ ፡ ትምህርተኪ ፡
ዘቀዲሙ ፡
አንቺ ፡ ግን ፡ የቀደመ ፡ ክፉ ፡ ትምህር
ትሽን ፡ ለልጆችሽ ፡ አስተማርሻቸው ፤

አኮኑ ፡ ማሕምም ፡ አኀዘኪ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡
ትወልድ ፡
ምጥ ፡ እንደያዛት ፡ ሴት ፡ ጭንቅ ፡
መከራ ፡ የያዘሽ ፡ በዚህ ፡ ኃጢአትሽ ፡
አይደለምን ፤ አንድም ፡ አኮኑ ፡ አንቲ ፡
መሀርኪዮሙ ፤ አንቺ ፡ ቀድሞ ፡ ያደረግ
ሽውን ፡ ክፉ ፡ ትምህርትሽን ፡ ለል
ጆችሽ ፡ አስተምረሻቸዋልና ፤ ማሕ
ምም ፡ አኀዘኪ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ትወልድ ፤
ምጥ ፡ የያዛት ፡ ሴት ፡ በመከራው ፡
ተይዛ ፡ እንድትጨነቅ ፡ አንቺንም ፡
የሚያስጨንቅ ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ አገኘሽ ፤

፳፪፤ ወእመ ፡ ትቤሊ ፡ በልብኪ ፡ በእንተ ፡
ምንት ፡ ረከበኒ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡
አንቺም ፡ በልቡናሽ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
መከራ ፡ ስለምን ፡ አገኘኝ ፡ ትይኝ ፡
እንደሆነ ፤

በእንተ ፡ ብዝኃ ፡ ኃጢአትኪ ፡
በኃጢአትሽ ፡ ብዛት ፡ ነው ፤ ተቀ
ፈጽኪ ፡ እምድኅሬኪ ፡ ማንሻ ፤
አንድም ፡ በእንተ ፡ ብዝኃ ፡ ኃጢአትኪ ፡
ተቀፈጽኪ ፡ እምድኅሬኪ ፡
በኃጢአትሽ ፡ ብዛት ፡ ከወደ ፡ ኋላሽ ፡
ተገፈፍሽ ፤

ወተከሥተ ፡ ሰኰናኪ ፡
ግዳጅሽም ፡ ከወደ ፡ ኋላሽ ፡ ተገለጠብሽ ፡
አለ ፤ ሴቶችን ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ ሲገኙ
ዋቸው ፡ ግዳጃቸው ፡ ሲገለጥባቸው ፡
ያፍራሉ ፤ ይደነግጣሉና ፡ በዚያ ፡ ግሥ ፡
ተናገረው ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ መከራሽ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ይገለጥብሻል ፡ ሲል ፡ ነው ፤
አንድም ፡ ድኅሬኪ ፡ ሰኰናኪ ፤ ያለው ፡
አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ መከራሽ ፡ እግር ፡
በእግር ፡ ተከታትሎ ፡ ይመጣብሻል ፡
አለ ፤ ቀጥሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
አንድም ፡ መከራው ፡ እግር ፡ በእግርሽ ፡
ተከታትሎ ፡ ይመጣል ፡ አለ ፤ አንቺን ፡
እየተከተለ ፡ ያጠፋል ፡ ሲል ፡ ነው ፤

፳፫፤ የኀድግኑ ፡ ዘይት ፡ ጽታሞ ፡
ወነምርኒ ፡ ኀበሪሁ ፡ ትክሉኑ ፡ አንትሙ ፡
ገቢረ ፡ ሠናይ ፡
ዘይት ፡ ጥመቱን ፤ ነምርም ፡ ዝንጉርጉ
ርነቱን ፡ ይተዋልን ፤ እናንተስ ፡ በጎ ፡
ሥራ ፡ መሥራት ፡ ይቻላችኋልን ፤
አንድም ፡ እመ ፡ የኀድግ ፤ ዘይት ፡
ጥመቱን ፡ ነምር ፡ ዝንጉርጉርነቱን ፡
ቢተው ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ይቻላ
ችኋልን ፤ እሱም ፡ አይተው ፡ እናንተም ፡
አትመለሱ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ባለው ፡
አብነት ፤ ይክልኑ ፡ ገብር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡
ወልጠ ፡ ኀበሪሁ ፡ ይላል ፤ የኢትዮጵያ ፡
አገልጋይ ፡ መልኩን ፡ መለወጥ ፡ ይቻለ
ዋልን ፤ እናንተስ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡
መሥራት ፡ ይቻላችኋልን ፤ አንድም ፡
እመ ፡ ይዌልጥ ፡ አገልጋይ ፡ መልኩን ፡
ቢለውጥ ፡ በጎ ፡ መሥራት ፡ ይቻላች
ኋልን ፤ እሱም ፡ አይለውጥ ፤ እናንተም ፡
አትሠሩ ፤

እስመ ፡ ተምህርክሙ ፡ እኩየ ፡
ክፋቱን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ተምራችሁ
ታልና ፡ ስለተማራችሁት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ወእዘርዎሙ ፡ ከመ ፡ ሐሠር ፡ ዘይነሥኦ፡ነፋስ፡በውስተ፡ገዳም፡
እዘርዎሙ፡እዝርዎሙ፡ይላል፤እኔም፡ በሠሩት፡ክፋታቸው፡ነፋስ፡ከምድረ፡ በዳ፡ጠራርጎ፡እንደሚጥለው፡አበቅ፡ ገለባ፡እበትናቸዋለሁ፤

፳፭፤ ዝውእቱ፡መክፈልትኪ፡ወርስትኪ፡ እምኀቤየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘከመ ፡ ረሳእክኒ፡ወተወከልኪ፡በሐሰት፡
እኔን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እንደዘነ ጋሽኝ ፡ በሐሰት ፡ በጣዖቱም ፡ እንደታ መንሽበት፡መጠን፡ከኔ፡ዘንድ፡የምታ ገኝው ፡ እድል ፡ ፈንታሽ ፡ ጽዋ ፡ ተርታሽ፡መከራው፡ይህ፡ነው፡አለ፡ እግዚአብሔር፤

፳፮፤ ወአነ ፡ እቀፍጸኪ ፡ እምድኅሬኪ ፡ መንገለ፡ገጽኪ፡
አንቺ ፡ እንዲህ ፡ አድርገሽ ፡ እንደ ፡ በደልሽኝ ፡ መጠን ፡ እኔም ፡ ከወደ ኋላሽ፡ወደፊትሽ፡አስገፍፍሻለሁ፤

ወያስተርኢ፡ኀሣርኪ፤
ግዳጅሽም ፡ ይገለጥብሻል ፡ ተቀ ፈጽኪ፡ያለውን፡እቀፍጸኪ፡ተከሥተ፡ ሰኰናኪ ፡ ያለውን ፡ ያስተርኢ ፡ ኃሣ ርኪ ፡ ብሎ፡ደገመው፡ሐተታ፡እንዳ ለፈው፡ነው፤

፳፯፤ ዝሙት፡ወምርዓት፤
አፍቀርኪ ፡ ያለበት ፡ ነው፤ ዝሙት ፡ በቁሙ ፡ ዝሙቱን ፤ ወምርዓተ ፡ ድርዓትን፡ደረመኝነትንም፡ወደድሽ፤

ዘምዎ፡ዘመውኪ፤
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሰሰንሽ፤ አንድም፡በኃጢአት፡በጣዖት፡ከእግዚ አብሔር፡ተለየሽ፤

ወአፈድፈድኪየ ፡ ለዝሙትኪ ፡ በው[...] አውግር፡ወበውስተሂ፡ገዳም፡
በኮረብታውና ፡ በምድረ ፡ በዳው[...] ዝሙትሽን ፡ ሰሰንሽን ፡ አብዝተ[...] ሠራሽው፤ ርኢኩ ፡ ርኵሰኪ ፡ ማ[...] ነው፤አንድም፡በውስተ፡አውግር፤

ወበውስተ፡ገዳምሂ፡ርኢኩ፡ርኵሰኪ፤
በምድረ ፡ በዳውና ፡ በኮረብታ[...] አብዝተሽ ፡ የሠራሽውን ፡ ርኵሰ[...] ኃጢአትሽን ፡ አንድም ፡ ርኵሰ[...] ይላል ፡ ያቆምሽው ፡ ጣዖትሽ[...] አየሁት፤

አሌ፡ለኪ፡ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌም፡ወዮልሽ፡አለ፤በሀገ[...] ሰዎቹን፡መናገር፡ነው፤

እስመ፡ኢነጻሕኪ፡ድኅሬየ፤
እኔን፡በሕግ፡በአምልኮት፡ተከት[...] ከኃጢአት፡ከጣዖት፡ንጹሕ፡አይ[...] ሽምና፡ወዮልሽ፤

እስከ፡ማእዜኑ፡እንከ፡ትነጽሒ፤
ከኃጢአት ፡ ከጣዖት ፡ ንጹሕ ፡ የ[...] ትሆኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነ[...] ኢትነጽሂ ፡ ይላል ፤ ከኃጢአት[...] ከጣዖት፡ አትነጪም፤ ንጹሕ[...] አትሆኝም፤አንድም፤አሌ፡ለኪ፡ኢ[...] ሳሌም፤ኢየሩሳሌም፡ወዮልሽ፤እስ[...] ኢነጻሕኪ ፡ ድኅሬየ ፤ ኪያየ ፡ ሲ[...] ነው፤እኔን፡በሕግ፡በአምልኮት፡[...] ልከሽኝ ፡ ሳለ፡ ጣዖቱን ፡ አል[...] ሽምና፡ወዮልሽ፤

እስከ፡ማእዜኑ፡እንከ፡ትነጽሒ፤
ጣዖቱን ፡ የምትጥዪው ፡ መቼ ፡ ነ[...] ኢትነጽሒ፡ ነገር፡ግን፡እኔን፡ስታ[...]



## ምዕራፍ፡፲፬፡

### ጉባዔ፡

፩፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዐባረ ፡ ዝናም፡
ድርቁ ፡ በእስራኤል ፡ እንዲታዘዝ ባቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ፡ ወደኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤አንድም፡ ዝናም፡ጠፍቶ፡ድርቅ፡እንዲሆን፡በኤ ርምያስ፡የተነገረ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፡ ወይቤ፡በእንተዝ፡ለሀወት፡ምድር፡ ዘይሁዳ፡
ሀገሪቱ ፡ ይሁዳ ፡ ድርቅ ፡ ሆኖባት ፡ አዘነች፤ አለቀሰች ፡ ብሎ ፡ የዚህን ፡ ነገር፡ተናገረ፤

በሀገሪቱ፡ሰውን፡መናገር፡ነው፤
ወዐርቀ፡አናቅጺሃ፡
አደባባይዋ ፡ ከሰው ፤ አንድም ፡ ሪቅ ፡ ኅተራውም፡ከእህል፡ባዶ፡ሆነ፤

ወጸልመ፡ላዕለ፡ምድር፤
በሀገሩም ፡ ድርቅ ፡ ጸና፤ አንድም ፡ ወይቤ ፡ በእንተዝ ፡ ለሀወት ፡ ይሁዳ ፤ ቤተ፡እስራኤል፡በመጣባት፡መከራ፡ ነገር፡አዘነች፤አለቀሰች፡አለ፤ወዐርቀ፡ አናቅጺሃ፡በቁሙ፡በሮቿ፡ባዶ፡ሆኑ፡ አለ፤ የሚወጣ ፡ የሚገባባት ፡ ሰው ፡ ጠፋ፤ አንድም ፡ ኃያላኖቿ ፡ ጠፉ፤ ወጸልመ ፡ ላዕለ ፡ ምድር፤ በልዑላኑ ፡ በትሑታኑ፡የመጣ፡መከረ.ም፡ጸና፤

ወዐርገ፡አውያቲሃ፡ለኢየሩሳሌም፡
ኢየሩሳሌም ፡ ቤተ ፡ እስራኤልም ፡ በመጣባት ፡ መከራ ፡ የለቀሰችው ፡ [...]ደረሰ፤

፫፡ ወፈነዉ ፡ መኳንንቲሃ ፡ መሐዛ ቲሆሙ፡መንገለ፡ማይ፡
በዚያም፡ወራት፡ሹማምንቲዋ፡ውሀ፡ ቀድታችሁ፡አምጡ፡ብለው፡ደቦሎቻ ቸውን፡ወደውሀው፡ላኳቸው፤

ወሐሩ፡ኀበ፡አዘቅት፡
ተጋፍተው ፡ እንደምንም ፡ ብለው ፡ ውሀውን ፡ ቀድተው ፡ ሊያመጡ ፡ ደቦሎች ፡ ተነሥተው ፡ ወደውሀው ፡ ጉድጓድ፡ሄዱ፤

ወኢረከቡ፡ማየ፡
ውሀውን ፡ አላገኙም፤ ሐተታ፡ ተራ ፡ አጥተው፤ አንድም ፡ ድርቅ ፡ ሆኖ ፡ ውሀው፡ደርቆባቸው፤

ወአሦጡ፡ቀሳውቲሆሙ፡ዕራቆ፡
ያን ፡ ጊዜ የውሀ ፡ መቅጃቸውን ፡ ባዶውን፡መለሱ፤

ኀሠሩ፡ወተሐፍሩ፡
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አፈሩ፤ በመከራው ፡ ጐሰቈሉ፤

፬፡ ወተገልበቡ ፡ ርእሶሙ ፡ በእንተ ፡ ተግባረ፡ምድር፡ዘሐልቀ፡
በርሻቸው፡ስለጠፋባቸው፡አዝመራ፤ አንድም ፡ ዘልሕቀ ፡ አድጎ ፡ ስለጠፋ ባቸው፡አዝመራ፡ራሳቸውን፡ተከና ንበው፡አለቀሱ፤

ወአልቦ፡ዝናም፡ውስተ፡ምድር፡
በዚያ፡ወራት፡በሀገራቸው፡ከሰማይ፡ የሚወርድ፡ዝናም፡አልነበረም፤

ተሐፍሩ፡ሐረስት፡ወገልበቡ፡ርእሶሙ፤
አራሾች፡አፈሩ፤ጐሰቈሉ፡ራሳቸውን፡ ተከናንበው፡አለቀሱ፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ ወኀየላትኒ፡ወለዳ፡በውስተ፡ገዳም፤
ዋሊያዎችም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳሉ፤
አንድም ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም ፡ በምድረ ፡
በዳ፡ያሉ፡ዋሊያዎችም፡ልጅ፡ወለዱ፤
ወኀደጋ፡ዕጐሊሆን፡እስመ፡አልቦ፡ሣዕር፤
በድርቁ፡ምክንያት፡የሚበሉት፡ሣር፡
ስለሌለ፡ልጆቻቸውን፡ጥለው፡ሣር፡
ለቀማ፡ሄዱ፤

፮፤ ሐለስትዮታትኒ ፡ ቆሙ ፡ ውስተ ፡
በድው፡ወአብቀዉ፡ውስተ፡ነፋስ፤
የምድረ፡በዳ፡አሕዮችም፡በምድረ፡
በዳው፡ቁመው፡መዓዛ፡ሣዕር፡መዓዛ፡
ማይ፡አሸተቱ፤
ከመ፡ሰገኖ፤
ወከመ ፡ ሰገኖ፤ ሲል ፡ ነው፤ እንደሰ
ጐንም ፡ ቃላቸውን ፡ አቅጥነው ፡
አለቀሱ፤
ወደከማ፡አዕይንቲሆሙ፡ኃጢአሙ፡ሣዕረ፤
የሚበሉት ፡ ሣር ፡ አጥተው ፡ ሣሩን ፡
በመመልከት፡ዓይኖቻቸው፡ደከሙ፤

፯፤ ኃጢአትነ፡ተቃወመነ፡እግዚኦ፤
አቤቱ፡ይህን፡ሁሉ፡መከራ፡አምጥቶ፡
የተቃወመን ፡ ኃጢአታችን፡ ነው፤
አንድም ፡ አቤቱ ፡ አንተን ፡ የበደል
ንበት ፡ ኃጢአታችን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
መከራ፡አምጥቶ፡ተቃወመን፤ግበር፡
በእንተ፡ስምከ፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡
እግዚኦ ፡ ግበር ፡ በእንተ ፡ ስምከ ፤
አቤቱ፡ ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተ
ሣህል፡ብለህ፡ስላልክ፡የቸርነትህን፡
ሥራ፡ሥራልን፤
እስመ፡በዝኃ፡ኃጢአትነ፡ቅድሜከ፤
አንተን፡የበደልንበት፡ኃጢአታችን፡
በፊትህ፡በዝቶ፡ተሠርቷልና፤
ወለከ፡አበስነ፤
ኪያከ፡ሲል፡ነው፤ኃጢአት፡ሠርተን፡
ጣዖት፡አምልከን፡አንተን፡በደልን፤

፰፤ ወጸንሑ ፡ እስራኤል ፡ መድኃኒተ፡
በዕለተ፡ምንዳቤ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ እስራኤልም ፡
በመከራው ፡ ተይዘው ፡ ሳለ ፡ ፈጣሪ
ያቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርግላ
ቸውን ፡ ድኅነታቸውን ፡ ደጅ ፡ ጠኑ፡
ጠበቁ፤
ለምንት፡ኮንከ፡ከመ፡ፈላሲ፡በዲበ፡ምድር፤
እስራኤል ፡ ከኃጢአት ፡ ከጣዖት ፡
ተመልሰው፡ከክፋታቸው፡ታግሠው፡
ሲለምኑህ ፡ አንተ ፡ ለምን ፡ እንደመ
ጻተኛ፡ሆንክባቸው፤ያ፡ፈጥኖ፡እንዳ
ይራዳ፡ፈጥነህ፡የማትራዳቸው፤
ወከመ፡ነግድ፡ተግህሥከ፡በውስተ፡ማኅደር፤
እንደመሸ፡አዳሪ፡ለምን፡ራቅህ፡አለ፤
ያ ፡ መሸ ፡ አዳሪ ፡ ድንኳኑን ፡ ተክሎ፡
ራቱን፡በልቶ፡አድሮ፡ጧት፡ሲሄድ፡
እንዳይራዳ፡እንደዚያ፡ለምን፡አትራ
ዳቸው፤

፱፤ ለምንት ፡ ትከውን ፡ ከመ ፡ ሰብእ፡
ዘይነውም፤
ይህስ ፡ ባይሆን ፡ ለምን ፡ እንደተኛ፡
ሰው፡ትሆናለህ፡አለ፤ያ፡የተኛ፡ሰው፡
በዓለሙ ፡ የሚደረገውን ፡ እንዳያይ፤
እንዳይሰማ ፡ አንተስ ፡ ወልድየ ፡
ዘበኵርየ ፡ ያልካቸው ፡ እስራኤልን፡
በዓይነ፡ምሕረት፡ለምን፡አትመለከ
ታቸው፤ ሲለምኑህስ ፡ ለምን ፡ አትሰ
ማቸው፤
ወከመ ፡ ዕዳለ ፡ እመሕያው ፡ ዘኢይክል ፡
አድኅኖ፤
ያስ ፡ ባያይ ፡ ባይሰማ ፡ ነው ፡ እያየ ፡
[illegible]



ቻለው ፡ እንደ ፡ ደካማ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡
ትሆንባቸዋለህ፤
ወአንተሰ፡እግዚኦ፡ሀሎከ፡ማዕከሌነ፤
አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ የለህም ፡
እንዳይሉ፤ በመካከላችን ፡ በረድኤት ፡
አድረህብን፡ትኖራለህ፤
ወስምከኒ፡ተሰምየ፡በላዕሌነ፤
ስምህም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተጠርቶ ፡
ይኖራል፡አለ፤ ሕዝበ፡እግዚአብሔር፡
ስንባል፡እንኖራለን፤
ወኢትርሥዓነ፤
አባት ፡ የበኵር ፡ ልጁን ፡ እንዳይዘ
ነጋው፡ አንተም ፡ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡
ያልከን ፡ እኛን ፡ ከመራዳት ፡ አትዘ
ንጋን፤

፲፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ዝ፡ሕዝብ፡አፍቀሩ፡አጽሕሶ፡በዕገሪሆሙ፤
እሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው፤ እሊህ ፡
ወገኖች ፡ ከቤተ ፡ ጣዖቱ፤ ገብተው ፡
ለጣዖቱ ፡ ምስጋና ፡ ሲያቀርቡ ፡ በእግ
ራቸው፡ማሽብሸብ፡ወደዱ፤
ወኢይትሐከዩ፤
ይኸንንም፡ክፉ፡ሥራቸውን፡ከቀን፡
ቀን፡ቸል፡አላሉትም፤
ወእግዚአብሔርኒ፡ኢይፈቅዶሙ፤
እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡
ሥራቸውን፡አልወደደላቸውም፤
ወይእዜኒ፡ይዜክር፡ኀጢአቶሙ፤
አሁንም ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ያስብባ
ቸዋል፤
ወይሔውጽ፡ጌጋዮሙ፤
በደላቸውንም ፡ ይጐበኛባቸዋል፤
ሐተታ ፡ ኃጢአት ፡ የጊዜው ፡ ጌጋይ ፡
[illegible] ኃጢአት ፡
በጥቂቱ ፤ ጌጋይ ፡ በእጅጉ ፡ ነው ፤
አንድም፡ኃጢአት፡የስህተት፤ጌጋይ፡
የድፍረት፡ነው፤ አንድም፡ኃጢአት፡
በቁሙ፡ኃጢአት፤ጌጋይ፡ክህደት፡
ነው፤

፲፩፤ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኢትጸሊ ፡ ሎሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ በእንተ ፡
ሠናይ፤
ለእሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው፤ አንተ ፡
እኔን፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አድርግላቸው ፡
ብለህ፤አንድም፡እኔ፡ለነሱ፡በጎ፡ነገር፡
ላደርግላቸው ፡ ለኒህ ፡ ወገኖች ፡ በጎ ፡
ነገር፡አድርግላቸው፡ብለህ፡አትለምን
ላቸው ፡ አትለምነኝ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤በተጣላበት፡ወራት፡አማላጅ፡
ይነሣልና፤

፲፪፤ እስመ ፡ እመሂ ፡ ጾሙ ፡ ኢይሰ
ምዖሙ፡ምህላሆሙ፤
ከኃጢአት፡ከጣዖት፡ሳይመለሱ፤ከክ
ፋታቸው፡ሳይታገሡ፡እየጾሙ፡ቢለ
ምኑኝም ፡ ልመናቸውን ፡ አልሰማ
ቸውም፤ ሐተታ ፡ ምህለላ ፡ ብቻ ፡
ለብቻ፡ ሆኖ ፡ የሚለምኑት ፤ ምህላ ፡
ብዙ፡ሆኖ፡የሚለምኑት፡ነው፤
ወእመሂ ፡ አብኡ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡
ኢይሠሥሎሙ፤
በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ሁነው ፡ ቍር
ባኑን ፡ መስዋዕቱን ፡ ቢያቀርቡልኝ ፡
ይቅር፡አልላቸውም፤
እስመ ፡ በኵናት ፡ ወበረኀብ ፡ ወበብድብድ ፡
አጠፍዖሙ፡አነ፤
እኔ፡በጦር፤በቀጠና፤በቸነፈር፡በኒህ፡
በሦስቱ ፡ ክፉ ፡ ሥራዎች ፡ አጠፋቸዋ
ለሁና፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወእቤ ፡ አነ ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡
እግዚኦ፡
እኔም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡
ወዮልኝ፡አልሁ፡

ወናሁ፡ነቢያት፡ዓላውያን፡ይቤልዎሙ፡ኢይ
ረክበክሙ ፡ ኲናት ፡ ወረኀብ ፡ ውብድብድ ፡
ኢይመጽአክሙ ፡ ዳዕሙ ፡ ሰላመ ፡ ወጽድቀ ፡
እሁብ፡ለዝ፡ሕዝብ፡

እስራኤልን ፡ የሚወነጅሉ ፡ አንድም ፡
ፈጣሪያቸው፡እግዚአብሔርን፡የሚወ
ነጅሉ፡ነቢያተ፡ሐሰት፡ጦር፡ቀጠና፡
ቸነፈር፡እኒህ፡ሦስቱ፡ክፉ፡ሥራዎች፡
አያገኟችሁም፤ ወኢይመጽአክሙ ፡
ሲል፡ነው፤ለዚህ፡ወገን፡ፍቅር፡አንድ
ነትን፡ቸርነትን፡እሰጠዋለሁ፡ብሏል፡
እንጂ፤ ይህ ፡ መከራው፡ አይመጣባ
ችሁም ፡ ብሏል ፡ እግዚአብሔር ፡
አሉዋቸው፤

፲፬፡ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፡

ሐሰዉ ፡ ነቢያት ፡ ዘተነበዩ ፡ በስምየ ፡ ዘኢፈነ
ውክዎሙ ፡ ወኢአዘዝክዎሙ ፡ ወኢተናገር
ክዎሙ፤

በስሜ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘኰሎ ፡ ይመልክ ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡
የተናገሩ፡ነቢያተ፡ሐሰት፡አበሉ፡ወዘ
ኢፈነውክዎሙ፡ያላክኋቸው፡ያላዘዝ
ኋቸው ፡ ያልተናገርኳቸው ፡ ነቢያተ ፡
ሐሰት ፡ ተናገሩ፤ዘተነበዩ ፡ ያለውንና ፡
ዘኢፈነውክዎሙ ፡ ያለውን ፡ ሁለ
ቱንም ፡ ቅጽል ፡ ለነቢያት ፡ ቀጸለ ፤
አንድም ፡ ዘተነበዩ ፡ በስምየ ፡ ዘኢፈነ
ውክዎሙ፡ይላል፤እኔ፡ያላክኋቸውን፡
ያላዘዝኋቸውን ፡ ያልተናገርኳቸውን ፡
ቃል ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ብለው ፡ በስሜ ፡ የተናገሩ ፡ ነቢያተ ፡
ሐሰት፡ሐሰት፡ተናገሩ፡አለኝ፤

እስመ፡ሐሰወ፡ሰገሎሙ፡
ጥንቆላቸው፡ሐሰት፡ነውና፤አንድም፡
እስመ ፡ ሐሰዉ ፡ ሰገሎሙ፤ በጥንቆ
ላቸው፡ሐሰት፡ተናግረዋልና፤

ወተዋርዶቶሙ፡በከ፡እምልቦሙ፡ዘፈጠሩ፡
ከልቡናቸውም፡የልብ፡ወለድ፡ነገር፡
አንቅተው ፡ በከንቱ ፡ ይቀባጥራሉና፡
ይትኔበዩ፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡ወተ
ዋርዶቶሙ፡በከ፡መቀባጠራቸውም፡
ከንቱ፡ነውና፤አንድም፡በከንቱ፡ይቀባ
ጥራሉና፤

ወእምልቦሙ፡ዘፈጠሩ፡ይትኔበዩ፤
ከልቡናቸውም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር፡
አንቅተው ፡ ሐሰት ፡ ትንቢት ፡ ይናገ
ራሉና፤

፲፭፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግ
ዚአብሔር፡
የዚህንስ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ፤

በእንተ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተነበዩ ፡ በስምየ፡
ሐሰተ፡ዘኢፈነውክዎሙ፡አነ፡
እለ ፡ ተነበዩና ፡ ዘኢፈነውክዎሙ ፡
አንድ ፡ ወገን፤ እኔ ፡ ያላክኋቸው ፡
ከመዝ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው፡
በሐሰት ፡ ትንቢት ፡ በተናገሩ ፡
በነቢያተ፡ሐሰት፤አንድም፡እኔ፡ያላክ
ኋቸውን፡ቃል፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር ብለው ፡ በሐሰት ፡ ትንቢት ፡
በተናገሩ፡በነቢያተ፡ሐሰት፡በመዓት፡
አለሁባቸው፡አለ፤

ወይቤሉ፡ኢይመጽአ፡ለዝ፡ሕዝብ፡ኵናት፡



ሐሰት ፡ ትንቢታቸው ፡ እንደምነዋ ፡
ትለኝ፡እንደሆነ፡በዚህ፡ወገን፡ጦር፡
ቀጠና፡ክፉ፡ሞት፡አይመጣበትም፡
አሉ፤ ሐተታ ፡ ብድብድ ፡ ያለውን ፡
ሞት፡እኩይ፡ብሎ፡ገለጸው፡የኃልቁ፡
ማንሻ፡ነው፤

፲፮፡ በመጥባሕት፡ወበረኀብ፡የሐልቁ፡
እሙንቱ፡ነቢያት፡ወሕዝብኒ፡እለ፡ሎሙ፡
ትትነበዩ፤
እነሱ፡መከራው፡አይመጣባችሁም፡
አሉ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ሐሰት ፡ የተናገሩ ፡
ነቢያተ፡ሐሰት፤ሐሰት፡ትንቢት፡የተ
ናገሩላቸው፡ሕዝቡም፡አንድ፡ሁነው፡
በጦር፡በቀጠና፡ያልቃሉ፤

ወእዘሩ፡አብድንቲሆሙ፡ውስተ፡ፍናዊሃ፡
ለኢየሩሳሌም፡እምገጸ፡ኲናት፡ወረኀብ፡
እም፡ያለው፡በ፡ነው፤እስመ፡እም፡
ይተረጐም ፡ ለኀበ ፡ ብዙኅ ፡ ያታ ፡
እንዲል፡በጦር፡በቀጠና፡አልቀው፤
አንድም፡ከጦሩ፡ከቀጠናው፡የተነሣ፡
አልቀው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በጎዳናዋ፤
አንድም፡በመንደሩዋ፡ሬሳቸውን፡እበ
ትናለሁ፤ ፍናው ፡ ያለው ፡ መንደር ፡
ነው፤ ፍናዊሃ ፡ ለጽዮን ፡ ይላህዋ ፡
እንዲል፤

ወአልቦ፡ዘይቀብሮሙ፡እሙንቱኒ፡ወአንስ
ቶሙኒ፡ወደቂቆሙኒ፡ወአዋልዲሆሙኒ፡
እነሱም፡ሚስቶቻቸውም፡ወንዶች፡
ልጆቻቸውና፡ሴቶች፡ልጆቻቸውም፡
አልቀው ፡ የሚቀብራቸው ፡ ወዳጅ ፡
ዘመድ ፡ የላቸውም፤ ሐተታ፡ አንዱ ፡
ቢቆም ፡ አንዱ ፡ ቢታመም ፡ አንዱ ፡
ቢሞት ፡ አንዱን ፡ አንዱ ፡ ያስታ
ምመው፡ይቀብረው፡ነበረና፡ጠዋሪ፡
ቀባሪ፡አታሳጣኝ፡እንዲሉ፤

ወእከዑ፡ላዕሌሆሙ፡እከዮሙ፡
መቅሥፍቱን፡በእነሱ፡አብዝቼ፡አመ
ጣባቸዋለሁ፤ እከይ ፡ አለው ፡ መቅሠ
ፍቱን፡በግብሩ፤አንድም፡ክፉ፡ሥራ፡
ሠርተው ፡ በክፋታቸው ፡ ስለመጣ
ባቸው፡እከይ፡አለው፤

፲፯፡ ወበሎሙ፡ዘ፡ነገረ፡
ሲናገረው ፡ የመጣውን ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡
አለው፤
አንድም፡ወደፊት፡የሚያመጣውን፡
ዘነገረ ፡ ለማነቃቃት ፡ ለማተጋጋት ፡
ይህንን ፡ ነገር ፡ ለእስራኤል ፡
ንገራቸው፤

አንብዕ ፡ ይውኅዝ ፡ እምአዕይንቲክሙ ፡
መዓልተ፡ወሌሊተ፡ዘኢይነጽፍ፡
አንብዕ፡ዘኢይነጽፍ፡ብለህ፡ግጠም፤
የማይገታ ፡ እንባ ፡ በመዓልትም ፡
በሌሊትም ፡ ካይናችሁ ፡ ይፈስሳል፤
አንድም ፡ ይውኅዝ ፡ መዓልተ ፡
ወሌሊተ ፡ የማይገታ ፡ ዕንባ ፡
ካይናችሁ፡ጢት፡ማታ፡እንደጐርፍ፡
ይፈስሳል፡በላቸው፤

እስመ፡ቅጥቃጤ፡ትትቀጠቀጥ፡ድንግል፡
ወለተ፡ሕዝብየ፡በዐቢይ፡ቀትል፡ጥቀ፡
የወገኔ፡ልጅ፡ቆንጆ፡ቤተ፡እስራኤል፡
በጽኑ፡ሰልፍ፡ተከባ፡ጽኑ፡መከራ፡
ትቀበላለችና ፤ ሐተታ ፡ ድንግል ፡
አላት፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ ያች ፡
ድንግል ፡ ልጅ ፡ ከመዳርዋ ፡ አስቀ
ድሞ፡ እንዳትተላለፍ ፡ ቤተ ፡ እስራ
ኤልም ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ከአም
ልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምል
ኮተ ፡ ጣዖት ፡ ከገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደ
ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ አልተላለፈችም፡
ነበረና፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፡ እመሂ ፡ ወጻእኩ ፡ ገዳመ ፡ እረክብ ፡
አብድንተ፡በኲናት፡
ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ያለበት፡ ነው፤ በዚያ ፡
ወራት፡ወደምድረ፡በዳውም፡ብወጣ፡
በጦር ፡ አልቀው ፡ ሙተው ፡ የሚቀብ
ራቸው ፡ አጥተው ፡ ሬሳቸውን ፡
ወድቀው፡ወድቀው፡አገኛለሁ፤

ወእመሂ፡ቦዕኩ፡ሀገረ፡
ወደ፡ከተማውም፡ብገባ፡
ወናሁ፡ምውታን፡በረኀብ፤
በቀጠና ፡ አልቀው ፡ በዝተው ፡
ወድቀው፡አገኟቸው፤
እስመ፡ነቢያትኒ፡ወካህናትኒ፡ሖሩ፡በፍኖት፡
ዘኢየአምሩ፤
ነቢያተ ፡ ሐሰትና ፡ ካህናተ ፡ ጣዖት ፡
ቀድሞ፡በማይወዱት፡ሥራ፡ጸንተው፡
ኑረዋልና ፡ አለ፤ መውደድስ ፡ ወደው ፡
ሠርተውታልና ፡ ብሎ ፡ ቀድሞ ፡
ሠርተውት፡በማያውቁት፡ክፉ፡ሥራ፡
ጸንተው፡ኑረዋልና፤

፲፱፡ለእመ፡መንኖ፡መነንኮ፡ለይሁዳ፡
ቤተ ፡ እስራኤል ፡ እንዲህ ፡ አድርጋ ፡
ብትበድልህ፡ይሁዳን፡ናቅኸው፡አቃ
ለልኸው፤
ወለእመ፡ጸልአታ፡ነፍስከ፡ለጽዮን፤
ልቡናህም፡ጽዮንን፡ፈጽማ፡ጠላቻት፤
ለምንት ፡ አውደቀነ ፡ ማንሻ ፡ ነው፤
አንድም ፡ ለእመ ፡ መንኖ ፡ መነንኮ ፡
ለይሁዳ፤ በአባታቸው ፡ በይሁዳ፡
ተገብተው ፡ ይናገራሉ፤ አባታችን ፡
ይሁዳን ፡ ብትንቀው ፡ ብታቃልለው፤
አንድም ፡ ሀገራቸው ፡ ነው፤ ይሁዳን ፡
ብትንቀው፡ብታቃልለው፡መላውን፡
ወእመ፡ጸልዐታ፡ነፍስከ፡ለጽዮን፡
ጽዮንንም ፡ ልቡናህ ፡ አባቶቻችን ፡

በበደሉህ፡በደል፡ብትጣላት፤
ለምንት፡አውደቀነ፡
አባቶቻችንስ፡ቢበድሉህ፡እኛን፡ል
ቻቸውን ፡ በመከራው ፡ ስለምን
ጣልኸን፤
ወኃጣእነ፡ፈውሰ፡
ካመጣህብንም ፡ መከራ ፡ የምን
ንበት፡አጣን፤
ተሰፈውነ፡ሰላመ፡
ተድላ፡ደስታውን፡ተስፋ፡አደረግን
ወኃጣእነ ፡ ሠናይተ ፡ ወሣህለ ፡ በመዋዕለ
ዘእንበለ፡ሐከክ፡
ከጸብ፡ከክርክር፡ባለ፡ዘመናችን፡ደ
ርታውን፡በጎውን፡ነገር፡ሁሉ፡አጣ

፳፡ አእመርነ ፡ እግዚኦ ፡ ኃጢአተነ
ወጌጋየ፡አበዊነ፡
ይህን፡ሁሉ፡መከራ፡ያመጣብን፡ዛሬ
የኛ ፡ ኃጢአት ፤ ቀድሞም ፡ የአ
ቶቻችን ፡ ኃጢአት ፡ እንደሆነ ፡ አቤ
አወቅን፤
እስመ፡አበስነ፡በቅድሜከ፡
አንተ፡ባወቅኸው፡ዛሬ፡እኛ፡ቀድሞ
አባቶቻችን ፡ በድለንሃልና ፡ ተመ
ጠነ፡ ማንሻ፤ አንድም ፡ አንተ
ባወቅኸው፡ዛሬ፡እኛ፡ቀድሞ፡አባ
ቶችን፡በድለንሃልና፤

፳፩፡ተመየጠነ፡በእንተ፡ስምከ፡
ስምየኒ፡መሐሪ፡ወመሥተሣህል፡
ስላልከው ፡ ከመዓት ፡ ወደምሕረት
ተመለስልን፤
ወኢትግድፍ፡መንበረ፡ስብሐቲከ፡
የጌትነህን ፡ ሥራ ፡ አትተው ፡ አ
ዝናም፡ለዘር፡ጠል፡ለመከር፡ማው
ድህን፡አትተው፤



ተዘከር፡
ዝናም፡ለዘር፡ጠል፡ለመከር፡ከማው
ረድስ ፡ የሚበልጥ ፡ ቀድሞ ፡ ለአባቶ
ቻችን፡በምድረ፡በዳው፡ማለ፡መና፡
ከደመና፡አውርደህ፡ውሀ፡ከደንጊያ፡
አፍልቀህ ፡ የመገብህበትን ፡ የቸርነ
ትህን፡ሥራ፡አስብ፤
ወኢትንሥት፡ሥርዓተከ፡ዘኀቤነ፡
ዛሬም፡በኛ፡ዘንድ፡የምታደርገው፡የጌ
ትነትህን ፡ ሥርዓት ፡ አታፍርሰው ፡
አለ፤ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡
ስጠን፤

፳፪፡ቦኑ፡ጣዖተ፡አሕዛብ፡ዘያዘንም፤
አያዘንምም ፡ እንጂ ፡ ቢያዘንምስ ፡
የአሕዛብ ፡ አምላክ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፤
ጠል፡ለመከር፡ይሰጣልን፤
ወእመሂ፡ወሀበ፡ሰማይ፡ጠለ፡
ሰማይ፡ዝናብ፡ለዘር፡ጠል፡ለመከር፡
ቢሰጥ፤
ወአጽገበ፡
ምድርንም፡ቢያጠግባት፤
አኮኑ፡አንተ፡ውእቱ፡አምላክነ፡
ብታዘንምልንስ፡ፈጣሪያችን፡አንተ፡
አይደለህምን፤
ወተሰፈውናከ፡
ዛሬም፡ዝናም፡ለዘር፡ጠል፡ለመከር፡
ይሰጠናል ፡ ብለን ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡
አደረግን፤
እስመ፡አንተ፡ገበርከ፡ዘንተ፡ኵሎ፤
በድርቁ ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
መከራ ፡ ያደረስክብን ፡ አንተ ፡
ስለሆንክ፡አለ፤ ከላይ፡በእንተ፡ዐባር፡
ብሎ፡የተናገረው፡አንቀጹ፡የድርቅ፡

ነውና ፡ እያለፈ ፡ እያለፈ ፡ የድርቁን ፡
ነገር፡ያዘክራል።

## ምዕራፍ፡፲፭፡

፩፡ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤
እመ ፡ ቆሙ ፡ ሙሴ ፡ ወሳሙኤል ፡ ቅድመ ፡
ገጽየ፡ኢ.ሀለወት፡ነፍስየ፡ኀቤሆሙ፡
ስንኳንስ፡አንተ ፡ ሙሴና ፡ ሳሙኤል ፡
ለማማለድ፡በፊቴ፡ቢቆሙ፡ልቡናዬ፡
ከነሱ፡ጋራ፡የለችም፤ ሐተታ፤ ምነው፡
ስንኳን፡አለ፡ቢሉ፡ካንድ፡አማላጅ፡
ሁለት ፡ አማላጅ ፡ ያስፈራል፤ ይከበ
ራልና፤ አንድም ፡ ስንኳንስ ፡ አንተ ፡
አፋሩ ፡ መምህር ፤ የማያፍሩ ፡ የማ
ይፈሩ፡መምህራን፡ሙሴና፡ሳሙኤል፡
በፊቴ፡ቢቆሙ፡ልቡናዬ፡ከነሱ፡ጋራ፡
የለችም፤ ሐተታ፡ኤርምያስን፡አፋር፡
መምህር፡አለው፤ አሴ፡ሊተ፡እግዚኦ፡
ናሁኬ ፡ ኢይክል ፡ ተናግሮ ፡ እስመ ፡
ንዑስ፡አነ፡ብሎ፡ሂደህ፡አስተምር፡
ባለው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ተናግሯልና፤
ሙሴና ፡ ሳሙኤልን ፡ አያፍሩም ፡
አላቸው፤ ሙሴ ፡ በፈርዖን ፡ ንጉሥ ፡
ግብፅ ፡ ፊት ፡ እየጸለየ ፡ ዐሥር ፡
መቅሠፍት ፡ አውርዷልና ፡ ኋላም ፡
ባሕር፡ከፍሏል፤ ጠላት፡ አጥፍቷልና፤
ሳሙኤልም፡ቀድሞ፡በሳዖል፡ኋላም፡
በዳዊት፡ፊት፡ተአምራት፡ሲያደርግ፡
አላፈረምና፤
ፈንዎሙ፡ዳዕሙ፡ለዝ፡ሕዝብ፡ይሑሩ፡
ለእሉ፡ሕዝብ፡ሲል፡ነው፤ ነገር፡ግን፡
እነዚህን፡ወገኖች፡ይሔዱ፡ዘንድ፡
ሒዱ፡ብለህ፡ስደዳቸው።

፪፡ ወለእመ፡ይቤሉከ፡አይቴኑ፡ነሐውር፡
እነሱ ፡ ግን ፡ የምንሄደው ፡ የትነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ብለው፡ቢጠይቁህ፤አንድም፡የት፡እን
ሄዳለን፡ቢሉህ፤

በሎሙ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤

ዘሂ፡ውስተ፡ሞት፡ለሞት፤
ወደሞት ፡ የሚሄደው ፡ ወደሞት ፡
ይሂድ፤

ወዘሂ፡ውስተ፡ኲናት፡ለኲናት፤
ወደጦርም ፡ የሚሄደው ፡ ወደጦር ፡
ይሂድ፤

ወዘሂ፡ውስተ፡ረኀብ፡ለረኀብ፤
ወደቀጠና ፡ የሚሄደው ፡ ወደቀጠና ፡
ይሂድ፤

ወዘሂ፡ውስተ፡ተፄውዎ፡ለተፄውዎ፤
ወደምርኮም፡የሚሄደው፡ወደምርኮ፡
ይሂድ፡በላቸው፤

፫፡ ወእትቤቀሎሙ ፡ ፬ተ ፡ በቀለ ፡ ይቤ ፡
እግዚአ፡ብሔር፡
አራት ፡ በቀል ፡ እበቀላቸዋለሁ ፡ አለ፡
እግዚአብሔር ፡ ዘሂ ፡ ውስተ ፡ ሞት ፡
ለሞት ፤ ወዘሂ ፡ ውስተ ፡ ኲናት ፡
ለኲናት ፤ ወዘሂ ፡ ውስተ ፡ ረኀብ ፡
ለረኀብ ፤ ወዘሂ ፡ ውስተ ፡ ተፄውዎ ፡
ለተፄውዎ ፤ እያለ፡ ሲናገራቸው ፡
የመጣውን ፡ አርባዕተ ፡ በቀለ ፡ አለ ፤
አንድም፡እንግዲህ፡ወዲያ፡ወደፊት፡
የሚያመጣባቸውን፡አርባዕተ፡በቀለ፡
አለ፤

እለሂ፡በኲናት፡ረገዝዎሙ፡ከለባት፡ይቤጽ
ልዎሙ፤
ለየቀረው ፡ ነው ፡ አሕዛብ ፡ በጦር ፡
ወግተው፡የጣሉዋቸውንም፡ሰዎች፡
ባደባባይ፡ወድቀው፡ውሾች፡ይቦጫ
ጭቋቸዋል፤

ወአዕዋፈ፡ሰማይ፡ወአራዊተ፡ገዳም፡ይበል
ዕዎሙ፤
ይህም ፡ ባይሆን ፡ሙተው ፡ የሚቀብ
ራቸው ፡ አጥተው ፡ ባደባባይ ፡
ወድቀው ፡ ቀን ፡ አዕዋፍ ፤ ሌሊት ፡
አራዊት፡ይበሏቸዋል፤

ወያማስንዎሙ፤
ከለባት፡አዕዋፍ፡አራዊት፡ያላቸውን፡
ነው፤ እነዚህን ፡ እንዲህ ፡ አድርገው፡
ያጠፏቸዋል፤

ወይዐይዑ፡ወየዐጽዩ፡
ከውሾች ፡ ከአዕዋፍ ፡ ከአራዊት ፡
የተረፉ ፡ ሬሶቻቸውም ፡ ይሸታሉ ፤
ይተላሉ፤

፬፤ ወእሁቦሙ ፡ ለምሳሌ ፡ ለኵሎሙ ፡
ነገሥተ፡ ምድር ፡ በእንተ ፡ ምናሴ ፡ ወልደ ፡
ሕዝቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡
ዘገብረ፡በኢየሩሳሌም፤
የይሁዳው፡ንጉሥ፡የሕዝቅያስ፡ልጅ፡
ምናሴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሠራውን ፡
ኃጢአት፡ሁሉ፡ስለሠሩ፤ከሱ፡በኋላ፡
የተነሡ፡ነገሥታቱን፡ሁሉ፡ለተረት፡
አደርጋቸዋለሁ፤አንድም፡በእንተንና
በእንተን ፡ እየራሱ ፡ ለማውጣት ፡
የይሁዳው፡ንጉሥ፡የሕዝቅያስ፡ልጅ፡
ምናሴ ፡ አስቀድሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ኃጢአት፡ስለሠራ፡አለ፤ኢሳይያስን፡
ስለአስገደለ፡ከሱም፡በኋላ፡የነገሡ፡
ነገሥታት ፡ እሱ ፡ የሠራውን ፡ ኃጢ
አት ፡ ስለሠሩ ፡ ተማርከው ፡ ሂደው፡
ለተረት፡አደርጋቸዋለሁ፤

፭፤ አልቦ፡ዘይምህከኪ፡ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌም ፡ ላንቺ ፡ የሚያዝንልሽ ፡
የሚራራልሽ ፡ የለም ፡ አለ፡ በቁሙ፤
አንድም፡ሰዎቹን፡ነው፤ኢየሩሳሌም፡



ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ላንቺ ፡ የሚያዝ
ንልሽ፡የሚራራልሽ፡የለም፤

ወአልቦ፡ዘይቴክዝ፡በእንቲአኪ፤
ባንቺም ፡ ጥፋት ፡ የሚያዝን ፡ የሚቆ
ረቆር፡የለም፤

ወአልቦ፡ዘይስእል፡ዳህናኪ፤
ላንቺም፡ድኅነትሽን፡የሚለምንልሽ፡
የለም።

፮፤እስመ፡ዐለውክኒ፤
ምነዋ ፡ ትይኝ ፡ እንደሆነ ፡ አንቺ ፡
በኃጢአት፡በጣዖት፡ወንጅለሽኛልና፤

ወኀደጊ፡ተሊዎትየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እኔን፡በሕግ፡በአምልኮት፡መከተል፡
ትተሽኛል፡ብሏልና፡እግዚአብሔር፤
ድኅሪተ ፡ ተሐውሪ ፡ ማንሻ ፡ ነው፤
አንድም፡እስመ፡ዐለውክኒ፡በገቢረ፡
ኃጢአት፡በአምልኮ፡ጣዖት፡እኔን፡
ወንጅለሽኛልና፡ወኀደጊ፡ተሊዎትየ፡
ይቤ ፡እግዚአብሔር፤ በሕግ፡ በአምል
ኮትም፡ እኔን ፡ መከተል ፡ ትተሻልና ፤

ድኅሪተ፡ተሐውሪ፤
በሞት ፡ አድሮ ፡ አነስ፤ አድኅ ፡ አነስ ፡
ትሆኛለሽ፤ አንድም ፡ የግርንግሪት ፡
ታሥረሽ፡ተማርከሽ፡ትሄጃለሽ፡አለ፡
እግዚአብሔር፤

ወአነሥእ፡እዴየ፡ላዕሌኪ፡ወአጠፍአኪ፤
እደ፡መዓቴን፤አንድም፡እደ፡ቃሌን፡
አንሥቼ፡አጠፋሻለሁ፤

ወኢይሴሕቶሙ፡እንከ፡ሞተ፤
የተወረወረ ፡ ጦር ፡ አይስታቸውም ፤
አንድም ፡ ወኢይሴሕቶሙ ፡ እንከ ፡
ሞት፤ እንግዲህ ፡ ሞት ፡ አያሳርፋ
ቸውም ፡ አለ፤ ጧት ፡ ማታ ፡ ይገድላ
ቸዋል፡ሲል፡ነው፤

፯፡ ወእዘርዎሙ ፡ ውስተ ፡ አጽናፍ ፡ ለሕዝ
ብየ፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ተማርከው ፡
ጽንፍ፡እስከ፡ጽንፍ፡እንዲሄዱ፡አደር
ጋቸዋለሁ ፤ አንድም ፡ ተማር
ከው፡ ሄደው ፡ በዳርቻ ፡ አገር ፡
እንዲኖሩ፡አደርጋቸዋለሁ፤

ወኮንኩ፡መካነ፤
የወላድ፡መካን፡ሆንሁ፤

ወኀጐልኩ፡ሕዝብየ፡እምፍኖቶሙ፤
ፈጣሪያቸው፡ከሥራላቸው፤አንድም፡
እኔ፡ካስተማርኳቸው፡ሕግ፡ወጥተው፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ተማርከው ፡
ሄደው ፡ አጣኋቸው፤ አንድም ፡ በኃጢ
አቶሙ ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአታቸው ፡
ተማርከው፡ሂደው፡አጣኋቸው፤

፰፤ በዝኃ ፡ እምኆፃ ፡ ባሕር ፡ መበለታ
ቲሆሙ፤
ረኀብ ፡ ብድብድ ፡ ባለው ፡ ነው፤
በቀጠና ፡ በቸነፈሩ ፡ ወንዶች ፡
ወንዶቹ፡ አልቀው ፡ ሴቶች ፡ ሴቶቹ ፡
ቀርተው፡ሴቶቻቸው፡ከባሕር፡አሸዋ፡
ይልቅ፡በዙ፡ይህስ፡ረኀብ፡ብድብድ፡
ያለው ፡ ለሁሉም ፡ ለሴቱም ፡ ለወ
ንዱም፡ ነውና ፡ ብሎ ፤ በፄዋዌ ፡
ወንዶች፡ወንዶቹ፡አልቀው፡ሴቶች፡
ሴቶቹ ፡ ቀርተው ፡ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡
በዙ፤ይህንንም፡ነቢያት፡እንደተገለጠ
ላቸው ፡ ተናግረውታል ፤ ከዚህ ፡
ኤርምያስ ፡ በዝኃ ፡ እምኆፃ ፡ ባሕር ፡
መበለታቲሆሙ ፡ ብሏል፤ ከዚያም ፡
ኢሳይያስ ፡ ወይእኀዛኁ ፡ ሰብዐ ፡
አንስት፡ለ፩ዱ፡ብእሲ፡ብሏል፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአምጻእኩ፡ወራዙተ፡ላዕለ፡እሞሙ፡

የአሕዛብን ፡ ጕልማሶች፡ በእናቶ
ቻቸው፤አመጣሁባቸው፡አለ፡በቍሙ፤
አንድም ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት፤
አንድም፡በነቢያት፡በካህናት፡የአሕ
ዛብን፡ጐልማሶች፡አመጣሁባቸው፡
አለ፤ማርከው፡እንዲወስዷቸው፡ነው፤

ወኃጥሮሙ፡በጊዜ፡መዓልት፡

ኃጥር ፡ ጉስቍልናቸው ፡ በቀትር ፡
ጊዜያት ፡ ነው ፡ አለ፤ ሌሊት ፡
ሲገሠግሱ፡ አድረው ፡ ቀን ፡ አደጋ ፡
ጥለው ፡ ያጠፏቸዋል፤ ያጐሰቍሏ
ቸዋል፤ አንድም ፡ ኃጥር ፡ ጕስቍል
ናቸው፡የሚመጣባቸው፡ባፍላ፡ባለጸ
ግነታቸው፡ጊዜ፡ነው፤

ወአውረድኩ ፡ ግብተ ፡ ላዕሌሃ ፡ ረዓደ ፡
ወምምዓ፡

በቤተ፡እስራኤልም፡ድንገት፡እንቅጥ
ቅጥታን፡ሽብርን፡አመጣሁባት፤

፱፡ሐልቀት፡እንተ፡ሰብዓተ፡ወለደት፡

በዚያ፡ወራት፡የሰባት፡እናት፡ሞተች፤
አንድም ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ጠፋች፤
አንድም ፡ ዐርቀት ፡ ይላል፤ ልጆቿ ፡
ጠፍተው ፡ እሱዋ ፡ ብቻ ፡ ቀረች ፤
አንድም ፡ ዐርቀት ፡ እስራኤል ፡
ጠፍተው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ብቻዋን ፡
ቀረች ፤ አንድም ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡
ወገኖቿ፡አልቀው፡ብቻዋን፡ቀረች፤

ወተቆጥዓት፡ነፍሳ፡

ከዚህ፡አስቀድሞ፡ባገኛት፡መከራ፡
ልቡናዋ፡ተበሳጨች፤ልጆቿ፡አልቀ
ውባት፤አንድም፡ሰባት፡መማከርት፡
ያሏት፡ቤተ፡እስራኤል፡በተድላ፡
በደስታዋ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሞተ ፤
አንድም፡ብዙ፡ነቢያት፡የነበሯት፡
አሪት፡አለፈች፤የልጆቿ፡የአይሁድ፡
ልቡና፡ብታልፍባቸው፡ተበሳጨች፤

ወዐረበ፡ፀሐይ፡ቀትረ፡መዓልት፡

ባፍላ ፡ ባለጸግነቷዋ ፡ ያገኛችው ፡
ተድላ፡ ደስታ ፡ ጠፋባት፤ አንድም ፡
ኃጥሮሙ፡በመከራቸው፡ጊዜ፡ባርባ፡
ዘመን፡በአይሁድ፡የሚመጣባቸው፡
ኃጥር ፡ ጕስቍልናቸው ፡ ጌታን ፡
በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ በቀትር ፡ ጊዜያት ፡
በሰቀሉት፡ፍዳ፡ነው፤

ወአውረድኩ ፡ ግብተ ፡ ላዕሌሃ ፡ ረዓደ ፡
ወምምዓ፡

ካርባ፡ዘመን፡በበኋላ፡እንቅጥቅጥታን፡
ሽብርን ፡ በቤተ ፡ አይሁድ ፡ አመጣ
ሁባት፤

ዐርቀት፡እንተ፡ሰብዓተ፡ወለደት፡

ፍጹም ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡
የነበራት፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ በዕለተ ፡
ዓርብ ፡ ባደረገችው ፡ ፍዳ ፡ ጠፋች፤
ሰባት ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ ነው፤ እስመ፡
ኲልቄ፡ ሳብእ ፡ በኀበ ፡ ዕብራውያን ፡
ፍጹም ፡ ውእቱ ፤ እንዲል፤ ወተቆ
ጥዓት፡ ነፍሳ ፡ ባገኛትም ፡ መከራ ፡
ልቡናዋ ፡ ተበሳጨች፤ወዐረበ፡ፀሐይ፡
ቀትረ፡መዓልት፤በዕለተ፡ዓርብ፡ባደረ
ገችው፡ፍዳ፡በቀትር፡ጊዜያት፡ፀሐይ፡
ገባባት፡ አለ፤ አይሁድ ፡ በጠፉ ፡ ጊዜ ፡
ባርባ ፡ ዘመን ፡ ፀሐይ ፡ ጨልሟል፤
ጨረቃ፡ደም፡ሁኗል፤ከዋክብት፡ረግ
ፈዋልና፤

ወተሐፍረት፡ወኃሥረት፡

ቤተ ፡ እስራኤል፤ አንድም ፡ ቤተ ፡
አይሁድ፡ፈጽማ፡ጐሰቈለች፤



ወለእለ ፡ ተርፉ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ውስተ ፡
ኲናት፡አገብአሙ፡በቅድመ፡ፀሮሙ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡

እምረኃብ ፡ ወእምብድብድ ፡ ብሎ ፡
ነበረና፤ ከቀጠናው ፡ ከቸነፈሩ ፡
የቀሩትን ፤ አንድም ፡ ካሥሩ ፡ ነገድ ፡
የቀሩትን ፤ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ በናቡከደ
ነፆር፤ አንድም ፡ ከናቡከደነፆር ፡
የቀሩትን ፡ በናቡዛርዳን፤ አንድም ፡
ከዐሥሩ፣ከሁለቱ፡ነገድ፡የቀሩ፡መቃ
ብያንን፡በጠላቶቻቸው፡ፊት፡እንዲ
ወድቁ፡አደርጋቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤

፲፡ አሌ፡ሊተ፡እምየ፡እስመ፡ወለድከኒ፡
ብእሴ ፡ ዘእሜነን ፡ ወእትዋቀስ ፡ በኲሉ ፡
ምድር፡

ላስተምር፡በምሄድበት፡አገር፡ሁሉ፡
የምጠላ፣ሳልገድል፡የምወቀስ፣እኔን፡
ወልደሽኛልና፤አንድም፡ዘእሜነን ወእ
ትዋቀስ፡ ይላል፤ ላስተምር ፡ በምሄ
ድበት፡አገር፡ሁሉ፡ዘእሜነን፡በአም
ልኮተ፡እግዚአብሔር፡የምጣላ፣ወእ
ትዋቀስ ፡ በመምከር ፡ በማስተማር ፡
ከነቢያተ፡ሐሰት፡ጋራ፡የምከራከር፡
እኔን ፡ ልጅሽን ፡ አምጠሽ ፡ ወልደሽ
ኛልና፡እናቴ፡ወዮልኝ፡አለ፡ነቢይ፤

ኢበቋዕኩ፡ወኢበቈዐኒ፡

እኔም፡ጧኤልን፡አልረባኋቸውም፤አል
ጠቀምኋቸውም ፤ እነሱም ፡ አልረ
ቡኝም ፤ አልጠቀሙኝም ፡ አለ፤
ሐተታ፡ ምነዋ ፡ ኢበቋዕኩ ፡ ወኢበ
ቈዐኒ ፡ አለ፤ ከመከረ ፡ ካስተማረ ፡
ዋጋው፡ይቀርበታልና፡እንዲህ፡አለ፡
ቢሉ፡ ካስተማረ ፡ አይቀር ፡ እነሱ ፡
ቢቀበሉት ፡ እሱንም ፡ ደስ ፡ ይለው ፡
ነበርና ፡ እንዲህ ፡ አለ፤ አንድም ፡
ማበርከት ፡ ይቀርበታልና ፡ አኮኑ ፡
ሐምሰ፡ መካልየ ፡ ወሀብከኒ ፡ ወናሁ ፡
ካልዓተ ፡ ሐምሰ ፡ መካልየ ፡ እለ ፡
ረባሕኩ ፡ አኮኑ ፡ ካልዓተ ፡ መካልየ ፡
ዘወሀብከኒ፡ወናሁ፡ካልዓተ፡ሐምሰ፡
መካልየ ፡ እለ ፡ ረባሕኩ ፡ ብሎ ፡
ማበርከት፡ይቀርበታልና፤

እስመ፡ኵሎሙ፡ይረግሙኒ፡

ምነዋ ፡ ስትመክራቸው ፡ ስታስተም
ራቸው፡አንተስ፡አትረባቸው፡አትጠ
ቅማቸው፡እነሱስ፡አይረቡሕ፡አይጠ
ቅሙህ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፣ ልመክ
ራቸው፡ላስተምራቸው፡ስሄድ፡ይህ፡
ዘብዛባ ፡ ምከረን ፡ አስተምረን ፡
ሳንለው፡ ሊመክረን ፡ ሊያስተምረን ፡
መጣ፡እያሉ፡ሁሉም፡ይሰድቡኛልና፡
ስለዚህ፡ነው፤

፲፩፡ ለይኩን ፡ እግዚኦ ፡ ለተሰርሖ ፡
ዚአሆሙ ፡ እመ ፡ ኢቆምኩ ፡ ኀቤከ ፡
በመዋዕለ፡ ምንዳቤሆሙ ፡ ወበጊዜ ፡
ሕማሞሙ፡በሠናይ፡

አቤቱ፡በመከራቸው፡ወራት፡መከራ፡
በሚቀበሉበትም ፡ ጊዜ ፡ በጎ ፡ ነገር፤
አንድም፡እነሱን፡ለማማለድ፡ባንተ፡
ፊት፡የቆምኩስ፡ባይሆን፡ይህ፡ሥራ፡
እነሱን፡ለማከናወን፡ይሁን፤ለኔ፡ይቅ
ርብኝና ፡ ይትአወቅኑ ፡ ማንሻ ነው፤
አንድም ፡ መከራ ፡ በሚቀበሉበት ፡
ወራት ፡ በመከራቸውም ፡ ጊዜ፡
እነሱን፡ ለማማለድ ፡ ባንተ ፡ ፊትማ ፡
ባልቆም፤

፲፪፡ በኀበ ፡ ዐር ፡ ይትዐወቅኑ ፡ ኀፂን ፡
እምሰሜን፡ወብርት፡እምደቡብ፡

እምሰሜንና እምደቡብ ፤ ብርት ፡
ወሐፂን፡አንድ፡ወገን፤በጠላቶቻቸው፡
ዘንድ፡ከባቢሎን፡ጦር፡እንዲመጣ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይታወቅ ፡ ነበርን ፤ አንድም ፡ ሰሜን ፡ ከፋርስ ፤ ደቡብ ፡ ከሜዶን ጦር ፡ እንደ ሚመጣ፡ይታወቅ፡ነበር?አንተ፡ካልገ ለጽክልኝ ፡ ጦር ፡ እንዲመጣ ፡ ይታ ወቅ ፡ ነበር ? ሐተታ ፡ ባቢሎንን ፡ ስለምን፡ሰሜን፡ደቡብ፡አላት፡ቢሉ፡ ግድፈት፡ ጸሐፊ ፡ ነው፤ አንድም ፡ የሁለት፡አገር፡አማርኛ፡ነው፤ባንዱ፡ አገር፡አማርኛ፡ሰሜን፡ባንዱ፡አገር፡ አማርኛ፡ደቡብ፡ብለዋታል፤አንድም፡ ዐራት፡ማዕዘን፡የሌለው፡አገር፡አለን፤ ለአንዱ ፡ አገር ፡ ሰሜን ፡ ብትሆን ፡ ላንዱ፡ አገር ፡ ደቡብ ፡ ትሆናለችና ፡ እንዲህ፡አለ፤

፲፫፤ ኀይለከ፡ወመዛግብቲከ፡እሁብ፡ለተ በርብሮ

ፍጹም ፡ ባለጸግነትህን ፤ አንድም ፡ ኃይለከ ፡ አዲሱን ፤ ወመዛግብቲከ፡ ድልቡን፡ለመበርበር፡አደርገዋለሁ፤

አኮ ፡ በቢሃ ፡ በኵሉ ፡ ኃጢአትከ ፡ ወበኵሉ ፡ ጌጋይከ፤

ይህንንም ፡ የማደርግብህ ፡ መቤዣ ፡ ተቀብዬ ፡ አይደለም ፡ አላ ፡ ያለበት ፡ ነው፤ በፍጹም ፡ በደልህ ፡ ነው ፡ እንጂ፤ አንድም ፡ በኵሉ ፡ ኃጢአትከ ፡ ለጊዜው፡ በሠራኸው ፡ በደልህ ፡ ወበኵሉ፡ጌጋይከ፡በዘገየው፡በደልህ፡ ነው፡እንጂ፤

ወበኵሉ፡በሐውርቲከ፤

ባገርህ ፡ ሁሉ ፡ ባደረግኸው ፡ ሥራህ ፡ ነው፡እንጂ፤

፲፬፤ ወአቀንየከ ፡ ለፀርከ ፡ ዘሀውድከ ፡ በብሔር፡ዘኢተአምር፤

በማታውቀው ፡ አገር ፡ ተማርከህ ፡ ሂደህ ፡ በዙሪያህ ፡ ላሉ ፡ ጠላቶችህም ፡ አስገዛሃለሁ፤

እስመ ፡ እሳት ፡ ትነድድ ፡ እመዓትየ፡ ላዕሌክሙ፤

ከቍጣዬ ፡ የተነሣ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍት ፡ በናንተ፡እንደ፡እሳት፡ትነድዳለችና፤

ወታውዒ፤

እናንተንም፡ታጠፋለችና፤

፲፭፤ አንተ፡ተአምር፡እግዚኦ፤

ኤርምያስ ፡ አንተስ ፡ ከእነሱ ፡ ሌላነህ? ትለኝ፡እንደሆነ፡እኔስ፡እንደነሱ፡እን ዳልበድልህ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ፤

ተዘከረኒ፡ወአድኅነኒ፡እምእለ፡ሮዱኒ፤

በቸርነትህ ፡ አስበህ ፡ ከከበቡኝ ፡ ጠላቶቼም፡አድነኝ፤

ወኢትትዓገሥ፡በእንቲአየ፤

የኔንም ፡ ነገር ፡ እያወቅኸው ፡ ቸል ፡ አትበለኝ፤

፲፮፤ ተዘከር ፡ ጽዕለትየ ፡ በእንቲአከ ፡ ለእለ፡አለዉ፡ቃለከ፤

ቃልህን ፡ የወነጀሉ ፡ እስራኤልን ፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብዬ፡ባስ ተምራቸው፡ይህ፡ዘብዛባ፡መምህር፡ ብለው ፡ የሰደቡኝን ፡ ስድብ፡ አስብ፤ አንድም፡ተዘከር፡ከመ፡ጸዐሉኒ፡በእን ቲአከ ፡ እለ ፡ ዐለዉ ፡ ቃለከ ፡ ይላል፤ ቃልህን፡ የወነጀሉ ፡ እስራኤል ፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብዬ፡ባስ ተምራቸው፡ይህ፡ዘብዛባ፡መምህር፡ ብለው ፡ እንደሰደቡኝ ፡ አስብ፤ አኅልቆሙ፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡ለ፡ የቀረው፡ነው፤ ለእለ፡ዐለዉ፡ቃለከ፡ አኅልቆሙ፡ይላል፤አሁንም፡ቃልህን፡ ወነጀሉ ፤ እስራኤልን ፡ አጥፋቸው፤

ወሊተሰ ፡ ይኩን ፡ ነገርከ ፡ ለፍሥሐየ ፡ ወለ ኀሤት፡ልብየ፤



ለኔስ ፡ ሕግህ ፡ ለልቡናዬ ፡ በልቡናዬ ፡ ለፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይሁነኝ፤

እስመ፡ተሰምየ፡ስምከ፡በላዕሌየ፡እግዚኦ፡ዘ፡ ኵሎ፡ትመልክ፤

ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ አቤቱ ፡ ስምህ ፡ በኔ፡ ላይ ፡ ተጠርቷልና፡አለ፤ነቢየ፡እግዚአ ብሔር ፡ ተብዬበታለሁና፤ አንድም ፡ ሁሉን፡የምትገዛ፡አቤቱ፡ስምህ፡በኔ፡ ላይ ፡ ተጠርቷልና ፡ አለ፤ ስምህን ፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብዬ፡በአ ንደበቴ፡አስተምረዋለሁና፤

፲፯፤ ወኢነበርኩ፡ውስተ፡ዐውደ፡ሙ፡ለመ ስተሣልቃን፡ዳዕሙ፡እፈርህ፡እምገጸ፡እዴከ፤

ከእደ ፡ መዓትህ ፡ የተነሣ ፡ እፈራለሁ ፡ እንጂ ፡ የላይ ፡ ፈሪ ፡ የታች ፡ ፈሪ ፡ እያሉ ፡ ሰውን ፡ በሚያጣሉ ፡ ሰዎች ፡ አደባባይ ፡ አልተቀመጥሁም፤ አንድም ፡ እጅ ፡ እግሩ ፡ በተቈረጠ ፡ ዓይኑ ፡ በፈረጠ ፡ በሚዘብቱ ፡ ሰዎች ፡ ሸንጎ ፡ አልተቀመ ጥሁም፤ ባሕቲትየ ፡ እነብር ፡ማንሻ ፡ ነው፤ አንድም ፡ ይህ ፡ የዳዕሙ ፡ ዋዌ ፡ ነው፤

ከእደ ፡ መዓትህም ፡ የተነሣ ፡ አንተን ፡ ፈርቼ፤

ባሕቲትየ፡እነብር፤

ከወንድሞቼ ፡ ከእስራኤል ፡ ተለይቼ ፡ ብቻዬን፡እቀመጣለሁ፤

ወጸገብኩዎ፡ለዕጕሥታር፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዬ ፡ ስምህን፡እየጠራሁ፤ባስተምር፤ሬቱን፡ ጠገብሁት ፡ አለ ፤ ክፉ ፡ ነገሩን ፡ ጠገብሁት፤

፲፰፤ለምንት፡ይጸንዑ፡እለ፡ያቴክዙኒ፤

ኤርምያስ፡አንተስ፡ከነሱ፡ሌላ፡ምን፡ ተበደልክ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እኔን ፡ የሚበድሉኝ ፡ የሚያሳዝኑኝ ፡ እስራ ኤል ፡ ለምን ፡ በተድላ ፡ በደስታው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ፤

ወዐብየ ፡ ቍስልየ፤

የኔስ ፡ ቍስለ ፡ መከራዬ ፡ ሰፋ፤

ወአልቦ ፡ ዘይፌውሰኒ፤

ከቍስለ ፡ መከራዬ ፡ የሚያድነኝ ፡ የሚራዳኝ፡ወዳጅ፡ዘመድ፡የለኝም፤

ከዊነ ፡ ኮነኒ ፡ ከመ ፡ ማየ ፡ ሐሰት ፡ ዘአልቦ ፡ ሃይማኖት፤

እኔስ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዬ ፡ የማስተምረው ፡ ትምህርት ፡ የም ናገረው ፡ ትንቢት ፡ መታመን ፡ እንደ ሌለው ፡ እንደጕርፍ ፡ ውሃ ፡ ሆነብኝ ፡ አለ፤ያ፡ለጊዜው፡ተሰምቶ፡እንዲጠፋ፡ የኔም ፡ ትምህርት ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ተሰምቶ ፡ ጠፋብኝ፡ አልያዙልኝም ፡ ሲል፡ነው፤

፲፱፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፤

እኔ፡ከዊነ፡ኮነኒ፡ብዬ፡የዚህን፡ነገር፡ ስለተናገርኩ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ አለኝ፤

ለእመ፡ተመየጥከ፡እመይጠከ፤

አንተ፡ከውዳሴ፡ከንቱ፡ከተመለስህ፤ አንድም ፡ ብትመለስ ፡ እኔም ፡ ወደ ፡ መምህርነትህ፡እመልስሃለሁ፤

ወትቀውም፡ቅድመ፡ገጽየ፤

በፊቴ ፡ በባለሟልነትም ፡ ጸንተህ ፡ ትኖራለህ፤

ወእመ ፡ አውጻእከ ፡ ክብረ ፡ ሥጋዌ ፡ ትከውን ፡ ከመ፡አፉየ፡እምልብከ፤

ውዳሴ ፡ ከንቱውን ፤ አንድም ፡ ክብረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልባዌ ፡ ይላል ፤ ንቡር ፡ ድልው ፡ ሲል ፡
ነው ፤ በልቡናህ ፡ አድሮ ፡ ጸንቶ ፡
የሚኖር ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱውን ፡ ካንተ ፡
ብታርቅ ፡ እንደ ቃሌ ፡ ታዛለህ ፤ እንደ ፡
እጄ ፡ ትይዛለህ ፤

ወይሠወጡ ፡ እሙንቱ ፡ ኀቤከ ፡ ወአንተሰ ፡
ኢትትመየጦሙ ፤
እነሱ ፡ ምከረን ፡ አስተምረን ፡ እያሉ ፡
ወዳንተ ፡ ሕግ ፡ ይመጣሉ ፤ አንተ ፡ ግን ፡
ወደነሱ ፡ ሕግ ፡ አትመለስላቸውም ፤

፳፤ ወእሬስየከ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡
ዓረፍተ ፡ ብርት ፡ ጽኑዕ ፤
ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ በዝ ፡ ሕዝብ ፡ ይላል ፤ ለዝ ፡
ሕዝብ ፡ ለዚህ ፡ ወገን ፤ በዝ ፡ ሕዝብ ፡
በዚህ ፡ ወገን ፡ እንደብረት ፡ ግድግዳ ፡
አደርግሃለሁ ፡ አለ ፤ ያ ፡ ጽኑዕ ፡ ነው ፤
በነሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደዚያ ፡ ጽኑ ፡ አደርግ
ሃለሁ ፤

ወይፀብዑከ ፡ ወኢይክሉከ ፤
ኤርምያስ ፡ አንተን ፡ ተሰብስበው ፡
ይጣሉሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አይችሉህም ፤
አንድም ፡ አይችሉህም ፡ እንጂ ፡ ተሰብ
ስበው ፡ ይጣሉሃል ፤

እስመ ፡ አነ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌከ ፤
እኔ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በረድዔት ፡ አለሁና ፤

ወአነ ፡ አድኀነከ ፡ እምእደ ፡ እኩያን ፡ ወእባ
ልሐከ ፡ እምእደ ፡ ዐላውያን ፤
አድኀነከና ፡ እባልሐከ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
እኩያን ፡ የወል ፡ ነው ፤ ዐላውያን ፡
ሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚወ
ነጅሉ ፡ ከእስራኤልም ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡
እንዳዳንኩህ ፡ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡
ፈጽሜ ፡ አድንሃለሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ፡

፩፤ ወአንተሰ ፡ ኢታውስብ ፡ ብእሲተ ፤
አንተ ፡ ሚስት ፡ አታግባ ፡ አለኝ ፤

፪፤ ወኢትለድ ፡ ወልደ ፡ ወወለተ ፡ በዝ ፡
ብሔር ፤
በራሱ ፡ እስራኤልን ፡ መናገር ፡ ነው ፤
አንተስ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ሚስት ፡
አግብተህ ፡ ወንድ ፡ ልጅና ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
አትውለድ ፡ አለው ፤

፫፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
በእንተ ፡ ደቂቅ ፡ ወአዋልድ ፡ እለ ፡ ይትወለዱ ፡
በዝ ፡ ብሔር ፤
በዚህ ፡ አገር ፡ ስለሚወለዱ ፡ ወንዶች ፡
ልጆችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፤

ወበእንተ ፡ እማቲሆሙ ፡ እለ ፡ ሐረሳሆሙ ፤
ባራስ ፡ ቤታቸው ፡ ሁነው ፡ ስለሚያጠ
ቡዋቸው ፡ እናቶቻቸውም ፤ አንድም ፡
ወበእንተ ፡ አዕማቲሆሙ ፡ እለ ፡
ሐረሳሆሙ ፡ ይላል ፤ አብነት ፡ እመቤቶ
ቻቸውንም ፡ በወለዱበት ፡ ቦታ ፡ ስለሚ
ያርሱዋቸው ፡ ሴቶች ፡ ባሮችም ፤

ወበእንተ ፡ አበዊሆሙ ፡ እለ ፡ ወለድዎሙ ፡
በዝ ፡ ምድር ፤
በዚህ ፡ አገር ፡ ስለወለደ ዋቸው ፡ ስለአባ
ቶቻቸውም ፡ እንዲጠፉ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮዋልና ፤
ሞተ ፡ እኩየ ፡ ይመውቱ ፡ ማንሻ ፡ ነው ፤
አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አለ ፡
ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ አባቶችና ፡ እናቶች ፡
ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡
ወንዶች ፡ ባሮችና ፡ ሴቶች ፡ ባሮች ፡
እነዚህ ፡ ሁሉ ፤



፬፤ ሞተ ፡ እኩየ ፡ ይመውቱ ፤
ክፉ ፡ ሞት ፡ ይሞታሉ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፤

ወኢይበክይዎሙ ፡ ወኢይቀብርዎሙ ፡
ጻዕሙ ፡ ይትሐበለይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡
ምድር ፤
በምድር ፡ ላይ ፡ ሰጣ ፡ ብለው ፡ ወድቀው ፡
ቀን ፡ አዕዋፍ ፡ ሌሊት ፡ አራዊት ፡ ይበዘ
ብዙዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ እነሱንስ ፡ ዘመዶ
ቻቸው ፡ አልቅሰው ፡ አይቀብሩዋ
ቸውም ፤ አንድም ፡ ዘመዶቻቸው ፡
አልቅሰው ፡ አይቀብሩዋቸውም ፤
ጻዕሙ ፡ ይትሐበለይዎሙ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ሰጣ ፡ ብለው ፡ ወድቀው ፡ ቀን ፡
አዕዋፍ ፡ ሌሊት ፡ አራዊት ፡ ይበዛበዙዋ
ቸዋል ፡ እንጂ ፤

ወይወድቁ ፡ በኩናት ፡ ወየኃልቁ ፡ በረኃብ ፤
ወደዘመቻ ፡ የሄዱት ፡ በጦር ፤ በከተማ ፡
የቀሩት ፡ በቀጠና ፡ በፃዕር ፡ ያልቃሉ ፤

ወይከውን ፡ አብድንቲሆሙ ፡ መብልዐ ፡
ለአዕዋፈ ፡ሰማይ ፡ ወለአራዊተ ፡ ገዳም ፤
ከዘመቻ ፡ የሄዱት ፡ በጦር ፤ ከከተማ ፡
የቀሩት ፡ በቀጠና ፡ አልቀው ፡ሙተው ፡
የሚቀብራቸው ፡ አጥተው ፡ ሬሳቸው ፡
ቀን ፡ ለአዕዋፍ ፡ ሌሊት ፡ ለአራዊት ፡
ምግብ ፡ ይሆናል ፤

፭፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ
ዋልና ፤

ኢትብክዮሙ ፤
ኢይበክይዎሙ ፡ ወኢይቀብርዎሙ ፡
ብሎ ፡ ነበርና ፡ ለነዚያ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፤
አንተም ፡ ለነሱ ፡ አትዘንላቸው ፡ አታል
ቅስላቸው ፤

ወኢትባእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ላህ ፡ ወኢትላ
ህዎሙ ፤
ከኃዘን ፡ ቤት ፡ ገብተህ ፡ አትላቀሳቸው ፤
አንድም ፡ ወኢትባእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡
ምሳህ ፡ ይላል ፤ እዝን ፡ ወደሚበላበት ፡
ቤት ፡ አትግባ ፤ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምሳህ ፡
ባለው ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምስሐግ ፡ ይላል ፤
እንደዚሁ ፡ ያስተረጕማል ፤
ዝ ፡ ምስሐግ ፡ ዘኢዮስያስ ፡ እንዲል ፤
ወኢትላህዎሙ ፤ አትዘንላቸው ፤ አታ
ልቅስላቸው ፤ ወኢትነጽሮሙ ፤
በዓይነ ፡ ምሕረትም ፡ አትመልከ
ታቸው ፤

እስመ ፡ አዕተትኩ ፡ ሰላምየ ፡ እምዝ ፡ ሕዝብ ፡
ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወምሕረትየሂ ፡ ወሣህ
ልየሂ ፤
ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ አን
ድነቱን ፡ ይቅርታዩን ፡ ቸርነቱን ፡
ከዚህ ፡ ወገን ፡ አርቅበታለሁ ፡ ብሏልና ፤

፮፤ ወይመውቱ ፡ ንዑስ ፡ ወዐቢይ ፡ በዝ ፡
ምድር ፤
ቃሌን ፡ ያልሰሙ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡
በዚህ ፡ አገር ፡ ይሞታሉ ፤

ወኢይቀብርዎሙ ፡ ወኢይላህውዎሙ ፡ ወኢ
ይከርዩ ፡ሎሙ ፡ ወኢይበክይዎሙ ፤
የተላለፈ ፡ ነው ፤
ኢይከርዩ ፡ ሎሙ ፡ ወኢይቀብርዎሙ ፡
ኢይላህውዎሙ ፡ ወኢይበክይዎሙ ፡
ሲል ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ዘመዶ
ቻቸው ፡ መቃብር ፡ ቆፍረው ፡
አልቅሰው ፡ አይቀብሩዋቸውም ፤
አንድም ፡ እንዳለ ፡ ይሆናል ፤ ዘመዶ
ቻቸው ፡ አልቅሰው ፡ መቃብር ፡
ቆፍረው ፡ አይቀብሯቸውም ፤ አንድም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘመዶቻቸው ፡ መቃብርን ፡ ቆፍረው ፡
ከቀበሯቸው ፡ በኋላ ፡ አያለቅሱላቸ
ውም ፤ ከቀበሯቸው ፡ በኋላ ፡ የሚያለ
ቅሱት ፡ ልቅሶ ፡ አለና ፤

ወኢይትላጸዩ ፤
አዘንም ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ አይላጩ
ላቸውም ፤

፯፤ ወኢይናዝዝዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘሞቱ ፤
ስለሞቱባቸው ፡ ዘመዶቻቸውም ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ያጥናችሁ ፤ አድርሶ ፡
አይመለስ ፤ የኃዘን ፡ ዳርቻ ፡ ያድርገው ፡
ብለው ፡ አያረጋጉዋቸውም ፤

ወኢይግዕቱ ፡ ሎሙ ፤
ወተት ፡ አይግቱዋቸውም ፤ ገንፎ ፡ አያገ
ነፉላቸውም ፤ ብኖር ፡ አመት ፡ ብበላ ፡
ጋት ፡ እንዲሉ ፤

ወኢይፌትቱ ፡ ሎሙ ፡ ኅብስተ ፤
እዝንም ፡ አይወስዱላቸውም ፤

ወጽዋዐ ፡ ኢያሰትይዎሙ ፡ በዘይትናዘዙ ፡
በእንተ ፡ አቡሆሙ ፡ ወእሞሙ ፤
ስለሞቱ ፡ አባትና ፡ እናታቸው ፡
በሚረጋጉ ፡ ገንዘብ ፡ የሚረጋጉበትን ፤
ወይንንም ፡ አያጠጡዋቸውም ፤
ሀብዎሙ ፡ ስካረ ፡ ለኅዙናን ፡ ወወይነ ፡
ይስተዩ ፡ ትኩዛን ፡ ከመ ፡ ይርሥዕዋ ፡
ለኃዘን ፡ እንዳለ ፡ ሰሎሞን ፤

፰፤ ወኢትባዕ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ቤተ ፡
ምስሐግ ፤
ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፤

ወኢትንበር ፡ ወኢትብላዕ ፡ ወኢትስተይ ፤
ከዕዝኑም ፡ ቤት ፡ ገብተህ ፡ ተቀምጠህ ፡
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ አትብላ ፤ አትጠጣ ፡ አለ ፤
ለማጸየፍ ፤

፱፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ኃያል ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፤
እንዲህ ፡ አድርጋችሁ ፡ በድላችሁት
ስላሳዘናችሁት ፡ አምጻኤ ፡ ዓለማት
ወላዴ ፡ ፍጥረት ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ እሥዕር ፡ እምዝንቱ ፡ ብሔር
በቅድመ ፡ አዕይንቲከሙ ፡ ወበመዋዕሊከ
ቃለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወቃለ ፡ ኃሤት ፡ ቃለ
መርዓዊ ፡ ወቃለ ፡ መርዓት ፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ እናንተ ፡ በ
ይናችሁ ፡ እያያችሁ ፡ ባላችሁበትም
ዘመን ፡ እገሌ ፡ ዕገሊትን ፡ አጨ
እገሊት ፡ እገሌን ፡ አጨች ፤ የም
ሉትን ፡ ቃል ፤ አንድም ፡ ባሥርቱ ፡ እ
ጨበጨቡ ፡ የሚዘፍኑት ፡ ጨዋታ
አለና ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋለሁ ፡ አለ ፤

፲፤ ወሶበ ፡ ነገርኮሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንተ
ኵሎ ፡ ነገረ ፤
ለእሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለእ
ዚህም ፡ ወገኖች ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር
በነገርካቸው ፡ ጊዜ ፤

ወይብሉከ ፡ ለምንት ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር
ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ እኩየ ፡ ዐቢየ ፡ ላዕሌነ ፤ ምንት
ጌጋይነ ፡ ወምንት ፡ አበሳነ ፡ ዘአበስነ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ አምላክነ ፤
የምንታገሠው ፡ በደላችን ፡ ምንድነው
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ የበ
ልንበት ፡ በደል ፡ ምንድነው ? እግዚ
ብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ
በናንተ ፡ ላይ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ብሎ
ለምን ፡ ተናገረብን ፡ ይሉሃል ፤
ትብሎሙ ፡ ማንሻ ፡ ነው ፤ አንድም
ወሶበ ፡ ነገርኮሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንተ
ኵሎ ፡ ነገረ ፤



ለኒህ ፡ ወገኖች ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡
አንተ ፡ ብትነግራቸው ፤

ወይብሉከ ፡ ለምንት ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘንተ ፤
እነሱም ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡
ይህን ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አደር
ገዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ ተናገረብን ?

ወምንት ፡ ጌጋይነ ፡ ወምንት ፡ አበሳነ ፤
ምን ፡ በደልን ? ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብ
ሔርንስ ፡ የበደልንበት ፡ ነገር ፡ ምንድ
ነው ? ብለው ፡ ቢጠይቁህ ፡ ይኽ ፡ ለ ፡
በግዕዝ ፡ የገባ ፡ ነው ፤
ወኢዐበስኩ ፡ ለአምላኪየ ፡ እንዲል ፤

፲፩፤ ትብሎሙ ፡ እስመ ፡ ኀደጉኒ ፡
አበዊክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤
ቀድሞ ፡ አባቶቻችሁ ፡ በሕግ ፡ በአም
ልኮት ፡ ትተውኛልና ፤

ወሖሩ ፡ ወተለዉ ፡ አማልክተ ፡ ነኪር ፡
ወተቀንዩ ፡ ሎሙ ፤
የአሕዛብንም ፡ ጣዖታት ፡ ተከትለው ፡
ሂደው ፡ ተገዝተውላቸዋልና ፤

ወኪያየሰ ፡ ኀደጉኒ ፤
እኔን ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ትተ
ውኛልና ፤

ወሕግየኒ ፡ ኢዐቀቡ ፤
ሕጌንም ፡ አልጠበቁምና ፤

፲፪፤ ወአንትሙኒ ፡ አብዛኅክሙ ፡ ገቢረ ፡
እከይ ፡ እምአበዊክሙ ፤
ዛሬም ፡ እናንተ ፡ ልጆቻቸው ፡
ከቀደሙ ፡ አባቶቻችሁ ፡ ይልቅ ፡
ክፋትን ፡ አብዝታችሁ ፡ ሠርታችሁ
ታልና ፤ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አለ ፡ በላቸው ፤

ወናሁ ፡ ኵልክሙ ፡ ተለውክሙ ፡ ፍትወተ ፡
ልብክሙ ፡ እኩየ ፤
ቀድሞም ፡ አባቶቻችሁ ፡ ዛሬም ፡
እናንተ ፡ ሁላችሁ ፡ ልጆቻቸው ፡ የልቡ
ናችሁን ፡ ክፉ ፡ ፈቃድ ፤
አንድም ፡ ፍትወተ ፡ ልብክሙ ፡ እኩይ ፡
ይላል ፤
የክፉ ፡ ልቡናችሁን ፡ ፈቃድ ፡ ተከት
ላችሁ ፡ ሠራችሁት ፤

ወዐበይክሙ ፡ ሰሚዖትየ ፤
በነቢያት ፡ በካህናት ፡ አድሬ ፡ የምነግራ
ችሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንሰማም ፡ እምቢ ፤
አንድም ፡ እምቢ ፡ አንሰማም ፡ አላችሁ ፤

፲፫፤ ወእገድፈክሙ ፡ እምዝ ፡ ምድር ፡
ውስተ ፡ ብሔር ፡ ዘኢተአምሩ ፡ ኢአንትሙ ፡
ወኢአበዊክሙ ፤
እምቢ ፡ አንሰማም ፡ ካላችሁ ፡ ግን ፡
ካገራችሁ ፡ አስማርኬ ፡ አስወጥቼ ፡
ዛሬ ፡ እናንተ ፡ ቀድሞ ፡ አባቶቻችሁ ፡
ወደማያውቁት ፡ አገር ፡ እሰዳችኋለሁ ፤

ወትትቀነዩ ፡ በህየ ፡ ለባዕዳን ፡ አማልክት ፡
መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ እለ ፡ ኢይምሕሩክሙ ፤
ከሀገራችሁም ፡ ተማርካችሁ ፡ በሄዳች
ሁበት ፡ አገር ፤ በመዓልትም ፡ በሌ
ሊትም ፡ ለማያዝኑላችሁ ፤ ለማይራሩ
ላችሁ ፡ ለጣዖታቱ ፡ ትገዛላችሁ ፤

፲፬፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡
መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤
ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ስላደረጋችሁ ፡ እንዲህ ፡
ያለ ፡ ወራት ፡ እነሆ ፡ ይመጣል ፡ አለ ፡
እግዚአብሔር ፤

፲፭፤ ወኢይብሉ ፡ እንከ ፡ ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ዘአውጽአሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡
እምድረ ፡ ግብፅ ፤ ዳዕሙ ፡ ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ዘአውጽአሙ ፡ ለቤተ ፡ ፳ኤል ፡
እምብሔረ ፡ ሰሜን ፤
ኋላ ፡ በሰባው ፡ ዘመን ፡ ትሩፋንን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከባቢሎን ፡ ያወጣቸው ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡
ቀድሞ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብፅ ፡
ያወጣቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡
ነው ፡ አይሉም፤ አንድም ፡ ስም ፡ ይወራ
ረሳል ፤ ግብፅ ፡ ያላት ፡ ባቢሎን ፡ ናት ፤
ሰሜን ፡ ያላት ፡ ግን ፡ ጽርዕ ፡ ናት ፤ ኋላ ፡
በሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ መቃብ
ያንን ፡ ከጽርዕ ፡ ያወጣ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ቀድሞ ፡
ትሩፋንን ፡ ከባቢሎን ፡ ያወጣ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ሕያው ፡ ነው ፡ አይሉም፤

ወእምኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ኀበ ፡ ወሰድክዎሙ ፡
ሀየ ፡ አአትዎሙ ፡ ውስተ ፡ ምድሮሙ ፡ ዘወሀብ
ክዎሙ ፡ ለአበዊሆሙ፤

እነሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡
ግን፡ ካስማረኩበት ፡ አገር ፡ ሰብስቤ ፡
ቀድሞ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ዛሬ ፡ ለነሱ ፡
ወደሰጠኋቸው ፡ አገር ፡ እወስዳቸ
ዋለሁ፤

፲፮፤ ወናሁ ፡ አነ ፡ እፌኑ ፡ ብዙኃነ ፡
መሠግራነ ፡ ያሠግርዎሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወእምዝ ፡ እፌኑ ፡ ብዙኃነ ፡ ነዓውያነ ፡
ወይነዕውዎሙ ፡ በላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አድባር ፡
ወበላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አውግር ፡ ወበላዕለ ፡ ኵሉ ፡
ንቅዓታተ ፡ ኰኵሕ፤

ብዙኆነ ፡ መሠግራንና ፡ ብዙኆነ ፡
ነዓውያነ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እኔም ፡ በነሱ ፡
እየፈለጉ ፡ የሚያድኑዋቸው ፡ ጠላቶቻ
ቸውን ፡ አመጣባቸዋለሁ ፤ አንድም ፡
እየራሱ ፡ ለማውጣት ፡ መሠግራነ ፡
ያሠግርዎሙ፤
ረኀብ ፡ ቸነፈር ፡ ናቸው ፤ ነዓውያነ ፡
ማርከው ፡ የሚወስዷቸው ፡ አሕዛብ ፡
ናቸው ፤ በተራራው ፡ በኰረብታው ፡
በገደል ፡ (ጥጋጥግ) ፡ በዚህ ፡ ሁሉ
እየፈለጉ ፡ የሚያድኗቸው ፡ አሕዛብን
አመጣባቸዋለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር

፲፯፤ እስመ ፡ አዕይንትየ ፡ ይኔጽራ ፡ ውስተ
ኵሉ ፡ ፍናዊሆሙ፤
ክፉ ፡ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ዓይኖቼ
አንድም ፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎቼ ፡ ይመለከ
ታሉና፤

ወኢይሤወር ፡ እምቅድመ ፡ አዕይንትየ
ኃጢአቶሙ ፡ ወኢይትኀባዕ ፡ ጌጋዮሙ፤
እኔንም ፡ የሚበድሉበት ፡ ፍጹም ፡ ኃጢ
አታቸው ፡ በደላቸው ፡ ካይኔ ፡ አይሠ
ወርም፤

፲፰፤ ወእፈድዮሙ ፡ ካዕበተ ፡ ዐመፃሆሙ
ወጌጋዮሙ ፡ በዘአርኰሱ ፡ ምድርየ ፡ በዕበ
ርኵሶሙ ፡ ወበኃጢአቶሙ ፡ ዘአርኰሱ
ርስትየ፤
ርስቴ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ባረከሱበት
ኃጢአታቸው ፡ ሀገሬ ፡ ኢየሩሳሌምን
ሰንፈው ፡ ባረከሱበት ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ
በሚሆን ፡ ኃጢአታቸው ፡ ፍዳውን
አመጣባቸዋለሁ፤
አንድም ፡ ወእፈድዮሙ ፡ ካዕበተ
ዐመፃሆሙ፡ ወጌጋዮሙ ፡ በፍጹም
በደላቸው ፡ መከራውን ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ
አድርጌ ፡ አመጣባቸዋለሁ።

፲፱፤ እግዚአብሔር ፡ ኃይልየ ፡ ወረዳዕየ
ወፀወንየ ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ፤
ነቢዩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሌ ፡ ነው
ረዳቴም ፡ ነው ፤ በመከራዬም ፡ ቀን
የሚረዳኝ ፡ አምባዬ ፡ መጠጊያዬ
ነው፤ የማይረዳ ፡ አምባ ፡ መጠጊያ
አለና ፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ እንዲህ ፡ አለ፤
ወይመጽኡ ፡ አሕዛብ ፡ ኀቤከ ፡ እምአጽናፈ
ምድር፤



አሕዛብ ፡ ያላቸው ፡ እስራኤል ፡ ናቸው፤
አሕዛብ ፡ እስራኤል ፡ ከተማረኩበት ፡
አገር ፡ ከጽንፈ ፡ ምድር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡
ወዳንተ ፡ ይመጣሉ ፡ አለ ፡ የእግር ፡ ነው፤
አንድም ፡ ወገኖችህ ፡ አሕዛብ ፡
እስራኤል ፡ ከያሉበት ፡ አገር ፡ በሕግ ፡
በአምልኮት ፡ ወዳንተ ፡ ይመጣሉ ፡ አለ ፡
የግብር ፡ ነው፤

ወይብሉ ፡ በከ ፡ ወሐሰተ ፡ ገብሩ ፡ አበዊነ ፡
ጣዖቶሙ ፡ ዘለምንትኒ ፡ ኢይበቊዖሙ፤
ቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ በከንቱ ፡
በሐሰት ፡ ነገር ፡ ለምንም ፡ ለምን ፡ የማይ
ረቧቸው ፡ የማይጠቅሟቸው ፡ ጣያ
ታቱን ፡ ሠሩ ፡ ይላሉ፤

፳፤ ይገብርኑ ፡ ሎቱ ፡ ሰብእ ፡ አማልክተ ፡
ዘኢኮኑ ፡ አማልክተ፤
አማልክት ፡ ያይደሉ ፡ ጣዖታቱን፤
አንድም ፡ እንዘ ፡ ኢኮኑ ፡ አማልክተ ፡
ይላል፤
አማልክት ፡ ስንኳ ፡ ሳይሆኑ ፡
አማልክት ፡ የሚባሉ ፡ ጣዖታቱን ፡
ሰው፡ ለራሱ ፡ መሥራት ፡ ይገባዋልን ፡
አይገባውም፤

፳፩፤ በአንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡
እነግሮሙ ፡ በዝ ፡ መዋዕል፤
ጣዖቱን ፡ ሠርተው ፡ እያመለኩ ፡ ስለበ
ደሉኝ ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ የሚመጣባ
ቸውን ፡ መከራ ፡ እነግራቸዋለሁ፤
ወእርእዮሙ ፡ እዴየ ፡ ወኃይልየኒ፤
እደ ፡ መዓቴንም ፡ ኃይሌንም ፡ እገልጥባ
ቸዋለሁ፤
ወየአምሩ ፡ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምየ፤
እነሱም ፡ ስሜ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንደሆነ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ያውቃሉ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡
### ጉባዔ፤

፩፤ ኃጢአት ፡ ለይሁዳ ፡ ጽሑፍ ፡ በቀለመ ፡
ሐጺን ፡ ውስተ ፡ ሠሌዳ ፡ ዕብን፤
የሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ኃጢአቷ ፡ በብረት ፡
ብርዕ ፡ በደንጊያ ፡ ሠሌዳ ፡ ተጽፏል ፤
ተቀርጿል ፡ አለ ፤ ቀለም ፡ ያለው ፡ ብርዕ ፡
ሲል ፡ ነው፤
ከመ ፡ ቀለመ ፡ ጸሐፊ ፡ ዘጠበጠበ ፡
ይጽሕፍ ፡ ልሳንየ ፡ እንዲል፤
በብረት ፡ ብርዕ ፡ የተጻፈ ፡ በደንጊያ ፡
ሠሌዳ ፡ የተቀረጸ ፡ እንዳይጠፋ ኃጢ
አቷ ፡ አይጠፋም ፡ ሲል ፡ ነው ፤
አንድም፡ በቁሙ ፡ በብረት ፡ ብርዕ ፡
ጽፈው ፡ በደንጊያ ፡ ሠሌዳ ፡ ቀርጸው ፡
ይተዉታልና፤

ወግሉፍ ፡ ውስተ ፡ ጽሌ ፡ ልቦሙ፤
ይኸውም ፡ በልቡናቸው ፡ ሠሌዳነት ፡
ተጽፏል ፡ አለ ፤ ጧት ፡ ማታ ፡ ኃጢ
አትን ፡ እንሥራ ፡ ጣዖቱን ፡ እናምልክ ፡
እያሉ ፡ ያስባሉና፤

ወበአቅርንተ ፡ ምሥዋዒሆሙ፤
በአቅርንተ ፡ ምሥዋዑም ፡ ላይ ፡
ተጽፎዋል ፡ አለ ፤ መሥዋዕተ ፡ አሪት ፡
በተሠዋበት ፡ በአቅርንተ ፡ ምሥዋዑ ፡
ላይ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ይሠዉበ
ታልና፤

፪፤ እስከ ፡ ይዜከሩ ፡ ደቂቆሙ ፡ ምሥዋ
ዒሆሙ ፡ ወምሕራማቲሆሙ ፤ ውስተ ፡ ዕፅ ፡
ዘፀ ፡ ጽላሎት ፡ ዲበ ፡ አውግር ፡ ልዑላት ፡
ወአድባረ ፡ ገዳም፤
ቀድሞ ፡ አባቶቻቸው ፡ ይሠዉበት ፡
የነበረ ፡ ምሥዋዑን ፡ አባቶቻቸው ፡
ይሠግዱበት ፡ የነበረ ፡ መስገጃውን ፡ በታ

www.ethiopianorthodox.org

ላላቆች፡ተራሮችና፡በጥቃቅን፡ኰረብ
ታዎች ፡ ላይ ፡ ያለ ፤ ጥላ ፡ ባለው ፡
እንጨት፡በታች፡ሁነው፡ኃጢአት፡
መሥራታቸውን ፡ ጣዖት ፡ ማምለካ
ቸውን፡ልጆቻቸው፡እስኪያስቡት፡
ድረስ፡ደርሰው፤

፫፤ ኃይለከ፡ ኵሎ፡ ወመዛግብቲከ፡ ለተበ
ርብሮ፡እሁብ፤
ቤተ፡እስራኤል፡ከኃጢአቴ፡አልመ
ለስም፤ከክፋቴ፡አልታገሥም፡ብለህ፡
እምቢ፡ካልኸኝስ፤
ኃይለከ ፡ ባለጸግነትህን ፡ የቤትህን ፤
ወመዛግብቲከ ፤ እሪቅ ፡ ጎተራህን ፤
አንድም ፡ ኃይለከ ፡ ኵሎ ፤ አዲሱን ፡
ወመዛግብቲከ፤
ድልብህን፡አሕዛብ፡መጥተው፡እንዲ
በረብሩት፡አደርገዋለሁ፤
ወአውግረ፡ጣዖትከ፡በኃጢአትከ፤
ጣዖት ፡ ያቆምህባቸው ፡ ኮረብታዎ
ችንም ፡ በኃጢአትህ ፤ አንድም ፡
ወአህጉረ ፡ ጣዖትከ ፡ ለኃጢአትከ ፡
ይላል፤
ኃጢአት ፡ ልትሠራባቸው ፡ ጣዖት ፡
ያቆምህባቸው፡አገሮችህንም፤
ወለኵሉ፡አድዋሊከ፤
አውራጃህንም ፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡
ወለኵሎን፡አዋልዲከ፡ይላል፤
ጥቃቅኖች ፡ አገሮችህንም ፡ ሁሉ ፡
ለአህዛብ፡አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፤

፬፤ ወተኃልቅ፡እምርስትከ፡ለርእስከ፡ዘወ
ሀብኩከ፡ለከ፤
ትትፈለጥ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ወረስሃት ፡
ልትገዛት ፡ አርሰህ ፡ ቆፍረህም ፡
ልትበላት፡ለራስህ፡ትሁንህ፡ብዬ፡
ከሰጠሁህ፡ርስትህም፡ትለያለህ፤

ወአቀንየከ፡ለፀርከ፡ውስተ፡ምድር፡ዘኢተ
አምር፤
ተማርከህም ፡ ሂደህ ፡ አይተኸው ፡
በማታውቅ፡በአሕዛብ፡አገር፡ሁነህ፡
ለጠላትህ፡ትገዛለህ፤
እስመ፡እሳት፡ትነድድ፡በመዓትየ፡እስከ፡
ለዓለም፤
በመዓትየ፡ከቍጣዬ፡ጋራ፤በ፡ያለው፡
ጋራ፡ሲል፡ነው፤ወተዋሐደ፡ቃል፡
በሥጋ፡እንዲል፤አንድም፡እመዓትየ፡
ይላል ፡ ከቍጣዬ ፡ የተነሣ ፡ ጦር ፡
መቅሠፍት፡ለዘላለሙ፡ትነድዳለችና፤

፭፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ርጉመ፡ለይኩን፡ኵሉ፡ሰብእ፡ዘይትአመን፡
በዕጓለ፡እመሕያው፤
በግብፃውያን፡ጦር፡የሚታመን፡ሰው፡
ሁሉ፤አንድም፡በሰው፡ሠራሽ፡ጣዖት፡
የሚያምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ፤ አንድም ፡
አካላዊ፡ቃል፡ባልተዋሐደው፡ዘርዓ፡
ዳዊት ፡ የሚያምን ፡ ሰው፡ ሁሉ ፡
ርጉም፡ይሁን፤
ወያሰምክ፡መዝራዕቶ፡በቱ፤
ልቡናውንም ፡ በሱ ፡ የሚያሳምን ፤
አንድም ፡ ወያሰምክ ፡ መዝራዕቶ ፡
ሎቱ፡ይላል፤
ያድነኛል፡ብሎ፡ሥልጣኑን፡የሚያ
ምነው፡ሰው፡ሁሉ፤
ወእምእግዚአብሔር፡ይርኅቅ፡ልቡ፤
ልቡናውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚ
ርቅ ፡ አለ ፤ የሚክድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ርጉም፡ይሁን፤

፮፤ ወይከውን፡ከመ፡ኳሂላ፡በውስተ፡
ገዳም፤



እንዲህ፡ያለው፡ሰው፡በወንዝ፡ዳር፡
ወድቆ፡እንደሚኖር፡እንደ፡ዶቅማ፡
እንደ፡አሐያ፡ይሆናል፤
ዘኢይሬኢ፡ሠናየ፡ሶበ፡ይመጽእ፤
ደመና ፡ ዝናም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ልምላሜ፡እንደማያይ፤
ወይነብር፡ውስተ፡ምድረ፡ጼው፡ወበድወ፡
ዘአልቦ፡ዘይነብሮ፤
ሰው፡በማይኖርበት፡በምድረ፡በዳ፡
በበረኃ፡ወድቆ፡እንደሚኖር፡እንደ
ዶቅማ፡እንደ፡አሐያ፡ይሆናል፤ይህ፡
ጽላሎት፡ነው፤አንድም፡ወይከውን፡
ከመ፡ኳሂላ፡በውስተ፡ገዳም፡እንዲህ፡
ያለው፤ሰው፡በወንዝ፡ዳር፡ወድቆ፡እን
ደሚኖር፡እንደ፡አሐያ፡እንደ፡ዶቅማ፡
ይሆናል፤ሐተታ፡ያ፡በወንዝ፡ዳር፡
የወደቀ፡አሐያ፡ዶቅማ፡በላዩ፡ሰው፡
በውስጡ ፡ ውሀ ፡ እንዲሄድበት ፡
እሱንም፡በውስጥ፡በአፍአ፡መከራ፡
ያገኘዋል፤
ወኢይሬኢ፡ሠናየ፡ሶበ፡ይመጽእ፤
ለበጎዎች ፡ እስራኤል ፡ ተድላ ፡
ደስታቸው ፡ በተደረገላቸው ፡ ጊዜ ፡
አለ፤እንደነአቤሜሌክ፡ላሉ፡ለነሱ፡
የተደረገላቸውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
አያይም፤
ወይነብር ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ጼው ፡
ወበድወ፡ዘአልቦ፡ዘይነብሮ፤
ከአቤሜሌክና ፡ ከባሮክ ፡ ወገኖች ፡
አንዱም፡አንዱ፡በማይኖርበት፡በባቢ
ሎንም፡ይኖራል፤
አንድም ፡ ወይከውን ፡ ከመ ፡ ኳሂላ ፡
በውስተ፡ገዳም፤
አካላዊ፡ቃል፡ባልተዋሐደው፡ዘርዓ፡
ዳዊት፡የሚያምን፡ሰው፡ያን፡ጊዜ፡
በውሀ ፡ ዳር ፡ ወድቆ ፡ እንደሚኖር ፡
እንደ፡ዶቅማ፡እንደ፡አሐያ፡ይሆናል፤
ያ ፡ በላይ ፡ ሰው ፤ በውስጥ ፡ ውሀ ፡
ሲሄድበት ፡ እንዲኖር ፡ እሱም ፡
በመንጸፈ፡ደይን፡ወድቆ፡በእግረ፡
አጋንንት፡ተጠቅጥቆ፡ይኖራል፤
ወኢይሬኢ፡ሠናየ፡ሶበ፡ይመጽእ፤
ኋላም ፡ ጌታ ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡
በግርማ፡መለኮት፡ተገልጦ፡በመጣ፡
ጊዜ፡መልክዐ፡ፍትሑን፡አያይም፤
ሑር፡እምኔየ፡ይባላል፤ወይነብር፡
ውስተ ፡ ምድረ ፡ ጼው ፡ ወበድወ ፡
ዘአልቦ፡ዘይነብሮ፤
ከጻድቃን፡አንዱም፡አንዱ፡በማይኖ
ርበት፡በገሃነምም፡ወድቆ፡ይኖራል፤

፯፤ ወቡሩክ፡ብእሲ፡ዘይትዌከል፡በእግዚ
አብሔር፤
ከእስራኤልም፡አንዱም፡አንዱ፡በእግ
ዚአብሔር፡የሚታመን፡ሰው፡ቡሩክ፡
ነው፤
ወእግዚአብሔር፡ተስፋሁ፡ይከውን፤
አለኝታውም፡እግዚአብሔር፡የሚሆ
ንለት፡ሰው፤አንድም፡እግዚአብሔር፡
አለኝታው ፡ የሚሆንለት ፡ ሰው ፡
ቡሩክ፡ነው፤

፰፤ ወይከውን ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡
ትክልት፡ኀበ፡ሙኀዘ፡ማይ፤
በፈሳሽ ፡ ውሀ ፡ አጠገብ ፡ እንደተተ
ከለች፡እንጨት፡ይሆናል፤አንድም፡
ወይከውን፡ከመ፡ዕፅ፡ይላል፤

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ዳር ፡ እንደ ፡ ተተከለች ፡ እንጨት ፡ ይሆናል፤

ወይጸንዕ፡ሥርዉ፤

ትክልት፡ካለ፡ሥርዋ፤ሥርውም፡ካለ፡ ትኩል ፤ ባለ ፡ በቀና ፡ ነበር ፤ እንዲህ ፡ ያለ፡ ልማደ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ መጽሐፍ፡ ምሥጢር ፡ እንጂ ፡ ዘይቤ ፡ አይጠነቅቅምና፡ሥሩ፡እንደሚጠና፤

ወኢይፈርህ፡ሶበ፡ይመጽእ፡ሐሩር፤

ድርቅ ፡ ዋዕይ ፤ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ማይፈራ፤

ወኢይከውን ፡ ንጉፈ ፡ ቈጽለ ፡ አዕጹቂሁ ፡ በዓመተ፡ዓባር፤

ድርቅም፡በታዘዘበት፡ወራት፡ቅጠሉ፡ እንደማይረግፍ፤

ኢይፈርህ፡ወኢያንቀለቅል፤

አንድም ፡ በዓመተ ፡ ዐባር ፡ ኢይፈርህ ፡ ድርቅ ፡ እንደማይፈራ ፡ ሥሩም ፡ እንደ ማይነዋወጥ፤

ወኢያነትግ፡ፈርየ፤

ማፍራቱን፡እንደማያቋርጥ፡እንጨት፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ ጽላሎት ፡ ነው ፤ አንድም፡ ወይከውን፡ከመ፡ዕፅ፡እንተ፡ ትክልት ፡ ይህ ፡ ከመ ፡ በባለቤት ፡ የገባ፡ ከመ ፡ ነው ፤ ዕፅ ፡ ሰውነት ፤ ሙኃዝ ፡ መጠበቅ፤ማይ፡ረድኤት፡ነው፤በዚያ፡ ወራት፡በእግዚአብሔር፡ያመነ፡ሰው፡ ሰውነቱ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብቆለት ፡ ይኖራል ፤ ወይጸንእ ፡ ሥርዉ፤አባትነቱም፡ጸንቶ፡ይኖራል፤

ወኢይፈርህ ፡ ሶበ ፡ ይመጽእ ፡ ሐሩር፤ በመምለክያን፡ጣዖት፡መከራ፡በመጣ ባቸውም ፡ ጊዜ ፡ ያንጊዜ ፡ መከራ ፡ ያገኘኛል ፡ ብሎ ፡ አይፈራም ፤ ወኢይ ከውን ፡ ንጉፈ ፡ ቈጽለ ፡ አዕጹቂሁ ፡ በዓመተ ፡ ዐባር ፡ በመምለክያን ፡ ጣዖት፤መከራ፡በታዘዘባቸው፡ወራት፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ልጅ ፡ ከብት ፡ አይጠፋ በትም ፤ ኢይፈርህ ፡ በዓመተ ፡ ዐባር ፡ ኢይፈርህ፡በመምለክያነ፡ጣዖት፤ መከራ ፡ በታዘዘባቸው ፡ ወራት ፡ እነሱን ፡ ያገኘ ፡ መከራ ፡ ያገኘኛል ፡ ብሎ ፡ አይፈራም ፤ ወኢያንቀለቅል፤ በመከራውም ፡ አይነዋወጥም ፤ ወኢያ ነትግ ፡ ፈርየ ፤ ልጁ ፡ ልጅ ፡ ሲወልድ፤ ልጁ፡ልጅ፡ሲተካ፡ይኖራል፤አያቋርጥ በትም፤አንድም፡ቡሩክ፡ብእሲ፡ዘይት ዌከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አካላዊ ፡ ቃል፡ በተዋሐደው ፡ ሥግው ፡ ቃል፡ የሚያምን፡ሰው፡ቡሩክ፡ነው፤

ወእግዚአብሔር፡ተስፋሁ፡ይከውን፤ አለኝታውም ፡ ሥግው ፡ ቃል ፤ አንድም፡ ሥግው ፡ ቃል፡ አለኝታው፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፤ ወይከውን፡ከመ፡ዕፅ፡እንተ፡ትክልት፡ ኅበ ፡ ሙኀዘ ፡ ማይ ፤ ዕፅ ፡ ሰውነት፡ ሙኃዝ ፡ መጠበቅ ፡ ማይ ፡ ልጅነት፡ ነው፤እንዲህ፡ያለው፡ሰው፡ሰውነቱ፡ በልጅነት ፡ ተጠብቆለት ፡ ይኖራል፤ ወይጸንዕ፡ሥርዉ፤

አባትነቱም ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤ ወኢይፈርህ ፡ ሶበ ፡ ይመጽእ ፡ ሐሩር ፤ መከራ፡ ነፍስ ፤ በኃጥአን ፡ በመጣባቸው፡ ጊዜ ፡ እኔንም፡ እንደነሱ ፡ መከራ ፡ ነፍስ፡ ያገኘኛል ፡ ብሎ ፡ አይፈራም ፤ ወኢይ ከውን ፡ ንጉፈ ፡ ቈጽለ፡ አዕፁቂሁ ፡ በዓመተ፡ዐባር፡መከራ፡ነፍስ፡በመና ፍቃን ፡ ቃል ፡ በመጣባቸውም ፡ ጊዜ ፡ አዕጹቂሁ፤እሱ፡ያስተማራቸው፡ደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ አይ ከዱም ፤ ቈጽል ፡ ያለው ፡ ሃይማኖት፡ ነው ፤ ወቆጽሎሙኒ ፡ ተነግፈ ፡ ብሎ ፡ በታችኛው ፡ ጉባዔ ፡ እንደተናገረው ፡ ከዚህም ፡ መልሶ ፡ ተናገረው ፤ ኢይፈ ርህ ፤ አንድም ፡ በዓመተ ፡ ዐባር ፡ ኢይፈርህ፡ይላል፤በመናፍቃን፡ቃል፡ መከራ ፡ በታዘዘበት ፡ ጊዜ ፡ እሳቱን ፡ ስለቱን፡ሞተ፡ሥጋውን፡አይፈራም፤ ወኢያንቀለቅል ፤ ከምግባር ፡ ከሃይማ ኖቱም፡አይነዋወጥም፤ወኢያነትግ፡ ፈርየ፡ተወስኮ፡ዘነሳሒያንም፡አያቋር ጥበትም፤እሙንቱሰ፡ይዌስኩ፡ሥነ፡ በዲበ፡ሥን፡እንዲል፤

፱፤ ዕሙቅ፡ልቡ፡እምኵሉ፡ሰብእ፤
እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ልቡናው ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፡ አለ ፤ በአእምሮ፡ነው፤

ወመኑ፡የአምሮ፤

ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ልቡናውን፡መርምሮ፡የሚያውቅለት፡ ማነው ፤ አንድም ፡ ዕሙቅ ፡ ልቡ ፤ እምኵሉ፡ሰብእ፡ይቤ፡ነቢይ፤

የእግዚአብሔር፡የባሕርይ፡ዕውቀቱ፡ ከሰው፡ሁሉ፡ዕውቀት፡ይልቅ፡ጥልቅ፡ ነው፤

ወመኑ፡የአምሮ፤

ከሰውስ፤ሁሉ፡አንዱም፡አንዱ፡የእግ ዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ዕውቀቱን ፡ መርምሮ፡የሚያውቅ፡ማነው?

፲፤ አነ፡እግዚአብሔር፡ዘእሬኢ፡ልበ፡
ወእፈትን፡ኵልያተ፡ከመ፡አሀበ፡ለለአሐዱ፡
በከመ፡ፍኖቱ፡ወበከመ፡ፍሬ፡ምግባሩ፤
እኔ፡እግዚአብሔር፡ግን፡ለሰው፡ሁሉ፡ ለእያንዳንዱ ፤ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ሥራው፡ ዋጋውን ፡ ልሰጠው ፡ ልቡ ፡ ያጤሰውን ፡ ኩላሊቱ፡ ያመላለሰውን ፡ መርምሬ፡የማውቅ፡እኔ፡ነኝ፡አለ፡እግ ዚአብሔር፤

፲፩፤ ነቀወት፡ቆቃህ፡ወአስተጋብአት፡
ዘኢወለደት፤
የቆቅ ፡ እናት ፡ ሌሊት ተነሥታ ፡ ጮኸች ፤ ያልወለደቻቸውንም ፡ ገላግ ልቱን፡ሰበሰበች፤

ዘይገብር፡ብዕሎ፡ዘእንበለ፡ጽድቅ፡የኀድጎ፡ በመንፈቀ፡መዋዕሊሁ፤

እንደዚህም፡ሁሉ፡ሰርቆ፡ቀምቶ፡ባለ ጸግነቱን ፡ ያጠራቀመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በዘመኑ፡እኩሌታ፡ይጠፋበታል፤

ወይከውን፡ዓብደ፡በደኀሪቱ፤

በፍጻሜ፡ዘመኑም፡ስንፍናው፡ይገለጥ በታል ፤ ሐተታ ፡ ይች ፡ የቆቅ ፡ እናት ፡ ልጆቿዋን ፡ አዳኞች ፤ አንድም ፡ ወጥመድ ፡ ገድሎባት ፡ ባገኘቻቸው ፡



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ትገዝ ፡
ብሎዋት ፡ ተነሥታ ፡ ትጮኻለች ፤
ባጠገቡዋ ፡ ያሉ ፡ ያልወለደቻቸው ፡
ገላግልቱ ፡ እናታቸው ፡ የጮኸች ፡
መስሏቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ወደሱዋ ፡
ይሄዳሉ ፤ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ መዓልትም ፡
አብረዋት ፡ ሲጭሩ ፡ ያረፍዳሉ ፤
በቀትር ፡ ጊዜያት ፡ ቀና ፡ ብለው ፡
አይተው ፡ ያልወለደቻቸው ፡ እናታ
ቸው፡ እንዳልሆነች ፡ አውቀው ፡
ጥለዋት ፡ ይሄዳሉ ፤ ሰርቆ ፡ ቀምቶ ፡ ባለጸ
ግነቱንም ፡ ያጠራቀመ ፡ ሰው ፡
ሳይበላው ፡ ሳይጠጣው ፡ ሲጠብቅ ፡
ኑሮ፡ በእኩሌታ ፡ ዘመኑ ፡ ይጠፋበ
ታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አንድም ፡ ቆቃህ ፡
ነቂወ ፡ ይነቁ ፡ ወያስተጋብእ ፡
ዘኢወለደ ፡ ይላል ፣ የቆቅ ፡ አውራ ፡
ልጆቹን ፡ አዳኞች ፤ አንድም ፡ ወጥመድ
አጥፍቶበት ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ትገዝ ፡
ብለውት ፡ ተነሥቶ ፡ ይጮኻል ፤ ያን ፡
ጊዜ ፡ ባጠገቡ ፡ ያሉ ፡ ያልወለዳቸው ፡
ገላግልቱ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደሱ ፡
ይሄዳሉ ፤ እነሱም ፡ አባታቸው ፡
መስሏቸው ፡ አብረውት ፡ ሲጭሩ ፡
ያረፍዳሉ ፤ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብለው ፡
አይተው ፡ አባታቸው ፡ እንዳይደለ ፡
አውቀው ፡ ጥለውት ፡ ይሄዳሉ ፤
ይኸውም ፡ ምሳሌ ፡ ነው፤ የቆቅ ፡
አውራ ፡ የዲያብሎስ ፣ ሌሊት ፡ የዘመነ ፡
ኦሪት ፣ ገላግልቱ ፡ የምዕመናን ፣ ሌሊት ፡
ተነሥቶ ፡ እንደመጮህ ፣ ዲያብሎስም ፣
አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ባልፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡
ኃጢአት ፡ ሲያሠራ ፡ ጣዖት ፡ ሲያስ
መልክ ፡ ኑሯል ፤ ገላግልቱ ፡ የምዕ
መናን፡ ምሳሌ ፡ አብረውት ፡ ሲጭሩ ፡
እንደማርፈድ ፡ ምዕመናንም ፡ አምስት
ሺ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡
ዲያብሎስ ፡ አባታችን ፣ ገሃነም ፡
ርስታችን ፣ ብለው ፡ ኑረዋል ፤ ቀትር ፡
የዘመነ ፡ ወንጌል ፡ ምሳሌ ፣ በቀትር ፡
ጊዜያት ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አይተው ፡
አባታቸው ፡ እንዳይደለ ፡ አውቀው ፡
ጥለውት ፡ እንደመሄድ ፣ ምዕመናንም ፡
በዘመነ ፡ ወንጌል ፡ ዲያብሎስ ፡ ፈጣሪ
ያቸው ፡ እንዳይደለ ፡ አውቀው ፡ እሱን ፡
ክደው ፡ እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ርስታችን ፡
ብለው ፡ ጥለውት ፡ የመሄዳቸው ፡
ምሳሌ፡ ነው ፤ ዘይገብር ፡ ብዕሎ ፡
ዘእንበለ ፡ ጽድቅ ፡ የኀድጎ ፡ በመንፈቀ ፡
መዋዕሊሁ ፣ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡
ሰርቆ ፡ ቀምቶ ፡ በሐሰት ፡ ባለጸግነቱን ፡
ያጠራቀመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲጠብቅ ፡
ኑሮ ፡ ሳይበላለት፡ በዘመኑ ፡ እኩሌታ ፡
ይጠፋበታል ፤ ወይከውን ፡ ዐብደ ፡
በደኀሪቱ፤

በፍጻሜ ፡ ዘመኑም ፡ ስንፍናው ፡ ይገለጥ
በታል ፤ ለካ ፡ እገሌ ፡ ያጠራቀመው ፡ ባለ
ፀግነቱ ፡ ሰርቆ ፡ ቀምቶ ፡ ነው ፤ ዛሬም ፡
ሳይበላው ፡ ሳይጠጣው ፡ መሞቱ ፡
በዚያ፡ ፍዳ ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ ይህ ፡
የምሳሌ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ያ ፡
የቆቅ ፡ አውራ ፡ ልጆቹን ፡ ባጣቸው ፡
ጊዜ ፡ ሌሊት ፡ ተነሥቶ ፡ ጩሆ ፡ ያል
ለዳቸው ፡ ልጆች ፡ ተሰብስበው ፡
አብረው ፡ ሲጭሩ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡
ጊዜያት ፡ እንዳረፈዱ ፣ ኋላም ፡ በቀትር ፡
ጊዜያት ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ አይተው ፡
አባታቸው ፡ እንዳይደለ ፡ አውቀው ፡
ጥለውት ፡ እንደሄዱ ፤ ዘይገብር ፡ ብዕሎ ፡
ዘእንበለ ፡ ጽድቅ ፡ የኀድጎ ፡ በመንፈቀ ፡
መዋዕሊሁ ፡ ዲያብሎስም ፡ ወገኖቹ ፡
አጋንንትን ፡ በኃጢአት ፡ በክህደት ፡
ባጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ባልፈጠረው ፡ ፍጥ
ረት ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ኃጢአት ፡ ሲያሠራ ፡ ጣዖት ፡
ሲያስመልክ ፡ የኖረ ፡ የዲያብሎስ ፡
ብዕለ ፡ ነፍሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ያ ፡
የቆቅ ፡ አውራ ፡ የሰበሰባቸውን ፡
ገላግልት ፡ በቀትር ፡ ጊዜያት፡ እንዳ
ጣቸው ፡ ዲያብሎስም ፡ በአምስት ፡
ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን፡ ተቆራኝ
ቷቸው ፡ የነበሩ ፡ ነፍሳትን ፡ አጥቷ
ቸዋል ፤ ወይከውን ፡ ዓብደ ፣ በደኃሪቱ ፣
በፍጻሜ ፡ ዘመኑ ፡ የዲያብሎስ ፡
ስንፍናው ፡ ይገለጥበታል ፡ አለ ፤ አሁን ፡
የተመቸ ፤

፲፪፣ መንበረ ፡ ክብር ፣
የክብር ፡ መገኛ ፤ አንድም ፡ መንበረ ፡
ስብሐት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሌላው ፡ ሁሉ
ፍጡር ፡ ቢመሰገን ፡ ጌታ ፡ ቢሆን ፡
ከፈጣሪው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባገኘው ፡
ነውና ፤

ልዑል ፡ እምልዑላን ፣
ከልዑላን ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ ልዑል ፡
አለው ፡

መካነ ፡ መቅደስነ ፣
የምስጋናችን ፡ ዓለም ፡ አለው ፤

፲፫፣ ተስፋሁ ፡ ለእስራኤል ፡ እግዚእ ፣
የእስራኤል ፡ አለኝታው ፡ አቤቱ ፡ ብሎ ፡
ይሰማዋል ፣

ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኃደጉከ ፡ ተኀፍሩ ፣
በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ አንተን ፡ የተዉ ፡
ሁሉ ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ መጥቶባቸው ፡
አፈሩ ፤

ወተገሥጹ ፡ ዐላውያን ፡ ውስተ ፡ ምድር ፣
አንተንም ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡
የወነጀሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በባቢሎን ፡
መከራ ፡ ተቀበሉ ፤

ወተጽሕፉ ፡ እለ ፡ ኃደግዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ነቀዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፣
የሕይወት ፡ መገኛ ፡ የሚሆን ፡ ፈጣሪ
ያቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአ
ምልኮት ፡ የተዉ ፡ ሰዎች ፡ ለጥፋት ፡
የተቆጠሩ ፤ አንድም ፡ እስመ ፡ ኃደግዎ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ነቅዐ ፡ ማየ ፡
ሕይወት፣ ይላል ፤ የሕይወት ፡ መገኛ ፡
የሚሆን ፡ ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ በሕግ፡ በአምልኮት ፡ ትተው
ታልና ፡ ለጥፋት፡ ተቈጠሩ ፤ አንድም ፡
ተስፋሁ ፡ ለእስራኤል ፡ እግዚእ ፡ የእስ
ራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ አለኝታው ፡ አቤቱ ፤
ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኀደጉከ ፡ ተሐፍሩ ፣
በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ የተዉህ ፡
መናፍቃን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ነፍስ ፡ መጥ
ቶባቸው ፡ አፈሩ ፤ ወተገሥጹ ፡
ዐላውያን ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ በምግባር ፣
በሃይማኖት ፡ የሚወነጅሉህ ፡ መናፍ
ቃንም ፡ ሁሉ ፡ በገሃነም ፡ ሁነው ፡
በመከራ ፡ ነፍስ ፡ ተገሥጹ ፤
ወተጽሕፉ ፡ እለ ፡ ኀደግዎ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ነቅዓ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፣
የልጅነት ፡ መገኛ ፡ የሚሆን ፡ ፈጣሪ



www.ethiopianorthodox.org

ያቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በምግባር ፡
በሃይማኖት ፡ የተዉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፤
አንድም ፡ እስመ ፡ ሐደግዎ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ነቅዓ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ይላል ፡
የልጅነት ፡ መገኛ ፡ የሚሆን ፡ ፈጣሪ
ያቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በምግባር ፡
በሃይማኖት ፡ ትተውታልና ፡ ለጥፋት ፡
ተቈጠሩ።

፲፬፤ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡
አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡
ወአሕይወኒ ፡ ወአድኅነኒ ፤
ፈጽመህ ፡ አድነኝ ፤
ወእድኅን
እኔም ፡ በቸርነትህ ፡ ከመከራው ፡ ልዳን ፤
እስመ ፡ አንተ ፡ ምክህየ ፤
መመኪያዬ ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ አንተ ፡
ስለሆንክ ፤

፲፭፤ ናሁ ፡ ይብሉኒ ፡ እሙንቱ ፡ አይ
ቴኑመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፤
ትንቢቱን ፡ ተናግሬው ፡ ትምህርቱን ፡
አስተምሬው ፡ ሳይደረግ ፡ ቢቀር ፡
እስራኤል ፡ ያ ፤ የተናገርከው ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ቃሉ ፡ የት ፡ ነው?
እስኩኬ ፡ ለይምጻእ ፡
እስቲ ፡ ይምጣ ፡ ይደረግ ፡ ይሉኛል ፡

፲፮፤ አንሰ ፡ ኢደከምኩ ፡ እንዘ ፡ እተሉ ፡
ድኅሬከ ፡
እኔስ ፡ አንተን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡
ስከተል ፡ አልደከምኩም ፡ አለ ፤ ለማስ
ተማር ፡ ስወጣ ፡ ስወርድ ፤
ወኢያፍተወኒ ፡ መዋዕለ ፡ ሰብእ ፤
የሰዎች ፡ የዘመናቸው ፡ ማጠሩም ፡ ደስ ፡
አላሰኘኝም ፤ አንድም ፡ ሰዎች ፡ የሚጠ
ፉበት ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ አላሰኘኝም ፡ አለ ፤
ተደርጎ ፡ ልየው ፡ አልልም ፤
ለሊከ ፡ ተአምር ፡ ዘይወጽእ ፡ እምከናፍርየ ፡
አቤቱ ፡ አንተስ ፡ ከነሱ ፡ ሌላ ፡ ነህ ፡
ትለኝ ፡ እንደሆን ፡ እኔ ፡ ከልቡናዬ ፡
አንቅቼ ፡ ከአንደበቴ ፡ አውጥቼ ፡ የምና
ገረውን ፡ ትንቢት ፡ የማስተምረውን ፡
ትምህርት ፡ አንተው ፡ ቅሉ ፡ ታውቀ
ዋለህ ፡
ቅድመ ፡ ገጽከ ፡ ውእቱ ፤
ይኸውም ፡ በፊትህ ፡ ነው ፡ አለ ፤ በፊት ፡
ያለ ፡ እንዳይሠወር ፡ አይሠወርህም ፡
ሲል ፡ ነው ፤

፲፯፤ ወኢይኩነኒ ፡ ሊተ ፡ ለተናክሮ ፤
ይኸውም ፡ ላለ ፡ ይበሉኝታ ፡ (ለውዳሴ ፡
ከንቱ) ፡ አይሁንብኝ ፤ አንድም ፡
ለመደነቅ ፡ አይሁንብኝ ፤ ይኸን ፡
ባለው ፡ ለተናግሮ ፡ የሚል ፡ አብነት ፡
ይገኛል ፡ እንደዚሁ ፡ ያስተረጕማል ፤
ምስካይየ ፡ አንተ ፡ እምዕለ ፡ እኪት ፡
መከራ ፡ ከታዘዘበት ፡ ቀን ፡ የምታ
ድነኝ ፡ አምባ ፡ መጠጊያዬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤

፲፰፤ ለይትኀፈሩ ፡ እለ ፡ ይሰድዱኒ ፡
የገለጥክልኝን ፡ ትንቢት ፡ ከመናገር ፤
ያዘዝከኝን ፡ ትምህርት ፡ ከማስተማር ፡
አስወጥተው ፡ የሚሰዱኝ ፡ እስራኤል ፡
ይፈሩ ፤ ይጐስቍሉ ፤
ወአንሰ ፡ ኢይትኃፈር ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሐር ፡ ብዬ ፡
ያንተን ፡ ስም ፡ የማስተምር ፡ እኔ ፡ ግን
መከራ ፡ መጥቶብኝ ፡ አልፈር ፤
አንድም ፡ ኀደጉ ፡ ቤትየ ፡ ወኃደጉ ፡
ርስትየ ፤ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ውጣ ፡ ከቤት ፤
ተነቀል ፡ ከመሬት ፡ ብለው ፡ አስወ
ጥተው ፡ የሚሰዱኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ ይፈሩ ፤
ይጎስቍሉ ፤ ወአንሰ ፡ ኢይትኀፈር ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤ ብዬ ፡ ስላ
ስተማርኩ ፡ ባንተ ፡ ስም ፡ አስወጥተው ፤
የሚሰዱኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አልፈር ፤



ለይደንግፁ ፡ እሙንቱ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይደንግፅ ፡
እነሱ ፡ ይደንግጡ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አልደ
ንግጥ ፡ አለ ፤
ለይትኃፈሩ ፡ ያለውን ፡ ለይደንግፁ ፡ ኢይ
ትኃፈር ፡ ያለውን ፡ ኢይደንግፅ ፡ ብሎ ፡
ገለጠው ፡ አንድም ፡ አብነት ፡ ይትኃፈሩ ፡
እለ ፡ ይሰድዱኒ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይትኃፈር ፡
ይላል ፤ ገና ፡ ወደፊት ፡ ውጣ ፡ ከቤት ፡
ተነቀል ፡ ከመሬት ፡ ብለው ፡ አስወ
ጥተው ፡ የሰደዱኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ እስራኤል ፡
መከራ ፡ መጥቶባቸው ፡ ያፍራሉ ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዬ ፡ ያስ
ተማርኩ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አላፍርም ፡
ይደነግፁ ፡ እሙንቱ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይደ
ነግፅ ፤ ይትኃፈሩ ፡ ያለውን ፡ ይደነግፁ ፤
ኢይትኃፈር ፡ ያለውን ፡ ኢይደነግፅ ፡
ብሎ ፡ ገለጠው ፤ ይህ ፤ ነቢይ ፡ ነውና ፡
ወደፊት ፡ የሚመጣባቸው ፡ መከራ
ቸውን ፡ ተናገረ ፤
አምጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዕለተ ፡ እኪተ ፤
መከራ ፡ የታዘዘባትን ፡ ቀን ፡ በነሱ ፡ አም
ጣባቸው ፤
በምክዕቢተ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ቀጥቅጦሙ ፡
አቤቱ ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ መከራ ፡
አምጥተህ ፤ አንድም ፡ በምክዕቢተ ፡
ቅጥቃጤ ፡ ቀጥቅጦሙ ፡ በዕጽፍ ፡
ድርብ ፡ መከራ ፡ አጥፋቸው ፡

፲፱፤ ከመዝ ፡ ይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡
እንዲህ ፡ አለኝ ፤
ሑር ፡ ወቁም ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ደቂቀ ፡ ሕዝብከ ፤
በወገኖችህ ፡ ልጆች ፡ በሮች ፤ ሒደህ ፡
ቁም ፡ አለኝ ፤
እንተ ፡ ኀበ ፡ ይበውዑ ፡ ኵሉ ፡ ነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡
ወእንተ ፡ ኀበ ፡ ይወጽኡ ፡ እምውስቴቶሙ ፤
የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በሚወጡ
ባቸው ፡ በሚገቡባቸው ፡ በሮች ፡ ሄደህ ፡
ቁም ፡ አለኝ ፤
ወበውስተ ፡ ኵሉ ፡ አናቅጸ ፡ ኢየሩሳሌም ፤
በኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ ከነዚያ ፡
ባንዱም ፡ ባንዱ ፤

፳፤ ወበሎሙ ፡ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡ ወኵሉ ፡ እለ ፡
ትነብሩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወእለ ፡ ትበውዑ ፡
ውስተ ፡ ዛ ፡ አንቀጽ ፤
ከዚያም ፡ ሄደህ ፡ ቁመህ ፡ በዚች ፡ በኢየ
ሩሳሌም ፡ በር ፡ ስትወጡ ፡ ስትገቡ ፡
የምትኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉና ፡ የይሁዳ ፡
ነገሥታት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ፡ በላቸው ፤ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡ ያመጣል ፤

፳፩፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዕቀቡ ፡ ነፍሰክሙ ፤
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ልቡና
ችሁን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፤ አንድም ፡ ሰውነ
ታችሁን ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ጠብቁ ፡ አለ ፡
እግዚአብሔር ፤ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤
ወኢታንሥኡ ፡ ምንተኒ ፡ ፆረ ፡ ክቡደ ፡ በዕለተ ፡
ሰንበት ፡ ወኢታብዑ ፡ እንተ ፡ አንቀጸ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፤
ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ሸክም ፡ አንሥ
ታችሁ ፡ ተሸክማችሁ ፡ ወደኢየሩ
ሳሌም ፡ በር ፡ አታግቡ ፤

፳፪፤ ወኢታውጽኡ ፡ ፆረ ፡ እምአብያ
ቲክሙ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበታት ፤
ቀዳም ፡ ቀዳም ፡ ቀን ፡ ከቤታችሁም ፡
ታላቅ ፡ ሸክም ፡ አታውጡ ፤
ወኵሎ ፡ ግብረ ፡ ኢትግበሩ ፤
ምንም ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ አትሥሩባት ፤
ወቀድሱ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበታት ፤
ቀዳም ፡ ቀዳምንም ፡ በሳምንት ፡
በሳምንት ፡ አክብሩ ፤
በከመ ፡ አዘዝክዎሙ ፡ ለአበዊክሙ ፤
ቀድሞ ፡ አባቶቻችሁን ፡ አክብሩ ፡ ብዬ ፡
እንዳዘዝኳቸው ፤

፳፫፤ ወኢሰምዑኒ ፡ ወኢያጽምዑኒ ፡ በዕዘ
ኒሆሙ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እነሱ፡በጆሮቻቸው፡ፈጽመው፡እንዳል
ሰሙኝ፤አንድም፡በዕዝነ፡ልቡናቸው፡
ሰምተው፡እንዳላወቁልኝ፤

ወአግዘፉ፡ክሣዶሙ፡ከመ፡ኢይስምዑኒ፡
ያዘዝኋቸውን፡እንዳይሰሙኝ፡ክሣደ፡
ልቡናቸውንም፡እንዳደነደኑ፤

ወአበዩ፡ተግሣጽየ፡
ምክር ፡ እዝናቴንም ፡ እምቢ ፡
አንሰማም ፤ አንቀበልም ፡ ብለው ፡
እምቢ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ፡ አባቶቻ
ችሁም፡አትሁኑ፤

፳፬፤ ወይእዜኒ፡እመ፡ሰሚዐ፡ሰማዕክሙ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እናንተ፡ግን፡እኔ፡በነቢያት፡አድሬ፡
ያስተማርኋችሁን፡እኔ፡ራሴ፡ያዘዝኋ
ችሁን፡ቃል፡ብትሰሙኝ፤

ወኢያባዕክሙ፡ፆረ፡እንተ፡ኖኃቲሃ፡ለዛ፡
ሀገር፡በዕለተ፡ሰንበት፤
ቅዳሜም፡ቀን፡ሸክም፡ተሸክማችሁ፡
ወደኢየሩሳሌም፡በሮች፡ባታገቡ፤

ወቀደስክሙ፡ዕለተ፡ሰንበት፤
ቅዳሜ፡ቅዳሜንም፡ብታከብሩ፤

ወኢገበርክሙ፡ኵሎ፡ግብረ፤
ሥራችሁንም፡ሁሉ፡ባትሠሩባት፤

፳፭፤ ይበውዑ ፡ እንተ ፡ አናቅጺሃ ፡ ለዛ ፡
ሀገር፡ ነገሥት ፡ ወመላእክት ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስተ፡መንበረ፡ዳዊት፤
እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡መንበረ፡ዳዊት፡
ያለውን፡ነገሥት፡ላለው፡ይቅጽኋል፤
በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የተቀመጡ ፡ ነገሥ
ታቱና ፡ አለቆች ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በሮች፡ ሲወጡ ፡ ሲገቡ፡ ይኖራሉ ፤

አንድም፡ወይነብሩ፡ውስተ፡መንበረ፡
ዳዊት ፡ ይላል ፤ ነገሥታቱ ፡ በዳዊት፡
ዙፋን፡ነግሠው፡ይኖራሉ፤

ወይጼዓኑ ፡ ውስተ ፡ ሠረገላ ፡ ወአፍራስ፡
እሙንቱ፡ወመላእክቲሆሙኒ፡ሰብአ፡ይሁዳ፡
ወእለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ በሚወ
ጡበት ፡ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ነገሥ
ታቱና ፡ አለቆች ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎችና፡
በኢየሩሳሌም፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡
በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡
ይመጣሉ፤

ወትነብር፡ዛ፡ሀገር፡ለዓለም፤
ይችም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ጠላት ፡ ጠፍ
ቶላት፡ለዘላለሙ፡በተድላ፡በደስታ፡
ትኖራለች፤

፳፮፤ ወይመጽኡ ፡ እምአህጉረ ፡ ይሁዳ፡
ወእምአድያመ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወእም
ብሔረ፡ብንያም፤
ከይሁዳ፡አገሮች፡ተውጣጥተው፡ከኢ
የሩሳሌም ፡ አውራጃዎች ፡ ተውጣ
ጥተው ፡ ከብንያምም ፡ አገር ፡ ተውጣ
ጥተው፡

ወእምአህቃላት፤
ከየምድረ፡በዳውም፡ተውጣጥተው፤

ወእምአድባር፤
ከየተራራው፤

ወእመንገለ፡ሰሜን፤
ከባቢሎንም፡ተውጣጥተው፡ይመጣሉ
ወያመጽኡ፡መሥዋዕተ፡ወቍርባነ፡
ሲመጡም፡መሥዋዕቱንና፡ቍርባኑ



ወመሐና፡
እጅ፡መንሻውን፤

ወስሒነ፤
ነጭ፡ዕጣኑን፡ይዘው፡ይመጣሉ፤

ወያመጽኡ ፡ አኰቴተ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
መጥተውም ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
የሚገባትን ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ፤
ለቤተ፡እግዚአብሔር፡የሚገባት፡የማ
ይገባት፡ምስጋና፡አለና፤

፳፯፤ወእመ፡ኢሰማዕክሙኒ፡
በነቢያት፡አድሬ፡ያስተማርኋችሁን፡
በቃሌ፡የነገርኋችሁን፡ባትሰሙኝ፤

ወኢቀደስክሙ፡ዕለተ፡ሰንበት፤
ቅዳሜንም፡ባታከብሩ፤አንድም፡ካላከ
በራችሁ፤

ወአባዕክሙ፡ፆረ፡እንተ፡አናቅጺሃ፡ለኢየሩ
ሳሌም፡በዕለተ፡ሰንበት፤
ቅዳሜም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
በሮች ፡ ሸክም ፡ ተሸክማችሁ ፡
ካገባችሁ፡ግን፤

አነድድ፡እሳተ፡ላዕለ፡ኖኃቲሃ፤
በበሮቿ ፡ እሳት ፡ አነድዳለሁ ፡ አለ ፤
በቁሙ ፡ ትቃጠላለች ፡ ሲል ፡ ነው ፤
አንድም ፡ እሳት ፡ ያለው ፡ ጦር ፡
መቅሠፍት ፡ ነው ፤ ኖኃቲሃ ፡ ያለው ፡
ኃያላን ፡ ናቸው ፤ በኃያላኖችዋ ፡ ጦር፡
መቅሠፍት፡አመጣለሁ፤

ወትበልዕ፡መሠረታቲሃ፡ለኢየሩሳሌም፤
ጦር ፡ መቅሠፍቲቱም ፡ የኢየሩሳ
ሌምን፡ሥር፡መሠረቷን፡ታጠፋለች፤

ወትጠፍዕ፤
ኢየሩሳሌምም፡እልም፡ድርግም፡ብላ፡
ትጠፋለች፤አንድም፡ወትበልዕ፡መሠ
ረታቲሃ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍቲቱ ፡
የኢየሩሳሌምን ፡ ሥር ፡ መሠረቷን ፡
ታጠፋለች፤

ወኢትጠፍዕ፤
አገሪቱ፡ትጠፋለች፡እንጂ፡ጦር፡መቅ
ሠፍቲቱ ፡ አትጠፋም ፤ ስታጠፋ ፡
ትኖራለች።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፤

፩፤ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀበ፡ኤርምያስ፤
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ወደ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡
ይህ፡ነው፤

፪፤ ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ ወረድ ፡ ቤተ፡
ለብሐዊ፤
ተነሥተህ ፡ ወደሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ቤት ፡
ውረድ፡አለው፤ቃል፡ዘኮነ፡ያለውን፡
አመጣ፤

ወበህየ፡አሰምዐከ፡ነገርየ፤
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ነገሬን ፡ አሰማሃለሁ ፡
አለው፤

፫፤ ወወረድኩ ፡ ቤተ ፡ ለብሐዊ ፡ ወረከ
ብክዎ፡ይገብር፡ግብሮ፡ላዕለ፡ኵኵሕ፤
ወደ፡ሸክላ፡ሠሪ፡ቤት፡ሰው፡ወርጄ፡
ሸክላ ፡ ሠሪውን ፡ በንጥፍ ፡ ደንጊያ ፡
ላይ፡ ተቀምጦ ፡ ሲሠራ ፡ አገኘሁት ፤
አንድም፡ሥራውን፡በንጥፍ፡ድንጊያ፡
ላይ፡ሲሠራ፡አገኘሁት፤

፬፤ወወድቀ፡እምእዴሁ፡ፃሕብ፡ዘይገብር፡
በዕቡር፡ዘዕቡር፤
ያንጊዜ ፡ በጭቃነት ፡ የሚሠራው ፡
ሸክላ ፡ ከእጁ ፡ ወደቀ ፤ አንድም ፡
ይገብር፡ ዘዕቡር ፡ ይላል ፤ የጭቃው ፡
ሥራ፡ከእጁ፡ወደቀ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወነሥአ ፡ ዳግመ ፡ ወገብሮ ፡ ፃሕበ ፡ ካልአ ፡
ዘከመ፡አደሞ፡በአዕይንቲሁ፡ገብሮ፤
ዳግመኛ ፡ እንሥቶ ፡ ለዓይኑ ፡ እንደወ
ደደው ፡ በዓይኑ ፡ እንደወደደው ፡
አድርጎ፡ሌላ፡ሥራ፡አድርጎ፡ሠራው፤

፭፤ወነበበኒ፡እግዚአብሔር፡ወይቤለኒ፡
ያንጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረኝ ፤
እንዲህ፡አለኝ፤

፮፤ ከመዝ ፡ ጥቀ ፡ መባሕት ፡ ለለብሐዊ፡
ኢይክልኑ፡አነ፡ገቢረ፡በቤተ፡፳ኤል፤
ለሸክላ ፡ ሠሪው ፡ በሸክላ ፡ ሥራው ፡
ላይ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡
የተሰጠው፡ለኔስ፡በቤተ፡እስራኤል፡
የወደድኩትን ፡ ባደርግ ፡ ሥልጣን ፡
የለኝምን ፤ አንድም ፡ ከመዝ ፡ ጥቀ ፡
ለለብሐዊ ፡ ይትከሀሎ ፤ ኢይክልኑ ፡
አነ፡ገቢረ፡በቤተ፡እስራኤል፡ይላል፤
ለሸክላ፡ሠሪ፡በሸክላ፡ሥራው፡ላይ፡
የወደደውን ፡ ማድረግ ፡ የተቻለው ፡
ከተቻለው፡እኔማ፡በእስራኤል፡ላይ፡
የወደድኩትን ፡ ማድረግ ፡ እንደምን ፡
አይቻለኝ ፤ አስማርኬ ፡ ማስመለስ ፡
አሳዝኜ ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ይቻለኛል ፡
እንጂ፤
ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ከመዝ፡ዕቡረ፡ለብሐዊ፡ከማሁ፡አንትሙሂ፡
ውስተ፡እዴየ፡ቤተ፡እስራኤል፡ዝንቱ፤
በሸክላ፡ሠሪ፡እጅ፡ያለ፡ጭቃ፡ሸክላ፡
ሠሪው፡የወደደውን፡እንዲያደርገው፡
ቤተ ፡ እስራኤል ፡ በሥልጣኔ ፡ የተያ
ዛችሁ፡እናንተም፡እንደዚያ፡ናችሁ፤
ያ፡የወደደውን፡እንዲያደርገው፡የወደ
ድኩትን፡አደርጋችኋለሁ፡ሲል፡ነው፤

፯፤ሕሉቀ፡ምዕረ፡እነግር፡ላዕለ፡ሕዝብ፡
ወላዕለ፡ነገሥት፡ከመ፡እንሥቶሙ፡ወእጥ
ፍዖሙ፡ወእደምስሶሙ፤
አስማርኬ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡
በሕዝቡና፡በነገሥታቱ፡አንድ፡ጊዜ፡
ቆርጬ፡ተናግሬባቸዋለሁ፤

፰፤ወእመሰ፡ተመይጡ፡እሙንቱ፡ሕዝብ፡
እምኵሉ፡እከዮሙ፡ዘነበብኩ፡ላዕሌሆሙ፤
እኔን፡በደሉኝ፡አሳዘኑኝ፡ብዬ፡ከተናገ
ርኩበት፡ከክፉታቸው፡ሁሉ፡እኒህ፡
ወገኖች፡ከተመለሱ፤
ወእኔስሕ ፡ በእንተ ፡ እኩይ ፡ ዘነበብኩ ፡
ወመከርኩ፡እግበር፡ላዕሌሆሙ፤
እኔም፡በነሱ፡ላይ፡አደርገዋለሁ፡ብዬ፡
ከመርኩት ፡ ከተናገርኩት ፡ ከክፉው፡
ነገር፡እመለስላቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤

፱፤ምዕረ፡እነብብ፡ላዕለ፡ሕዝብ፡ወላዕለ፡
ነገሥት፡በዘይትሐነፀ፡ወይትከሉ፤
እኔስ፡ለወገኖቼ፡ለእስራኤል፡ለነገሥ
ታቱም፡በረድዔቱ፡በሚታነፁና፡በሀ
ገራቸው፡ጸንተው፡በሚኖሩ፡ገንዘብ፡
ሚጠትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እናገርላቸ
ዋለሁ፤

፲፤ወገብሩ፡እኩየ፡ላዕሌየ፤
እነሱ፡ግን፡እምቢ፡ብለው፡በኔ፡ክፉ
ሥራ፡ሠሩ፤
ወኢሰምዑኒ፡ቃልየ፤
ያዘዝኳቸውን ፡ ቃሌን ፤ ያስተማርኳ
ቸውን፡ትምህርቴንም፡አልሰሙም፤
ወነሳሕኩ፡በእንተ፡ኵሉ፡ሠናይ፡ዘመከርኩ፡
እግበር፡ላዕሌሆሙ፤



ከኃጢአታቸው ፡ ባይመለሱ ፡ ከክፉ
ታቸው፡ባይታገሡ፡እኔም፡ለነሱ፡አደ
ርገዋለሁ ፡ ብዬ ፡ ስለመከርኩት ፡
ስለበጎው ፡ ነገር ፡ አዘንሁ ፡ አንድም ፤
ዘመሀርኩ፡እግበር፡ላዕሌሆሙ፡ይላል፤
ለነሱ ፡ ላደርግላቸው፡ በነቢያት ፡
አድሬ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ብዬ፡ያስተማርኩላቸውን፡የበጎውን፡
ነገር፡ሳላደርግላቸው፡ለቀረ፡አዘንሁ፤

፲፩፤ ወይእዜኒ ፡ በሉሙ ፡ ለሰብአ ፡ ይሁዳ፡
ወለእለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
አሁንም ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡
በላቸው፤
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤
ናሁ፡አነ፡እፈጥር፡እኩየ፡ላዕሌክሙ፤
እናንተ ፡ ከልቡናችሁ ፡ አንቅታችሁ ፡
በልቡናችሁ ፡ አስባችሁ ፡ ኃጢአት ፡
ሠርታችሁ ፤ እኔን ፡ ከበደላችሁኝስ ፡
እኔም ፡ ከልቤ ፡ አንቅቼ ፡ በልቡናዬ ፡
አስቤ፡በእናንተ፡ክፉ፡ነገር፡አመጣባ
ችኋለሁ፤
ወእመክር፡እኩየ፡ምክረ፡ዲቤክሙ፤
እናንተ ፡ እኔን ፡ ለማሳዘን ፡ እኔን ፡
ለመበደል ፡ ኃጢአት ፡ እንሥራ ፤
ጣዖት፡እናምልክ፡ብላችሁ፡በኔ፡እንደ
መከራችሁብኝ፡እኔም፡በናንተ፡ክፉ፡
ምክር፡ላመጣባችሁ፡እመክራለሁ፤
ተመየጡ ፡ ኵልክሙ ፡ እምፍኖትክሙ ፡
እኩይ፤
አሁንም ፡ ግዱን ፡ ከክፉ ፡ ሥራችሁ ፡
ተመለሱ፤
ወአሠንዩ፡ፍኖተክሙ፡ወምግባረክሙ፤
ፍጹም ፡ ክፉ ፡ ሥራችሁን ፡ ለውጣ
ችሁ፡በጎ፡ነገር፡አድርጉት፤አንድም፡
ፍጹም፡ በጎ ፡ ሥራችሁን ፡ ያማረ ፡
የተወደደ፡በጎ፡ነገር፡አድርጉት፡አለ፤
ከበጎነቱ ፡ እንዳይለወጥ ፡ አድርጉት ፡
ሲል፡ነው፤

፲፪፤ ወይቤሉ ፡ አጥባዕነ ፡ ንትሉ ፡ በዕል
ወትነ፤
እኔ፡እንዲህ፡አልኋቸው፤እነሱ፡ግን፡
ወንጀላችንን ፤ ልንከተል ፡ ወደን ፡
ጨክነናል፤ አይሆንም ፡ አሉኝ ፤
አንድም፡በክፉ፡ወንጀላችን፡ጸንተን፡
ጣዖቱን ፡ ልንከተል ፡ ጨክነናል፤
አይሆንም፡አሉኝ፤
ወንሐር፡ኵልነ፡
ለጣዖቱ፡በዓል፡ሁላችንም፡ልንሔድ፤
ወንግበር፡እኩየ፡ዘይሔውፃ፡ለልብነ፤
ሂደንም ፡ ለልቡናችን ፡ ደስ ፡ የሚያሰ
ኛትን ፡ ክፉውን ፡ ሥራ ፡ ነገር ፡ ሁሉ፡
ልንሠራ ፡ ጨክነናል ፤ አይሆንም ፡
አሉኝ፤

፲፫፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፤
የዚህንስ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤
ተሰአልዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ እመቦ ፡ ዘሰምዐ ፡
ዘከመዝ፡መደንግፀ፡ጥቀ፡ዘገብረት፡ድንግለ፡
እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ቆንጆ ፡ ያደረገችው ፡
እንዲህ፡ ያለ ፡ የሚያስደነግጠውን ፡
ሥራ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ አሕዛብ ፡
ሰምተውት ፡ ያውቁ፡ እንደሆነ ፡
አሕዛብን ፡ ጠይቋቸው ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ይነጽፍኑ፡ፈልፈል፡እምኰኵሕ፡ወአስሐትያ፡እምሊባኖስ፡

ካለት ፡ ድንጋይ ፡ ምንጫ ፡ ምንጩ ፤ ከደጋ ፡ ውርጫ ፡ ውርጩ ፡ ይጠፋልን ፤ አንድም ፡ ይነጽፍኑ ፡ እምኰኵህ ፡ አስሐትያ ፡ሊባኖስ ፡ ይላል ፤ የደጋ ፡ ውርጭ ፡ ካለት ፡ ደንጋይ ፡ ይጠፋልን ፡ እንደዚሁስ ፡ ሁሉ ፡ ከልቡናችሁ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይጠፋልን ፡ ይህን ፡ ባለው ፤ ወይትመየጥኑ ፡ ውኂዘ ፡ ማይ ፡ በኃያል ፡ ነፋስ፡ ይላል፤ምንስ ፡ ቢሆን ፡ ከላይ ፡ የወረደ ፡ ዝናም ፡ በኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይመለሳልን፤ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ምንስ ፡ ቢሆን ፡ ከናንት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ወደበጎ ፡ ነገር ፡ ይመለሳልን፤ አይሆንም ፤ አይመለስም፤

፲፭፤ እስመ ፡ ረስዑኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ወአጠኑ ፡ ለከንቱ፡፡

ምነዋ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ እኔን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ዘንግተውኛልና፤ ለከንቱ ፡ ጣዖትም ፡ ሂደው ፡ አጥነዋልና፡ ስለዚህ ፡ ነው፤

ወደክሙ ፡ በፍኖቶሙ ፡ ድካመ ፡ ዘለዓለም ፡ ለሐዊር ፡ ፍኖተ ፡ ጠዋየ ፡ ወመብዕሰ፡

ተማርከው ፡ ሲሄዱ ፡ በጠማማው ፡ በጐዳጉፅ ፡ ጎዳና ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፉን፡ ተሸክመው ፡ ለመሔድ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የዘላለም ፡ ድካምን ፡ ደከሙ፡ አለ ፤ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሲሡሩ ፡ ለጣዖቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ላሙን ፡ ሲያርዱ፡ ሥጋውን ፡ ሲያወራርዱ ፡ ሲያነጥፉ ፡ ሲጋርዱ ፡ ይደክማሉና ፤ አንድም ፡ ለሐዊር ፡ ፍኖተ ፡ ጠዋየ ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወመብዕሰ ፡ ክህደት፣ ይኸንን ፡ ለማድረግ ፡ የዘለዓለምን ፡ ድካም ፡ ደከሙ ፡ አለ፤ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ወደ ፡ ጣዖቱ ፡ ሲሄዱ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ቢክዱ ፡ ፈርዶ ፡ በሥጋቸው ፡ አሕዛብን ፡ አምጥቶ ፡ አስማርኳቸዋል፤ ኋላም ፡ በነፍሳቸው ፡ መንጸፈ ፡ ደይን ፡ ያወርዳቸዋልና፤ ድካመ፡ ዘለዓለም ፡ አለ፤

፲፮፤ ወይከውና ፡ አህጉሪሆሙ ፡ ለተፋጽዮ፡ እስከ፡ለዓለም፡

እነሱ ፡ ተማርከው ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ ለዘላለም ፡ አገራቸው ፡ ለፉጨት ፡ ይሆናል ፡ አለ ፤ የአንክሮ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ብንጣሬ ፡ ይሰሙናል ፡ ብሎ፡ ነው፤

ወኵሉ፡ዘየኃልፍ፡እንተ፡ህየ፡ይደነግፅ፡

በዚያም ፡ የሚተላለፍ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተፈትታ ፡ ጠፍታ ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ይደነግጣል፤

ወየሐውስ፡ርእሶ፡

ራሱንም ፡ ይነቀንቃል ፡ የአንክሮ ፡ ሐተታ፡እንዳለፈው፤

፲፯፤ ከመ ፡ ዐውሎ ፡ መርቄ ፡ እዘርዎሙ ፡ በቅድመ፡ፀሮሙ፣

በቆላ ፡ የተነሣ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ትቢያውን ፡ አቧራውን ፡ ጠራርጎ ፡ እንዲበትነው፤እኔም፡እንደዚያ፡እነሱን፡ በጠላቶቻቸው፡ፊት፡እበትናቸዋለሁ፤

ዘባነ፡ወአኮ፡ገጸ፣

እነሱም ፡ ባጭር ፡ ታጥቀው ፡ ዘገር ፡ ነቅንቀው ፡ ጋሻ ፡ ነጥቀው፤ ፊታቸውን፡ መልሰው ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ጋር ፡



የተዋጉ ፡ አይደለም ፤ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ጀርባቸውን ፡ ቀልሰው ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ሸሽተው ፡ ሄዱ ፡ እንጂ፤ አንድም ፡ ዘባነ ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የመለሱ ፡ አይደሉም፤ ገጸ ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደጣዖቱ ፡ መለሱ ፡ እንጂ፤

ወአርእዮሙ፡ዕለተ፡ሞቶሙ፤

የሚሞቱበትን ፡ ቀን ፡ አምጥቼ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አሳያቸዋለሁ፤

፲፰፤ወይቤሉ፡ንዑ፡ንምክር፡ምክረ፡ላዕለ፡ ኤርምያስ፤

እነሱስ ፡ ኑ ፡ በኤርምያስ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ እንምከር ፡ አሉ፤

እስመ፡ኢይትረሣዕ፡ሕግ፡በኀበ፡ካህን፤

ምንም ፡ ቢሆን ፡ በካህን ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ሕግ ፡ አይዘነጋምና፤

ወምክር፡በኀበ፡ጠቢብ፤

በጎ ፡ ምክርም ፡ በብልህ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ አይዘነጋምና፤

ወኢነገር፡በኀበ፡ነቢይ፡

ቁም ፡ ነገርም ፡ በነቢይ ፡ ዘንድ ፡ አይታጣምና ፤አንድም ፡ ወይቤሉ ፡ ንዑ ፡ ንምክር ፡ ምክረ ፡ ላዕለ ፡ ኤርምያስ ፤ እነሱስ ፡ በኤርምያስ ፡ ኑ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ እንምከርበት ፡ አሉ ፤ እስመ ፡ ኢይትረሣዕ ፡ ሕግ ፡ በኀበ ፡ ካህን ፤ በካህን ፡ በኤርምያስ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሕግ ፡ አይዘነጋምና ፡ ገድለነው፡ እንረፍ፡ አሉ፤ ወምክር ፡ በኀበ ፡ ጠቢብ ፤ በብልህ፡ በኤርምያስ ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ምክር ፡ አይጠፋምና፤ወኢነገር ፡ በኀበ ፡ ነቢይ ፤ቁም ፡ ነገርም ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ዘንድ ፡ አይጠፋምና፤

ንዑ፡ንቅትሎ፡በልሳን፤

ነገር ፡ ሠርተን ፡ በነገር ፡ ሥራት ፡ ኑ ፡ እንግደለው፤

ወኢንስማዕ፡ኵሎ፡ዘይብል፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ፡ ያስተማረንንም ፡ ሁሉ ፡ አንስማ ፡ አሉ፤

፲፱፤ስምዓኒ፡እግዚኦ፤

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ፤

ወአጽምዕ፡ቃለ፡ሥዕለትየ፤

ካንደበቴ ፡ የወጣውንም ፡ ቃል ፡ ነገር፤ አንድም ፡ ቃለ ፡ ቅስትየ ፡ ይላል ፤ የፀቤን ፡ የክርክሬን ፡ ነገር ፡ ስማ፤

፳፤ይፈድዩኒ፡እኪተ፡ህየንተ፡ሠናይት፤

በጎ ፡ ነገር ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡ ምላሽ ፡ ይመልሱልኛል ፡ አለ፤ ስለ ጾምኩላቸው ፡ ስለጸለይኩላቸው ፡ ፈንታ፤

ከረዩ፡ግበ፡ለነፍስየ፤

ለሰውነቴ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፈሩላት ፡ አለ፤ አጽንተው ፡ መከሩባት ፡ እንግደላት ፡ አሉ ፡ ሲል ፡ ነው፤

ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ቁመትየ ፡ ከመ ፡ እትናገር ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ሠናየ ፡ በቅድመ ፡ ገጽከ ፡ ከመ፡ ትሚጥ ፡ መዓተከ ፡ እምላዕሌሆሙ፡

አንተስ ፡ ቁጣህን ፡ ከነሱ ፡ ትመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለነሱ ፡ በጎውን ፡ ነገር፡ ለማማለድ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ የቆምኩትን ፡ ቁመት ፡ በቸርነትህ ፡ አስብ፤

፳፩፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ፈኑ ፡ ረኀበ ፡ ላዕለ ፡ ውሉዶሙ፤

እኔ ፡ እያማለድኳቸው ፡ አንተ ፡ እያዘንክላቸው ፡ እየራራህላቸው ፡ አንመለስም፡ ስላሉ ፡ በልጆቻቸው ፡ ረኀብን ፡ አምጣባቸው፤ ጽኑ ፡ ርግማን ፡ ይረግማቸዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

በቀጠና ፡ ዘመን ፡ እናት ፡ አባት ፡ ልጆቻቸው፡ተርበው፡አንገታቸውን፡ ደፍተው ፡ ባዩዋቸው ፡ ጊዜ ፡ የነሱ ፡ ረኀብ፡ተዘንግቷቸው፡በልጆቻቸው፡ ረኀብ፡ያዝናሉ፤ያለቅሳሉና፤

ወአስተጋብአሙ፡ውስተ፡እደ፡ኲናት፤
ውስተ ፡ አፈ ፡ ኲናት ፡ ሲል ፡ ነው፤ ከቀጠናው፡የተረፉትንም፡ሰብስበህ፡ በአሕዛብ፡ጦር፡አጥፋቸው፤

ወይኩና ፡ አንስቲያሆሙ ፡ መካናተ ፡ ወመበለታተ፤
ወንዶች፡ወንዶቼ፡በጦር፡አልቀው፡ ሚስቶቻቸው፡ከልጅ፡ይምከኑ፤ባል፡ ልጅም፡አጥተው፡ድኖች፡ይሁኑ፤

ወያሕልቆሙ፡ብድብድ፡ለዕደዊሆሙ፤
ከጦር፡ከቀጠና፡የቀሩትንም፡ሰዎች፡ ቸነፈር፡ያጥፋቸው፤

ወወራዙቶሙ፡ይደቁ፡በውስተ፡ቀትል፤
ጐልማሶቻቸውም፡በሰልፍ፡ይጥፉ፤

፳፪፤ ወይሰማዕ ፡ አውያት ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ፤
በቀጠናም ፡ በጦርም ፡ በቸነፈርም፡ አልቀው ፡ በየቤታቸው ፡ ልቅሶ ፡ ይሰማ፤

ወአምጽእ፡ላዕሌሆሙ፡ፈያተ፡ግብተ፤
በዚሁም፡መከራቸው፡ላይ፡ድንገት፡ የቤት፡ወምበዴ፡አምጣባቸው፤

እስመ፡ከረዩ፡ግበ፡የአኀዙኒ፤
ሊይዙኝ፡አዝልቀው፡ጕድጓድ፡ቆፍ ረውልኛልና ፡ አለ ፤ አዝልቀው ፡ የቆፈሩት ፡ ጕድጓድ ፡ ጥልቅ ፡ እንደሆነ፡ እንግደለው ፡ ብለው ፡ አጽንተው፡መከረውብኛልና፤

ወመሥገርተ፡ኀብኡ፡ለእገርየ፤
ለእግሮቼም፡ወጥመድን፡ሠውረው፡ አኑረውብኛልና፡አለ፤በዚህ፡ወጣ፤ በዚህ፡ወረደ፡ብለውኛልና፤

፳፫፤ለሊከ፡እግዚኦ፡ተአምር፡ከመ፡እኩየ፡መከሩ፡ላዕሌየ፡ይቅትሉኒ፤
ንዑ ፡ ንምክር ፡ ምክረ ፡ ላዕለ ፡ ኤርምያስ፡ ንዑ ፡ ንቅትሎ ፡ በልሳን ፡ ብሎ ፡ ከላይ ፡ ተናግሮት፡ ነበርና ፤ አቤቱ፡ ጌታዬ ፡ እኔንስ ፡ ሊገድሉኝ ፡ በኔ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ እንደመከሩብኝ ፡ አንተው፡ቅሉ፡ታውቀዋለህ፤

ኢትሥረይ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወኢትደምስስ፡ጌጋዮሙ፡እምቅድመ፡ገጽከ፤
አሁንም ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ኃጢአ ቶሙ ፡ ለጊዜው ፡ የሠሩትን፡ ኃጢአ ታቸውን፡ጊጋዮሙ፡የዘገየውን፡በደላ ቸውን፡ይቅር፡አትበላቸው፤አትፋቅ ላቸው፤

ወይኩን፡ሥዑለ፡ቅድሜከ፤
ኃጢአታቸው ፡ በደላቸው ፡ በፊትህ ፡ የተሣለ፡የተቀረጸ፡ይሁን፤በፊት፡ያለ፡ እንዳይጠፋ፡የማይጠፋ፡ይሁን፡ሲል፡ ነው፤

ወረስዮሙ፡ለጊዜ፡መዓትከ፤
በተቆጣህባቸውም፡ጊዜ፡አሁን፡እንደ ተናገርኩት፡አድርግባቸው።

## ምዕራፍ፡፲፱፤

፩፤ ከመዝ፡ይቤለኒ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤

ሑር፡ተሣየጥ፡ለከ፡ቀሱተ፡ልሕኵት፡ግብረ፡እደ፡ለብሐዊ፤
የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ የሠራው ፡ የሸክ ላውን፡ማድጋ፡ሒደህ፡ለራስህ፡ግዛ፡ አለኝ፤



ወንሣእ፡እምውስተ፡ረበናቶሙ፡ለሕዝብ፤
ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ የተማሩ ፡ መምህ ሮችን፡አለ፤ከጨዋ፡ወገን፡የሚሆኑ፡ ሲል፡ነው፤

ወእምረበናተ፡ካህናት፤
ከካህናትም ፡ ወገን ፡ የተማሩ ፡ መምህ ራኑን፡እነዚህን፡ይዘህ፤

፪፤ ወተሐውር፡ውስተ፡ቈላተ፡ወልደ፡ሄኖም፡ዘኖኀተ፡አንቀጸ፡ኰራሲ፤
ኰራሲ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በሚጠ ብቀው፡በር፡ደጃፍ፡ወዳለ፡ወደሄኖም፡ ልጅ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሂድ ፡ አለኝ ፤ ወልደ ፡ ሄኖም ፡ ያለው ፡ የነገደ ፡ ዛብሎን፡አለቃ፡ነው፤

ወአንብብ ፡ ሎሙ ፡ በህየ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘነገርኩከ፤
ሒደህም ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ እኔ ፡ የነገር ኩህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ አንብበህ፡አሰማቸው፤

፫፤ ወበሎሙ ፡ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ ብሔር፡ነገሥተ፡ይሁዳ፡ወእለ፡ትነብሩ፡ኢየ ሩሳሌም፤
የይሁዳ፡ነገሥታትና፡በኢየሩሳሌም፡ የምትኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡የእግዚአብ ሔርን፡ቃል፡ስሙ፡በላቸው፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ፳ኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አመጽእ፡ላዕለ፡ዝ፡ብሔር፡እኩየ፡ከመ፡ ኵሉ፡ዘሰምዖ፡ይደንግፅ፡ወየአኀዝ፡ዕዘኒሁ፤
ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ያለውን፡ አመጣ፤ይህንን፡ነገር፡የሰማ፡ሰው፡ ሁሉ፡ ይደነግጥ ፡ ዘንድ ፡ ሁለቱንም ፡ ጆሮዎቹን፡ይይዝ፡ዘንድ፡እኔ፡በዚህ፡ አገር፡ክፉውን፡ነገር፡ሁሉ፡አመጣበ ታለሁ፡አለ፤አንድም፡ናሁ፡አመጽእ፡ ላዕለ፡ዝ፡ብሔር፡እኩየ፡እኔ፡በዚህ፡ አገር፡እነሆ፡ክፉውን፡ነገር፡ሁሉ፡ አመጣበታለሁ ፤ ወኵሉ ፡ ዘሰምዖ ፡ ይደነግፅ ፡ ይኸንንም ፡ የሰማ ፡ ሰው፡ ሁሉ ፡ ይደነግጣል ፤ ወይእኀዝ ፡ ክልዔሆን ፡ ዕዘኒሁ ፡ ሁለቱን ፡ ጆሮዎ ቹንም፡ይይዛል፡አለ፤ይህ፡የፍርሃት፡ የአንክሮ፡ነው፤

፬፤እስመ፡ኃደጉኒ፤
ምነዋ ፡ ምን ፡ በደሉህ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ፡እነሱ፡በሕግ፡በአምልኮት፡ እኔን፡ትተውኛልና፤

ወተናከርክዎ፡ለዝ፡ቤት፤
እኔም ፡ ይህንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በረድዔት፡ተለይቼዋለሁና፤

ወአጠኑ ፡ በውስቴቱ ፡ ለአማልክተ ፡ ነኪር ፡ ዘኢየአምርዎሙ ፡ ኢእሙንቱ ፡ ወኢአበዊሆሙ፤
ዛሬም ፡ እነሱ ፡ ቀድሞም ፡ አባቶ ቻቸው፡ ለማያውቋቸው ፡ ለከነዓን ፡ ጣዖታት፡በቤተ፡መቅደስ፡አጥነዋል፡ ሠውተዋልና፤

ወነገሥተ ፡ ይሁዳኒ ፡ መልዕዎ ፡ ለዝ ፡ ቤት ፡ ደመ፡ጻድቃን፤
የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ የነቢያትን ፡ ደም፡በዚህ፡ቤተ፡መቅደስ፡መልተው በታልና፤ ሐተታ ፡ ደመ ፡ ኢሳይያስ ፡ ደመ፡ዘካርያስ፡ነው፤

፭፤ ወሐነፁ ፡ ምሥዋዓ ፡ ለበዐል ፡ ከመ ፡ ይሡዑ፡ደቂቆሙ፡በውስቴቱ፡በእሳት፡ዘኢ አዘዝክዎሙ፡ወዘኢሐለይክዎ፡በልብየ፤

www.ethiopianorthodox.org

እኔ፡አድርጉት፡ብዬ፡ያላዘዝኳቸውን፡
እነሱም ፡ ያደርጉታል ፡ ብዬ ፡ ያላሰብ
ኩትን፤አንድም፡እነሱ፡ይተዉታል፡
ብዬ፡ያላሰብኩትን፡ሴቶች፡ወንዶች፡
ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ሊሠዉበት ፡
ለጣዖቱም፡ምሥዋዕ፡ጸፍጽፈዋልና፤
አንድም ፡ በዓል ፡ ሊያደርጉበት ፡
ምሥዋዑን፡ጸፍጽፈዋልና፡ስለዚህ፡
ነው፡አለ፤

፮፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡
መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡
እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፡አለ፡
እግዚአብሔር፤

ወኢይሰመይ፡እንከ፡ዝ፡ቤት፡ጣፌጥ፤
እንግዲህስ፡ወዲያ፡ይህ፡ቤት፡ጣፌጥ፡
አይባልም፤

ወቈላተ፡ወልደ፡ሄኖም፤
የነገደ ፡ ዛብሎን ፡ አለቃ ፡ ጐልትም ፡
አይባልም፤

ዘእንበለ፡ቈላተ፡ቅቱላን፤
እስራኤል ፡ ያለቁበት ፡ ቈላ ፡ ይባላል ፡
እንጂ ፤ አንድም ፡ እስራኤል ፡
ያለቁበት፡ ቈላ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡
የነገደ፡ ዛብሎን ፡ አለቃ ጐልት ፡
አይባልም፤

፯፤ ወእከፍል ፡ ምክረ ፡ ይሁዳ ፡ ወምክረ ፡
ኢየሩሳሌም፡በዝ፡መካን፤
በዚያውም፡ቦታ፡የይሁዳና፡የኢየሩሳ
ሌምን ፡ ሰዎች ፡ ምክር ፡ እከፋፍለ
ዋለሁ፡ አለ ፤ በምክር ፡ አንድ ፡ እንዳ
ይሆኑ ፡ አደርጋለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡
ሰውን፡በተጣላበት፡ወራት፡በምክር፡
አንድ፡ሆኖ፡እንዳያደርግ፡ያደርገዋል፤

ወእነጽሖሙ፡በኲናት፡በቅድመ፡ፀሮሙ፤
በጠላቶቻቸውም ፡ ፊት ፡ በጦር ፡
እንዲጠፉ፡አድርጋለሁ፤

ወበእደ፡እለ፡የሐሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤
በእደ ፡ እለ ፡ የኀሥሥዋ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ሰውነታቸውን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈ
ልጓት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ በጦር ፡ አጠፋቸ
ዋለሁ ፡ አለ ፤ ፀሮሙ ፡ ያለውን ፡ በእደ ፡
እለ ፡ የኀሥሥዋ ፡ ብሎ ፡ ገለጠው ፤
አንድም ፡ እንዳለ ፡ ይሆናል ፤ ፀሮሙ ፡
የሞአብ ፡ የአሞን ፡ ሰዎች፡ የጎረቤት ፡
ጠላቶቻቸው፡ናቸውና፡ወበእደ፡እለ፡
የሐሥሥዋ ፤ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡
ናቸው፤ ቀድሞ ፡ በሞአብ ፡ በአሞን ፡
ሰዎች፡ኋላ፡ግን፡በባቢሎን፡ሰዎች፡
እጅ፡በጦር፡አጠፋቸዋለሁ፤

ወእሬሲ ፡ አብድንቲሆሙ ፡ መብልዓ ፡
ለአዕዋፈ፡ሰማይ፡ወለአራዊተ፡ገዳም፤
በነዚህ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡
አልቀው፤ሙተው፡የሚቀብራቸው፡
አጥተው፡ሬሳቸውን፡ቀን፡ለአዕዋፍ፡
ሌሊት ፡ ለአራዊት ፡ ምግብ ፡ አደር
ጋለሁ፤

፰፤ ወእሬስያ ፡ ለዛ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡
ዘሐለፈ ፡ እንተ ፡ ላዕሌሃ ፡ ይትፋጻይ ፡ ወይደ
ነግፅ፡በእንተ፡ኵሉ፡መቅሠፍታ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ጎዳና ፡
የሚሔድ፡ሰው፡ሁሉ፡እሱዋ፡የጠፋች
በትን ፡ መቅሠፍት ፡ ስላየ ፡ እንዲደ
ነግጥ ፡ እንዲያፏጭባት ፡ አደርጋ
ታለሁ፤ሐተታ፡ማፏጨት፡የአንክሮ፡
ነው፤አንድም፡ብንጣራ፡ይሰሙናል፡
ብሎ፡ነው፤

፱፤ወአበልዖሙ፡ሥጋ፡ደቂቆሙ፡ወሥጋ፡
አዋልዲሆሙ፤



በዚያ ፡ ወራት ፡ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡
ልጆቻቸውን ፡ ሥጋ ፡ አስበላቸዋለሁ ፡
በቁሙ፤አንድም፡አባት፡እናት፡የልጆ
ቻቸውን፡ከብት፡ቀምተው፡እንዲበሉ
ባቸው፡አደርጋለሁ፤

ወ፩ዱ፩ዱ ፡ ይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ካልዑ ፡ በምንዳቤሁ፡ አመ ፡ ያመነድብዎሙ ፡ ፀሮሙ ፡
ወእለ፡የኀሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤
የልጆቻቸውን ፡ ሥጋ ፡ የሚበሉ ፡
አባት፡እናት፡ብቻ፡ናቸውን፡ትለኝ፡
እንደሆነ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ የሞአብ ፡
የአሞን ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውንም ፡
ለጥፋት ፡ የሚፈልጓት ፡ የባቢሎን ፡
ሰዎች ፡ በእስራኤል ፡ መከራ ፡ ባጸኑ
ባቸው፡ ወራት ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡
በመከራው ፡ ተይዞ ፡ የባልንጀራውን ፡
ሥጋ፡ይበላል፤አንድም፡ከብቱን፡ይበ
ላበታል፤ሥጋ፡ያለው፡ገንዘብ፡ነው፤
ኤፍሬም፡ይበልዖ፡ለምናሴ፡እንዲል፤

፲፤ወትቀጠቅጣ፡ለዛ፡ቀሱት፡በቅድመ፡አዕይንቲሆሙ፡ለዕደው፡እለ፡የሐውሩ፡ምስሌከ፤
ያንጊዜ ፡ ይዘሃት ፡ የሄድካትን ፡ ሸክላ ፡
ካንተ ፡ ጋር ፡ በሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡
ቁመህ፡እያዩህ፡ስበራት፤

፲፩፤ ወትብሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ኃያል፤
ያንጊዜ ፡ አምጻዔ ፡ ዓለማት ፡ ወላዴ ፡
ፍጥረታት ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤

ከመዝ ፡ እቀጠቅጦሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ወለዛ ፡
ሀገር ፡ በከመ ፡ ተቀጥቀጠት ፡ ዛቲ፡ ቀሱት ፡
ልሕኵት፡ዘኢይክል፡ሐይወ፡እንከ፤
መጽሐፍ ፡ ምሥጢር ፡ እንጂ ፡ ዘይቤ ፡
አይጠነቅቅምና ፡ ተቀጥቀጠት ፡ ብሎ ፡
ዘኢይክል ፡ ሐይወ፡ አለ ፤ ከተሰበረች ፡
በኋላ፡መዳን፡የማይቻላት፡ይች፡በሸክ
ላነት፡የተሠራች፡ማድጋ፡እንደተሠባ
በረች፡እኔም፡ወገኖቼ፡እስራኤልንና፡
ኢየሩሳሌምን ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ አለ ፡
እግዚአብሔር፡በላቸው፤

ወበጣፌጥ፡ይትቀበሩ፤
በጦርም ፡ ሙተው ፡ በጣፌጥ ፡
ይቀበራሉ ፡ አለ ፤ በጎሡር ፡ ቦታ ፡
ይቀበራሉ፡ሲል፡ነው፤

እስመ ፡ አልቦሙ ፡ መካን ፡ ለመቃብር ፡ ዘይትቀበሩ፤
የሚቀበሩበት ፡ ክቡር ፡ ቦታ ፡ የለምና፤
አንድም ፡ በጣፌጥ ፡ ወድቀው ፡
አራዊት ፡ ይበሏቸዋል ፤ የሚቀብ
ራቸው ፡ አጥተው ፡ ቀን ፡ አዕዋፍ ፡
ሌሊት ፡ አራዊት ፡ ይበሉዋቸዋል ፤
እስመ ፡ አልቦሙ፡ መካን ፡ ለመቃብር ፡
የሚቀበሩበት፡ቦታ፡የላቸውምና፤

፲፪፤ ከመዝ ፡ እሬስዮሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ፡
ወለዝ ፡ ብሔር ፡ ወለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ለዛ ፡ ብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይቺን ፡ አገር ፡
በሱዋ ፡ የሚኖሩትንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
እንደዚህ፡አደርጋቸዋለሁ፡አለ፡እግዚ
አብሔር ፤ ከመዝ ፡ ያለው ፡ ሲናገረው ፡
የመጣውን፡ነው፤

ወእሬስያ፡ከመ፡ጣፌጥ፡ለዛ፡ሀገር፤
ይቺን፡አገራችሁን፡ኢየሩሳሌምንም፡
እንደጣፌጥ፡አደርጋታለሁ፤

ወአመዘብራ፤
ከመ፡ጣፌጥም፡ያልሁት፡ጣፌጥ፡እን
ደጠፋች ፡ አገራችሁ ፡ ኢየሩሳሌ
ምንም፡አጠፉታለሁ፤

፲፫፤ ወይከውን ፡ አብያተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ወአብያተ ፡ ነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡ ከመ ፡ መካነ ፡
ጣፌጥ፡ርኩሳነ፤

www.ethiopianorthodox.org

ይከውኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በኢየሩሳሌም ፡
ያሉ ፡ የሕዝቡ ፡ ቤቶችና፡ የይሁዳ ፡
ነገሥታት ፡ ቤቶች ፡ የጣፌጥ ፡
ቦታዎች፡ እንደረከሱ ፡ እነሱም ፡
የረከሱ፡ይሆናሉ፤

ወኵሉ ፡ አብያት ፡ ኀበ ፡ የዓጥኑ ፡ ዘአጠኑ፡
ውስተ፡አንህስቲሆሙ፡ለከዋክብተ፡ሰማይ፡
ወአውጽሑ ፡ ሞጻሕቶሙ ፡ ለአማልክተ ፡
ነኪር፡

ይህም ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የሚደረግ
ባቸው፡ ለከነዓን ፡ ጣዖታት ፡ በዓል ፡
አድርገው ፡ ወይኑን ፡ ፍልቅ ፡
አድርገው፡በሚጠጡበት፡ለሰማይም፡
ከዋክብት ፡ ምስል ፡ በሚያጥኑባቸው ፡
ሰገነት፡ ባሉዋቸው ፡ ቤቶች ፡ ነው፤
አንድም ፡ በሚያጥኑባቸው ፡ ሰገነት ፡
በሆኑ፡ቤቶች፡ነው፤

፲፬፤ ወአተወ ፡ ኤርምያስ ፡ እምጣፌጥ ፡
ዘፈነዎ፡እግዚአብሔር፡ይትነበይ፡በህየ፡

ኤርምያስም ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ትንቢት ፡
ሊናገር፡እግዚአብሔር፡ትንቢት፡ተና
ገርበት ፡ ብሎ ፡ ከላከው ፡ ከላከበት ፡
ከጣፌጥ ፡ ተመለሰ ፤ አንድም፡
ኤርምያስ ፡ ዘፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይትነበይ ፡ በህየ ፡ አተወ፡ እምጣፌጥ፤
በዚያ ፡ ቦታ ፡ ትንቢት ፡ ሊናገር ፡
ትንቢት ፡ ተናገር ፡ ብሎ ፡ እግዚአ
ብሔር፡የላከው፡ኤርምያስ፡ከጣፌጥ፡
ተመለሰ፤

ወቆመ፡ውስተ፡ዐፀደ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡

ከዚያም፡ተመልሶ፡ሂዶ፤በቤተ፡እግዚ
አብሔር ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ባምስቱ ፡
በስድስቱ ፡ በሰባቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡
ገብቶ፡ቆመ፤

፲፭፤ ወይቤሎሙ፡ለኵሉ፡ሕዝብ፡ከመዝ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፡

ከዚያ ፡ ቦታም ፡ ቆሞ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡
ለሕዝቡ ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤

ናሁ፡አመጽእ፡ላዕለ፡ዛ፡ሀገር፡ወላዕለ፡ኵሉ፡
አህጉሪሃ፡ኵሎ፡እኩየ፡ዘነበብኩ፡ላዕሌሃ፡

እነሆ ፡ በዚች ፡ አገርና ፡ በአውራጃዋ ፡
ሁሉ ፡ በሱዋ ፡ አመጣባታለሁ ፡ ብዬ ፡
የተናገርሁትን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡
አመጣዋለሁ፤

እስመ ፡ አጽንዐ ፡ ሐዳፎሙ ፡ ከመ ፡
ኢይስምዑ፡ቃልየ፡

እኔ ፡ የነገርኋቸውን ፡ ቃል ፡ እሺ ፡ በጎ ፡
ብለው ፡ እንዳይሰሙ ፡ ዕዝነ ፡ ልቡና
ቸውን ፡ ከድንጋይ ፡ ይልቅ ፡ አጽንተው
ታልና።

## ምዕራፍ፡፳፡

### ጉባዔ፡

፩፤ ወሰምዓ፡ጳስኮር፡ወልደ፡ኤሞር፡ካህን፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ የካህኑ ፡ የኤሞር ፡ ልጅ፡
ጳስኮር፡ይህንን፡ነገር፡ሰማ፤

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተሠይመ ፡ መኰንነ ፡ ለቤተ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይትኔበይ፡ ኤርምያስ ፡
ዘ፡ነገረ፡

ሰምዐ ፡ እንዘ ፡ ይትኔበይ ፡ ኤርምያስ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተሠይመ ፡ መኰንነ ፡
ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር፡
የተሾመው ፡ አለቃው ፡ እሱ ፡ ነበርና ፡
ኤርምያስ ፡ ይህን ፡ ትንቢት ፡ ሲናገር ፤
ጳስኮር ፡ ሰማ ፡ ምነዋ ፡ መስማትማ ፡ ያል
ተሾመስ ፡ ይሰማ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡
በዚያ፡ ወራት ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ተሹሞ ፡
ከዚያው ፡ ነበርና ፤ አንድም ፡ ቀሠፎ ፡
[illegible]



፪፤ ወቀሠፎ ፡ ጳስኮር ፡ ለኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡
ወሞቅሖ፤

ጳስኮርም፡ኤርምያስን፡ገረፈው፤

ወወደዮ ፡ ውስተ ፡ አዘቅት ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡
ብንያም ፡ ላዕላይ ፡ ዘውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡

ከገረፈውም ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ ነገደ፡ ብንያም ፡
በሚወጡበት ፡ በሚገቡበት ፡ በር ፡
አጠገብ ፡ ባለ ፡ ጕድጓድ ፡ አሥሮ ፡
አጋዘው፤

፫፤ ወእምዝ ፡ በሳኒታ ፡ አውጽአ ፡ ጳስኮር ፡
ለኤርምያስ፡እምውስተ፡አዘቅት፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በበነጋው ፡ ጳስኮር ፡
አሥሮ ፡ አግዞ ፡ ካኖረበት ፡ ከጕድጓድ፡
ኤርምያስን፡አወጣው፤

ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለጳስኮር ፤ አኮ ፡ ጳስኮር፡
ዘሰመየከ፡እግዚአብሔር፡

ያንጊዜ ፡ ኤርምያስ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጳስኮር፡ያለህ፡አይደለም፤

ዳዕሙ፡ፈላሲ፡ዘየዐውድ፡

አገር ፡ ላገር ፡ የሚዞር ፡ መጻተኛ ፡
ብሎሃል፡እንጂ፤አንድም፡አገር፡ላገር፡
የሚዞር ፡ መጻተኛ ፡ ብሎሃል ፡ እንጂ ፡
እግዚአብሔር ፡ በዓለ ፡ ሀገር ፡ በዓለ ፡
ርስት ፡ ያለህ፡ አይደለም ፤ ጳስኮር ፡
ማለት ፡ በዓለ፡ ሀገር ፡ በዓለ ፡ ርስት ፡
ማለት፡ነውና፤

፬፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎዋልና፤

ናሁ፡አነ፡አፈልሰከ፡ምስለ፡ኵሉ፡አኃዊከ፡
ወኵሉ፡አዕርክቲከ፤

ከሥጋ፡ወንድሞችህና፡ከወዳጆችህ፡
ሁሉ፡ጋራ፡እኔ፡አሁን፡አስማርኬ፡እሰ
[illegible]

ወትወድቅ ፡ በኲናተ ፡ ፀርከ ፡ እንዘ ፡ ትሬኢ፡
በአዕይንቲከ፡

ዓይንህ ፡ እያየ ፡ በጠላቶችህ ፡ ጦር ፡
ትጠፋለህ፤

ወኪያከኒ ፡ ወለኵሉ ፡ ይሁዳ ፡ አገብኦሙ፡
ውስተ፡እደ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡

ወለከሂ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንተንና ፡
የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በባቢሎን ፡
ንጉሥ፡እጅ፡እጥላቸዋለሁ፡ብሏል፤

ያፈልስዎሙ፡ወይወስድዎሙ፡ባቢሎን፡

አሕዛብ ፡ መጥተው ፡ ካገራቸው ፡
ማርከው ፡ ወደባቢሎን ፡ ይወስዱ
ቸዋል፤

ወይቀትልዎሙ፡በኲናት፡

ማርከውም፡ወስደው፡በጦር፡ይገድሉ
ዋቸዋል ፡ አለ ፤ ተማርከው ፡ ከሄዱ ፡
በኋላ ፡ በጦር፡ የሞቱ ፡ አሉና ፡ እንዲህ ፡
አለ፤አንድም፡ከዚህ፡አስቀድሞ፡በሀገ
ራቸው፡የተደረገው፡ነው፤

፭፤ወእሁብ፡ኵሎ፡ጽንዓኒሃ፡ለዛቲ፡ሀገር፡

የዚችንም፡አገር፡አርበኞቿዋን፡ሁሉ፡

ወኵሎ፡ፃማሃ፤

የደከመችበትን ፡ አዝመራዋን ፡ ሁሉ፡
በዱር፡ያለ፡አዝመራዋን፡አዝርዕቱን፡
አትክልቱን፤

ወለኵሉ፡ክብራ፡

ባለጸግነቷንም ፡ ሁሉ ፡ አለ ፤ ከቤት ፡
የገባውን፡ሪቅ፡ገ፦ተራውን፤አንድም፡
ወኵሉ ፡ ፃማሃ ፡ የደከመችበትን ፡ ባለጸ
ግነቷን፡ሁሉ፡አለ፤ይህ፡የወል፡ነው፡
ወለኵሉ፡ክብራ፡የድሆችን፡

ወለኵሉ ፡ መዛግብተ ፡ ነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ውስተ ፡
እደ፡ጸላዕቶሙ፡ይበርብርዎሙ፡

የይሁዳ ፡ ነገድን ፡ ድልብ ፡ ሁሉ ፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

የባለጸጋን፤ አንድም ፡ ወለኵሉ ፡
መዛግብተ፡ ነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡ ይላል፤
የይሁዳንም ፡ ነገሥታት ፡ ድልብ ፡
ሁሉ፡ይበረብሩዋቸው፡ዘንድ፤እንዲበ
ረብሩዋቸው ፡ ብጠላቶቻቸው፡ እጅ ፡
አሳልፌ፡ እሰጥባቸዋለሁ ፤ አንድም ፡
ወይበረብርዎሙ ፡ ወይነሥእዎሙ ፡
ወያበውእዎሙ ፡ ባቢሎን ፡ ይህን ፡
ሁሉ፡ ባለጸግነታቸውን ፡ በርብረው ፡
ወስደው፡ወደባቢሎን፡ያገቡባቸዋል፤

፮፤ ወአንተሰ፡ጳስኮር፡ወኵሉ፡ቤትከ፡
ተሐውሩ፡
አንተሂ፡ሲል፡ነው፤አንተም፡ጳስኮር፡
በቤትህ፡ያሉ፡ቤተ፡ሰቦችህም፡ሁሉ፡
ተማርካችሁ፡ትሄዳላችሁ፤

ወይዔውውከሙ፡ባቢሎን፡
የባቢሎንም፡ሰዎች፡ማርከው፡ወደባ
ቢሎን፡ይወስዷችኋል፤

ወበህየ ፡ ትመውት ፡ አንተ ፡ ወበህየ ፡
ይቀብሩከ፡
አንተ፡ተማርከህ፡ሄደህ፡በባቢሎን፡
ሙተህ፡በባቢሎን፡ትቀበራለህ፤

ወኵሎሙ፡አዕርክቲከ፡ዘተነበይከ፡ሎሙ፡
ሐሰተ፡
ትንቢተ ፡ ሐሰት ፡ የተናገርክላቸው ፡
ወዳጆችህም ፡ ሁሉ ፡ በባቢሎን ፡
ሙተው፡በባቢሎን፡ይቀበራሉ፤

፯፤ ቀሠፍከኒ፡እግዚኦ፡ወተቀሠፍኩ፡
ቀሠፎ ፡ ጳስኮር ፡ ለኤርምያስ ፡ ብሎ ፡
ነበርና፤ምን፡ይህ፡ብቻ፡ነው፤አንተ፡
በክፉዎች ፡ አድረህ ፡ በመከራው ፡
ገረፍከኝ፤ እኔም ፡ ባንተ ፡ አምኜ ፡
መከራውን፡ተቀበልሁት፤

ወአጽናዕከኒ፡
አንተም ፡ መከራውን ፡ ለመቀበል፡
አጸናኸኝ፤

ወከህልከ፡አሕይዎትየ፡
እኔንም፡ከመከራው፡ማዳን፡ተቻለህ፤

ወኮንኩ፡ሰሐቀ፡ወሥላቀ፡በኵሉ፡መዋዕል፡
በምመክርበት ፡ በማስተምርበትም ፡
ዘመን፡ሁሉ፡ለሰው፡ሁሉ፡መዘበቻ፡
ሆንሁ፤

ወኵሉ፡ይሣለቀኒ፡
ስመክር፡ሳስተምር፡መልኬን፡ያየኝ፡
ቃሌን፡የሰማኝ፡ሁሉ፡ይህ፡ዘብዛባ፡
ጀመረ፡እያለ፡ይዘብትብኛል፤

፰፤ እስመ ፡ ለለተናገርኩ ፡ አዐወዩ ፡
በግፍዕ፡
እየመከርኋቸው ፡ እያስተማርኋቸው፡
ቢበድሉኝ፡በዚህ፡ግፌ፡አዝናለሁና፤

ወበኃሣር፡እጼውዕ፡
ባገኘኝም፡መከራ፡ሁሉ፡ግፌን፡እናገ
ራለሁና፤

ወኮነኒ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘይትሐ
በቡኒ፤
በምመክርበት ፡ በማስተምርበት ፡
ወራት ፡ የማስተምረው ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ቃሉ ፡ እኔን ፡ ሐብሐብ ፡
የሚሉበት፡ሆነብኝ፤አንድም፡በዘይት
ሔዘቡኒ ፡ ይላል፤ እኔን ፡ የሚጠራጠ
ሩበት፡ሆነብኝ፤

ወይዘነጉጉኒ፡ኵሎ፡አሚረ፤
እኔንም ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ የሚያሾሚጥ
ጡበት፡ሆነብኝ፤

፱፤ ወእቤ፡ኢይዜክር፡እንከ፡ስመ፡እግ
ዚአብሔር፡
ከመከራዬም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡
እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የእግዚአብሔርን፡



ስም ፡ ጠርቼ ፡ አላስተምርም፡ ብዬ ፡
በልቡናዬ፡አሰብሁት፤

ወኢይነግር፡በስሙ፡ዚአሁ፡
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብዬ፡አላ
ስተምርም፡ብዬ፡በቃሌም፡ተናገርሁ፤

ወኮነ፡ልብየ፡ከመ፡እሳት፡ዘይነድድ፤
በልቡናዬም ፡ ባሰበው ፡ በቃሌም ፡
ብናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡
በልቡናዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚነድ ፡
ሆነብኝ፤

ወአውዐየኒ፡አዕፅምትየ፡
ሰውነቴንም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ፈጀኝ፤
አቃጠለኝ፤

ወስዕንኩ፡ዐዊሮቶ፡
እሱንም፡መታገሥ፡ተሳነኝ፤

ወኢክህልኩ፡
እሱንም፡መታገሥ፡አልተቻለኝም፤

፲፤ እስመ ፡ ሰማዕኩ ፡ ውውዓሆሙ ፡
ለብዙኃን፡እለ፡ተጋብኡ፤በላዕሌየ፡
በኔ ፡ ጥፋት ፡ የተሰበሰቡ፤ አንድም ፡
ኪያየ ፡ ሲል ፡ ነው፤ እኔን ፡ ለማጥፋት፡
የተሰበሰቡ ፡ የብዙ ፡ ጠላቶቼን ፡
ውካታ፡ግርግርታ፡ሰምቻለሁና፤

ወአገቱኒ፡
ውካታቸውንም ፡ ግርግርታቸውንም፡
ብቻ፡ሰምቼ፡አልቀረሁ፤ተሰብስበው፡
መጥተው ፡ ከበቡኝ ፡ አለ፤ ተጋብኡ ፡
በላዕሌየ፡ያለውን፡አመጣ፤

ተንሥኡ፡ወንትነሣእ፡ይቤሉ፡ኵሉ፡ዕደወ፡
ሰላምየ ፡ እለ ፡ ይትዓቀቡ ፡ ቍስልየ ፡ እመ ፡
ይስሕት ፡ ወንክል ፡ ተመጥዎቶ ፡ በቀለነ ፡
እምኔሁ፤
ተሰብስበው ፡ ከበውኝም ፡ ምናልባት፡
እሱ ፡ ቢስት ፡ እኛም ፡ ተሰብስበን ፡
ከበን፡ ከሱ ፡ በቀላችንን፡ መከፈል ፡
ምናልባት፡ቢቻለን፡ብለው፡ቀድሞ፡
ይወዱኝ፡የነበሩ፡ወዳጆቼ፡ዛሬ፡ግን፡
ቍስለ ፡ መከራዬን ፡ የሚጠባበቁ ፡
ጠላቶቼ ፡ ተነሡ፤ እንነሣበት ፡
ተባባሉ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ይስሕት ፡
ወንክል፡ይላል፤ቀድሞ፡ወዳጆቼ፡ኋላ፡
ግን፡ቍስለ፡መከራዬን፡የሚጠባበቁ፡
ጠላቶቼ ፡ እሱ ፡ እንዲስት ፡ እንዲ
በድል፡እኛም፡ከሱ፡በቀላችንን፡እንድ
ንከፈል፤ በጠላትነት ፡ ተነሡ፤ እንነ
ሣበት ፡ ተባባሉ፤ አንድም ፡ ከመ ፡
ይስሐት ፡ ወንክሃል ፡ ይላል፤ ቀድሞ ፡
የኔን ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የሚወዱ ፡
ወዳጆቼ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ቍስለ ፡
መከራዬን፡የሚጠባበቁ፡እሱ፡ይስት፡
ይበድል፡ዘንድ፡እኛም፡ከሱ፡በቀልን፡
መከፈል ፡ ይቻለን ፡ ዘንድ ፡ በጠላ
ትነት፡ተነሡ፤እንነሣበት፡አሉ፤

፲፩፤ ወእግዚአብሔር ፡ ምስሌየ ፡ ከመ፡
ጽኑዕ፡መስተቃትል፤
ዘምስሌየ፡ሲል፡ነው፤ነገር፡ግን፡ከኔ፡
ጋር፡በረድኤት፡ያለ፡እግዚአብሔር፡
እንደ ፡ ጽኑ ፡ አርበኛ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡
ለነሱ፡ይህ፡ሁሉ፡አይቻላቸውም፤

በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እለ ፡ ይዴግኑኒ ፡ ደከሙ ፤
ወኢክህሉ ፡ ማንሻ ፡ ነው፤ አንድም ፡
ከኔ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡ ያለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንደጽኑ ፡ አርበኛ ፡ ያለ ፡
ነውና፡ስለዚህ፡እኔን፡ለማጥፋት፡በጠ
ላትነት፡ የሚከተሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ደከሙ፤

ወኢክህሉ፤
እኔን ፡ መቀዋወምም ፡ አልተቻላ
ቸውም፤

ወተሐፍሩ፡ጥቀ፤
ፈጽመውም፡አፈሩ፡ጐሰቈሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ኢያእመሩ፡ኀሣሮሙ፡እንተ፡ኢትት
ረሣዕ፡ለዓለም፡
በሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ፡የማትረሳ፡መከራቸው፡እን ድትመጣባቸው፡አላወቁምና፤

፲፪፤ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ዘትጤ
ይቃ፡ለጽድቅ፡
የሰውን ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ መርምረህ፡ የምታውቅለት፤አንድም፡ዘትጤይቆ፡ ለጻድቅ ፡ ይላል፤ በምግባር ፡ በሃይ ማኖት፡የሚያመልክህ፡ደጉን፡ሰው፡ ከወገኖቹ፡ከኃጥአን፡ለይተህ፡የምታ ውቀው፤

ወተአምር፡ልበ፡ወኵልያተ፡
ሰው፡በልቡናው፡ያሰበውን፡ኵላሊት፡ ያጤሰውን ፡ ያመላለሰውን ፡ መር ምረህ፡የምታውቅ፡አቸናፊ፡እግዚአ ብሔር፤

ፍታሕ፡ሊተ፡ፍትሕየ፡ዘእምኀቤከ፡
ካንተ ፡ የተገኘውን ፡ ፍርድ ፡ ፍረ ድልኝ፤

እስመ፡ለከ፡ከሠትኩ፡ቅስትየ፡
ወቀሳዬን፡ላንተ፡ዳኝነት፡ብከ፡ባንተ ዳኝነት፡ገልጬ፡ተናግሬያለሁና፤

፲፫፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕ
ኵትዎ፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ይመክራል፤ ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ ከክፋታችሁ ፡ ታግሣችሁ፡ከኃጢአታችሁ፡ተመል ሳችሁ ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ጸንታችሁ፡ፈጣሪያችሁ፡እግዚአብ ሔርን ፡ ፈጽማችሁ ፡ አመስግኑት፤ አንድም፡አክብራችሁ፡አመስግኑት፤ አንድም፡አመስግናችሁ፡አክብሩት፡ ክብሮ፡የማይመሰገን፡ተመስግኖ፡የማ ይከበር፡አለና፡አክብራችሁ፡አመስ ግኑት፡አለ፤

እስመ ፡ አድኀና ፡ ለነፍሰ ፡ ነዳይ ፡ እምእደ ፡
እኩያን፡
የድኃውን ፡ ሰውነት ፡ ከክፉዎች ፡ ጠላቶቹ፡እጅ፡አድኗልና፤

፲፬፤ ርግምተ፡ትኩን፡ዕለት፡እንተ፡ባቲ፡
ተወለድኩ፡እመ፡ወለደተኒ፡እምየ፡
እናቴ፡እኔን፡በወለደችበት፡ወራት፡ ያቺ፡የተወለድኩባት፡ቀን፡ከቀኑ፡ ሁሉ ፡ ተለይታ ፡ ርግምት ፡ ትሁን፤ ሐተታ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ባማ ፡ ክህደት ፡ መላእክትንና ፡ ሰውንም ፡ ባማ፡ ኃጢአት ፡ ይሆንብኛል ፡ ብሎ፡ ከመከራው፡ጽናት፡የተነሣ፡የተወለደ ባትን ፡ ቀን ፡ ረገመ ፤ ከመከራውም ፡ ጽናት፡የተነሣ፡የተወለደባትን፡ቀን፡ መርገም ፡ ልማድ ፡ ነው፤ ከዚያም ፡ ኢዮብ፡ወረገማ፡ለዕለት፡እንተ፡ባቲ፡ ተወልደ፡ወይቤ፡ኢዮብ፡ለትጥፋዕ፡ ይእቲ፡ዕለት፡እንተ፡ባቲ፡ተወለድኩ፡ እንዳለ፤

፲፭፤ ወኢይኩን፡ቡሩከ፡ርጉመ፡ለይኩን፡
ብእሲ፡ዘዜነዎ፡ለአቡየ፡ወይቤሎ፡ተባዕት፡
ተወልደ፡ለከ፡ፍሥሐ፡ዘያስተፌሥሐ፡
ላባቴ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደልህ ፡ የምስራች፡ደስ፡ይበልህ፡ብሎ፡ነግሮ፡ አባቴን፡ደስ፡ያሰኘው፡ሰው፡ከሰው፡ ተለይቶ ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፤ ቡሩክ ፡ አይሁን፤

፲፮፤ ወይኩን ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡
አህጉር፡እለ፡ገፍትዖን፡እግዚአብሔር፡ወኢ
ተሠሃሎን፡



ይህም፡ላባቴ፡የምሥራች፡የነገረው፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ቀድሞ፡እንዳጠፋቸው፡ኋላም፡ይቅር፡ እንዳላላቸው ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ እንደ ገሞራ፡ይሁን፤

ወይስማዕ ፡ አውያት ፡ በጽባሕ ፡ ወብካይ ፡
በመዓልት፡
እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ጧቱን ፡ መርዶ ፡ ሰምቶ ፡ ቀኑን ፡ ሲያለቅስ ፡ ይዋል፤

፲፯፤ እስመ፡ኢቀተለኒ፡በውስተ፡ማኅፀን፡
ትኩነኒ ፡ እምየ ፡ መቃብርየ ፡ ወማኅፀናኒ ፡
ነሣኢትየ፡ለዓለም፡
እናቴ ፡ መቃብሬ ፤ ማኅፀኑዋም ፡ ለዘላለሙ፡ሞግዚቴ፡ትሆነኝ፡ዘንድ፡ እኔንም ፡ በማኅፀን ፡ ሳለሁ ፡ አልገደለ ኝምና፡አለ፤በእናቴ፡ማኅፀን፡ሳለሁ፡ ደም፡ወርዶ፡አጥንት፡ሁኖ፡ቀረ፡አላለ ኝምና፤

፲፰፤ ወለምንት ፡ ወጻእኩ ፡ እማኅፀን ፡
ከመ፡እርአይ፡ሕማመ፡ወሥራኀ፡
መከራውን ፤ ጽዋትወ ፡ መከራውን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ከናቴ ፡ ማኅፀን፡ ወጥቼ፡ተወለድኩ፤

ወኀልቀ፡መዋዕልየ፡በኀሣር፤
ዘመኔም ፡ በመከራ ፡ ተፈጸመ፤ በራሱ፡ በመጣበት ፡ መከራ ፡ እንዲህ፡ አለ፤ አንድም ፡ ለምንት ፡ ወጻእኩ ፡ እማኅፀን፡ ከመ ፡ እርአይ ፡ ሕማመ ፡ ወሥራኀ፤የእስራኤል፡መከራቸውን፡ ጸዋትወ፡መከራቸውን፡አይ፡ዘንድ፡ ለምን ፡ ከናቴ ፡ ማኅፀን፡ ተወልጄ ፡ ወጣሁ፤ወኀልቀ፡መዋዕልየ፡በኀሣር፡ ያለ፡ዘመኔም፡የእስራኤልን፡መከራ ቸውን ፡ በማየት ፡ በማሰብ ፡ በመከ ራው፡ተፈጸመ።

## ምዕራፍ፡፳፩፡

፩፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ወደ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡የመጣ፡የእግዚአብሔር፡ ቃሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ፡ይህ፡ነው፤

አመ ፡ ለአከ ፡ ኀቤሁ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ንጉሥ ፡
ጳስኮርሃ ፡ ወልደ ፡ ሜልክዩ ፡ ወሶፎንያስሃ ፡
ወልደ፡ማሴው፡ካህን፡
የሜልክዩ፡ልጅ፡ጳስኮርንና፡የካህን፡ የማሴው፡ልጅ፡ሶፎንያስን፡ንጉሡ፡ ሴዴቅያስ፡ወደሱ፡በላከ፡ጊዜ፡የመጣ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው፤ ሐተታ፡ ይህ፡ጳስኮር፡ያው፡የቀደመው፡ነው፤ ከታች ፡ ወልደ ፡ ኤሞር ፡ ያለውን ፡ ከዚህ፡ ወልደ ፡ ሜልክዩ ፡ አለው፤ ላንድ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ስም ፡ አለውና፤ አንድም፡ሌላ፡ጳስኮር፡ነው፤

፪፤ ወይቤሎ፡ሰአሎ፡ለእግዚአብሔር፡በእ
ንቲአነ፡
ስለኛ ፡ ብለህ፤ አንድም ፡ የኛን ፡ ነገር፡ እያመለከትህ፡ፈጣሪያችን፡እግዚአብ ሔርን፡ለምነው፡አለው፤

እስመ ፡ መጽአ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡
ባቢሎን፡ይፅብዓነ፡
የባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ሊወጋን፡መጥቷልና፤

www.ethiopianorthodox.org

እመቦ ፡ ከመ ፡ ይገብር ፡ ለነ ፡ እግዚአብሔር፡ በኵሉ፡ተአምሪሁ፡ወየሐውር፡እምላዕሌነ፡

እመቦና ፡ ከመ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይ ወጡም ፤ ከመን ፡ ለማውጣት ፡ ፈጣሪ ያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ተአምራቱን ፡ ሁሉ፡እንዲያደርግልን፡እሱም፡እንደ፡ ፋቂሂ ፡ ወልደ ፡ ሮሜልዩ ፡ ከኛ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲሄድልን ፡ ሰአሎ፤ አንድም ፡ እመቦን ፡ ለማውጣት ፡ እመቦ፡ ይገብር ፡ ለነ፤ እግዚአብሔር ፡ ተአምራቱን ፡ ምናልባት ፡ ቢያደር ግልን ፡ እሱም ፡ እንደፋቂሂ ፡ ወልደ ፡ ሮሜልዩ ፡ ምናልባት ፡ ቢመለስልን ፡ ሰአሎ ፡ ለምነው፤ እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መጠራጠር ፡ አይ ደለም ፤ ራሱን ፡ መጠራጠር ፡ ነው ፡ እንጂ፤

፫፤ ወይቤሎሙ ፡ ኤርምያስ ፡ ከመዝ ፡ በልዎ፡ለሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡

ኤርምያስም ፡ መላከተኞቹን ፡ የይሁ ዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በሉት፡አላቸው፤

፬፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡ እስራኤል፡

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡አነግፈከሙ፡ንዋየ፡ሐቅልከሙ፡ ዘውስተ፡እዴከሙ፡ዘአንትሙ፡ትትቃተሉ፡ ቦቱ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለከላውዴዎን ፡ እለ፡ሐፀሩከሙ፡እንተ፡አፍዓ፡እምጥቅም፤

ወዘአንትሙ ፡ ትትቃተሉ ፡ ቦቱ ፡ ከቅጥር ፡ በአፍዓ ፡ ሁነው ፡ በጦር ፡ ያጠሯችሁ ፡ የከለዳውያን ፡ ሰዎችንና፡ የባቢሎኑን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆርን ፡ እናንተ ፡ የምትወጉበት ፡ በእጃችሁ ፡ የተያዘ ፡ የበዳ ፡ ፀብታችሁን ፡ እኔ፡ ከጃችሁ፡አስረግፋችኋለሁ፡አለ፡እግ ዚአብሔር ፡ ብላችሁ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንገሩት፡አላቸው፤

ወአስተጋብአክሙ፡ማዕከለ፡ዛ፡ሀገር፡

እናንተንም ፡ ሰብስቤ ፡ በከተማዩቱ ፡ አጠፋችኋለሁ፤ አንድም ፡ ወአስተጋ ብአሙ፡ማዕከለ፡ዛ፡ሀገር፡ይላል፤በኢ የሩሳሌም ፡ መካከል ፡ ባለች ፡ በከተ ማዩቱ፡ሁነው፡ሊያጠፏችሁ፡ጠላቶ ቻችሁን፡ሰብስቤ፡አመጣቸዋለሁ፡

፭፤ ወአነ ፡ እትቃተለከሙ ፡ በእድ ፡ ጽንዕት፡ወበመዝራዕት፡ልዕልት፡

በጽኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምዋጋችሁ ፡ እኔ፡ ነኝ፤ሌላ፡አይምሰላችሁ፤አንድም፡እን ግዲህም ፡ ወዲያ ፡ ዳግመኛ ፡ ብትበ ድሉኝ፤ እንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ በጽኑ ፡ ሥልጣኔ፡እኔ፡እዋጋችኋለሁ፤

፮፤ በመዓት፡ወበመቅሠፍት፡ዓቢይ፡

በመዓተ ፡ መቅሠፍት ፡ ዓቢይ ፡ ሲል ነው፤በእድ፡ጽንዕት፡ወበመዝራዕት፡ ልዑልም ፡ ያልሁት ፡ ጽኑ ፡ መቅሠ ፍቱን ፡ በሚያመጣ ፡ በቁጣዬ፡ ነው፤ አንድም ፡ በመቅሠፍተ ፡ መዓት ፡ ዓቢይ ፡ ይላል፤ ጽኑ፡ ቍጣዬ ፡ በሚፈጸ ምበት ፡ በመቅሠፍቴ ፡ ነው፤ አንድም፡ እንዳሴ ፡ ይሆናል፤ በመዓት ፡ በሐልዮ፡ ወበመቅሠፍት ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ በእድ ፡ ጽንዕት ፡ ወበመዝራዕት ፡ ልዑልም ፡ ያልሁት ፡ አስቤ ፡ ተናግሬ፡ በማመጣባችሁ፡መቅሠፍት፡ነው፤

ወእቀትሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ፡ዛ፡ሀገር፡

በዚች ፡ አገር ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ የሚ ኖሩትንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡



አድርጌ፡አጠፋቸዋለሁ፤

ሰብእኒ ፡ ወእንስሳኒ ፡ ይመውቱ ፡ በሞት ፡ ዓቢይ፡

ሰውና ፡ ከብቱም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ በጽኑ፡ ሞት ፡ ይሞታሉ፤ ኵሎሙ ፡ ያለውን ፡ ሰብእኒ ፡ ወእንስሳኒ ፡ እቀትሎሙ ፡ ያለውን ፡ ይመውቱ ፡ በሞት፡ዐቢይ፡ብሎ፡ገለጠው፤

፯፤ ወእምዝ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

አገብአሙ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ ወለ ደቂቁኒ ፡ ወለሕዝብኒ ፡ እለ ፡ ተርፉ፡ ውስተ፡ ዛ፡ ሀገር፡ እምነ፡ ሞት፡ ወኩናት፡ ወረኃብ፡ ውስተ፡እደ፡ናቡከደነፆር፡

ከሞት፡ ከጦርና፡ ከቀጠና፡ በዚች፡ አገር፡ የቀሩ፡ ልጆቹን፡ ሠራዊቱንና፡ የይሁዳው፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስን፡በናቡ ከደነፆር፡እጅ፡እጥላቸዋለሁ፤

ወውስተ፡እደ፡ፀሮሙ፤

በጠላቶቻቸው፡ እጅ፡ አለ፡ በሞዓብ፡ በአሞን፡እጅ፤

ወውስተ፡እደ፡እለ፡የኀሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤

ሰውነታቸውንም፡ ለጥፋት፡ በሚፈ ልጓት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ እጥላቸዋለሁ ፡ አለ፤በባቢሎን፡ሰዎች፡እጅ፤

ወይመትርዎሙ፡በኩናት፡

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥ ተው፡በጦር፡ያጠፏቸዋል፤

ወኢይምሕክዎሙ፡ወኢይሠሃልዎሙ፤

ተሰብስበው ፡ መጥተውም ፡ አዝ ነው፡ራርተው፡ይቅር፡አይሏቸውም፤ አንድም፡ወይመትርዎሙ፡በኩናት፤ አሕዛብ ፡ መጥተው ፡ በጦር ፡ ያጠፏ ቸዋል ፤ ወኢይምሀክሙ ፡ ወኢይሠ ሃሎሙ፡እኔም፡እነሱ፡ሲያጠፏቸው፡ አይቼ ፡ አዝኜ ፡ ራርቼ ፤ ይቅር ፡ አልላ ቸውም፤

፰፤ ወበሎሙ፡ለዝ፡ሕዝብ፡ከመዝ፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፡

ለእሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እኒህን ፡ ወገኖች፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡ በላቸው፤

ናሁ ፡ አነ ፡ እሠይም ፡ ቅድመ ፡ ገጽከሙ ፡ ፍኖተ፡ሕይወት፡ወፍኖተ፡ሞት፤

የሕይወትንና፡የሞትን፡ሥራ፡ጐዳና፡ በፊታችሁ ፡ እነሆ ፡ አኖራለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በላቸው ፤ ፍኖተ ፡ ሕይወት፡ፍኖተ፡ሞት፡ብሎ፡ሁለት፡ አርእስት ፡ ተናግሮዋል ፤ ለሁለቱም ፡ ያመጣል፤

፱፤ ዘነበረ፡ውስተ፡ዛ፡ሀገር፡ይመውት፡ በኩናት፡ወበብድብድ፡ወበረኃብ፤

ጠላት ፡ (ወባት) ፡ አልገባም ፡ ብሎ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ የተቀመጠ ፡ ሰው ፡ በጦር፡ በቸነፈር ፡ በቀጠና ፡ ይጠፋል ፡ አለ፡ፍኖተ፡ሞት፡ላለው፤

ወዘወጽአሰ ፡ ኀበ ፡ ፋርስ ፡ እለ ፡ አገቱከሙ ፡ የሐዩ፡ወትከውን፡ነፍሱ፡ፄዋ፤

በጦር፡ወደከበቡዋችሁ፡ወደ፡ፋርስ፡ ሰዎች ፡ ወጥቶ ፡ ወባት፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ግን፡ አይሞትም ፡ ይድናል ፤ ሰው ነቱም ፡ ትማረካለች ፡ እንጂ ፡ አት ሞትም፡አለ፡ፍኖተ፡ሕይወት፡ላለው፤

፲፤ እስመ ፡ አጽናዕኩ ፡ ገጽየ ፡ ላዕለ ፡ ዛ ፡ ሀገር፡ለእኩይ፡ወአኮ፡ለሠናይ፡

ለበጎ ፡ ያይደለ ፡ ለክፉ ፡ ነገር ፡ በዚች ፡

www.ethiopianorthodox.org

አገር ፡ ገጸ ፡ መዓቴን ፡ አጽንቼባታ ለሁና፣ አንድም ፡ በእኩይ ፡ ወአኮ ፡ በሠናይ፡ይላል፤በበጎ፡ያይደለ፡በክፉ፡ ነገር ፡ ገጸ፡ መዓቴን ፡ አጽንቼባታ ለሁና፣

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትገብዕ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፣

ይቺው ፡ አገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በባቢሎን፣ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር፡ እጅ፡ትያዛለች፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወያውእያ፡በእሳት፡ለቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤

ናቡከደነፆርም፡የይሁዳ፡ንጉሥ፡የሴዴ ቅያስን፡ቤት፡በእሳት፡ያቃጥላታል፤

፲፩፣ ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ቤተ፡ ዳዊት፣

የዳዊት፡ወገኖች፡ነገሥታት፡የእግዚ አብሔርን፡ቃል፡ስሙ፤

፲፪፣ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ፍትሑ፡ፍትሐ፡በጽባህ፣

ለድኃው ፡ ፈጥናችሁ ፡ እውነት ፡ ፍረ ዱለት፡አለ፤

ወአንግፉ ፡ ዘተመሥጠ ፡ እምእደ ፡ ዘሄዶ፡ ከመ፡ ኢይንድድ ፡ መዓትየ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ወያውዒ፣

ሰውን፡ሁሉ፡ሊያጠፋ፡እንደ፡እሳት፡ ቁጣዬ፡እንዳይነድ፡ከቀማው፡ሰው፡ እጅ ፡ እውነት ፡ ፈርዳችሁ ፡ የተቀ ማውን፡የድኃውን፡ገንዘብ፡አስመል ሱለት፣

ወአልቦ ፡ ዘያጠፍዖ ፡ እምገጸ ፡ እከየ ፡ ምግባሮሙ፣

እምቢ ፡ ብትሉ ፡ ግን ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው፡የተነሣ፤አንድም፡እምገጸ፡ እከየ፡ምግባሪክሙ፡ይላል፤እምቢ፡ ብትሉ ፡ ግን ፡ ከክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ የተነሣ፣ ተቆጥቼ ፡ በናንተ ፡ የማመ ጣውን፡ገጸ፡መዓቴን፡አማልዶ፡የሚ መልሰው፡የለም፤

፲፫፣ ናሁ፡አነ፡ላዕሌከ፡ዘትነብር፡ውስተ፡ ቈላተ፡ኰኵሕ፡ወውስተ፡ገዳም፣

በቈላውና፡በምድረ፡በዳ፡ዋሻ፡ያለ፡ ጥምብ፡አሞራ፡በላይ፡መርግ፡በታች፡ ቀስት፡እንዳያገኘው፡ከዋሻው፡ሁኖ፡ እንዲታበይ፣ በዋሻህ ፡ ሁነህ ፡ በምት ታበይ፡ባንተም፡በመዓት፡አለሁብህ፡ አለ፤ሴዴቅያስ፤ናቡከደነፆር፡መጣ፡ መጣ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ ከዋሻ ፡ ገብቶ፡ነበርና፤

ይቤ፡እግዚአብሔር፡እለ፡ትብሉ፡አልቦ፡ዘያ ደነግፀነ፣

የሚያስደነግጠን፡ጠላት፡የለብንም፤

ወአልቦ፡ዘይበውእ፡ውስተ፡አብያቲነ።፤

ወደቤታችንም ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ የሚገ ባብን ፡ የለም ፡ የምትሉ ፡ እናንተንም ፡ በመዓት፡እጐበኛችኋለሁ፡አለ፡እግዚ አብሔር፤

፲፬፣ ወእዋኅያ፡ለኃጢአትክሙ፡በከመ፡ ፍሬ፡ምግባሪክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፣

እንደ፡ክፉ፡ሥራችሁም፡መጠን፡ኃጢ አታችሁን፡እጐበኛታለሁ፡አለ፤እመ ረምራታለሁ፡ሲል፡ነው፤

ወአነድድ፡እሳተ፡ውስተ፡አዕዋሚሃ፤

በዛፎችዋ፡ሁሉ፡እሳት፡አነድዳለሁ፤

ወትበልዕ፡ኵሎ፡ዘዓውዳ፣

እሳቲቱም፡በዙሪያዋ፡ያለውን፡ሁሉ፡ ታቃጥላለች፡አለ፡በቁሙ፤አንድም፡ ወአነድድ፡እሳተ፡ውስተ፡አዕዋሚሃ፡



ጦር ፤ መቅሠፍቲቱን ፡ በኃያላኑ ፡ አመጣለሁ፤ወትበልዕ፡ኵሎ፡ዘዓውዳ፡ ጦር ፡ መቅሠፍቲቱም ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉትን፡ሁሉ፡ታጠፋለች።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪

፩፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ሑር፡ረድ፡ውስተ፡ቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤

ወደ፡ይሁዳ፡ንጉሥ፡ወደሴዴቅያስ፡ ቤት፡ወርደህ፡ሂድ፤

ወንግር፡በህየ፡ዘ፡ነገረ፣

ይኸንንም ፡ ነገር ፡ በዚያው ፡ ቦታ፡ ተናገር፤ዘ፡ነገረ፡ያለውን፡ወደፊት፡ ያመጣል፤

፪፣ ወትብል፡ስማዕ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ ንጉሠ፡ይሁዳ፡ዘትነብር፡ውስተ፡መንበረ፡ ዳዊት፣

በአባትህ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የተቀ መጥህ፡የይሁዳ፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፡ የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስማ፡በለው፤

አንተ ፡ ወደቂቅከ ፡ ወሕዝብከሂ ፡ እለ ፡ ይበውኡ፡ወይወጽኡ፡እምዝ፡አንቀጽ፣

በዚህ፡በር፡የሚወጡ፡የሚገቡ፡ወገኖ ችህና ፡ አንተ ፡ የወለድካቸው ፡ ልጆችህም፡ይህነን፡ነገር፡ስሙ፤

፫፣ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡፤

ግበሩ፡ፍትሐ፡ወጽድቀ፤

ግበሩ ፡ ፍትሐ ፡ ጽድቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤ አንድም ፡ እንዳለም ፡ ይሆናል ፤ ግበሩ ፡ ፍትሐ ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ፡ ፍረዱ ፤ ወጽድቀ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ያዙ፤ እውነት ፡ ነገር ፡ ከያዙ ፡ ፍርድ ፡ አይጠፋምና፤

ወአንግፉ፡ዘተመሥጠ፡እምእደ፡ኀያዲሁ፤

እውነት፡ፈርዳችሁ፡ከቀማው፡ሰው፡ እጅ ፡ የተቀማውን ፡ የድኃውን ፡ ገንዘብ፡አስመልሱለት፤

ወኢትትአገሉ ፡ ፈላሴ ፡ ወእቤረ ፡ ወዕጓለ፡ ማውታ፤

መጻተኛውን፡ ባልቴቲቱንና ፡ እናት፡ አባቱ ፡ የሞቱበት ፡ ድኃ ፡ አደጉን፡ አትቀሙ፤

ወኢተአምፁ፡ወኢትክዐዉ፡ደመ፡ንጹሐ፡ በዝ፡ብሔር፣

በዚህም ፡ በምትኖሩበት ፡ አገር ፡ ሳላችሁ፡በግፍዕ፡የድኃውን፡ንጹሕ፡ ደም፡አታፍስሱ፤

፬፤ ወይእዜኒ፡እመ፡ትገብሩ፡ገቢረ፡ዘ፡ ነገረ፡ይበውዑ፡ውስተ፡ዛ፡አንቀጽ፡እለ፡ ይነብሩ፡ውስተ፡መንበረ፡ዳዊት፣

አሁንም፡ይህንን፡ነገር፡ፈጥናችሁ፡ ብታደርጉት፤አንድም፡ፈጥናችሁ፡ ካደረጋችሁት ፡ ነግሠው ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ የሚኖሩ ፡ ነገሥታቱ ፡ በዚች ፡ በር ፡ ሲወጡ ፡ ሲገቡ፡ይኖራሉ፤

ወይጼዓኑ ፡ ዲበ ፡ ሠረገላ ፡ ወአፍራስ ፡ ውእቱሂ፡ወደቂቁሂ፡ወሕዝቡሂ፣

እሱና ፡ ልጆቹ ፡ ወገኖቹም ፡ ሁነው ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ ይወጣሉ፡ይገባሉ፤

፭፤ ወእመሰ ፡ ኢትሰምዑ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ መሐልኩ ፡ በርእስየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ፡ይማስን፡ዝ፡ቤት፣

ይህነን ፡ ነገር ፡ አንሰማም ፡ ብላችሁ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እምቢ ፡ ካላችሁስ ፡ ይህ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ እልም ፡ ድርግም ፡ ብሎ ፡ እንዲጠፋ፡ሕያው፡እነ፡አማንየ፡ብዬ፡ በራሴ፡ማልኩ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፮፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ላዕለ፡ቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤

እግዚአብሔር ፡ በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ ቤት ፡ በመዓት ፡ አለሁበት፡ብሎ፡ተናግሯልና፤

ገለዓድ፡አንተ፡ሊተ፡መኰንኑ፡ለሊባኖስ፡

ገለዓድ ፡ የወል ፡ ስም ፡ ነው ፤ ቤተ፡ እስራኤል ፡ ደጋውን ፡ ቈላውን ፡ ስትገዛ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ለኔ፡ ትገዛልኝ ፡ ነበር ፤ አንድም ፡ ገለዓድ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ለኔ ፡ ስትገዛ ፡ አሕዛብን፡ትገዛ፡ነበር፤

እመ፡ኢረሰይኩከ፡መዝበረ፡ከመ፡አህጉር፡ ዘአልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴቶን፤

ዛሬ፡ግን፡ለኔ፡ካልተገዛህ፡እኔን፡ካላ መለከኝ፡ግን፡የሚኖርባቸው፡ሰው፡ እንደሌለ ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ እንደ ፡ ገሞራ፤ አንድም፡ሰው፡እንደማይኖር ባቸው፡እንደ፡ሰዶም፡እንደ፡ገሞራ፡ አገሮችህ ፡ የፈረስክ ፡ ባላደርግህ ፡ እስኪ፡ታይ፤

፯፤ ወአመጽእ ፡ ላዕሌከ ፡ ብእሴ ፡ ዘይሴ ርወከ፤

አንተን፡እልም፡ድርግም፡አድርጎ፡ የሚያጠፋ፡ሰውን፡አመጣብሃለሁ፤

ወይገዝም ፡ በጕድብ ፡ ኵሎ ፡ መሠንየ ፡ አርዝከ፡ወያነድድ፡በእሳት፤

ያም ፡ አንተን ፡ የሚያጠፋ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ በገጀሞ ፡ መልካም ፡ መል ካሙን ፡ ዛፍህን ፡ ቆርጦ ፡ ቆርጦ ፡ በእሳት፡ያቃጥለዋል፤

፰፤ ወይመጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ አሕ[ዛብ ፡]
እንተ፡ዛ፡ሀገር፡ላዕለ፡ዛ፡ሀገር፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ ክተት ፡ ሠራዊ[ቱ] ምታ፡ነጋሪት፡ብለው፡ብዙ፡አሕ[ዛብ] ወደዚች፡አገር፡ይመጡባታል፤

ወበህየ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካ[ልኡ] ይብሉ፡

ምስለ ፡ ካልዑ ፡ ካለ ፡ ይብል፤ ይብ[ል] ካለ ፡ አሐዱ ፡ ወካልዑ ፤ ባለ ፡ በ[...] ነበር፤ ሌሊት፡ምስለ፡መዓልት፡ይ[...] ፈልዖ፡ዕሩየ፡ለዘመን፡እንዳለው፡[...] ነው ፤ በዚያ ፡ ቦታ ፡ አንዱም ፡ አን[...] ካንዱም ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ ሁነ[ው] እንዲህ፡ይላሉ፤

ለምንት፡ከመዝ፡ረሰያ፡እግዚአብሔር[፡] ሀገር፡ዐባይ፤

ይቺን ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ኢየሩሳሌም[ን] እግዚአብሔር ፡ ለምን ፡ እንዲ[ህ] አድርጎ፡አጠፋት፡ይላሉ፤

፱፤ ወይብልዎሙ ፡ እስመ ፡ ኅደጉ፡[...] እግዚአብሔር፡አምላኮሙ፤

መላሾች ፡ የፈጣሪያቸው ፡ የእግዚ[አብ] ሔርን፡ሕግ፡ትተዋልና፤

ወሰገዱ፡ለአማልክተ፡ነኪር፤

ለከነዓን ፡ ጣዖታት ፤ አንድም ፡ ለ[...] ልክት ፡ ነኪራን ፡ ይላል ፤ ልዩ ፡ ል[...] ለሆኑ ፡ ጣዖታት ፡ ሰግደዋል[ና] ነኪራን፡ አላቸው ፤ ከእግዚአብሔ[ር] ነው፤አንድም፡ከወርቁ፡የብሩ፤ከ[...] የሸክላው ፡ ከሸክላው ፡ የእንጨ[ቱ] ከእንጨቱ፡የደንጊያው፡በሥራ፡[...] ልዩ፡ናቸውና፡ነኪራን፡አላቸው፤

ወተቀንዩ፡ሎሙ፡በህየ፤

በዚያውም ፡ ቦታ ፡ ተገዝተው [...]



[...] ኢትብክይዎ ፡ ለዘሞተ ፡ ወኢትላ [...]ዎ፤

[...]ተው፡ሰው፡አትዘኑለት፡አታልቅ [...]ት፤

[...]ይዎስ፡ለዘይወጽእ፤

[...]ገሩ ፡ ከርስቱ ፡ ከጕልቱ ፡ ከነገዱ ፡ [...]መዱ፡ተለይቶ፤ሳይሞት፡ተማርኮ፡ [...]ሄድ፡ሰው፡ለኢኮንያን፡እዘኑለት፤ [...]ቅሱለት፡እንጂ፤

[...]መ፡ኢይገብእ፡እንከ፡ወኢይሬኢ፡እንከ፡ [...]ረ፡ሙላዱ፤

[...]ማርኮ፡ከሄደ፡በኋላ፡ተመልሶ፡የተ [...]ደበትን፡አገር፡ርስቱን፡ጉልቱን፤ [...]ዱን፡ነገዱን፡አያይምና፤ሐተታ፡ [...]ትማ፡የሞተውስ፡መች፡ተመልሶ፡ [...]ል ፡ ቢሉ ፡ የሞተው ፡ የተለየ ፡ [...]ማም ፡ በሞት ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ግን ፡ [...]ሞት ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ [...]ና ፡ በጸናው ፡ ተናገረ ፤ ይህም ፡ [...]ስጭት፡ኃዘን፡አነጋገር፡ነው፤

[፲]፩፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ [...]ለ ፡ ሳሌም ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ንጉሠ ፡ [ይሁ]ዳ፡ዘነግሠ፡ህየንተ፡ኢዮስያስ፡አቡሁ፡ [...]ጽአ ፡ እምዝ ፡ ብሔር ፡ ኢይገብዕ ፡ [...]ከ፡ህየ፤

[...] ፡ እስመ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፤ እስመ ፡ [...]ኖን፣ ደወሎሙ ፡ እንዲል ፤ ባባቱ ፡ [ኢ]ዮስያስ፡ፈንታ፡ተተክቶ፡በነገሠ፡ [የተ]ወለደበት ፡ አገር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ [ተማ]ርኮ ፡ በሄደ ፡ በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ [ኢ]ዮስያስ፡ልጅ፡በሳሌም፡ተማርኮ፡ [ሄ]ደ፡በኋላ፡ወዳገሩ፡እንዳይመለስ፡ [ሳይ]መለስም ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ [...] ኢዮ

ስያስ ፡ ያልተወቀ ፡ ልጁ ፡ በነገሥት ፡ ያልተጻፈ፡በሕፁፃን፡የተጻፈ፡ይህም፡ ተወልዶ ፡ አድጎ፡ ሳይነግሥ ፡ ሙቷ ዋል ፤ ዘይነግሥ፡ ህየንቴሁ ፡ አለ ፤ ቢኖር፡ይነግሥ፡ነበርና፤አንድም፡የኤ ልያቄም ፡ የሴዴቅያስ ፡ ሁለተኛ ፡ ሁለተኛ፡ስማቸው፡ነው፤ላንድ፡ሰው፡ ሁለት ፡ ስም ፡ አለውና ፤ ዘነግሠ ፡ ህየንተ፡ኢዮስያስ፡አቡሁ፡የተመቸ፤

፲፪፤ እስመ ፡ ይመውት ፡ በብሔር ፡ ኀበ ፡ ፄወውዎ፤

ማርከው ፡ በወሰዱበት ፡ አገር ፡ ይሞታልና፤

ወኢይሬኢ፡እንከ፡ብሔሮ፤

ተመልሶም ፡ የተወለደበትን ፡ አገር ፡ አያይምና፤

፲፫፤ አሌ፡ሎቱ፡ዘየሐንፅ፡ቤቶ፡በዐመፃ፡ ወጽርሖ፡ዘእንበለ፡ጽድቅ፤

ሰርቆ ፡ ቀምቶ ፡ በድኃው ፡ ከብት ፡ እልፍኝና፡አዳራሹን፡ለሚሠራ፡ሰው፡ ወዮለት፤ቤቶ፡ያለው፡እልፍኝ፡ነው፤ ጽርሕ፡ያለው፡አዳራሽ፡ነው፤ቅዱስ፡ ጽርሕከ ፡ ወመንክር ፡ በጽድቅ ፡ እንዲል ፣ አዳራሽ ፡ ሲል ፤ አንድም ፡ ቤት፡ ያለው ፡ አዳራሽ ፡ ነው ፤ ጽርሕ ፡ ያለው ፡ እልፍኝ ፡ ነው ፤ ደቀ ፡ ጽርሕ ፡ እንዲል፤

ወቢያሂ፡ይቀኒ፡በከንቱ፡ወኢይሁቦ፡አስቦ፤

ባልጀራውንም ፡ በከንቱ ፡ ደመወዝ ፡ ሳይሰጥ ፡ በከንቱ ፡ ለሚገዛው ፡ ሰው ፡ ወዮለት፤

፲፬፤ወይቤ፡ሐነፅኩ፡ሊተ፡ቤተ፡ዘዓቢይ፡ አምጣኑ፡ወጽርሑ፤

ሠርቶም፡ከጨረሰ፡በኋላ፡ለወንድሞቹ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለባልንጀሮቹ ፤ ዘዓቢይ ፡ አምጣኑ ፡ ቂመቱ ፤ ወጽርሑ ፡ ወርዱ ፡ ታላቅ ፡ ስፋቱ፡ታላቅ፡ቤት፡ሠራሁ፡ይላል።

ወመሳክዊ፡ወጠፈሩ፡ዘአርዝ፤

ጠፈሩ ፡ የዋንዛ ፡ የዝግባ ፡ የሚሆን፡ መስኮት፡ያለው፡ቤት፡ሠራሁ፡ይላል። አንድም ፡ መተርጉሙ ፡ መስኮት ፡ ያለው ፡ ጠፈሩ ፡ የዋንዛ ፡ የዝግባ ፡ የሚሆን፡ቤት፡ሠራ፡ይላል።

ወቀብዖ፡በሠሌዳ፤

አልፎ ፡ አልፎም ፡ የዋንዛ ፡ የዝግባ ፡ ሠሌዳ ፡ አደረገበት ፤ አንድም ፡ ወቀብዖ፡ ለሠሌዳ ፡ ይላል ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያለውን ፡ ሠሌዳ ፡ ቀለም ፡ ቀባው።

፲፭፤በኑ፡ትነግሥ፡

እንዲህ ፡ ማድረግህ ፡ በውኑ ፡ ለዘላለሙ፡ነግሠህ፡ትኖራለህን።

እስመ፡አንተ፡ሐነዕከ፡በአርዘ፡አቡከ፡

ያባትህን፡ዛፍ፡እየቆረጥህ፤አንድም፡ ባባትህ፡ቤት፡ላይ፡እልፍኝ፡አዳራሽ፡ ሠርተሃልና።

አኮኑ፡ይበልእ፡ወይሰቲ፡ዘይገብር፡ጽድቀ፡ ወርትዓ፡

እውነት ፡ ነገርን ፡ የሚናገር ፡ የቀና ፡ ሥራ ፡ የሚሠራማ ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ በጤና፡ሲበላ፡ሲጠጣ፡የሚኖር፡አይደ ለምን ፤ አንድም፡ እውነት ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ የቀና ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ፡ ሰው፡ ገንዘቡን ፡ በጤና፡ ይበላል ፡ ይጠጣልና።

አሚሃ፡ይሤኒ፡ሎቱ፡

ጠኢሚሃ ፡ ሰል ፡ ነው ፤ ያገኘዋ፡

በጎው፡ነገር፡ይደረግለታልና።

፲፮፤ ፍታሕ፡ፍትሐ፡ነዳይ፡ወምስ

የድኃውንና ፡ የጦም ፡ አዳሪ

ፍርድ፡ አውጥተህ ፡ አውር

አስበህ፡እውነት፡ፍርድ፡ፍረድ፤

የሚለው ፡ ያመት ፡ ልብስ ፡ የዕ

ጉርስ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ በሌ

የሚቸገር፡ነው፤ምስኪን፡የሚ

ያመት ፡ ልብስ ፡ የዕለት ፡ ጉ

የሌለው፡ጦም፡አዳሪውን፡ነው፤

አሜሃ፡ሠናይ፡ውእቱ፡አእምሮ፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በዚያ፡ወራት፡በጎ፡ሥራ፡የሠራ

ያ፡የሠራው፡በጎ፡ሥራ፡በጎ፡አ

ያሰኘዋል፡አለ፡እግዚአብሔር።

፲፯፤ ናሁ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ አዕይ

ወልብከሂ፤

ክፉውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዓይንህ

አይደለም፡አለ፤ከፍና፡ዝቅ፡አደ

አትኩሮ ፡ ያያልና ፤ አንድም ፡ ዓ

ልቡናህ፡አለ፤ክፉውን፡ነገር፡ይ

ታልና፤ ልቡናህም ፡ ክፉ ፡ ነውና፤

ጠማማ ፡ ክፉ ፡ ነውና፤ አንደ

ጥመትን፡ክፋትን፡ያስባልና።

ዳዕሙ፡ውስተ፡ትዕግልት፤

ወደ፡ቅሚያ፡ያስባል፡እንጂ።

ወውስተ፡ክዒወ፡ደመ፡ጻድቅ፤

የድኃውን ፡ የነቢዩን ፡ ደም ፡ በግ

ለማፍሰስ፡ይመለከታል፡እንጂ።

ወውስተ፡ግፍዕ፤

ግፍ፡ለመሥራት።

ወውስተ፡ቀትል፤



ዝንቱ፡ዳዕሙ፡ግብርከ፤

ዳዕሙና ፡ ዳዕሙ ፡ አንድ ፡ ወገን፤ ሥራህ፡ይህ፡ብቻ፡ነው፡እንጂ፤ኢኮነ፡ ሠናየ፡አዕይንቲከ፤

፲፰፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፤

ስለክፉው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡አለ።

ላዕለ፡ኢዮአቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ ይሁዳ፤

ንጉሠ ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም ፡ ይቀጥኋል፤ ክፋትን ፡ ክህደትን ፡ አብነት፡ሁኖ፡በሚያሠራ፡በይሁዳው፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ፡ በኢዮ አቄም፡በመዓት፡አለሁበት፡አለ።

አሌ፡ሎ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘአልቦ፡ዘይበክዮ፤

ተማርኮ፡በሄደ፡ጊዜ፡የሚያዝንለት፡ የሚያለቅስለት፡ለሌለ፤አንድም፡በተ ማረከበት፡አገር፡በሞተ፡ጊዜ፡የሚያ ዝንለት፡የሚያለቅስለት፡ለሌለ፡ለኢ ዮአቄም፡ለሴዴቅያስ፡ወዮለት።

ወኢይብልዎ፡ወይ፡እግዚእነ፡ወይ፡እኁነ፡

በተማረከበትም፡አገር፡በሞተ፡ጊዜ፡ ወይ፡ጌታችን፡ወይ፡ወንድማችን፡ ብለው፡አያለቅሱለትም።

፲፱፤ወይቀብርዎ፡መቃብረ፡መሪረ፡

ምኑን፡ሲል፡ነው፤በተናቀ፡መቃብር፡ ይቀብሩታል።

ወይጠበልልዎ፡ብወዲፈት፡በድኖ፡

መቃብረ፡ምኑን፡ያለውን፡አመጣ፤ ሬሳውንም ፡ በቍራጭ ፡ ዳውጃ ፡ በክልስ፡ማቅ፡ገንዘው፡ይቀብሩታል።

ወይገድፍዎ ፡ አፍአ ፡ እምአንቀጸ ፡ ኢየሩ

ኤልያቄምን፡ከኢየሩሳሌም፡በአፍአ፡ ባለ ፡ በገነተ ፡ አዛ ፡ ይቀብሩታል፤ አንድም፡ሴዴቅያስን፡ከኢየሩሳሌም፡ በአፍአ ፡ በባቢሎን ፡ ይቀብሩታል፤ (ይጥሉታል)።

፳፤ ዕርጊ ፡ ውስተ ፡ ሊባኖስ ፡ ወጽርሒ፡

ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ይሆንልሽ ፡ እንደሆነ፡ እስቲ ፡ ወደዳገው ፡ ወጥተሽ፡ጩሂ።

ወከልሂ፡ውስተ፡ባሳን፤

እስቲ ፡ ወደቆላውም ፡ አሰምተሽ ፡ ጩሂ፤ አንድም፤ ዕርጊ ፡ ውስተ ፡ ሊባኖስ፡ ወጽርሒ፡ ወከልሂ፡ ውስተ፡ ባሳን፤ሊባኖስም፡ባሳንም፡ያላቸው፡ አገሮች ፡ ናቸው፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ይረዱሽ፡ያዝኑልሽ፡እንደሆነ፡እስቲ፡ ሊባኖስ፡ባሳን፡ወደሚባሉ፡አገሮች፡ ጩሂ።

አውይዊ ፡ በቃልኪ ፡ ወጽርሒ ፡ ውስተ ፡ ማዕዶተ፡ባሕር፤

በባሕር፡ማዶ፡ወዳሉትም፡አገሮች፡ እርዱኝ፡አድኑኝ፡ብለሽ፡በቃልሽ፡ ጩኸት፡አሰሚ።

እስመ፡ተቀጥቀጡ፡ኵሎሙ፡ፍቁራንኪ፤

ምነዋ፡እኔ፡አልዋጋምና፡ነው፡ይህን፡ የምትለኝ፡ትይኝ፡እንደሆነ፡ባጭር፡ ታጥቀው፡ዘገር፡ነጥቀው፡የሚዋጉ፡ አርበኞችሽ፡ሁሉ፡እልም፡ድርግም፡ ብለው፡ጠፍተዋልና።

፳፩፤ወነገሩኪ፡ኃሣረኪ፤

ከኔ፡አስቀድመው፡የነበሩ፡ነቢያትም፡ የሚያገኝሽን ፡ መከራ ፡ ገልጠው ፡ ነገሩሽ፤ አንድም ፡ ወነገርኩኪ ፡ ኃሣረኪ፡እኔም፡እንዳቅሜ፡የሚያገ ኝሽን፡መከራ፡ገልጬ፡ነገርኩሽ፡አስ ተማርኩሽ።

www.ethiopianorthodox.org

ወትብሊ፡እንብየ፡ኢይሰምዕ፡
አንቺ ፡ ግን ፡ እምቢ ፡ አልሰማም፤
አንድም፡አልሰማም፡እምቢ፡አልሽ፤

ዝንቱ፡ዳዕሙ፡ፍኖትኪ፡እምንዕስኪ፡
ዳዕሙን፡ታገሠው፤ይህ፡ክፉ፡ሥራሽ፡
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ነው፤ አንድም ፡
ከጥንት፡ጀምሮ፡የምትሠሪው፡ክፉ፡
ሥራሽ፡ይህ፡ብቻ፡ነው፤አንድም፡
ይህ፡ እንጂ ፡ ነው፤ አንድም ፡ የምት
ሠሪው፡ይህ፡ክፉ፡ሥራሽ፡እንጂ፡
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ነው፤ ሐተታ ፡
ይህንስ፡ ለምን ፡ ይሻዋል ፡ ቢሉ ፡
ክፋትሽ ፡ ዛሬ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡
ክፋትሽ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፡
ማለት፡ነው፤

ወዐበይኪ፡ሰሚዐ፡ቃልየ፡
በነቢያት ፡ አድሬ ፡ የምነግርሽንም ፡
ቃሌን፡አልሰማም፡እምቢ፡አልሽ፤

፳፪፤ ወለኵሎሙ፡ኖሎትኪ፡ነፍሳት፡ይነ
ሥእዎሙ፡
የሚመክሩሽ፡የሚያስተምሩሽ፡መም
ህራኖችሽንም፤አንድም፡የሚሰሩሽ፤
የሚቀጡሽ ፡ ነገሥታቶችሽንም ረቂ
ቃን ፡ የሚሆኑ ፡ መቅሠፍታቱ ፡
አጠፏቸው፤

ወለመሐዛንኪ፡ይጼውዎሙ፡
ባጭር ፡ ታጥቀው ፡ ዘገር ፡ ነጥቀው ፡
የሚዋጉልሽ ፡ አርበኞችሽንም ፡
ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚጠ
ፉበት፡ቦታ፡ጠርቶ፡ይወስዳቸዋል፤
አንድም ፡ ይጼውውዎሙ ፡ ይላል ፡
አሕዛብ፡ባጭር፡ታጥቀው፡ዘገር፡
ነጥቀው፡ማርከው፡ይወስዷቸዋል፤

ወትትኀፈሪ፡ሶቢሃ፡
ያንጊዜ፡አንቺ፡ብቻሽን፡ቀርተሽ
ታፍሪያለሽ፤

፳፫፤ ወተኀሥሪ ፡ እምኵሎሙ ፡ እለ
ያፈቅሩኪ፡እንተ፡ትነብሪ፡ውስተ፡ሊባኖስ
በደጋውም ፤ በቆላውም ፡ ሁነሽ
ጠላት፡ ጠፍቶልሽ፡ትኖሪ፡የነበርሽ
አንቺ፤አንድም፡ሊባኖስ፡ከተማው
ነው ፤ በከተማሽ ፡ ሁነሽ ፡ ጠላት
ጠፍቶልሽ፡ተዘልለሽ፡ትኖሪ፡የነበረ
አንቺ ፡ ከሚወዱሽ ፡ ካርበኞችሽ
ተለይተሽ ፤ አንድም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ
በመከራው፡ተይዘሽ፡ታፍሪያለሽ፤

ወታስቆቅዊ፡ውስተ፡አርዝ፡
ጣዖት፡ታመልኪበት፡በነበረው፡ዛፍ
እግር፡ተቀምጠሽ፤አንድም፡አታ
ልትሽ፡ዛፍሽ፡ተቆርጦብሽ፡ያነን
አይተሽ፡ታለቅሻለሽ፤

ምንተ፡ወሀበኪ፡ሶበ፡አኀዘኪ፡ማኅምም
ከመ፡እንተ፡ትወልድ፡
ለመውለድ፡የደረሰች፡ሴት፡በምጡ
ተይዛ፡እንድትጨነቅ፡እንደዚያ፡የሚ
ያስጨንቅ ፡ መከራ ፡ በያዘሽ ፡ ጊዜ
ቀድሞ ፡ የምታመልኪው ፡ የነበረ
ጣዖት፡ምን፡አደረገልሽ?ምን፡ሰጠሽ

፳፬፤ ሕያው፡አነ፡ይቤ፡እግዚአብሔር
ከመ፡ኢትሄሉ፡እንከ፡ኢኮንያን፡ወልደ
ኢዮአቄም፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ማኅተመ፡ላዕለ
እዴየ፡ዘየማን፡
ንጉሠ ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም
ይቀጥኣል፤የይሁዳው፡ንጉሥ፡የኢዮ
አቄም፡ልጅ፡ኢኮንያን፡በቀኝ፡እጅ
ያለ፡ሐቲም፡ቀለበት፡በዚያው፡ጸንቶ
እንዲኖር፡አንተም፡እንግዲህ፡ወዲያ



ነኝ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወኢይሬስየከ፡እንተ፡ባቲ፡ከደንኩከ፡
ያ፡በጣት፡ያለ፡ቀለበት፡ተጣብቆ፡
እንዲኖር ፡ እኔም ፡ በረድዔቴ ፡
ተጠብቀህ ፡ እንድትኖር ፡ አላደር
ግህም፤

፳፭፤ ወአገብአከ ፡ ውስተ ፡ እዴሆሙ ፡
ለእለ፡የኀሥሥዋ፡ለነፍስከ፡ወውስተ፡እደ፡
እለ፡ፈራህከ፡እምገጾሙ፡ወውስተ፡እደ፡ናቡ
ከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ወውስተ፡እደ፡ከላ
ውዴዎን፡
እኔስ፡ሰውነትህን፡ለጥፋት፡በሚፈ
ልጉት፡ሰዎች፡እጅ፡አንተም፡ከገጸ፡
መዓታቸው፡የተነሣ፡በምትፈራቸው፡
ሰዎች፡እጅ፡በሠራዊቱና፡በባቢሎኑ፡
ንጉሥ፡በናቡከደነፆር፡እጅም፡እጥል
ሃለሁ፡እንጂ፤

፳፮፤ ወእዌርወከ፡ኪያከ፡ወእመከ፡እንተ፡
ወለደተከ፡ውስተ፡ብሔር፡ካልእ፡ኀበ፡ኢተ
ወለድክሙ፡ቦቱ፡
የወለደችህ ፡ እናትህንና ፡ አንተን፤
አንድም ፡ ምስለ ፡ እምከ ፡ እንተ ፡
ወለደተከ ፡ ይላል ፤ አንተን ፡ ከወለ
ደችህ፡ከናትህ፡ጋራ፡ወዳልተወለዳች
ሁበት፡ወደሌላ፡አገር፡አስማርኬ፡እሰ
ዳችኋለሁ፤

ወበህየ፡ትመውቱ፡
በዚያውም፡በተማረካችሁበት፡አገር፡
አንተና፡እናትህ፡ትሞታላችሁ፤

፳፯፤ ወውስተ፡ብሔር፡እንተ፡ትትሜነይ፡
ነፍስክሙ፡ኢትገብኡ፡እንከ፡ህየ፡
ልቡናችሁ፡እመለሳለሁ፡ብላ፡ወደም
ትመኛት ፡ ወዳገራችሁ ፡ ወደኢየሩ

፳፰፤ ኀሥረ፡ኢኮንያን፡ወኮነ፡ከመ፡
ግተት፡ ዘለምንት ፡ ኢይበቍዕ ፡ ወኢይት
ፈቀድ፡
ጌታም ፡ በነቢይ ፡ አድሮ ፡ እንዲህ ፡
አድርጎ፡ከዘለፈው፡በኋላ፡ኢኮንያን፡
ጐሰቈለ፤ለምንም፡ለምን፡ነገር፡እንደማ
ይረባ፡እንደማይጠቅም፡ግትቻም፡ሆነ፤

እስመ ፡ ገደፍዎ ፡ ወወረውዎ ፡ ሎቱ ፡ ወለ
ዘርዑ፡ውስተ፡ብሔር፡ዘኢየአምር፡
እሱንና፡ልጆቹን፡ቀድሞ፡ወደማያ
ውቀው፡ወደአሕዛብ፡አገር፡ጠላቶች፡
ማርከው፡ወስደውታልና፤

## ጉባዔ፤

፳፱፤ ምድር፡ምድር፡ምድር፡ስምዒ፡
ቃለ፡እግዚአብሔር፡ፈጣሪኪ፡
ምድር፡ብሎ፡ያሰማታል፤የፈጣሪሽ፡
የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስሚ፡አላት፤
ሐተታ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡
ተናገረው ፤ ለአጽንዖተ ፡ ነገር ፡ ነው፤
አንድም፡እንደሦስት፡ምስክር፡ከዚያ፡
ኖኅ ፡ ስምዓኒ ፡ ስምዓኒ ፡ ስምዓኒ ፡
ሥልሰ፡ እንዳለ፤ አንድም ፡ በሀገ
ራቸው፡ደጊመ፡ቃል፡ልማድ፡ነውና፡
መላልሶ፡ተናገረ፤

፴፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ጸሐፎ፡ለዝ፡ብእሲ፡
ከመ፡ዘሞተ፡ያለበት፡ነው፤ይህንንስ፡
ሴዴቅያስን፡ኢኮንያንን፡እንደሞተ፡
ሰው፡ቍጠረው፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡ኢይሤራህ፡በመዋዕሊሁ፡
ባለ፡ዘመኑ፡ሁሉ፡አይከናወንምና፤
አንድም፡መዋዕሊሁ፡ይላል፤ዘመኑ፡
አይከናወንለትምና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢይኄራሀ፡እምዘርዐ፡ዘይነብር፡ውስተ፡ መንበረ፡ዳዊት፤

ከልጆቹ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ነግሦ ፡ ባባቱ፡በዳዊት፡ዙፋን፡ተቀምጦ፡አይ ከናወንምና፤

ወአልቦ ፡ መኰንን ፡ እንከ ፡ ለይሁዳ ፡ በይሁዳም ፡ ነግሦ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ፍርድ ፡ ጠንቅቆ ፡ ድኃ ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ የለምና፤ አንድም ፡ እምዘርዐ፡ ዘይነብር ፡ በመንበረ ፡ ዳዊት፡ መኰንነ ፡ እንከ ፡ ለይሁዳ ፡ ብለው ፡ ይገጥሙታል፤ ከልጆቹ ፡ አንዱም፡አንዱ፡በይሁዳ፡ገዥ፡ሁኖ፡ ፍርድ ፡ ጠንቅቆ ፡ ድኃ ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር፡የሚገዛ፡መኰንን፡የለምና፤

## ምዕራፍ ፡ ፴፫

፩፤ ወይ፡ሎሙ፡ለኖሎት፡ቀታልያን፡እለ፡ ትዘርዉ፡አባግዓ፡መርዔትየ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፤

ተዘርኡ፡ተዘርዉ፡ይላል፤መምህራኑ፡ እንምክር ፡ እናስተምር ፡ ብላችሁ፤ አንድም ፡ ነገሥታቱ ፡ እንሥራ ፡ እንቅጣ ፡ ብላችሁ ፡ ወገኖቼ ፡ እስራ ኤልን ፡ አስማርካችሁ ፡ ለሰደዳች ኋቸው፡ለናንተ፡ለመምህራኑና፡ለነገ ሥታቱ፡ወዮታ፡ይገባችኋል፡ለናንተ፡ ነው፤አንድም፡ወዮታ፡ለናንተ፡ነው፡ አለ፡በላቸው፡አለኝ፡እግዚአብሔር፤

፬፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፡በእንተ፡ኖሎት፡ እለ፡ርእይዎሙ፡ለሕዝብየ፡አንትሙ፡ዘረው ክምዎሙ ፡ ለአባግዕየ ፡ ወሰደድክምዎሙ ፡ ወኢሐለይክምዎሙ፡አንትሙ፤

ይህን፡ሁሉ፡አድርገው፡አብዝተው፡

ስለበደሉት፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡ ዚአብሔር ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤል የሚጠብቁ ፡ የመምህራኑን ፡ የነ ታቱን፡ነገር፡እንዲህ፡አለ፤ምን፡ ወገኖቼ፡እስራኤልን፡አንመክር፡ ስተምር፡አንሠራ፡አንቀጣ፡ብላች ዘረውክምዎሙ ፡ እና ፡ ሰደድ ዎሙ፡አንድ፡ወገን፤ከሀገራቸው፡ ማርካችሁ፡ሰደዳችኋቸው፤ስንኳ ልትጠብቋቸው፡ካሉ፡ከሌሉ፡አ ችኋቸውም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ናሁ፡አነ፡እዋሕየክሙ፡በከመ፡እከየ፡ ሪክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

እዋህየክሙ፡ባለው፡እትቤቀለከ ይላል፤እንደተናገሩ፡ይመልሱ፤ ተለሙ ፡ ያርሱ ፡ እንዲሉ፤ እኔ እናንተን ፡ እንደክፉ ፡ ሥራች መጠን ፡ በመዓት ፡ እጐበኛችኋ አንድም፡በክፉ፡ሥራችሁ፡ተበ አጠፋችኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔ

፫፤ ወአነ፡አስተጋብኦሙ፡ለእለ፡ ሕዝብየ፡እምኵሉ፡በሐውርት፡ኀበ፡ ክዎሙ፡ወኀበ፡ወሰድክዎሙ፡ህየ፤

ለናንት፡ይባላችሁ፡እንጂ፡አስማ ከሰደድኩበት፡አገር፡ከሞት፡የ ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ እሰበ ዋለሁ፤

ወአገብኦሙ፡ውስተ፡ፒአቶሙ፤

ከተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ሰብ አምጥቼ ፡ ወደመስካቸው ፡ አ ዋለሁ፤ ሐተታ ፡ አባግዕየ ፡ ብሏ ነበርና፡ውስተ፡ፒያቶሙ፡አለ፡እ ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ወደቦ ሀገራቸው፡እመልሳቸዋለሁ፡ሰ

በዝኀ፡ወይመልዑ፤
ንት ፡ ሀገራቸውም ፡ ሁነው ፡
ተው፡ይመላሉ፤

፬ ወእሠይም፡ሎሙ፡ኖሎተ፡እለ፡ይርዕ
ሙ፤

ያ፡በኋላ፡ግን፡ነቅተው፡ተግተው፡
ጠብቋቸው ፡ ጠባቆችን ፡ እሾ
ሁ ፡ አለ፤ ነቅተው ፡ ተግተው ፡
መክሩ ፡ የሚያስተምሩ፡ መምህ
ን፤ ነቅተው፡ተግተው፡የሚሠሩ፡
ቀጡ ፡ ነገሥታቱን ፡ እሾምላች
ሁ፤

ኢይፈርሁ፡እንከ፡ወኢይደነግፁ፡ይቤ፡እግ
ብሔር፡

ምህራኑና፡ነገሥታቱ፡መኳንንቱ፡
ፈሩ፡ሳይደነግጡ፡ይጠብቋቸዋል፡
ለ፡እግዚአብሔር፤አንድም፡በዚያ፡
ራት ፡ እስራኤል ፡ ኃጢአት ፡
ርተን፡ ጣዖት ፡ አምልከን ፡ ፈጣሪያ
ን፡በድለን፡መከራ፡ይመጣብናል፤
ሕዛብ ፡ መጥተው ፡ ያጠፉናል ፡
ለው ፡ አይፈሩም፤ አይደነግጡም ፡
ለ፡እግዚአብሔር፤

፬፤ ናሁ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግዚ
ብሔር፤

ግዚአብሔር፡እንዲህ፡ያል፡(ያለ)፡
ራት፡ይመጣል፡አለ፤

አቀውም፡ለዳዊት፡ሠርፀ፡ጽድቅ፤
ዳዊት ፡ ወገን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡
ሚጠብቅ ፡ ዘሩባቤልን ፡ አስነሣለ
ለሁ፤

ይነግሥ፡ንጉሥ፡ዘይሔሊ፡ወይገብር፡
ድቀ፡ወርትዐ፤

ስቦ ፡ ጽድቀ ፡ እውነት ፡ ነገርን፤
ርትዐ፡የቀና፡ፍርድን፡የሚያደርግ፡

የሚፈርድ፤አንድም፡ጽድቀ፡ኢታም ልክን ፡ ወርትዐ ፡ ዘጠኙን፤ አንድም ፡ ጽድቀ ፡ ፲ቱ ፡ ቃላትን ፡ ወርትዐ ፡ መላው፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ዘሩባቤል፡ይነግሣል፤

፲፮፡ ወበመዋዕሊሁ፡ይድኅን፡ይሁዳ፡

በዘሩባቤልም ፡ ዘመን ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ከመከራው፡ይድናል፤

ወእስራኤልኒ፡ይነብር፡ተአሚኖ፡

ዓሥሩም ፡ ነገድ ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶለት ፡ ተዘልሎ፡ይኖራል፤

ወዝ፡ውእቱ፡ስሙ፡ዘሰመየ፡እግዚአብሔር፡ ኢዮሴዴቅ፡በውስተ፡ነቢያት፤

ስሙም፡ነቢያት፡በሚጠብቁት፡ሕግ፡ ዘንድ ፡ ስሙን ፡ ያወጣለት ፡ እግዚአ ብሔር፡ጽድቅነ፡ብሎ፡ነው፤አንድም፡ ወእሠይሞ ፡ ኖሎተ ፡ እለ ፡ ይርዕ ይዎሙ፤ ካ፰ሽ ፡ ካ፰፻ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የሚጠብቋቸው፡ሐዋርያትን፡፸፡አር ድዕትን ፡ መምህራንን ፡ ለምዕመናን ፡ እሾምላቸዋለሁ፤ወይርዕይዎሙ፤እነ ሱም፡መክረው፡አስተምረው፡በነፍስ፡ ይጠብቋቸዋል፤ወኢይፈርሁ፡እንከ፡ ወኢይደነግፁ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤ በዚያ፡ ወራት ፡ ሐዋርያት ፤ ፸ አር ድዕት ፡ መምህራን ፤ ሊቃውንት ፡ ፀበዐ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ ይነሣናል ፡ ብለው ፡ አይፈሩም ፤ አንድም ፡ ምዕ መናን ፡ ፀበዐ፡ አጋንንት፡ ድል ፡ ይነሣል ፡ ብለው ፡ አይፈሩም፤ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡ያል፡ወራት፡አሁን፡ ይመጣል ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤ አቀውም ፡ ለዳዊት ፡ ሠርፀ ፡ ጽድቅ ፤ ከዳዊት ፡ ወገን ፡ ክርስቶስን ፡ አሥነ



www.ethiopianorthodox.org

ሣለሁ ፡ አለ ፤ ወይነግሥ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይሔሊ ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ ፡ ወርትአ፡ አስቦ ፡ ጽድቀ ፡ ጽድቀ ፡ አሚንን ፡ ወርትዐ ፡ ርትዓተ ፡ ልቡናን ፡ ለሰው ፡ የሚሰጥ፤ አንድም ፡ አስቦ ፡ ጽድቀ ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ ወርትዐ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ለሰው ፡ የሚሠራ ፡ ክርስቶስን ፡ አነግ ሣለሁ፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ይድኅን ፡ ይሁዳ ፡ ወ፳ኤልኒ ፡ ይነብር ፡ ተአሚኖ፤ ክርስቶስም ፡ ሰው ፡ በሆነበት ፡ ወራት ፡ ይሁዳ ፡ ዘነፍስ ፡ ከፀብአ ፡ አጋንንት ፡ ይድናል ፤ እሥራኤል ፡ ዘነፍስም ፡ የነፍስ ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶለት ፡ በነፍስ ፡ ተዘልሎ ፡ ይኖራል፤ ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ስሙ ፡ ዘሰመዮ ፡ እግዚአብሔር ፤ ኢዮ ሴዴቅ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያወጣለት ፡ ስሙ ፡ ይህ ፡ ነው፤ ኢዮሴዴቅ ፡ ኢየሱስ ፡ ጽድቅነ ፡ በውስተ ፡ ነቢያት ፤ ነቢያት ፡ በተናገሩት ፡ ትንቢት ፡ ዘንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ጽድቅነ ፡ ማለት ፡ ነው፤

፯፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያል ፡ (ያለ) ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፡ አለ፤

፰፡ ወኢይብሉ ፡ እንከ ፡ ሕያው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ዘአውጽአሙ ፡ ለቤተ ፡ ፳ኤል ፡ እምድረ ፡ ግብፅ ፡ ዳዕሙ ፡ ሕያው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ዘአዕረጎሙ ፡ ወአውጽአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ዘርዓ ፡ ፳ኤል ፡ እምድረ ፡ ሰሜን ፡ ወእምኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ኀበ ፡ ወሰዶሙ ፡ ወአ ግብዖሙ ፡ ውስተ ፡ ብሔሮሙ ፡ ህየ፡

የእስራኤልን ፡ ወገኖች ፡ ከግብፅ ፡ አገር ፡ ያወጣቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በትኩሱ ፡ አይምሉም፤

የእስራኤልን ፡ ወገኖች ፡ አስማርኮ ፡ ከወሰደበት ፡ ሁሉና ፡ ከባቢሎን ፡ ያወጣቸው አብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብ በዘገየው ፡ ይምላሉ ፡ እንጂ፤ አ ከባቢሎን ፡ አገር ፡ አስማርኮ ደበት ፡ ከያገሩም ፡ ሁሉ ፡ የእስራ ወገኖች ፡ ያወጣቸው ፡ እግዚአ ሕያው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በት ይምላሉ ፡ እንጂ ፡ ከግብፅ ፡ የ፳ኤልን ፡ ወገኖች ፡ ያወጣቸው አብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብ በዘገየው ፡ አይምሉም፤

ወአግብአሙ ፡ ውስተ ፡ ብሔሮሙ ፡ ህ ጥንት ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ወደ ራቸው ፡ መለሳቸው፤ አንድም ብሔሮሙ ፡ ለነቢር ፡ ይላል ራቸው ፡ ሊኖሩ ፡ ወደጥንት ራቸው ፡ መለሳቸው፤

፱፡ ለነቢያትኒ ፡ ተቀጥቀጠኒ ፡ በላዕሌየ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ለነቢያ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ የተነሣ ፡ በ ልቡናዬ ፡ ተቀጠቀጠብኝ ፡ አ ሣብኝ ፡ ወደቀብኝ፤

ወአንቀልቀለ ፡ ኵሉ ፡ አዕጽምትየ፤

ሰውነቴም ፡ ሁሉ ፡ በመከራው ዋወጠ፤

ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ቅጥቁጥ፤

በመከራው ፡ እንደተቀጠቀጠ ሆንኩ፤

ወከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘያተነትኖ ፡ ስካ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ስብሐተ ፡ ክብሩ፤

ከእግዚአብሔር ፡ ክብሩ ፡ ...



የተነሣ ፡ ከክብሩም ፡ መገለጥ ፡ የተነሣ ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ የወይን ፡ ስካር ፡ እንደ ሚያፍገመግመው ፡ ሰው ፡ ሆንኩ፤

፲፡ እስመ ፡ ዝሙቶሙ ፡ መልዓ ፡ ምድረ፤

ከኃጢአት ፡ ከጣዖት ፡ መለስናቸው፤ አንድም ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ መለየታቸው ፡ ምድርን ፡ በምድር ፡ መልቷልና፤ አንድም ፡ ምልዓ ፡ ምድር ፡ በዓለሙ ፡ ምሉ ፡ ነውና፤ ሐተታ ፡ ዝሙት ፡ የሚለው ፡ የሴትና፤ የወንድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ እግዚአ ብሔር ፡ የማይወደውን ፡ የሚጠላውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መሥራትን ፡ ዝሙት ፡ ይለዋል፤

ወእምገጸ ፡ መርገም ፡ ለሀወት ፡ ምድር፤

ከድርቁም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ አለ ቀሰች ፡ አለ ፤ የሰዎችን ፡ ለምድር ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ፤

ወዓብረ ፡ ኵሉ ፡ ወፍር ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም፤

በምድረ ፡ በዳ ፡ ያለው ፡ መሠማር ያውም ፡ ሁሉ ፡ ድርቅ ፡ ሆነ፤ አንድም ፡ ለሀወት ፡ ምድር ፡ እምገጸ ፡ መርገም፤ ከድርቅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ አለቀሰች ፡ አለ ፤ የወል ፡ ነው ፤ ወዓብረ ፡ ኵሉ ፡ ወፍር ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያለው ፡ መሰማርያውም ፡ ሁሉ ፡ ደረቀ፤

ወማሰነ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሮሙ ፡ ወፃማሆሙ፤

ፈጽመው ፡ የደከሙበትም ፡ ሁሉ ፡ በድርቁ ፡ ጠፋ፤ አንድም ፡ ተግባሮሙ ፡ አዝርእታቸው ፤ ወፃማሆሙ ፡ አትክል ታቸው ፡ ቤታቸው ፡ አጥራቸው ፤ አን ድም ፡ ተግባሮሙ ፤ ፊት ፡ የገባው ፡ አዝ መራቸው ፤ ወፃማሆሙ ፡ በዱር ፡ ያለው ፡ አዝመራቸው ፡ ጠፋባቸው፤

እኩሉ ፡ ከመዝ፤ ...

ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አይደ ለምን ፡ ከመዝ ፡ ባለው ፡ ከማሁ ፡ ይላል፤

፲፩፡ እስመ ፡ ነቢይ ፡ ወካህን ፡ ረኵሱ፤

ስንኳን ፡ ሕዝቡ ፡ ትንቢት ፡ የሚና ገረው ፡ ነቢዩ ፡ የሚመክረው ፡ የሚያስ ተምረው ፡ ካህኑ ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ረክሰዋልና፤ አንድም ፡ እስመን ፡ ትቶ ፡ ከማሁ ፡ ነቢይኒ ፡ ወካህንኒ ፡ ረኵሱ ፡ ይላል፤ ሕዝቡስ ፡ ይቅርና ፡ ነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ አሁን ፡ እንደተ ናገርኩት ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ የረከሱ ፡ አይደለምን፤

ወበቤትየኒ ፡ ረከብኩ ፡ እከዮሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፤

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በምመሰገንባት ፡ ቤቴ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚያመል ኩትን ፡ ጣዖት ፡ ቋሞ ፡ አገኘሁት ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤ ምናሴ ፡ ባ፳ቱ በ፯ቱ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ሥዕለ ፡ ንስር ፡ አቁሞ ፡ ነበርና ፡ ያንንም ፡ እከይ ፡ አለው፤ በግብሩ ፡ ነው፤ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ነገር ፡ የሚያ መጣባቸው ፡ ስለሆነ፤ አንድም ፡ እነሱ ፡ በክፋታቸው ፡ ፀንተው ፡ ስላቆሙት ፡ እንዲህ ፡ አለ፤ እከይ ፡ አለው፤

፲፪፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ዳሕፀ ፡ ይከውን ፡ ፍኖ ቶሙ ፡ ወጽልመተ፤

ዳሕፀ ፡ ወጽልመተ ፡ ይከውን ፡ ፍኖቶሙ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተማርከው ፡ የሚሄዱበት ፡ ጎዳናቸው ፡ ድጥ ፡ ጨለማ ፡ ይሆንባቸዋል ፡ አለ፤ መማረካቸው ፡ በሐምሌ ፡ በዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ነውና ፡ ይህስ ፡ አይደለም፤ በኛ ፡ ክረምት ፡ ቢሆን ፡ በነሱ ፡ በጋ ፡ ነውና ፡ ብሎ ፡ በድጥ ፡ በጨለማ ፡ የሚሄድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሰው ፡ መከራ ፡ እንዲጸናበት ፡ እነ
ሱንም ፡ ተማርከው ፡ ሲሄዱ ፡ መከራ ፡
ይጸናባቸዋል ፡ ሲል ፡ ነው ።

ወይወድቁ ፡ ቦቱ ፡
በመከራውም ፡ ተይዘው ፡ ይነሡ
በታል ፤ ይወድቁበታል ።

ወናሁ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ ላዕሌሆሙ ፡
እኔም ፡ ቍጣዬን ፡ አብዝቼ ፡ በነሱ ፡ አመ
ጣባቸዋለሁ ።

ወበመዓት ፡ እዋህዮሙ ፡
በመዓቴም ፡ እጐበኛቸዋለሁ ።

፲፫ ፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነቢያተ ፡
ሰማርያሂ ፡ ርኢኩ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ዘተነበዩ ፡
በስምየ ፡ ለበዓል ፡ ወአስሐትዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡
ኟኤል ፤
ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርኢኩ ፡
ኃጢአቶሙ ፡ ለነቢያተ ፡ ሰማርያ ፡
ዘተነበዩ ፡ በስምየ ፡ ለበዓል ፡ ወአስሐ
ትዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ኟኤል ፡ ሲል ፡
ነው ፤ ለጣዖቱ ፡ በስሜ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር ፡ ዘኰሎ ፡ ይመልክ ፡
ብለው ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩ ፡ ወገኖቼ ፡
እስራኤልንም ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ብለው ፡
ያሳቱዋቸው ፡ የሰማርያ ፡ ነቢያተ ፡
ሐሰትን ፡ ኃጢአት ፡ በዝቶ ፡ ሲሠራ ፡
አየሁት ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤
አንድም ፡ እንዳለም ፡ ይሆናል ፤
ለነቢያተ ፡ ሰማርያ ፤ ሰማርያ ፡ ባለው ፡
በነቢያተ ፡ ሰማርያ ፡ ይላል ፤ ከመዝ ፡
ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡
ትንቢተ ፡ ሐሰት ፡ የተናገሩበት ፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤልንም ፡ ሰላም ፡
ሰላም ፡ እያሉ ፡ ያሳቱበት ፡ ኃጢአታ
ቸውን ፡ በሰማርያ ፡ ነቢያተ ፡ ...

፲፬ ፤ ወለነቢያተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ር...
ዝሙቶሙ ፡ መደንግፀ ፤
መደንግፀ ፡ ዝሙቶሙ ፡ ለነቢያተ ፡ ...
ሩሳሌም ፡ ርኢኩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በኢ...
ሳሌም ፡ ያሉ ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ የ...
ስደነግጥ ፡ በኃጢአት ፡ በጣዖት ፡ ...
ሥናቸውን ፡ በዝቶ ፡ ተሠርቶ ፡ አየሁ...
አንድም ፡ ወበነቢያተ ፡ ኢየሩሳሌ...
ርኢኩ ፡ ዝሙቶሙ ፡ መደንግፀ ፤ ፡ በ...
ሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት...
ላይ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ዝሙታቸ...
በዝቶ ፡ ተሠርቶ ፡ አየሁት ፤

ወየሐውሩ ፡ በሐሰት ፤
ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በሐሰ...
ነገራቸው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ...
አንድም ፡ በሐሰት ፡ በጣዖቱ ፡ ጸንተ...
ይኖራሉ ፤ ፡ አንድም ፡ ወደ ፡ ሐሰ...
ወደጣዖቱ ፡ ተነሥተው ፡ ይኖራሉ...
ያለው ፡ ወደ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ወተመይ...
በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፤

ወይትአኀዙ ፡ እደዊሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢ...
መየጡ ፡ እምፍኖተ ፡ እከዮሙ ፤
ከክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ እንዳይመለ...
ለመሐላ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘ...
ወደ ፡ ጣዖቱ ፡ ይሄዳሉ ፡ አለ ፡ በቁ...
አንድም ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ የተያያዘ ፡ ...
ተፋፍሮ ፡ ወደኋላ ፡ እንዳይመለ...
እነሱም ፡ ተፋፍረው ፡ ከክፉ ፡ ሥ...
ቸው ፡ አይመለሱም ፤

ወኮኑኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ከመ ፡ ሰዶም ፡ ወእ...
ይነብርዋ ፡ ከመ ፡ ገሞራ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩባት ፡ ወገና...
ሁሉ ፡ ክፋት ፡ በመሥራት ፡ እ...
ሰዶም ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ሰዎች ፡ ሆኑብ...



...ሆንን ፡ ክፋታቸውንም ፡ አብዝተው ፡
...ሠሩ ፡ አምጻኤ ፡ ዓለማት ፡ ወላዴ ፡
...ፈረታት ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአት ፡
...ሚያሠሯቸው ፡ ጣዖት ፡ በሚያስመል
...ቸው ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ በመዓት ፡
...ሁባቸው ፡ አለ ፤

...፡ አነ ፡ እሴስዮሙ ፡ ሕማመ ፡ ወእሰትዮሙ ፡
...የ ፡ ዕጕስታር ፡
...ቢያተ ፡ ሐሰት ፡ መከረው ፡ አስተ
...ረው ፡ ኃጢአት ፡ ስላሠሯቸው ፡
...ዖት ፡ ስላስመለኳቸው ፡ እነሱም ፡ በኀ
...አታቸው ፡ በጣዖታቸው ፡ ስለበ
...ሉኝ ፡ እኔም ፡ መከራውን ፡ አበላቸ
...ለሁ ፤ እመግባቸዋለሁ ፤ የሬት ፡
...ውሀም ፡ አጠጣቸዋለሁ ፡ አለ ፤ አሁን ፡
...ከራ ፡ የሚበላ ፡ የሬቱም ፡ ውሀ ፡
...ሚጠጣ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፤ በመከራ ፡
...ዜ ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ ደስ ፡ እንዳ
...ሰኘ ፡ ደስ ፡ አላሰኛቸውም ፡ ሲል ፡
...ው ፤ አንድም ፡ የድርቅ ፡ እህል ፡ እመግ
...ቸዋለሁ ፤ የድርቅ ፡ ውሀ ፡ አጠጣቸ
...ለሁ ፤

...ስመ ፡ እምነቢያተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጽአ ፡
...ኵስ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፤
...ኢየሩሳሌም ፡ ከሚኖሩ ፡ ከነቢያተ ፡
...ሐሰት ፡ ርኵስ ፡ ቤል ፡ ኃጢአቱ ፤ ርኩስ ፡
...ሊል ፡ ጣዖቱ ፡ ተገኝቷልና ፤

፲፭ ፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃያል ፡
...ትስምዑ ፡ ነገሮሙ ፡ ለነቢያት ፡ እለ ፡
...ትኔበዩ ፡ ለክሙ ፡ እምከንቶሆሙ ፤
...ንቱ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፤
...ንድም ፡ እምልቡናሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
...ንቱ ፡ ከሆነ ፡ ከልቡናቸው ፡
...ንቅተው ፡ የሐሰት ፡ ትንቢት ፡ የሚያ
... ሐሰትን ፡

ትምህርት ፡ አትስሙ ፤ ሐተታ ፡ ምነዋ ፡
መስማትማ ፡ ጆሮ ፡ መባረቅትንስ ፡
ይሰማ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፤ ኢትእመኑ ፡
ሲል ፡ ነው ፤

እሙንቱ ፡ ለክሙ ፡ ይነግሩ ፡ ዘኢኮነ ፡ እምአፈ ፡
እግዚአብሔር ፤
እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምነዋ ፡
ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እነሱስ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ያልተገኘውን ፡ ቃል ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይነግ
ሩችኋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፤

፲፮ ፤ ወይብልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ያምዕዑ ፡ ቃለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ይከውን ፡ ለክሙ ፤
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለሚማሩ ፡
ሰዎችም ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይደረግላ
ችኋል ፡ ይሏቸዋልና ፤ አንድም ፡ ለእለ ፡
ያምዕዑ ፡ ባለው ፡ ለእለ ፡ የዓብዩ ፡
ይላል ፤ የተናገራችሁት ፡ ትንቢት ፡ ላይ
ደረግልን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
አንማርም ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ ለሚሉ
ዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይደ
ረግላችኋል ፡ ይሉዋቸዋልና ፤

ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በግዕዞሙ ፤
በክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ ጸንተው ፡ ለሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፤

ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በኄጋየ ፡ ልቦሙ ፤
ከልቡናቸው ፡ አንቅተው ፡ በሚሠሩት ፡
በደል ፡ ጸንተውም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፤

ወይብልዎሙ ፡ ኢይረክበክሙ ፡ እኩይ ፤
ክፉ ፡ ነገር ፡ አያገኛችሁም ፡ ይሉዋ
ቸዋል ፤

፲፯ ፤ እስመ ፡ መኑ ፡ ዘይቀውም ፡ ውስተ ፡
ምክረ ፡ እግዚአብሔር ፤

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ማነው ? ማነውና፤

ወይሬኢ፡ወይሰምዕ፡ቃሎ፡
ቃሉንስ ፡ አስተውሎ ፡ የሚሰማው ፡ ማነው? ፡ ማነውና ፡ አስተውሎ ፡ የሚሰማው ፡ አለ ፡ ሳያስተውሉ ፡ መስማት፡አለና፤

መኑ፡አጽምዓ፡ቃሎ፡ወሰምዓ፡
ይሬኢ ፡ ያለውን ፡ አጽምዓ ፤ ይሰምዕ ፡ ያለውን፡ሰምዐ፡ብሎ፡ደገመው፤

፲፱፡ ናሁ፡ይመጽእ፡ድልቅልቅ፡እምገጸ፡እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር ፡ ከገጸ ፡ መዓቱ ፡ የተነሣ ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ አሁን ፡ ይመጣል፤ አንድም ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል፤ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ ንውጽውጽታ፡ይመጣል፡ሲል፡ነው፤

ወይመጽእ ፡ መቅሠፍት ፡ ከመ ፡ ያንቀልቅሎሙ፡ወይገፍትዖሙ፡
ከመቅሠፍቱም ፡ በመከራው ፡ ሊያነዋውጣቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ ይመጣባቸዋል፤

ወይገፈትዖሙ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ኃጥኣን፡ወይመጽእሙ፤
መቅሠፍቱም ፡ መጥቶ ፡ ኃጥአንን ፡ ራሳቸውን ፡ ያጠፋቸዋል፤ ራሳቸውን ፡ አለ ፡ በልጅ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ይዘገያልና፤ አንድም ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ኃጥአን ፡ ጥፋቱ ፡ በኃጥአን ፡ ባለቆቻቸው ፡ ይጀመራል፤አንድም፡ላዕለ፡ ርእሰ፡ኃጥአን፡ያለውን፡ትቶ፡ወይገፈ
[illegible]

፳፡ ወኢይትመየጥ ፡ መዓተ ፡ እግዚአብሔር፡እስከ፡ይገብር፡ዘንተ፡
እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቶ ፡ ያመጣው ፡ መዓቱ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ እስኪያደርግ፡ድረስ፤

ወያቀውም፡ዘሐለየ፡በልቡ፡
በልቡናው ፡ ያሰበውንም ፡ ሁሉ ፡ አጽንቶ ፡ እስኪያደርገው ፡ ድረስ ፡ መዓቱ፡አይመለስም፤

፳፩፡ ወበደኃሪ፡መዋዕል፡የአምርዎ፡ዘአፈነውክዎሙ፡ለነቢያት፡
በፍጻሜ ፡ ዘመናቸው ፡ ግን ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ አስተምሩ ፡ ብዬ ፡ እንዳላልኳቸው፡ነገሩን፡ያውቁታል፤

ለሊሆሙ፡የሐውሩ፡ወዘኢይቤልዎሙ፤
እነሱ ፡ ወደእስራኤል ፡ ሂደው ፡ አስተምሩ ፡ ያላልኳቸውን ፡ ያላዘዝኳቸውን፡ያስተምራሉ፤

ወለሊሆሙ፡ይትኔበዩ፡
እኔ፡ያላዘዝኳቸውን፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡እያሉ፡ያስተምራሉ፤

፳፪፡ ሶበሰ ፡ ቆሙ ፡ በቃልየ ፡ ወሰምዑ፡ ነገርየ ፡ ይሚጥዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ እምእኩይ፡ምግባሮሙ፤
በቃሌ ፡ ከጸኑ ፤ ነገሬንስ ፡ ከሰሙ ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ መክረው ፡ አስተምረው ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ይመልሷቸው፤

፳፫፡ አምላክ፡ቅሩብ፡አነ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ወኢኮንኩ፡አምላከ፡ርኁቀ፡
እንዲህ ፡ እንጂ ፡ የምናደርግ ፡ ስንለምንህ ፡ ባትሰማን ፡ ብትርቀን ፡ ነው፡
[illegible]



ሩቅ፡አምላክ፡አይደለሁም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፬፡ ቦሁ፡ሰብእ፡ይትኀባዕ፡እምኔየ፡
ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ ሰው ፡ ከኔ ፡ በውኑ፡ ይሠወራልን፤

ወቦሁ፡ኀበ፡ይሤወሩ፡እምኔየ፡
ሰዎችስ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ከኔ ፡ የሚሠወሩበት ፡ ቦታ ፡ በውኑ ፡ አላቸውን፤

ወኢይሬኢኑ፡አነ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እኔስ፡ከተሠወሩበት፡ቦታ፡መርምሬ፡ አላያቸውምን፤

አኮኑ፡አነ፡ዘመላዕኩ፡ሰማየ፡ወምድረ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እንሠወርስ ፡ ቢሉ ፡ ከየት ፡ ቦታ ፡ ሁነው፡ ይሠወራሉ ፤ ሰማይን ፡ የዘረጋሁ፤ምድርን፡ያረጋሁ፡እኔ፡አይደለሁምን፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፭፡ ሰማዕኩኬ፡ዘይብሉ፡ነቢያት፡
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ የሚናገሩትንስ ፡ ነገር፡ሰማሁት፤

ወይትኔበዩ፡በስምየ፡ነገረ፡ሐሰት፡
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ፡ ሐሰት፡ትንቢትን፡ይናገራሉ፤

ሐለምነ፡ሐለምነ፡ይቤሉ፡
በትንቢተ ፡ ሐሰቱም ፡ ላይ ፡ አለምን ፡ አለምን፡ይላሉ፤

፳፮፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ቦ፡ ዘውስተ ፡ ልበ፡ ነቢያት፡ትንቢተ፡ሐሰት፡
ዝንቱ፡ትንቢቱ፡ሐሰት፡ሲል፡ነው፤
ቤ፡ያላገኙትን፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ

ትንቢተ ፡ ሐሰታቸው ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት፡ልቡና፡ጸንቶ፡የሚኖር፡እስከ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው? አንድም ፡ እስከ ፡ ምንትኑ ፡ ይላል ፤ ይህ ፡ ሐሰት ፡ ትንቢታቸው ፡ በልቡናቸው ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር፡ምን፡እስኪሆኑ፡ድረስ፡ነው?

፳፯፡ወእለ፡ይትኔበዩ፡እምፈቃደ፡ልቦሙ፡ ዘሐለዩ ፡ ከመ ፡ ያርስዕዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ስምየ፡ በሕልሞሙ ፡ ዘይትናገሩ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ፡ ካልዑ ፡ በከመ ፡ ረስዑ ፡ አበዊሆሙ ፡ ስምየ፡እንበይነ፡በዓል፡
ቀድሞ ፡ አባቶቻቸው ፡ ስለጣዖቱ ፡ ፍቅር ፡ ብለው ፡ ስሜን ፡ እንደዘነጉት ፡ ዛሬም ፡ ከልቡናቸው ፡ አስበው ፡ አንቅተው ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ማስተማራቸው ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ካንዱ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ አለምን ፡ አለምን ፡ ብለው ፡ በተናገሩት ፡ ነገራቸው ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ስሜን ፡ ያዘነጓቸው፡ዘንድ፡ነው፤

፳፰፡ ነቢይ ፡ ዘኀቤሁ ፡ ሕልም ፡ ይነግር ፡ ሕልሞ፡
ሐሰተኛ ፡ ሕልም ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝበት ፡ ነቢየ ፡ ሐሰትም ፡ ሐሰተኛ ፡ ሕልሙን ፡ ከልቡናው ፡ አንቅቶ ፡ ይናገራል፤

ወዘሂ ፡ ቃልየ ፡ ኀቤሁ ፡ ይነግር ፡ ቃልየ ፡ በጽድቅ፡
እውነተኛ ፡ ቃሌ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝበት፡ነቢየ፡ጽድቅ፡ግን፡እውነተኛ፡ ቃሌን ፡ በውነት ፡ ይናገረዋል ፤ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ነቢየ ፡ ጽድቅ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፤ ለሁለቱም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምንተ ፡ ይከውን ፡ ኀሠር ፡ በኀበ ፡ ሥርናይ ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ነገር ፡ ግን ፡ በስንዴ ፡ ምርት ፡ ዘንድ ፡ ገለባው ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለው ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደዚሁስ ፡ ሁሉ ፡ በነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ዘንድ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው፤ ምን፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለው፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ነቢይ፡ዘነቢሁ፡ሕልም፡ይነግር፡ሕልሞ፡

ሕልሞ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፤ እንድም ፡ ምንተ ፡ ይከውን ፡ ሥርናይ፡ በኀበ ፡ ኀሠር ፡ ይላል ፤ የስንዴ ፡ ምርት ፡ በገለባው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለው ፡ ምንድነው፡ አለ ፤ ከገለባውማ፡ ምርቱ ፡ የሚበልጥ ፡ አይደለም ፡ ሲል፡ ነው ፤ እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ከነቢየ ፡ ሐሰቱማ፡ነቢየ፡ጽድቁ፡የሚበልጥ፡አይደለምን፡አለ፤

ወዘሂ፡ ቃልየ ፡ ነቢሁ፡ ይነግር ፡ ቃልየ ፡ በጽድቅ፡

የእኔ ፡ ቃል ፡ ያደረበት ፡ ነቢይ ፡ እውነት፡ትንቢትን፡ይናገራል፤

፳፱፡ አኮኑ፡ከመ፡እሳት፡ነገርየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ወከመ ፡ መፍጽሕ ፡ ዘይፈጽሕ ፡ ኰኵሐ፡

አኮኑ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ነገርየ ፡ ወከመ ፡ መፍጽሕ ፡ ዘይፈጽሕ ፡ ኰኵሐ ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ሲል፡ነው፤በነቢያተ፡ ጽድቅ ፡ አድሬ ፡ የተናገርኩት ፡ ነገሬ ፡ እንደሚያቃጥል፡እሳት፡ደንጊያውን፡ እንደሚፈረካክስ ፡ እንደሚገማምስ ፡ እንደ ፡ ድጅኖ ፡ አይደለምን ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ እናንተ፡እንደገለባው፡እንደ፡ደንጊያው፡ጠፊ ፡ ናችሁ ፤ የኔ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ እንደ፡ እሳቱ፡እንደ፡ድጅኖው፡አጥፊ፡ነው፡ ሲል፡ነው፤

፴፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ናሁ፡አነ፡ላዕለ፡ነቢያት፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡እለ፡ይሰርቁ፡ ቃልየ፡አሐዱ፡አሐዱ፡በኀበ፡ካልዑ፡

ላዕለ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ይሰርቁ ፡ ቃልየ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ በኀበ ፡ ካልዑ ፡ ሲል፡ ነው ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ፡ ሁኖ፡ ቃሌን ፡ በሚሰርቁ ፡ በነቢያተ፡ ሐሰት ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ብለውና፡ ሐሰት ፡ ትምህርት ፡ ስላስተማሩ ፡ በመዓት ፡ አለሁባቸው፡ አለ፡ እግዚአብሔር ፤ አንድም ፡ እንዳለም፡ ይሆናል፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ብለው ፡ ሐሰት ፡ ትምህርት ፡ ስላስተማሩ ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ በመዓት፡ አለሁባቸው ፡ አለ ፤ ይሰርቁ ፡ ቃልየ፡ እነዚሁም ፡ በመዓት ፡ አለሁባቸው፡ ያልኳቸው፡አንዱም፡አንዱ፡ካንዱም፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ ሁነው፡ ቃሌን ፡ የሚሰርቁ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤እግዚአብሔር፡አስተምሩ፡ያላቸውን፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ እያሉ ፡ ያስተምራሉና ፡ እለ፡ ይሰርቁ፡ ቃልየ፡ አለ፤ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ በነቢያተ ፡ ጽድቅ ፡ አድሮ ፡ ይሆናል፡ ይደረጋል፡ያለውን፡እነሱ፡አይሆንም፡ አይደረግም ፤ አንድም ፡ በነቢያተ፡ ጽድቅ ፡ አድሮ፡ አይሆንም ፡ አይደረግም ፡ ያለውን ፡ እነሱ ፡ ይሆናል፡ ይደረጋል ፡ ብለው፡ እያሉ ፡ ሰርቀው፡ ያስተምራሉና ፡ እንዲህ ፡ አለ፡ አንድም፡እለ፡ይሰርቁ፡ቃልየ፡ያላቸው፡ አጋንንት ፡ ናቸው ፡ ከጌታ ፡ ቃል፡



ምሕረትም ፡ መዓትም፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ፡ ኪሩቤል ፡ ይሰማሉ፤ ከኪሩቤል ፡ ታዝዘው ለሱራፌል ፡ ይነግራሉ ፤ ሱራፌል ፡ ለሚካኤል ፡ ለገብርኤል ፡ ለሩፋኤል፡ይናገራሉ፤እነዚያ፡ሄደው፡ ለነቢያተ ፡ ጽድቅ ፡ ይናገራሉ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በአየር ፡ ያሉ ፡ አጋንንት ፡ ያነን ፡ ሰምተው ፡ ለነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ይናገራሉ ፤ ነቢያተ ፡ ሐሰትም ፡ ከአጋንንት ፡ ሰምተው ፡ ይናገራሉና ፤ አጋንንትን፡እለ፡ይሰርቁ፡ቃልየ፡አላቸው፤ ዛሬ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተመከረውን ፡ ምክር ፡ ያማከረው ፡ ሳይኖር፡ ባላገር፡ሰው፡ዛሬ፡ከቤተ፡መንግሥት፡ እንዲህ ፡ ተመከረ፤ ፡ እንዲህ ፡ ተደረገ ፡ እያለ፡እንዲያወራ፤

፴፩፡ ናሁ፡አነ፡ላዕለ፡ነቢያት፡ይቤ፡እግዚአብሔር ፡ እለ ፡ ያወጽኡ ፡ ተነብዮ ፡ ልሳኖሙ፤

ላዕለ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ያወጽኡ ፡ ተነብዮ፡ ልሳኖሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ካፋቸው ፡ ያገኙትን ፡ አውጥተው ፡ በሚናገሩ ፡ በነቢያት፤ አንድም ፡ ተነብዮ ፡ እምልሳኖሙ፡ይላል፤ከልቡናቸው፡ሳይሆን፡ ካፋቸው ፡ አንቅተው፡ ሐሰት ፡ ትንቢት፡ በሚናገሩ ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት፡ በመዓት፡ አለሁባቸው ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤

ወይብሉ፡ተረፈ፡እግዚአብሔር፤

ይኸንንም ፡ ካፋቸው ፡ አውጥተው ፡ የሚናገሩትን፡ትንቢተ፡ሐሰት፡ከእግዚአብሔር፡የተገኘ፡ነው፡አሉ፤

፴፪፡ ናሁ፡ አነ፡ ላዕለ፡ ነቢያት፡ እለ ፡ ይትኔበዩ፡ሕልመ፡ሐሰት፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ የሐሰቱን ፡ ሕልም ፡ አለምን ፤ አለምን ፡ በሚሉ፡ በነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ በመዓት ፡ አለሁባቸው፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወይነግርዎሙ፡ለሕዝብየ፡

ይኸንኑም ፡ ሐሰቱን ፡ ሕልም ፡ ለወገኖቼ ፡ ለእስራኤል ፡ አለምን ፡ አለምን፡ብለው፡ይነግሯቸዋል፤

ወያስሕትዎሙ፡በሐሰቶሙ፡ወበጌጋዮሙ፤

ሐሰት ፡ ተናግረው ፡ በሚበድሉት ፡ ፍጹም ፡ በደላቸውም ፡ ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ያስቱዋቸዋል ፤ አንድም ፡ በሐሰቶሙ ፡ በሐሰት ፡ ነገራቸው፤ ወበጌጋዮሙ ፡ በበደሉትም ፡ በደላቸው ፡ ያስቱዋቸዋል፤

ወአንሰ፡ኢፈነውክዎሙ፡ወኢአዘዝክዎሙ፤

እኔ፡ግን፡አስተምሩ፡ትንቢተ፡ሐሰት፡ ተናገሩ ፡ ብዬ ፡ አዝገቤ ፡ አላክኋቸውም፤

ወአልቦ፡ዘይበቍዕዎሙ፡ለሕዝብየ፡ወኢይረብሕዎሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

እነሱ፡ግን፡በሐሰት፡ትምህርታቸው፡ በሐሰት፡ትንቢታቸው፡ወገኖቼ፡እስራኤልን፡አልረቡዋቸውም፤አልጠቀሙዋቸውም፡አለ፡እግዚአብሔር፤ አንድም ፡ የረቡዋቸው ፡ የጠቀሙዋቸው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤

፴፫፤ ወለእመ ፡ ተስዕሉከ ፡ ሕዝብ ፡ አው ፡ ነቢይ፡አው፡ካህን፡ወይቤሉከ፡ምንተ፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በዚያ ፡ ወራት ፡ ሕዝቡም ፡ ነቢየ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጽድቂም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ምን ፡ ተናገረብን ፤ ምን ፡ አናገ
ረብን ፡ (ተናገረ) ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁህ፤

ወትብሎሙ ፡ በእንቲአክሙ ፡ ውእቱ ፡ ገ ፡
ነገር፡

በናንተስ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡
ነው ፡ ገ ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡ ያመጣል፤

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እነጽሐክሙ ፡ ወእገድ
ፈክሙ፤

እግዚአብሔርስ ፡ አንሥቼ ፡ እጥላች
ኋለሁ ፡ ብሏል ፡ በላቸው ፤ አንሥቶ ፡
የጣሉት ፡ እንዲጎዳ ፡ እንዲጠፋ ፡ በእና
ንተም ፡ የሚጎዳ ፡ የሚያጠፋ ፡
መቅሥፍት ፡ አመጣለሁ ፡ ሲል ፡ ነው፤

፴፬፤ ለነቢይሂ ፡ ወለካህንሂ ፡ ወለሕዝብሂ ፡
ዘይቤ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እትቤቀሎ ፡
ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወለቤቱሂ፤

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባለው ፡ ተረፈ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይላል ፤ ይህ ፡ የተ
ገኘው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
የሚያስተምር ፡ ነቢዩ ፡ ሐሰቱንና ፡
ካህኑ ፡ ጣዖቱን ፤ እትቤቀሎ ፡ ለውእቱ ፡
ብእሲ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ አስቀድሜ ፡ እበቀ
ለዋለሁ ፤ ወለቤቱሂ ፤ ከሱም ፡ በኋላ ፡
ወገኑን ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ አጠፋለሁ፤

፴፭፤ ከመዝ ፡ በሉ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡
ካልዑ ፡ ወ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ እኁሁ ፡ ምንተ ፡
ተሰጥወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወምንተ ፡ ይቤ ፡ እግ
ዚአብሔር፤

እናንተስ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ባልን
ጀራው ፡ ካንዱም ፡ ካንዱ ፡ ባልን
ጀራው ፡ ጋራ ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡
ወንድሙ፤ ካንዱም ፡ ካንዱ ፡ ከወን
ድሙ ፡ ጋራ ፡ ሁናችሁ ፤ እግዚአብሔር ፡
በነቢያት ፡ አድሮ ፡ ምን ፡ አናገረብን ፤
እግዚአብሔርስ ፡ በኛ ፡ ምን ፡ ተናገ
ረብን ፡ በሉ፤

፴፮፤ ወተረፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢት
ዝክሩ ፡ እንከ፤

እናንተስ ፡ ከልቡናችሁ ፡ አንቅታችሁ ፡
ካፋችሁ ፡ አውጥታችሁ ፡ የምትናገ
ሩትን ፡ ትንቢተ ፡ ሐሰት ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ አትበሉ፤

እስመ ፡ ተረፈ ፡ ይከውን ፡ ለብእሲ ፡ ነገሩ፤

ከልቡናው ፡ አንቅቶ ፡ የተናገረውን ፡
ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ የሚያስተምር ፡ ሰው ፡ ነገሩ ፡
ልብ ፡ ወለድ ፡ ይሆንበታልና፤

ወገፍታዕክሙ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው፤

እናንተስ ፡ የሕያወ ፡ ባሕርይ ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ነገር ፡ አገለባበጣችሁት ፡
አለ፤ ትንቢተ ፡ ሐሰቱን ፡ ትንቢተ ፡
ጽድቅ ፤ ትንቢተ ፡ ጽድቁን ፡ ትንቢተ ፡
ሐሰት ፡ አድርጋችሁ ፡ ተናገራችሁት፤

እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ፤

ይኸውም ፡ ማገለባበጣችሁ ፡ ሊታ
ወቅ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳያድር
ባችሁ ፡ አቸናፊ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አድሮብናል ፡ ትላላችሁ፤

፴፯፤ ወከመዝ ፡ በሉ ፡ ኀበ ፡ ነቢይ ፡ ምንተ ፡
ተሠጥወከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወምንተ ፡ ቃለ ፡
እግዚአብሔር፤

በነቢዩ ፡ ጽድቁ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡ አለህ፤
በኛስ ፡ የተናገረብን ፡ ቃሉ ፡ ምንድነው ፡
በሉ ፡ ብላችሁ ፡ ጠይቁ፤



፴፰፤ ወለእመ ፡ ተረፈ ፡ እግዚአብሔር ፡
ትብ(ቢ)ሉ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግ
ዚአብሔር፤

ከፈጣሪያችሁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያላገ
ኛችሁትን ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡
የተገኘ ፡ ነው ፡ ካላችሁ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ፤

እስመ ፡ ትብሉ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ ተረፈ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

ከእግዚአብሔር ፡ ያላገኛችሁትን ፡
ይህነን ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተ
ገኘ ፡ ነው ፡ ትላላችሁና፤

ለአከ ፡ ኀቤክሙ፤

ይህነን ፡ እንዳትሉ ፡ ነቢያትን ፡
ወደናንተ ፡ ላክሁባችሁ፤

ወእቤለክሙ ፡ ኢትበሉ ፡ ተረፈ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

በነቢያትም ፡ አድሬ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ያልተገኘውን ፡ ነገር ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ አትበሉ ፡
አልኳችሁ ፤ አንድም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡
ጠቅልሎ ፡ ይናገረዋል ፤ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ያልተገኘውን ፡ ነገር ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ አትበሉ ፡ ብዬ ፡
ነቢያትን ፡ ካህናትን ፡ ወደናንተ ፡
ላክኋቸው ፡ አለ፤

፴፱፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አነ ፡ እነሥአክሙ ፡
ወእነጽሐክሙ፤

ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያል
ተገኘውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡
ነው ፡ እያሉ ፡ ስላስተማሩዋችሁ ፡
እናንተም ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ቃል ፡
እውነት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ስለተቀበ
ላችሁ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አንሥቼ ፡ እጥላ
ችኋለሁ ፡ አለ ፤ አንሥቶ ፡ የጣሉት ፡
እንዲጎዳ ፡ የሚጎዳ ፡ የሚያጠፋ ፡
መከራ ፡ አመጣባችኋለሁ ፡ ሲል ፡ ነው፤

ወለሃገር ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ወሀብኩ ፡ ለክሙ ፡ ወለ
አበዊክሙ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽየ፤

ከገጸ ፡ መዓቴም ፡ የተነሣ ፡ ዛሬ ፡
ለእናንተ ፡ ቀድሞ ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ የሰ
ጠኋትንም ፡ አገር ፡ አንሥቼ ፡ እጥላ
ታለሁ፤

፵፤ ወእሁበክሙ ፡ ኀሣረ ፡ ወጽዕለተ ፡
ዘለዓለም ፡ ዘኢይትረሣዕ፤

ለዘላለሙ ፡ የማይዘነጋ ፡ ስድቡንና ፡
ጉስቍልናችሁን ፡ አመጣባችኋለሁ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬፤

### ጉባኤ፤

፩፤ ወአርአየኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክልዔተ ፡
አዕጹቀ ፡ በለስ ፡ ንቡራነ ፡ ቅድመ ፡ ቤተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እምድኅረ ፡ አፍለሶ ፡ ናቡክደነፆር ፡
ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ለኢኮንያን ፡ ወልደ
ኢዮአቄም ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ፤ ወለመላእክተ ፡
ይሁዳ ፡ ወለኪነትሂ ፡ ወለሙቁሓን ፡ ወለቢ
ያሙሂ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ወወሰዶሙ ፡
ባቢሎን፤

የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡክደነፆር ፡
የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኤልያቄምን ፡
ልጅ ፡ ኢኮንያንን ፡ የይሁዳንም ፡
አለቆች ፡ ጠበብቱንም ፡ በእግር ፡
ብረት ፤ በሰንሰለት ፡ የታሠሩትን ፡ ወለ
ቢያሙሂ ፡ በዓይነ ፡ ቁራኛ ፡ የተያ
ዙትን ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ማርኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ከወሰዳቸው ፡
በኋላ ፡ ንቡራነ ፡ እንዘ ፡ ንቡራን ፡ በቤተ ፡
እግዚአብሔር ፡ አንፃር ፡ ተካክለው ፡
የቆሙ ፡ ሁለት ፡ የበለስ ፡ ጫፎችን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አሳየኝ ፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ወ፩ዱስ ፡ አጽቀ ፡ በለስ ፡ ሥሙር ፡ ጥቀ ፡ ከመ፡በለሰ፡ማዕረር፡

ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ የበለስ ፡ ጫፍ ፡ እንደ መከር ፡ በለስ ፤ አንድም ፡ የመከር ፡ በለስ፡ እንደመሆኑ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ፡ነው፤

ወካልዑስ፡አጽቀ፡በለስ፡ሙሱን፡ጥቀ፡ዘኢ ይትበላዕ፡በእከዩ፡

በመምረሩ ፡ በመጐምረሩ፤ አንድም፡ በእንተ፡ እከዩ፡ ይላል ፡ ስለመምረሩ ፡ ስለመጐምረሩ ፤ አንድም ፡ እምእከዩ ፡ ይላል ፤ ከመምረሩ ፡ ከመጐምረሩ ፡ የተነሣ፡ የማይበላ ፤ ሁለተኛው ፡ የበለስ፡ ጫፍ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ የመረረ ፡ የጐመረረ፡ነው፤

፫፤ ወይቤለኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምንተ፡ ትሬኢ፡ኤርምያስ፡

በዚያ ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ ኤርምያስ ፡ ምን ፡ ታያለህ ? አለኝ ፤ ያየው፡ ጠፍቶት ፡ አይደለም ፤ ሊያና ግረው፡ሊተረጉምለት፡ነው፤

ወእቤ፡በለሳተ፡ቢፃተ፡

በቁመትም ፡ በመልክም ፡ የተካከሉ ፡ ሁለት ፡ የበለስ ፡ ጫፎችን ፡ አያለሁ ፡ አልሁት፤

ሠናይሂ፡ጥቀ፡ሠናይ፡

ያማረ፡የተወደደውም፡እጅግ፡ያማረ፡ የተወደደ፡ነው፤

ወሙሱንሂ ፡ እኩይ ፡ ጥቀ ፡ ዘኢይትበላዕ፡ እምእከዩ፡

በመምረሩ ፡ በመጐምረሩ ፡ የማይ በላው፡ክፋው ፡ በለስም ፡ እጅግ ፡ ክፉ፡ ነው፡

፬፤ ወነበበኒ፡እግዚአብሔር፡ወይቤለኒ፡

እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ተናገረኝ፤እንዲህ፡አለኝ፡ምን፡አለኝ፤

፭፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡ ፳ኤል፡

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡አለ፡ብለህ፡አስተምር፡አለኝ፤

ከመዝ፡በለስ፡ሠናይ፡ከማሁ፡እገብር፡ለእለ፡ ፈለሱ፡እምይሁዳ፡እለ፡ፈነውክዎሙ፡እምዝ ብሔር፡ውስተ፡ብሔረ፡ፋርስ፡ለሠናይ፤

ከኢየሩሳሌምና፡ከይሁዳ፡አስማርኬ፡ ወደፋርስ ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ለሰደድ ኳቸው፡ ሰዎች ፡ እንደዚህ ፡ እንዳ ማረው፡ እንደ ፡ ተወደደው ፡ በለስ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነገር ፡ አደርግላቸ ዋለሁ ፤ ሐተታ ፡ ለሠናይ ፡ አለ ፡ ወሐሊቆ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ እትቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለኵሉ ፡ ሰብኡ ፡ ያለውን ፡ ተስፋ ፡ ነግሮ ፡ አስማርኳቸ ዋልና፤

፮፤ ወአጸንዕ፡አዕይንትየ፡ላዕሌሆሙ፤

በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ በባቢሎን ፡ በዓይነ፡ምሕረት፡እመለከታቸዋለሁ፤ ዓይነ፡ምሕረቴን፡አጸናላቸዋለሁ፤

ወእሠውጦሙ፡ውስተ፡ዝ፡ምድር፡በሠናይ፤

ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ተወለዱበት ፡ ወዳገራ ቸውም፡በበጎ፡ነገር፡እመልሳቸዋለሁ፡ አለ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከባቢሎን ፡ ስትወጣ፡እንደ፡ወጓት፡ወግታ፡እንደ፡ ዘረፏት ፡ ዘርፋ ፡ ተመልሳለችና ፤ አንድም፡ለሠናይ፡ይላል፡ጠላት፡ጠፍ ቶላቸው ፡ ተዘልለው ፡ በተድላ ፡ በደስታ፡ሊኖሩ፡ሲል፡ነው፤

አሐንፆሙ፡ወኢይነሥቶሙ፤

በሀገራቸውም ፡ አጽንቼ ፡ አኖራቸ ዋለሁ፤



እተክሎሙ፡ወኢይመልሖሙ፡

እተክላቸዋለሁ ፡ አልነቅላቸውም፤ በሕንፃ፡ይመስላቸዋልና፡አሐንፆሙ፡ ወኢይነሥቶሙ፡አለ፤በተክል፡ይመስ ላቸዋልና ፤ እተክሎሙ ፡ ወኢይመ ልሖሙ ፡ አለ ፤ እንዲህ ፡ ማለት፡ በሀገ ራቸው፡ አጽንቼ ፡ አኖራቸዋለሁ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አላስማርካቸውም ፡ ሲል፡ነው፤

፯፤ ወእሁቦሙ፡ልበ፡በዘየአምሩኒ፡

በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እኔን ፡ በሚያ ውቁኝ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያውቁበት ፡ ልቡና ፡ እሰጣቸዋለሁ ፤ አንድም ፡ ወእሁቦሙ ፡ ልበ ፡ ዘየአምሩኒ ፡ ይላል ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እኔን ፡ የሚያው ቁበት፡ልቡና፡እሰጣቸዋለሁ፤

እስመ፡አነ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፤

አዋቂ፡ልቡና፡የምፈጥር፡እኔ፡እግዚአ ብሔር፡ነኝና፡እኔ፡ስለሆንሁ፤

ወይከውኑኒ፡ሕዝብየ፡ወአነሂ፡እከውኖሙ፡ አምላኮሙ፤

በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ እኔን ፡ የሚያው ቁበት ፡ ልቡና ፡ ከሰጠኋቸው ፡ በኋላ ፡ እነሱም ፡ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ ልጅ ፡ ይሆኑኛል ፤ እኔም ፡ የፍቅር ፡ የሃይ ማኖት፡አባት፡እሆናቸዋለሁ፤

እስመ፡ይትመየጡ፡ኀቤየ፡በኵሉ፡ልቦሙ፤

በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ በሕግ ፡ በአም ልኮት፡ ወደኔ፡ ይመለሳሉና፤አንድም፡ እመ ፡ ተመይጡ ፡ ኀቤየ ፡ ይላል ፤ በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ በሕግ ፡ በአም ልኮት፡ወደኔ፡ከተመለሱ፡የፍቅር፡የሃ ይማኖት፡አባት፡እሆናቸዋለሁ፤

፰፤ ወበከመ ፡ በለስ ፡ ሙሱን ፡ ዘኢይበ ላዕዎ፡በእንተ፡እከዩ፤

ስለመምረሩ፡ስለመጐምረሩ፡እንደማ ይበላው ፡ እንደመረረው ፡ እንደጐመ ረረው፡በለስም፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ከማሁ፡ እሬስዮሙ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ፡ወለመገብቱሂ፡ወለእለ፡ተርፉ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ወለእለ ፡ ተርፉ ፡ ውስተ ፡ ዛ ፡ ሀገር ፡ ወለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ግብፅ ፤ የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስንና፡ ሹማምንቱን ፡ በኢየሩ ሳሌም፡ የቀሩትንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ፡ በይሁዳም ፡ የቀሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የግብፅንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፤ ይህስ ፡ አይ ደለምና ፡ ብሎ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሂደው፡ በግብፅ ፡ የሚኖሩ ፡ እስራኤልንም ፡ ሁሉ ፡ እንደመረረው ፡ እንደጐመ ረረው፡በለስ፡አደርጋቸዋለሁ፤

፱፤ ወእሬስዮሙ፡ከመ፡ይዘረዉ፡ውስተ፡ ኵሉ፡መንግሥታተ፡ምድር፤

በአሕዛብ፡ነገሥታት፡አገርም፡ሁሉ፡ ተማርከው ፡ እንዲሄዱ ፡ አደርጋቸ ዋለሁ፤

ወይከውኑ ፡ ለጽዕለት ፡ ወለምሳሌ ፤ ወለተ ስናን ፡ ወለሁከት ፡ በኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ኀበ ፡ እዘርዎሙ፡ህየ፤

አስማርኬ ፡ በምሰዳቸውም ፡ አገር፡ ሁሉ ፡ ገዶ ፡ ገብሮ ፡ እያሉ ፡ እንዲሰድ ቧቸው ፡ ለተረት ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ አለ፤ ልብስ ፡ ያነሰውን፡ ወራት ፡ የባሰውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ይህስ ፡ የእስራ ኤልን፡ወገን፡ይመስላል፡ይሉዋቸው፡ ነበርና፤ለፀብዕ፡ለክርክር፡ለሁከትም፡ አደርጋቸዋለሁ፤ኀበ፡እዘርዎሙ፡ህየ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባለው ፡ ኀበ ፡ ወሰድኩዎሙ፡ ህየ ፡
ይላል፤እንደዚሁ፡ያስተረጕማል፤

፲፡ ወእፌኑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መጥባሕተ፡
ወረኀበ ፡ ወብድብደ ፡ እስከ ፡ የሐልቁ ፡
እምላዕለ፡ምድር፡እንተ፡ወሀብኩ፡ሎሙ፡
ወለአበዊሆሙ፤
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ቀድሞ ፡ በሀገ
ራቸው፡ሳሉ፡ዛሬ፡ለነሱ፡ቀድሞ፡ለአ
ባቶቻቸው፡ከሰጠኋቸው፡አገር፡ከኢየ
ሩሳሌም፡እልም፡ድርግም፡ብለው፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ቸነፈሩንና ፡
ቀጠናውን ፡ ጦር ፡ መቅሠፍቱን ፡
በነሱ፡አመጣባቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአ
ብሔር።

## ምዕራፍ፡፳፭፡

፩፡ ነገር፡ዘኮነ፡ኀበ፡ኤርምያስ፡በእንተ፡
ኵሉ ፡ ሕዝበ ፡ ይሁዳ ፡ በራብዕ፡ ዓመተ ፡
መንግሥቱ፡ለኢዮአቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡
ንጉሠ፡ይሁዳ፤
ንጉሥ ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም ፡
ይቀጥሏል፤የይሁዳው፡ንጉሥ፡የኢዮ
ስያስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡
ባራተኛው፡ዓመት፡የይሁዳ፡ወገኖች፡
ሁሉ፡ስለሚጠፉበት፡ነገር፡ከእግዚአ
ብሔር ፡ ወደኤርምያስ ፡ መጥቶ ፡
የተነገረ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤
ወይእቲ፡ዓመት፡ቀዳሚት፡መንግሥቱ፡ለና
ቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ይችውም ፡ ራብዕት ፡ ዓመተ ፡
መንግሥቱ ፡ ለኤልያቄም ፡ ያልኋት ፡
ለይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ለኤልያቄም ፡
አራተኛ፡ዘመን፡ናት፡አልኋት፡እንጂ፡
ለባቢሎን፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆርስ ፡
መጀመሪያ፡የነገሠባት፡ዘመን፡ናት፤

፪፡ ዘ፡ነገረ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡ለኵሎሙ፡
ሕዝበ ፡ ይሁዳ ፡ ወለኵሎሙ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡
ኢየሩሳሌም፤
ነገር፡ዘኮነ፡ኀበ፡ኤርምያስ፡ያለውን፡
አመጣ፤ነቢዩ፡ኤርምያስ፡ለይሁዳ፡
ወገኖችና፡በኢየሩሳሌም፡ለሚኖሩ፡
ሰዎች፡ሁሉ፡የተናገረው፡ቃል፡ይህ፡
ነው፤
ወይቤሎሙ፤
እንዲህ፡ብሎ፡የተናገረው፡ቃል፡ይህ፡
ነው፤

፫፡ እምአመ፡፲ወ፫ዓመተ፡መንግሥቱ፡
ለኢዮስያስ፡ወልደ፡አሞጽ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
እስከዛ፡ዕለት፡ዝንቱ፡፳ወ፫፡ዓመት፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የአሞጽ ፡ ልጅ ፡
ኢዮስያስ ፡ ከነገሠባት ፡ ካሥራ
ሦስተኛው፡ዘመን፡ጀምሮ፡እስከዚች፡
ቀን ፡ድረስ ፡ ይኸውም ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡
ዘመን ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ትች ፡ አድርግ፤
ኮነ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኀቤየ፤
የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡ መጽአ ፡
ተነግረ ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ ፤
ሐተታ፡፳፫ያለው፡የኢዮስያስ፡መላ፡
ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ፴፩ ነው ፤
ኤርምያስ ፡ ኢዮስያስ ፡ በነገሠ ፡
በ፲፫ኛው፡ዘመን፡ተነሥቶ፡ዜዋዌን፡
ሚጠትን ፡ ተናግሯል ፤ ከኢዮስያስ፡
፲፱፡የኤልያቄም፡አራት፡፳፫፡ያለው፡
ይህ፡ነው፤
ወጌሥኩ፡ኀቤክሙ፡ወነገርኩክሙ፡ወአይዳ
ዕኩክሙ፡ወኢሰማዕክሙ፤
እኔም፡በዚያ፡ወራት፡ፈጥኜ፡መጥቼ፡
ይኸንን ፡ ነገር ፡ ፈጽሜ ፡ ነገርኋችሁ፤
እናንተን ፡ ግን ፡ አልሰማችሁም ፤
አንድም፡አልሰማችሁትም፡እንጂ፡እኔ፡



ግን ፡ ፈጥኜ ፡ መጥቼ ፡ ፈጽሜ ፡ ነገር
ኳችሁ፤

፬፡ ወፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤክሙ ፡
ኵሎ ፡ አግብርቲሁ ፡ ነቢያተ፡ በጽባሕ ፡
ይጊሡ፤
ከኔም ፡ በኋላ ፡ ከኔም ፡ አስቀድሞ ፡
ፈጥነው፡ገሥግሠው፡ወደ፡እናንተ፡
መጥተው፡ሊያስተምሩዋችሁ፡አገል
ጋዮቹ ፡ ነቢያትን ፡ ወደናንተ፡ ላከ ፤
ምከሩ፡አስተምሩ፡ብሎ፤
ወፈነወ፡ወኢሰማዕክምዎሙ፤
ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምከሩ ፡
አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ ነቢያትን ፡ ወደ
ናንተ፡ላከ፤እናንተ፡ግን፡አልሰማችኋ
ቸውም፤
ወኢያጽማዕክሙ፡ዕዘኒክሙ፡ለሰሚዕ፤
በዕዝነ ፡ ሥጋችሁ ፡ ለመስማት ፡
በዕዝነ፡ ልቡናችሁ ፡ ለመረዳት ፡
ወደነሱ ፡ አልቀረባችሁም ፤ ለመስ
ማት፡ለመረዳት፡አለ፤ላለመስማት፡
ላለመረዳት፡ጆሮ፡ማቅረብ፡አለና፤
ይኸውም፡የጆሮ፡ቀበገቦት፡ነው፤

፭፡ ወይቤ ፡ ተመየጡ ፡ ኵልክሙ ፡
እምፍኖተ፡እኪይክሙ፡ወእምእከየ፡ምግባ
ሪክሙ፤
እግዚአብሔርም ፡ በነቢያት ፡ በካ
ህናት ፡ አድሮ ፡ ከክፉ ፡ ሥራችሁ ፡
ከክፉ፡ በደላችሁም፡ግዱን፡በንስሐ፡
ተዉ፡ተመለሱ፡አለ፤
ወትነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡
ወሀበክሙ፡እግዚአብሔር፡ለክሙ፡ወለአበ
ዊክሙ፡እምዓለም፡ወእስከ፡ለዓለም፤
ይህን፡ያደረጋችሁ፡እንደሆነ፡እግዚአ
ብሔር፡ቀድሞ፡ለአባቶቻችሁ፡ዛሬ፡

ለናንተ ፡ ባወረሳት ፡ አገር ፡ በኢየሩ
ሳሌም፡በተድላ፡በደስታ፡ለዘላለሙ፡
ጸንታችሁ፡ትኖራላችሁ፡አለ፤

፮፡ ወኢትሑሩ ፡ ዳዕሙ ፡ ወኢትትልዉ ፡
አማልክተ፡ነኪር፡ከመ፡ትትቀነዩ፡ሎሙ፡
ወትስግዱ፡ሎሙ፤
ሎሙና፡ሎሙ፡አንድ፡ወገን፤እናንተ፡
ግን ፡ ለእነሱ ፡ ተገዝታችሁ ፡ ለመ
ስገድ ፤ አንድም ፡ ለነሱ ፡ ሰግዳችሁ፡
ለመገዛት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚሆኑ ፡
ጣዖታቱን፡ተከትላችሁ፡አትሒዱ፤
አንድም፡ለነሱ፡ሰግዳችሁ፡ለመገዛት፡
ልዩ፡ልዩ፡የሆኑ፡ጣዖታቱን፡ ተከት
ላችሁ ፡ አትሒዱ ፡ እንጂ፡ ወደጣ
ዖታቱ፡ካልሔዳችሁስ፡ትነብሩ፤
ወኢታምዕዕኒ፡በግብረ፡እደዊክሙ፡ወኢያ
ሐስም፡ብክሙ፤
በነቢያት፡በካህናት፡አድሬ፡ብመክ
ራችሁ፡ባስተምራችሁ፡አንመለስ፡
ብላችሁ፡በእጃችሁ፡በቃላችሁ፡ሥራ፡
አታሳዝኑኝ ፤ እኔም ፡ ግዱን ፡ ክፉ ፡
ሥራ፡ አልሠራባችሁም ፤ አንድም ፡
ዋዌውን፡ትቶ፡ኢያሕስም፡ብክሙ፡
ይላል፤እኔ፡በናንተ፡ክፉ፡ሥራ፡እንዳ
ልሠራባችሁ ፡ እናንተ ፡ በእጃችሁ ፡
በቃላችሁ፡ሥራ፡ግዱን፡አታሳዝኑኝ፤

፯፡ ወኢሰማዕክሙኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ከመ ፡ ታምዕዑኒ ፡ በግብረ ፡
እደዊክሙ፡ለአእከዮ፡ለክሙ፤
ብክሙ፡ሲል፡ነው፤እኔ፡በናንተ፡ክፉ፡
ነገር ፡ ላደርግባችሁ ፡በእጃችሁ ፡
በቃላችሁ፡በሠራችሁት፡ሥራ፡እንድ
ታሳዝኑኝ ፡ ሁናችሁ ፡ በነቢያት ፡
በካህናት ፡ አድሬ ፡ የምነግራችሁን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቃል፡አልሰማችሁኝም፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤

፰፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር : ኃያል : እስመ : ኢሰማዕክሙኒ :
ነገርየ፡

ስለዚህ : ነገር : አምጸኤ : ዓለማት፡
ወላዴ : ፍጥረታት : እግዚአብሔር :
በነቢያት፡በካህናት፡አድሬ፡የነገርኋ
ችሁን፡አልሰማችሁኝም፡እኮን፡አለ፤
ናሁ : አነ : እፌኑ : ማንሻ : ነው ፤
አንድም : በእንተ : ዝንቱ : በክፋ
ታችሁ : ጸንታችሁ : ስለኖራችሁ :
ነገሬን፡አልሰማችሁኝምና፤

ናሁ፡አነ፡እፌኑ፡
እነሆ : መቅሥፍቱን : አመጣባች
ኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአነሥእ፡ኵሎ፡በሐውርተ፡ሰሜን፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡
በባቢሎን : አውራጃ : ያሉ : አገሮ
ችንም፡ሁሉ፡አነሣሥቼ፡አነቃቅቼ፡
አመጣባችኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፱፤ ወኀበሂ፡ናቡከደያር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
ገብርየ፡እልእክ፤
ወደአገልጋዬ፡ወደ፡ባቢሎኑ፡ንጉሥ፡
ወደ፡ናቡከደነፆርም፡ና፡ብዬ፡እልክበ
ታለሁ፤ገብርየ፡አለው፡በተፈጥሮ፤
አንድም፡ባሪያ፡ወዳዘዙት፡እንዲላክ፡
ያዘዙትን : እንዲያደርግ : እሱም :
ሁለቱ : ነገድ : ቢበድሉ : ከእግዚአ
ብሔር : ዘንድ : ታዝዞ : የታዘዘውን :
ሊሠራ፡መጥቶአልና፤

ወአመጽእ፡ውስተ፡ዛ፡ምድር፡ወላዕለ፡እለ፡
ይነብሩ፡ውስቴታ፤
አገልጋዬ : ናቡከደነፆርንም : በሀ
ገሬቱ : በኢየሩሳሌም : የሚኖሩ : ሰ

ችን : ሊያጠፉ : ወደ : ኢየሩሳሌም፡
አመጣዋለሁ፤

ወዲበ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ዘዓውዳ፤
በከተማዪቱ፡በዙሪያዋ፡ወዳሉ፡እስራ
ኤልም፡ሁሉ፡አመጣዋለሁ፤አንድም፡
በቁሙ : አሕዛብ : ናቸው : በዙሪያዋ፡
ወዳሉ፡አሕዛብም፡አመጣዋለሁ፡አለ፤
ሲመጣ፡በዳር፡በዳር፡ያሉ፡አሕዛብን፡
ሁሉ፡አጥፍቷልና፤

ወአጠፍዖሙ፡ወአማስኖሙ፤
ናቡከደነፆርንም : አምጥቼ : ፈጽሜ፡
አጠፋቸዋለሁ፤አንድም፡ያጠፍአሙ፡
ወያማስኖሙ፡ይላል፤ናቡከደነፆርም፡
በኔ፡ትእዛዝ፡መጥቶ፡ፈጽሞ፡ያጠፋ
ቸዋል፤

ወይትፋጸይዋ፤
ያዩዋትም : ሰዎች : ሁሉ : ያፏጩ
ባታል : አለ ፤ ብንጣራ : ሰዎች፡
ይሰሙናል : ብለው ፤ አንድም :
የአንክሮ : ነው ፤ አንድም : ይትፋ
ጸይዋ፡ ወየኀሥርዋ፡ለዓለም፡ይላል፤
አሕዛብ፡ መጥተው : ያፏጩባታል፡
ለዘላለሙም : ያጉሰቍሏታል ፤ ለዘ
ፈን፡ለቀረርቶ፡ፉጨት፡መጀመሪያ፡
ነውና፤

፲፤ ወእሥዕር : እምኔሆሙ : ቃለ፡
ትፍሥሕት፡ወቃለ፡ሐሤት፡ቃለ፡መርዓዊ፡
ወቃለ፡መርዓት፤
ከእስራኤልስ፡ወገን፡እገሌ፡እገሌትን፡
አጨ ፤ እገሊት : እገሌን : አጨች፡
የሚሉ፡ቃልን፡አጠፋለሁ፤አንድም፡
ባሠርቱ፡የሚዘፍኑት፡ዘፈን፡አለና፡
ያነን፡አጠፋባቸዋለሁ፤

ወቃለ፡ማኅረፅ፤
በዚያ : ወራት : ወፍጮ : ድ : ሲል፡



ወብርሃነ፡ማኅቶት፤
የፋናም : መብራት : ተግ : ብሎ :
አይበራም፤

፲፩፤ ወትማስን፡ኵላ፡ምድር፤
ኢየሩሳሌም : ሁላ : እንዲህ : ሁና፡
ትጠፋለች፤

ወይትቀነዩ፡ለእሉ፡አሕዛብ፡ወለንጉሠ፡
ባቢሎን፡፸፡ዓመተ፤
ኢየሩሳሌምም : ከጠፋች : በኋላ :
እስራኤል : ለሠራዊቱ : ለባቢሎን :
ንጉሥ : ለብልጣሶር : ሰባ : ዘመን :
ሙሉ፡ይገዛሉ፤

፲፪፤ ወሐሊቆ፡፸፡ዓመት፡እትቤቀሎሙ፡
ለንጉሠ፡ባቢሎን፡ወለእሉ፡አሕዛብ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡በኃጢአቶሙ፡ለብሔረ፡
ፋርስ፤
ሰባው : ዘመን : ካለቀ : በኋላ : ግን፡
ካለፈ፡ ብትልም፡የባቢሎን፡ንጉሥ፡
ብልጣሶርን፡ሠራዊቱንም፡ሁሉ፡በኃ
ጢአታቸው : ተበቅዬ : አጠፋቸዋ
ለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወዲበ : ብሔረ : ፋርስ : ወእሬስዮሙ :
ሙሱናነ፡ለዓለም፤
የፋርስ፡ሰዎች፡ሰባ፡ዘመን፡ሙሉ፡
ግፍ : በሠሩበት : ኃጢአታቸው :
ዋዌውን : ታግሦ : እስራኤልን :
እንዳጠፉ : እነሱንም : ለዘላለሙ :
እንዲጠፉ፡አደርጋቸዋለሁ፡አለ፤

፲፫፤ ወአመጽእ : ላዕለ : ይእቲ : ሀገር፡
ኵሎ፡ነገርየ፡ዘነበብኩ፡በእንቲአሃ፤
ባቢሎንን፡አጠፋታለሁ፡ብዬ፡የተናገ
ርኩበትን : ነገሬን : ሁሉ : ዛሬ :
በባቢሎን፡አገር፡አመጣባታለሁ፤

ወኵሎ፡ዘተጽሕፈ፡ውስተ፡ዝ፡መጽሐፍ፡
ዘተነበየ፡ኤርምያስ፡ዲበ፡ኵሉ፡አሕዛብ፤
ነቢዩ፡ኤርምያስም፡ከሚጠት፡በኋላ፡
አሕዛብ : ሁሉ : ይጠፋሉ : ብሎ :
ትንቢት : በተናገረበት : በዚህ :
መጽሐፍ፡የተጻፈውንም፡ነገር፡ሁሉ፡
በባቢሎን፡አመጣባታለሁ፤

፲፬፤ እስመ : ይቀንይዎሙ : እሙንቱኒ :
አሕዛብ : ብዙኃን : ወነገሥት : ዐበይት :
የባቢሎን : ሰዎች : ሠራዊቱ : ታላ
ላቆቹ፡የባቢሎንም፡ነገሥታት፡ሁሉ፡
ሰባ፡ዘመን፡ሙሉ፡እስራኤልን፡አስ
ጨንቀው : ይገዙዋቸዋልና፡ የሚገ
ዟቸው፡ስለሆነ፤

ወእፈድዮሙ፡በከመ፡ምግባሮሙ፡ወዘከመ፡
ግብረ፡እደዊሆሙ፤
እኔም፡እንደቃላቸው፡እንደ፡እጃቸው፡
ሥራ : መጠን : ፍዳውን : እጥፍ :
አድርጌ፡አመጣባቸዋለሁ፤

፲፭፤ እስመ : ከመዝ : ይቤለኒ : እግዚአ
ብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፤
ይኸ : እስመ : ዋዌ : ነው ፤ እስመ :
አርኖን : ደወሎሙ : እንዲል ፤ የእስ
ራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡በዚያ፡
ወራት፡እንዲህ፡አለኝ፤

ንሣእ : ጽዋዐ : ወይን : ዘኢኮነ : ቱሱሐ :
እምእዴየ፤
ማየ : ርኅራኄ : ያልተቀላቀለው ፤
አንድም፡ፍሡሐ፡ይላል፤ወይን፡ያሥ
ተፌሥሕ : ልበ : ሰብእ : እንዳለው :
ያይደለ : ጽዋዓ : መዓትን : ከእጄ :
ተቀበል፡አለኝ፤

ወአስትዮሙ : ለኵሎሙ : አሕዛብ : እለ :
እፌንወከ፡ኀቤሆሙ፡አነ፡ህየ፤
ሒድ፡አጠጣቸው፡ብዬ፡እኔ፡ወደነሱ፡
አንተን : የምልክባቸው : አሕዛብን :

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ፡ ጽዋዓ ፡ መዓቱን ፡ ወስደህ ፡ አጠጣቸው፤

፲፮፤ ከመ ፡ ይስተዩ ፡ ወይመምዑ ፡ ወይንትዑ ፡ እምገጸ ፡ ኲናት ፡ እንተ ፡ እፌኑ፡ አነ፡ማዕከሎሙ፡

ጽዋዐ፡መዓቱንም፡ከእጄ፡ተቀብለህ፡ ወስደህ ፡ አጠጣቸው ፡ ማለቴ ፡ ለበጎ ፡ አይደለም ፤ እኔ ፡ ወደነሱ ፡ ከማመጣ ባቸው፤አንድም፡እኔ፡በመካከላቸው፡ ከማመጣባቸው፡ ጦር ፡ የተነሣ ፡ ያነን ፡ ጠጥተው ፡ ይሸበሩ ፡ ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡ ነው፡እንጂ፤

፲፯፤ ወነሣእኩ፡ውእተ፡ጽዋዐ፡እምእደ፡ እግዚአብሔር፡

ያነንም ፡ ጽዋዓ ፡ መዓቱን ፡ ከእግዚአ ብሔር፡እጅ፡ተቀበልሁት፤

ወአስተይክዎሙ፡ለአሕዛብ፡እለ፡ኀቤሆሙ፡ ፈነወኒ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር ፡ ሒድ ፡ አጠጣቸው ፡ ብሎ ፡ ወደነሱ ፡ የላከኝንም ፡ አሕዛብ፡ ሁሉ ፡ ጽዋዐ ፡ መዓቱን ፡ ተቀብዬ ፡ ወስጄ ፡ አጠጣኋቸው ፤ አሕዛብ ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡ እየተረተረ ፡ ያመጣል፤

፲፰፤ ለኢየሩሳሌም፡ወለአህጉረ፡ይሁዳ፡

በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ላሉ፡ሠራዊት፤

ወለነገሥተ፡ይሁዳ፡

ለይሁዳም፡ነገሥታት፤

ወለመላእክቲሃ፡

ለአለቆችዋ፤

ከመ፡ያማስኖሙ፡

እልም ፡ ድርግም ፡ አድርጎ ፡ ሊያጠ ፋቸው፤

ወይኩኑ፡ዓፀ፡ወበድወ፡

ከረድዔቱም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በረሃ ፤ ሊሆኑበት፤

ወለመርገም፡ከመ፡ዛቲ፡ዕለት፡

እንደዚችም፡ቀን፡ለስድብ፡ለጥፋት፡ ሊሆኑበት፡መጀመሪያ፡ለነሱ፡አጠጣ ኋቸው፤

፲፱፤ ወለፈርዖንሂ ፡ ንጉሠ ፡ ግብፅ ፡ ወለደቂቁ ፡ ወለመሳፍንቲሁ ፡ ወለኵሉ ፡ ሕዝቡ፡

ለአሽከሮቹና ፡ ለግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለመሳፍ ንቱም ፡ አጠጣኋቸው ፤ ማለት ፡ ነገር ኋቸው፡አስተማርኋቸው፤

፳፤ ወለኵሎሙ፡እለ፡ይደመሩ፡

ከኢየሩሳሌምና ፡ ከይሁዳ ፡ ነገሥታት፡ በኋላ፡ግን፡ለግብፅ፡ንጉሥ፡ለፈርዖንና፡ ለልጆቹ ፤ አንድም ፡ ወለደቂቁ ፡ ለባለ ሟሎቹ፡ደቀ፡ጽርሑ፡እንዲል፡ለሹማ ምንቱና ፡ ለወገኖቹ ፡ ከነሱም፡ ጋራ ፡ አምነው ፡ ተጋብተው ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች፡ሁሉ፡ጽዋዓ፡መዓቱን፡አጠጣ ኋቸው፤

ወለኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ ምድረ ፡ ኦፅ'ኦስ' ፤

ለኤዶምያስ ፡ አገር ፡ ነገሥታትም ፡ ሁሉ፤

ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ምድረ፡ኢሎፍሊ፡ወለአስ ቀሎና፤ወለጋዛ፤ወለአቃሮን፡ወለእለ፡ተርፉ፡ በአዛጦን፡

ለኢሎፍሊና ፤ ለአስቀሎና ፤ ለጋዛና ፤ ለአቃሮን ፡ በአዛጦንም ፡ ለቀሩ ፡ ነገሥታት፡ሁሉ፡አጠጣኋቸው፤

፳፩፤ ወለኤዶምያስ፡

ምድረ ፡ ኦፅ ፡ ምድረ ፡ ኦስ ፡ ያለውን ፡



ኤዶምያስ፡ብሎ፡ገለጠው፤አንድም፡ ኦስ ፡ ኦፅ ፡ ያለው ፡ ከተማይቱ፡ ናት፤ ኤዶምያስ፡መላዩቱ፡ናት፤

ወለሞዓብ፡ወለደቂቀ፡አሞን፡

ለሞዓብ ፡ ሰዎችና ፡ ለአሞን ፡ ነገ ሥታት፡ሁሉ፤

፳፪፤ ወለነገሥተ፡ጢሮስ፡ወሲዶና፡

ለጢሮስና ፡ ለሲዶና ፡ ነገሥታትም ፡ ሁሉ፤

ወለኵሉ ፡ ነገሥተ ፡ ደሴት ፡ እለ ፡ ማዕዶተ ፡ ባሕር፡

በባሕሩ ፡ ማዶ ፡ ላሉ ፡ ደሴት ፡ ለምትባል፡አገር፡ነገሥታትም፡ሁሉ፡ ደሴት ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ደሴት፡ነው፤

፳፫፤ወለዴዳን፡ወለቴማን፡

ለዴዳንና ለቴማንም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ፤

ወለሮስ፡

ለሮስ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ አጠጣ ኋቸው፤

ወለኵሎሙ፡ቅሩጻነ፡ገጽ፡

ፊታቸውንም ፡ ለተከተቡ ፡ ለተፈለቁ፡ ለአሕዛብ፡ሁሉ፡አጠጣኋቸው፤ይህን፡ ባለው ፡ ልጹያነ ፡ አጽሐም ፡ ቅሩጻነ ፡ ጸጉረ ፡ ከናፍር ፡ ይላል ፤ የእስማኤል ፡ ወገኖች፡ናቸው፤

፳፬፤ ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ዓረብ፡

በምዕራብ፡ላሉ፡ነገሥታት፡ሁሉ፤

ወለእለ፡ይነብሩ፡ሐቅለ፡

በምድረ፡በዳ፡ለሚኖሩ፡ነገሥታትም፡ ሁሉ፤ አንድም ፡ ወለኵሉ ፡ ነገሥተ ፡ ዓረብ፤

በከተማ ፡ ላሉ ፤ ወለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ሐቅለ፡ በገጠር ፡ ላሉ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ፤

፳፭፤ ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ዘምሬ፡

ዘምሬ፡ለምትባል፡አገር፡ነገሥታት፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡ ዘምሬ ፡ ሶርያ ፡ ናት፤ ለሶርያም፡ነገሥታት፡ሁሉ፤

ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ኤላም፡

ለኤላምም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፤ ይህች፡ ኤላም ፡ በፋርስና ፡ በባቢሎን ፡ መካ ከል ፡ ያለች ፡ አገር ፡ ናት ፤ አንድም ፡ ፋርስ ፡ ናት ፤ አንድም ፡ ኤላም ፡ የምትባል፡ሌላ፡ሀገር፡ናት፤

ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ሜዶን፡

ለሜዶንም፡ነገሥታት፡ሁሉ፤

፳፮፤ ወለኵሉ፡ነገሥተ፡ሰሜን፡

ለባቢሎንም፡ነገሥታት፡ሁሉ፤

ለቅሩባን ፡ ወለርኁቃን ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ ካልዑ፡

ነሣሣለትና ፡ አንዱም ፡ አንዱ፡ ካን ዱም ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ ለቀረ ቡትና ፡ ለራቁትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጽዋዓ፡መዓትን፡አጠጣኋቸው፤

ወለኵሉ፡ነገሥት፡እለ፡ገጸ፡ኵሉ፡ምድር፡

ባሬቱ ፡ መዓዝን ፡ ላሉ ፡ ነገሥታትም ፡ ሁሉ፡አጠጣኋቸው፤

ወንጉሠ፡ሲሳር፡ይስተይ፡እምድኅሬሆሙ፤

ከነዚህ ፡ በኋላ ፡ ከነዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሲሳሩ ፡ ንጉሥ ፡ ይጠጣ ፤ አንድም ፡ ሲሳር፡የሚባል፡ንጉሥ፡ይጠጣ፤ይህ፡ ያልታወቀ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የብልጣሶር፡ሁለተኛ፡ስሙ፡ነው፤

፳፯፤ ወትብሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ አምላከ፡ እስራኤል፡

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤

ስትዩ፡ወስከሩ፡ወተንትኑ፡ወደቁ፡ወኢትት ነሥኡ፡እምገጸ፡ኲናት፡እንተ፡እፌኑ፡አነ፡ ማዕከሌክሙ፤

ይኸንንም ፡ ጽዋዐ ፡ መዓትን ፡ ጠጥታችሁ ፡ ስከሩ ፤ በመከራውም ፡ ተፍገምገሙ ፤ በመካከላችሁም ፡ እኔ ፡ ከማመጣባችሁ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍት ፡ የተነሣም፡ወድቃችሁ፡አትነሡ፤

፳፰፤ ወዘኢፈቀደ ፡ ይትመጠዎ ፡ ለውእቱ፡ ጽዋዕ ፡ እምእዴከ ፡ ለሰትይ ፡ በሎሙ፤

ይኸንንም ፡ ጽዋዐ ፡ መዓት ፡ ከእጅህ ፡ ሊቀበለው ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር፡ ሥላሴን፡ጠጡ፡በላቸው፡አለ፤መሐላ፡ ነው፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፡ሰትየ፡ ስትዩ፤

አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ ሥላሴን፡ጠጡ፡በላቸው፡አለ፤መሐላ፡ ነው፤

፳፱፤ እስመ፡ናሁ፡ሀገር፡እንተ፡ተሰምየ፡ ስምየ፡በላዕሌሃ፡አነ፡እኬንኖሙ፡በእኩይ፤

በ፩ ፡ ስሜ ፡ የተጠራባት ፡ ሀገሬ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡ስንኳ፤

ወአነ፡እኬንኖሙ፡በእኩይ፤

በሱዋም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችማ ፡ በክፉ፡ ሥራቸው፡የፈረድኩባቸው፤ከፈረድኩ ባቸው፤ እንድም ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ሀገር ፡ እንተ፡ተሰምየ፡ስምየ፡በላዕሌሃ፤ ስሜ፡የተጠራባት፡ሀገሬ፡ኢየሩሳሌም፡ ስንኳ ፡ ጠፍታለችና፤ እሱዋ ፡ ከጠፋች ፡ ወአነ፡እኬንኖሙ፡በእኩይ፤

በሱዋም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በክፉ ሥራቸው ፡ ፈርጀባቸዋለሁና ፡ ከፈረ ኩባቸው፤

አንትሙኑ፡ነጺሐ፡ትነጽሑ፡ወኢትነጽሑ

እናንተ ፡ ከነዚያ ፡ ተለይታችሁ ከፍዳው፡ ከኃጢአቱ ፡ ንጹሕ ፡ ትሆ ላችሁ? ንጹህ ፡ አትሆኑም፤ አንድም አንትሙኑ፡ ድኂነ ፡ ትድኅኑ ፡ ወኢ ድኅኑ ፡ ይላል ፤ እናንተ ፡ ከነዚያ ፡ ተለ ታችሁ ፡ ከመከራው ፡ ትድናላችሁን ከነዚያ ፡ ተለይታችሁ ፡ ከመከራው አትድኑም፤

እስመ ፡ አነ ፡ እጼውዕ ፡ ኲናተ ፡ ላዕለ ፡ እለ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ይቤ ፡ እግዚ ብሔር፡ፀባዖት፤

እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ሁሉ፡ጦር፡መቅሠፍትን፡ጠርቼ፡አመ ጣባቸዋለሁ፡ብሏልና፡አቸናፊ፡እግዚ አብሔር፡ከመከራው፡አትድኑም፤

፴፤ ወአንተ፡ተነበይ፡ሎሙ፡ዘ፡ነገረ

አንተ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ትንቢትህን ገልጠህ፡አስተምራቸው፤

ወበሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአርያም ይጥሕር ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ወእምቤተ መቅደሱ፡ይሁብ፡ቃሎ፤

በልዕልና ፡ ያለ ፤ አንድም ፡ በጽርሐ አርያም ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር በምስጋና፡ ማደሪያው ፡ በጽርሐ አርያምም ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር አንድም ፡ እምአርያም ፡ ወእምቤተ መቅደሱ ፤ አንድም ፡ ከምስጋና ፡ ማደ ሪያው፡ከጽርሐ፡አርያም፡ሆኖ፡እግዚአ ብሔር፡እንደ፡አንበሳ፡ጣሕረ፡ቃሉን



በማስፈራት ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ይሰዳል፤

ጥሒረ፡ይጥሕር፡ላዕለ፡ማኅደሩ፤

በማደሪያው ፡ በጽርሐ ፡ አርያም ፡ ሁኖ፤ አንድም ፡ በማደሪያዎቹ ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ሆኖ ፡ ጣሕረ ፡ ቃሉን ፡ እንደ ፡ አንበሳ፡ያሰማል፡አለ፤አስቀድሞ፡በሀገ ራችሁ፡አባር፡ቸነፈር፡ይደረግባችኋል፤ ኋላም፡ፄዋዌ፡ያገኛችኋል፡ብሎ፤

ቃለ፡ድንጋፄ፤

ያንጊዜ፡በእስራኤል፡ከተማ፡የሚያስ ደነግጥ ፡ ቃል ፡ ይሰማል፤ አንድም ፡ ከነቢያት፡ከካህናት፡አንደበት፡የሚያ ስደነግጥ፡ቃል፡ይሰማል፤

ወውስተ ፡ ፍኖቶሙ ፡ ያወሥእ ፡ ኅበ ፡ ኵሉ ፡ እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ምድር፤

በየጎዳናቸው ፤ አንድም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ቸውን፡አይቶ፤ይኸ፡ውስተ፡በግዕዝ፡ የገባ፡ነው፤ወአንሰ፡አነብብ፡ውስተ፡ ወንጌል፡ዘሠርዖ፡እግዚእነ፡እንዲል፤ በኢየሩሳሌም ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶላቸው፡ ተዘልለው ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች፡ ዘንድ፡ በነቢያት፡በካህናት፡አድሮ፡የሚጠፉ በትን፡ትንቢት፡ያናግርባቸዋል፤

፴፩፤ ይመጽእ፡ተሠርዎ፡እስከ፡አጽናፈ፡ ምድር፤

ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ባሉ ፡ በእስ ራኤል፡ ጥፋታቸው ፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም፡ጥፋታቸው፡ጽንፍ፡እስከ፡ ጽንፍ፡ይመጣባቸዋል፤

እስመ ፡ ለሊሁ ፡ ቅስተ ፡ ይትዋቀሶሙ ፡ ለአሕዛብ፤

ክፉ ፡ ሥራቸውንም ፡ አይቶ ፡ አስ ቀድሞ ፡ እስራኤልን ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ በቁሙ፡ አሕዛብን ፡ ይወቅሳቸዋልና ፡ ይጣላቸዋልና፤

ወውእቱ፡ይኴንን፡ኵሎ፡ዘሥጋ፤

ብቻ ፡ እነሱን ፡ አይደለም ፤ ክፉ ፡ ሥራ ፡ በሚሠራ ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድበታልና፤

ወለኃጥአን፡አገብኦሙ፡ለመጥባሕት፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በኃጢአታቸው ፡ የሚበድሉኝንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለጦር ፤ ለመቅሠፍት ፡ አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአ ብሔር፤

፴፪፤ ወከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት፤

አቸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ወራት፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡ትመጽእ፡እኪት፡እምሕዝብ፡ውስተ፡ ሕዝብ፤

እነሆ፡መከራ፡ካንዱ፡ወገን፡ወዳንዱ፡ ወገን ፡ እያለች ፡ ትመጣለች፤ ይህ ፡ ለጊዜው ፡ የሆነው፡ ነው፤ አንድም ፡ መከራ ፡ ካሥሩ ፡ ነገድ፡ ወደሁለቱ ፡ ነገድ፡ታገዛ፡ትመጣለች፤

ወይወጽእ ፡ ዐውሎ ፡ ዐቢይ ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር፤

ረቂቅ፡መቅሠፍቱም፡ከጽንፍ፡እስከ፡ ጽንፍ ፡ ታገዘ ፡ ይመጣል ፤ አንድም ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስራ ኤልን፡ለማጥፋት፡ይመጣል፤

፴፫፤ ወይከውኑ፡ቅቱላነ፡እምኀበ፡እግዚ አብሔር ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር፡እስከ፡አጽናፈ፡ምድር፤

ያንጊዜስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

መከራው ፡ ታዝዞ ፡ መጥቶባቸው ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ያሉ ፡ እስራኤል፡ ሙተው ፡ ወድቀው ፡ ወድቀው፡ይገኛሉ፤አንድም፡ቅቱላን፡ ይከውኑ፡እምአጽናፈ፡ምድር፡እስከ፡ አጽናፈ፡ምድር፡ይላል፤መከራው፡ከእ ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ መጥቶ ባቸው ፡ እስራኤል ፡ በአሕዛብ ፡ ጦር ፡ ሙተው፡ የሚቀብራቸው ፡ አጥተው ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ወድቀው ፡ ወድቀው፡ይገኛሉ፤

ወያስቆቅዉ፡ወኢይትቀበሩ፡

ያንጊዜ ፡ ወዳጆቻቸውም ፡ ዘመዶቻ ቸውም፡አልቀው፡አይቀብሯቸውም፤ አንድም ፡ ኢያስቆቅዉ፡ ወኢይት ቀበሩ፡ ይላል ፤ ወዳጆቻቸው ፡ ዘመዶ ቻቸው ፡ ለሞቱት፡ ስናለቅስ ፡ ድምፅ ፡ ሰምተው ፡ አሕዛብ ፡ መጥተው ፡ ያጠፉናል ፡ ብለው ፡ አያለቅሱላቸ ውም፤ወኢይትቀበሩ፤

እነሱን ፡ እስክንቀብር ፡ ድረስ ፡ አሕ ዛብ ፡ መጥተው ፡ ያጠፉናል ፡ ብለው፡ ባያደርሳቸውም ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ዘመ ዶቻቸው፡አይቀብሯቸውም፤

ዳዕሙ ፡ ስጡሐነ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ምድር፡ ይከውኑ፡

በየጎዳናው ፡ ሰጣ ፡ ብለው ፡ ወድቀው፡ ይገኛሉ፡እንጂ፤

፴፬፤ ክልሑ ፡ ኖሎት ፡ ወአውይዉ ፡ አባሕኰ፡አባግዕ፡

ዘላኖችም ፡ የበግ ፡ አውራዎችም ፡ በዚያ፡ ወራት ፡ ጩሁ ፡ አለ፤ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ኖሎት ፡ ነገሥታቱ፤ አባሕኰ፡ አባግዕ፡መኳንንቱ፡አንድም፡ኖሎት፡ መምህራኑ ፡ አባሕኰ ፡ አባግዕ ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ በመከራው ፡ ተይዛችሁ፡ ጩሁ፡

እስመ ፡ በጽሐ ፡ መዋዕሊክሙ ፡ ከመ ፡ ይጥብሑክሙ፡ወይዝርዉክሙ፡

እናንተን፡በ ትንው፡ወስደው፡ሊያር ዷችሁ፡ሊ ወራርዷችሁ፡የምትታረ ዱበት ፡ የምትወራረዱበት፡ ጊዜው፡ ደርሷልና፤

ወትወድቁ፡ከመ፡ንዋይ፡መፍትው፡

ብርሌ፡ብርጭቆ፡ወድቆ፡እንዲሰበር፡ ወድቃችሁ ፡ ትሰባበራላችሁ፤ ብርሌ፡ ከነቃ ፡ አይሆንም ፡ እቃ ፡ እንዲሉ፤ አንድም፡በርሮ፡እንደጠፋ፡በግ፡ትሆ ናላችሁ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ (ሞኝ) ፡ ካመረረ፡ በግ ፡ ከበረረ ፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ያዕቆብ፡በሰቂሞን፡እንደቀ በረው ፡ ወርቅ ፡ ትሆናላችሁ፤ ወአኅጉሎ፡እስከ፡ዮም፡እንዲል፡

፴፭፤ ወእልቦ ፡ ዘኢይማስን ፡ እምውስተ፡ ኖሎት፡ወኢይድኅኑ፡አባሕኰ፡አባግዕ፡

ከዘላኖች ፡ ወገን ፡ የማይጠፋ ፡ የለም፤ የበጎዎችም ፡ አውራዎች ፡ አይድኑም፡ አለ ፡ በቁሙ ፤ አንድም ፡ ከነገሥታቱ፡ ወገን ፡ ከመኳንንቱም ፡ ወገን፤ አን ድም፡ከመምህራኑ፡ወገን፡ከደቀ፡መዛ ሙርቱም፡ ወገን ፡ የማይጠፋ ፡ የለም፤ ከመከራውም አይድኑም፤

፴፮፤ ቃለ ፡ አውያቶሙ ፡ ለኖሎት ፡ ወገዐሮሙ ፡ ለአባሕኰ ፡ አባግዕ ፡ እስመ ሠረዎ፡እግዚአብሔር፡ለመራዕይሆሙ፤

እግዚአብሔር፡መንጋቸውን፡አጥፍቶ ታልና ፤ አንድም ፡ በመራዕይሆሙ ፡ እስመ፡ሠረዎሙ፡ይላል፡



እግዚአብሔር ፡ ከመንጋቸው ፡ ጋራ ፡ አጥፍቷቸዋልና ፡ የዘላኖች ፡ ጩኸ ታቸው ፡ የበጎች ፡ አውራዎች ፡ ድምፃቸው ፡ ይሰማል ፡ አለ ፤ ዘላኖች ፡ የግንግሬት ፡ ታሥረው ፡ የበግ ፡ አውራዎች ፡ ከመንጋቸው ፡ ጋራ ፡ ሲነ ዱዋቸው ፡ እየተንጫጩ ፡ ሒደዋልና፡ አንድም፡ለመራዕይሆሙ፡ወንድሞቻ ቸውን ፡ አንድም፡ ሠራዊቶቻቸውን ፡ እግዚአብሔር ፡ አጥፍቷቸዋልና፤ አን ድም ፤ እስመ ፡ ሠረዎሙ ፡ እግዚአ ብሔር፡ በመራዕይሆሙ ይላል ፡ እነሱን፡ ከሠራዊቶቻቸው ፡ ጋራ፤ አንድም ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ጋራ ፡ እነሱን፡አጥፍቷቸዋልና፡ኖሎት፤ የነገሥታቱ፡አባሕኰ፡አባግዕ፡የመኳ ንንቱ፡ቃል፤አንድም፡ኖሎት፡የመም ህራኑ፡ቃል፡አባሕኰ፡አባግዕ፡የደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ቃል ፡ ይሰማል ፡ አለ ፤ ተማርከው ፡ የግርንግሬት ፡ አሥረው ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ አሸክመው ፡ እየገፉ ፡ እያዳፉ፡ ሲወስዷቸው ፡ እየተ ጯጯሁ፡ወርደዋልና፡እንዲህ፡አለ፤

፴፯፤ ወይወድቅ ፡ መሠንየ ፡ ሰላም ፡ እምገጸ፡ መቅሠፍተ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚአ ብሔር፤

እግዚአብሔር ፡ ካመጣበት ፡ መቅ ሠፍት ፡ የተነሣ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያማረለት ፡ የበጀለት ፡ ንጉሡም ፡ ከዚያ፡በኋላ፡ይጠፋል፤

፴፰፤ ኀደገ፡ከመ፡አንበሳ፡ማኅደሮ፡

እንዳንዱን፡በቃል፤አንበሳ፡ካዳኞች፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ማደሪያውን ፡ ለቆ ፡ እንዲሄድ ፡ ቤተ ፡ እስራኤልም ፡ ማደ ሪያው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለቆ ፡ ሄደ ፤ አንድም ፤ ከመ ፡ አንበሳ ፤ አንበሳ ፡ ካዳኞች ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ማደሪ ያውን፡ ለቆ ፡ እንዲሄድ ፡ እስራኤልም፡ ከዱዋዊ ፡ የተነሣ ፡ ኀደገ ፡ ማኅደሮ ፡ ማደሪያው፡ኢየሩሳሌምን፡ትቶ፡ሄደ፤

፴፱፤ እስመ ፡ ኮነት ፡ ምድሮሙ ፡ አፀ ፡ እምገጸ፡ መጥባሕተ ፡ አረሚ ፡ ወእምገጸ ፡ መቅሠፍተ፡መዓቱ፡ለእግዚአብሔር፤

ወእምገጸ ፡ መዓተ ፡ አረሚ ፡ ባለው ፡ እምገጸ ፡ መዓተ ፡ ዮናኒ ፡ ይላል ፤ ጠላታቸው ፡ አሕዛብ ፡ ካመጣባቸው ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ የተነሣ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተቆጥቶ ፡ ካመጣ ባቸው ፡ ገጸ ፡ መቅሠፍት ፡ የተነሣ ፡ አገራቸው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በረሐ ፡ ሁናለችና፡ አለ፤ በበረሐ፡ ሰው፡ እንዳይ ኖርበት ፡ ሰው ፡ የማይኖርባት ፡ ሁና ለችና፤አንድም፡በበረኃ፡አራዊት፡እን ዲሠለጥኑበት፡ቋያ፡እንዲበቅልበት፡ በጽዮንም ፡ በከተማይቱ ፡ አራዊት ፡ ሠልጥነውባታል፤ቋያ፡በቅሎባታል፡ ፈት፡ሁናለችና፡እንዲህ፡አለ።

## ምዕራፍ፡፳፬፡

፩፤ በቀዳሚ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለኢዮ አቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡

ንጉሥ ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም ፡ ይቀ ጥኋል ፤ የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮ ስያስ፡ ልጅ፡ኢዮአቄም፡በነገሠ፡በመ ጀመሪያው፡ዓመት፤

ኮነ፡ዝ፡ቃል፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡

ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡የእግ ዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ወይቤ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ቁም፡ውስተ፡ዐፀደ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፤
በቤተ፡እግዚአብሔር፡አጠገብ፡ባሉ፡ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ በሰባቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ሂደህ ፡ ቁም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር፤
ወንግር ፡ ለኵሉ ፡ አህጉረ ፡ ይሁዳ ፡ እለ ፡ መጽኡ፡ ይስግዱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘአዘዝኩከ ፡ ከመ ፡ ትንግሮሙ፤
በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊሰግዱ ፡ ለመጡ ፡ ለይሁዳ ፡ ሀገሮች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ንገራቸው ፡ ብዬ ፡ ልትነግራቸው፡ ያዘዝኩህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ንገራቸው፤

፫፤ ኢታንትግ፡ቃለ፡ለእመ፡ይሰምዑከ፡ወይትመየጡ፡አሐዱ፡አሐዱ፡እምፍኖቶሙ፡እኩይ፤
ይኸንን ፡ የነገርኩህን ፡ ቃል ፡ እነሱ ፡ ከሰሙህ ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ ከተመለሱ ፤ አንድም ፡ አይሰሙህም ፡ እንጂ ፡ ቢሰሙህስ ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ አይመለሱም ፡ እንጂ፡ከተመለሱስ፡ንገራቸው፡ብዬ፡ያዘዝኩህን፡ቃል፡አነሰ፡ብለህ፡አትጨምርበት፤በዛ፡ብለህ፡አትክፈለው፤
ወአኀድግ፡እንከ፡ዝኩ፡እኩየ፡ዘሐለይኩ፡እግበር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አነ ፡ በከመ ፡ እከየ ፡ ምግባሮሙ፤
እነሱስ፡ክፋታቸውን፡ከተዉ፡እኔም፡እንደሥራቸው ፡ ክፋት ፤ አንድም ፡ በእኵይ፡ምግባሮሙ፡ይላል፤በክፉ፡ሥራቸው፡በነሱ፡ላደርግባቸው፡ያሰብኩትን ፡ ክፋውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እተዋለሁ፤

፬፤ ወትብሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤
ለእመ፡ኢሰማዕክሙኒ፤
በነቢያት፡በካህናት፡አድሬ፡ያስተማርኳችሁን፡ቃል፡ካልሰማችሁኝ፤
ወኢሖርክሙ ፡ በሕግየ ፡ ዘወሀብኩክሙ፤ቅድመ፡ገጽክሙ፡ከመ፡ትስምዑ፡ቃለ፡አግብርትየ፡ነቢያት፡እለ፡ፈነውክዎሙ፡አነ፡ኀቤክሙ፡ይጊሡ፡ወኢሰማዕክምዎሙ፤
ቢመክሯችሁ፥ቢያስተምሯችሁ፡አልሰማችኋቸውም ፡ እንጂ ፤ አንድም ፤ ወኢሰማዕክሙኒ ፡ ይላል ፤ እኔ ፤ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ አድሬ ፡ ብመክራችሁ ፡ ባስተምራችሁ ፡ አልሰማችሁኝም፡እንጂ፡ፈጥነው፡ገሥግሠው፤ወደእናንተ ፡ መጥተው ፡ ሊመክሯችሁ፡ ሊያስተምሯችሁ ፡ ያዘዝኳቸው ፡ የወዳጆቼ ፡ የነቢያት ፡ የካህናትን፡ቃል፡ልትሰሙት፡ልትማሩት፤በደብረ፡ሲና፡ፊት፡ለፊት፡በሠራሁላችሁ፡በሕጌ፡በሥርዓቴ፡ጸንታችሁ፤ካልኖራችሁ፤

፭፤ እሬስዮ፡ለዝ፡ቤት፡ከመ፡ሴሎም፤
ቀድሞ፡በሴሎም፡የነበረችው፡ቤተ፤መቅደስ ፡ እንደፈረሰች ፡ ዛሬም ፤ እናንተ፡ያላችሁበትን፡ይህን፡ቤተ፤መቅደስ፡አፈርሰዋለሁ፤
ወእሬስያ፡ለዛ፡ሀገር፡ርግምተ፡በኀበ፡ኵሉ፡አሕዛበ፡ምድር፤
ከባቢሎን፡በመጡ፡በአሕዛብ፡ዘንድ፤ይችን ፡ ያላችሁባት ፡ ኢየሩሳሌምን፤ሰማርያ፡እንደጠፋች፡እንደዚያ፡አጠፋችኋለሁ፤



፮፤ ወሰምዕዎ ፡ ካህናት ፡ ወሐሳውያነ ፡ ነቢያት፡ወኵሉ፡ሕዝብ፡ለኤርምያስ፡እንዘ፡ይነግር፡ዘ፡ነገረ፡በቤተ፡እግዚአብሔር፤
ከዚያ፡በኋላ፡ኤርምያስ፡በቤተ፡እግዚአብሔር ፡ አጠገብ ፡ ባሉ ፡ ባምስቱ ፡ በስድስቱ ፡ በሰባቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ ቁም፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ሲመክር ፡ ሲያስተምር፡ካህናቱ፡መምህራንን፡የሚያሳብሉ ፤ አንድም ፡ በመምህራን ፡ የሚያብሉ ፤ አንድም ፡ ሐሳውያን ፡ ነቢያት ፡ ይላል ፤ ሐሰተኞች ፡ መምህራን፡ህዝቡም፡ሁሉ፡ኤርምያስን፡ሰሙት፤

፯፤ ወእምዝ፡አሕሊቆ፡ኤርምያስ፡ኵሎ፡ዘ፡ነገረ፡ዘአዘዞ፡እግዚአብሔር፡ይንግር፡ለኵሉ፡ሕዝብ፤
ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ሊመክር ፡ ሊያስተምር፡ እግዚአብሔር ፡ ምከር ፡ አስተምር፡ብሎ፡ያዘዘውን፡ይኸንን፡ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኤርምያስ ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ፡ከጨረሰ፡በኋላ፤
ወአኀዝዎ፡ካህናት፡ወሐሳውያነ፡ነቢያት፡ወኵሉ፡ሕዝብ፤
ካህናቱ ፡ በመምህራን ፡ የሚያብሉ ፡ ነቢያተ፡ሐሰትና፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡ተሰብስበው፡ኤርምያስን፡ያዙት፤
ወይቤልዎ፡ሞተ፡ትመውት፤
አንተ፡ሞትን፡ትሞታለህ፡አሉት፤

፰፤ ለምንት፡ተነበይከ፡በስመ፡እግዚአብሔር፤
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብለህ፡የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠርተህ ፡ ለምን፡አስተማርከ?
ወትቤ፡ከመ፡ሴሎም፡ይከውን፡ዝ፡ቤት፤
ይህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቀድሞ ፡ በሴሎም ፡ እንደነበረው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ይሆናል፤
ወትማስን፡ዛ፡ሀገር፤
ይቺም፡ኢየሩሳሌም፡እንደ፡ሰማርያ፡ሁና፡ትጠፋለች፤
ወአልቦ፡ዘይነብራ፤
ሰማርያ፡ተፈታ፡ጠፍታ፡ሰው፡እንዳይኖርባት ፡ ይህቺም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተፈታ፡ጠፍታ፡ሰው፡አይኖርባትም፡ብለህ፡ለምን፡አስተማርከ፡አሉት፤አንድም፡ጠላቶቹ፡ነቢያተ፡ሐሰት፡ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ ከበው ፡ ከያዙት ፡ በኋላ፡ ወዳጆቹ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብለህ፡ለምን፡አስተማርከ?
ወትቤ፡ከመ፡ሴሎም፡ይከውን፡ዝ፡ቤት፤
ይህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቀድሞ ፡ በሴሎም፡ እንደነበረው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ይሆናል፤
ወትማስን፡ዛቲ፡ሀገር፤
ይቺም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደሰማርያ ፡ ትጠፋለች፤
ወአልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴታ፤
ሰማርያ፡ተፈታ፡ጠፍታ፡ሰው፡እንዳይኖርባት ፡ ይህቺም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተፈታ፡ጠፍታ፡ሰው፡አይኖርባትም፡ብለህ፡ለምን፡አስተማርከ፡ብለው፡መከሩት፤
ወአንገለጉ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ላዕለ፡ኤርምያስ፡በቤተ፡እግዚአብሔር፤
ኤርምያስ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳለ፤አንድም፡እነሱ፡በቤተ፡እግዚአብሔር፡ሁነው፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡በኤርምያስ፡ዶለቱበት፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወሰምዑ፡መላእክተ፡ይሁዳ፡ዘ፡ነገረ፡
ወዐርጉ፡እምቤተ፡ንጉሥ፡ውስተ፡ቤተ፡እግ
ዚአብሔር፡
የይሁዳ ፡ አለቆችም ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡
ሰምተው ፤ አንድም ፡ ወሰምዑ ፡
መላእክተ ፡ ይሁዳ፡ ዘገብሩ ፡ ይላል ፤
ነቢያት፡ሐሰት፡ካህናተ፡ጣዖት፡ያደረ
ጉትን ፡ ሁሉ ፡ ሰምተው ፡ ከንጉሡ ፡
ቤት፡ ወጥተው ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ሄዱ፤
ወነበሩ፡ውስተ፡ዶዶ፡አንቀጸ፡ቤተ፡እግዚአ
ብሔር፡ሐዲስ፡
ባዲሱ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በር ፤
አንድም፡ሐዲስ፡ይላል፤አዲስ፡ሁኖ፡
በተሠራው ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ደጃፍ ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ፤ ሐዲስ ፡
አለው ፡ አሣፍ ፡ አርጅቶ ፡ አግኝቶት ፡
አድሶት፡ነበርና፤
፲፩፡ ወይቤሉ ፡ ካህናት ፡ ወሐሳውያን ፡
ነቢያት ፡ ለመላእክት ፡ ወለኵሉ ፡ ሕዝብ ፡
ሞት፡ኵነኔሁ፡ለዝ፡ብእሲ፡
ያንጊዜም ፡ ካህናተ ፡ ጣዖቱ ፡ ሐሰ
ተኞች ፡ መምህራንም ፡ ላለቆችና ፡
ለሕዝቡ፡የዚህ፡ሰው፡ፍርዱ፡ይሙት፡
በቃ፡ነው፡አሉ፤
እስመ ፡ ተነበየ ፡ ላዕለ ፡ ዛ ፡ ሀገር ፡ ዘከመ ፡
ሰማዕክሙ፡በዕዘኒክሙ፡
እናንተ፡በጆሯችሁ፡እንደሰማችሁት፡
በዚች ፡ አገር ፡ ትጠፋለች ፡ ብሎ ፡
ትንቢት፡ተናግሯልና፤
፲፪፡ ወነገሮሙ ፡ ኤርምያስ ፡ ለኵሉ ፡
መላእክት ፡ ወለኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወይቤሎሙ ፡
እግዚአብሔር፡ፈነወኒ፡እትነበይ፡ላዕለ፡ዝ፡
ቤት፡ወላዕለ፡ዛ፡ሀገር፡ኵሎ፡ዘ፡ነገረ፡ዘሰማ
ዕክሙ፡

ሳስተምር ፡ ስመክር ፡ የሰማችሁትን ፡
ይህንን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዚች ፡ አገርና ፡
በዚህ፡ቤተ፡መቅደስ፡ሳስተምር፡እግ
ዚአብሔር፡ምክር፡አስተምር፡ብሎ፡
ላከኝ ፡ ላለቆችና ፡ ለሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡
ነገራቸው፤
፲፫፡ ወይእዜኒ፡አሠንዩ፡ፍናዊክሙ፡ወም
ግባሪክሙ፡
አሁንም ፡ ቃሌን ፡ አልመልሰው ፡
ፍጹም ፡ ክፉ ፡ ሥራችሁን ፡ ያማረ ፡
የተወደደ፡የበጎ፡አድርጉት፤
ወስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አምላክክሙ፡
በኔ ፡ አድሮ ፡ የሚነግራችሁ ፡ የፈጣሪ
ያችሁ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡
ስሙ፤ወይእዜኒ፡አሠንዩ፡ፍናዊክሙ፡
ብሎ፡ነበርና፡እንዲህ፡አለ፤አንድም፡
ከኔ ፡ አስቀድሞ ፡ በነበሩ ፡ በነቢያት ፡
አድሮ ፡ የነገራችሁን ፡ የፈጣሪያችሁ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤
አንድም ፡ አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፡
አድሮ፡የነገራችሁን፡የፈጣሪያችሁን፡
ቃል፡ስሙ፤
ወየኀድግ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኩየ ፡ ዘነበበ፡
ላዕሌክሙ፤
ይኸን ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ፈጣሪ
ያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በናንተ ፡ አደር
ገዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ክፉ
ውን፡ነገር፡መልሶ፡ይተወዋል፤
፲፬፡ ወነየ ፡ አነኒ ፡ ውስተ ፡ እደዊክሙ ፡
ረስዩኒ፡ዘፈቀድክሙ፡ወዘይረትዓክሙ፡በአ
ዕይንቲክሙ፤
እኔስ ፡ በእጃችሁ ፡ ጭብጥ ፡ በእግ
ራችሁ፡ እርግጥ ፡ ሁኜ ፡ የተያዝኩ
ነኝና፡እናንተ፡የወደዳችሁትን፡ለዓይ
ናችሁም ፡ የቀናውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛ
ችሁን፡ነገር፡አድርጉብኝ፤



፲፭፡ ዳዕሙ፡አእምሮ፡አእምሩ፡ወጠይቁ፡
ኩ ፡ ለእመ ፡ ቀተልክሙኒ ፡ ፍዳ ፡ ደም ፡
ንጹሕ፡ይገብእ፡ላዕሌክሙ፡
ነገር፡ግን፡እኔን፡በግፍዕ፡ብትገሉኝ፡
የንጹሑ፡የደሜ፡ፍዳ፡ወደናንተ፡እን
ዲመለስ ፡ እወቁ ፤ አንድም ፡ እኔን ፡
በግፍዕ ፡ ብትገድሉኝ ፡ የንጹሑ ፡
የደሜ፡ ፍዳ ፡ ወደናንተ ፡ እንዲመለስ
ባችሁ፡እወቁ፡እንጂ፤ረስዩኒ፡ዘፈቀ
ድክሙ ፤ የወደዳችሁትን ፡ አድር
ጉብኝ፤
ላዕሌክሙ፡ባለው፡ላዕለ፡ርእስክሙ፡
ይላል፤እንደዚሁ፡ያስተረጉማል፤
ወላዕለ፡ዛ፡ሀገር፡ወላዕለ፡እለ፡ይነብርዋ፡
የንጹሑ ፡ የደሜ ፡ ፍዳ ፡ ወደዚች ፡
አገርና ፡ ወደሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡
ይመለሳል፤
እስመ ፡ እሙነ ፡ ለአከኒ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀቤክሙ ፡ እንግር ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ ውስተ ፡
ዕዘኒክሙ፡ኵሎ፡
ኵሎ ፡ ዘነገረ ፡ እንግር ፡ ውስተ ፡
ዕዘኒክሙ፤
ሲል ፡ ነው ፤ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡
በጆሯችሁ ፡ እየሰማችሁኝ ፡ ልነግ
ራችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደናንተ ፡
በውነት ፡ ልኮኛልና ፤ ይገብእ ፡
ላዕሌክሙ፡ላለው፤
፲፮፡ ወይቤሉ ፡ መላእክት ፡ ወኵሉ ፡
ሕዝብ፡ ለካህናት ፡ ወለሐሳውያን ፡ ነቢያት ፡
አልቦ፡ኵነኔ፡ሞት፡ላዕለ፡ዝ፡ብእሲ፡
ያንጊዜም ፡ አለቆችና ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰብ
ስበው ፡ ለካህናቱና ፡ በመምህራን ፡
ለሚያብሉ ፡ መምህራንን ፡ ለሚያ
ሳብሉ ፤ አንድም ፡ ለሐሳውያን ፡
ነቢያት ፡ ይላል ፤ ለሐሰተኞችም ፡

መምህራን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ይሙት ፡
በቃ፡ፍርድ፡የለበትም፡አሉ፤
እስመ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡
ነገረነ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡
የፈጣሪያችንን፡ስም፡ጠርቶ፡በፈጣሪ
ያችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ነግሮ
ናልና፡ስለነገረን፤
፲፯፡ ወተንሥኡ ፡ ዕደው ፡ እምሊቃናተ ፡
ብሔር፡
ሊቃናት፡የነገር፡ናቸው፤ባገር፡ነገር፡
ከሚያውቁ፡ሰዎች፡ወገን፡ያን፡ጊዜ፡
ተመራርጠው፡ተነሥተው፤
ወይቤልዎሙ፡ለኵሎሙ፡ማኅበረ፡አሕዛብ፤
ለተሰበሰቡት ፡ ለእስራኤል ፡ ሁሉ ፡
እንዲህ፡አሏቸው፤
፲፰፡ ሚክያስ ፡ ሜሮታዊ ፡ (ሞሮታዊ) ፡
ነበረ፡ ይትነበይ ፡ በመዋዕለ ፡ ሕዝቅያስ ፡
ንጉሠ፡ይሁዳ፤
በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡
ዘመን ፡ የሜሮት ፡ ሰው ፡ ሚክያስም ፡
እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ሲመክር ፡ ሲያስ
ተምር፡ነበረ፤
ወይቤሎሙ፡ለኵሉ፡ሕዝበ፡ይሁዳ፤
ለይሁዳ፡ወገኖች፡ሁሉ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት ፡
የሐርስዋ፡ለጽዮን፡ከመ፡ገራህት፡
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡ጽዮን፡ከተማ
ይቱን፡እንደርሻ፡ያርሱዋታል፡አለ፡
ብሎ፡አላቸው፤ነገራቸው፤የሐርስዋ፡
አለ፤በውኑ፡አርሰዋታልን፡ቢሉ፡አላ
ረሱዋትም ፤ ጐንደር ፡ ይታረስ ፡
እንዲሉ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ በዔዋዌ ፡
ጠፍታ ፡ ተፈታ ፡ አርሰዋታል ፤
አንድም፡ በዳዊት ፡ በሰሎሞን ፡

www.ethiopianorthodox.org

መቃብር ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ እንደተገኘበት፡እኛም፡እንደዚያ፡ወርቅ፡ብር፡ እናገኝባታለን ፡ ብለው ፡ አርሰዋታልና፤ አንድም ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ የመዝጊያው ፡ የመድረኩ ፡ የመቃኑ ፡ ጉብጉባቱ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ነበር ፤ ያንን፡በምዝራጥ፡በአንካሴ፡እየቀረፉ፡ ወስደውታልና ፡ ያንን ፡ ሲያይ ፡ የሐርስዋ፡አለ፤

ወኢየሩሳሌም፡ትከውን፡አፀ፡ወልጎተ፡

ኢየሩሳሌምም ፡ ጠፍታ ፡ ተፈታ ፡ ምድረ፡በዳ፡በረኃ፡ትሆናለች፤

ወደብረ፡ዝኒ፡ቤት፡ይከውን፡ዖመ፡

የቤተ ፡ መቅደስም ፡ ፫ቱ ፡ ፯ቱ ፡ ፺ቱ ፡ ቆመ፡ብእሲ፡ጠፍቶ፡ተፈቶ፡ዛፍ፡ይበቅልበታል ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የሚሮቱ፡ ሰው ፡ ሚክያስ ፡ መከረ ፤ አስተማረ፤

፲፰፤ ቦኑ ፡ ቀቲለ ፡ ዘቀተሎ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ንጉሠ፡ይሁዳ፡

ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የሚሮት ፡ ሰው ፡ ሚክያስ ፡ ቢመክር ፡ ቢያስተምር ፡ የይሁዳው፡ንጉሥ፡ሕዝቅያስ፡በውኑ፡ የገደለውን፡መግደል፡አለን፤

ወኵሉ፡ይሁዳ፡

የይሁዳ፡ሰዎችስ፡የገደሉት፡መግደል፡ አለን፤

አኮኑ፡ፈርሆ፡ለእግዚአብሔር፡

ስንኳን ፡ ሊገድለው ፡ ሚክያስ ፡ በመከረው ፡ ባስተማረው ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቅያስ፡እግዚአብሔርን፡የፈራው፡ ያመለከው፡አይደለምን፤

ወተማኅለለ፡ለገጸ፡እግዚአብሔር፡

የእግዚአብሔርንስ ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱን ፡ ለማግኘት ፡ የለመነ ፡ የተለማመጠ ፡ አይደለምን፤

አንድም ፡ አኮኑ ፡ ፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር፡ይላል፡ወኵሉ፡ይሁዳ፡ብሎ፡ ነበረና ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎችስ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈሩት ፡ ያመለኩት ፡ አይደለምን ፤ ወተማኅለሉ ፡ ለገጸ ፡ እግዚአብሔር ፤ የእግዚአብሔርንስ ፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ለማግኘት፡የለመኑ፡የተለማመጡ፡አይደለምን፤

ወኀደገ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኩየ ፡ ዘነበበ፡ ላዕሌሆሙ፤

ፈጣሪያቸው፡እግዚአብሔርስ፡የሕዝቅያስን፡ኀዘንና፡የሕዝቡን፡ልመና፡ ሰምቶ፡በነሱ፡አደርገዋለሁ፡ብሎ፡የተናገረውን ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ መልሶ፡ የተወው፡አይደለምን፤

ወንሕነኒ ፡ ዐቢየ ፡ እኩየ ፡ ገበርነ ፡ ላዕለ፡ ነፍስነ፤

እኛም፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ ብሎ፡ ያስተማረንን ፡ እንሰማ ፡ እንቀበል ፡ ብለን ፡ እሱን ፡ ብንገድለው፡ በራሳችን፡ክፉውን፡መቅሠፍት፡ማድረጋችን ፡ ነው ፡ አሉ፤ እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ያደረባቸው፡ዕውቀት፡የተሰጣቸው ፡ የቀና፡ ፍርድ ፡ የተገለጠላቸው፤

፲፱፤ ወሀሎ ፡ ብእሲ ፡ ዘተነበየ ፡ በስመ፡ እግዚአብሔር፤

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ብሎ፡የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ያስተማረ፡አንድ፡ሰው፡አለ፤

ኦርያስ፡ወልደ፡ሴምዩ፡ዘቀርያታርም፤

ይኸውም ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፤ብሎ፡ያስተማረ፡አንድ፡ሰው፡



አለ ፡ ያልነው ፡ የቀርያታርሙ ፡ ሰው ፡ የሴምዩ፡ልጅ፡ኦርያስ፡ነው፤

ዘተነበየ፡ላዕለ፡ዛ፡ሀገር፡

በዚች ፡ አገር ፡ ትንቢት ፡ የተናገረው ፡ ኦርያስ፡ነው፡አለ፡በከተማዪቱ፡፡

ወላዕለ፡ዛ፡ምድር፤

በኢየሩሳሌምም ፡ ትንቢት ፡ የተናገረ ፡ አለ፡በገጠሩ፤

ወከመ፡ኵሉ፡ነገሩ፡ለኤርምያስ፡

ነገሩም፡ሁሉ፡እንደ፡ኤርምያስ፡ነገር፡ ነው፤

፳፤ ወሰምዐ፡ንጉሥ፡ኢዮአቄም፡

ኦርያስም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ንጉሡ፡ኢዮአቄም፤

ወኵሉ፡ሰብኡ፡

ሠራዊቱም፡ሁሉ፡ሰሙ፤

ወኵሎሙ፡መላእክት፡ኵሎ፡ነገሮ፡

አለቆችም፡ሁሉ፡የተናገረውን፡ነገር፡ ሁሉ፡ሰሙ፤

ወፈቀደ፡ንጉሥ፡ይቅትሎ፡

ንጉሡም፡ሊገድለው፡ወደደ፤

ወሰምዐ፡ኦርያስ፡ወፈርሀ፡

ሰምዐ ፡ ያለውን ፡ ፈርሀ ፡ ብሎ ፡ ገለጠው፤ኦርያስም፡መኳንንቱ፡የመከሩትን ፡ ንጉሡም ፡ ምክራቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ እገድለዋለሁ ፡ ያለውን ፡ ሰምቶ፤

ወጐየ፡ወሖረ፡ብሔረ፡ግብፅ፤

ፈርቶ፡ሸሽቶ፡ወደግብፅ፡አገር፡ሄደ፤

፳፩፤ ወፈነወ፡ንጉሥ፡ኢዮአቄም፡ዕደወ፡ ብሔረ፡ግብፅ፤

ንጉሡ ፡ ኢዮአቄምም ፡ ሂዱ ፡ ያዙት ፡ ብሎ ፡ ሰዎችን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ አገር ፡ ሰደደ፤

ኤልታንሃ ፡ ወልደ ፡ አቤኮር ፡ ወዕደወ ፡ ምስሌሁ፡ግብፀ፡

የአቤኮር፡ልጅ፡ኤልታንንና፡ሰዎችን፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ጨምሮ ፡ ወደግብፅ ፡ ሰደዳቸው ፤ አንድም ፡ ወዕደው ፡ ምስሌሁ ፡ ግብፀ ፡ ይላል ፤ የአቤኮር ፡ ልጅ ፡ ኤልታንን ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ሹሞ፡ የሚያዝበትንም ፡ ምሥጢር ፡ ለብቻው ፡ ነግሮ ፡ ሰዎች ፡ ጨምሮ ፡ ላከው ፤ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሁነው፡ወደ፡ግብፅ፡ተሻግረው፡ሔዱ፤

፳፪፤ ወአምጽእዎ፡እምህየ፡ለኦርያስ፡

እነዚያም፡ከኤልታን፡ጋራ፡ተልከው፡ የሔዱ ፡ ሰዎች ፡ ሒደው ፡ ኦርያስን ፡ ከግብፅ፡አመጡት፤

ወአብእዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡

ከግብፅም ፡ አምጥተው ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮአቄም ፡ ወዳለበት ፡ እልፍኝ ፡ አገቡት፤

ወቀተሎ ፡ በመጥባሕት ፡ ወወረወ ፡ በድኖ ፡ ውስተ፡መቃብረ፡ደቂቀ፡ሕዝቡ፡

ንጉሡ ፡ ኢዮአቄምም ፡ ኦርያስን ፡ በሾተል ፡ አስገደሎ ፡ ሬሳውን፤ በወገኖቹ፡ልጆች፡መቃብር፡አጠገብ፡ ጣለው፤

፳፫፤ ወዳዕሙ ፡ እደ ፡ ኪርቃም ፡ ወልደ ፡ ሳፋን፡ሀለወ፡ምስለ፡ኤርምያስ፡ከመ፡ኢያግብዕዎ፡ለሕዝብ፡ይቅትልዎ፤

ሕዝቡ፡ተሰብስበው፡እንዳይገድሉት፡ ሊገድሉት ፡ በጠላቶቹ ፡ እጅ ፡ አሳልፈው፡እንዳይሰጡት፡የሳፋን፡ልጅ፡ የኪርቃም፡ቃሉ፡ከኤርምያስ፡ጋራ፡ ነበር፤አንድም፡ዳዕሙ፡እደ፡ወለተ፡ ኪርቃም ፡ ወልደ ፡ ሳፋን ፡ ሀለወ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምስለ፡ኤርምያስ፡ከመ፡ኢያግብዕዎ፡ ለሕዝብ ፡ ወኢይቅትልዎ ፤ ይላል ፤ ሕዝቡ ፡ ለጠላቶቹ ፡ አሳልፈው፡ ሰጥተውት ፡ ጠላቶቹ ፡ እንዳይገድሉት፡ የኪርቃም፡ልጅ፡ቃሉዋ፡ከኤርምያስ፡ ጋራ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ኢዮአቄምስ ፡ እሱን፡ ገድሎ ፡ ገደፈ ፡ በድኖ፡ ብለህ ፡ እሠር።

## ምዕራፍ፡፳፯፤

### ጉባዔ፤

፩፤ በቀዳሚ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለኢዮአቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ኮነ፡ ዝቃል ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር፡

ንጉሠ ፡ ይሁዳን ፡ ለሁለቱም ፡ ይቀጥሏል፤ የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮስያስ፡ልጅ፡ኢዮአቄም፡በነገሠ፡በመጀመሪያው፡ዘመን፡ይህ፡ቃል፡ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡መጣ፡ተነገረ፤

፪፤ ወይቤ፤

እንዲህ፡ብሎ፤

ከመዝ፡ይቤለኒ፡እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤

ግበር፡ለከ፡ጋገ፡ወሐግለ፤

ጋገ፡ያንገት፡ጃንጀር፤ሐግለ፡ቀምበር፤ አንድም ፡ ጋገ ፡ ያንገት ፡ ጃንጀር ፡ ቀምበር ፤ ሐግለ ፡ ቅትርት ፡ ማነቆ ፡ ሥራ፡አለኝ፤

ወደዮ፡ውስተ፡ክሣድከ፤

ይህንንም ፡ ሥርተህ ፡ ባንገትህ ፡ እሠረው፡አለኝ፤

፫፤ ወፈኑ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ኤዶምያስ፡ወኀበ፡ንጉሠ፡ሞዓብ፡ወኀበ፡ንጉሠ፡ደቂቀ፡አሞን፡ወኀበ፡ንጉሠ፡ጢሮስ፡ወኀበ፡ንጉሠ፡ሲዶና፡ በእደ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኢየሩሳሌም፡ኀበ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤

ንጉሥ፡ወደ፡ንጉሥ፡ይላላካልና፡ወደ ይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ወደሴዴቅያስና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተልከው ፡ በሚመጡ፡በመልእክተኞች፡ቃል፡ወደኤዶምያስ፡ንጉሥና፡ወደሞአብ፡ንጉሥ፡ ወደአሞን፡ልጆችም፡ንጉሥ፡ወደጢሮስና፡ወደሲዶናም፡ንጉሥ፡ላከው፡ አለኝ፤

፬፤ ወአዝዞሙ ፡ ይንግርዎሙ ፡ ለአጋዕዝቲሆሙ፤

ለጌቶቻቸው ፡ ሊነግሯቸው ፡ መልእክተኞችህንም፡እዘዛቸው፡አለኝ፤

ወይበሉ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ፀባዖት፡አምላከ፡፳ኤል፤

የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡ብለው፡ለጌቶቻቸው ፡ ይነግሯቸው ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው፡አለኝ፤

ከመዝ፡በልዎሙ፡ለአጋዕዝቲክሙ፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነበርና፡ ጌቶቻችሁን ፡ እንዲህ ፡ በሏቸው፤

፭፤ አነ፡ገበርክዋ፡ለምድር፤

እኔ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ምድርን ፡ ፈጠርኋት፤

ወሰብአ፡ወእንስሳ፡ዘላዕለ፡ገጸ፡ምድር፤

ምድርንም ፡ ከፈጠርኩ ፡ በኋላ ፡ ሰውንና፡ እንስሳትን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፈጠርኩ፤ አንድም ፡ አነ ፡ ገበርክዋ ፡ ለምድር ፡ ሰብአ ፡ ወእንስሳ ፡ ዘላዕለ ፡ ገጸ፡ ምድር ፡ ይላል፤ ዘላዕለ ፡ ገጸ ፡ ምድርና ፡ ለምድር፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እኔስ ፡ ለምድር፡ሰውንና፡እንስሳትን፡ከዚህ፡ቀድሞ፡ፈጠርኩላት፤



በኃይልየ፡ዐቢይ፡ወበመዝራዕትየ፡ልዕልት፤

በጽኑ፡ሥልጣኔ፡ፈጠርኩላት፤

ወወሀብክዎ፡ለዘአደመኒ፡በአዕይንትየ፤

ይህን፡ሁሉ፡ፈጥሬ፡ባይኔ፡ደስ፡ለሚያሰኘኝ ፡ ለሰው ፡ ሰጠሁት ፤ አንድም ፡ ወወሀብክዋ ፡ ለዘአደመኒ ፡ በአዕይንትየ ፡ ይላል፤ ምድርንም ፡ ፈጥሬ ፡ ለዓይኔ ፡ ደስ ፡ ለሚያሰኘኝ ፡ ለአዳም ፡ ሰጠኋት፤

፮፤ ወይእዜኒ ፡ አነ ፡ አግባዕክዋ ፡ ለኵላ ፡ ምድር ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፡ገብርየ፤

ዛሬ ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡ እንዲህ ፡ አድርጌ ፡ የፈጠርኋት፡ምድርን፡በእጁ፡ጭብጥ፡በእግሩ፡እርግጥ፡አድርጎ፡ሊገዛት፡ለአገልጋዬ፡ለባቢሎኑ፡ንጉሥ፡ለናቡከደነፆር ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋት፤ ናቡከደነፆርን ፡ ገብርየ ፡ አለው ፡ በተፈጥሮ ፤ አንድም ፡ ባሪያን ፡ ካሰቡት ፡ እንዲልኩት ፡ ካዘዙት ፡ እንዲደርስ ፡ እሱንም፡ አስቦ ፡ አዝዞ ፡ ሊያጠፉ ፡ ወደሁለቱ ፡ ነገድ ፡ አገር ፡ አምጥቶታልና፤

ወአራዊተ፡ገዳምኒ፡ወሀብኩ፡ሎቱ፡ከመ፡ ይትቀነይዎ፤

ስንኳን ፡ ሰውን ፡ ለሱ ፡ ሊገዙለት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያሉ ፡ አራዊትንም ፡ ሰጠሁት ፡ አለ ፡ በቁሙ፤ አንድም ፡ ለማዳ ፡ አራዊት ፡ ናቸው፤ አንድም ፡ አሕዛብ፡ናቸው፤

፯፤ ወይትቀነዩ፡ሎቱ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ ለወልዱ ፡ ወለውሉደ ፡ ውሉዱ ፡ እስከ፡ ይበጽሕ፡ዕድሜ፡ምድሩ፤

ወአራዊተ ፡ ገዳምኒ ፡ ወሀብኩ ፡ ሎቱ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ አገሩ ፡ የሚጠፋበት ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ አስቀድመው፡ለልጁ፡ኋላም፡ለልጅ፡ልጁ፡ ይገዛሉ፤

ወሎቱኒ ፡ ይትቀነዩ ፡ አሕዛብ ፡ ብዙኃን ፡ ወነገሥት፡ዐበይት፤

ዛሬም ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ታላላቅ ፡ ተወራራጅ፡ነገሥታት፡ሁሉ፡ለእሱ፡ ይገዛሉ፤

፰፤ ወይከውን፡ሕዝብ፡ወመንግሥታት፡ እለ፡ ኢይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፤

ለወዳጄ፡ለባቢሎኑ፡ንጉሥ፡ለናቡከደነፆር፡እንገዛም፡የሚሉ፡ያሉ፡ነገሥታቱና፡ሠራዊቱ፤

ወኢይወድዩ፡ክሣዶሙ፡ታሕተ፡አርዑተ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፤

አንገታቸውንም ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፥ ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡አንገብርም ፡ አንቀቅልም ፡ ያሉም፡ሰዎች፡ሁሉ፤

በመጥባሕት ፡ ወበረኃብ ፡ ወበብድብድ ፡ ይወድቁ፤

ይከውን ፡ ያለውን ፡ አመጣ፤ በጦርና ፡ በመቅሠፍት ፡ በቀጠና ፡ በቸነፈር ፡ ይጠፋሉ፤

ወእዋኅዮሙ፡ለእሙንቱ፡አሕዛብ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡እስከ፡የኃልቁ፡በእዴሁ፤

ለናቡከደነፆር ፡ አንገዛም ፡ ያሉ ፡ ሕዝቡንና ፡ አሕዛቡንም ፡ በናቡከደነፆር፡እጅ፡እስኪጠፉ፡ድረስ፡እኔም፡በመዓት፡እጐበኛቸዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወአንትሙሰ፡ኢትስምዕዎሙ፡ለሐሳ
ውያነ፡ነቢያቲክሙ፤
በመምህራን ፡ የሚያብሉ ፡ ነቢያተ ፡
ሐሰትን፡ግን፡አትስሟቸው፤

ወለእለ፡ይሰግሉ፡ለክሙ፤
የሚጠነቍሉላችሁን፤አንድም፡የሚ
ያስጠነቍሉላችሁን፤

ወለሐላምያኒክሙ፤
አለምን፡አለምን፡የሚሉላችሁንም፤

ወለረአይያኒክሙ፤
ራእዩን፡አየን፡አየን፡የሚሉላችሁን፤

ወለሰብአ፡ሥራይ፤
ሟርተኞቻችሁን፤ አንድም ፡ ሥር ፡
የሚምሱላችሁን፡ቅጠል፡የሚበጥሱ
ላችሁን፡ሰዎች፤

እለ ፡ ይብሉክሙ ፡ ኢትትቀነዩ፡ ለንጉሠ ፡
ባቢሎን፤
ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡
አትገዙ ፤ አንድም ፡ ኢትትቀነዩ ፡
ይላል፤ አትገዙም ፡ የሚሏችሁን ፡
ሰዎች፡ሁሉ፡አትስሟቸው፤

፲፤ እስመ፡ሐሰተ፡ተነበዩ፡ለክሙ፡ከመ፡
ያርኅቁክሙ፡እምብሔርክሙ፤
ካገራችሁ ፡ አስማርከው ፡ አርቀው ፡
ሊሰዷችሁ፤

ወይዝርዉክሙ፡ወያጥፍዑክሙ፤
ከወገኖቻችሁ፡ለይተው፡በአሕዛብ፡
አገር ፡ በትነው ፡ ሊያጠፏችሁ ፡
ለናንተ፡ ሐሰት ፡ ትንቢት ፡ ነግረዋች
ኋልና፤ አንድም ፤ እስመ ፡ ሐሰተ ፡
ተነበዩ፡ለክሙ፡ከመ፡ያርኅቁክሙ፡
እምብሔርክሙ ፡ ወእዘርወክሙ ፡
ወትጠፍዑ፡ይላል፤ከሀገራችሁ፡አስ
ማርከው ፡ አርቀው ፡ ሊሰዷችሁ ፡
ሐሰት፡ትንቢት፡ስለነገሩዋችሁ፤ኢት
ስምዕዎሙ፡ይኸንን፡ቃሌን፡እምቢ፡
ብትሉ ፡ ግን ፤ እዘርወክሙ ፡ ከሀገ
ራችሁ፡ አስማርኬ፡ በአሕዛብ፡ አገር፡
እበትናችኋለሁ ፤ ወትጠፍዑ ፡ እና
ንተም፡ከሀገራችሁ፡እልም፡ድርግም፡
ብላችሁ፡ትጠፋላችሁ፤

፲፩፤ ወሕዝብሰ፡ዘይወዲ፡ርእሶ፡ታሕተ፡
አርዑተ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወይትቀነይ ፡
ሎቱ፤
ለ፡የቀረው፡ነው፤ራሱን፡ዝቅ፡ዝቅ፡
አድርጎ፡ለባቢሎኑ፡ንጉሥ፡ለናቡከደ
ነፆር ፡ የገበረ ፤ የቀቀለ ፤ ለእሱም ፡
የተገዛ፡ሰውን፡ግን፤

አነብሮ ፡ ውስተ ፡ ምድሩ ፡ ይቤ፡ እግዚአ
ብሔር፤
በተወለደበት ፡ አገር ፡ በተድላ ፡
በደስታ፡ አኖረዋለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

ወይትጌበራ፡ወየኃድር፡ውስቴታ፤
ውስተ፡ምድሩ፡ብሎ፡ነበርና፤የተወለ
ደባትንም ፡ አገር ፡ እያረሳት ፡ እየቆ
ፈራት ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይኖር
ባታል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፪፤ ወነገርክዎ ፡ ኵሎ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ ለሴዴ
ቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
ለይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስም፡
ሒጄ፡ይህን፡ሁሉ፡ነገር፡ነገርሁት፤

ወእቤሎ ፡ አትሕቱ ፡ ክሣደክሙ፤ ውስተ፡
አርዑተ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ለባቢሎኑ፡ንጉሥ፡ለናቡከደነፆር፡አን
ገታችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጋችሁ፡
[illegible]



ወተቀነዩ፡ሎቱ፡ወለሕዝቡ፤
ለሱም፡ለሠራዊቱም፡ግዱን፡ተገዙ፤

ወተሐይዉ፤
ይህን፡ያደረጋችሁ፡እንደሆነ፡ከሞት፡
ትድናላችሁ፤ በሕይወት ፡ ትኖራ
ላችሁ፤

፲፫፤ ለምንት ፡ ትመውት ፡ አንተ ፡
ወሕዝብከ፡በመጥባሕት፡ወበረኃብ፡ወበብ
ድብድ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለሕዝብ፡ዘኢተቀንየ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡
ባልተገዛ ፡ ወገን ፡ እግዚአብሔር ፡
መቅሠፍት ፡ አመጣበታለሁ ፡ ብሎ ፡
እንደተናገረ ፡ ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለና
ቡከደነፆር፡አንገብርም፤አንቀቅልም፤
ለሱም ፡ አንገዛም ፡ ብላችሁ ፡ በጦር፤
በመቅሠፍት፤ በቀጠና ፡ በቸነፈር ፡
አንተና፡ወገኖችህ፡እስራኤል፡ለምን፡
ትሞታላችሁ፡አልኩት፤

፲፬፤ ወኢትስምዑ ፡ ቃሎሙ ፡ ለነቢያት ፡
እለ ፡ ይቤሉክሙ ፡ ኢትትቀነዩ ፡ ለንጉሠ፡
ባቢሎን፤
ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡
አትገዙ ፤ አንድም ፡ አትገዙም ፡
የሚሏችሁ ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰትንም ፡
ቃል፡አትስሙ፤

እስመ፡ሐሰተ፡እሙንቱ፡ይትኔበዩ፡ለክሙ፤
እነሱ ፡ ሐሰት ፡ ትንቢትን ፡ ይነግሯች
ኋልና፤

፲፭፤ እስመ፡ኢፈነውክዎሙ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፤
[illegible]

ተናገሩ፡ብዬ፡አልላክኋቸውምና፤

ወውእቶሙሰ ፡ ይትኔበዩ ፡ ለክሙ ፡ ሐሰተ ፡
በስምየ ፡ ከመ ፡ ያኅጕሉክሙ ፡ ወትጠፍዑ ፡
አንትሙ፤
ከሀገራችሁ ፡ አስማርከው ፡ ሊያጠ
ፏችሁ ፡ እነሱ ፡ ከልቡናቸው ፡
አንቅተው ፤ ካፋቸው ፡ አውጥተው ፡
በሐሰት፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ብለው፡ያስተምሯችኋል፡እንጂ፤የኔን፡
ቃል ፡ ትታችሁ ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡
ቃል ፡ የሰማችሁ ፡ እናንተም ፡ ከሀገ
ራችሁ፡ትጠፋላችሁ፤

ወነቢያቲክሙሂ ፡ እለ ፡ ተነበዩ ፡ ለክሙ ፡
በሐሰት፤
በሐሰት ፡ ትንቢታቸውም ፡ አትጠ
ፉም ፡ ብለው ፡ ያስተማሯችሁ ፡
ነቢያተ፡ ሐሰት ፡ መምህሮቻችሁም ፡
ከናንተ፡ጋራ፡ይጠፋሉ፤

፲፮፤ ለካህናትኒ፡ወለኵሉ፡ሕዝብ፡ዘንተ፡
ነገረ፡ነገርክዎሙ፤
እኔም ፡ ሒጄ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ለካህ
ናቱና፡ለሕዝቡ፡ነገርኋቸው፤

ወእቤ ፡ ኢትስምዕዎሙ፡ ለነቢያት ፡ እለ ፡
ይትኔበዩ፡ለክሙ፤
እኔም፡ሒጄ፡ሐሰት፡ትንቢት፡የሚያ
ስተምሯችሁ፡ነቢያተ፡ሐሰትን፤

ወይቤሉክሙ ፡ ናሁ ፡ ያገብኡ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡
እግዚአብሔር፡እምባቢሎን፡ይእዜ፡ፍጡነ፤
ይእዜና ፡ ፍጡነ ፤ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው፤
እንኳን፡ከዚህ፡ያለው፡የቤተ፡እግዚአ
ብሔር፡ዕቃ፡ሊማረክ፡ቀድሞ፡ወደባ
ቢሎን ፡ የወረደውን ፡ የቤተ ፡ እግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመልሱታል ፡ ብለው ፡ የነገሯችሁ ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ፡ አልኋቸው፤

እስመ፡ሐሰተ፡ተነበዩ፡ለክሙ፡

ሐሰት፡ትንቢት፡ተናግረዋልና፤

፲፯፤ ወኢትስምዕዎሙ፡ተቀነዩ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤

እነሱን ፡ አትስሟቸው ፤ ይልቁንስ ፡ ለባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ተገዙ፤

ወተሐይዉ፡አንትሙ፤

ይኸን ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እናንተ፡ከሞት፡ከፄዋዌ፡ትድናላችሁ፤

ለምንት፡ትከውን፡ዛቲ፡ሀገር፡ገዳመ፤

እኔ ፡ የነገርኋችሁን ፡ ቃል ፡ እምቢ ፡ እያላችሁ ፡ የነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ቃል ፡ እየሰማችሁ ፡ እናንተ ፡ ተማርካችሁ ፡ ባቢሎን፡ሂዳችሁ፡በናንተ፡ኃጢአት፡ እናንተን ፡ አጥታ ፡ ጠፍታ ፡ ተፈታ ፡ ይቺ፡ አገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለምን ፡ ምድረ፡በዳ፡ትሆናለች?

፲፰፤ እመሰ፡ነቢያት፡እሙንቱ፡ወቦሙ፡ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ይምጽኡኬ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት፡ ከመ፡ኢይባኡ፡እለ፡ተርፉ፡ንዋያት፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ወቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ወበኢየሩሳሌም፡ባቢሎን፤

እነሱስ ፡ ነቢያተ ፡ ጽድቅ ፡ ከሆኑ ፡ ሀብተ ፡ ትንቢቱም ፡ በነሱ ፡ ካደረባቸውስ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድዔት ፡ ወዳደረባት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡መጥተው፡በእግዚአብሔር፡ ማደሪያ፡በቤተ፡መቅደስ፡በይሁዳው፡ ንጉሥ፡ቤትና፡በኢየሩሳሌም፡የቀሩ፡ ዕቃዎችን፡ተማርከው፡ወደባቢሎን፡ እንዳይገቡ፡ያድርጉ፤

፲፱፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፤

አቸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡ ብሏልና፤

በእንተ፡አዕማድ፤

አዕማድ፡እንዲፈርሱ፤

ወበእንተ፡ባሕር፤

ባሕረ፡ብርትም፡እንድትፈርስ፤

ወበእንተ፡ሜኮኖታት፤

ዐሥሩ ፡ የብረት ፡ ጋኖችም ፡ እን[ዲ] ፈርሱ፤

ወበእንተ፡ንዋያት፡እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ዛቲ፡ሀገር፤

ነሣሣለትና ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ስለቀሩ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠፉ፡ ተና[ገ]ሯልና፤

፳፤ ዘኢነሥአሙ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፡አመ፡አፍለሶ፡ለኢኮንያን፡ወልደ፡ኢዮአቄም፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡እምኢየሩሳሌም፡ባቢሎን፤

የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር፡ የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንን ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ማርኮ፡ወደባቢሎን፡በወሰደው፡ጊዜ፡

ወለኵሉ፡መላእክተ፡ይሁዳ፡ወኢየሩሳሌም፡

የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ አለቆች፡ሁሉ፡ማርኮ፡በወሰደ፡ጊዜ፡ ማርኮ፡ያልወሰዳቸው፡እነዚህ፡ሁሉ፡ እንዲጠፉ፡ተናግሯልና፤

፳፩፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፤



ቢርቀው ፡ ደገመው ፤ አንድም ፡ አምላከ፡ እስራኤል ፡ ለማለት ፡ ደግሞታል ፤ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ፡እግዚአብሔር፤

በእንተ፡ንዋያት፡እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፤

በቤተ፡እግዚአብሔር፡የቀሩ፡የንዋየ፡ቅድሳትን፡ነገር፤

ወቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ወኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌምና፡በይሁዳው፡ንጉሥ፡በሴዴቅያስ፡ቤት፡የቀሩ፡ዕቃዎችን፡ነገር፡ተናግሯልና፤

፳፪፤ ይበውኡ፡ውስተ፡ባቢሎን፤

ምን ፡ ብሎ ? በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ ቤት፡ ናቡከደነፆር ፡ ሳይማርካቸው ፡ የቀሩ ፡ ዕቃዎች ፡ ኋላ ፡ በናቡዛርዳን ፡ ተማርከው፡ወደ፡ባቢሎን፡ይገባሉ፡ብሎ፡ ተናግሯልና፤

ወሀየ ፡ ይሄልዉ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ እዋህዮሙ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፤

ኋላ፡በሰባው፡ዘመን፡በረድዔት፡እስክ ጐበኛቸው ፡ ድረስ ፡ ሰዎችም ፡ ዕቃዎቹም፡በባቢሎን፡ይኖራሉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወተዓርጉ፡ወትሠወጡ፡ውስተ፡ዝ፡ብሔር፤

ወኃሊቆ ፡ ፸ ዓመት ፡ እትቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ያልኋችሁ ፡ ቀን፡ ከደረሰ፡በኋላ፡ግን፤ሰዉም፡ከብቱም፡ ዕቃውም ፡ ከባቢሎን ፡ ወጥታችሁ ፡ ወደጥንት ፡ ሀገራችሁ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡ትመለሳላችሁ።

## ምዕራፍ፡፳፰፤

፩፤ ወእምዝ ፡ ኮነ ፡ በውእቱ ፡ ዓመት ፡ በቀዳሚት፡መንግሥቱ፡ለሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ሆነ፡ ኮነ ፡ ያለውን ፡ ወደፊት ፡ ያመጣዋል ፤ የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠባት ፡ በመጀመሪያዪቱ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ መጽሐፍ፡ ምሥጢር ፡ እንጂ ፡ ዘይቤ ፡ አይጠነቅቅምና ፡ በውእቱ፡ ዓመት ፡ ብሎ፡በቀዳሚት፡መንግሥቱ፡አለ፤

በዓመት፡ራብዒት፡በኀምስ፡ወርኀ፤

ዓመተ፡ኀድገት፡በሆነ፡በአራተኛው፡ ዘመን ፡ ባምስተኛው ፡ ወር፡ ኀምስ ፡ ወርኀ፡ያለው፡አልታወቀም፤አንድም፡ ታውቋል፤ ባምስተኛው ፡ ወር ፡ በነሐሴ፣ ኀምስ፡ ወርኀ ፡ አለው ፡ ነሐሴን፡ ለሚያዝያ ፣ ዘመን፡ የሚለው ጡበት፡በሚያዝያ፡ነውና፤

ይቤለኒ ፡ ሐናንያ ፡ ወልደ ፡ ሐዞር ፡ ሐሳዊ፡ ነቢይ፡ ዘገባዖን ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድመ፡ካህናት፡ወኵሉ፡ሕዝብ፤

ወልደ፡ሐዞር፡ዘገባዖን፡ሐሳዊ፡ነቢይ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የገባዖን ፡ ሰው ፡ የሐዞር ፡ ልጅ ፡ ሐናንያ ፤ አንድም ፡ እንዳለም ፡ ይሆናል፤ወልደ፡ሐዞር፡ሐሳዊ፡ነቢይ፡ በገባዖን ፡ ይላል ፤ የሐዞር ፡ ልጅ ፡ በገባዖን ፡ ሐሰት ፡ የሚያስተምር ፡ ነቢየ፡ ሐሰት ፡ ሐናንያ ፡ በሕዝቡና ፡ በካህናቱ ፡ ፊት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር፡ ቁሞ፤ አንድም ፡ በቤተ ፡ እግዚ

www.ethiopianorthodox.org

አብሔር ፡ ቆሜ ፡ ሳለሁ ፡ በካህናቱና ፡ በሕዝቡ፡ፊት፤

ይቤ፡

ይቤና፡ይቤለኒ፡አንድ፡ወገን፡እንዲህ፡ አለኝ፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፡ አምላከ፡፳ኤል፤

የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

፫፤ ቀጥቀጥክዎ ፡ ለአርዑተ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን፡እስከ፡፪ቱ፡ዓመት፡፡

እስከ ፡ ፪ት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ የባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነፆርን፡ አገዛዝ ፡ አጠፋሁት ፡ አለኝ ፤ አገብእ፡ ማንሻ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ እስከ ፡ ፪ቱ ፡ ዓመት፤

አነ፡አገብእ፡ውስተ፡ዝ፡መካን፡ኵሎ፡ንዋየ፡ ቤተ፡እግዚአብሔር፡ዘነሥአ፡ናቡከደነፆር፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ እምዝንቱ ፡ ብሔር ፡ ወወሰዶ፡ባቢሎን፡

የባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ከዚች ፡ አገር ፡ ማርኮ ፡ ወደባቢሎን፡ የወሰደው ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ወደዚህ፡ አገር ፡ እመልሰዋለሁ ፡ ብሏል፡አለኝ፤

፬፤ ወለኢኮንያን ፡ ወልደ ፡ ኢዮአቄም ፡ ንጉሠ፡ይሁዳ፤

የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄም ፡ ልጅ፡ኢኮንያንንም፤

ወለኵሉ፡ፄዋ፡ይሁዳ፡ዘወሰዶሙ፡ባቢሎን፡ ናቡከደነፆር፡ማርኮ፡ወደባቢሎን፡የወ ሰዳቸው ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮኞችንም ፡ ሁሉ፤

አነ፡እመይጥ፡ውስተ፡ዝ፡ብሔር፡ይቤ፡እግዚ አብሔር፡

ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ እመል ሳለሁ፡ብሏል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡እሰብር፡አርዑቶ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤

የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነፆርን፡ ሥልጣን፡አጠፋበታለሁና፤አንድም፡ ከመ ፡ እስብር ፡ አርዑቶ ፡ ለንጉሠ፡ ባቢሎን ፡ ይላል ፤ የናቡከደነፆርን፡ ሥልጣን ፡ አጠፋበት ፡ ዘንድ ፡ እስከ፡ ሁለት፡ዓመት፡እመልሳለሁ፡ብሏል፤

፭፤ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ ለሐናንያ፡ ነቢይ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ፡ ወበቅድመ፡ካህናት፡እለ፡ይቀውሙ፡ውስተ፡ ዐፀደ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ይቤ፡ኤርምያስ፡ ነቢይ፤

ይቤሎና ፡ ይቤ ፤ ኤርምያስ ፡ ነቢይና፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ በቤተ፡እግዚአብሔር፡አጠገብ፡ባሉ፡ ባምስቱና ፡ በስድስቱ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ፡ መካከል፡ በሚቆሙ ፡ በካህናቱና ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ነቢየ ፡ ጽድቅ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ሐናንያን፡ እንዲህ፡አለው፤

፮፤ አማን ፡ ከመዝ ፡ ይግበር ፡ እግዚአ ብሔር፡

አሁን፡የተናገርከው፡ቃል፡እውነት፡ ነው፤እግዚአብሔርም፡አሁን፡እንደ ተናገርከው ፡ ይበጅ ፡ ያድርግ ፤ አንድም፡ አማን ፡ ይላል ፤ እግዚአ ብሔር፡ አሁን ፡ እንደተናገርከው ፡ ነገር፡በእውነቱ፡ያድርግ፤

ወያቅም፡እግዚአብሔር፡ቃለከ፡ዘተነበይከ፡ ከመ፡ያግብኡ፡ንዋየ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ ዘአፍለሰ፡እምነ፡ባቢሎን፡ነበ፡ዝ፡መካን፤



እሕዛብ፡ማርከው፡የወሰዱት፡የቤተ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደዚህ ፡ ቦታ ፡ እንዲመልሱት ፡ ይመለሳል፡ብለህ፡ትንቢት፡የተናገር ክበትንም ፡ ቃል፡ እግዚአብሔር ፡ ያጽናልህ፡አለው፤

፯፤ወባሕቱ፡ስማዕ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ ዘእነግር ፡ አነ ፡ ውስተ ፡ ዕዝንከ ፡ ወውስተ ፡ ዕዝነ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡

ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ስትሰማኝ ፡ ሕዝቡም፡ሁሉ፡ሲሰሙኝ፡እኔ፡የምነ ግርህን፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስማ፤

፰፤ነቢያትሂ፡እለ፡ኮኑ፡እምቅድሜየ፡ወእ ምቅድሜከ፡

ከኔም፡አስቀድመው፡የነበሩ፡ነቢያት፡ ካንተም ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ነቢያት፤

እምዓለም፡ተነበዩ፡በብዙኅ፡በሐውርት፡

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፤ አንድም፡በብዙ፡አገሮች፡አንድም፡ ለብዙኅ፡በሐውርት፡ይላል፤

ወለነገሥታት፡ዐበይት፡

ለብዙ፡ነገሥታት፡እንደኔ፡ትንቢት፡ የተናገሩ ፤ እንዳንተም ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩ፡ነቢያት፡አሉ፤እለ፡ኮኑ፡እም ቅድሜየ ፤ ወእምቅድሜከ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፤ ለሁለቱም፡ያመጣል፤

በእንተ ፡ አጽባዕት ፡ ወእኩይ ፡ ሕማም ፡ ወብድብድ፡

እንደኔ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍት ፡ ጽኑ ፡ መከራ፡ አባር ፡ ቸነፈር ፡ ይመጣል ፡ ብለው፡የተናገሩ፡ነቢያት፡አሉ፡አለ፤ እለ፡ኮኑ፡እምቅድሜየ፡ላለው፤

፱፤ነቢይ፡ዘተነበየ፡በእንተ፡ሰላም፡

እንዳንተም ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ብሎ ፡ ያስተማረ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ አለ ፡ አለ ? ወእምቅድሜከ፡ላለው፤

ሶበ ፡ ይበጽሕ ፡ ነገሩ ፡ የአምርዎ ፡ ለውእቱ፡ ነቢይ፡ከመ፡በአማን፡ፈነዎ፡እግዚአብሔር፡

ይህንንም፡ትምህርት፡የሚያስረዳው፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ፡ እግዚአ ብሔር፡ብሎ፡የተናገረው፡ትንቢተ፡ ሐሰቱ ፡ በደረሰለት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ነቢየ ፡ ጽድቁ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር፡ብሎ፡ያስተማረው፡ትንቢተ፡ ጽድቁ ፡ በደረሰለት ፡ ጊዜ፡ እግዚአ ብሔር፡በእውነት፡አስተምር፡ብሎ፡ የላከው ፡ ነቢይ ፡ እንደሆነ ፡ ያንጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ያውቁለታል ፤ ያንተንም ፡ ትንቢተ ፡ ሐሰት ፡ የኔንም ፡ ትንቢተ ፡ ጽድቅ፡ጊዜ፡ይግለጠው፡ሲል፡ነው፤

ወነሥአ ፡ ሐናንያ ፡ ነቢይ ፡ ጋገ ፡ በቅድመ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ ፡ እምክሣዱ ፡ ለኤርምያስ ፡ ወቀጥቀጦ፡

ያንጊዜ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ሐናንያ ፡ ቢነደው ፡ ቢቆጨው ፡ ያንገት ፡ ጃንጅሩን፡(የእንጨት፡ቀምበር)፡ማነ ቆውን ፡ ከኤርምያስ፡ አንገት ፡ አን ሥቶ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት፤ አንድም ፡ ሕዝቡ፡እያዩት፡ቀጥቅጦ፡ሰበረው፤

፲፩፤ ወይቤ ፡ ሐናንያ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ከመዝ፡ እቀጠቅጥ፡አርዑቶ፡ለናቡከነደነፆር፡ንጉሠ፡ ባቢሎን፡እምድኅረ፡፪ቱ፡ዓመት፡እምክሣደ፡ ኵሉ፡ሕዝብ፡

ያንጊዜም ፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ሐናንያ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ እንዲመስልለት ፡ ሕዝቡ፡ሁሉ፡እያዩት፡እግዚአብሔር፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ፡ አለ ፤ ይህ ፡ ያንገት ፡ ጃንጅር ፡ (የእንጨት ፡ ቀምበር) ፡ እንደተሰበረ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነፆርን ፡ ጽኑ ፡ አገዛዝ ፡ ከሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አንገት ፡ አጠፋለሁ ፡ ብሏል ፡ አለ ፤

ወአተወ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ ፍኖቶ ፤
ይህንን ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ጥንት ፡ ወደሚሄድበት ፡ ጎዳና ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ፤

፲፪ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ እምድኅረ ፡ ቀጥቀጠ ፡ ሐናንያ ፡ ጋገ ፡ እምላዕለ ፡ ክሣዱ ፡ ለኤርምያስ ፡ ነቢይ ፤
ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ሐናንያ ፡ ከነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ከኤርምያስ ፡ አንገት ፡ ያንገት ፡ ጃንጅሩን ፡ ቀምበሩን ፡ አንሥቶ ፡ ቀጥቅጦ ፡ ከሰበረው ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፤ ተነገረ ፤ አንድም ፡ መጥቶ ፡ ተነገረ ፤

፲፫ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ንግሮ ፡ ለሐናንያ ፤
ሒደህ ፡ ለሐናንያ ፡ ንገረው ፡ ብሎ ፡ መጣ ፤ ተነገረ ፤

ወበሎ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በለው ፤

ጋገ ፡ ዘዕፅ ፡ ቀጥቀጥከ ፤
አንተ ፡ የእንጨቱን ፡ ጃንጅር ፡ (የእንጨቱን ፡ ቀምበር) ፡ ሰበርከው ፤

ወገበርኩ ፡ ህየንቴሁ ፡ ጋገ ፡ ዘሐፂን ፤
እኔ ፡ ግን ፡ አብልጬ ፡ በዚያው ፡ ተክቼ ፡ የብረት ፡ ቀምበር ፡ የብረት ፡ ጃንጅር ፡ ሠራሁ ፤ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ጽኑ ፡ አገዛዝ ፡ አላመጣም ፡ ብዬ ፡ ነበር ፤ እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ ጽኑ ፡ አገዛዝ ፡ አመጣለሁ ፡ በለው ፡ ሲል ፡ ነው ፤

፲፬ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔ[ር] ፡ ፀባዖት ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ ጋገ ፡ ሐፂ[ን] ፡ ወደይኩ ፡ ውስተ ፡ ክሣደ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከ[መ] ፡ ይትቀነዩ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ሊገዙ ፡ ሊገብሩ ፡ ሊቀቅ[ሉ] ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ አገዛዝ ፡ አመጣ[...] ባቸው ፡ አለ ፤ ይህ ፡ እስመ ፡ ዋዌ ፡ ነ[ው] ፡ እስመ ፡ አርኖን ፡ ደወሎሙ ፡ እንዲል ፤

ወአራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወሀብኩ ፡ ሎቱ ፤
ስንኳንስ ፡ ሰዎቹን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያ[...] አራዊትን ፡ ሰጠሁት ፡ አለ ፤ በቁ[...] ለማዳውን ፡ አውሬ ፤ አንድም ፡ ታድ[...] የሚመጣውን ፤ አንድም ፡ አሕዛብ[...] ሁሉ ፡ ግዛ ፡ ንዳ ፡ ብዬ ፡ ሰጠሁት ፤

፲፭ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢ[ይ] ፡ ለሐናንያ ፡ ነቢይ ፤
ያን ፡ ጊዜ ፡ ነቢየ ፡ ጽድቁ ፡ ኤርም[ያስ] ፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ሐናንያን ፡ እንዲ[ህ] ፡ አለው ፤

ስማዕ ፡ ሐናንያ ፤
ሐናንያ ፡ ስማ ፡ አለው ፤

ኢለአከከ ፡ እግዚአብሔር ፤
ለካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላከህ[ም] ፡ አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ አላከህ[ም] ፡ ሐሰትህ ፡ ነው ፤

ወአንተ ፡ አሰፈውኮሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ሐ[...] ለእሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እ[...] ሐሰት ፡ ትንቢት ፡ እየተናገርክ ፡ ሰ[...] ሰላም ፡ እያልክ ፡ ለኒህ ፡ ወገኖች ፡ ተ[...] ደስታውን ፡ ሰጠሃቸው ፤



፲፮ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ሚጠት ፡ አይደረግም ፡ ያለውን ፤ አንተ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይደረጋል ፡ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ ስለአስተማርክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ አዓትተከ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ አጠፋሃለሁ ፡ አለ ፤

ወትመውት ፡ በዝንቱ ፡ ዓመት ፤
አንተስ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ትሞታለህ ፡ አለ ፤ ዝንቱ ፡ ዓመት ፡ ያለው ፡ የተነጋገሩ በትን ፡ ዓመት ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ዘመን ፡ ሳይለወጥ ፡ ትሞታለህ ፡ ሲል ፡ ነው ፤

እስመ ፡ ዓመፃ ፡ ተናገርከ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፤
በእግዚአብሔር ፡ በእውነተኛ ፡ ቃሉ ፡ ላይ ፡ አንተ ፡ ሐሰት ፡ ተናግረህበታልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ሚጠት ፡ አይደረግም ፤ አይሆንም ፡ ያለውን ፡ አንተ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሚጠት ፡ ይደረጋል ፤ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ ሐሰት ፡ ተናግረሃልና ፤ አንድም ፡ ወኃሊቆ ፡ ፸ ፡ ዓመት ፡ እትቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ተናግረሃልና ፤ ይህ ፡ ላዕለ ፡ ገቢር ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሐወጸ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕለ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ይህ ፡ ላዕለ ፡ በባለቤት ፡ የገባ ፡ ነው ፤ ወሐሊቆ ፡ ፸ ዓመት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሐሰት ፡ ተናገረ ፡ ብለሃልና ፤ አንድም ፡ ላዕለን ፡ ታናብብ ፡ እስመ ፡ ዓመፃ ፡ ተናገርከ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፤ ብትጋፋ ፡ ብትጋፋ ፡ ወደላይ ፡ ተጋፍተህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐሰት ፡ ተናገረ ፡ ብለሃልና ፤

፲፯ ወሞተ ፡ ሐናንያ ፡ ነቢይ ፡ በውእቱ ፡ ዓመት ፡ በሳብዕ ፡ ወርኅ ፤
ያንጊዜ ፡ ነቢየ ፡ ሐሰቱ ፡ ሐናንያ ፡ በዚያው ፡ ወራት ፡ ሞተ ፤ ውእቱ ፡ ዓመት ፡ የተነጋገሩበት ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ዘመን ፡ ሳይለወጥ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በሳብዕ ፡ ወርኅ ፡ አለ ፤ ይህን ፡ በተነጋገሩ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ሞተ ፤ ወርኍ ፡ አልታወቀም ፤ አንድም ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በጥቅምት ፡ ሞተ ፡ ሳብዕ ፡ ወርኅ ፡ አለው ፡ ጥቅምትን ፡ ለሚያዝያ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ፤

### ጉባዔ ፤

፩ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘፈነወ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ረበናት ፡ እለ ፡ አፍለስዎሙ ፤
የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ማርከው ፡ ወደወሰዷቸው ፡ ከሞት ፡ ወደቀሩ ፡ ወደመምህራኑ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጽፎ ፡ የላከው ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ጽፎ ፡ ከሞት ፡ ወደቀሩ ፡ መምህራን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የላከው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘፈነወ ፡ ኤርምያስ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ወደፊት ፡ ገልጦ ፡ እስኪያመጣው ፡ ድረስ ፡ ጠብቀው ፤ ጠንቅቀው ፤

ወኀበ ፡ ካህናት ፡ ወሐሳውያነ ፡ ነቢያት ፤
ከኢየሩሳሌም ፡ ወደነቢያተ ፡ ሐሰትና ፡ ወደካህናተ ፡ ጣዖቱ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወነበ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ዘአፍለሰ፡ናቡከደነፆር፡
ንጉሠ፡ባቢሎን፡እምኢየሩሳሌም፡
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፡ከኢየ
ሩሳሌም ፡ ማርኮ ፡ ወደወሰዳቸው ፡
ወደሕዝቡ፡ሁሉ፤

፪፡ እምድኅረ፡ወጽአ፡ኢኮንያን፡ንጉሥ፡
ንጉሡ ፡ ኢኮንያን ፡ ተማርኮ ፡ ከሄደ ፡
በኋላ፤

ወነጋሥያት፡
እናቶቹ፡አክስቶቹ፡እኅቶቹ፡ሚስቶቹ፤

ወሕፅዋን፡
ባለሚሎቹ፤

ወመላእክተ፡ይሁዳ፡ወኢየሩሳሌም፡
የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ አለቆች ፡
ተማርከው፡ከሄዱ፡በኋላ፤

ወኵሉ፡አግዓዚ፡
ጌቶች፤

ወሙቁሐን፡
ባሮቹ ፤ አንድም ፡ ወኵሉ ፡ አግዓዚ ፡
ያልታሠሩ ፡ በዓይን ፡ ቁራኛ ፡
የሚጠበቁ ፡ ወሙቁሐን ፡ በእግር ፡
ብረት፡በሰንሰለት፡የታሠሩ፤

ወኪነት፡እምኢየሩሳሌም፡
ፈላስፎችም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተማ
ርከው ፡ ከንጉሡ ፡ ከኢኮንያን ፡ ጋራ ፡
ተማርከው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ናቡከደ
ነፆር፡ ማርኮ ፡ ወደወሰዳቸው ፡ ወደ
እስራኤል፡የላከው፤

፫፡ በእደ፡ኤልሳፅ፡ወልደ፡ሳፋን፡
በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በኤልሳፅ ፡ ቃል ፡
የላከው ፡ ይህ ፡ ኤልሳፅ ፡ ነቢዩ ፡
አይደለም፤ ሌላ ፡ ኤልሳፅ ፡ ነው፤ ስም ፡
ለስም፡ይጋጠማልና፤አንድም፡በእደ፡
አሲአሳህ ፡ ወልደ ፡ ሳፋን ፡ ይላል፤
በሳፋን፡ልጅ፡በአሲአሳህ፡ቃል፡አለ፡
ኤልሳፅን፡አሲአሳህ፡አለው፤ለአንድ፡
ሰው፡ሁለት፡ስም፡አለውና፡

ወገማርዩ፡ወልደ፡ኬልቅዩ፡
በኬልቅዩ ፡ ልጅ ፡ በገማርዩም ፡ ቃል
የተላከ፤

እለ፡ፈነወ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሡ፡ይሁዳ፡ኀበ፡
ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወደባ
ቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ወደናቡከደነፆር፤
ግብር ፡ አሲዞ ፡ በላካቸው ፡ በነሀ፡
በሁለቱ፡ሰዎች፡ቃል፡የላከው፤

፬፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እግዚአ ፡ ኃያላን ፡ አምላከ ፡
እሥራኤል፡
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ የኃያላን ፡ የመላ
እክት ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡
አለ፡ብሎ፡የላከው፤አንድም፡እግዚአ፡
ኃያላን ፡ ብሎ ፡ አምላከ ፡ እሥራኤል፡
አለ ፤ እስራኤልን ፡ ፈጥሮ ፡ የማይገ
ዛቸው፡መላእክትን፡ገዝቶ፡የማይፈጥ
ራቸው፡ሆኖ፡አይደለም፤መላእክትን፡
ፈጥሮ ፡ ይገዛቸዋል ፤ እስራኤልንም፡
ፈጥሮ፡ይገዛቸዋልና፡ፈጣሪነቱንም፡
ገዥነቱንም ፡ ሲያጠይቅ ፡ እንዲህ፡
አለ፤

ለኵሉ፡ፈላስያን፡እለ፡አፍለስኩ፡እምኢየሩ
ሳሌም፡ውስተ፡ባቢሎን፡
ከኢየሩሳሌም ፡ አስማርኬ ፡ ወደባ
ቢሎን ፡ ለሰደድኳቸው ፤ ተማርከው፡
መጻተኛ ፡ ሁነው ፡ በባቢሎን ፡
ለሚኖሩ፡ ለእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

፭፡ ሕንፁአ፡አብያተ፡ወንበሩ፡



የምሥራች ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡
አስቀድሞ ፡ አትወጡምና ፡ ቤት ፡
ሠርታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ብሏል ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ብሎ፤ ዘፈነወ ኤርምያስ ፡
ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ መጽሐፍ፤
ዘፈነወ ፡ ኤርምያስ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡
ውስጥ፡ለውስጥ፡ሲያጓድድ፡መጥቶ፡
አሁን ፡ ሕንፁአ ፡ አብያተ ፡ ወንበሩ ፡
ብሎ፡ገለጠው፤

ወትክሉ፡አቅማሐተ፡ወብልዑ፡ፍሬሁ፡
ነቅታችሁ፡ተግታችሁ፡አትክልቱን፡
ትከሉ፤አርማችሁ፡ኰትኵታችሁም፡
አፍርቶላችሁ፡ፍሬውን፡ተመገቡ፤

፮፡ ወንሥኡ፡ብእሲተ፡ወለዱ፡ውሉደ፡
ወአዋልደ፡
ሚስትም፡አግብታችሁ፡ሴት፡ልጅ፡
ወንድ፡ልጅ፡ውለዱ፤

ወንሥኡ፡አንስተ፡ለውሉድክሙ፡ወሀቡ፡
አዋልዲክሙ፡ለዕደው፡
ከአሕዛብ ፡ ሴቶች ፡ ለወንዶች ፡
ልጆቻችሁ፡አጋቡዋቸው፤የናንተን፡
ሴቶች፡ልጆች፡ለአሕዛብ፡ወንዶች፡
ልጆች፡ዳሩላቸው፤

ወይለዱ፡ደቂቀ፡ወአዋልደ፡
የናንተ፡ወንዶች፡ልጆች፡የአሕዛብን፡
ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አግብተው ፡ ወን
ዶችና፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይውለዱ፤ የአ
ሕዛብም፡ወንዶች፡ልጆች፡የናንተን፡
ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አግብተው ፡ ወን
ዶችና፡ሴቶች፡ልጆች፡ይውለዱ፤

ወብዝኁ፡በህየ፡ወኢትውኅዱ፡
በባቢሎን ፡ አገር ፡ ሳላችሁ ፡ ተጋብ
ታችሁ፡ተዋልዳችሁ፡ተባዙ፡እንጂ፡
አትነሱ፡ብሏል፡እግዚአብሔር፡አለ፤
ምነዋ፡ከአሕዛብማ፡አትጋቡዋቸው፤
ገንዘባቸውንም ፡ አትንኩ ፡ ብሎ ፡
የለም፡ ቢሉ ፤ አምነው ፡ ተጋብተው ፡
የኖሩ፡አሕዛብ፡አሉና፡ስለዚህ፡ነው፤
አንድም ፡ ከወገኖቻችሁም ፡ ቢሆን ፡
በሁለት ፡ ዓመት ፡ ልንወጣ ፡ ምን ፡
ሚስት ፡ ያጋባናል ፡ ልጅ ፡ ያስወል
ደናል፡ አትበሉ፤ ሚስት ፡ አግብ
ታችሁ፡ ልጅ ፡ ወልዳችሁ ፡ ተባዝ
ታችሁ፡ኑሩ፡ሲል፡ነው፤ምሥጢሩ፡
ግን ፡ ቤተ ፡ እስራኤል፡ ኋላ ፡ በሰባ ፡
ዘመን፡ስትወጣ፡እንደወጓት፡ወግታ፤
እንደዘረፏት ፡ ዘርፋ ፡ የምትወጣ ፡
ናትና፡በዝታ፡በርትታ፡እንድትቆይ፡
በባሕርይ፡ጥበቡ፡የሠራው፡ነው፤

፯፡ ኅሡ ፡ ሰላማ ፡ ለሀገር ፡ ኀበ ፡ አፍለስ
ኩክሙ፡ህየ፡
እናንተን፡አስማርኬ፡ሰድጄ፡የምትኖ
ሩባትን ፡ አገር ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
ፈልጉላት፤

ወጸልዩ፡በእንቲአሃ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
ወደፈጣሪያችሁ ፡ ወደእግዚአብሔ
ርም ፡ ይህችን ፡ አገር ፡ በረድዔት ፡
ጠብቃት፡እያላችሁ፡ጸልዩላት፤ሐተታ፡
ምንም፡የባዕድ፡ሀገር፡ቢሆን፡ለሚኖ
ሩበት፡አገር፡መጸለይ፡ይገባል፤አገሩ፡
በረድዔተ፡እግዚአብሔር፡ከተጠበቀ፡
ሰውዬውም፡ከሀገሩ፡ጋራ፡በረድዔተ፡
እግዚአብሔር ፡ ተጠብቆ ፡ ይኖራልና፡
ጎረቤትህ ፡ ደኅና ፡ ይዋል፤ አንተም ፡
በደኅና፡እንድትውል፡እንዲሉ፤ኅሡ፡
ሰላማ፡ለሀገር፡ባለው፡ለብሔር፡ይላል፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡በሰላመ፡ዚአሃ፡ይከውን፡ሰላምክሙ፤
ለሀገሪቱ፡በሚደረገው፡ተድላ፡ደስታ፡
ለናንተም፡ተድላ፡ደስታ፡ይደረግላች
ኋልና፤ አንድም ፡ አገባቡን ፡ ታግሦ ፡
ለሀገሪቱ፡የሚደረገው፡ተድላ፡ደስታ፡
ለናንተ፡ነውና፤ለናንተ፡ስለሆነ፤

፰፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአ፡ኃያላን፡አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ የኃያላን ፡
መላእክት ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡ብሏልና፤

ኢያስሕቱክሙ፡ነቢያቲክሙ፡እለ፡ውስቴ
ትክሙ፤
በናንተ፡ውስጥ፡ያሉ፡ነቢያተ፡ሐሰት፤
አንድም ፡ እለ ፡ ኀቤክሙ ፡ ይላል፤
በናንተ፡ዘንድ፡ያሉ፡ነቢያተ፡ሐሰት፤
አንድም ፡ እለ ፡ እምኔክሙ ፡ ይላል፤
ከናንተ፡ወገን፡የተወለዱ፡ነቢያተ፡
ሐሰት፡አያስቷችሁ፤

ወኢያስሕቱክሙ፡መሠግላኒክሙ፤
ጧት፡ማታ፡እየሄዳችሁ፡የምታስጠነ
ቍሏቸው፤ አንድም ፡ ጧት ፡ ማታ ፡
ወደናንተ ፡ እየመጡ ፡ የሚጠነቍሉ
ላችሁ ፡ ጠንቋዮቻችሁም ፡ አያስ
ቷችሁ፤

ወኢትስምዕዎሙ፡ለሐላምያኒክሙ፡እለ፡
የሐልሙ፡ለክሙ፤
ጧት፡ማታም፡ለናንተ፡በጎ፡ሕልም፡
አለምንላችሁ ፡ የሚሉዋችሁንም ፡
ሰዎች ፤ ኢትስምዕዎሙ ፡ አትስ
ሟቸው፤ መስማትማ ፡ ጆሮ ፡ መብ
ረቅስ፡ትሰማ፡የለምን፡ብሎ፡ኢትእ
መንዎሙ፡ሲል፡ነው፤

፱፤ እስመ ፡ ሐሰተ ፡ ይትኔበዩ ፡ ለክሙ ፡
በስምየ ፡ ወኢለአክዎሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ኢለአክዎሙ ፡ ባለው ፡ ወኢፈነው
ክዎሙ፡ይላል፤እኔ፡ሳላድርባቸው፡
እግዚአብሔር፡አድሮብናል፡እያሉ፤
አንድም፡በስሜ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር ፡ እያሉ ፡ እኔም ፡ ሂዱ ፡
አስተምሩ ፡ ሳልላቸው ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ልኮናል፡እያሉ፡ወደናንተ፡
መጥተው፡ሐሰት፡ትንቢትን፡ያስተ
ምራሉና፤

፲፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
አመ፡ፈጸምክሙ፡ሰብዓ፡ዓመተ፡ውስተ፡
ባቢሎን፤
ይህን ፡ ባለው ፡ አመ ፡ ኃልቀ ፡ ሰባ ፡
ዓመት ፡ ውስተ ፡ ባቢሎን ፡ ይላል ፤
በባቢሎን፡ሳላችሁ፡ሰባው፡ዘመን፡
በተፈጸመ፡ጊዜ፤አንድም፡በባቢሎን፡
ኑራችሁ ፡ ሰባውን ፡ ዘመን ፡ በፈጸማ
ችሁት፡ጊዜ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡
ብሏልና፤

እሔውጸክሙ፤
እግዚአብሔር፡በረድዔት፡እጐበኛች
ኋለሁ፡ብሏልና፤

ወአቀውም፡ኀቤክሙ፡ቃልየ፡ዘሠናይ፡ከመ፡
አግብእክሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ብሔርክሙ፤
ቀድሞ ፡ ተወልዳችሁ ፡ ወደአደጋች
ሁበት ፡ ወደአገራችሁ ፡ እንድመል
ሳችሁ፤ኀቤክሙ፡ለክሙ፡ሲል፡ነው፤
ወኃሊቆ፡ሰብዓ፡ዓመት፡እትቤቀሎ፤
ብዬ ፡ ለናንተ ፡ የተናገርኩላችሁ ፡
ቃሌንም፡አጸናላችኋለሁና፤አንድም፡
ኀቤክሙ፡እንዳለ፡ይሆናል፤ወኃሊቆ፡
ሰብዓ ፡ ዓመት ፡ እትቤቀሎ ፡ ብዬ ፡
የተናገርኩት ፡ ቃሌንም ፡ በናንተ ፡



ዘንድ፡አጸናዋለሁ፤

ወአገብአክሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ብሔርክሙ፤
ቀድሞ ፡ ተወልዳችሁ ፡ ወዳደጋች
ሁበት ፡ አገራችሁ ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡
በኋላ፡ እመልሳችኋለሁ ፤ ወአገብ
አክሙ ፡ ባለው ፡ ወእሠውጠክሙ ፡
ይላል፡እንደዚሁ፡ያስተረጕማል፤

፲፩፤ እስመ፡አነ፡አአምር፡ሕሊና፡ዘአነ፡
እሔሊ፡ላዕሌክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከሰባ፡ዘመን፡በኋላስ፡እኔ፡ለናንተ፡
ያሰብኩላችሁን፡ሐሳብ፡እኔ፡አውቀ
ዋለሁ፡ብሏልና፡እግዚአብሔር፤

ሕሊና፡ሰላም፤
እናንተ፡አታውቁትም፡እንጂ፡እኔስ፡
ፍቅር፡አንድነትን፡ላደርግላችሁ፡አስ
ቤያለሁ፤

ወአኮ፡እኩይ፤
ያሰብኩላችሁም፡ክፉ፡ነገር፡ላደርግ
ባችሁ፡አይደለም፤አንድም፡ይኸ፡ወ
ዘ፡ነው ፤ ይህም ፡ ያሰብኩላችሁ ፡
ሐሳብ፡ ክፉ ፡ ሐሳብ ፡ ያይደለ ፡ በጎ ፡
አሳብ፡ነው፤

ከመ፡አሀብክሙ፡ዘንተ፤
ሕሊና ፡ ሰላም ፡ ያለውን ፡ አመጣ ፤
ይህም፡ ያሰብኩላችሁ ፡ አሳብ ፤ አገብ
አክሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ብሔርክሙ፡
ያልኩትን፡እሰጣችሁ፡ዘንድ፡ነው፤

፲፪፤እምድኅረዝ፡ትውክልት፡ትጼውዑኒ፡
ወተሐውሩ፤
ወኃሊቆ፡ሰብዓ፡ዓመት፡እትቤቀሎ፡
ለንጉሠ፡ባቢሎን፡ያልኩትን፡ተስፋ፡
አምናችሁ፡ከኖራችሁ፡በኋላ፡ጊዜው፡
ደርሶላችሁ፤ ሚጠቱ ፡ ተደርጎላችሁ ፡
ስሜን፡ እየጠራችሁ ፡ ትኖራላችሁ ፤
ሖረን ፡ ኖረ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለምንት ፡
የሐውር ፡ ወልደ ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡
ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ዳዕሙ ፡ እለ ፡
የሐውሩ፡ ያመስጡ ፡ ባቲ ፡ እንዲል ፤
አንድም ፡ ተሐውሩ ፡ እንዳለም ፡
ይሆናል ፤ ስሜን ፡ ልትጠሩ ፡ ጧት ፡
ማታ፡ወደቤተ፡እግዚአብሔር፡ትሄዳ
ላችሁ፤

ወትጼልዩ፡ኀቤየ፡ወእሰምዐክሙ፤
ያንጊዜም፡በነቂሐ፡ሕሊና፡በተጊሐ፡
ልቡና ፡ ሁናችሁ ፡ ወደኔ ፡ ትለምና
ላችሁ፤እኔም፡ልመናችሁን፡እሰማች
ኋለሁ፤

፲፫፤ ተኃሥሡኒ፡ወትረክቡኒ፤
ለምናችሁም ፡ ታገኙኛላችሁ ፡ አለ ፤
ለምኖ ፡ ማጣት ፡ አለና ፤ አንድም ፡
ተኃሥሡኒ ፡ ወእትረከበክሙ ፡
እምከመ ፡ ኀሠሥክሙኒ ፡ በኵሉ ፡
ልብክሙ ፤ ከቂም ፡ ከተንኮል ፡
ከኃጢአት ፡ ከጣዖት ፡ ተለይታችሁ ፡
በፍጹም ፡ ልቡናችሁ ፡ ከለመናች
ሁኝስ፡የምትፈልጉኝ፡እናንተ፡ብቻ፡
አይደላችሁም፤እኔም፡ፈልጌ፡እገናኛ
ችኋለሁ ፡ አለ ፤ መገናኘት ፡ የጋራ ፡
ከሆነ፡ ብሎ ፡ አስተርእየክሙ ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር፡ማንሻ፡ነው፤አንድም፡
ከቂም ፡ ከተንኮል ፡ ከኃጢአት ፡
ከጣዖት ፡ ተለይታችሁ ፡ በፍጹም ፡
ልቡናችሁ፡ከለመናችሁኝስ፤

፲፬፤ አስተርእየክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እኔ፡ፈልጌ፡እገለጥላችኋለሁ፡አለ፡እግ
ዚአብሔር፤እትራከበክሙ፡ያለውን፡

www.ethiopianorthodox.org

ደገመው፤
አንድም፡አስተሠርየክሙ፡ይላል፤በእ
ውነትስ ፡ ከለመናችሁኝ ፡ ኃጢአታ
ችሁን ፡ አስተሠርይላችኋለሁ ፡ አለ ፡
እግዚአብሔር ፤ መማረካቸው ፡ ኃጢ
አት ፡ ቢሠሩ ፡ ጣዖት ፡ ቢያመልኩ፡
ነውና፤

ወእመይጥ፡ፄዋክሙ፤
ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡
በኋላ፡ምርኳችሁን፡እመልሳለሁ፤

ወአስተጋብአክሙ፡እምኵሉ፡አሕዛብ፤
ትገዙላቸው ፡ ከነበረ ፡ ከአሕዛብም ፡
ለይቼ፡እሰበስባችኋለሁ፤

ወእምኵሉ፡በሐውርት፡ኀበ፡ዘረውኩክሙ፡
ህየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እናንተን፡አስማርኬ፡በትኖችሁ፡ትገ
ዙባቸው ፡ ከነበሩ ፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡
አውጥቼ ፡ በሀገራችሁ ፡ እሰበስባች
ኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአገብአክሙ፡ኀበ፡መካን፡እምኀበ፡አፍለስ
ኩክሙ፡እምህየ፤
እምህየና ፡ እምኀበ ፡ አፍለስኩክሙ ፡
አንድ ፡ ወገን ፤ እናንተን ፡ አስማርኬ ፡
ሰድጃችሁ፡ስትገዙ፡ከነበራችሁበት፡
አገር ፡ አውጥቼ ፡ ወደጥንተ ፡
ሀገራችሁ፡እመልሳችኋለሁ፡አለ፤አገ
ብአክሙ፡አገብአክሙ፡አገብአክሙ፡
ብሎ፡ሦስት፡ጊዜ፡መላልሶ፡ተናገረው፤
ፄዋዌም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሚጠትም ፡
ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፤ ፄዋዌ ፡ ሦስት ፡
ጊዜም፡ቀድሞ፡በሆሴዕ፡ወልደ፡ዔላ፡
አሥሩን፡ነገድ፡ስልምናሶር፤ኋላም፡
በኢኮንያን፡ሁለቱን፡ነገድ፡ናቡከደ
ነፆር፤ሦስተኛ፡በሴዴቅያስ፡ናቡከደ
ነፆር፡ማርኳቸዋል፤ሚጠት፡ሦስት፡
ጊዜ፡ነው፡አለ፤መጀመሪያ፡በኤር
ምያስ ፤ ሁለተኛ ፡ በዘሩባቤል ፡
ሦስተኛ፡ በካልዕ ፡ ዕዝራ ፡ ነውና ፡
ሦስት፡ጊዜ፡መላልሶ፡ተናገረው፤

፲፭፤ እስመ፡ትብሉ፡አቀመ፡ለነ፡እግዚእ
ብሔር፡ነቢያተ፡በባቢሎን፤
እግዚአብሔር፡የሚመክሩን፡የሚያስ
ተምሩን፡ነቢያትን፡በባቢሎን፡አስነ
ሣልን፡ብላችኋልና፤አንድም፡እስከ፡
ትብሉ፡ይላል፡እግዚአብሔር፤የሚመ
ክሩን ፡ የሚያስተምሩን ፡ ነቢያትን ፡
በባቢሎን ፡ አስነሣልን ፡ እስክትሉ ፡
ድረስ፡ደርሳችሁ፤ተኀሥሡኒ፡ወትረ
ክቡኒ፡አገብአክሙ፡ላለው፡ስጥ፤
እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

፲፮፤ ለንጉሥ፡ዘይነብር፡ዲበ፡መንበረ፡
ዳዊት፤
በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ ለነገሠ፡
ላንዱም፡ላንዱ፡ንጉሥ፤

ወላዕለ፡ሕዝብ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ዛ፡
ሀገር፤
በዚችም ፡ አገር ፡ ለሚኖሩ ፡ ወገኖች ፡
ሁሉ፤

ወለአኃዊክሙ፡እለ፡ኢመጽኡ፡ምስሌክሙ፡
ውስተ፡ፍልሰት፤
ከናንተ፡ጋራ፤አንድም፡እንደናንተ፡
ወደምርኮ፡ተማርከው፡ባልሄዱ፡ወን
ድሞቻችሁም፤

፲፯፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
እግዚአ፡ኃያላን፤



ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔርና ፡
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ፡ኃያላን፡አንድ፡
ወገን ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ቢርቀው ፡
ደግሞታል ፤ አንድም ፡ ናሁ ፡ አነ ፡
እፌኑ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለማለት ፡ ደግ
ሞታል፤

ናሁ፡አነ፡እፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡መጥባሕተ፡
ወረኃበ፡ወብድብደ፤
በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጦር ፡ መቅሠፍትን ፡
ቀጠናን፡አባር፡ቸነፈርን፡አመጣባቸ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወእሬስዮሙ፡ከመ፡በለሰ፡ሱአሪም፡ዘኢይ
ትበላዕ፡እምእከዩ፤
ከመምረሩ፡ከመኅምረሩ፡የተነሣ፡እን
ደማይበላ ፡ እንደቃሪያ ፡ በለስ ፤
አንድም፡በእንተ፡እከዩ፡ይላል፤ስለመ
ምረሩ ፡ ስለመጐምዘዙ ፡ ስለመኅ
ምረሩ፤ አንድም ፡ በእከዩ ፡ ይላል ፤
በመምረሩ ፡ በመጐምዘዙ ፡ (በመኅ
ምረሩ)፡እንደማይበላ፡ቃሪያ፡በለስ፡
አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፤

፲፰፤ ወእዴግኖሙ ፡ ድኅሬሆሙ ፡
በኵናት፡ወበረኃብ፡ወበብድብድ፤
እኔም ፡ በአሕዛብ ፡ አድሬ ፡ በጦር ፡
በቀጠና ፡ በአባር ፡ በቸነፈር ፡ እየተከ
ተልኩ፡አጠፋቸዋለሁ፤

፲፱፤ ወእሜጥዎሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
ነገሥተ፡ ምድር ፡ ካልዓን ፡ ለመሐላ ፡
ወለሙስና ፡ ወለተፋጽዮ ፡ ወለጽዕለት ፡
ለኵሉ፡ አሕዛብ ፡ ኀበ ፡ ዘረውክዎሙ ፡ ህየ ፤
በእንተ ፡ ዘኢሰምዑ ፡ ቃልየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
በነቢያት ፡ አድሬ ፡ የነገርኳቸውን ፡
ቃሌን፡ስላልሰሙኝ፡ተማርከው፡በሔ
ዱባቸው፡በነገሥታቱ፡አገሮች፡ሁሉ፡
ለማረኳቸው፡አሕዛብ፡ስድብ፡ሊሆኑ፡
ለፍጹም ፡ ጥፋት ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ ፡ ፈነውኩ ፡ ኀቤሆሙ ፡ አግብርትየ ፡
ነቢያተ፡በጽባሕ፤
አገልጋዮቼ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡
ምከሩ፡ አስተምሩ ፡ ብዬ ፡ ፈጥኜ ፡
ወደነሱ፡ልኬያቸው፡ነበርና፡ምንም፡
ብልካቸው፡ቃሌን፡ስላልሰሙኝ፤

ወፈነውኩ ፡ ወኢሰምዑኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ከዚህም፡ቀድሞ፡ነቢያት፡ካህናትን፡
ምከሩ ፡ አስተምሩ ፡ ብዬ ፡ ሰደድሁ ፤
እነሱ ፡ ግን ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡
አድሬ፡የነገርኳቸውን፡ቃሌን፡አልሰ
ሙኝም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፤ አንትሙኒ ፡ ስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ ፈላስያን ፡ እለ ፡ ፈነው
ኩክሙ፡እምኢየሩሳሌም፡ውስተ፡ባቢሎን፤
ከኢየሩሳሌም ፡ አስማርኬ ፡ ወደባ
ቢሎን፡የሰደድኋችሁ፤ተማርካችሁ፡
በባቢሎን፡የምትኖሩ፡እናንተ፡ስንኳ፡
ጥቂት፡ከነሱ፡ብትሻሉ፡እስኪ፡የእግ
ዚአብሔርን፡ቃል፡ስሙኝ፤

፳፩፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
እግዚአ፡ ኃያላን ፡ አምላከ ፡ ፳ኤል ፡ ላዕለ ፡
አኪያ፡ወልደ፡ቆልዩ፡ወላዕለ፡ሴዴቅያስ፡
ወልደ ፡ ማሴው ፡ እለ ፡ ይትኔበዩ ፡ ለክሙ ፡
በስምየ፡በዓመፃ፤
አኪያ ፡ ወልደ ፡ ቆልዩ ፡ ባለው ፡
አኪያብ፡ ወልደ፡ቆልያ፡ይላል፤የእስ
ራኤል፡ፈጣሪ፡የኃያላን፡የመላእክት፡
ገዥ፡እግዚአብሔር፡ከመዝ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡እያሉ፡ስሜን፡እየጠሩ፡
በሐሰት፡በሚያስተምሯችሁ፡በማሴው፡

www.ethiopianorthodox.org

ልጅ ፡ በሴዴቅያስና፡ በቆልያ ፡ ልጅ ፡
በአኪያ፡በመዓት፡አለሁባቸው፡አለ፤

ወናሁ፡አነ፡እሜጥዎሙ፡ውስተ፡እደ፡ናቡከ
ደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ እነሱን ፡
በባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡
እጅ፡አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፤

ወይቀትሎሙ፡በቅድመ፡አዕይንቲከሙ፤
ናቡከደነፆርም፡በፊታችሁ፤አንድም፡
እናንተ፡እያያችሁ፡እነሱን፡ያስገድላ
ቸዋል፤

፳፪፤ ወይነሥኡ ፡ እምኔሆሙ ፡ መርገመ ፡
በኵሉ፡ፈላስያነ፡ይሁዳ፡ዘውስተ፡ባቢሎን፤
ከይሁዳ ፡ ተማርከው ፡ ሔደው ፡
በባቢሎን ፡ በሚኖሩ ፡ ምርኮኞች ፡
ሁሉ፡ዘንድ፡ከነሥ፡የተነሣ፤አንድም፡
እምድኅሬሆሙ፡ይላል፤እነሱ፡ከጠፉ፡
በኋላ ፤ አንድም ፡ እምድኅሬሆሙ ፡
ከነሱ ፡ ቀጥሎ ፡ እኩሌቶች ፡ ከእኩ
ሌቶች ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ ስድብን ፡
መርገምን፡ገንዘብ፡ያደርጉባቸዋል፤
ይነሥኡ ፡ እምኔሆሙ ፡ ያለውን ፡
ወደፊት ፡ ወይብሉ ፡ ይረሲከ ፡ ብሎ ፡
ያመጣዋል፤

ወይብሉ ፡ ይረሲከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡
ረሰዮሙ ፡ ለአኪያ ፡ ወለሴዴቅያ ፡ እለ ፡
ጠገኖሙ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡በእሳት፤
እስራኤል፡ፀብ፡ክርክር፡ባነሡ፡ጊዜ፡
የባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
በእሳት ፡ አቃጥሎ ፡ እንደገደላቸው ፡
እንደ፡ሴዴቅያና፡እንደ፡አኪያ፡እግዚ
አብሔር ፡ እንደነዚያ ፡ ያድርግህ ፡
ብለው፡ይማማሉባቸዋል፤

፳፫፤እስመ፡ገብሩ፡እኩየ፡ላዕለ፡፳ኤል፤
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የማይገባ ፡ ሥራ፡
ሠርተዋልና፤

ወዘመዉ፡በአንስትያ፡ቢፆሙ፤
በባልንጀራቸው ፡ በኢዮአቄም ፡
ሚስት ፡ ሰስነዋልና ፤ ገብሩ ፡ እኩየ፡
ያለውን ፡ አመጣ ፤ ሐተታ ፡ ምንዋ፡
እኒህንማ ፡ እስራኤል ፡ በድንጋይ፡
ወግረው ፡ የገደሏቸው ፡ አይደለም ?
ስለምን ፡ እለ ፡ ጠገኖሙ ፡ ንጉሥ፡
በእሳት፡አለ፡ቢሉ፡ሌሎች፡ረበናት፡
ናቸው፤አንድም፡እነዚያው፡ናቸው፤
አይሁድ፡እንደሀገራቸው፡ሥርዓት፡
በድንጋይ ፡ ወግረው ፡ ከገደሏቸው፡
በኋላ፡ናቡከደነፆር፡በሀገሩ፡ሥርዓት፡
በእሳት ፡ አቃጥሏቸዋልና ፡ እንዲህ፡
አለ፤

ወነገሩ ፡ ነገረ ፡ ሐሰት ፡ በስምየ ፡ ዘኢአዘዝ
ክዎሙ፤
እኔ፡ምክሩ፡አስተምሩ፡ብዬ፡ያላዘዝ
ኳቸው፡ያላከኳቸው፡ሁለቱ፡ረበናት፡
እግዚአብሔር ፡ ልኮናል ፡ አዞናል ፡
ብለው፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እያሉ፡በስሜ፡ሐሰት፡ነገርን፡ተናገሩ፤

ወአነ፡እዛለፎሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እኔም ፡ ሐሰት ፡ ነገር ፡ በማስተማ
ራቸው፡ በመምከራቸው ፡ እዘልፋቸ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፬፤ ወትብሎ፡ለሳምያ፡ኤልማዊ፤
ኤሎማዊ ፡ ኤልማዊ ፡ ይላል ፤ ኤሎም፡
ስመ፡ሀገር፡ነው፤አንድም፡ስመ፡ሰብእ፡
ነው፤የኤሎማ፡ሰው፡ሳምያን፡ከኤሎም፡
ወገን ፡ የተወለደ ፡ ሳምያን ፤ አንድም፡
ለሳምያ ፡ ሐላሚ ፡ ይላል ፤ አለምሁ፡
አለም



አድርገህ ፡ ተናገረው ፤ አንድም ፡
አለምሁ፡አለምሁ፡ለሚል፡ለሳምያ፡
ነገርህን፡አውጥተህ፡ንገረው፤

፳፭፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ፀባዖት፡አምላከ፡፳ኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

እስመ፡አንተ፡ፈነውከ፡መጻሕፍተ፡በስምከ፡
ኀበ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ዘውስተ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ ወደሚኖሩ ፡ ወገኖች ፡
ሁሉ ፡ ነቢዩ ፡ ሳምያ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡
ብላችሁ ፡ ንገሩ ፡ ብለህ ፤ አንድም ፡
በስምየ፡ይላል፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ብለህ ፡ መጻሕፍትን ፡ ልከ
ሃልና፤

ወኀበ፡ሶፎንያስ፡ወልደ፡ማሴው፡ካህን፤
የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ወደ
ሚሆን፡ወደማሴው፡ልጅ፡ወደሶፎን
ያስም፡ልከሃልና፤

ወኀበ፡ኵሎሙ፡ካህናት፤
በኢየሩሳሌም፡ወደሚኖሩም፡ካህናት፡
ልከሃልና፤

፳፮፤ ወትቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሤመከ ፡
ካህነ፡ህየንተ፡ዮዳሄ፡ካህን፡ሊቀ፡በውስተ፡
ቤተ፡እግዚአብሔር፡ለኵሉ፡ሰብእ፡እለ፡
ይትኔበዩ፤
ከልቡናቸው፡አንቅተው፡ከአፋቸው፡
አውጥተው ፡ ሐሰት ፡ ትንቢት ፡
የሚናገሩ ፡ ሰዎችን ፡ ሁሉ ፡ ልትሠ
ራቸው ፡ ልትቀጣቸው ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡
በቀድሞው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በዮዳሄ ፡
ፈንታ፡ተክቶ፡አንተን፡ሊቀ፡ካህናት፡
አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሾሞሃል ፡
ብለህ፡

ወለኵሉ፡ሰብእ፡ዘይትቄረድ፤
ከልቡናው፡አንቅቶ፡የሆነውን፡ያልሆ
ነውን፡ነገር፡የሚለፈልፈውን፡ሰው፤

ከመ፡ትዕፅዎ፤
ልታሥረው፡ልታግዘው፤

ወታስጥሞ፡ውስተ፡ውኂዝ፤
ይህም ፡ ባይሆን ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡
አሥረህ፡በፈሳሽ፡ውሀ፡ጥለህ፡ልታሠ
ጥመው ፡ በዮዳሄ ፡ ተክቶ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ሾሞሃል፡ብለህ፡ልከሃልና፤

፳፯፤ ወይእዜኒ ፡ ለምንት ፡ ዘኢገሠጽኮ ፡
ለኤርምያስ፡ዘእምአናቶት፡ዘተነበየ፡ለከሙ፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፤ ብሎ ፡
ትንቢት ፡ የተናገረላችሁ ፡ የአናቶት ፡
ሰው፡ኤርምያስን፡ለምን፡ዛሬ፡አልሠ
ራኸው ፤ አልቀጣኸው ፡ ብለህ ፡
ልከሃልና፤

፳፰፤ እኮኑ፡በበይነ፡ዝንቱ፡ለአከ፡ኀቤነ፡
ውስተ፡ባቢሎን፤
አንተ፡ባትሠራው፡ባትቀጣው፡እሱ፡
በሕግ ፡ በሥርአት ፡ ጸንቶ ፡ ባይኖር ፡
ቢጠግብ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ በባቢሎን ፡
ወደምንኖር ፡ ወደኛ ፡ የላከ ፡ አይደ
ለምን፡ብለህ፡ልከሃልና፤

ወይቤ፡ሕንፁ፡አብያተ፡ወንበሩ፤
አሁንም፡የምሥራች፡ከሰባ፡ዘመን፡
አስቀድሞ፡ከባቢሎን፡አትወጡምና፡
ቤት፡አንፃችሁ፡ኑሩ፤በዚያው፡በሠራ
ችሁት፡ቤትም፡ሰባ፡ዘመን፡ኑሩበት፤

ወትክሉ፡አቅማሃተ፡ወብልዑ፡ፍሬሁ፤
ዘር ፡ ዝሩ ፤ አትክልትም ፡ ትከሉ ፤
ፍሬውም፡ደርሶላችሁ፡ብሉ፡ብሏል፡
እግዚአብሔር፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፤ ወአንበባ፡ሶፎንያስ፡ካህን፡ለይእቲ፡
መጽሐፍ፡ውስተ፡ዕዝነ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ያንጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሶፎንያስ፡
ይቺን ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀብሎ ፡ ነቢዩ ፡
ኤርምያስ፡እየሰማ፡አነበባት፤

፴፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ፡
ኤርምያስ፤
ያን፡ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡ቃሉ፡ወደ፡
ኤርምያስ፡መጥቶ፡ተነገረ፤

ወይቤሎ፤
እንዲህ፡ብሎ፡እንዲህ፡የሚል፤

፴፩፤ ለአክ፡ኀበ፡ኵሉ፡ፈላስያን፡እንዘ፡
ትብል ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለሳምያ፡ሐላሚ፤
አለምሁ፡አለምሁ፡የሚል፡ሳምያን፡
ነገር፡አድርገህ፡ተናገረው፤አንድም፡
ለኤሎሙ ፡ ሰው ፡ ለሳምያ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡
ተማርከው፡ በባቢሎን ፡ ወደሚኖሩ ፡
ሰዎች፡ላክ፤

እስመ፡ተነበየ፡ለክሙ፡በስምየ፡ሳምያ፡ዘኢ
ለአክዎ፡አነ፤
እኔ ፡ ምክር ፡ አስተምር ፡ ብዬ ፡ ያልላ
ኩትን ፡ ነገር ፡ አለምሁ ፡ አለምሁ ፡
የሚል ፡ ሳምያ ፡ ከመዝ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ብሎ፡ሐሰት፡ትንቢት፡ተናግ
ሯልና፤

ወአሰፈወክሙ፡ሐሰተ፤
እኔ፡በሰባ፡ዘመን፡ትወጣላችሁ፡ብዬ፡
የተናገርኩትን ፡ እሱ ፡ በሁለት ፡
ዓመት፡ ትወጣላችሁ ፡ ብሎ ፡ ሐሰት ፡
ነገሩን፡ተናግሮ፡በሁለት፡ዓመት፡እን
ወጣለን፡ብላችሁ፡ተስፋ፡አድርጋች
ኋልና፤

፴፪፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፤
እኔ ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ትወጣላችሁ ፣
ከሰባ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ግን ፣
አትወጡም ፡ ብዬ ፡ የተናገርኩትን ፣
የኔን ፡ ቃል ፡ ሐሰት ፡ አድርጎ ፡ የሱን ፣
ሐሰት ፡ ትንቢት፡ እውነት፡ አድርጎ ፣
በሁለት፡ዓመት፡ትወጣላችሁ፡ብሎ፣
ስላስተማረ፡እናንተም፡የሱን፡ቃል፣
እውነት፡አድርጋችሁ፡እውነት፡ነው፤
በሁለት ፡ ዓመት ፡ እንወጣለን ፡ ብላ
ችሁ ፡ ተስፋ ፡ ስላደረጋችሁ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ ፡ አነ ፡ እዋሕዮሙ ፡ ለሳምያ ፡ ሐላሚ ፣
ወለዘርኡ፤
እነሆ፡እኔ፡አለምሁ፡አለምሁ፡የሚል፡
ሳምያንና ፡ ልጆቹን ፡ የልጅ ፡ ልጆ
ቹንም፡በመዓት፡እጐበኛቸዋለሁ፤

ወኢይሄሉ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይነብር ፡
በማዕከለ፡ኵሉ፡ሕዝብ፤
በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ በመምህ
ርነት ፡ ጸንቶ ፡ የሚያስተምር ፡ ከሱ ፣
ወገን፡አንድ፡ሰው፡ስንኳ፡አይኖርም፤

ወዘይሬኢ ፡ ሠናያተ ፡ ዘአነ ፡ እገብር ፣
ለሕዝብየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ይቤ ፣
እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ እኔ ፣
ለወገኖቹ ፡ የማደርገውንም ፡ ተድላ ፣
ደስታ፡ከእሱ፡ወገን፡የሚያይ፡የለም፤
አይኖርም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡ዓመፃ፡ተናገረ፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፣



በፈጣሪው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ላይ፡እሱ፡ደፍሮ፡ሐሰት፡ነገር፡ተናግ
ሮዋልና ፤ አንድም ፡ ላዕለን ፡ ጥሶ ፡
ወሐሊቆ፡፸፡ዓመት፡ብሎ፡የተናገረ፡
እግዚአብሔርን ፡ ሐሰት ፡ ተናገረ ፡
ብሎታልና።

## ምዕራፍ፡፴፤

፩፤ ዝንቱ፡ነገር፡ዘነገሮ፡እግዚአብሔር፡
ለኤርምያስ፡ወይቤሎ፤
እግዚአብሔር፡ለኤርምያስ፡እንዲህ፡
ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነገር፡ ይህ ፡ ነው ፤
አንድም፡ለኤርምያስ፡እግዚአብሔር፡
የነገረው፡ነገር፡እንዲህ፡ብሎ፡ነው፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡
እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤

ጸሐፍ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘነገርኩከ ፡ ውስተ፡
መጽሐፍ፤
በመጽሐፍ፡ጽፌ፡የነገርኩህን፡ሁሉ፡
አንተም ፡ በመጽሐፍ ፡ ጻፈው ፤
አንድም፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘነገርኩከ ፡
ጸሐፍ፡ውስተ፡መጽሐፍ፡ይላል፤የነገ
ርኩህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመጽሐፍ፡
ጻፈው፡አለ፤መጽሐፍ፡አለው፡ከሆነ፡
በኋላ ፤ አንድም ፡ ጸሐፍ ፡ ውስተ ፡
መጽሐፍ፡ይላል፡በብራናው፡ጻፈው፡
ሲል፡ነው፤

፫፤ እስመ፡ናሁ፡መዋዕል፡ይመጽእ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡
ይመጣል፡ብሏልና፤
ወእመይጥ፡ፄዋ፡ሕዝብየ፡እስራኤል፡ወይሁዳ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፤
ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡
የወገኖቼ ፡ ያሥሩን ፡ ነገድና ፡
የሁለቱን፡ነገድ፡ምርኮ፡እመልሳለሁ፡
ብሏልና፤

ወአገብኦሙ፡ውስተ፡ምድሮሙ፡ዘወሀብኩ፡
ለአበዊሆሙ፡ይረስዋ፤
ወርሰዋት ፡ ሊኖሩ ፡ ቀድሞ ፡ ለአባቶ
ቻቸው ፡ ወደሰጠኋት ፡ አገራቸውም ፡
እመልሳቸዋለሁና ፤ ይረስዋ ፡ ባለው ፡
ይኰንንዋ፡ይላል፤እንደዚሁ፡ያስተረ
ጉማል፤ አንድም ፡ ወአገብኦሙ ፡
ውስተ፡ ምድሮሙ ፡ ዘወሀብክዎሙ ፡
ለአበዊሆሙ ፡ ወይኴንንዋ ፡ ይላል፤
ቀድሞ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደ ፡
ሰጠኋቸው ፡ አገራቸው ፡ እመልሳቸ
ዋለሁ ፤ እነሱም ፡ ከዚያ፡ ገብተው ፡
ተካፍለው ፡ ይገዙዋታል ፤ ወይኴ
ንንዋ፡ ባለው ፡ ወይወርስዋ ፡ ይላል ፤
እንደዚሁ፡ያስተረጉማል፤

፬፤ ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ነገር ፡ ዘነበበ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ላዕለ፡እስራኤል፡ወላዕለ፡ይሁዳ፤
ላሥሩ፡ ነገድና ፡ ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ይቅርታው፡እንዲደረግላቸው፡እግዚ
አብሔር ፡ የተናገረው ፡ ነገር፡ ይህ ፡
ነው፤

፭፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ድምፀ፡ግርማሁ፡ግሩመ፡ትሰምዑ፡ወአልቦ፡
ሰላም፤
ዛሬ ፡ ግን ፡ ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል ፡ የነጋ
ሪቱን ፡ ድምፅ ፡ ትሰማላችሁ፤ ፍቅር ፡
አንድነቱ ፡ ግን ፡ የለም ፤ አይደረግላ

www.ethiopianorthodox.org

ችሁም ፤ አንድም ፡ ድምፀ ፡ ግርማ ፡
ሰማዕነ ፡ ወአልቦ፡ ሰላም ፡ ው ጋ ፡ ው ጋ ፡
የሚል ፡ የነጋሪቱን ፡ ድምፅ ፡ ሰማን ፤
ፍቅር፡ አንድነቱ ፡ ግን ፡ የለም ፤ አይደረ
ግልንም፡ይላል፡ነቢዩ፤

፮፤ ተሰአሉ ፡ እስኩ ፡ ወአእምሩ ፡ እመ፡
ወልድ፡ተባዕት፤

ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነቅንቆ ፡ ጋሻ ፡
ነጥቆ፡የሚዋጋ፡ወንድ፡ልጅ፡እንዳለ፡
እስኪ፡ጠይቁ፡መርምራችሁ፡እወቁ፤

ለምንት ፡ እሬኢ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ እዴሁ ፡
ውስተ፡ሐቋሁ፡ከመ፡እንተ፡ትወልድ፤

ኤርምያስ ፡ ባጭር ፡ ታጥቀን ፡ ዘገር ፡
ነጥቀን ፡ አንዋጋምና ፡ ነው? እንዲህ ፡
የምትለን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፤ ባጭር ፡
ታጥቃችሁ ፡ ዘገር ፡ ነጥቃችሁ ፡ ከተዋ
ጋችሁ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጁን ፡ በወገቡ ፡
አድርጎ ፡ ወገቡን ፡ ሲያፍተለትል፡
በእጁ ፡ ያች ፡ ምጥ ፡ የያዛት ፡ ሴት ፡
በምጡ፡ ተይዛ፡እንድትጨነቅ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ በመከራው ፡ ተይዞ ፡ ሲጨነቅ ፡
አየዋለሁ፤

ወተወለጠ፡ኵሉ፡ገጾሙ፡ወጸልመ፡ሌሊት፤
መዓልቱ ፡ በጨለማው ፡ እንዲጠቁር ፤
እንዲለወጥ ፡ የሰው ፡ ሁሉ፡ ፊትስ ፡
በመከራው ፡ ተይዞ፡ ጠቍሮ ፡ ተለ
ውጦ፡ለምን፡አየዋለሁ፤

፯፤ አሌ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ ዓባይ ፡ ይእቲ፡
ዕለት፤

ዬዋዬ ፡ የሚደረግባት ፡ ይቺ ፡ ቀን ፡
ታላቅ፡ናትና፤

ወአልቦ፡ዘከማሃ፤
እንደሱዋም ፡ ያለ ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡
የሚደረግባት፡የለምና፡ወዮልኝ፤

ወመዋዕለ፡ምንዳቤ፡ይእቲ፡ለያዕቆብ፤

ለእስራኤልም ፡ መከራ ፡ የሚታዘ
ዝባት፡ቀን፡ናት፤ያዕቆብ፡አለው፡እስ
ራኤልን ፡ በአባቱ ፤ ከዚያ ፡ በደቂቀ ፡
ነቢያት፡ ዓሥሩን፡ ነገድ ፡ በአባቱ፡
ኤፍሬም፡እንዳለው፤

ወእምኔሁ፡ይድኅን፤

ያንጊዜ ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ የሠራ፡
ሰው ፡ ግን ፡ ከመከራው ፡ ይድናል ፤
አንድም ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ይድኅን ፡
ይላል ፤ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡
ያዕቆብ ፡ እስራኤል ፡ ከመከራው ፡
ይድናል፤

፰፤ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡
ፀባኦት፡አርዑተ፡እስዕር፡እምክሣድከ፤

በዚያ ፡ ወራት ፡ የባቢሎንን ፡ ጽኑ፡
አገዛዝ ፡ ካንተ ፡ አጠፋለሁ ፡ አለ ፡
አቾናፊ፡እግዚአብሔር፤

ወእሰብር፡መዋቅሕቲከ፤

በቁሙ ፡ እግር ፡ ብረትህን ፡ ሰንሰለ
ትህን፡እሰብርልሃለሁ፤አንድም፡ጽኑ፡
አገዛዝህን፡አጠፋልሃለሁ፤

ወኢትትቀነይ፡እንከ፡ለነኪር፤

ካንተ ፡ ልዩ ፡ ለሆነ ፡ ለአሕዛብም ፡
አትገዛም፤

፱፤ ወይትቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
አምላኮሙ፡ወለዳዊት፡ንጉሦሙ፡ዘአነሥእ፡
ሎሙ፤

ከሰባ፡ዘመን፡በኋላስ፡ለፈጣሪያቸው፡
ለእግዚአብሔርና ፡ እኔ ፡ ለማነግሥ
ላቸው ፡ ለንጉሣቸው ፡ ለዘሩባቤል ፡
አንድ ፡ ሁነው ፡ ይገዛሉ ፡ ዳዊት ፡



አለው ፤ ዘሩባቤልን ፡ ከዳዊት ፡ ወገን ፡
ስለተወለደ ፡ አካዘንም ፡ ከዳዊት ፡
ወገን፡ ስለተወለደ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡
ዘንተ፡ ዳዊት ፡ ደንገፀት ፡ ነፍሱ ፡
ወነፍሰ፡ኵሉ፡ሕዝቡ፡እንዲል፤

፲፤ ወኢትፍራህ፡አንተ፡ገብርየ፡ያዕቆብ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡ወኢትደንግፅ፡ኧኤል፤

አገልጋዬ ፡ ዓሥሩ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ፡
ይኸንን ፡ ነገር ፡ ባየህ ፡ በሰማህ ፡ ጊዜ ፡
እንደተማረክሁ ፡ እቀራለሁ፡ ብለህ ፡
አትፍራ ፤ አትደንግጥ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

፲፩፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ አድኅነከ ፡ እምርኁቅ ፡
ወለዘርእከ፡እምድረ፡ፍልሰቶሙ፤

ከሰባ፡ዘመን፡በኋላ፤አንድም፡ከፋርስ፤
ከባቢሎን ፡ ከጽርዕ ፡ ከሜዶን ፤
አንድም፡ እምርኁቅ ፡ ከሰማይ ፡ ሁኜ ፡
በረድኤት ፡ አድንሃለሁና ፤ ልጆች
ህንም ፡ ከተማረኩበት ፡ አገር ፤
አንድም፡ እምድኅረ ፡ ፍልሰቶሙ ፡
ይላል ፤ ከተማረኩ በኋላ ፡ አድናቸዋ
ለሁና፤

ወይትመየጥ ፡ ያዕቆብ ፡ ወየዓርፍ ፡ ወይት
ዓመን፤

ያዕቆብም ፡ ከተማረከበት ፡ ሀገር ፡
ከባቢሎን ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ጠላት ፡
ጠፍቶለት ፡ ከመከራው ፡ አርፎ ፡
ተዘልሎ፡ይኖራል፤

ወአልቦ፡ዘያደነግፆ፤

በዚያ ፡ ወራትም ፡ መጣሁ ፡ ታጠቅ ፡
ብሎ ፡ የሚያስደነግጠው፡ ጠላት ፡
የለም፤

፲፪፤ እስመ ፡ ምስሌከ ፡ አነ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ከመ፡አድኅንከ፤

አንተን ፡ ከመከራው ፡ ላድንህ ፡ እኔ ፡
ካንተ፡ጋራ፡በረድኤት፡እኖራለሁና፤

እስመ ፡ እገብር ፡ ማኅለቅተ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
አሕዛብ፡ኅበ፡ዘረውኩከ፤

አንተን ፡ በማረኩ ፡ በአሕዛብ ፡ የመከ
ራውን ፡ ፍጻሜ ፡ አደርግባቸዋለሁና ፤
አንድም ፡ ኅበ ፡ ዘረውኩከ ፤ አንተን ፡
አስማርኬ ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ በባ
ቢሎን ፡ ካኖርኩህ ፡ በኋላ ፡ የመከራ ፡
ፍጻሜ፡አደርግልሃለሁና፤

ወኪያከኒ፡ኢይሬስየከ፡ትኅልቅ፤
አንተን፡ግን፡ጨርሰህ፡ትጠፋ፡ዘንድ፡
ጨርሰህ፡እንድትጠፋ፡አላደርግህም፤

ወገሠፅኩከ፡ለኵነኔ፤
መከራውን፡ልትቀምሰው፡በመከራው፡
ገሠፅኩህ፤

ወአንጽሖ፡ኢያነጽሐከ፤
መከራውን ፡ ግን ፡ ሳላቀምስ ፡ አልተ
ውህም ፤ አንድም ፡ መከራውን ፡ ሳላቀ
ምስህ፡ከፍዳ፤ከኃጢአት፡አላነጻሕም፤

፲፫፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ተንሥአ፡ጸልዐ፡ቍስለ፡መቅሠፍትከ፤
መቅሠፍተ ፡ መከራህን ፡ የሚያመ
ጣብህ ፡ ቍስለ ፡ መከራህ ፡ ሰፍቶብ
ሃልና ፡ አለ ፤ ብዙ መቅሠፍት ፡
የሚያመጣ፡ኃጢአትህ፡ብዙ፡ነውና፡
ሲል፡ነው፤

፲፬፤ ወአልቦ፡ዘይፈትሕ፡ፍትሐከ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ ትሩፍ ፡ ያለአገባብ ፡
ተበድሏል ፡ ብሎ ፡ የጠመመውን ፡ የተ
ፈረደብህን ፡ ፍርድ ፡ አቅንቶ ፡ የሚፈር
ድልህ፡የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢይበቍዓከ፡ዘተፈወስከ፡ቍስለከ፡
ከዚህ፡ቀድሞ፡ሰላም፡ሰላም፡ብለው፡
ነቢያተ፡ሐሰት፡ከቍስለ፡መከራህ፡
ያዳኑህ፡ማዳን፡ዛሬ፡አይረባህም፡አይ
ጠቅምህም፤

ኵሎሙ ፡ አዕርክቲከ ፡ ረሥዑከ ፡ ወኢ...
ሠሡከ፤
ስንኳን ፡ ሌላው ፡ እንደ...ችው ፡
አድርገው ፡ የሚወዱህ ፡ ወ...ጆችህ ፡
ሁሉ ፤ አንድም ፡ አንተ ፡ እን...ስህ ፡
አድርገህ ፡ ትወዳቸው ፡ የነበረ ፡
ወዳጆችህ ፡ ዘነጉህ ፤ የት ፡ ወደቀ ፡
ብለው፡አልፈለጉህም፤

እስመ ፡ አቍሰሉከ ፡ ፀርከ ፡ ...
ጽኑዕ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ጌጋይከ፡
በበደልኸኝ ፡ በደል ፡ ... በጽኑ፡
መቅሠፍት ፡ ተይዘህ ... ፡
ጠላቶችህ፡ አሕዛብ ፡ ... ፡
ብለው ፡ አቍስለውሃልና ... ፡
እስመ፡አቍሰሉከ፡ፀር... ፡
አሕዛብ ፡ ከበው ፡ ው... ፡
ብለው፡አቍስለውሃልና ...ከ፡
አለ፤

መቅሠፍተ፡ጽኑዐ፡ላዕለ፡...
በበደልኸኝ ፡ በደል ፡ ... ጽኑ ፡
መቅሠፍት፡አመጣብ...

እስመ፡በዝኃ፡ኃጣውኢከ
ኃጢአትህ፡ብዙ፡ስለ...

፲፭፤ ምንተ፡ተዐወዩ፡...
በቍስለ ፡ መከራህ ፡ ... ፡ ለምን፡
ታዝናለህ?፡ታለቅሳለ...

ተንሥአ፡ቍስልከ፡
ቍስለ፡መከራህስ፡... ...ቷል፡
እወቀው፤

በእንተ፡ብዝኃ፡ጌጋይከ፡ጸንዐ፡ኃጣውኢከ፡
ብዙ፡በደል፡ሠርተህ፡ስለበደልኸኝ፡
ፍዳዎቹ፡ጸኑብህ፤ኃጣውእ፡ያላቸው፡
ፍዳዎቹን፡ነው፤በግብሩ፡ፍዳውን፡
ኃጢአት፡አለው፤አንድም፡ኃጢአት፡
ሠርቶ፡ፍዳው፡ስለመጣበት፡ፍዳውን፡
ኃጢአት፡አለው፤

ዘንተ፡ኵሎ፡ገበርኩ፡ለከ፡
ብከ፡ሲል፡ነው፤አንተ፡በኔ፡ይኸን፡
ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ስላደረግህብኝ ፡
እኔም፡ባንተ፡ይህን፡ሁሉ፡መከራ፡አደ
ረግሁብህ ፤ አንድም፡ እንዳለም ፡
ይሆናል፤ይህን፡ሁሉ፡ሚጠትን፡አደረ
ግሁልህ፡አለ፤ገና፡ወደፊት፡የሚያመ
ጣውን፤

፲፮፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡
ይበልዑከ፡ይትበልዑ፡
አንተ ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ስላመለክህ ፡
ስላመንክ፡ ያንተን፡ገንዘብ፡ዘርፈው፡
ገፍፈው ፡ የበሉ ፤ ሰዎች፡ የነሱም ፡
ገንዘብ፡ይዘረፍባቸዋል፡ይበላባቸዋል፤

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፄውዉከ ፡ ውስተ ፡ ፄዋ፡
የሐውሩ፤
አንተንም፡ማርከው፡የወሰዱ፡ሰዎች፡
ኋላም፡እነሱ፡ተማርከው፡ይሄዳሉ፤

ወእለሂ፡በርበሩከ፡ይትበረበሩ፤
ያንተንም ፡ ገንዘብ ፡ በርብረው ፡
የወሰዱ፡ሰዎች፡የነሱም፡ገንዘብ፡ይበ
ረበራል፤

ወለኵሎሙ፡እለ፡ማኅረኩከ፡እሁቦሙ፡ለተ
ማህርኮ፤
አንተን ፡ ማርከው ፡ የወሰዱ ፡ ሰዎ
ችንም፡ አሳልፌ፡ኋላ፡ለምርኮ፡እሰጣ
ቸዋለሁ፤



፲፯፤ እስመ ፡ እፌውሰከ ፡ እምቍስልከ፡
እኩይ፤
ከሰባ፡ዘመን፡በኋላ፡ከክፉ፡ቍስለ፡
መከራህ፡አድነሃለሁና፤

እስመ፡አዓርግ፡ለከ፡ፈውሰ፤
ድኅነትን፡አመጣልሃለሁና፤

ወእምቍስልከ ፡ አሐይወከ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እግዚአብሔርም፡ከቍስለ፡መከራህ፡
አድንሃለሁ፡ብሏልና፤

እስመ፡ተሠመይኪ፡ዝሩተ፡አንቲ፡ጽዮን፤
ጽዮን ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ የተበተነች ፡
የጠፋች፡ናት፤ስለተባልሽ፡አንድም፡
ተብለሻልና፤

ወአልቦ፡ዘይትኃሠሥ፡ለኪ፤
ባንቺም ፡ አዝኖ ፡ ተቆርቁሮ ፡ ባጭር ፡
ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ የሚዋጋልሽ ፡
አርበኛ ፡ ስለሌለሽ ፡ ስላልኖረሽ ፤
አንድም፡ባጭር፡ታጥቆ፡ዘገር፡ነጥቆ፡
የሚዋጋልሽ ፡ አርበኛ ፡ የለምና ፡
አሐይወከ፡ብለህ፡እሠር፤

፲፰፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እመይጥ፡ፈላስያነ፡ቤተ፡ያዕቆብ፤
ተማርኮ ፡ የሄደ ፡ የያዕቆብን ፡ ወገን ፡
ሁሉ ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ እነሆ፡ እመል
ሳለሁ፤

ወማኅደሪሁኒ፡እሠሃል፤
ማደሪያውንም፡ይቅር፡እላለሁ፡አለ፤
ተፈትታ ፡ ጠፍታ ፡ የነበረች ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ተመልሳ ፡ ትቀናለች ፡ ሲል
ነው፤

ወትትሐነፅ፡ሀገር፡በኑኃ፤
አገሪቱም ፡ ባቈልቋይዋ ፡ በወርዱ ፡
ትቀናለች ፡ አለ፤ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡
ትቀናለች፡ሲል፡ነው፤አንድም፡ቤተ፡
መቅደስ፡እንደቀድሞ፡እንደሰሎሞን፡
ዘመን፡ጊዜ፡ባቈልቋይዋ፡ትሠራለች፡
አለ፤ሰቀልኛ፡ናትና፤

ወኤርሞን፡በከመ፡ሕጉ፡ይገብእ፤
ኤርሞን ፡ ቅጽር ፡ ነው ፤ ቅጽሩም ፡
ባራቱ፡ ማዕዘን ፡ እንደቀድሞው ፡
ይቀጸራል፤አንድም፡አራት፡ማዕዘን፡
ያለው ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ እንደቀ
ድሞው ፡ በአራት ፡ ኅብር ፡ ይሠራል፤
አንድም ፡ ኤርሞን ፡ ገኸሮው ፡ እንደቀ
ድሞው ፡ አራቱን ፡ ማዕዘን ፡ ይገዛል፤
አንድም ፡ ኤርሞን ፡ ሰማይ ፡ ነው፤
ሰማይ፡እንደቀድሞው፡ዝናም፡ለዘር፡
ጠል፡ለመከር፡ይሰጣል፤

ወሕዝብኒ፡ይገብኡ፡በበሥርዓቶሙ፤
ሕዝቡም ፡ እንደቀድሞው ፡ በየሥርዓ
ታቸው፡ሰፍረው፤አንድም፤በየሥርዓ
ታቸው፡ቆመው፡ሊያገለግሉ፡ወደማ
ገልገል፡ይመለሳሉ፤

፲፱፤ ወይወጽእ ፡ እምህየ ፡ አኰቴት ፡
ወቃለ፡ተውኔት፤
እምህየ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ፤ አንድም ፡
ከአፋቸው፡ካንደበታቸው፡ከቃላቸው፡
በዝቶ ፡ ምስጋና ፡ ዘፈን ፡ ጨዋታ ፡
አጭብጫቦ፡ይሰማል፤

ወአበዝኆሙ፡ወኢይውኅዱ፡እንከ፤
እንደቀድሞው፡ዘመን፡አበዛቸዋለሁ፤
ከዚህ፡ቀድሞ፡በፄዋዌ፡አንሰው፡እን
ደነበረ፡ከሚጠት፡በኋላ፡አያንሱም፤

፳፤ ወይከውኑ፡ደቂቁ፡ከመ፡ትካት፤
ልጆቹም፡እንደቀድሞው፡በዝተው፡
ያመሰግናሉ፤

ወይረትዕ፡ስምዖሙ፡በቅድመ፡ገጽየ፤
ምስክርነታቸውም፡በኔ፡ፊት፡የቀና፡
ምስክርነት፡ይሆናል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእዋህዮሙ፡ለእለ፡አስርሕዎሙ፤
ሰላም ፡ ሰላም ፡ እያሉ ፡ ያደከሟቸው ፡
ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ካህናተ ፡ ጣዖትን፤
አንድም፡ለእለ፡አርስእዎሙ፡ይላል፤
ሕግ፡እግዚአብሔርን፡እንዳይጠብቁ፡
እንዲዘነጉ፡ያደረጉዋቸው፡ነቢያተ፡
ሐሰት፡ ካህናተ ፡ ጣዖትን፤ አንድም ፡
ለእለ ፡ አርስሕዎሙ ፡ ይላል ፤ በኃ
ጢአት ፡ በጣዖት ፡ ያረከሱዋቸው ፡
ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ካህናተ ፡ ጣዖትን ፡
በመዓት፡እጐበኛቸዋለሁ፤

ወይትመውዑ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ እስራኤልም ፡
ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ቢገጥሙ ፡
ድል፡ይነሣሉ፤አንድም፡ወይመውቱ፡
ይላል፤እስራኤል፡ጦርነት፡ቢገጥሙ፡
አይገድሉም፤ እነሱ ፡ ይሞታሉ፤ አን
ድም ፡ አትሞቱም ፡ ብለው ፡ የመከሩ፡
ያስተማሩ፡ነቢያተ፡ሐሰት፡ካህናተ፡
ጣዖት፡እነሱ፡አስቀድመው፡በጦር፡
ይሞታሉ፤

፳፩፤ ወመልአክሂ ፡ ይሠየም ፡ እምውስ
ቴቶሙ፤
ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ዘሩባቤል ፡
ከነሱ ፡ ወገን ፡ ተወልዶ ፡ ይነግሥላ
ቸዋል፤ አንድም ፡ ወመልአከሂ ፡ እሠ
ይም ፡ እምኔሆሙ ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡
የተወለደ፡ዘሩባቤልን፡እኔ፡አነግሥላ
ቸዋለሁ፤

ወአስተጋብእሙ፡ወእመይጦሙ፡መንገሌየ፡
ያንጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ከባቢሎን ፡
ሰብስቤ ፡ በረድዔት ፡ ወደማድርባት ፡
ወደኢየሩሳሌም ፡ አመጣቸዋለሁ ፤
አንድም፡ከሚጠት፡በኋላ፡ዓሥሩን፡
ሁለቱን፡ነገድ፡በሕግ፡በአምልኮት፡
አንድ፡አድርጌ፡ልቡናቸውን፡ወደኔ፡
እመልሰዋለሁ፤

፳፪፤ ወትከውኑኒ፡ሊተ፡ሕዝበ፤
በዚያ፡ወራት፡እናንተ፡በሕግ፡በአም
ልኮት፡የምታመልኩኝ፡ወገኖች፡ትሆ
ኑኛላችሁ፤

ወአነሂ፡እከውነክሙ፡አምላከክሙ፤
እኔም፡ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ አባት ፡
እሆናችኋለሁ፤

መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘቦ ፡ ልብ ፡ ከመ ፡
ይግባእ፡ኀቤየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ወደኔ ፡ ይመጣ ፡
ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ እውቀት ፡
ያለው፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አለ፡ እግዚአ
ብሔር፤

፳፫፤ እስመ ፡ መዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ወጽአ፡በመቅሠፍት፤
ቍጣዬ ፡ ከመቅሠፍቱ ፡ ጋራ ፡ ታዝዞ ፡
አንድ ፡ ሆኖ ፡ መጥቷልና ፡ ከዚህ ፡
ይድን፡ዘንድ፤

ወአምጽአ ፡ መንሱተ ፡ መዓቱ ፡ ወአግብአ ፡
ላዕለ፡ኃጥአን፤
ቍጣው ፡ የታዘዘበት ፡ ጥፋቱን ፡
አብዝቶ ፡ አምጥቶ ፡ ወደባቢሎን ፡
ሰዎች፡መለሰባቸው፤

ወኢይትመየጥ፡መቅሠፍተ፡መዓቱ፡ለእግዚ
አብሔር፡እስከ፡ይገብር፡ወእስከ፡ያቀውም፡
ዘሐለየ፡በልቡ፤
እግዚአብሔር ፤ በልቡ ፡ ያሰበውን፤
አንድም፡ዘሐለየ፡በልቡ፡ይላል፤እግዚ
አብሔር፡ያሰበውን፡እስኪያደርገው፡
እስኪያጸናው ፡ ድረስ ፡ ተቆጥቶ፡
ያመጣው፡መቅሠፍቱ፡አይመለስም፤

ወበደኃሪ፡መዋዕል፡ተአምርዎ፤
እግዚአብሔር፡አሕዛብን፡መጣላቱን፡



እስራኤልን፡መራዳቱን፡ኋላ፡በሰባ፡
ዘመን ፡ መርምራችሁ ፡ ታውቁታ
ላችሁ።

## ምዕራፍ፡፴፩፡

፩፤ ይእተ፡አሚረ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እከውኖሙ ፡ አምላኮሙ ፡ ለሕዝበ ፡
እሥራኤል፤
ያንጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስ
ራኤል፡ወገኖች፡የፍቅር፡የሃይማኖት፡
አባት፤የፍቅር፡የሃይማኖት፡አምላክ፡
እሆናቸዋለሁ፤

ወእሙንቱኒ፡ይከውኑኒ፡ሕዝብየ፤
እነሱም፡የፍቅር፡የሃይማኖት፡ልጆች፡
ይሆኑኛል ፡ አለ፤ ቀድሞ ፡ ወልድየ ፡
ዘበኵርየ፡እስራኤል፡ብሎ፡ተናግሮ፡
ነበርና፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ረከበ ፡ ሞገሰ ፡ በገዳም ፡ ሕዝብየ፡ ዘያፈቅር ፡
ጸብዐ፤
ቀድሞ፡ ጢት፡ማታ፡ሰልፍ፡ይወድ፡
የነበረ ፡ ወገኔ ፡ እስራኤል ፡ ዛሬ ፡
በምድረ፡በዳው፡ከኔ፡ክብር፡ባለሟል
ነትን ፡ አገኘ ፡ ሕዝብየ ፡ ዘያፈቅር ፡
ጸብአ ፡ ባለው ፡ ሕዝብየ ፡ ድኅረ ፡
ተቀትለ፡በመጥባሕት፡ይላል፤ወገኔ፡
እስራኤል፡በአሕዛብ፡ጦር፡ተወግቶ፡
ከተማረከ፡በኋላ፡ዛሬ፡ግን፡በሰባው፡
ዘመን ፡ ከሰው ፤ ከከብት ፡ ተለይታ ፡
ምድረ፡በዳ፡በሆነች፡በኢየሩሳሌም፡
ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ ባለሟልነትን ፡
አገኘ፤ አንድም ፡ ከረድዔት ፡ ምድረ ፡
በዳ፡በሆነች፡በባቢሎን፡መዋጋትን፡
የሚወድ ፡ ቤተ ፡ እሥራኤል ፡ ክብር ፡
ባለሟልነትን፡አገኘ፤

ሑሩ፡ወኢታጥፍዕዎሙ፡ለእሥራኤል፤
ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ በቃለ ፡ ትንቢቱ ፡
ንዑ ፡ ወተጋብዑ ፡ ብሎ ፡ አሕዛብን ፡
ጠርቷቸው ፡ ነበርና፡ ከሚጠት ፡
በኋላ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ አታጥፉ፤
ተመልሳችሁ፡ወደሀገራችሁ፡ሒዱ፡
አላቸው፤አንድም፡ወደጥፋት፡ሒዱ፡
አላቸው፤

፫፤ እስመ፡እግዚአብሔር፡አስተርአየኒ፡
እምርኁቅ፤
እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ሆኖ፤
አንድም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፤
አንድም ፡ እምን ፡ በ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
በፋርስ፡ በባቢሎን ፡ ሳለሁ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ታይቶኛል፤ተነጋግሮኛልና፤

ወፍቅረ፡ዘለዓለም፡አፍቀርኩከ፤
በኔ ፡ አድሮ ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡
የዘላለም ፡ በሚሆን ፡ ፍቅሬ ፡ ወደ
ድኩህ፡ አለው፤ አንድም ፡ በባቢሎን ፡
ሳለሁ ፡ የዘላለም፡ በሚሆን፡ ፍቅሬ ፡
ወደድኩህ፡አለኝ፤

ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ውስተ ፡ ሣህልየ ፡
ሰሐብኩከ፤
ስለዚህ፡ነገር፡ይቅርታዬ፡ወደሚደረ
ግባት፡ወደኢየሩሳሌም፡ስቤ፡ጐትቼ፡
አወጣሁህ ፡ አለኝ፤ አንድም ፡ ቤተ ፡
እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለወደድኩህ ፡
በሰባው፡ዘመን፡ይቅርታዬ፡ወደሚደ
ረግባት ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ስቤ ፡
ጐትቼ፡አመጣሁህ፡አለው፤

፬፤ ወዓዲ ፡ አሐንፀኪ ፡ ወትትሐነፂ ፡
ድንግለ፡ወለተ፡እስራኤል፤
ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ የነበርሽ ፡ የእስ
ራኤል ፡ ቆንጆ ፡ ቀድሞ ፡ በረድዔት ፡

www.ethiopianorthodox.org

አንፅሽ ፡ እንደነበረ ፡ ዛሬም ፡ ከሰባው ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በረድኤት ፡ አንፅሻለሁ፤ አንቺም ፡ ቀድሞ ፡ በረድዔት ፡ ትታነጪ፡ እንደነበረ ፡ ዛሬም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን፡በኋላ፡በረድዔት፡ትታነጫለሽ፤

ንሥኢ ፡ ከበሮኪ ፡ ወጻኢ ፡ ምስለ ፡ ማኅበር ፡ እለ፡ይትዋነዩ፤

ዛሬም ፡ ከበሮሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ይዘሽ ፡ በዝተው ፡ ከሚጫወቱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ልትጨዋወቺ ፡ ወደአደባባይ ፡ ውጪ፤ አንድም ፡ ከሚጨዋወቱ ፡ ወገኖችሽ ፡ ጋራ፡በዝተሽ፡ወደአደባባይ፡ውጪ፤

፭፤ ዓጺ ፡ ትተክሊ ፡ አዕፃዳተ ፡ ወይን ፡ ውስተ፡አድባረ፡ሰማርያ፤

ቀድሞ ፡ በሰማርያ ፡ ተራራ ፡ ወይኑን ፡ ትርንጎውን፡ትተክሊበት፡እንደነበረ፡ ከሰባ ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ እንደቀ ድሞው፡ በሰማርያ ፡ ተራራ ፡ ወይኑን ፡ ትርንጎውን ፡ ትተክሊበታለሽ ፤ ትክሉ፡ እለ ፡ ትተክሉ ፡ ማንሻ ፤ አንድም፡ ውስተ፡አድባረ፡ሰማርያ፡

ትክሉ፡እለ፡ትተክሉ፤

ቀድሞ ፡ በሰማርያ ፡ ተራራ ፡ ወይኑን ፡ ተክላችሁ፡ ታርሙት ፡ ትኰተኲቱ ፡ የነበራችሁ፡እስራኤል፡ዛሬም፡ከሰባ፡ ዘመን ፡ በኋላ፡እንደቀድሞው፤ዛሬም፡ በሰማርያ ፡ ተራራ ፡ ወይኑን ፡ የምት ተክሉ፡እስራኤል፡ወይኑን፡ትክሉ፤

ወሰብሑ፤

ወይኑንም ፡ ከተከላችሁ ፡ በኋላ ፡ ለሀገ ራችን፡ለኢየሩሳሌም፡ያበቃኸን፡ዘር፡ ዘርተን፡ተክል፡ተክለን፡እንድንኖር፡ ያደረግኸን ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአ ብሔር፡ተመስገን፤ምስጋና፡ይገባሃል፡ ብላችሁ ፡ ለፈጣሪያችሁ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ምስጋና፡አቅርቡ፤

፮፤ እስመ፡ሀለወት፡ዕለት፡ጸዋዔከሙ፡ እናንተን ፡ ወደጥንት ፡ ሀገራችሁ ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ የሚጠራብት ፡ ሚጠት፡ የሚደረግባት፡ቀን፡በረድዔቱ፡ተጠባ ቃለችና፤

ወታወሥኡ፡ውስተ፡አድባረ፡ኤፍሬም፤

ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ በሚጠት ፡ ወደሀገ ራችሁ ፡ ወደሰማርያ ፡ ተመልሳችሁ፡ እንደጥንቱ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር፡ በሰማርያ፡ተራራ፡ትጫወታላችሁ፤

ተንሥኡ፡ንዕርግ፡ውስተ፡ጽዮን፡ኀበ፡እግዚ አብሔር፡አምላክነ፤

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በረ ድዔት፡አድሮባት፡ወደሚኖር፡ወደጽ ዮንም ፡ ተነሡ ፤ ለገቢረ ፡ በዓል፡ እንውጣ፡ትላላችሁ፤

፯፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ተፈሥሑ፡ትፍሥሕተ፡ቤተ፡ያዕቆብ፤

ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ብላችሁ፤ አንድም፡ በእንተ ፡ ያዕቆብ ፡ ይላል ፤ ስለሁለቱ፡ ነገድ ፡ ትንቢት ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ፡ ዓሥሩ ፡ ነገድ ፡ ተጨምረው ፡ የወጡ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ተስፋ ፡ ነውና፤ አንድም ፡ ተፈሥሑ ፡ ቤተ ፡ ያዕቆብ፡ ትፍሥሕተ ፡ ይላል ፡ ያሥሩን ፡ ነገድ፡ ተናግሮ ፡ ነበርና ፡ የያዕቆብ ፡ ወገኖች፡ ሁሉቱም ፡ ነገድ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ፤

ወከልሑ ፡ ውስተ ፡ አርእስተ ፡ አሕዛብ ፡ ወአስምዑ፡ወሰብሑ፤

የአሕዛብ፡ቸብቸቦ፡በሰባ፡ዘመን፡ስለ ተቆረጠላችሁ ፤ አንድም ፡ የአሕዛብ፡ አለቆች ፡ እነብልጣሶር ፡ ስለጠፉ ላችሁ፡ ጮኻችሁ ፡ አዳኙ ፤ ፈጣሪያች ሁንም፡አመስግኑ፤



ወበሉ፡አድኃነ፡እግዚአብሔር፡ሕዝቦ፡እለ፡ ተርፉ፡እምእስራኤል፤

በሥሩ ፡ ነገድ ፡ ተማርከው ፡ ሒደው ፡ ከሞት ፡ የቀሩ ፡ ወገኖቹን ፡ ዓሥሩን ፡ ነገድ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ አዳነ፡በሉ፤አንድም፡እለ፡ተርፉ፡እም እስራኤል፡ባለው፡እለ፡ተርፉ፡እምኢ የሩሳሌም ፡ ይላል፤ ከኢየሩሳሌም ፡ ተማርከው ፡ ሒደው ፡ ከሞት ፡ የቀሩ ፡ ወገኖቹ ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ እግዚአ ብሔር፡በሰባ፡ዘመን፡አዳነ፡በሉ፤

፰፤ናሁ፡አነ፡አመጽአሙ፡እምሰሜን፡ወአ ስተጋብአሙ፡እምአጽናፈ፡ምድር፡በበዓለ፡ ፋሲካ፤

ቀድሞ፡በበዓለ፡ፋሲካ፡ይሰበሰቡ፡እን ደነበረ ፤ አንድም ፡ ለበዓለ ፡ ፋሲካ ፡ ይላል፤ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካን ፡ ሊያደርጉ ፡ እምሰሜን ፡ ከባቢሎን ፤ እምአጽናፈ ፡ ምድር ፡ ከፋርስ ፤ ከጽርዕ፤ ከሜዶን ፡ ሰብስቤ ፡ አመጣቸዋለሁ፤

ፀንሰት፡ወወለደት፡ማኅበረ፡ዓቢየ፡በህየ፤

ቤቱ ፡ እስራኤል ፡ በባቢሎን ፡ ሳለች ፡ ፀንሳ፡ ወልዳ ፡ ብዙ ፡ ሁና ፡ ወጣች ፡ አለ፤ ከዚያው ፡ ተፀንሰው ፡ ከዚያው ፡ ተወ ልደው ፡ አድገው ፡ የወጡ ፡ እስራኤል ፡ አሉና፤እንደነዘሩባቤል፡ይህን፡ባለው፡ ወይትወለዱ፡ብዙኃን፡አሕዛብ፡በህየ፡ ይላል፤ በባቢሎን ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ተወልደው፡ወይመጽኡ፡ዝየ፤ወደኢየ ሩሳሌም ፡ ይመጣሉ ፡ አለ፤ አምነው ፡ ተጋብተው፡ ተዋልደው ፡ አብረው ፡ የወጡ፡አሕዛብ፡አሉና፤

፱፤ እንዘ ፡ ይበክዩ ፡ ኀለፉ ፡ ወእንዘ ፡ ይትፌሥሑ፡አእትዎሙ፤

ቀድሞ ፡ ተማርከው ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ ተሸከመው ፡ ሲሔዱ ፡ እያለቀሱ ፡ ሔዱ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ እንደወጓቸው ፡ ወግተው ፡ እን ደዘረፏቸው ፡ ዘርፈው ፡ ገድለው ፡ ሰልበው ፡ እያገረሩ ፡ እየደነፉ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ወደሀገራቸው ፡ ወደኢየሩ ሳሌም፡እመልሳቸዋለሁ፤

ወየኃድሩ ፡ ውስተ ፡ሙኃዘ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ፡መጽያሕት፤

በሰፊው ፡ ጥርጊያ ፡ ጎዳና ፡ ሲመጡ ፡ በየፈሳሹ፡ዳር፡እያደሩ፡ይመጣሉ፤ አንድም፡በጥርጊያ፡ጎዳና፡መጥተው፡ የረድዔቱ ፡ መፍሰሻ ፡ መፋሰሻ ፡ በሆነች፡ በሰማርያ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኖራሉ፤

ወኢይደክሙ፡እንከ፤

በጥርጊያ ፡ ጎዳናም ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ሲመጡ፡ አይደክሙም፤ ኢይደክሙ ፡ ባለው ፡ ወኢየኀይሉ ፡ እንከ ፡ እምኔየ፡ ይላል፤ ቀድሞ፡ ከአግ ፡ ከሴዎን ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብን ፡ ፈርተው ፡ በስርጥ፡ ጎዳና ፡ ዙረው፡ይሔዱ፡እንደነበረ፡ኋላ፡በሰባ፡ ዘመን ፡ ከባቢሎን ፡ ሲወጡ ፡ ግን ፡ አሕዛብን፡ፈርተው፡ከጥርጊያ፡ጎዳና፡ ወጥተው ፡ ዙረው ፡ በስርጥ ፡ ጎዳና ፡ አይሄዱም፤

እስመ ፡ ኮንክዎ ፡ ለእስራኤል ፡ አባሁ ፡ ወኤፍሬም፡በኵርየ፡ውእቱ፤

ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ለእስራኤል ፡ አባቱ፡ ሆኜዋለሁና፡አለ፡ለሠራዊቱ፡ ነው፤ ኤፍሬምም ፡ የበኽር ፡ ልጄ ፡ ነውና፡ አለ ፤ የበኽር ፡ ልጅ ፡ እንዲ ወደድ ፡ እወደዋለሁ፤ ንጉሡ ፡ ነው ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ የተናገረ ፤ ላሥሩም ፡ ለሁለቱም፡ነገድ፡ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፤ ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አሕዛብ፡
አሕዛብ ፡ ይህንን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ስሙ ፡ አለ፡ በቁሙ፤ አንድም ፡
አሕዛብ፡ያላቸው፡እስራኤል፡ናቸው፤

ወዜንዉ፡ውስተ፡ደሰያት፡ዘርኁቅ፡
ይህንንም፡የሰማችሁትን፡የእግዚአብ
ሔርን፡ቃል፡በሩቅ፡ላሉ፡ደሴቶች፡
ሁሉ፡ንገሩ፤

ወበሉ፡ዘዘረዎ፡ለእሥራኤል፡ያስተጋብኦ፡
ቀድሞ፡ያስማረከው፡ፈጣሪው፡እግዚ
አብሔር ፤ በሰባ ፡ ዘመን ፡ መልሶ ፡
ሰብስቦ፡ያመጣዋል፡በሉ፤

ወየዐቅቦ፡ከመ፡ኖላዊ፡ዘይርዒ፡መርዔቶ፡
መንጋውን ፡ የሚጠብቅ ፡ እረኛ ፡
አውሬ፡ይነጥቅብኛል፤ ሌባ፡ይሰርቅ
ብኛል፤ መንጋ፡ከመንጋ፡ተሳስተው፡
ይጠፉብኛል ፡ ብሎ ፡ ነቅቶ፤ ተግቶ ፡
መንጋውን፡እንዲጠብቅ፡በኃጢአት፡
በጣዖት፡ይስትብኛል፡ ብሎ፡እግዚአ
ብሔር ፡ በረድዔት ፡ ይጠብቀዋል ፡
በሉ፤አንድም፡ወበሉ፡ዘዘረዎ፡ለእሥ
ራኤል፡አስተጋብኦ፡ይላል፤ ቀድሞ፡
አስማርኮ ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡
የበተነው፡ እግዚአብሔር ፡ በሰባ ፡
ዘመን ፡ ሰበሰበው ፤ ወዐቀቦ ፡ ከመ ፡
ኖላዊ፡ዘይርዒ፡መርዔቶ፡መንጋውን፡
የሚጠብቅ፡እረኛ፡ነቅቶ፡ተግቶ፡እን
ዲጠብቅ፡ፈጣሪው፡እግዚአብሔርም፡
በረድዔት ፡ ከስሕተት ፡ ከኃጢአት ፡
ከጣዖት፡ጠበቀው፡በሉ፤

፲፩፤ እስመ ፡ አድኃኖ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለያዕቆብ፡ወባልሖ፡እምእደ፡ዘይኄይሎ፡
እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ከሰባ ፡
ዘመን፡መከራ፡ከሚበረታበትም፡ከብ
ልጣሶር፡እጅ፡ፈጽሞ፡አድኖታልና፡
ስላዳነው፤

፲፪፤ ወይመጽኡ፡ወይትፌሥሑ፡በደብረ፡
ጽዮን፡
በሰባ ፡ ዘመን ፡ ከባቢሎን ፡ ተሰብ
ስበው፡ወጥተው፡በደብረ፡ጽዮን፡በኢ
የሩሳሌም፡በከተማዪቱ፡ፈጽሞ፡ደስ፡
ይላቸዋል ፤ በመዲናዪቱ ፡ መናገር ፡
ነው፡እንጂ፡ተድላ፡ደስታውንስ፡የሚ
ያደርጉ፡በየሀገራቸው፡ነው፤አንድም፡
ካመት፡ሦስት፡ጊዜ፡ለገቢረ፡በዓል፡
እየተሰበሰቡ፡ተድላ፡ደስታውን፡ያደ
ርጉባታልና፡እንዲህ፡አላት፤

ወይመጽኡ ፡ ውስተ ፡ ሠናይተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡
ዓሥሩም፡ሁለቱም፡ነገድ፡ሁነው፡የእ
ግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ወደሚደረ
ግባት ፡ ወደሀገራቸው ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ይመጣሉ፤

ውስተ፡ብሔረ፡እክል፡ወወይን፡ወውስተ፡
ቅብዕ፡
ሠናይተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡
ይተረትራል ፤ እክል ፡ ወደሚዘመ
ርበት፡ ዘይትና ፡ ወይን ፡ ወደሚተከ
ልበት፤

ወመዓር፡ወቅብዕ፡
ማርና፡ቅቤ፡ወደሚበላበት፤

ወአባግዕ፡ወአልሕምት፡
ላምና ፡ በግ ፡ ወደሚረባበት ፡ ወደ ፡
ሀገራቸው፡ይመጣሉ፤

ወትከውን፡ነፍሶሙ፡ከመ፡ገነት፡ርውይት፡
ያን ፡ ጊዜም ፡ መስኖ ፡ የምትጠጣ ፡
ተክል፡ ለምልማ፡እንድትኖር፡ሰውነ
ታቸውም ፡ በረድዔቱ ፡ ለምልማ ፡
ትኖራለች፤



ወኢይርኅቡ፡እንከ፡
እነሱም፡ይኽን፡ሁሉ፡ተድላ፡ደስታ፡
አጥተው፡አይራቡም፤

፲፫፤ ውእተ፡አሚረ፡ይትፌሥሓ፡ደናግል፡
በሐሤት፡ወወራዙት፡ወሊቃውንት፡ኅቡረ፤
ያንጊዜም፡ጐልማሶችና፡ሽማግሎች፡
ቆነጃጅቱ ፡ ከልቡናቸው ፡ ባነቁት ፡
በተድላ፡በደስታው፡አንድ፡ሁነው፡
ደስ፡ይላቸዋል፤ከልቡ፡ሳይሆን፡ደስ፡
የሚለው ፡ አለና ፡ ኅቡረም ፡ አለ ፤
ተለያይቶ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የሚያ
ደርግ፡አለና፤

ወእሬስዮ፡ለላሆሙ፡ፍሥሓ፡
የቀድሞውን ፡ ልቅሷቸውንም ፡
መልሼ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደርግላቸ
ዋለሁ፤

ወእስተፌሥሖሙ ፡ ፍሥሓ ፡ ከመ ፡ ይት
ሐሠዩ፡
እነሱም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡
ዘንድ፡ እኔም ፡ በተድላ ፡ በደስታው ፡
ደስ፡አሰኛቸዋለሁ፤

፲፬፤ ወአዐብዮሙ፡
አከብራቸዋለሁ፡አገናቸዋለሁ፡አለ፡
በቁሙ ፤ አንድም ፡ ሕዝቡ ፡ አሕዛቡ ፡
እንዲያከብሯቸው፡አደርጋለሁ፤

ወአረውያ፡ለነፍሶሙ፡ለካህናት፡ለደቂቀ፡
ሌዊ፡
ለና ፡ ለ ፡ የተደራረበ ፡ ቀለም ፡ ነው ፤
ለአብ ፡ ለዘይኄንን ፡ ለመርዓት ፡
ለብእሲተ ፡ በግዕ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡
ነው ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ የሚሆኑ ፡ የካህ
ናቱን ፡ ሰውነትም ፡ ረድዔቱን ፡ አረካ
ታለሁ፤

ወይጸግቡ፡ሕዝብየ፡እምበረከትየ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤልም ፡ በሰባው ፡
ዘመን፡ከበረከቴ፡ይጠግባሉ፡አለ፡እግ
ዚአብሔር፤በእም፡ተናገረው፤አንድ፡
ሰው፡ብቻ፡ተቀብሎት፡አይቀርም፤
እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡
ሲቀበለው፡ይኖራልና፤

ጉባዔ፤

፲፭፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ቃል፡ተሰምዓ፡በራማ፡
በራማ፡ቃል፡ተሰማ፤ ራማ፡በቁሙ፡
ሰማይ፡ነው፤አንድም፡ከፍ፡ያለ፡ቦታ፡
ነው ፤ አንድም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡
ሲል፡ነው፤አንድም፡በልዑላኑ፡ዘንድ
ተሰማ፤ ቀድሞ ፡ ትሑታኑ ፡ ሲያዝኑ ፡
ሲጨነቁ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ልዑላኑ ፡ ያረጋ
ጉዋቸው ፡ ነበርና ፡ ያንጊዜ ፡ ግን ፡
ሁሉም፡አንድ፡ሁነው፡አልቅሰዋል፤
አዝነዋልና፡እንዲህ፡አለ፤ አንድም፡
በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ሲል፡ነው፤

ብካይ፡
ልጆቻቸውን ፡ ከእናቶቻቸው ፡ ሲለዩ
ዋቸው፤

ወላህ፡
እናቶቻቸውን ፡ ከልጆቻቸው ፡ ሲለዩ
ዋቸው፤

ወገዓር፡
ልጆቹን ፡ ጠምዝዘው ፡ ሲያርዱዋ
ቸው፤አንድም፡ብካይ፡አይለወጥም፤
ልጆቻቸውን፡ከእናቶቻቸው፡ሲለዩ
ዋቸው፡ወላህ፡እናቶቻቸውን፡ከልጆ
ቻቸው፡ሲለዩዋቸው፡ላህ፡ባለው፡
ሰቆቃው፡ይላል፤እንደዚሁ፡ያስተረ

www.ethiopianorthodox.org

ጉማል፤አንድም፡ብካይ፡የወል፡ነው፤
ወላህ ፡ ልጆችን ፡ ከእናቶቻቸው ፡
ለይተው፡ሲወስዷቸው፡ወሰቆቃው፡
እናትን፡አባትን፡ከልጆቻቸው፡ሲለዩ
ዋቸው፡ወገዓር፡ልጆችን፡ጠምዝዘው፡
ሲያርዷቸው፤

ወሕማም፡ብዙኅ፡ያላል፡
ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ካምስት ፡ ቀን ፡ የፀነሰ ፡
ማኅፀን፡አይችልምና፤

ራኄል፡እንዘ፡ትበክዮሙ፡ለደቂቃ፡
ይህ፡ሁሉ፡መደረጉ፡ራኄል፡ለልጆቿ፡
ስታዝን ፡ ስታለቅስላቸው ፡ ነው ፤
አንድም፡ራሄል፡ለልጆቿ፡ስታዝን፡
ስታለቅስ ፡ ቃል ፡ ተሰምዓ ፡ በራማ ፡
አለ፤

ወዐበየት ፡ ተናዝዞ ፡ ወነጊፈ ፡ ላህ ፡ ላዕለ ፡
ደቂቃ፡
ለልጆቿ ፡ ስታለቅስ ፡ መረጋጋትን ፡
እምቢ፡አለች፤ግፉ፡ያሳዝናልና፡የፃር፡
(የጣር) ሞት ፡ ነውና ፡ ሀዘን ፡ በየደጁ ፡
ሁኗልና፤

እስመ፡ኢሀለዉ፡
ልጆቿ ፡ ከሱዋ ፡ ጋራ ፡ የሉምና ፤
አንድም፡በሕይወት፡ሥጋ፡የሉምና፤
እስመ ፡ ኢሀለዉ ፡ ባለው ፡ እስመ ፡
ኢኮንዋ ፡ ውሉዳ ፡ ውሉደ ፡ ይላል ፤
ልጆቿ፡ልጆች፡አልሆኑዋትምና፡አለ፤
ልጆቿን ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ፡ አጥታ
ለችና፤

፲፮፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ክልዒ፡ቃለኪ፡እምብካይ፡
ቃልሽን፡ከለቅሶ፡ከልክዪ፤

ወአዕይንተኪ፡እምአንብዕ፡
ዓይኖችሽንም፡ከእንባ፡ከልክዪ፤

እስመ፡ቦ፡ዕሤት፡ለምግባርኪ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ ለዔዋዌሽ ፡ ሚጠት፡
አለው፡ብሏልና፤

ወይሠወጡ፡እምድረ፡ፀር፡
ከጠላት፡አገር፡ይመለሳሉ፤

፲፯፤ ወቦ፡ተስፋ፡ለደኃሪትኪ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡
ለሚጠትሽ፡ብዕለ፡አሕዛብ፡አለው፡
አለ፡እግዚአብሔር፤

ወይትመየጡ፡ደቂቅ፡ውስተ፡ደወሎሙ፤
ልጆች፡ወደ፡ሀገራቸው፡ወደ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ይመለሳሉ፤አንድም፡ቃል፡
በራማ፡ብለህ፡መልስ፤በሄሮድስ፡
ጊዜ፡ያለቁ፡ሕፃናት፡በዚያ፡ነውና፡
እንዲህ፡አለ፤ብካይ፡ወላህ፡አይለ
ወጥም፡ከመዝ፡እንደ፡አለፈው፡በል፤
እስመ፡ቦ፡ዕሤት፡ለሰማዕትነትሽ፡
ዋጋ፡አለውና፤ወይሠወጡ፡ከሲኦል፡
ከገሃነም፡ይመለሳሉ፤ወቦ፡ተስፋ፡
ለሞትሽ፡ትንሣኤ፡አለው፡አለ፡እግዚ
አብሔር፤ወይትመየጡ፡ወደ፡ገነት፡
ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
ይመለሳሉ፤

፲፰፤ ሰማዕኩ፡ሰሚዓ፡
ነገር፡ሰማሁ፤

ኤፍሬም፡እንዘ፡ይግዕር፡
ኤፍሬም፡ሲያጣጥር፡ሲግር፡ሰማሁ፤

ገሠፅከኒ፡ወተገሠፅኩ፤
በመከራው ፡ ገሠፅከኝ ፡ እኔም ፡
በመከራው፡ተገሠፅኩ፤

ከመ፡ላሕም፡ዘኢተምህረ፡
ቀንበር ፡ መሸከምን ፡ እንዳልተማረ፡



(እንዳልተማረ) ፡ ወይፈን ፡ ያ ፡ እንዲያ
ጣጥር፡ ያጣጥራልና ፡ አንድም ፡
ዘተምህረ፡ቢል፡ቀንበር፡መሸከምን፡
ተምሮ ፡ እንደ ፡ ገደፈ ፡ (እንደ ረሣ) ፡
በሬ፡ያ፡እንዲያጣጥር፡ያጣጥራልና፡

ወይብል፡ሚጠኒ፡
ወደ፡ሀገሬ፡መልሰኝ፡ይላል፤

ወእትመየጥ፡
እኔም፡ወደ፡ሀገሬ፡ልመለስ፤

እስመ፡አንተ፡እግዚእ፡አምላኪየ፡
አቤቱ፡ፈጣሪዬ፡አንተ፡ነህና፤

፲፱፤ እምድኅረ፡ተመየጥኩ፡ተፈሣሕኩ፡
ከአምልኮተ፡ጣዖት፡ወደ፡አምልኮተ፡
እግዚአብሔር ፡ በተመለስሁ ፡ ጊዜ ፡
ተስፋ ፡ ሚጠትን ፡ ከሰማሁ ፡ በኋላ ፡
ደስ፡አለኝ፤

ወእምድኅረ፡አእመርኩ፡ጠፋሕኩ፡እደውየ፡
ሚጠትን ፡ ከአወቅሁ ፡ በኋላ ፡ እጄን ፡
አጨበጨብሁ፡ማለት፡ደስ፡አለኝ፤

ወኀፈርኩ፡
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡
መከራ፡አፈርኩ፤

ወእትኃፈር፡
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ በመከራው ፡
አፍራለሁ፤

እስመ፡ነሣዕኩ፡ዕዕለተ፡ንዕስየ፤
የሕፃንነቴን፡ስድብ፡ተቀብያለሁና፤

፳፤ ወልድ፡ዘአፈቅር፡ኤፍሬም፡ሊተ፡
እኔስ ፡ ኤፍሬም ፡ የምወደው ፡ ልጅ ፡
ነበር፤ከመ፡ሕፃን፡ልሕድ፡እየተናገ
ርሁት ፡ እንደ ፡ ድልድል ፡ እንደ ፡
ቅምጥል ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፤ አንድም ፡
እመ፡ ሕፃን ፡ ቢል ፡ እየተናገርሁት ፡
ድልድል፡ቅምጥል፡ልጅ፡ቢሆን፡

ለእለ፡ተናገርክዎ፡ተዘክሮ፡እዜክሮ፡
በዔዋዌ፡አስበዋለሁ፤

በእንተዝ፡ተሐውክ፡አማዑትየ፡ሎቱ፡
ወልድ ፡ ዘአፈቅር ፡ ኤፍሬም፡ ሊተ ፡
ውእቱ፡ብሎ፡ነበርና፡ስለዚህ፡ነገር፡
ልቡናዬ፡ታወከ፤

ተሣህሎ፡እሠሃሎ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ይቅር፡እለዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፩፤ አቅሚ፡ለኪ፡አዕዋናተኪ፡
አምባዎችሽን፡አጽኚ፤

ወግበሪ፡ለኪ፡ትእምርታተ፡
ሰንደቅ፡ዓላማውን፡ትከዪ፤

ደዪ፡ውስተ፡ልብኪ፡መዕያሕተ፡ፍኖት፡
ወደ ፡ ሀገርሽ ፡ ትመለሺ ፡ ዘንድ ፡
በልቡናሽ ፡ የቀና ፡ ሕግን ፡ ያዥ ፡
አሳድሪ፡ብትልም፤

ተሠወጢ ፡ ውስተ ፡ ሀገርኪ ፡ ድንግለ ፡
እስራኤል፡
የእስራኤል ፡ ቆንጆ ፡ ወደ ፡ ሀገርሽ ፡
ተመለሺ፤

፳፪፤ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ትላህዊ ፡ ወለት ፡
ዕሉት፤
አንቺ፡ወንጀለኛ፡ልጅ፡እስከ፡መቼ፡
ድረስ፡ታለቅሻለሽ፤

እስመ፡እግዚአብሔር፡ገብረ፡ሐዲስ፡ውስተ
ምድር፤
እግዚአብሔር፡በምድር፡ዔዋዌን፡አድ
ርጓልና፡ታገሺ፡እንጂ፡እስከ፡መቼ፡
ድረስ፡ታለቅሻለሽ፤አንድም፡እግዚአ
ብሔር፡ሚጠትን፡አድርጓልና፤

ወይመጽእ፡ሰብእ፡ውስተ፡መድኃኒት፡
ሰው፡ድኅነት፡ወደሚደረግባት፡ወደ፡
ኢየሩሳሌም፡ይመጣል፤

፳፫፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
ፀባዖት፡አምላከ፡እሥራኤል፡

www.ethiopianorthodox.org

የእሥራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ዓዲ ፡ ይብሉ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ በይሁዳ ፡ ወበአህ
ጉሪሁ፤

ዳግመኛ ፡ በይሁዳና ፡ በአውራጃዎቹ ፡
ይናገራሉ ፤ አመ ፡ ሚጥኩ ፡ ፄዋሆሙ ፤
ምርኮዋቸውን፡በመለስሁ፡ጊዜ፤

ይትባረክ፡እግዚአብሔር፡ማኅደረ፡ጽድቅ፡
ደብረ፡መቅደስከ፤

የክብራችን ፡ ማደሪያ ፡ የምስጋናህ ፡
መገኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡
ይመስገን፤

፳፬፤ ወእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡
ይሁዳ ፡ ወኵሉ ፡ አህጉሪሁ ፡ ኅቡረ ፡ ኀረሳ
ውያን፤

በይሁዳ ፡ አውራጃዎችና ፡ በሀገሩ ፡
ሁሉ፡አንድነት፡የሚኖሩ፡አራሾች፤

ያነሥኡ፡መራዕየ፤

መንጋቸውን፡ይጠብቃሉ፤

፳፭፤ እስመ ፡ አርወይኩ ፡ ኵላ ፡ ነፍሰ ፡
ጽምዐተ፤

የተጠማችውን፡ሰውነት፡መጠጡን፡
አጠጥቻታለሁና ፡ ማለት ፡ ትምህ
ርቱን፡ረድኤቱን፡አጥግቤያታለሁና፤

ወአጽገብኩ፡ኵላ፡ነፍሰ፡ርህብተ፤

የተራበችውንም ፡ ሰውነት ፡ ረድዔ
ቱን፡አጥግቤያለሁና፤

፳፮፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ነቃሕኩ፤

እሥራኤል ፡ የሚማረኩ ፡ ስለሆነ ፡
ተኝቼ፡ተነሣሁ፤

ወርኢኩ፤

ፄዋዌን፡አየሁ፤

ወጥዕመኒ፡ንዋምየ፤

ዕንቅልፌ ፡ ደስ ፡ አሰኘኝ ፡ ማለት ፡
ባልተኛ ፡ ፄዋዌን ፡ መቼ ፡ አይ ፡ ነበር ፤
አንድም፡በእንተ፡ዝንቱ፡ነቃሕኩ፤
እሥራኤል ፡ የሚመለሱ ፡ ስለሆነ ፡
ወርኢኩ ፡ ሚጠትን ፡ አየሁ ፤
ወነቃሕኩ ፤ አይቼ ፡ ተነሣሁ ፤
ወጥዕመኒ፡ንዋምየ፤ዕንቅልፌ፡ደስ፡
አሰኘኝ፡ማለት፡ባልተኛ፡ሚጠትን፡
መች፡አይ፡ነበር፤አንድም፡በእንተ፡
ዝንቱ፡ርኢኩ፤ምዕመናን፡የሚድኑ፡
ስለሆኑ፡ድኅነተ፡ምዕመናንን፡አየሁ፤
ወነቃህኩ፡ሦስት፡መዓልት፡ሦስት፡
ሌሊት፡በከርሠ፡መቃብር፡አድሬ፡
ተነሣሁ፤ወጥዕመኒ፡ንዋምየ፤ሞቴ፡
ደስ፡አሰኘኝ፡አለ፤ባልሞት፡መቼ፡
ድኅነተ፡ምዕመናንን፡አይ፡ነበረ፤

፳፯፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ መዋዕል ፡
ይመጽእ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እነሆ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ወራት ፡ ይመጣል ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

ወእዘርአሙ፡ለቤተ፡እሥራኤል፡ወለቤተ፡
ይሁዳ፡ዘርዐ፡ዕጓለ፡እመሕያው፤

ዐሥሩን ፡ ነገድ ፤ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡
የሰው፡ዘር፡አደርጋቸዋለሁ፤

ወዘርዓ፡እንስሳ፤

የእንስሳትንም፡ዘር፡አበዛለሁ፤

፳፰፤ በከመ ፡ ተጋህኩ ፡ በእንቲአሆሙ ፡
ከመ፡እንሥቶሙ፤

አጠፋቸው፤

ወአሕምሞሙ፤

መከራም፡አጸናባቸው፡ዘንድ፤

ከማሁ፡እተግህ፤

በነሱ፡እንደተጋሁ፤

ከመ፡እሕንፆሙ፡ወእትክሎሙ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፤



በረድዔት ፡ አንፃቸው ፡ አጸናቸው ፡
ዘንድ፡እንደዚህም፡ሁሉ፡እተጋለሁ፡
አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፱፤ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ኢይብሉ ፡ እንከ ፡
አበው፡በልዑ፡ቆዐ፤

ያን፡ጊዜ፡እንግዲህ፡ወዲህ፡አባቶች፡
ጨርቋ፡በሉ፡አይሉም፤

ወደቂቅ፡ፀርሱ፡ስነኒሆሙ፤

ውሉድ፡(ልጆች)፡ተወላመሙ፡ጥርሳ
ቸውን ፡ አጠረሳቸው ፡ አይሉም ፤
አንድም ፡ አበው ፡ በልዑ ፤ አበው ፡
ኃጢአት ፡ ሠሩ ፤ ወደቂቅ ፡ ውሉድ ፡
በፍዳ ፡ ተያዙ ፡ አይሉም ፤ አንድም ፡
በአበው ፡ ኃጢአት ፡ ውሉድ ፡ በፍዳ ፡
ተያዙ፡አይሉም፤

፴፤ ዳዕሙ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ይመውት፡
በኃጢአቱ፤

አንዱም ፡ አንዱ ፡ በኃጢአቱ ፡
ይሞታል፡እንጂ፤

ወዘሂ፡በልዐ፡ቆዐ፡ለሊሁ፡ይፀርስ፡ስነኒሁ፤

ጨርቋ ፡ የበላ ፡ እሱ ፡ ይወላመማል ፤
ጥርሱን ፡ ያጠርሰዋል ፡ ማለት ፡
ኃጢአት፡የሠራ፡በሠራው፡ኃጢአት፡
በፍዳ፡ይያዛል፤

፴፩፤ ናሁ፡መዋዕል፡ይመጽእ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፤

እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፡
አለ፡እግዚአብሔር፤

ወእሠርዕ ፡ ለቤተ ፡ እሥራኤል ፡ ወለቤተ ፡
ይሁዳ፡ሥርዓተ፡ሐዲሰ፤

ለአሥሩ፡ነገድ፡ለሁለቱ፡ነገድ፡ሕገ፡
ኦሪትን፡እሠራለሁ፤

፴፪፤ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡
ዘሠራዕኩ፡ለአበዊሆሙ፤

ይህም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እንደሠራሁ
ላቸው፡ሕግ፡አይደለም፤ሕጉስ፡ሕጉ፡
ነው፤የቀደመው፡እንደፈረሰ፡አይፈ
ርስም፡ሲል፡ነው፤

አመ፡አኀዝኩ፡በእደዊሆሙ፤

የደከመን፡ሰው፡ከክፉ፡ቦታ፡አይዞህ፡
አይዞህ፡እያሉ፡እጁን፡ይዘው፡እንዲያ
ወጡት ፤ አንድም ፡ እመ ፡ አኀዝኩ ፡
ይላል ፤ ፲ቱ ፡ ቃላትን፡ ጽፋችሁ ፡
በእጃችሁ ፡ ብትይዙ ፡ ከአባር ፡
ከቸነፈር፡ይጠብቃችኋል፡ብለዋቸው፡
ጽፈው፡በእጃቸው፡ይዘው፡ኑረዋልና፤

ወአውጻእክዎሙ፡እምድረ፡ግብፅ፤

ከግብፅ፡አወጣኋቸው፤

እስመ፡እሙንቱሂ፡ኢነበሩ፡በኪዳንየ፤

እነሱ ፡ በቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ጸንተው ፡
አልኖሩም፡ነበርና፤ምንም፡ባይኖሩ፡
ከግብፅ፡አወጣኋቸው፤

ወአነሂ ፡ ተሀየይክዎሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

እኔም፡ቸል፡አልኳቸው፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤

፴፫፤ ወከመዝ፡ይእቲ፡ሥርዓት፡እንተ፡
እሠርዕ፡ለቤተ፡እስራኤል፤

ለእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ የምሠራት ፡
ሥርዓት፡እንዲህ፡ናት፤

እምድኅረ፡እማንቱ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፤

ከሰባ፡ዘመን፡በኋላ፡እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፤

እወዲ፡ሕግየ፡ውስተ፡ልቦሙ፤

ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ በልቡናቸው ፡ አሳድ
ራለሁ፡አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእጽሕፎ፡ውስተ፡ሕሊናሆሙ፡

በልቡናቸው፡ሡሌዳነት፡እጽፈዋለሁ፤

ወእሬስዮሙ፡እንከ፡

እንዲደኑ፡አደርጋቸዋለሁ፤

ወእከውኖሙ፡አምላኮሙ፡

የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ አባት ፡ እሆናቸ ዋለሁ፤

ወእሙንቱኒ፡ይከውኑኒ፡ሕዝብየ፡

እነሱም፡የፍቅር፡የሃይማኖት፡ልጆቼ፡ ይሆኑኛል ፤ አንድም ፡ ወእሠርዕ ፡ ለቤተ፡ እስራኤል፡ ለእስራኤል ፡ ዘነፍስ፡ ለይሁዳ ፡ ዘነፍስ ፤ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ እሠራለሁ ፤ አሁን ፡ የተመቸ፡ወአኮ፡ሕገ፡ወንጌል፡ለአባቶ ቻቸው፡እንደ፡ሠራሁላቸው፡እንደ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ አይደለም ፤ አመ ፡ አኃዝኩ፡እንዳለፈው፡በል፤ወአውጻእ ክዎሙ ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም ፡ አወጣ ኋቸው ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ እነሱ ፡ በሕጊ፡ዐንተው፡አልኖሩም፡ነበርና፤ ምንም ፡ ባይኖሩ ፡ አወጣኋቸው፤ ወአነሂ ፡ እኔም፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን፡ቸል፡አልኋቸው፡አለ፡እግዚአ ብሔር ፤ ወከመዝ ፡ ለእስራኤል ፡ ዘነፍስ፡ለይሁዳ፡ዘነፍስ፡የምሠራት፡ ሕገ፡ወንጌል፡እንዲህ፡ናት፤እምድ ኅረ ፡ እማንቱ ፡ ከአምስት፡ ሺህ ፡ ከአምስት፡መቶ፡ዘመን፡በኋላ፡እግዚ አብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

እወዲ፡ሕገ፡ወንጌልን፡በ[illegible]ናቸው፡ አሳድራለሁ ፤ ወእጽሕፎ ፡ በልቡ ናቸው፡ሡሌዳነት፡እጽፈዋለሁ፤ወእ ሬስዮሙ ፡ ከሲኦል ፡ ከገሃነም፡ እንዲደኑ ፡ አደርጋቸዋለሁ፡ ወእከ ውኖሙ፡እንደ፡አለፈው፤

፴፬፡ ወኢ[illegible]፡ዘይሜህር፡እንከ፡አሐዱ፡ አሐዱ፡እኁሁ፡

አንዱም፡አንዱ፡ወንድሙን፡የሚያስ ተምር፡የለም፤

ወአሐዱ፡አሐዱ፡ቢጾ፡

አንዱም፡አንዱ፡ባልንጀራውን፡የሚ ያስተምር፡የለም፤የአእምሮዋቸውን፡ ስፋት፡ብዛት፡መናገር፡ነው፤

ወይቤሎ፡አእምሮ፡ለእግዚአብሔር፡

እግዚአብሔርን፡በሕግ፡በአምልኮት፡ እወቀው፡የሚለው፡የለም፤

እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ የአምሩኒ ፡ ንዑሶሙ ፡ ወዓቢዮሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር ፡ ሁሉም ፡ ታናሹም፡ ታላቁም ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ያውቁኛል፡ብሏልና፡

እስመ፡እሠሪ፡ሎሙ፡ኃጢአቶሙ፡

ኃጢአታቸውን፡የማስተሠርይላቸው፡ ስለሆነ፤

ወኢይዜከር፡እንከ፡ሎሙ፡አበሳሆሙ፡

እንግዲህ፡ወዲህ፡በደላቸውን፡አላስብ ባቸውም ፤ ሠርተውት ፡ አላስብባ ቸውም ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ ጥን ቱንም፡አይሠሩትም፡ሲል፡ነው፤

፴፭፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤



ዘወሀበ፡ፀሐየ፡ያብርህ፡መዓልተ፡

በመዓልት ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ ፀሐይን ፡ የሰጠ፤

ወወርኃ፡ወከዋክብተ፡ያብርሁ፡ሌሊተ፡

በሌሊት፡ያበሩ፡ዘንድ፡ጨረቃን፡ከዋ ክብትን፡የሠጠ፤

ዘያረምማ፡ለባሕር፡

ውቅያኖስን ፡ ፀጥ ፡ የሚያደርጋት፤ እንድም፡ባቢሎንን፡የሚያጠፋት፤

ወለድምፀ፡ማዕበላ፡

የውቅያኖስን ፡ የማዕበሏን ፡ ድምፅ ፡ ፀጥ፡ የሚያደርገው ፤ አንድም ፡ የባቢ ሎንን፡ጦር፡የሚያጠፋው፤

እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ስሙ፡

የእግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ፡ነው፤

፴፮፡ ወገዘኒ ፡ ኵሉ ፡ ለእመ ፡ ሐደገ ፡ ሥርዓቶሙ፡እምቅድመ፡ገጽየ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፡

እግዚአብሔር፡እነዚህ፡ሁሉ፡በፊቴ፡ ሥርዓታቸውን፡ቢተዉ፡አለ፤ፀሐይ፡ በመዓልት ፡ ጨረቃ፡ ከዋክብት ፡ በሌሊት፡ማብራታቸውን፡ቢተዉ፤

ዘርዓ፡እስራኤልኒ፡ይትሐደግ፡እምከዊነ፡ ሕዝብየ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽየ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል፡

የእስራኤልም፡ልጆች፡ባለ፡በዘመኑ፡ ሁሉ፡በፊቴ፡የእኔ፡ወገኖች፡ከመሆን፡ ይታጣሉ፡አለ፤እነዚያም፡አይተዉ፤ እሥራኤልም፡የኔ፡ወገኖች፡ከመሆን፡ አይታጡም፡ሲል፡ነው፤

፴፯፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ሶበ፡ጥቀ፡ይትሌዓል፡ሰማይ፡ወይትዓተት፡

ሰማይ ፡ ያለበትን ፡ ትቶ ፡ እጅግ ፡ ፈጽሞ፡ወደ፡ላይ፡ብቅ፡ቢል፤

ይቤ፡እግዚአብሔር፡

እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ምድርኒ፡ይወርድ፡ወይቴሐት፡

ምድርም፡ወደ፡ታች፡ዝቅ፡ቢል፤

ወአነሂ ፡ እሜንኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ዘርዓ፡ እስራኤል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ፡ ኵሉ፡ምግባሮሙ፡

እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው፡ የእስራኤልን፡ወገኖች፡ሁሉ፡እንቃቸ ዋለሁን፡አለ፤ያም፡አይል፡እኔም፡አል ንቃቸው፡ሲል፡ነው፤

፴፰፡ ናሁ፡መዋዕል፡ይመጽእ፡ይቤ፡እግ ዚአብሔር፡

እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወራት፡ይመጣል፡አለ፤

ወትትሐነፅ ፡ ሀገር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እማሕፈደ ፡ አናምሔል ፡ እስከ ፡ ኆኅተ ፡ ማዕዘንት፡

አናምሔል ፡ ከሚጠብቀው ፡ ግንብ ፡ ጀምሮ ፡ ማዕዘን ፡ እስከ ፡ አለው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ሀገሪቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ፡ሁና፡ትቀናለች፤

፴፱፡ ወይበጽሕ፡አምጣኒሃ፡እስከ፡ወግረ፡ ጋሬብ፡

አውራጃዋ ፡ (ወሰኗ) ፡ እስከ ፡ ጋሬብ ፡ ኰረብታ፡ይደርሳል፤ወኵሉ፡ቈላት፤ ቈላው፡ሁሉ፡ይቀናል፤ወኵሉ፡በአስ ሪሞት፡ደጋው፡ይቀናል፤አንድም፡ ወኵሉ፡ቈላት፡በአስሪሞት፡ይላል፤ ቈላው ፡ በአራት ፡ ኅብር ፡ ይሠራል፤ አንድም፡በማዕዘን፡ይሠራል፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፤ እስከ፡ፈለገ፡ቄድሮስ፤
ዋንዛ፡ዝግባ፡እስከ፡አለበት፡ወንዝ፡
ድረስ፡ይቀናል፤
ወእስከ ፡ ማዕዘንተ ፡ ዴዴ ፡ አፍራስ ፡
እምጽባሕ፤
ከምሥራቅ፡ጀምሮ፡ፈረስ፡እስከሚሞ
ክሩበት፡(እስከሚገሩበት)፡በር፡ሜዳ፡
ድረስ፡ይቀናል፤
ይከውን፡ቅዱሰ፡ለእግዚአብሔር፤
ይኸውም፡ለእግዚአብሔር፡የተለየ፡
የከበረ፡ቦታ፡ይሆናል፤
ወኢየሐልቅ፡እንከ፡ወኢይትነሰት፡እንከ፡
ለዓለም፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለዘለዓለሙ ፡
አይጠፋም።

## ምዕራፍ፡፴፪፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ወደ፡ነቢዩ፡ወደ፡ኤርምያስ፡የመጣ፡
የተነገረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡
ነው፤
በዐሠርቱ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለሴዴቅያስ፡
ንጉሠ፡ይሁዳ፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡
በነገሠ፡በዐሥረኛው፡ዓመት፤
ወበ፲ቱ፡ወሰመንቱ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለና
ቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
በነገሠ ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡
ዓመት ፡ የመጣ ፤ የተነገረ ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤
፪፤ አሜሃ ፡ ሠራዊተ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡
ዐገትዋ፡ለኢየሩሳሌም፤
ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ላለው፡
ሳያመጣ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አገባበት፡
ያንጊዜ፡የባቢሎን፡ንጉሥ፡ሠራዊት፡
ኢየሩሳሌምን፡ ከበቧት ፤ አንድም፡
ከበቧትገትች፤
ወየአቅብዎ ፡ ለኤርምያስ ፡ በዐፀደ ፡ ሞቅሕ፡
ዘቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
በይሁዳው፡ንጉሥ፡ቤት፡ባለ፡ግዞት፡
ቤት፡ኤርምያስን፡ይጠብቁት፡ነበር፤
፫፤ ዘአዕቀቦ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
ወይቤሎ፡ለምንት፡ተነበይከ፡አንተ፡እንዘ፡
ትብል፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ናሁ፡
አነ፡አገብአ፡ለዛቲ፡ሀገር፡ውስተ፡እደ፡
ንጉሠ፡ባቢሎን፤
እግዚአብሔር፡እነሆ፡እኔ፡በናቡከደ
ነፆር ፡ እጅ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እጥ
ታለሁ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ለምን ፡ ተና
ርከ፡ብሎ፡ኤርምያስን፡አሥሮ፡ያስጠ
በቀው፡የይሁዳው፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ
ነው፤
ወይነሥእ፤
እጅ ፡ ያደርጋታል ፡ ብለህ ፡ ለምን
ትንቢት፡ተናገርከ፡ብሎ፤
፬፤ ወሴዴቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ
ኢይድኅን፡እምእዴሆሙ፡ለከለዳውያን፤
የይሁዳው፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፡ከከለዳ
ውያን፡እጅ፡አይድንም፤
እስመ ፡ ገቢአ ፡ ይገብእ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ
ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ይያዛልና፡
ወይትናገሮ፡አፈ፡በአፍ፤
ቃል፡ለቃል፡ይናገረዋልና፤
ወይሬእዮ፡ዐይነ፡በዐይን፤
ዐይን ፡ ለዐይን ፡ ያየዋልና ፡ ብለህ



ለምን፡ትንቢት፡ተናገርህ፡ብሎ፡ያስ
ጠበቀው፡ሴዴቅያስ፡ነው፤
፭፤ ወይበውእ፡ሴዴቅያስ፡ባቢሎን፡
ሴዴቅያስ፡ተማርኮ፡ወደ፡ባቢሎን፡
ይገባል፤
ወይነብር፡ሀየ፡እስከ፡አመ፡እፄሀዮ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፤
በሞት፡እስክጐበኘው፡ድረስ፡በዚያ፡
ይኖራል፡አለ፡እግዚአብሔር፤
ለእመ ፡ ትትቃተሉ ፡ ምስለ ፡ ከለዳውያን ፡
ኢትሤርሑ፤
ከከለዳውያን፡ጋራ፡ብትዋጉ፡ድል፡
አትነሡም፡አለ፤
፮፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤
በመካከሉ ፡ ሌላ ፡ አገባበት ፡ ባለው ፡
አማርኛ፡ያሉ፡እንደሆነ፡ይህ፡ዋዌ፡
ነው፤ትች፡ያሉ፡እንደሆነ፡ቃለ፡እግዚ
አብሔር፡ዘኮነ፡ያለውና፡ይህ፡ወኮነ፡
አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡ መጣ ፤
ተነገረ፤
ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤
፯፤ ናሁ ፡ አናምኤል ፡ ወልደ ፡ ሴሎም ፡
እኁሁ፡ለአቡከ፤
እነሆ፡የአባትህ፡ወንድም፡የሚሆን፡
የሴሎም፡ልጅ፡አናምኤል፤
ይመጽእ፡ኀቤከ፡ወይብለከ፤
ወደ፡አንተ፡መጥቶ፡እንዲህ፡ይልሃል፤
ተሣየጥ፡ገራህትየ፡ዘአናቶት፤
በአናቶት ፡ ያለ ፡ እርሻዬን ፡ ግዛ ፡
ይልሃል፤
እስመ፡አንተ፡ርቱዕ፡ታጥርያ፤
አንተ፡ትገዛት፡ዘንድ፡አገባብ፡ነውና፤
፰፤ ወመጽአ፡ኀቤየ፡አናምኤል፡ወልደ፡
እኁሁ፡ለአቡየ፡በቃለ፡እግዚአብሔር፡
የአባቴ፡የወንድም፡ልጅ፡አናምኤል፡
በእግዚአብሔር፡ትእዛዝ፡ወደ፡እኔ፡
መጣ፤
ኀበ፡ዓፀደ፡ሞቅሕ፤
እኔ ፡ ወደ ፡ አለሁበት ፡ ወደ ፡ ግዞት፡
ቤት፡መጣ፤
ወይቤለኒ ፡ ተሣየጥ ፡ ገራህተ ፡ በምድረ ፡
ብንያም፡ዘምድረ፡አናቶት፡
በአናቶት ፡ ዕፃ ፡ ባለ ፡ በብንያም ፡
ምድር፡ያለ፡እርሻን፡ግዛ፡አለኝ፤
እስመ፡አንተ፡ርቱዕ፡ታጥርያ፡
አንተ ፡ ትገዛት ፡ ዘንድ ፡ አገባብህ፡
ነውና፤
ወአንተ፡ትረሳ፡
አንተ ፡ ትወርሣት ፡ ዘንድ ፡ አገባብ ፡
ነውና፤
ወአእመርኩ፡ከመ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደሆነ ፡
አውቅሁ፤
፱፤ ወተሣየጥኩ፡ውእተ፡ገራህተ፡እምአ
ናምኤል፡ወልደ፡እኁሁ፡ለአቡየ፡ዘአናቶት፡
በአናቶት ፡ ያለ ፡ ያባቴ ፡ የወንድም፡
ልጅ ፡ ከሚሆን ፡ ከአናምኤል ፡ ያንን ፡
እርሻ፡ገዛሁ፤
ወወሀብክዎ፡፲ተ፡ወ፯ተ፡ጠፋልሐ፡ሰቅለ፡
ብሩር፡
አሥራ ፡ ሰባት ፡ ምዝምዝ ፡ ብር ፡
ሰጠሁት ፤ አሠርተ ፡ ወኀምስተም ፡
ይላል፤
፲፤ ወጸሐፍኩ፡መጽሐፈ፡ወሐተምክዋ፤
መጽሐፍ፡ጽፌ፡አተምኩባት፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአኪድኩ፡ሰማዕተ፡
መሳክርቱን ፤ ዳር ፡ ድንበሩን ፡ አስረ
ገጥሁ ፤ አንድም ፡ ወአፆድኩ፡ ይላል ፤
መሳክርቱን፡አዙሬ፡አሳየሁ፤

ወደለውኩ፡ሎቱ፡ብሩር፡በመዳልው፡
ብሩን፡በሚዛን፡መዘንኩ፤

፲፩፤ ወተመጠውኩ ፡ መጽሐፈ ፡
ማኅተትየ፡ኅቱመ፡
የታጠፈ፡መሣክርቶቼ፡የተጻፉበትን፡
መጽሐፍ፡ተቀበልኩ፤

፲፪፤ ወወሀብክዎ፡መጽሐፈ፡ማኅተትየ፡
ለባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፡ወልደ፡ማሴው፡
መሣክርቱ ፡ የተጻፉበትን ፡ መጽሐፍ፡
የማሴው ፡ ልጅ ፡ ለሚሆን ፡ ለኔርዩ ፡
ልጅ፡ለባሮክ፡ሰጠሁት፤

በቅድመ ፡ አናምኤል ፡ ወልደ ፡ እኁሁ ፡
ለአቡየ፡
የአባቴ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ በሚሆን ፡
በአናምኤል፡ፊት፤

ወበቅድመ፡ሰማዕት፡እለ፡ቆሙ፡ወዐለሙ፡
ውስተ፡ይእቲ፡መጽሐፈ፡ማኅተትየ፤
መሣክርቶቼን ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ፡
በጻፉ፡ሰዎች፡ፊት ፤ አንድም፡ወእለ፡
ተዓለሙ፡እንደ፡ማለት፡መሣክርቱ፡
በተጻፉበት፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡
በተጻፉ፡ሰዎች፡ፊት፤

ወበቅድመ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡
ውስተ፡ዓፀደ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡
በግዞት ፡ ቤት ፡ በሚቆሙ ፡ በአይ
ሁድም፡ፊት፡ሰጠሁት፤

፲፫፤ ወአዘዝክዎ፡ለባሮክ፡
ባሮክን፡አዘዝሁት፤

ወእቤሎ፡በቅድሜሆሙ፡

በፊታቸው፡እንዲህ፡አልሁት፤

፲፬፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፣
ዘይነግሥ፡ለኵሉ፡አምላከ፡እስራኤል፤
ለዓለሙ፡ሁሉ፡ነግሦ፡የሚኖር፡የእስ
ራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤

ንሣዕ፡ዘ፡መጽሐፈ፡ማኅተት፡ዘኅቱም፤
የታጠፈውን ፡ መሣክርቱ ፡ የተጻፉ
በትን፡ይህን፡መጽሐፍ፡ወስደህ፤

ወአንብሮ፡ወደዮ፡ውስተ፡ንዋየ፡ልሕኵት፤
በሸክላ፡ዕቃ፡ውስጥ፡አኑረው፤

ይንበር፡ብዙኃ፡መዋዕለ፡
ብዙ፡ዘመን፡ይኖር፡ዘንድ፤

፲፭፤ እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ዓዲ፡ታጠርዩ፡በገ፡ብሔር፡አብያተ፡
ዳግመኛ፡በዚህ፡ሀገር፡ቤቱን፤

ወአዕፃዳተ፡ወይን፡
የወይኑን፡ቦታ፤

ወገራውሀ፡
እርሻውን፡ትገዛላችሁ፡ብሏልና፤

፲፮፤ ወጸለይኩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር፤
እምድኅረ፡መጠውክዎ፡መጽሐፈ፡ማኅተት፤
ለባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፡
ለኔርዩ፡ልጅ፡ለባሮክ፡መሣክርት፡የተ
ጻፉበትን፡ደብዳቤ፡ከሰጠሁት፡በኋላ፤
ወደ እግዚአብሔር ፡ ጸለይኩ ፤
አንድም፡ ማኅተትየ ፡ መሣክርቶቼ፤
የተጻፉበትን፡ደብዳቤ፡ለኔርዩ፡ልጅ፤
ለባሮክ፡ከሰጠሁት፡በኋላ፡ጸለይኩ፤

፲፯፤ ወእቤ፡እግዚኦ፡እግዚአብሔር፤
አቤቱ፡ገዥ፡እግዚአብሔር፡አልሁ፤

ናሁ፡አንተ፡ፈጠርከ፡ሰማየ፡ወምድረ፤
ሰማይን፡ምድርን፡የፈጠርህ፡እነሆ፤



አንተ ፡ ነህና ፤ አንድም ፡ ሰማይን ፡
ምድርን፡የፈጠርህ፡አቤቱ፤

በኃይልከ፡ዓቢይ፡
ገናና፡በሆነ፡ኃይልህ፤

ወበመዝራዕትከ፡ልዑል፡
ልዑል፡በሆነ፡ሥልጣንህ፡ሰማይን፡
ምድርን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህና ፤
የፈጠርህ፡አቤቱ፤

ወአልቦ፡ምንትኒ፡ዘይሰዓን፡እምኔከ፡
ምንም ፡ ምን ፡ ከአንተ ፡ የሚሠወር ፡
የለምና፤የሌለ፡አቤቱ፤

፲፰፤ ወትገብር ፡ ምሕረተከ ፡ እስከ ፡
እዕላፍ፤
እስከ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ይቅር
ታህን፡ታደርጋለህና፤አንድም፡የምታ
ደርግ፡አቤቱ፤

ወትፈዲ፡ኃጢአተ፡ወላዲ፡ውስተ፡ሕዕነ፡
ውሉዶሙ፡ድኅሬሆሙ፤
መስለው ፡ ቢሠሩ ፡ የአባቶችን ፡
ኃጢአት ፡ ከእነሱ ፡ በኋላ ፡ በልጆ
ቻቸው ፡ ፍዳን ፡ ታመጣለህና ፡ የምት
ከፍል፡አቤቱ፤

አምላከ፡ዓቢየ፡ምክር፡
በምክር ፡ ዕኑዕ ፡ የምትሆን ፡ ፈጣሪ፡
ነህና ፤ አንድም ፡ በምክር ፡ ገናና ፡
የምትሆን፤

ወፅኑዓ፡ምግባር፡
በሥራ፡የፀናህ፡ነህና፡የፀናህ፡አቤቱ፤

፲፱፤ ወእግዚአብሔር፡ዘይነግሥ፡ለኵሉ፡
ለዓለሙ፡ሁሉ፡ነግሠህ፡የምትኖር፡
እግዚአብሔር፡አንተ፡ነህና፡ነግሠህ፡
የምትኖር፡አቤቱ፤

ዓቢይ፤
ገናና ፡ ነህና ፤ ገናና ፡ የምትሆን ፡
አቤቱ፤

ወጠቢብ፡
የባሕርይ፡አዋቂ፡ነህና፤
የባሕርይ፡አዋቂ፡የምትሆን፡አቤቱ፤

ወአዕይንቲከ ፡ ይሬእያ ፡ ፍናዊሁ ፡ ለዕጓለ ፡
እመሕያው፤
አይኖችህም፡የሰውን፡ሥራውን፡ይመ
ለከታሉና፤የሚመለከቱ፡አቤቱ፤

ወትፈድዮ፡ለለአሐዱ፡አሐዱ፡በከመ፡ፍኖቱ፡
ወበከመ፡ፍሬ፡ምግባሩ፤
ለአንዱም ፡ ለአንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡
እንደ፡ሥራው፡መጠን፡ዋጋውን፡ትከ
ፍለዋለህና፡የምትከፍለው፡አቤቱ፤

፳፤ ዘገበርከ ፡ ትእምርተ ፡ ወመንከረ ፡
በምድረ፡ግብፅ፡እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡ወበውስተ፡
እሥራኤልኒ፡ወበውስተ፡አሕዛብ፤
በግብፅ፡እስከዚች፡ቀን፡ድረስ፡በእሥ
ራኤልና ፡ በአሕዛብ ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡
ተአምራትን ፡ ምልክትን ፡ አድርገ
ኻልና፤ያደረግህ፡አቤቱ፤

ወገበርከ፡ለከ፡ስመ፡እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፤
እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ስምህን ፡ አስጠርተ
ሃልና፡የአስጠራህ፡አቤቱ፤

፳፩፤ ወአውጻእከ፡ሕዝበከ፡እሥራኤልሃ፡
እምድረ፡ግብፅ፤
እሥራኤልን፡ከግብፅ፡አውጥተሃልና፡
ያወጣህ፡አቤቱ፤

በተአምራት፡ወመንከራት፤
ድንቅ፡ድንቅ፡በሆነ፡ተአምራት፤

በእድ፡ጽንዕት፤
በጸናችሥልጣን፤

ወበመዝራዕት፡ልዕልት፡
ገናና፡በሆነች፡ሥልጣን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበግርማ፡ዓቢይ፤
በጽኑ ፡ መፈራት ፡ እሥራኤልን ፡ ከምድረ ፡ ግብፅ ፡ አውጥተሃልና ፡ ያወጣህ፡አቤቱ፤

፳፪፤ ወወሀብኮሙ ፡ ዛተ ፡ ምድረ ፡ ዘመሐልከ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ምድረ ፡ እንተ ፡ ታውኅዝ፡ሐሊበ፡ወመዓረ፤
ቀድሞ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እሰጣችኋለሁ፡ብለህ፡የማልክላቸው፡ተድላ፡ደስታ፡የሚደረግባት፡አገር፡ኢየሩሳሌምን፡ሰጥተሃቸዋልና፡የሰጠሃቸው፡አቤቱ፤

፳፫፤ ወቦኡ፡ወነሥእዋ፤
ገብተው ፡ እጅ ፡ አድርገዋታልና ፡ ያደረጓት፡አቤቱ፤

ወኢሰምኡ፡ቃለከ፡
ቃልህን ፡ አልሰሙምና ፡ አንድም ፡ ቃልህን፡ያልሰሙ፡አቤቱ፡

ወኢሖሩ፡በትእዛዝከ፡ወበሕግከ፡
በሕግህ፡በትእዛዝህ፡ፀንተው፡አልኖሩምና፡ፀንተው፡ያልኖሩ፡አቤቱ፡

ወኢገብሩ፡ነተሎ፡ዘአዘዝኮሙ፡
ያዘዝካቸውን ፡ ሁሉ ፡ አላደረጉምና ፡ ያዘዝኻቸውን፡ያላደረጉ፡አቤቱ፡

ወረከቦሙ፡ዝ፡ነተሉ፡እኩይ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ መከራ ፡ አግኝቷቸዋልና፡ያገኛቸው፡አቤቱ፡

፳፬፡ ወመጽኡ፡አሕዛብ፡ወነሥእዋ፡ለዛ፡ሀገር፡
አሕዛብ፡መጥተው፡ይችን፡ሀገር፡ኢየሩሳሌምን፡እጅ፡አድርገዋታልና፡እጅ፡ያደረጓት፡አቤቱ፡

ወገብዓት፡ዛ፡ሀገር፡ውስተ፡እደ፡ፋርስ፡እለ፡ ዐብእዋ፡እምገጸ፡ኩናት፡ወረሀብ፡
ይህቺ፡ሀገር፡ኢየሩሳሌም፡ከረሀብ ከጦር፡የተነሣ፡በወጓት፡በፋርስ ሰዎች፡እጅ፡ተይዛለችና፡የተያዘች አቤቱ፤

ወኮነ፡በከመ፡ነበብከ፡
እንደ ፡ ተናገርህ ፡ ተደርጓልና የተደረገ፡አቤቱ፤

፳፭፡ ወትቤለኒ፡አንተ፡እግዚአ፡እግ ብሔር፡
አቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ እንዲህ፡አልኸኝ፤

ተሣየጥ፡ገራህተ፡በብሩር፡
በብር ፡ እርሻን ፡ ግዛ ፡ አልኸኝ አንድም፡ያልኸኝ፡አቤቱ፤

ወአስምዕ፡ሰማዕተ፡
መሣክርቱን ፡ አዳኝ ፡ አልኸኝ ያልኸኝ፡አቤቱ፡

ወጸሐፍኩ፡መጽሐፈ፡ወኀተምክዋ፡
ደብዳቤውን ፡ ጻፌ ፡ አተምኩ ፡ የአ ምኁት፡አቤቱ፡

ወአኪድኩ፡ሰማዕተ፡
መሣክርቱን ፡ ዳር ፡ ድንበሩን ፡ አ ገጥሁ፡ አንድም ፡ ወአያድኩ ፡ መ ርቱን፡አዙሬ፡አሳየሁ፡

ወገብዓት፡ዛ፡ሀገር፡ውስተ፡እደ፡ከለዳው ይቺ፡አገር፡ኢየሩሳሌም፡በከለዳው እጅ፡ተይዛለችና፡የተያዘች፡አቤቱ፡

ወውስተ፡እደ፡ፋርስ፡
በፋርስ፡ሰዎች፡እጅም፡ተይዛለች የተያዘች ፡ አቤቱ፡ እንዲህ ፡ እንዲ ከሆነች ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ የሚገ የሚሸጥ፡ አለና ፡ ሰው ፡ ይገኛልና ተሣየጥ ፡ አልኸኝ ፡ ብዬ ፡ ወጸለይ ...



፳፮፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፤
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ መጣ፡ተነገረ፤

፳፯፤ ወይቤ፡አነ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡ አምላከ፡ለነተሉ፡ዘሥጋ፡
ለሥጋዊ፡ለደማዊ፡ሁሉ፡ገዥ፡ፈጣሪ፡ የምሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ፤

ሁ፡እንጋ፡ምንትኒ፡ዘይትኀባዕ፡እምኔየ፡
ውት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ከእኔ ፡ የሚ ሰወር፡አለን፡እንጃ፤

፳፰፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚ አብሔር፡
ለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡አለ፡

ኢትገብእ፡ዛ፡ሀገር፡ውስተ፡እደ፡ፋርስ፡
ኢየሩሳሌም ፡ በፋርስ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ትያዛለች፡

ውስተ፡እዴሁ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፡
ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ እጅም፡ትያዛለች፡

ይነሥእ፡
እጅ፡ያደርጋታል፡አለ፡

፳፱፡ ወይመጽኡ ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ እለ ፡ ይፀብእዋ፡ለዛ፡ሀገር፡
ኢየሩሳሌምን ፡ የወጓት ፡ የፋርስ ፡ ሰዎች፡መጥተው፡

ያውዕይዋ፡ለዛ፡ሀገር፡በእሳት፡
ይችን፡ሀገር፡በእሳት፡ያቃጥሏታል፡

ያውዕዩ፡አብያተ፡እለ፡በውስተ፡አንሕስ ...ሙ፤
...ገበ፡ በሰገነት፡ ሆነው፡ ለጣዖት ፡ ...

ያቃጥላሉ ፡ አንድም ፡ ለጣዖት ፡ መሥዋዕት ፡ የሠዉባቸው ፡ ቤቶች ፡ ይቃጠላሉ፤

ወዓጠኑ፡ለበዓል፡
ለጣዖት ፡ ዕጣን ፡ ያጠኑባቸውን ፡ ቤቶች፡ያቃጥላሉ፤

ወአውጽሑ፡ሞጻሕተ፡ለባዕዳን፡አማልክት፡ ከመ፡ያምዕዑኒ፡
ያሳዝኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ለሆኑ ፡ ጣዖታት፡ወይኑን፡ፍልቅ፡አድርገው፡ ያፈሰሱባቸውን፡ቤቶች፡ያቃጥላሉ፡

፴፡ እስመ ፡ ኮኑ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወደቂቀ፡ይሁዳ፡ባሕቲቶሙ፡ገብሩ፡እኩየ፡ በቅድሜየ፡እምንዕሰሙ፡
የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች፡ብቻቸውን፡ከሕፃንነታቸው፡ ጀምሮ፡በፊቴ፡የማይገባ፡ሥራ፡ሠርተ ዋልና፡

እስመ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ኮኑ፡ዘያምዕዑኒ፡ ኪያየ፡በምግባረ፡እደዊሆሙ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፡
እግዚአብሔር፡የእስራኤል፡ልጆች፡ በእጃቸው፡በሠሩት፡ሥራ፡እኔን፡የሚ ያሳዝኑኝ፡ሁነዋል፡ብሏልና፡

፴፩፡ እስመ፡ውስተ፡መዓትየ፡ወመቅሠ ፍትየ፡ሀለወት፡ዛ፡ሀገር፡
ይች ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመዓቴ ፡ በመቅሠፍቴ፡ተይዛለችና፡

እምአመ ፡ ሐነፅዋ ፡ እስከ ፡ ዛ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ዕሥአራ፡እምቅድመ፡ገጽየ፡
ከአቀኗት ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከፊቴ ፡ አጠፋት ፡ ዘንድ ፡ በመዓቴ፡ተይዛለችና፡

፴፪፡ በእንተ ፡ ነተሉ ፡ እከዮሙ ፡ ለደቂቀ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስራኤል ፡ ወደቂቀ ፡ ይሁዳ ፡ ዘገብሩ ፡ ከመ ፡
ያምዕዑኒ፡እሙንቱ፡ወነገሥቶሙኒ፤
ያሣዝኑኝ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡
ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡
ሠሩት፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡
ተይዛለችና፡እነሱና፡ነገሥታቱ፤
ወመላእክቲሆሙኒ፡ወካህናቲሆሙኒ፤
አለቆቻቸውና፡ካህናቱ፤
ወነቢያቲሆሙኒ፤
ነቢያቶቻቸው፤
ወሰብአ፡ይሁዳ፤
የይሁዳ፡ሰዎች፤
ወእለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያሳዝኑኝ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡
ሠሩት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ በመዓቴ ፡ በመቅ
ሠፍቴ፡ተይዛለችና፤

፴፫፤ ወሜጡ ፡ ኅቤየ ፡ ዘባኖሙ ፡ ወአኮ ፡
ገጾሙ፤
ገጽ፡ልቡናቸውን፡ያይደለ፡ዘባነ፡ልቡ
ናቸውን፡ወደ፡እኔ፡መለሱ፤
ወመሀርክዎሙ፡በበዕለቱ፤
በየቀኑ፡በየዕለቱ፡አስተማርኋቸው፤
ወኢሰምዑኒ፤
ነገር፡ግን፡አልሰሙኝም፤
ወኢተወከፉ፡ተግሣፅየ፤
ምክር፡እዝናቴንም፡አልተቀበሉም፤

፴፬፤ ወገብሩ ፡ ርኵሶሙ ፡ ውስተ ፡ ቤትየ ፡
ዘተሰምየ፡ስምየ፡ላዕሌሁ፡ከመ፡ያርኵስዎ፤
ያረከሱት፡ዘንድ፡ስሜ፡በተጠራበት፡
በቤተ፡መቅደስም፡ኃጢአት፡ሠሩ፤

፴፭፤ ወሐነፁ ፡ ምሥዋዓ ፡ ለበዓል ፡
በቈላተ፡ወልደ፡ሄኖም፤
በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡
...ጠዕት፡መሠዋዩ፡ሠሩ፤

ከመ ፡ ይሡዑ ፡ በህየ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወአዋል
ዲሆሙ፡ለሞሎሕ፤
ወንዶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሴቶች ፡ ል
ቻቸውን ፡ ሞሎሕ ፡ ለሚባል ፡ ጣዖት፡
በዚያ፡ይሠዉ፡ዘንድ፤
ዘኢአዘዝክዎሙ፤
ሥሩት፡ብዬ፡ያላዘዝኋቸውን፤
ወኢሐለይክዎ፡በልብየ፤
አዝዛቸዋለሁ ፡ ብዬ ፡ በልቡናየ ፡ ያላ
ብኩትን፤ አንድም ፡ ይተዉታል፤ ይጠ
ቅማቸዋል፡ብዬ፡ያላሰብኩትን፤
ከመ ፡ ይግበርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ርኵሶሙ ፡ በዘያ
ሕትዎ፡ለይሁዳ፤
ይሁዳን፡በሚያስቱ፡ገንዘብ፡ጣዖቱን
ይሠሩ፡ዘንድ፤

፴፮፤ ወበእንተዝ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ኃያል፡አምላከ፡እስራኤል፤
ስለዚህ፡ነገር፡ኃያል፡የሚሆን፡የእስ
ራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፤
ለዛ፡ሀገር፡እንተ፡ትብሉ፡አንትሙ፡ገብዓት
ውስተ፡እዴሁ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፡በኲናት
ወበረሀብ፡ወበብድብድ፤
እናንተ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ
በኲናት፡በጦር፡በቀጠና፡በቸነፈር
ወደቀች፡የምትሏት፡ይህቺን፡ሀገር
አቀናታለሁ፡አለ፤

፴፯፤ ወናሁ፡አነ፡አስተጋብአሙ፡እም
በሐውርት፡ኀበ፡ዘረውክዎሙ፡ህየ፤
እነሆ፡እኔ፡አስማርኬ፡ከበተንኋቸው
አገሮች፡ሁሉ፡እሰበስባቸዋለሁ፤
በመዓትየ፡ወበመቅሥትየ፡ዓቢይ፤
ጽኑ፡በሆነ፡መቅሥፍትና፡በቁጣ
አስማርኬ ፡ ከሰደድኋቸው ፡ አገሮች
...



ወእመይጠሙ፡ውስተ፡ዝ፡ብሔር፤
ወደዚህ፡ሀገር፡እመልሳቸዋለሁ፤
ወአነብሮሙ፡ተአሚኖሙ፤
ጠላት ፡ ጠፍቶላቸው ፡ ተዘልለው ፡
እንዲኖሩ፡አደርጋቸዋለሁ፤

፴፰፤ወይከውኑኒ፡ሕዝብየ፤
ወገኖቼ፡ይሆኑኛል፤
ወአነሂ፡እከውኖሙ፡አምላኮሙ፤
እኔም ፡ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ ፈጣሪ፤
እሆናቸዋለሁ፤

፴፱፤ወእሁቦሙ፡ካልአ፡ፍኖተ፡ወካልአ፡
ልበ፡ሐዲሰ፤
ሌላ፡ሥራ፡ሌላ፡እንግዳ፡ዕውቀት፡እሰ
ጣቸዋለሁ፤
በዘይፈርሁኒ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡
ለሠናይ፤
ለበጎ፡ነገር፡ባለ፡በዘመናቸው፡ሁሉ፡
በሚፈሩኝ፡ገንዘብ፤
ወለውሉዶሙኒ፡እምድኅሬሆሙ፤
ከነሱም፡በኋላ፡ለልጆቻቸው፡እሰጣቸ
ዋለሁ፤

፵፤ወእሠርዕ፡ሎሙ፡ሥርዓተ፡ዘለዓለም፤
ለዘለዓለም፡የሚሆን፡ሥርዓትን፡እሠ
ራላቸዋለሁ፤
በዘኢይትአተት፡እምድኅሬሆሙ፤
ከነሱ፡በኋላ፡በማይርቅ፡በማይጠፋ፡
ገንዘብ፤
ወእወዲ፡ፍርሀትየ፡ውስተ፡ልቦሙ፤
በልቡናቸው ፡ መፈራቴን ፡ አሳድ
ራለሁ፤
ከመ፡ኢይርኅቁ፡እምኔየ፤
በሕግ፡በአምልኮት፡ከኔ፡እንዳይርቁ፤

፵፩፤ወእሠሃሎሙ፤
ይቅር፡እላቸዋለሁ፤

ወእሡኒ፡ሎሙ፤
በጎ፡ነገር፡አደርግላቸዋለሁ፤
ወእተክሎሙ ፡ ውስተ ፡ ዛ ፡ ምድር ፡ በርትዕ ፡
ወበሃይማኖት፤
በቀና ፡ ነገርና ፡ በሃይማኖት ፡ በዚች ፡
አገር፡አጸናቸዋለሁ፤
በኵሉ፡ልብየ፡ወበኵሉ፡ነፍስየ፤
በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ በፍጹም ፡ ሰው
ነቴ፡አጸናቸዋለሁ፤

፵፪፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤
በከመ ፡ አምጻእኩ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብ ፡ ኵሎ ፡
ዘንተ፡እኩየ፡ዓቢየ፤
ይህን ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ክፉ ፡ መከራ ፡
በሕዝቡ፡ላይ፡እንዳመጣሁ፤
ከማሁ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ ሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ሠናየ ፡
ዘነበብኩ፡ላዕሌሆሙ፤
አሁን ፡ እንደተናገርሁት ፡ እኔ ፡ ለነሱ ፡
የተናገርሁትን ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
አመጣላቸዋለሁ፤

፵፫፤ ወዓዲ ፡ ያጠርዩ ፡ ገራውሀ ፡ በዛቲ ፡
ምድር፤
ዳግመኛ ፡ በዚች ፡ ሀገር ፡ እርሻውን ፡
ይገዛሉ፤
እንተ፡ትብሉ፡ዓፀ፡ይእቲ፡እምሰብእ፡ወእም
እንስሳ፤
ከሰውና፡ከእንስሳ፡ተለይታ፡ምድረ፡
በዳ ፡ ሆነች ፡ በምትልዋት ፡ በዚች ፡
አገር፤
ወገብአት፡ውስተ፡እደ፡ፋርስ፤
በፋርስ፡ንጉሥ፡እጅ፡ወደቀች፡በምት
ልዋት፡በዚች፡አገር፡እርሻን፡ይገዛሉ፤

፵፬፤ወይሣየጡ፡ገራውሀ፡በወርቆሙ፤
በገንዘባቸው፡እርሻን፡ይገዛሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወትጽሕፍ፡መጽሐፈ፡ወተኀትማ፤
መጻሕፍቱን፡ጽፈህ፡አትማት፤

ወታስምዕ፡ሰማዕተ፡በምድረ፡ብንያም፤
በብንያም፡ዕፃ፡መሣክርቱን፡አዳኝ፤

ወበዐውዳ፤ ለኢየሩሳሌም፤ ወበአህጉረ፤
ይሁዳ፤
በኢየሩሳሌም ፡ አውራጃና ፡ በይሁዳ ፡
አውራጃ፤

ወበአህጉር ፡ ዘውስተ ፡ ደብር ፡ ወአህጉረ ፡
ሳፌላ፤
በደጋው ፡ አውራጃና ፡ በሳፌላ ፡
አውራጃ፤

ወአህጉረ፡ናጌብ፤
ናጌብ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ዘመንገለ፡ኵለሄ፡ሲል፡ነው፤ በሀገሩ፡
ሁሉ ፤ አንድም ፡ ዘመንገለ ፡ ሣህል፤
ይቅርታ ፡ በሚደረግበት ፡ አገር ፡
ታስምዕ፡ብለህ፡እሥር፤

እስመ፡እመይጠሙ፡ለፈላስያን፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፤
እግዚአብሔር፡የተማረኩትን፡እመል
ሳቸዋለሁ፡ብሏልና።

## ምዕራፍ፡፴፫፡

፩፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡ዳግመ፤
ዳግመኛ፡ወደኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአ
ብሔር፡መጣ፤ተነገረ፤

እንዘ፡ሀሎ፡ዓዲሁ፡በዐፀደ፡ሞቅሕ፤
ገና ፡ በእሥራት ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ መጣ ፡
ተነገረ፤

ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ዘገብራ፡
ለምድር፡ወፈጠራ፡ከመ፡ያርትዓ፤
ያቀናት ፡ ዘንድ ፡ ምድርን ፡ ፈጽሞ ፡
የፈጠራት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
አለ፤

እግዚአብሔር፡ስሙ፤
ስሙ ፡ አቸናፊ ፡ የሚባል ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

፫፤ጽራህ፡ኀቤየ፡ወአወሥአከ፤
ወደ፡እኔ፡ጮኽኽ፡ለምን፡እመልስል
ሃለሁ፤

ወእነግረከ፡ዓቢያተ፤
ገናና፡ገናና፡ሥራዎችን፡እነግርሃለሁ፤

ወኃይላተ፡ዘኢተአምሩ፤
እናንተ ፡ የማታውቋቸው ፡ ተአም
ራትን ፡ እነግርሃለሁ፤ አንድም ፡
ዓቢያተ ፡ ዼዋዌን ፤ ወኃይላተ ፡ ሚጠ
ትን፡እነግርሃለሁ፤

፬፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡ብሎ፡ተናግሯልና፤

በእንተ ፡ ዓብያተ ፡ ሀገር ፡ ዛቲ ፡ ወበእንተ ፡
ዓፀደ፡አብያተ፡ነገሥተ፡ይሁዳ፤
ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ቤቶች ፡
ቦታና፡ስለዚች፡ሀገር፡ቤቶች፤

እለ፡ንኅሉ፡በሠራዊት፡ወእለ፡ተመዝበሩ፤
በከለዳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ፈጽመው ፡
ስለጠፉ፡እንዲህ፡ብሎአልና፤

፭፤ እስመ ፡ መጽኡ ፡ መስተቃትላን ፡
ዘፋርስ፡ይትቃተሉ፤
ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ የፋርስ ፡ አርበኞች ፡
መጥተዋልና፤

ወእመልዕ ፡ አብድንተ ፡ ሰብእ ፡ ዘቀተልኩ ፡
በመዓትየ፤
በመዓቴ ፡ ተቆጥቼ ፡ የገደልኋቸውን ፡
[illegible]



ወሜጥኩ ፡ ገጽየ ፡ እምዛቲ ፡ ሀገር ፡ በእንተ ፡
ኵሉ፡እከዮሙ፤
ስለ፡ኃጢአታቸው፡ከዚች፡ሀገር፡ገጸ፡
ረድኤቴን፡መለስሁ፤

፮፤ ናሁ ፡ አነ ፡ አዐርግ ፡ ላቲ ፡ ፈውሠ ፡
ወሥራየ፤
እነሆ፡እኔ፡ሚጠትን፡አደርጋለሁ፤

ወእከሥት፡ሎሙ፡ፍኖተ፡ሰላም፡ወጽድቅ፤
የምግባርና ፡ የሃይማኖት ፡ ሥራን ፡ እገ
ልጥላቸዋለሁ፤

፯፤ ወእመይጥ ፡ ፈላስያነ ፡ ይሁዳ ፡ ወፈላ
ስያነ፡እስራኤል፤
ከአይሁድና ፡ ከእስራኤል ፡ የተማረ
ኩትን፡እመልሳለሁ፤

ወአሐንፆሙ፡ከመ፡ትካት፤
እንደ፡ቀድሞው፡በረድኤት፡አጸናቻ
ዋለሁ፤

፰፤ወአነጽሖሙ፡እምኵሉ፡ኃጢአቶሙ፡
ዘአበሱ፡ሊተ፤
እኔን ፡ ከበደሉበት ፡ ከኃጢአታቸው ፡
ሁሉ፡አነጻቸዋለሁ፤

ወእሠሪ፡ሎሙ፡ኵሎ፡ጌጋዮሙ፡ዘአለዉኒ፤
እኔን ፡ የወነጀሉበትን ፡ ኃጢአታ
ቸውን፡ሁሉ፡አስተሠርይላቸዋለሁ፤

፱፤ወይከውን፡ፍሥሐ፡ዓቢየ፤
ታላቅ፡ደስታን፡አደርጋለሁ፤

ወክብረ፤
ክብርን፤

ወዕበየ፡ለኵሉ፡አሕዛበ፡ምድር፤
ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ገናንነትን ፡ እሰ
ጣለሁ፤

እለ፡ሰምዑ፡ኵሎ፡ሠናየ፡ዘገበርኩ፡አነ፤
እኔ ፡ ያደረግሁትን ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ለሰሙ ፡ ለምድረ ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ፡ገናንነትን፡አደርጋለሁ፤

ይፈርሁ፡ወይደነግፁ፡በእንተ፡ኵሉ፡ሠናይ፡
ወበእንተ፡ኵሉ፡ሰላም፡ዘእገብር፡ሎሙ፡አነ፤
እኔ፡ስለማደርግላቸው፡ፍቅር፡አንድ
ነትና፡ስለ፡በጎው፡ሁሉ፡እስራኤል፡
የደስታ ፡ ድንጋጤን ፡ ይደነግጣሉ ፡
ይፈራሉ፤

፲፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ዓዲ ፡ ይሰማዕ ፡ በዝ ፡ ብሔር ፡ ዘትብልዎ ፡
በድው፡ውእቱ፡እምሰብእ፡ወእንስሳ፤
ዳግመኛ ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳት ፡
ተለይቶ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ ፡
በምትሉት፡በዚህ፡ሀገር፡ይሰማል፤

በአህጉረ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ፡አውራጃና፤

ወበአፍአሃ፡ለኢየሩሳሌም፡ጽብዕት፤
በጦር ፡ በተወጋች ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በአፍአ፤

ወአልቦ፡ዘይነብር፤
የሚኖርባት፡ሰው፡የለም፡በምትሉት፤

ወአልቦ፡ሰብእ፡ወእንስሳ፤
ሰው ፡ ከብት ፡ አይኖርበትም ፡ በም
ትሉት፡በዚህ፡ሀገር፤

፲፩፤ቃለ፡ፍሥሐ፡ወቃለ፡ኃሤት፤
የተድላ፡የደስታ፡ቃል፡ይሰማል፤

ወቃለ፡መርዓዊ፡ወቃለ፡መርዓት፤
ዕገሌ ፡ እገሌትን ፡ ያግባ፤ ዕገሊት ፡
ዕገሌን ፡ ታግባ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡
ይሰማል፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ዐሥርት ፡
ያለ፡የሚያከብሩት፡በዓል፡አለና፤

ወቃለ ፡ ዘይብል ፡ እመኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ዘይነግሥ፡ለኵሉ፡በጽድቅ፤

www.ethiopianorthodox.org

በእውነት ፡ ለሁሉ ፡ ነግሦ ፡ በሚኖር ፡
በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ፡ የሚል ፡
ቃል፡ይሰማል፤

እስመ፡ኄር፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ቸር፡ነውና፤

ወለዓለም፡ምሕረቱ፤
ቸርነቱም፡ለዘለዓለም፡ነውና፤

ወያበውዑ፡ቍርባነ፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአ
ብሔር፤
ወደ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ቍርባኑን፡
ያቀርባሉ፤

እስመ፡እመይጥ፡ፈላስያነ፡ይእቲ፡ሀገር፡
ከመ፡ትካት፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ እንደቀድሞው ፡
ከዚች፡ አገር ፡ የተማረኩትን ፡ እመል
ሳለሁ፡ብሏልና፤

፲፪፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ዓዲ፡ይሰማዕ፡በዝ፡ብሔር፡ዘማሰነ፡በኃጢአ፡
ሰብእ፡ወእንስሳ፤
ዳግመኛ ፡ ሰውና ፡ ከብት ፡ በማጣት ፡
በጠፋ፡በዚህ፡ሀገር፡ይሰማል፤

በኵሉ፡አህጉር፤
በሀገሩ፡ሁሉ፤

ማኅደረ፡ኖሎት፤
የዘላኖች፡መኖሪያ፡በሚሆን፤

ወአዕፃደ፡አባግዕ፤
የበጎች፡መሰማሪያዎች፡በሚሆኑ፤

፲፫፤ውስተ፡አህጉረ፡አድባር፤
በደጋው፡ባሉ፡አውራጃዎችና፤

ወውስተ፡አህጉረ፡ሳፌላ፤
በሳፌላ፡አውራጃዎች፤

ናጊብ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ዘመንገለ፡ኵለሄ፡ይላል፤
በሀገሩ ፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡ ዘመንገለ ፡
ሣህል ፡ ይላል ፤ ይቅርታ ፡ በሚደረ
ግበት፡አገር፤

ወበምድረ፡ብንያም፤
በብንያም፡ዕፃ፤

ወበአድያመ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወበአህጉረ ፡
ይሁዳ፤
በኢየሩሳሌም ፡ አውራጃና ፡ በይሁዳ፡
አውራጃ፡ዓዲ፡ይሰማዕ፡ብለህ፡እሠር፤

ወዓዲ፡ይወፍራ፡አባግዕ፡በእደ፡ዘይኈልቆን፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ዳግመኛ ፡ በጎች ፡ በሚቈጥሯቸው ፡
ሰዎች ፡ እጅ ፡ ይሰማራሉ ፤ አንድም ፡
እሥራኤል ፡ በሚመክሯቸው ፡ በሚያ
ስተምሯቸው ፡ በነቢያት ፡ ቃል ፡
ይጠበቃሉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፬፤ናሁ፡ይበጽሕ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፤
እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፡
አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአቀውም፡ቃልየ፡ሠናየ፡ዘተናገርኩ፡
ለቤተ፡እሥራኤል፡ወለቤተ፡ይሁዳ፤
ለዐሥሩ፡ ነገድና ፡ ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ወገኖች ፡ የተናገርሁትን ፡ ቃሌን ፡
አጸናለሁ ፡ ማለት ፡ ወሐሊቆ ፡ ፭ ፡
ዓመት ፡ እትቤቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡
ባቢሎን፡ያልሁትን፡አጸናለሁ፤

፲፭፤ በእማንቱ፡መዋዕል፡ይእተ፡አሚረ፡
አሠርፅ፡ለዳዊት፡ሠርፀ፡ጽድቅ፤
ወኀሊቆ፡ሰብዓ፡ዓመት፡ያልሁትን፡ባፀ
ናሁበት፡ወራት፡ያን፡ጊዜ፡እውነተኛ፡
[illegible]



ወይገብር፡ፍትሐ፡ወጽድቀ፡ውስተ፡ምድር፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ እውነት ፡ ፍርድን ፡
ይፈርዳል ፤ ዘይገብር ፡ ቢል ፡ እውነት፡
ፍርድን ፡ የሚፈርድ ፡ ዘሩባቤልን ፡ አነ
ግሣለሁ፤

፲፮፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ትድኅን ፡
ይሁዳ፤
ወሐሊቆ ፡ ሰብአ ፡ ዓመት ፡ ያልሁትን ፡
ባፀናሁበት ፡ ወራት ፡ ይሁዳ ፡ መላዋ ፡
ሀገር፡ትድናለች፤

ወኢየሩሳሌም፡ትነብር፡ተአሚና፤
ኢየሩሳሌም ፡ ከተማይቱ ፡ ጠላት ፡
ጠፍቶላት፡ተዘልላ፡ትኖራለች፤

ወዝ ፡ ዘይሰብክ ፡ ላቲ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጽድቅነ፤
ይህ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስ
ተምር፡ዮሴዕ፡ወልደ፡ዮሴዴቅ፡ነው፤
አንድም ፤ ወአቀውም ፡ ለእስራኤል ፡
ዘነፍስ ፡ ለይሁዳ፡ ዘነፍስ ፤ የተናገር
ሁትን ፡ ቃሌን ፡ አፀናለሁ ፡ ማለት ፡
በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ያልሁትን፡
አጸናለሁ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡
በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ያልሁትን ፡ ባፀና
ሁበት፡ወራት፡ያን፡ጊዜ፡እውነተኛ፡
ንጉሥ ፡ ክርስቶስን ፡ አስነሣለሁ ፤
ወይገብር ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እውነት ፡
ፍርድን ፡ ይፋርዳል ፤ ዘይገብር ፡ ቢል፤
ሕገ፡ወንጌልን፡የሚያስተምር፡ክርስ
ቶስን፡አስነሣለሁ፤ወበእማንቱ፤
በአምስት ፡ ሺህ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ይሁዳ ፡ ዘነፍስ ፡ ትድናለች ፡
በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ያልኹትን ፡ በአፀና
ሁበት ፡ ወራት ፡ ብትልም ፤ ወኢየሩ
[illegible]

ጠፍቶላት፡ተዘልላ፡ትኖራለች፤
ወዝ ፡ ዘይሰብክ ፤ ይህ ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡
የሚያስተምር፡ ክርስቶስ ፡ ጻድቅ ፡
ባሕርይ፡ነው፤

፲፯፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ኢይትመተር ፡ ብእሲ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡
መንበረ፡ቤተ፡እሥራኤል፤
በእሥራኤል፡ወገኖች፡ዙፋን፡ነግሦ፡
የሚኖር፡ሰው፡አይጠፋም፡ብሏልና፤
አንድም ፤ ኢይመትር ፡ ብእሴ ፡
ዘይነብር፤
በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ነግሦ ፡ የሚኖር፡
ሰውን፡አላጠፋም፡ብሎ፡ተናግሯልና፤

፲፰፤ ወእምካህናት ፡ ወሌዋውያን ፡ ኢይት
መተር፡ብእሲ፡ዘይቀውም፡በቅድሜየ፤
ከካህናትና ፡ ከሌዋውያንም ፡ ወገን ፡
በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ ሰው ፡ አይጠፋም፡
ብሏልና፤

ወዘያዓርግ፡ቍርባነ፤
ቍርባኑን፡የሚያሣርግ፤

ወዘየዐጥን፡ዕጣነ፤
ዕጣኑን፡የሚያጥን፤

ወዘያበውዕ፡መባዓ፤
መባእውን፡የሚያቀርብ፤

ወዘይሠውዕ፡መሥዋዕተ፡ኵሎ፡መዋዕለ፤
ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ መሥዋዕቱን ፡
የሚሠዋ፡ሰው፡አይጠፋም፡ብሏልና፤

፲፱፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
መጣ፡ተነገረ፤

፳፤ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

እመ ፡ ይትቄለጥ ፡ ሥርዓተ ፡ መዓልት ፡ ወሥርዓተ ፡ ሌሊት ፡ ከመ ፡ ኢይኩኑ ፡ መዓልት፡ወሌሊት፡በበጊዜሆሙ፡
በየጊዜያቸው ፡ መዓልቱ ፡ መዓልት ፣ ሌሊቱ ፡ ሌሊት ፡ እንዳይሆኑ ፡ የመዓልትና ፡ የሌሊት ፡ ሥርዓታቸው፡ ቢለወጥ፤

፳፩፤ ሥርዓትየሂ ፡ ይትቄለጥ ፡ ዘምስለ፡ ዳዊት፡ገብርየ፡
ከባሪያዬ ፡ ከዳዊት ፡ ጋር ፡ የተማማልሁት ፡ መሐላዬም ፡ ይፈርሳል ፡ ማለት፡ ያም ፡ አይለወጥ ፣ መሐላዬም ፣ አይፈርስ፡ሲል፡ነው፤

ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡ ዘይነግሥ፡ በዲበ፡መንበሩ፡
በዙፋኑ ፡ ነግሦ ፡ የሚኖር ፡ ልጅ ፡ እንዳ ይኖር፤

ወእምሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ዘይትለአከኒ ፡
ከሌዋውያን፣ከካህናት፡ወገንም፡የሚያገለግለኝ፡ሰው፡እንዳይኖር፡አይፈርስም፤

፳፪፤ በከመ ፡ ኢይትኌለቍ ፡ ኃይለ ፡ ሰማያት፡
የሰማይ፡ሠራዊት፡ከዋክብት፡እንዳይ ቈጠሩ፤

ወኢይሠፈር፡ኖፃ፡ባሕር፡
የባሕር፡አሸዋም፡እንዳይሠፈር፤

ከማሁ፡አበዝኆ፡ለዘርዓ፡ዳዊት፡ገብርየ፡
አሁን፡እንደ፡ተናገርሁት፡አገልጋዬ፡ የሚሆን ፡ የዳዊትን ፡ ወገን ፡ አበዛ ዋለሁ፤

ወለሌዋውያን፡እለ፡ይትለአኩኒ፡
የሚያገለግሉኝ፡ሌዋውያንንም፡አበዛ ቸዋለሁ፤

፳፫፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፡
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ መጣ፣ተነገረ፤

፳፬፤ወይቤ፡
እንዲህ፡አለ፤

ርኢከኑ፡ምንተ፡ይትናገር፡ዝንቱ፡ሕዝብ፡
ይህ ፡ ወገን ፡ ምን ፡ ይናገራል ፡ ኤርምያስ፡አየህን፡ሰማህን፤

ለብሂል፡ክልዔቱ፡ሕዝብ፡ዘኅረዮሙ፡እግዚ አብሔር፡
እግዚአብሔር፡የመረጣቸው፡ሁለቱ፣ ነገድ፡ናቸው፤

ወመነኖሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ያስተቀሥጥዎሙ እምከዊነ፡ሕዝብየ፡ቅድሜሆሙ፤
የናቃቸው ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ፣ ለማለት ፤ አንድም ፡ በብሂል ፡ ቢል ፣ የመረጣቸው ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡ ናቸው፤ ወመነኖሙ፤
የናቃቸው ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ፣ በማለት፡ ምን ፡ ይናገራል ፤ለሕዝብየ፣ ያስተቀሥጥዎሙ፤
በፊታቸው ፡ የእኔ ፡ ወገኖችን ፣ ከመሆን፡ አውጥተው ፡ ወገኖቼን ፡ ያበሳጩቸው፡ዘንድ፤

፳፭ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

አመ፡ይትመተር፡መዓልት፡ወሌሊት፡
የመዓልትና ፡ የሌሊት ፡ ሥርዓት ፣ ቢለወጥ፤



ወሥርዓተ፡ሰማይ፡ወምድር፡ዘኢረሰይኩ፡
ከዚህ፡አስቀድሞ፡እኔ፡ያላደረግሁት፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ሥርዓታቸው ፡ ቢለወጥ፤

፳፮፤ ወዘርዓ፡ያዕቆብኒ፡ወዳዊት፡ገብርየ፡ እሜንን፡
የያዕቆብና ፡ የአገልጋዬ ፡ የዳዊትን ፡ ወገን ፡ እንቃለሁ ፡ ማለት ፡ ያም ፡ አይለወጥ፤እኔም፡አልንቅ፤

ከመ፡ኢይትነሣዕ፡እምዘርዑ፡መኳንንተ፡
ከወገኑ፡ገዥ፡እንዳይነሣ፤

ኀበ፡ዘርዓ፡አብርሃም፡ይስሐቅ፡ወያዕቆብ፡
ከአብርሃምና፡ከይስሐቅ፡ከያዕቆብም፡ ወገን፡አልንቅም፤

እስመ፡እመይጥ፡ፄዋሆሙ፡
ምርኳቸውን፡እመልሳለሁና፤

ወእምሕሮሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ እላቸዋለሁ ፡ አለ።

## ምዕራፍ፡፴፬፡

፩፤ ቃል፡ዘኮነ፡ኀበ፡ኤርምያስ፡እምኀበ፡ እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ታዝዞ፡ወደ፡ ኤርምያስ፡የመጣ፡የተነገረ፤አንድም፡ በኤርምያስ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው፤

ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ላለው ፡ ሳያመጣ ፡ በመካከሉ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አገባበት ፤ የባቢሎን፡ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፤

ወኵሉ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወኵሉ ፡ መንግሥታተ፡ ምድር፡ያነሥኡ፡እደ፡
የዚህ፡ዓለም፡ነገሥታት፡ሁሉ፡ሥል ጣናቸውን፡ከፍ፡ከፍ፡ያደርጋሉ፤

ወኵሉ፡አሕዛበ፡ምድር፡ይትቃተልዋ፡ለኢየ ሩሳሌም፡
የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ኢየሩሳ ሌምን፡ይወጓታል፤

ወለኵሉ፡አሕጉረ፡ይሁዳ፡
የይሁዳን፡አውራጃዎች፡ሁሉ፡ይወጓ ቸዋል፤

ወይቤ፡
ወይቤ ፡ ዋዌ ፡ ነው ፤ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ያለውን፡አመጣ፤አንድም፡የባቢሎን፡ ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፡ሠራዊቱ፡ሁሉ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣና ቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋሉ ? ትቹ ፡ ነው ፣ ወይቤ ፡ ዋዌውን ፣ ትተህ ፡ ወደ ፡ ታች፡ይዘህ፡ውረድ፡እንዲህ፡አለ፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡ እሥራኤል፡
የእሥራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡አለ፤

ሑር፡ኀበ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
ወደ ፡ ይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሴዴቅያስ፡ሒደህ፤

ወበሎ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በለው፤

ተውህቦ፡ትትወሀብ፡ዛ፡ሀገር፡ውስተ፡እደ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፡
ይህቺ ፡ ሀገር ፡ በባቢሎን ፡ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ፡መሰጠትን፡ትሰጣለች፤

ወይነሥኣ፡
እጅ፡ያደርጋታል፤

ወያውዕያ፡በእሳት፡
በእሳት፡ያቃጥላታል፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ ወአንተ፡እምእዴሁ፡ኢትድኅን፡
አንተም፡ከእርሱ፡እጅ፡አትድንም፤

ወተነሥኦ፡ትትነሣእ፡
ትማረካለህ፤

ወውስተ፡እዴሁ፡ትትወሀብ፡
በእሱ ፡ እጅ ፡ ትሰጣላህ ፡ ማለት ፡
ትጣላለህ፤

ወአዕይንቲከ፡ለአዕይንቲሁ፡ይሬእያ፡
አይኖችህ፡አይኖቹን፡ያያሉ፤

አፉከ፡ምስለ፡አፉሁ፡ይትናገር፡
አፍህም፡ከአፉ፡ጋራ፡ይነጋገራል፤

ወውስተ፡ባቢሎን፡ትገብእ፡
ወደ፡ባቢሎን፡ተማርከህ፡ትሔዳለህ፤

፬፤ ወባሕቱ ፡ ስማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር፡
ኦ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሆይ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስማ፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡በእንቲአከ፡
የአንተን ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤

፭፤ኢትመውት፡በኲናት፡
በጦር፡አትሞትም፤

አላ፡በሰላም፡ትመውት፤
በሰላም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ትሞ
ታለህ፡እንጂ፤

ወበውዕየተ ፡ አበዊከ ፡ ነገሥት ፡ ቀደምት፡
ዘኮኑ፡እምቅድሜከ፡
ከአንተ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡
አባቶችህ ፡ ነገሥታቱ ፡ ሽቱ ፡ እንደ ፡
ተቀቡ፤

ከማሁ፡ያውዕዩ፡ለከ፡
አንተንም ፡ ሽቱ ፡ ቀብተው ፡ ይቀብ
ሩሀል፤

ወይብሉ፡እንዘ፡ያስቆቅዉ፡ለከ፡
ሲያለቅሱልህ፡እንዲህ፡ይላሉ፤

ወይብሉከ፡ወይ፡እግዚኦ፡
ጌታችን፡ወዮ፡ጌታችን፡ይሉሃል፤

እስመ፡ሰማዕከ፡ቃለከ፡ዘነበብከ፡አነ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ የተናገርኸውን፡
ቃልህን፡ሰማሁ፡ብሏልና፤

፮፤ወነበቦ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡ለሴዴቅያስ፡
ንጉሠ፡ይሁዳ፡ኵሎ፡ዘነገረ፡በኢየሩሳሌም፤
ነቢዩ፡ኤርምያስ፡ለይሁዳው፡ንጉሥ፡
ለሴዴቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም፡ ይህን ፡
ሁሉ፡ነገር፡ነገረው፤

፯፤ወኃይለ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ይጸብእ፡ለኢ
የሩሳሌም፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ ኢየሩሳ
ሌምን፡ይወጋታል፤

ወዲበ፡አህጉረ፡ይሁዳ፡እለ፡ተርፉ፤
በቀሩ፡በይሁዳ፡አውራጃዎችና፡

ወዲበ፡ለኪሶን፤
በለኪሶን፤

ወዲበ፡አዜቃ፡
በአዜቃም፡ይዘምትባቸዋል፤

እስመ ፡ እማንቱ ፡ ተርፋ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ፡
ይሁዳ፡አህጉር፡ፅኑዓት፡
በይሁዳ፡አውራጃዎች፡የጸኑ፡ሀገሮች፤
እነዚህ፡ቀርተዋልና፤

ጉባዔ፡

፰፤ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ እምኀበ፡
እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ ወደ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣ ፤ አንድም ፡ በኤር
ምያስ፡የተነገረ፡ነገር፡ይህ፡ነው፤



ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

እምዘ፡አኅለቀ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሥ፡ኪዳነ፡
ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፡መሐላውን፡ካጸና፡
በኋላ፡እንዲህ፡አለ፤

ኀበ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ዘውስተ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡
መሐላውን፡ካጸና፡በኋላ፤

ከመ፡ይጸውዕ፡ሎሙ፡ኅድገተ፡
አመተ ፡ ኅድገትን ፡ ያደርግላቸው ፡
ዘንድ፡ካጸና፡በኋላ፡እንዲህ፡አለ፤

፱፤ከመ፡ይፈኑ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ገብሮ፡
አንዱም፡አንዱ፡ወንድ፡ባሪያውን፤

ወ፩ዱ፡፩ዱ፡አመቶ፤
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ሴት ፡ ባሪያውን
ያሰናብት፡ዘንድ፤

ዕብራውያነ፡ወዕብራውያተ፡አግዓዝያነ፡
ዕብራውያንንና ፡ ዕብራውያት ፡ ባሮ
ቹን፡ያሰናብት፡ዘንድ፤

ከመ ፡ ኢይቅኒ ፡ ሰብእ ፡ በይሁዳ ፡ ብእሲ ፡
እኅዋሁ፤
ሰው፡በይሁዳ፡ወንድም፡ወንድሙን፡
እንዳይገዛ፡ካጸና፡በኋላ፤

፲፤ወሰምዑ፡ኵሉ፡ዓበይት፡
መኳንንቱ፡ሁሉ፤

ወኵሉ፡ሕዝብ፡እለ፡ቦኡ፡ውስተ፡ኪዳን፤
ወደ፡ሕጉ፡የገቡ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡ሰሙ፤

ይፈኑ፡፩ዱ፡፩ዱ፡ገብሮ፡
አንዱም፡አንዱ፡ወንድ፡ባሪያውን፤

ወ፩ዱ፡፩ዱ፡አመቶ፡አግዓዝያነ፤
አንዱም፡አንዱ፡ሴት፡ባሪያውን፡ነፃ፡
አውጥቶ፡ያሰናብት፡ዘንድ፡ሰሙ፤

ከመ፡ኢይቅንይዎሙ፡እንከ፡
በአመተ፡ኅድገት፤እንዳይገዟቸው፤

ወሰምዑ፡ወፈነዉ፤
ሰምተው፡አሰናበቱ፤

፲፩፤ወተመይጡ፡እምድኅረዝ፡
ካሰናበቱ፡በኋላ፡ተመልሰው፤

ወሜጡ፡አግብርቲሆሙ፡ወአዕማቲሆሙ፡
ወንዶች፡ባሮቻቸውን፡ሴቶች፡ባሮቻ
ቸውን፡ወደ፡መግዛት፡ተመለሱ፤

እለ ፡ ፈነውዎሙ ፡ አግዓዝያነ ፡ ወገቢኦሙ፡
ወረሰይዎሙ፡አግብርተ፡ወአዕማተ፤
ነፃ ፡ አውጥተው ፡ የሰደዷቸውን ፡
ተመልሰው ፡ ወንዶች ፡ ባሮችንንና ፡
ሴቶች፡ባሮችን፡አደረጓቸው፤

፲፪፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
መጣ፤ተነገረ፤

፲፫፤ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡
እሥራኤል፤
የእሥራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፤

አነ፡ሜምኩ፡ኪዳነ፡ኀበ፡አበዊክሙ፤
በአባቶቻችሁ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ሕግን ፡
ሠራሁ፡አለ፤

በዕለተ፡አውጻዕክዎሙ፡እምድረ፡ግብፅ፡
ከግብፅ፡ባወጣኋቸው፡ቀን፤

ወእምቤተ፡ቅኔ፤
ከአገዛዝም ፡ ባወጣኋቸው ፡ ቀን ፡
ሕግን፡ሠራሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወእቤ፤
እንዲህ፡አልኩ፤
አመ፡መልአ፡፮ቱ፡ዓመት፤
ስድስተኛው፡ዓመት፡በመላ፡ጊዜ፤
ትፌኑ፡እኅዋኪ፡ዕብራዌ፡ዘተሠይጠ፡ለከ፤
የተገዛልህን ፡ ዕብራዊ ፡ ወንድምህን፡
አሰናብት፤
ወይትቀነይ፡ለከ፡፮ተ፡ዓመተ፤
ስድስት፡ዓመት፡ይገዛልህ፤
ወትፌንዎ፡አግዓዚ፡እምኀቤከ፤
ከአንተ ፡ ነፃ ፡ አውጥተህ ፡ ስደደው ፡
አልሁ፤
ወኢሰምዑኒ፡አበዊክሙ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አባቶቻችሁ ፡ አልሰ
ሙኝም፤
ወኢያጽምዑኒ፡በዕዝኖሙ፤
በጆሮዋቸው፡አላደመጡኝም፤
፲፭፤ ወተመየጥክሙ ፡ አንትሙ ፡ ዮም ፡
ለገቢረ፡ርትዕ፡በቅድመ፡አዕይንትየ፤
እናንተም ፡ በፊቴ ፡ የቀና ፡ ሕግን ፡
ለማድረግ፡ተመለሳችሁ፤
ከመ፡ትጸውዑ፡ኅድገተ፤
ዓመተ፡ኅድገትን፡ታደርጉ፡ዘንድ፤
አሐዱ፡አሐዱ፡ለቢፁ፤
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለባልንጀራው ፡
ዓመተ ፡ ኅደገትን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡
ተመለሳችሁ፤
ወኀልቀ፡ኪዳን፡በቤት፡ዘተሰምየ፡ዲቤሁ፡
ስምየ፤
ስሜ፡ በተጠራበት፡ በቤተ፡ መቅደስ፡
መሐላው፡ጸና፤አንድም፡መሐላው፡ፈረሰ፤
፲፮፤ወገባዕክሙ፡ወአርኰስክሙ፡ስምየ፤
ተመልሳችሁ፡ስሜን፡አስነቀፋችሁ፤
ከመ፡ያግብዕ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ገብሮ፤
አንዱም፡አንዱ፡ወንድ፡ባሪያውን፤
ወአሐዱ፡አሐዱ፡አመቶ፤
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡
ወደ፡መግዛት፡ይመለስ፡ዘንድ፤
ዘፈነውክሙ፡ግዑዛነ፡ለነፍሶሙ፤
ለራሳቸው፡ነፃ፡አውጥታችሁ፡የሰደዳ
ችኋቸው፡ሰዎች፡ወንድ፡ባሪያውን፡
ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ወደ ፡ መግዛት ፡
ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ስሜን ፡ አስነቀ
ፋችሁ፤
ወሜጥክምዎሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑክሙ ፡
አግብርተ፡ወአእማተ፤
ወንዶች ፡ ባሮች ፡ ሴቶች ፡ ባሮች ፡
ይሆኗችሁ፡ዘንድ፡መለሳችኋቸው፤
፲፯፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡አምላከ፡እሥራኤል፤
ስለዚህ፡ነገር፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግ
ዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ኢሰማዕክሙ፡አንትሙኒ፡ከመ፡ትጸውዑ፡
ኅድገተ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ለእኁሁ፤
አንዱም፡አንዱ፡ለወንድሙ፡ዓመተ፡
ኅድገትን፡ታደርጉ፡ዘንድ፡እናንተ፡
አልሰማችሁም፡አለ፤
ወአሐዱ፡አሐዱ፡ለቢፁ፤
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለባልንጀራው ፡
ዓመተ፡ኅድገትን፡ታደርጉ፡ዘንድ፤
ናሁ፡አነ፡እጼውዕ፡ለክሙ፡ኅድገተ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፤
እነሆ፡እኔ፡ዓመተ፡ኅድገትን፡አደርግ
ላችኋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤
ውስተ፡ኲናት፤
በጦር፡መጣልን፡አመጣባችኋለሁ፤
ወውስተ፡ሞት፡ወውስተ፡ረኃብ፤
በሞትና፡በቀጠና፡መውደቅን፡አመጣ
ባችኋለሁ፤
ወእዘርወክሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ነገሥተ ፡
ምድር፤



በዚህ፡ዓለም፡ባሉ፡ነገሥታት፡ሁሉ፡
አስማርኬ፡እሰዳችኋለሁ፡አለ፤
፲፰፤ወእሁቦሙ፡ለዕደው፡እለ፡ተዓደዉ፡
ኪዳንየ፡ዘተካየዱ፡በቅድመ፡ገጽየ፤
በፊቴ፡የተማማሉበትን፡መሐላዬን፡
ለአፈረሱ፡ሰዎች፡እሰጣቸዋለሁ፤
ወእለ፡ኢያቀውሙ፡ቃለ፡ኪዳንየ፤
የመሐላዬን፡ቃል፡ለማያጸኑ፡ሰዎች፡
አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፤
ወላሕመ፡ዘመተሩ፡ለክልዔ፤
ላሙን፡ከሁለት፡የቆረጡትን፤
ወሐለፉ፡እንተ፡ማዕከለ፡መክፈልቱ፤
በተከፈለው፡መካከል፡ያለፉትን፡እጥ
ላቸዋለሁ፤ላሙን፡ከሁለት፡ከሁለት፡
ቆርጠው ፡ በመሐከል ፡ እያለፉ ፡
እንዲህ፡ይቁረጠን፡መሐላውን፡አናፈ
ርስም፡ይላሉና፤አንድም፡ወላሕመ፡
ዘመተሩ ፤ ጣዖቱን ፡ ከሁለት ፡ ያቆ
ሙትን፡ወኃለፉ፡በጣዖቱ፡መሐከል፡
ያለፉትን፡ እጥላቸዋለሁ ፤ አንዱን ፡
በዳን ፡ አንዱን ፡ በቤርሳቤህ ፡
አቁመው፡ለማምለክ፤
፲፱፤መላእክተ፡ይሁዳ፤
የይሁዳን፡አለቆችና፤
ወመላእክተ፡ኢየሩሳሌም፤
የኢየሩሳሌምን፡አለቆች፤
ሕፅዋን፤
ባለሟሎችን፤
ወካህናት፤
ካህናቱን፤
ወኵሉ፡ሕዝበ፡ምድር፡እለ፡ሐለፉ፡እንተ፡
ማዕከለ፡መክፈልቱ፡ለላሕም፤
በተከፈለው ፡ ላም ፡ መካከል ፡ ያለፉ ፡
[illegible]
መሐከል፡ያለፉትን፤
፳፤ ወእሁቦሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እለ ፡
የኃሥሥዋ ፡ ለነፍሶሙ ፡ ወውስተ ፡ እደ ፡
ፀሮሙ፤
ሰውነታቸውን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈ
ልጓት፡ሰዎች፡እጅና፡በጠላቶቻቸው፡
እጅ፡አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፤
ወእሁቦሙ ፡ አብድንቲሆሙ ፡ መብልዓ ፡
ለአዕዋፈ፡ሰማይ፡ወለአራዊተ፡ገዳም፤
ሬሣቸውን፡ቀን፡ለአዕዋፍ፤ ሌሊት፡
ለአራዊት፡ምግብ፡አድርጌ፡እሰጣቸ
ዋለሁ፤
፳፩፤ወለሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ወለመ
ላእክቲሁ፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስንና ፡
አለቆቹን ፤ እሁቦሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡
ፀሮሙ ፤ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡
አሳልፌ፡ እሰጣቸዋለሁ ፤ ወውስተ ፡
እደ፡እለ፡የኀሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤ሰው
ነታቸውን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈልጓት ፡
ሰዎች፡እጅ፡እጥላቸዋለሁ፤
ወውስተ፡እደ፡ኃይለ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡እለ፡
ዐርጉ፡እምላዕሌክሙ፤
በእናንተ፡ላይ፡በዘመቱ፡በባቢሎን፡
ንጉሥ፡ሠራዊት፡እጅ፡እጥላቸዋለሁ፤
፳፪፤ ናሁ ፡ አነ ፡ እኤዝዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እነሆ፡እኔ፡ጥፋትን፡አዝዝባቸዋለሁ፡
አለ፡እግዚአብሔር፤
ወአገብአ፡ለዛቲ፡ምድር፤
ይችን፡አገር፡በከለዳውያን፡እጅ፡እጥ
ላታለሁ፤
ወይጸብእዋ፤
ይወጓታል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይነሥእዋ፡ኪያሃ፡
እሷን፡እጅ፡ያደርጓታል፤

ወያውዕይዋ፡በእሳት፡
በእሳት፡ያቃጥሏታል፤

ወለአህጉረ፡ይሁዳሂ፡እሁቦን፡ለአብድዎ፤
የይሁዳንም ፡ አውራጃዎች ፡ ለምድረ በዳነት ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ለነጉልም፡ይላል፤

ከመ፡አልቦ፡ዘይነብሮን፡
የሚኖርባቸው፡ሰው፡እንዳይኖር።

## ምዕራፍ፡፴፭፡

፩፤ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡መጥቶ፡የተነገረ፤አንድም፡ በኤርምያስ፡የመጣ፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

በመዋዕለ ፡ ኢዮአቄም ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ንጉሠ፡ይሁዳ፡
በይሁዳው፡ንጉሥ፡በኢዮስያስ፡ልጅ፡ በኢዮአቄም፡ዘመን፡የመጣ፡የተነገረ፡ ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፤ወይቤ፡
እንዲህ፡አለ፤

ሑር፡ቤተ፡ራኬቤን፡
ወደራኬቤን፡ወገኖች፡ሒደህ፤

ወአምጽአሙ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምጣቸው፤

ወተናገሮሙ፡
ተናገራቸው፤

ወአብእሙ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ አሐቲ፡እምሕዋራት፡
ከብዙ፡መደቦች፡አንዷት፡ወደሆነች፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መደብ፤ አግባቸው፤

ወአስትዮሙ፡ወይነ፡
ወይን፡አጠጣቸው፡አለ፤

፫፤ወነሣእክዎሙ፡ወአምጻእክዎሙ፡ለኢያዛንያን፡ወልደ፡ኢያሬምያን፡
የኢያሬምያን፡ልጅ፡የሚሆን፡ኢያዛን ያንን፤

ወልደ፡ከበሲን፡
የከበሲን ፡ ልጅ ፡ የሚሆን ፡ የኢያሬ ምያን፡ልጅ፤

ወለአኃዊሁ፡
ወንድሞቹን፤

ወለደቂቁ፡
ልጆቹን፤

ወለኵሉ፡ቤተ፡ራኬቤን፡
የራኬቤንን፡ወገኖች፡ሁሉ፡አያ ኀቼ፤

፬፤ወአባእክዎሙ፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ጽስጦፎርያል ፡ ለደቂቀ፡ ሐናን፡
የሐናን፡ልጆች፡የሚጠብቁት፡ዕቃ፡ ቤት ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአ ብሔር፡አገባኋቸው፤

ወልደ፡ጌዴልያ፡
የጌዴልያ ፡ ልጅ ፡ ብሎ ፡ ለሐናን ቀጠለ፤

ብእሲ፡ዘእግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡የሾመው፤

ዘውእቱ፡ቅሩብ፡ኀበ፡ሕዋረ፡መላእክት፡ዘመልዕልተ፡ጽርስፎራ፡ማሴው፡ወልደ፡ሴሎም፡ ዘየአቅብ፡አንቀጸ፡
በሩን ፡ የሚጠብቅ ፡ የሴሎም ፡ ልጅ ማሴው ፡ ከሚጠብቀው ፡ ከኀብስተ



ገጹ ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ አለቆች ፡ በሚቀመ ጡበት ፡ አጠገብ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር፡አገባኋቸው፤

፭፤ ወወሀብኩ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ለቤተ ፡ ራኬብ፡ጸሕባተ፡ምሉዓነ፡ወይን፡
ለራኬቤን ፡ ወገኖች ፡ በፊታቸው ፡ ወይንን ፡ የተመሉ ፡ ፊቀኖችን ፡ ሰጠኋቸው፤

ወጽዋዓተ፡
ጽዋውን፡ሰጠኋቸው፤

ወእቤ፡ስትዩ፡ወይነ፡
ወይኑን፡ጠጡ፡አልኋቸው፤

፮፤ወይቤሉ፡ኢንሰቲ፡ወይነ፡
ወይን፡አንጠጣም፡አሉኝ፤

እስመ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ወልደ ፡ ራኬብ ፡ አቡነ ፡ አዘዘነ፡
የራኬብ ፡ ልጅ ፡ የሚሆን ፡ አባታችን ፡ ኢዮናዳብ፡አዝዞናልና፤

ወይቤለነ፡ኢትስተዩ፡ወይነ፡አንትሙ፡ወደቂቅክሙ፡እስከ፡ለዓለም፤
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ እናንተም ፡ ልጆቻ ችሁም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ወይን ፡ አት ጠጡ፡ብሎ፡አዝዞናልና፤

፯፤ቤተ፡ኢትሕንፁ፡
ቤት፡አትሥሩ፤

ወዘርዓ፡ኢትዝርዑ፤
ዘር፡አትዝሩ፤

ወወይነ፡ኢትትክሉ፤
ወይንም፡አትትከሉ፡ብሎ፡አዝዞናል፡ አሉ፤

እስመ ፡ በደባትር ፡ ተኀድሩ ፡ ኵሎ ፡ መዋዕ ሊክሙ፤
ባለ ፡ በዘመናችሁ ፡ ሁሉ ፡ በድንኳን ፡ ትኖራላችሁና፤

ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡ ውስተ ፡ ምድር፡ዘሖርክሙ፡አንትሙ፡ውስቴታ፡
እናንተ ፡ በሔዳችሁባት ፡ በምድር ፡ ብዙ፡ዘመን፡ትኖሩ፡ዘንድ፤

፰፤ ወሰማዕነ ፡ ቃለ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ወልደ ፡ ራኬብ፡አቡነ፡
የራኬብ ፡ ልጅ ፡ የአባታችን ፡ የኢዮና ዳብን፡ቃል፡ሰማን፤

በዘኢንሰቲ፡ወይነ፡ኵሎ፡መዋዕሊነ፡
ባለ ፡ በዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ ወይን ፡ ባንጠጣ፡ገንዘብ፤

ንሕነ፡ወአንስቲያነ፡
እኛም፡ሚስቶቻችንም፤

ወደቂቅነ፡ወአዋልዲነ፡
ወንዶች፡ልጆቻችንም፡ሴቶች፡ልጆቻ ችንም፡ወይን፡ባንጠጣ፡ገንዘብ፡የአባ ታችን፡የኢዮናዳብን፡ቃል፡ሰማን፤

፱፤ኢለነዲቅ፡አብያተ፡
ቤት፡እንዳንሠራ፤

ወኢለነቢር፡ህየ፡
ከዚያ፡እንዳንኖር፤

ወወይን፡
ወይን፡እንዳንጠጣ፤

ወገራህት፡
እርሻ፡እንዳናርስ፤

ወዘርዕ፡ኢኮነ፡ለነ፡
ዘር ፡ እንዳንዘራ ፡ እንዳልተገባን ፡ ሰማን፤

፲፤ወኀደርነ፡በደባትር፡
በድንኳን፡ኖርን፤

ወሰማዕነ፡ወገበርነ፡ኵሎ፡
ሰምተን፡ሁሉን፡አደረግን፤

በከመ፡አዘዘነ፡ኢዮናዳብ፡አቡነ፤

www.ethiopianorthodox.org

አባታችን፡ኢዮናዳብ፡እንደ፡አዘዘን፡
አደረግን፤

፲፩፤ ወኮነ ፡ አመ ፡ ዓርገ ፡ ናቡከደነፆር ፡
ንጉሠ፡ባቢሎን፡ዲበ፡ምድር፤
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፡ወደ፡
ምድር፡በዘመተ፡ጊዜ፡እንዲህ፡ሆነ፤

ወይቤሉነ፡ባእ፤
ግቡ፡አሉን፤

ወቦእነ፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም፡እምገጸ፡ኃይለ፡
ከለዳውያን፤
ከከለዳውያን፡ሠራዊት፡ጦር፡የተነሣ፡
ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ገባን፤

ወእምገጸ፡ኃይለ፡አራም፤
ይኸውም፡ወደ፡ከተማ፡መግባታችን፡
ከሦርያ፡ሠራዊት፡ጦር፡የተነሣ፡ነው፤

ወነበርነ፡ህየ፡በኢየሩሳሌም፤
ከዚያ፡በኢየሩሳሌም፡ኖርን፤

፲፪፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
መጥቶ፡ተነገረ፤

ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

፲፫፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ሑር፡ወበሎሙ፡ለሰብአ፡ይሁዳ፤
ሂደህ፡የይሁዳን፡ሰዎች፤

ወለእለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም፡የሚኖሩትን፡እንዲህ፡
በላቸው፤

ኢትነሥኡኑ፡ትእምርተ፡ለሰሚዐ፡ነገርየ፡
የእኔን፡ነገር፡ለመስማት፡ምልክት፡
አታደርጉምን፡(አትይዙምን)፡ብት
ልም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፲፬፤ቆመ፡ቃለ፡ኢዮናዳብ፡ወልደ፡ራኬብ፤
የራኬብ፡ልጅ፡የኢዮናዳብ፡ቃልስ፡
እንኳ፡ጸና፤

ዘአዘዘሙ፡ለደቂቁ፡ኢይስተዩ፡ወይነ፤
ወይን ፡ እንዳይጠጡ ፡ ልጆቹን ፡
ያዘዛቸው፡የኢዮናዳብ፡ቃልስ፡እንኳ፡
ጸና፤

ወኢሰትዩ፡ወይነ፡እንከ፡እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡
እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ወይን ፡
አልጠጡም፤

እስመ ፡ ሰምዑ ፡ ትእዛዘ ፡ ኢዮናዳብ ፡
አቡሆሙ፤
የአባታቸው፡የኢዮናዳብን፡ትእዛዝ፡
ሰምተዋልና፤

ወአነ፡ነበብኩ፡በእንቲአክሙ፡በጽባሕ፡
እኔም ፡ ፈጥኜ ፡ የእናንተን ፡ ነገር፡
ተናገርሁ፤

ወነበብኩ፡ወኢሰማዕክሙኒ፤
ተናገርኩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሰማች
ሁኝም፤እኔን፡ከራኬብ፡አሣንሳችሁ፡
እናንተ፡ከልጆቹ፡አንሣችሁ፡አልሰማ
ችሁኝምና ፡ የኢዮናዳብ ፡ ቃልስ፡
እንኳ፡ጸና፤

፲፭፤ ወፈነውኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ አግብርትየ፡
ነቢያተ፤
አገልጋዮቼን ፡ ነቢያትን ፡ አስተምሩ፡
ብዬ፡ወደ፡እናንተ፡ሰደድሁ፤

ወእቤ ፡ ግብኡ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምፍ
ትክሙ፡እኩይ፤
አንዳንድም ፡ አንዱ ፡ ከክፉ ፡ ሥራችሁ፡
ተመለሱ፡አልሁ፤



ወሕሊናክሙ፡ሠናየ፡ግበሩ፤
በጎ፡ሐሳብን፡አስቡ፤

ወኢትሑሩ፡ድኅረ፡አማልክተ፡ነኪር፤
ጣዖት፡አታምልኩ፤

ኢትትቀነዩ፡ሎሙ፤
አትገዙላቸው፡አልሁ፤

ወተኀድሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ወሀብኩ ፡
ለክሙ፤
እንዲህ ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡
ለእናንተ፡በሰጠኋችሁ፡በምድር፡ትኖ
ራላችሁ፤

ወለአበዊክሙ፤
ለአባቶቻችሁም ፡ በሰጠኋት ፡ ሀገር ፡
ትኖራላችሁ፡አልሁ፤

ወኢያጽማዕክሙ፡በዕዘኒክሙ፤
ነገር፡ግን፡አላደመጣችሁም፤

ወኢሰማዕክሙኒ፤
አልሰማችሁኝም፤

፲፮፤ወዓቀሙ፡ደቂቀ፡ኢዮናዳብ፡ወልደ፡
ራኬብ፡ትእዛዘ፡አቡሆሙ፡ዘአዘዞሙ፤
የራኬብ፡ልጅ፡የኢዮናዳብ፡ልጆች፡
አባታቸው ፡ የአዘዛቸውን ፡ ትእዛዝ ፡
አጸኑ፤

ወኢሰምዑ፡ዝንቱ፡ሕዝብ፤
እነዚህ፡ወገኖች፡አልሰሙም፤

፲፯፤ወበእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡ፀባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡አመጽእ፡ለይሁዳ፤
እነሆ፡እኔ፡ለሁለቱ፡ነገድ፤

ወለኵሉ፡እለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም፡በሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፤
ኵሎ፡እኩየ፡ዘነበብኩ፡ላዕሌሆሙ፤
በእነሱ ፡ ላይ ፡ የተናገርሁትን ፡
ክፉውን፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አመጣለሁ ፡
አለ፤

እስመ፡ተናገርክዎሙ፡ወኢሰምዑኒ፤
ብናገራቸው፡አልሰሙኝምና፤

ወጸዋዕክዎሙ፡ወኢያውሥኡኒ፤
በነቢያት፡አድሬ፡ብጠራቸው፡አልመ
ለሱልኝምና፤

፲፰፤ወለቤተ፡ራኬብ፡ይቤ፡ኤርምያስ፤
ለራኬብ ፡ ወገኖች ፡ ኤርምያስ ፡
እንዲህ፡አለ፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት ፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

እስመ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ቃለ ፡ ኢዮናዳብ ፡
አቡክሙ፤
የአባታችሁ፡የኢዮናዳብን፡ቃል፡ሰም
ታችኋልና፤

ወአቀብክሙ፡ኵሎ፡ትእዛዞ፤
ትእዛዙን፡ሁሉ፡ጠብቃችኋልና፤

ወገበርክሙ፡ኵሎ፡ዘአዘዘክሙ፤
ያዘዛችሁን፡ሁሉ፡አድርጋችኋልና፤

፲፱፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡ፀባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፤
ስለዚህ፡ነገር፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግ
ዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ብእሲ ፡ ኢየኀልቅ ፡ እምደቂቀ ፡ ኢዮናዳብ ፡
ወልደ፡ራኬብ፤
ከራኬብ፡ልጅ፡ከኢዮናዳብ፡ልጆች፡
ሰው ፡ አይጠፋም ፡ ኢያኀለቅ ፡ ቢል ፡
ሰውን፡አላጠፋም፡አለ፤

ዘይቀውም፡ቅድመ፡ገጽየ፡በኵሉ፡መዋዕል፤

www.ethiopianorthodox.org

ባለ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ በባለሟ
ልነት፡የሚቆም፡ከኢዮናዳብ፡ልጆች፡
ሰው፡አይጠፋም፡አለ።

## ምዕራፍ፡፴፮፤

### ጉባዔ፤

፩፤ወኮነ፡በራብዒት፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡
ለኢዮአቄም ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ንጉሠ ፡
ይሁዳ፤
የይሁዳው፡ንጉሥ፡የኢዮስያስ፡ልጅ፡
ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛዪቱ ፡
ዘመን፡እንዲህ፡ሆነ፤
ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀበ፡ኤርምያስ፤
ቃል ፡ ኮነ ፡ ያለውን ፡ ኮነ ፡ ብሎ ፡
አመጣው ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ታዝዞ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የእግ
ዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፤ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤
ንሣእ፡ክርታሰ፡መጽሐፍ፤
መጽሐፍ ፡ የሚሆነውን ፡ መጽሐፍ ፡
የሚጻፍበትን፡ወረቀት፡አምጥተህ፤
ወጸሐፍ ፡ ውስቴቱ ፡ ኵሎ ፡ ዘነበብኩ ፡ ላዕለ፡
እስራኤል፡ኀቤከ፤
በአንተ ፡ ዘንድ ፡ በእሥራኤል ፡ ላይ ፡
የተናገርሁትን፡ሁሉ፡ጻፍ፤
ወላዕለ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ፡ሰዎች፤
ወላዕለ፡ኵሉ፡አሕዛብ፤
በአሕዛብ፡ሁሉ፡ላይ፡የተናገርሁትን፡
ጻፍ፤
እምዕለት፡ ዘነበብኩ ፡ ለከ ፡ እምአመ ፡
መዋዕለ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡ወእስከ፡
እምዕለትና ፡ እመአመ ፡ መዋዕለ ፡
ኢዮስያስ፡አንድ፡ወገን፤የይሁዳው፡
ንጉሥ፡ኢዮስያስ፡ከነገሠበት፡ቀን፡
ጀምሮ፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡የተናገር
ሁትን፡ጻፍ፡አለው፤ኤርምያስ፡በነቢ
ይነት፡መነሣቱ፡ኢዮስያስ፡ከነገሠ፡
ከአሥራ፡ሦስት፡ዘመን፡ጀምሮ፡ነውና፤

፫፤ እመ ፡ ይሰምዑ ፡ ቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ኵሎ፡
እኩየ፡ዘነበብኩ፡ላዕሌሆሙ፤
የይሁዳ፡ሰዎች፡በነሱ፡ላይ፡የተናገር
ሁትን፡ክፉውን፡ነገር፡ሁሉ፡ይሰሙ፡
እንደሆነ፤
ወዘሐለይኩ ፡ ከመ ፡ ይሰወጡ ፡ እምእከየ፡
ፍኖቶሙ፤
ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ፡
ያሰብኩትን፡ይሰሙ፡እንደሆነ፡ጻፍ፤
አንድም፡እመ፡ይሰምዑ፡ቤተ፡ይሁዳ፤
የይሁዳ፡ወገኖች፡በነሱ፡ላይ፡የተናገር
ሁትን፡ክፉውን፡ነገር፡ሁሉ፡ቢሰሙ፤
ወዘሐለይኩ ፡ ከመ ፡ ይሰወጡ ፡ እም
እከየ ፡ ፍኖቶሙ ፤ ከክፉ ፡ ሥራቸው፡
ይመለሱ፡ዘንድ፡ያሰብኩትን፡ቢሰሙ፤
ወእሠሃል፡ዲበ፡ኃጢአቶሙ፡ወጌጋዮሙ፤
በኃጢአታቸው፡የመጣውን፡መከራ፡
ይቅር፡እላለሁ፤ኃጢአታቸውን፡በደላ
ቸውን፡ይቅር፡እላለሁ፡ብትልም፤

፬፤ ወጸውዖ ፡ ኤርምያስ ፡ ለባሮክ ፡ ወልደ፡
ኔርዩ፤
ኤርምያስ ፡ የኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ባሮክን፡
ጠራው፤
ወጸሐፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ባሮክ ፡ እምአፈ፡
ኤርምያስ፤
ባሮክም ፡ ከኤርምያስ ፡ አ…



ኵሎ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ዘነበበ፡ኀቤሁ፡
በክርታሰ፡መጽሐፍ፤
መጽሐፍ፡በተጻፈበት፡ወረቀት፡በሱ፡
ዘንድ ፡ የተናገረውን ፡ የእግዚአብ
ሔርን፡ነገር፡ሁሉ፡ጻፈ፤

፭፤ ወአዘዞ ፡ ኤርምያስ ፡ ለባሮክ ፡ ወልደ ፡
ኔርዩ፤
ኤርምያስ ፡ የኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ባሮክን ፡
አዘዘው፤
ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤
አነ፡ሙቁሕ፤
እኔ፡እንዳልሔድ፡ታሥሬያለሁ፤
ወኢይክል ፡ በዊአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መግባት ፡
አይቻለኝም፡አለው፤

፮፤ወትበውእ፡አንተ፤
አንተ፡ገብተህ፤
ወታነብብ፡ዘንተ፡ክርታሰ፡ዘጸሐፍከ፡እም፡
አፉየ፤
ካንደበቴ ፡ እየሰማህ ፡ የጻፍከውን ፡
ይህን፡ወረቀት፡አንብብ፤
ነገረ፡እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔር፡ነገር፡አንብብ፤
ውስተ፡ዕዝነ፡ሕዝብ፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአ
ብሔር፡በዕለተ፡ጾም፤
ሕዝቡ ፡ ሲሰሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ማደሪያ፡በቤተ፡መቅደስ፡በታኅሣሥ፡
በዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ጾመ ፡ አስተርዕዮን ፡
ይጾማሉና፡በሚሰበሰቡበት፡ቀን፡አን
ብብላቸው፡አለው፤
ከየሀገራቸው ፡ የመጡ ፡ የይሁዳ ፡
ሰዎች፡ሁሉ፡ሲሰሙ፤
ወታነብብ፡በቅድሜሆሙ፤
በፊታቸው፡አንብብላቸው፡አለው፤

፯፤ እመ ፡ ቦ ፡ ከመ ፡ ይወድቅ ፡ ሣህሎሙ ፡
ቅድመ፡እግዚአብሔር፤
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይቅር ፡
ይላቸው፡እንደሆነ፤
ወይገብኡ፡እምእኩይ፡ፍኖቶሙ፤
ከክፉ ፡ ሥራቸውም ፡ ይመለሱ ፡
እንደሆነ፡አንብብላቸው፤
እስመ፡ዓቢይ፡መቅሥፍተ፡መዓቱ፡ለእግዚ
አብሔር፡ዘነበበ፡በውእቶሙ፡ሕዝብ፤
በነዚህ ፡ ወገኖች ፡ የተናገረ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ተቈጥቶ ፡ ያመጣው ፡
መቅሥፍት፡ጽኑ፡ነውና፤

፰፤ወገብረ፡ባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፤
የኔርዩ፡ልጅ፡ባሮክ፡እንዲህ፡አደረገ፤
በከመ፡ኵሉ፡ዘአዘዞ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ እንደ ፡ አዘዘው ፡
አደረገ፤
ከመ ፡ ያንብብ ፡ በመጽሐፍ ፡ ነገረ ፡ እግዚአ
ብሔር፡በቤተ፡እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔርን፡ነገር፡በቤተ፡እግዚ
አብሔር፡በመጽሐፍ፡ያነብብ፡ዘንድ፤

፱፤ወኮነ፡በዓመት፡ኃምሲት፡እምዘነግሠ፡
ኢዮአቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
የይሁዳው፡ንጉሥ፡የኢዮስያስ፡ልጅ፡
ኢዮአቄም፡በነገሠ፡በአምስተኛዪቱ፡
ዘመን፡እንዲህ፡ሆነ፤
በታስዕ፡ወርኅ፤
በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በታኅሣሥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሰበኩ፡ጾመ፡ከመ፡ይጾሙ፡ቅድመ፡እግዚ
አብሔር፡
በእግዚአብሔር፡ፊት፡ጾም፡ይጾሙ፡
ዘንድ፡ጾም፡እንጹም፡ብለው፡አዋጅ፡
ነገሩ፤

ኵሉ፡ሕዝብ፡በኢየሩሳሌም፡
በኢየሩሳሌም፡ያሉ፡ሕዝቡ፤

ወኵሉ፡ሕዝብ፡እለ፡መጽኡ፡እምይሁዳ፡
ከይሁዳ ፡ የመጡ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
አዋጅ፡ነገሩ፤

፲፤ ወአንበበ ፡ ባሮክ ፡ ውእተ ፡ መጽሐፈ ፡
ዘነገሮ፡ኤርምያስ፡በቤተ፡እግዚአብሔር፡
ባሮክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡
በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ኤርምያስ ፡ የነገ
ረውን፡መጽሐፉን፡አነበበ፤

በሕዋረ፡ገማርዩ፡ወልደ፡ሳፉን፡ጸሐፊ፡
በጸሐፊው፡በሳፉን፡ልጅ፡በገማርዩ፡
መደብ፡አነበበ፤

በዐፀድ፡ዘላዕሉ፡
በአምስቱ፡በስድስቱ፡በሰባቱ፡ቆመ፡
ብእሲ፤

በአንቀጽ ፡ ውስተ ፡ ዶዴ ፡ ቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ሐዲስ፡
አዲስ ፡ በሚሆን ፡ በቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ዓደባባይ ፡ አነበበ ፤ አዲስ ፡
አለው፡አሳፍ፡አሠርቶት፡ነበርና፤

በዕዝነ፡ኵሉ፡ሕዝብ፤
ሕዝቡ፡ሁሉ፡ሲሰሙ፡አነበበላቸው፤

፲፩፤ወሰምዐ፡ሚክያስ፡ወልደ፡ገማርዩ፡
የገማርዩ፡ልጅ፡ሚክያስ፡ሰማ፤

ወልደ፡ሳፉን፡
የሳፉን፡ልጅ፤

ዘ፡ኵሎ፡ነገረ፡እግዚአብሔር፡እመጽሐፍ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ከመጽሐፍ፡ሰማ፤

፲፪፤ ወወረደ ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ኀበ ፡ ሕዋረ ፡
ጸሐፊ፡
ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጸሐፊው ፡
መደብ፡ወረደ፤

ወናሁ፡ህየ፡ኵሉ፡መላእክት፡ይነብሩ፡
እነሆ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡
ተቀምጠው፡ነበር፤

ኤሊሲማዕ፡ጸሐፊ፡
ጸሐፌ፡ትእዛዝ፡ኤሊሲማዕ፤

ወመዳልያስ፡ወልደ፡ሴዴምዩ፡
የሴዴምዩ፡ልጅ፡መዳልያስ፤

ወዮናታን፡ወልደ፡አክቦር፡
የአክቦር፡ልጅ፡ዮናታን፤

ወገማርዩ፡ወልደ፡ሳፉን፡
የሳፉን፡ልጅ፡ገማርዩ፤

ወሴዴቅያ፡ወልደ፡ሐናንያ፡
የሐናንያ፡ልጅ፡ሴዴቅያ፤

ወኵሎሙ፡መላእክት፡
አለቆች፡ሁሉ፡ከዚህ፡ተቀምጠው፡
ነበር፤

፲፫፤ ወአይድዐ ፡ ሚክያስ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡
ዘሰምአ፡
ሚክያስ ፡ የሰማውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ተናገረ፤

ሶበ፡አንበበ፡ባሮክ፡መጽሐፈ፡ውስተ፡ዕዝነ፡
ሕዝብ፡
ሕዝቡ፡ሲሰሙ፡ባሮክ፡መጽሐፉን፡
በአነበበ፡ጊዜ፡የሰማውን፡ተናገረ፤

፲፬፤ ወፈነዉ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ ኀበ ፡
ባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፡
አለቆች፡ሁሉ፡ወደ፡ኔርዩ፡ልጅ፡ወደ፡
[illegible]



ይሁዳሃ፡ወልደ፡ናታንዩ፡
የናታንዩ፡ልጅ፡ይሁዳን፡ላኩ፤

ወልደ፡ሴልምዩ፡
ናታንዩን፡የሴልምዩ፡ልጅ፡አለው፤

ወልደ፡ኩሲ፡
ሴልምዩን፡የኩሲ፡ልጅ፡አለው፤

ወይቤልዎ፡
እንዲህ፡አሉት፤

ክርታሰ፡ዘአንበብከ፡ውስተ፡ዕዝነ፡ሰብእ፡
ሰዎች ፡ ሲሰሙ ፡ ያነበብከውን ፡
ወረቀት፤

ንሣእ፡በእዴከ፡ወነዓ፡
በእጅህ፡ይዘህ፡ና፡አሉት፤

ወነሥአ ፡ ባሮክ ፡ ወልደ ፡ ኔርዩ ፡ መጽሐፈ ፡
በእዴሁ፡
የኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ መጽሐፉን ፡
በእጁ፡ይዞ፤

ወወረደ፡ውስቴቶሙ፡
ወደ፡እነሱ፡ወረደ፤

፲፭፤ወይቤልዎ፡
እንዲህ፡አሉት፤

ንበር፡እስኩ፡ወአንብብ፡በዕዘኒነ፡
እስኪ ፡ ተቀምጠህ ፡ ስንሰማ ፡ አንብ
ብልን፡አሉት፤

ወአንበበ፡ባሮክ፡ውስተ፡ዕዘኒሆሙ፤
ሲሰሙ፡ባሮክ፡አነበበላቸው፤

፲፮፤ወኮነ፡ሶበ፡ሰምዑ፡ኵሎ፡ዘ፡ነገረ፡
ሁሉም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
እንዲህ፡ሆነ፤

ፈርሁ፤
ኮነ፡ያለውን፡ፈርሁ፡ብሎ፡አመጣው፡
እጅግ፡ፈሩ፤
[illegible]

አንዱም ፡ አንዱም ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡
ተማከሩ፤

ወይቤልዎ፡ለባሮክ፡
ባሮክን፡እንዲህ፡አሉት፤

ነጊረ፡ንነግሮ፡ለንጉሥ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ነገረ፤
ይህንንማ፡እኛ፡ብቻ፡ሰምተነው፡ይቀ
ራልን፡ለንጉሡም፡እንንገረው፡አሉ፤

፲፯፤ወተስእልዎ፡ለባሮክ፤
ባሮክን፡ጠየቁት፤

ወይቤልዎ፤
እንዲህ፡አሉ፤

ንግረነ፡እስኩ፤
እስኪ፡ንገረን፤

እፎኑ፡ጸሐፍከ፡ዘ፡ነገረ፡ኵሎ፤
ይህንን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደምን ፡
አድርገህ፡ጻፍኸው፡አሉት፤

፲፰፤ወይቤ፡ባሮክ፤
ባሮክ፡እንዲህ፡አለ፤

እምአፉሁ ፡ አይድዓኒ ፡ ኤርምያስ ፡ ዘ ፡ ኵሎ ፡
ነገረ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ኤርምያስ ፡ ከአን
ደበቱ፡አውጥቶ፡ነገረኝ፡አላቸው፤

ወጸሐፍኩ፡በመጽሐፍ፡በእዴሁ፤
በእርሱ፡ቃል፡መጽሐፉን፡ጻፍኩ፤
አንድም ፡ በእዴየ ፡ ይላል ፤ ከእርሱ ፡
እየሰማሁ፡በእጄ፡ጻፍሁ፡አለ፤

፲፱፤ወይቤልዎ፡መላእክት፡ለባሮክ፡
አለቆች፡ባሮክን፡እንዲህ፡አሉት፤

ሑር፡ወተኀባዕ፡አንተ፡ወኤርምያስ፤
አንተና፡ኤርምያስ፡ተሠወሩ፤

ሰብእ፡ኢይርአይክሙ፡አይቴ፡አንትሙ፤
እናንተ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡
ሰው፡አይያችሁ፡አሉት፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፤ወቦኡ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ዓፀደ፤
ንጉሥ፡ወደ፡አለበት፡ቦታ፡ገቡ፤
ወመጽሐፈኒ ፡ አዕቀቡ ፡ ውስተ ፡ ሕዋረ ፡
ኤሊሲማዕ፡ጸሐፊ፤
መጽሐፉንም ፡ በጸሐፊው ፡ በኤሊ
ሲማዕ፡መደብ፡አስቀመጡ፤
ወነገርዎ፡ለንጉሥ፡ዘ፡ኵሎ፡ነገረ፤
ነገሩን፡ሁሉ፡ለንጉሥ፡ነገሩት፤

፳፩፤ ወፈነዎ ፡ ንጉሥ ፡ ለይሁዳ ፡ ይንሣእ ፡
ክርታሰ፤
ወረቀቱን ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡
ይሁዳን፡ላከው፤(ሰደደው)፤
ወነሥአ ፡ እምሕዋረ ፡ ኤሊሲማዕ ፡ ጸሐፊ ፡
ይሁዲ፤
ይሁዲም ፡ ይለዋል ፡ ይሁዳም ፡
ይለዋል፤ ከጸሐፊው ፡ ከኤሊሲማዕ ፡
መደብ፡አመጣ፤
ወአንበበ፡ውስተ፡ዕዝነ፡ንጉሥ፤
ንጉሥ፡ሲሰማ፡አነበበው፤
ወውስተ ፡ ዕዝነ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡
ይቀውሙ፡ቅድመ፡ንጉሥ፤
በንጉሥ፡ፊት፡የሚቆሙ፡አለቆችም፡
ሲሰሙ፡አነበበ፤

፳፪፤ ወንጉሥ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡
ምክራም፡በታስዕ፡ወርኅ፤
ንጉሡ ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ክረምት ፡
በሚቀመጥበት ፡ ቤት ፡ ተቀምጦ ፡
ነበር፤ ቤተ፡ምክራም፡የሚለው፡የእስ
ራኤል ፡ ነገሥታት ፡ በጋ ፡ ከደጋ ፤
ከደርብ ፤ ክረምት ፡ ከምድር ፡ ቤት ፤
ከቆላ፡ይከርማሉና፤
ወአፍሐመ ፡ እሳት ፡ ቅድሜሁ ፡ ይነድድ፤
በብረት፡ማንደጃ፡ሆኖ፡እሳት፡በፊቱ፡
ይነድድ፡ነበር፤

፳፫፤ ወኮነ፡ሶበ፡አንበበ፡ይሁዳ፡ሠለስተ፡
ሠሌዳተ፡ወአርባዕተ፤
ይሁዳ፡ሦስት፡ቅጠል፡አራት፡ቅጠል፡
አንድም ፡ ሦስት ፡ ጥራዝ ፡ አራት ፡
ጥራዝ ፡ በአነበበ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡
ሆነ፤
መተሮ፡በመጥባሕተ፡ጸሐፊ፡ንጉሥ፤
በመጥባሕተ ፡ ኤሊሲማዕ ፡ ጸሐፊ ፡
ይላል ፤ ንጉሥ ፡ በጸሐፊው ፡ በኤሊ
ሲማዕ ፡ ወቅለምት ፡ አርፎ ፡ አርፎ፤
(ቆርጦ፡ቆርጦ)
ወወገሮ፡ውስተ፡እሳት፡ዘአፍሐም፤
ፍም፡ባለበት፡እሳት፡ጣለው፤
እስከ ፡ ሐልቀ ፡ ኵሉ ፡ ክርታስ ፡ በእሳት፡
ዘአፍሐም፤
ወረቀቱ፡ሁሉ፡ፍም፡ባለበት፡እሳት፡
እስኪፈጸም፡ድረስ፡ጣለው፤

፳፬፤ ወኢደንገፁ ፡ ወኢሠጠጡ ፡ አልባ
ሲሆሙ፡ንጉሥ፡ወኵሉ፡አግብርቲሁ፤
ንጉሥና ፡ አገልጋዮቹ ፡ ሁሉ ፡ አልደነ
ገጡም ፡ ልብሳቸውንም ፡ አልቀ
ደዱም፡አላሰለቡም፤
እለ፡ሰምዑ፡ውእተ፡ነገረ፤
ይህንን፡ነገር፡የሰሙ፡አገልጋዮቹ፤

፳፭፤ወኤልያታንሂ፡ወጎዶልያ፤
ኤልያታንና፡ጎዶልያ፤
ወገማርያ፤
ገማርያ፤
ረሰይዎ፡ለንጉሥ፡ከመ፡ኢያውዒ፡ክርታሰ፤
ወረቀቱን ፡ እንዳያቃጥል ፡ ንጉሥን፡
ለመኑት ፡ ማለዱት፤ አንድም ፡ ኢረ
ሰይዎ፡ይላል፤ወረቀቱን፡እንዳያቃጥል፡
አልለ[illegible]ም፤



ወኢሰምዖሙ፡ንጉሥ፤
ንጉሥ፡አልሰማቸውም፤

፳፮፤ወአዘዞ፡ንጉሥ፡ለኢርምያል፡ወልደ፡
ንጉሥ፤
ንጉሥ፡የንጉሥ፡ልጅ፡ኢርምያልን፤
ወለሴርያ፡ወልደ፡አዜርኤል፤
የአዜርኤል፡ልጅ፡ሴርያልን፤
ወለሴልምያ፡ወልደ፡አብዲኤል፤
የአብዲኤል ፡ ልጅ ፡ ሴልምያን ፡
አዘዛቸው፤
ይንሥእዎ፡ለባሮክ፡ጸሐፊ፤
ጸሐፊው፡ባሮክን፡ይይዙት፡ዘንድ፤
ወለኤርምያስ፡ነቢይ፤
ነቢዩ ፡ ኤርምያስንም ፡ ያመጡት ፡
ዘንድ፡አዘዘው፤
ወሠወሮሙ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ግን፡ሠወራቸው፤

፳፯፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፤
ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል፡መጣ፡ተነገረ፤
እምድኅረ፡አውዓየ፡ንጉሥ፡ክርታሰ፤
ንጉሥ፡ወረቀቱን፡ካቃጠለ፡በኋላ፤
ወቃለ ፡ ነገር ፡ ዘጸሐፈ ፡ ባሮክ ፡ እምአፈ ፡
ኤርምያስ፤
ከኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እየሰማ ፡ ባሮክ ፡
የጻፈውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡
ካቃጠለ፡በኋላ፡ተነገረ፤
ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

፳፰፤ንሣእ፡ለከ፡ካዕበ፡ክርታሰ፡ካልአ፤
ሁለተኛ ፡ ሌላ ፡ ወረቀት ፡ ተቀብለህ ፡
[illegible]ዐ፤

ወጸሐፍ፡ውስቴቱ፡ኵሎ፡ነገረ፡ዘቀዳሚ፤
የቀደመውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡
ጻፍ፡አለው፤
ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ክርታስ ፡ ዘአውዓየ ፡
ኢዮአቄም፡ንጉሥ፤
ንጉሡ ፡ ኢዮአቄም ፡ በአቃጣለው ፡
ወረቀት፡ያለውን፡ሁሉ፡ጻፍ፡አለው፤

፳፱፤ወለኢዮአቄም፡ንጉሥ፡ትብሎ፤
ንጉሡን፡ኢዮአቄምን፡እንዲህ፡በለው፤
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
አንተ፡አውዓይከ፡ክርታሰ፤
አንተ፡ወረቀቱን፡አቃጠልክ፤
እንዘ፡ትብል፤
እንዲህ፡ብለህ፤
ለምንት፡ጸሐፍከ፡ቦቱ፡እንዘ፡ትብል፡በዊአ፡
ይበውእ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ለሠርዎ፡ምድር፡
ዝንቱ፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
ይህን፡ ሀገር ፡ ለማጥፋት ፡ ይገባል ፡
ስትል ፡ ለምን ፡ ጻፍክ ፡ ብለህ ፡
ወረቀቱን፡ አቃጠልክ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፡በለው፤
ወየኀልቁ፡ሰብእ፡ወእንስሳ፤
ሰዎችም ፡ ከብቶችም ፡ ያልቃሉ ፡
ብለህ፡ለምን፡ጻፍክ፤

፴፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤
ለኢዮአቄም፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
ለይሁዳው፡ንጉሥ፡ለኢዮአቄም፤
ኢይቀውም ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡
መንበረ፡ዳዊት፤

www.ethiopianorthodox.org

በዳዊት፡ዙፋን፡ነግሦ፡የሚኖር፡ልጅ፡
አይተካለትም፤

ወበድኑ ፡ ይትገደፍ ፡ ለላህበ ፡ መዓልት ፡
ወለቍረ፡ሌሊት፤
ሬሳውም ፡ ቀን ፡ በሐሩር ፡ ሌሊት ፡
በቍር፡ይወድቃል፤

፴፩፤ወእሔውጽ፡ላዕሌሁ፤
እሱን፡በመዓት፡እጐበኛለሁ፤

ወላዕለ፡ዘርዑ፤
ወገኖቹንም፤

ወዲበ፡አግብርቲሁ፡ኀጢአቶሙ፤
እሱን፡በበደሉበት፡በኃጢአታቸው፡
አገልጋዮቹን ፡ በመዓት ፡ እጐበኛቸ
ዋለሁ፤

እስመ፡አመጽእ፡ላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ወሰብአ፡ይሁዳ፤
በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ሰዎችና፡
በይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ መከራን ፡ አመጣ
ለሁና፤

ኵሎ፡እኩየ፡ዘነበብኩ፡ላዕሌሆሙ፤
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የተናገርሁትን ፡
ክፉውን፡ነገር፡ሁሉ፡አመጣለሁና፤

ወኢሰምዑ፤
ያልሰሙትን፤

፴፪፤ ወተመጠወ ፡ ኤርምያስ ፡ ካልዐ ፡
ክርታስ፤
ኤርምያስ፡ሌላ፡ወረቀት፡ተቀብሎ፤
ወወሀቦ፡ለባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፤
ለኔርዩ፡ልጁ፡ለባሮክ፡ሰጠው፤

ወጸሐፈ፡ቦቱ፡ባሮክ፡እምአፈ፡ኤርምያስ፡
ኵሎ፡ቃለ፡መጽሐፍ፤
ባሮክ ፡ ከኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እየሰማ ፡
የመጽሐፉን፡ቃል፡ሁሉ፡ጻፈበት፤

ዘአውዓየ ፡ ኢዮአቄም ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡
በእሳት፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡
በእሳት ፡ ያቃጠለውን ፡ የመጽሐፉን ፡
ቃል፡ጻፈበት፤

ወዓዲ፡ተወሰከ፡ቦቱ፡ነገር፡ብዙኅ፤
ዳግመኛ፡ብዙ፡ነገር፡ተጨመረበት።

## ምዕራፍ፡፴፯፤

፩፤ወነግሠ፡ሴዴቅያስ፡ወልደ፡ኢዮስያስ፤
የኢዮስያስ፡ልጅ፡ሴዴቅያስ፡ነገሠ፤

ህየንተ፡ኢኮንያን፡ወልደ፡ኢዮአቄም፤
ስለ፡ኢዮአቄም፡ልጅ፡ስለ፡ኢኮንያን፡
ፈንታ፡ነገሠ፤

ዘአንገሦ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ባቢሎን ፡
በምድረ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ያነገሠው ፡የባቢሎን ፡
ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፡ነው፤

፪፤ወለሊሁኒ፡ኢሰምዓ፤
እርሱ፡ቅሉ፡አልሰማም፤

ውእቱ፡ወደቂቁሂ፤
እርሱ፤ልጆቹ፤

ወሕዝበ ፡ ምድር ፡ ዘነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡
በእደ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፤
የእዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ በነቢዩ ፡
በኤርምያስ፡ቃል፡እግዚአብሔር፡የተ
ናገረውን፡ነገር፡አልሰሙም፤

፫፤ ወፈነዎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ለአካ
ዝያስ፡ወልደ፡ሰላምዩ፤
ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ የሰላምዩ ፡ ልጅ ፡
አካዝያስን፤

ወሶፎንያ ፡ ወልደ ፡ ማሴው ፡ ካህን ፡ ኀበ፡
ኤርምያስ፤
አገልጋይ ፡ የሚሆን ፡ የማሴው ፡ ልጅ ፡
ሶፎንያን፡ [illegible]



እንዘ፡ይብል፤
እንዲህ፡ሲል፤

ጸሊ ፡ በእንቲአነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፤
ስለ፡እኛ፡ወደ፡ፈጣሪያችን፡ወደእግዚ
አብሔር፡ለምንልን፡ሲል፤

፬፤ ወኤርምያስ ፡ ይበውዕ ፡ ወይወጽእ ፡
ማዕከለ፡ሕዝብ፤
ኤርምያስ፡በሕዝቡ፡መካከል፡ይወጣ፡
ይገባ ፡ ነበር ፤ መውጣት ፡ መግባቱ ፡
ባይታሠር፡ነው፡ለማለት፤

ወኢያብእዎ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፤
ወደ፡ግዞት፡ቤት፡አላገቡትም፡ነበር፤

ወኃይለ፡ፈርዖን፡ወጽአ፡እምግብፅ፤
የፈርዖን፡ሠራዊት፡ከግብፅ፡ወጣ፤

ወሰምዑ ፡ ከለዳውያን ፡ እለ ፡ ዐርጉ ፡ይትቃ
ተልዋ፡ለኢየሩሳሌም፡ስሙዓቶሙ፤
ግብፃውያን ፡ ለእስራኤል ፡ ረዳት ፡
ሆነው፡ሊወጓቸው፡መዝመታቸውን፡
ኢየሩሳሌምን ፡ ይወጓት ፡ ዘንድ ፡
የዘመቱ፡ከለዳውያን፡ሰሙ፤

ወዐርጉ፡እምኢየሩሳሌም፤
ከኢየሩሳሌም፡ዘመቱ፤

፭፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ፡
ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ወደ፡ነቢዩ፡ወደ፡ኤርምያስ፡የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ተነገረ፤

እንዘ፡ይብል፤
እንዲህ፡ሲል፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡
እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፡ሲል፡ተነገረ፤

፮፤ከመዝ፡ትብልዎ፡ለንጉሠ፡ይሁዳ፤
የይሁዳውን፡ንጉሥ፡እንዲህ፡በሉት፤

ዘፈነወክሙ፡ኀቤየ፡ይኅሥሡኒ፤
በጸሎት፡ይፈልገኝ፡ዘንድ፡ወደ፡እኔ፡
የላካችሁ ፡ የይሁዳው ፡ ንጉሥን ፡
እንዲህ፡በሉት፤

ናሁ ፡ ኃይለ ፡ ፈርዖን ፡ ዘውጽአ ፡ ለረዲኦ
ትክሙ፤
እነሆ ፡ እናንተን ፡ ለመርዳት ፡ የመጣ ፡
የፈርዖን፡ሠራዊት፤

ተመይጠ፡ለምድሩ፡ግብፅ፤
ወደሀገሩ፡ወደ፡ግብፅ፡ተመለሰ፤

፯፤ ወይትመየጡ ፡ ከለዳውያን ፡ ወይትቃ
ተልዋ፡ለዛቲ፡ሀገር፤
ከለዳውያን ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡
ሀገር፡ይወጓታል፤

ወይነሥእዋ፤
እጅ፡ያደርጓታል፤

ወያውዕይዋ፡በእሳት፤
በእሳት ፡ ያቃጥሏታል ፡ በሉት ፡ ሲል ፡
መጣ፡ተነገረ፤

፰፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ኢትየውህዋ፡ለነፍስክሙ፤
ሰውነታችሁን ፡ ልቡናችሁን ፡ አታታ
ሏት፡አትሸልጓት፤

እንዘ፡ትብሉ፤
እንዲህ፡እያላችሁ፤

ሐሊፈ፡የሐልፉ፡እምኔነ፡ከለዳውያን፤
ከለዳውያን ፡ ከእኛ ፡ አልፈው ፡
ይሔዳሉ ፡ እያላችሁ ፡ ልቡናችሁን ፡
አታታሏት፤

፱፤ እስመ ፡ ኢየሐውሩ ፡ ከለዳውያን ፡
ዘእንበለ፡ይቅትሉ፡ኵሎ፡ኃይለ፡ከለዳውያን፤

www.ethiopianorthodox.org

ከለዳውያንና ፡ ኃይለ ፡ ከለዳውያን፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ የከለዳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉን ፡ ሳያጠፉ ፡ አይሄ ዱምና ፤ አንድም ፡ ኵሉ ፡ ኃይለ ፡ ከለዳ ውያን ፤ የከለዳውያንን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ፡ሳያጠፉ፡አይመለሱምና፤

እለ፡ይትቃተሉ፡ኪያክሙ፤
እናንተን፡የሚዋጉ፡ከለዳውያን፡አይ ሄዱምና፤

ወይተርፉ፡በሙ፡ዕደው፡ርጉዛን፡ለለ፩ዱ፡ በመካኑ፤
በየቦታው፤አንድም፡አንዱ፡በጦር፡ የተወጉ ፡ ሰዎችን ፡ በማስታመም ፡ መከራ፡ሊሆንባቸው፡ወጥተው፡ይቀ ሩባቸዋል፤

ይትነሥኡ፡ወያውዕዩ፡ዛተ፡ሀገረ፡በእሳት፤
በጠላትነት ፡ ተነሥተው ፡ ይችን ፡ ሀገር፡በእሳት፡ያቃጥላሉ፤

፲፡ ወኮነ፡ሶበ፡ዓርገ፡ኃይለ፡ከለዳውያን፡ እምኢየሩሳሌም፤
የከለዳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ከኢየሩ ሳሌም፡ በዘመቱ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ፡ ሆነ፤

እምገጸ፡ኃይለ፡ፈርዖን፤
ከፈርዖን ፡ ሠራዊት ፡ ገጸ ፡ መዓት፡ የተነሣ፡እንዲህ፡ሆነ፤

፲፩፤ወጽአ፡ኤርምያስ፡እምኢየሩሳሌም፤
ኤርምያስ፡ከኢየሩሳሌም፡ወጣ፤

ለሐዊረ፡ምድረ፡ብንያም፤
የነገራቸውን፡የማይሰሙት፡ቢሆኑ፡ የነሱ ፡ ዳፋ ፡ በቅቶኝ ፡ ለምን ፡ እማረ ካለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ፡ ብንያም ፡ ዕፃ ፡ ለመሔድ፡ወጣ፤

ይንበር፡ህየ፡ማዕከለ፡ሕዝብ፤
በሕዝቡ፡መካከል፡ይኖር፡ዘንድ፤

፲፪፤ወኮነ፡በውእቱ፡አንቀጽ፡ዘብንያም፤
በብንያም፡በር፡እንዲህ፡ሆነ፤

ወሀሎ፡ህየ፡ብእሲ፡ዘየዓቅብ፡አንቀጸ፤
በር፡የሚጠብቅ፡አንድ፡ሰው፡ከዚያ፡ ነበር፤

ወስሙ፡ስርዋስ፡ወልደ፡ሳሎምያ፤
ስርዋስም ፡ ስርዋህም ፡ ይለዋል ፤ ስሙም ፡ የሳሎምያ ፡ ልጅ ፡ ስርዋስ፡ ይባል፡ነበር፤

ወልደ፡ሐናንዩ፤
ሳሎምያን፡የሐናንዩ፡ልጅ፡አለው፤

ወአኃዞ፡ለኤርምያስ፡ነቢይ፤
ይህ ፡ ቀጣፊ ፡ ነቢይ ፡ እንጂ ፡ ቢመክ ራቸው ፡ ቢያስተምራቸው፡ የማይ ሰሙት ፡ ቢሆን ፡ ከለዳውያንን ፡ አምጥቶ፡ሊያስማርካቸው፡ይሔዳል? ብሎ፡ነቢዩ፡ኤርምያስን፡ያዘው፤

ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤

ኀበ፡ከለዳውያን፡አንተ፡ታመሥጥ፤
አንተ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ሒደህ፡ ልታመልጥ፡ነው?አለው፤

፲፫፤ወይቤ፡ኤርምያስ፤
ኤርምያስ፡እንዲህ፡አለ፤

ሐሰ፡ኢያመስጥ፡ውስተ፡ከለዳውያን፡አነ፤
እኔ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ሒጄ ፡ አላመ ልጥም፡ወደ፡ከለዳውያን፡አምልጬ፡ አልሔድም፤

ወኢሰምዖ፤
አልሰማውም፤

ወአኃዞ፡ስርዋህ፡ለኤርምያስ፤
ስርዋህ ፡ ሶርህያ ፡ ይለዋል ፡ ኤርም ያስን፡ይዞ፤



ወወሰዶ፡ኀበ፡መላእክት፤
ወደ፡አለቆች፡ወሰደው፤

፲፬፤ ወተምዑ ፡ መላእክት ፡ ላዕለ ፡ ኤርምያስ፤
አለቆችም፡በኤርምያስ፡ላይ፡ተቆጡ፤

ወዘበጥዎ፤
ደብድበው፤

ወፈነውዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ቤተ ፡ ዮናታን፡ጸሐፊ፤
በጸሐፊው፡በዮናታን፡ቤት፡አጠገብ፡ ወደ፡አለ፡ግዞት፡ቤት፡ሰደዱት፤

እስመ፡ኪያሁ፡ገብሩ፡ዓቃቤ፡ለቤተ፡ሞቅሕ፤
እርሱን፡የግዞት፡ቤት፡ሹም፡አድርገ ውታልና፤

፲፭፤ወመጽአ፡ወነበረ፡ኤርምያስ፡ውስተ፡ ቤተ፡አዘቅት፤
ኤርምያስ ፡ መጥቶ ፡ በአዘቅቱ ፡ አጠገብ፡ባለ፡እሥር፡ቤት፡ተቀመጠ፤

እስመ፡ባቲ፡ግብ፡ክሪት፡በቤቱ፤
በቤቱ፡አጠገብ፡የተቆፈረ፡ጕድጓድ፡ ነበረና፤አንድም፡ወክሪት፡ክርክራት፡ ነበረና፤

ወነበረ፡ኤርምያስ፡ህየ፡ብዙኀ፡መዋዕለ፤
ኤርምያስ ፡ ከዚያ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጠ፤

፲፮፤ወፈነወ፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፤
ንጉሡ፡ሴዴቅያስ፡ወደ፡ኤርምያስ፡ መልእክተኛ፡ላከ፤

ወነሥኦ፤
ኤርምያስን፡አስመጥቶ፤

ወተስእሎ፡ንጉሥ፡በቤቱ፡በኅቡዕ፤
ንጉሡ፡በቤቱ፡በቆይታ፡በምሥጢር፡ ጠየቀው፤

ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤

ቦኑ፡ቃል፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፤
በውኑ፡ከእግዚአብሔር፡የሰማኸው፡ ቃል፡አለን፡አለው፤

ወይቤሎ፡ኤርምያስ፤
ኤርምያስ፡እንዲህ፡አለው፤

እወ፡ቦ፤
አዎን፡አለ፡አለው፤

ወይቤሎ ፡ በእደ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ትትወሀብ፤
ይህቺ፡ሀገር፡በባቢሎን፡ንጉሥ፡እጅ፡ ትያዛለች፡አለው፤

፲፯፤ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለንጉሥ ፡ ሴዴቅያ፤
ኤርምያስ ፡ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያን ፡ እን ዲህ፡አለው፤

ምንት፡ኃጢአትየ፡ለከ፤
አንተን ፡ የበደልሁበት ፡ ኃጢአቴ፡ ምንድ፡ነው?

ወለአግብርቲከ፤
ባሮችህንስ፤

ወለዝንቱ፡ሕዝብ፤
እነዚህን ፡ ወገኖች ፡ የበደልሁበት፡ ኃጢአቴ፡ምንድነው?አለው፤

እስመ፡ወሀብክሙኒ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፤
ለእሥር ፡ ቤት ፡ ሰጥታችሁኛልና ፤ ለአሣሪ ፡ ቤት ፡ ሰጥታችሁኛልና ፤ አንድም ፡ ዘወሀብክሙኒ ፡ ለእሥር፡ ቤት፡የሰጣችሁኝ፡በምን፡እዳዬ፡ነው?

፲፰፤ወአይቴ፡ሀለዉ፡ነቢያቲክሙ፤
ነቢያቶቻችሁ፡ወዴት፡አሉ?

www.ethiopianorthodox.org

እለ፡ይትኔበዩ፡ለክሙ፤
ትንቢት ፡ የሚናገሩላችሁ ፡ ነቢያት ፡
ወዴት፡አሉ?
እንዘ፡ይብሉ፤
እንዲህ፡ብለው፤
ኢይበውእ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ላዕሌክሙ፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ እናንተ፡
አይገባም፤
ወላዕለ፡ዛ፡ምድር፤
ወደዚችም፡ሀገር፡አይገባም፡ብለው፡
ትንቢት ፡ የተናገሩላችሁ፡ ነቢያት ፡
ወዴት፡ናቸው?

፲፱፤ወይእዜኒ፡እግዚኦ፤
አሁንም፡አቤቱ፤
ንጉሥ፡ይደቅ፡ሣህልየ፡ቅድመ፡ገጽከ፤
ንጉሥ፡ልመናዬ፡በፊትህ፡ይድረስ፤
ወኢታብአኒ ፡ ቤተ ፡ ዮናታን ፡ ጸሐፊ ፡
ኢይሙት፡በህየ፤
በዚያ፡እንዳልሞት፡ወደ፡ጸሐፊው፡
ወደ ፡ ዮናታን ፡ ቤት ፡ አታግባኝ ፡
አለው፤

፳፩፤ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፤
ንጉሡ፡ሴዴቅያስ፡አዘዘ፤
ወአዕቀቦ፡ለኤርምያስ፡በዐፀደ፡ሞቅሕ፤
ኤርምያስን ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አስጠ
በቀው፤
ወወሀብዎ፡ኅብስተ፡ለለዕለት፡እምአፍአ፡
ኅባውዘ፡እለ፡የኀብዙ፤
እንጀራን ፡ የሚጋግሩ ፡ ሰዎች ፡
በየዕለቱ፡ በአፍአ ፡ በከተማው ፡
ይሰጡት፡ነበር፤
እስከ፡ኀልቀ፡ኅብስት፡እምሀገር፤
በከተማው ፡ ያለ ፡ እንጀራ ፡ እስከ ፡
አለቀ፡ ድረስ፤ አንድም ፡ ወወሀብዎ ፡
ከከተማ ፡ በአፍአ ፡ እያመጡ ፡ ዕለት ፡
ዕለት ፡ እንጀራን ፡ ሰጡት ፤ እስመ፡
ኀልቀ፡ በከተማ ፡ ያለ ፡ እንጀራ፡
አልቋልና፤
ወነበረ፡ኤርምያስ፡በዐፀደ፡ሞቅሕ
ኤርምያስ፡በግዞት፡ተቀመጠ።

## ምዕራፍ፡፴፰፡

፩፤ወሰምዐ፡ሶፎንያስ፡ወልደ፡ናታን፤
የናታን፡ልጅ፡ሶፎንያስ፡ሰማ፤
ወጎዶልያ፡ወልደ፡ጳስኮር፤
የጳስኮር፡ልጅ፡ጎዶልያ፡ሰማ፤
ወዮአክል፡ወልደ፡ሴልምዩ፤
የሴልምዩ፡ልጅ፡ዮአክልም፡ሰማ፤
ወጳስኮር፡ወልደ፡ሜልያ፤
የሜልያ፡ልጅ፡ጳስኮር፡ሰማ፤
ነገረ፡ዘነገረ፡ኤርምያስ፡ለኵሉ፡ሕዝብ፤
ኤርምያስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የተና
ረውን፡ነገር፡ሰማ፤
ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

፪፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ዘኀደረ ፡ ውስተ ፡ ዛ ፡ ሀገር ፡ ይመውት
በኩናት፤
በዚች ፡ ሀገር ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ በጦር
ይሞታል፤
ወበረሀብ፡ወበብድብድ፤
በቀጠና፡በቸነፈር፡ይሞታል፤
ወዘወጽአ፡ኀበ፡ከለዳውያን፡የሐዩ፤
ወደ፡ከለዳውያን፡ወጥቶ፡የሔደ፡ሰው
ግን፡ይድናል፤
ወትከውን፡ነፍሱ፡ምርካበ፤
ሰውነቱ ፡ የተድላ ፡ የደስታ ፡ መገኛ
ትሆናለች፤



ወየሐዩ፤
ይድናል፤

፫፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤
ተውህቦ ፡ ትትወሀብ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ውስተ ፡
እደ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ይህቺ፡ሀገር፡በባቢሎን፡ንጉሥ፡እጅ፡
ትጠፋለች፡ብሏልና፤
ወይነሥአ፤
እጅም፡ያደርጋታል፡ብሏልና፤

፬፤ወይቤልዎ፡መላእክት፡ለንጉሥ፤
አለቆች፡ንጉሥን፡እንዲህ፡አሉት፤
ይሙት፡ዝንቱ፡ብእሲ፤
ይህ፡ሰው፡ይሙት፤
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ያደክም ፡ እደወ ፡ ሰብአ፡
ጸባእያን፤
እርሱ፡አርበኞች፡ሰዎችን፡እጃቸውን፡
ከመወርወር፡ ቃላቸውን ፡ ከመምከር ፡
ያደክማልና፤
እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ዛቲ፡ሀገር፤
በዚህች ፡ ሀገር ፡ የቀሩ ፡ የአርበኞችን ፡
እጃቸውን ፡ ከመወርወር ፡ ቃላቸውን
ከመምከር፡ያደክመዋልና፤
ወእደወ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ዘነገሮሙ ፡ ውእቱ፡
ነገረ፤
ይህንን ፡ ነገር ፡ የነገራቸውን ፡
የሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ እጃቸውን ፡ ከመወ
ርወር ፡ ቃላቸውን ፡ ከመምከር ፡ ያደክ
ማልና፤
እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ኢየኃሥሥ ፡ ሰላመ ፡
ለዝንቱ፡ሕዝብ፡ዘእንበለ፡እኩይ፤
ይህ፡ሰው፡ከመከራ፡በቀር፡ለእነዚህ፡
ወገኖች ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ የማይ
ፈልግ፡ስለሆነ፤

፭፤ወይቤ፡ንጉሥ፡ሴዴቅያስ፤
ንጉሡ፡ሴዴቅያስ፡እንዲህ፡አለ፤
ናሁ፡ውእቱ፡በእዴክሙ፤
እነሆ፡በእጃችሁ፡ተይዟል፤
እስመ፡ኢይክል፡ንጉሥ፡ተናግሮቶሙ፤
ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ መናገር ፡ አይቻ
ለውም ፡ ነበርና ፡ አለ፤ ሥልጥነውበት ፡
ነበርና ፤ አንድም፡ ተናግሮተክሙ ፡
ንጉሥ፡እናንተን፡አይናገራችሁምና፤

፮፤ወነሥእዎ፡ለኤርምያስ፤
ኤርምያስን፡ወሰደው፤
ወገደፍዎ፡ውስተ፡አዘቅተ፡ሜልክዩ፡ወልደ፡
ንጉሥ፤
የንጉሥ፡ባለሟል፡የሚሆን፡ሜልክዩ፡
በሚጠብቀው፡ጕድጓድ፡ጣሉት፤
ዘበዐፀደ፡ሞቅሕ፤
በግዞት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ባለ ፡
ጕድጓድ፡ጣሉት፤
ወአውረድዎ ፡ ለኤርምያስ ፡ በአሕባል ፡
ውስተ፡አዘቅት፤
ኤርምያስን፡በገመድ፡አሥረው፡ወደ፡
ጕድጓድ፡አወረዱት፤
አዘቅቱሂ፡ዘአልቦ፡ማይ፡ዘእንበለ፡ጻዕሙ፡
ዕቡር፤
ጕድጓዱም፡ጭቃ፡ነው፡እንጂ፤ውሀ፡
አልነበረበትም ፤ ስለ ፡ እርጥብነቱ ፡
ዕቡር ፡ ብሎታል ፡ እንጂ ፡ አዘቅተ ፡
ኵስሕ፡ነው፤
ወጠግዓ፡ኤርምያስ፡በዕቡር፤
ኤርምያስ፡ከጭቃው፡ጋራ፡ተጣጋ፤

፯፤ ወሰምዐ ፡ አቤሜሌክ ፡ ገብረ ፡ ንጉሥ ፡
ኢትዮጵያዊ፤
ከወደ ፡ ሀገራችን ፡ የሔደ ፡ የንጉሥ ፡
አገልጋይ፡የሚሆን፡አቤሜሌክ፡ሰማ፤

www.ethiopianorthodox.org

ብእሲ፡ሕፅው፡
የንጉሥ፡ባለሟል፡የሚሆን፤

ወውእቱ፡ውስተ፡ቤቱ፡ለንጉሥ፡
እርሱ፡በንጉሥ፡ቤት፡ሁኖ፡ሰማ፤

ከመ፡ወሀብዎ፡ለኤርምያስ፡ውስተ፡አዘቅት፡
ኤርምያስን፡ከጕድጓድ፡እንደጣሉት፡ሰማ፤

ወንጉሥሰ፡ይነብር፡በዴዴ፡ብንያም፡
ንጉሥ ፡ ግን ፡ በብንያም ፡ በር ፡ ተቀምጦ፡ነበር፤

፰፤ ወወጽአ ፡ አቤሜሌክ ፡ እምቤተ ፡ ንጉሥ፤
አቤሜሌክ፡ከንጉሡ፡ቤት፡ወጥቶ፤

ወነገረ፡ኀበ፡ንጉሥ፤
ለንጉሡ፡ተናገረ፤

ወይቤ፤
እንዲህ፡አለ፤

፱፤እግዚእየ፡ንጉሥ፤
ጌታዬ፡ንጉሥ፡አለ፤

አሕሠሙ፡እሉ፡ዕደው፡ኵሎ፡ዘገብሩ፡በኤርምያስ፡ነቢይ፤
በነቢዩ፡በኤርምያስ፡ሁሉን፡ያደረጉ፡እነዚህ፡ሰዎች፡ክፉ፡ሥራ፡ሠሩ፤

እለ፡ገደፍዎ፡ውስተ፡አዘቅት፡ይሙት፡በሀየ፡እምገጸ፡ረሀብ፤
ከቀጠና ፡ የተነሣ ፡ በዚያ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ፡በጕድጓድ፡የጣሉት፤

እስመ፡አልቦ፡ኅብስት፡ዓዲ፡በሀገር፤
በከተማ፡ገና፡ኅብስት፡አልነበረምና፡ ይሙት፡ብለው፡በጕድጓድ፡የጣሉት፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ፤ አንድም፡ በከተማ ፡ ገና ፡ ኅብስት ፡ የለምና፡ ብለው ፡ ከቀጠና ፡ የተነሣ ፡ በቀጠና፡ይሞት፡ዘንድ፡ክፉ፡ሥራ፡ሠ[illegible]

፲፤ ወአዘዞ ፡ ንጉሥ ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ኢት[ዮ]ጵያዊ፡
ንጉሡ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አቤሜሌክን ፡ አዘዘው፤

ወይቤሎ፤
እንዲህ፡አለው፤

ንሣእ፡በእዴከ፡እምዝየ፡ሠላሳ፡ሰብአ፤
ከዚህ፡ሠላሳ፡ሰው፡ወስደህ፤

ወአውፅኦ፡ለኤርምያስ፡ነቢይ፡እምአዘቅ[ት]፡ ዘእንበለ፡ይሙት፤
ሳይሞት ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስን ፡ ከጕድጓድ፡አውጣው፡አለው፤

፲፩፤ ወነሥአ ፡ አቤሜሌክ ፡ ሰብአ፡ በእዴሁ፤
አቤሜሌክ፡ሰውን፡በቃሉ፡ይዞ፤

ወቦአ ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ቤተ፡ መዛግብት፤
በንጉሥ፡ቤት፡አጠገብ፡ወዳሉ፡ዕቃ፡ ቤቶች፡ገባ፤

ወነሥአ፡እምህየ፡አዕርቅተ፡ብሉያተ፡
በዘየሐሥዩ ፡ ቦቱ ፡ አፍራስ ፡ ይላ[ሉ]፡ ፈረስ ፤ የሚወለውሉበትን ፡ አሮጌ፡ ጨርቅ፡አመጣ፤

ወአሕባለ፡ብሉያተ፤
አዲሱ፡ገመድ፡እጁን፡እንዳይበላው፡ የለሰለሰ፡አሮጌ፡ገመድ፡አመጣ፤

ወወገረ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ ውስተ ፡ አዘቅት፡ በአሕባል፤
በገመድ ፡ ቋጥሮ ፡ ኤርምያስ ፡ ወደ፡ አለበት፡ጕድጓድ፡ጣለው፤

፲፪፤ ወይቤሎ ፡ ለኤርምያስ ፡ አቤሜሌክ ፡ [illegible]



አቤሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው፤

ደይ ፡ እሎንተ ፡ አዕርቅተ ፡ ታሕተ ፡ እዴከ ፡ ወታሕተ፡አሕባል፤
ከገመዱ ፡ በታች ፡ በእጅህ ፡ ውስጥ ፡ ጨርቁን፡ጠምጥምበት፡አለው፤

ወገብረ፡ኤርምያስ፡ከመዝ፤
ኤርምያስ፡እንደዚሁ፡አደረገ፤

፲፫፤ ወሰሐብዎ፡በአሕባል፡ወአውጽእዎ፡ እምአዘቅት፤
በገመድ ፡ ስበው ፡ ከጕድጓድ ፡ አወጡት፤

ወነበረ፡ኤርምያስ፡ኀበ፡ዐፀደ፡ሞቅሕ፤
ኤርምያስ፡በግዞት፡ቤት፡ተቀመጠ፤

፲፬፤ወፈነወ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሥ፤
ንጉሡ፡ሴዴቅያስ፡ልኮ፤

ወነሥአ ፡ ለኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ ኀበ ፡ ሙባእ ሣልስ፡ዘቤተ፡እግዚአብሔር፤
በቤተ፡እግዚአብሔር፡አጠገብ፡ካለ፡ ከሦስተኛው፡ቆመ፡ብእሲ፡መግቢያ፡ ነቢዩ፡ኤርምያስን፡ጠራው፤

ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ለኤርምያስ፤
ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ፡አለው፤

እሴአለከ፡አሐ፡ቃለ፤
እኔ፡ቃል፡እጠይቅሃለሁ፤

ወኢትኅባዕ፡እምኔየ፡ቃለከ፤
ቃልህን፡ከእኔ፡አትሠውር፡አለው፤

፲፭፤ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንጉሥ፤
ኤርምያስ፡ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ፡አለው፤

እመ፡አይዳዕኩከ፡ሞተ፡እመውት፤
ብነግርህ፡የሞት፡ሞት፡እሞታለሁ፡ አለው፤

ወእመ፡አምከርኩከ፡ኢትሰምዓኒ፤
ባማክርህም፡አትሰማኝም፡አለው፤

፲፮፤ ወመሐለ ፡ ሎቱ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ለኤርምያስ፤
ንጉሡ፡ሴዴቅያስ፤

በኅቡእ፤
በቈይታ ፤ አንድም ፡ በኅቡእ ፡ ለኤርምያስ፡ማለለት፤

ወይቤ፡ሕያው፡እግዚአብሔር፡ዘገብረ፡ለነ፡ ዛተ፡ነፍሰ፤
ይችን ፡ ነፍስ ፡ የፈጠረልን ፡ እግዚአብሔር፡ሕያው፡ነው፡አለ፤

ከመ፡ኢይቀትለከ፤
እንዳልገድልህ፤

ወኢይሁበከ፡ውስተ፡እደ፡እሉ፡ሰብእ፡እለ፡ የኀሥሥዋ፡ለነፍስከ፤
ሰውነትህን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈልጓት ፡ ሰዎች ፡ እጅም ፡ አሳልፌ ፡ እንዳልሰጥህ፡ሕያው፡ነው፡አለ፤

፲፯፤ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለሴዴቅያስ ፡
ኤርምያስ ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት፤ አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአብሔ፡እንዲህ፡አለ፤

እመ ፡ ወጺአ ፡ ወጻእከ ፡ ኀበ ፡ መላእክተ ፡ ንጉሥ፡ዘባቢሎን፤
ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ መውጣትን፡ብትወጣ፤

ተሐዩ፡ሕይወተ፡ነፍስከ፣
ሰውነትህ፡ትድናለች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዝንቱ፡ሀገር፡ኢይውዒ፡በእሳት፤
ይህም፡ሀገር፡በእሳት፡አይቃጠልም፤

ወተሐዩ፡አንተ፤
አንተ፡ከሞት፡ትድናለህ፤

ወኵሉ፡ቤትከ፤
ወገኖችህ፡ሁሉ፡ይድናሉ፤

፲፰፤ወእመሰ፡ኢወጻእከ፡ኀበ፡መላእክተ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ ባትወጣ፡ግን፤

ትትወሀብ፡ዛቲ፡ሀገር፡በእደ፡ከለዳውያን፤
ይህች ፡ ሀገር ፡ በከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ትጠፋለች፤

ወትውዒ፡በእሳት፤
በእሳት፡ትቃጠላለች፤

ወአንተሂ፡ኢትድኅን፡እምእዴሆሙ፤
አንተም፡ከእጃቸው፡አትድንም፤

፲፱፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ለኤርምያስ፤
ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ፡አለው፤

አነ፡እፈርሆሙ፡ለአይሁድ፤
እኔ፡አይሁድን፡እፈራቸዋለሁ፤

ዘአምሠጡ፡ኀበ፡ከለዳውያን፤
ከኔ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ አምልጠው ፡ የሔዱ፡አይሁድን፡እፈራቸዋለሁ፤

ከመ፡ኢያግብኡኒ፡ውስተ፡እዴሆሙ፤
በእጃቸው፡እንዳይጥሉኝ፤

ወኢይሣለቁኒ፤
እንዳይዘብቱብኝ፤

፳፤ወኤርምያስ፡ይቤ፡ኢይሣለቁከ፤
ኤርምያስም፡አይዘብቱብህም፡አለ፤

ስማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአነ ፡ ዕብል፡ ኀቤከ፤
እኔ፡ለአንተ፡የምነግርህን፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ስማ፤

ዘይኄይስ፡ይከውን፡ኀቤከ፤
ለአንተ ፡ ከሱ ፡ የሚበልጥ ፡ በጎ ፡ ነገር፡ ይደረግልሃል፤

ወነፍስከ፡ለሕይወት፤
ሰውነትህ፡ለሕይወት፡ትሆናለች፤

፳፩፤ወለእመ፡ኢትፈቅድ፡አንተ፡ወጺአ፤
አንተ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ፡ አለቆች፡መውጣትን፡ባትወድ፡ግን፤

ዝንቱ፡ቃል፡ዘአርአየኒ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ የገለጠልኝ ፡ ቃል፡ ይህ፡ነው፤

፳፪፤ወናሁ፡ኵሎን፡አንስት፡እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ቤተ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
እነሆ ፡ በይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ቤት፡ ከሞት፡የቀሩ፡ሴቶች፡ሁሉ፤

ይወጽአ፡ኀበ፡መላእክተ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች፡ ይወጣሉ፤

እማንቱ፡ይቤላከ፤
እነሱ፡እንዲህ፡ይሉሃል፤

አስሐቱከ፤
እነሱ፡አሳቱህ፤

ወክህሉከ፡ዕደው፡ሰላምከ፤
ወዳጆችህ፡አስገኙህ፡ይሉሃል፤

ወያገብኡከ፡ውስተ፡ማእሠረ፡እገሪከ፤
ወደ፡ማሣሠር፡ያገቡሃል፤

ገብኡ፡ድኅረ፡እምኔከ፤
ካንተ፡ተለይተው፡ወደኋላ፡ሸሹ፤

፳፫፤ወለኵሎሙ፡አግብርቲከ፡ወደቂቅከ፡ያወጽእዎሙ፡ኀበ፡ከለዳውያን፤



ወንዶች ፡ ልጆችህንና ፡ ባለሟሎችህ
ን፡ወደ፡ከለዳውያን፡ያስማርኳቸዋል፤

ወአንተ፡ኢትድኅን፡እምእዴሆሙ፤
አንተም፡ከእጃቸው፡አትድንም፤

እስመ፡ውስተ፡እደ፡ባቢሎን፡ትትአኀዝ፤
በባቢሎን፡ንጉሥ፡እጅ፡ትያዛለህና፤

ወዛቲ፡ሀገር፡ትውዒ፡በእሳት፤
ይችም፡ሀገር፡በእሳት፡ትቃጠላለችና፤

፳፬፤ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ለኤርምያስ፤
ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ፡አለው፤

ኢትንግር፡ለሰብእ፤
ለሰው፡አትናገር፡አለው፤

ወብእሲ፡ኢያእምር፡ዘንተ፡ቃለ፤
ሰውም፡ይህንን፡ነገር፡አይወቅ፤

ወአንተ፡ኢትመውት፤
አንተም፡አትሞትም፡አለው፤

፳፭፤ ወእመ ፡ ሰምዑ ፡ መላእክት ፡ ከመ፡ ተናገርኩ፡ምስሌከ፤
ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተነጋገርኩ ፡ አለቆች፡ቢሰሙ፤

[illegible]መጽኡ፡ኀቤከ፡ወይብሉከ፤
[illegible]ዳንተ፡መጥተው፡እንዲህ፡ይሉሃል፤

[illegible]ግረነ፡እስኩ፤
[illegible]ስኪ፡ንገረን፤

[illegible]ንተ፡ተናገርከ፡ለንጉሥ፤
[illegible]ጉሡን፡ምን፡ብለህ፡ተናገርከው፤

[illegible]ምንተ፡ተናገረከ፤
[illegible]ሱስ፡ምን፡ተናገረህ፡ይሉሃል፤

[illegible]ትኅባእ፡እምኔነ፤
[illegible]ኝ፡አትሠውር፤

[illegible]ኢንቀትለከ፤
[illegible]ንገልህም፡[illegible]

፳፮፤ ወበሎሙ ፡ እገድፍ ፡ አነ ፡ ምሕረትየ ፡ መንገለ፡አዕይንተ፡ንጉሥ፤
እኔ ፡ ልመናዬን ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አቀር ባለሁ፡በላቸው፤

ከመ፡ኢያግብአኒ፡ቤተ፡ዮናታን፤
ዮናታን ፡ ወደሚጠብቀው ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ እንዳይመልሰኝ ፡ እለምናለሁ ፡ በላቸው፤

ከመ፡ኢይሙት፡በህየ፤
በዚያ፡እንዳልሞት፤

፳፯፤ ወመጽኡ ፡ ኵሉ ፡ መላእክት ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፤
አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡ መጥተው፤

ወተሰአልዎ፤
ጠየቁት፤

ወይቤሎሙ ፡ በከመ ፡ ኵሉ ፡ ነገር ፡ ዘአዘዞ ፡ ንጉሥ፤
ንጉሡ፡እንደ፡አዘዘው፡ሁሉ፡እንዲህ፡ አላቸው፤

ወአርመሙ፡እምኔሁ፤
እርሱን፡ከመጣላት፡ዝም፡አሉ፤

እስመ፡ኢተሰምዐ፡ዝ፡ነገር፤
ይህ፡ነገር፡አልተሰማምና፤

፳፰፤ወተመይጠ፡ኤርምያስ፤
ኤርምያስ፡ተመልሶ፤

ወነበረ ፡ በዐፀደ ፡ሞቅሕ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ተእኅዘት፡ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌም፡እስከ፡ተያዘችበት፡ቀን፡ ድረስ፡በግዞት፡ቤት፡ተቀመጠ።

## ምዕራፍ፡፴፱፤

### ጉባኤ፤

፩፤ወኮነ፡ሶበ፡ተእኅዘት፡ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌም፡በተያዘች፡ጊዜ፡እንዲህ፡
[illegible]ነ፤ኮነ፡ያለውን፡ያምጣው፤

www.ethiopianorthodox.org

በታስዕ ፡ ዓመት ፡ መንግሥቱ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንጉሥ፡ዘይሁዳ፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ፡በዘጠነኛው፡ዘመን፤

በአሥር፡ወርኀ፤
በአሥረኛው፡ወር፡በጥር፤

መጽአ፡ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
ኮነ ፡ ያለውን ፡ መጽአ ፡ ብሎ ፡ አመጣው፤የባቢሎን፡ንጉሥ፡ናቡከደነፆር፡መጣ፤

ወኵሉ፡ኃይሉ፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፤
ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ፤

ወአገትዋ፡ለኢየሩሳሌም፡ወተቃተሉ፤
ኢየሩሳሌምን፡ከበው፡ተዋጉባት፤

፪፤እስከ፡፲ወ፩፡ዓመት፡ሴዴቅያስ፡እም፡ነግሠ፤
ሴዴቅያስ ፡ ከነገሠ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አንደኛው፡ዘመን፡ድረስ፤

በራብዕ፡ወርኀ፤
በአራተኛው፡ወር፡በሐምሌ፤

በተሱዓ፡ሠርቅ፤
ሐምሌ፡በባተ፡በዘጠኝ፡ቀን፤

ተናፈቀት፡ሀገር፤
እኩሉ ፡ እንዋጋ ፡ እኩሉ ፡ እንሽሽ ፡ እኩሉ ፡ እንገብር ፡ እኩሉ ፡ አንገብር ፡ በማለት፡ ሀገሪቱ ፡ እርስ ፡ በእርሷ ፡ ተለያየች፤

፫፤ወገብዑ፡ኵሎሙ፡መሳፍንተ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ሹማምንቱ፡ሁሉ፡ገቡ ፤ እንዲያው ፡ የገቡ ፡ አይደለም ፤ መልአኩ፡ቅዱስ፡ሚካኤል፡ባኡ፡ከለውዳውያን ፡ ወዬውውዎሙ ፡ ለዕብራውያን፡ብሎ፡በሩን፡ከፍቶ፡አስገብቷቸዋል፤

ወነበሩ፡ውስተ፡አንቀጸ፡ማሴው፤
ማሴው ፡ በሚጠብቀው ፡ በር ፡ ተቀመጡ፤

መንገናስር፤
መንገናስር፤

ሰማጎት፤
ሰማጎት፤

ናቡስኮር፤
ናቡስኮር፤

ናቡሴሪስ፤
ናቡሴሪስ፤

ናግርጎስናሴር፤
ናግርጎስናሴር፤

ረብማግ፤
ረብማግ

ኔሬጋል
ኔሬጋል፤

ሠሪአጼር፤
ሠሪአጼር ፡ እነዚህ ፡ ተቀመጡ ፤ አንድም ፡ ማሴው ፡ ማዕከል ፡ ማለት፡ ነው፤በመካከለኛው፡በር፡ተቀመጡ፤ አንድም፡በአንቀጽ፡በበር፡ተቀመጡ፤ አንድም ፡ ማሴው ፡ ማሴው፡ መንገናሥር ፡ሰማጎት ፡ እነዚህ ፡ በበር ፡ ተቀመጡ፤

ወኵሉ ፡ እለ ፡ተርፉ ፡ መሳፍንት ፡ ዘንጉሠ፡ ባቢሎን፤
የቀሩ ፡ በባቢሎን ፡ የነገሠ ፡ የናቡከደነፆር፡ሹማምንት፡ሁሉ፡ተቀመጡ፤

፬፤ወኮነ፡ሶበ፡ርእየሙ፡ሴዴቅያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤



የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ተቀምጠው፡ባያቸው፡ጊዜ፡እንዲህ፡ሆነ፤

ወኵሉ፡መስተቃትላን፤
አርበኞች፡ሁሉ፡በአይዋቸው፡ጊዜ፡እንዲህ፡ሆነ፤

ጐዩ፡በሌሊት፡እምነ፡ሀገር፤
ኮነ፡ያለውን፡ጐዩ፡ብሎ፡አመጣው፤ ከከተማ፡ወጥተው፡በሌሊት፡ሸሹ፤

ፍኖተ ፡ ገነተ ፡ ንጉሥ ፡ በአንቀጽ ፡ ማዕከለ ፡ ዓረፍት፤
ከተማውን ፡ ወጥተው ፡ ንጉሡ ፡ ባለበት፡ ጐዳና ፡ ሔዱ ፤ እንደ ፡ አፄ ፡ ቤትና ፡ እንደ ፡ ዓደባባይ ፡ ኢየሱስ ፡ ተክል ፡ይጐበኙበት ፡ እንደነበረ ፡ ዳዊትና፡ሰሎሞን፡ያበጁት፡የተክል፡መጐብኛ ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ወጥተው ፡ ሔዱ፤

በአንቀጽ፡ማዕከለ፡ዓረፍት፤
በቅጽር፡መካከል፡ባለው፡በር፡ሸሹ፤

ወወጽአ፡ፍኖተ፡ዓረብ፤
በምዕራብ፡ባለው፡ጐዳና፡ወጣ፤

፭፤ወዴገንዎ፡ኃይለ፡ፋርስ፡እምድኅሬሁ፤
ከእነሱ ፡ በኋላ ፡ የፋርስ ፡ ሠራዊት ፡ ተከተሉት፤

ወአኃዝዎ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ በአራቦት ፡ ዘኢያሪኮ፤
ዘደቂቀ፡አሞን፡አለና፡ዘኢያሪኮ፡አለ፡ ኤርምያስን ፡ የኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ በምትሆን፡በአራቦት፡ያዙት፤

ወነሥእዎ ፡ ወአዕረግዎ ፡ ኀበ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ይዘው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነፆር፡አወጡት፤

ዴብላታ፡በምድረ፡ኤማት፤
በኤማት፡አጠገብ፡ባለ፡ናቡከደነፆር፡ወደሠፈረበት ፡ ወደ ፡ ዴብላታ ፡ አወጡት፤

ወተናገሮ፡ቅሥተ፤
ወቀሠው፤እችላለሁ፡አትል፡አትዋጋ፤ አልችልም፡አትል፡አትገብር፡ብሎ፡ ምነው፡ይኸማ፡ባልችል፡አይለውም፡ ቢሉ ፡ ፍትሐ ፡ ይላል ፡ ከእንጨት ፡ መርጦ ፡ ለታቦት ፤ ከሰው ፡ መርጦ ፡ ለሹመት ፡ እንዲሉ ፡ መርጬ ፡ ባነግሥህ ፡ የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊት ፡ ቁር፡ ያስመታኸኝ ፡ለምን ፡ ነው ፡ ተፋረደኝ፡አለው፤

፮፤ ወረገዞሙ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ለደቂቀ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በዴብላታ ፡ በቅድመ ፡ አዕይንቲሁ፤
ለመንግሥት ፡ የደረሱ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በዴብላታ፡ እያየ ፡ ወጋቸው ፤ ኃዘን ፡ ይዕናበት፡ብሎ፤

ወለኵሎሙ ፡ መሳፍንተ ፡ ይሁዳ ፡ ረገዞሙ ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የይሁዳን ፡ መሳፍንት ፡ ሁሉ ፡ የባቢሎን፡ንጉሥ፡ወጋቸው፤

፯፤ወተዘርዉ፡ኵሉ፡ሠራዊቱ፤
ሠራዊቱ፡ሁሉ፡ተበተኑ፤

ወእምዝ፡ዐየሮ፡አዕይንቲሁ፡ለሴዴቅያስ፤
ከዚህ፡በኋላ፡የሴዴቅያስን፡ዓይኑን፡ አጠፋው፤ክፉ፡በአየበት፡መልካም፡ አይይበት፡ብሎ፤

ወአሠሮ፡በመዋቅሕተ፡ሐፂን፤

www.ethiopianorthodox.org

በእግር ፡ ብረት ፡ አሠረው ፤ አንድም ፡ በድንብኩል፡አሥሮ፤

ወወሰዶ፡ባቢሎን፡
ወደ፡ባቢሎን፡ወሰደው፤

፰፡ ወቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ወአብያተ ፡ ሕዝብ ፡ አውዐዩ፡በእሳት፡ከለዳውያን፡
የንጉሡን፡ቤትና፡የሕዝቡን፡ቤቶች፡ ከለዳውያን፡በእሳት፡አቃጠሉት፤

ወአረፋቲሃ፡ለኢየሩሳሌም፡ነሠቱ፡
የኢየሩሳሌምንም፡ቅጽሯን፡አፈረሱ፤

፱፡ ወተረፈ፡ሕዝብ፡እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ ሀገር፡
በከተማ፡የቀሩ፡ሕዝቡን፤

ወእለ፡አምሠጡ፡ወገብኡ፡ኀቤሁ፡
አምልጠው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ የተመለ ሱትን፤

አፍለሰ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ሊቀ ፡ መበስላን ፡ ባቢሎን፡
የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን፡ማርኮ፡ሮሰደ፤

፲፡ ወእምሕዝብ ፡ ነዳያን ፡ ዘአልቦሙ ፡ ምንትኒ፡
ከሕዝቡ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሌላቸው ፡ ድሆችን፤

አትረፈ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ሊቀ ፡ መበስላን ፡ በምድረ፡ይሁዳ፡
ያዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡በይሁዳ፡ ዕፃ፡አስቀረ፡ዕደው፡ነዳያን፡ማለት፡ ነው ፤ ወይን ፡ የሚያርሙ ፡ የሚኮ ተኩቱ፡ናቸው፤

ወወሀቦሙ፡አዕፃዳተ፡ወይን፡
የወይን፡ቦታ፡ሰጣቸው፤

ወምክያዳተ፡ወይን፡
የወይን፡ዓውድማንም፡ሰጣቸው፤

፲፩፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ አዘዘ ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፡በእንተ፡ኤርምያስ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደ ነፆር፡የኤርምያስን፡ነገር፡አዘዘ፤

በእደ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፡
በአዛገሮች፡አለቃ፡በናቡዛርዳን፡ቃል፡ አዘዘ፤

፲፪፡ወይቤ፡ንሥአ፡
ወደ፡አንተ፡አስመጣው፡አለ፤

ወአዕይንቲከ፡ሢም፡ላዕሌሁ፡
በፍቅር፡እየው፤

ወኢትግበር፡ሎቱ፡ምንተኒ፡እኩየ፡
ምንም ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድር ግበት፤

ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ተናገረከ ፡ ከማሁ፡ ግበር፡ምስሌሁ፡
እርሱ፡እንደተናገረ፡በጎ፡ነገር፡አድር ግለት፡እንጂ፡በእርሱ፡ምንም፡ምን፡ ክፉ፡ነገር፡አታድርግበት፡አለ፤

፲፫፡ወፈነወ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፡
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡ላከ፤

ወኔቡሳዜካኮን ፡ ረበባሰሪስ ፡ ወኔርጋል ፡ ሴሪአጼር፡ረብማግ፡
እነዚህ፡ሁሉ፡ላኩ፤

ወኵሉ፡መላእክተ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ላኩ፤

፲፬፡ወፈነዉ፡ሰብአተ፡ዕደወ፡
ሰባት፡ሰዎች፡ላኩ፤

ወነሥእዎ፡ለኤርምያስ፡እምዓፀደ፡ሞቅሕ፡
ኤርምያስን፡ከግዞት፡ቤት፡አምጥተው፤



ወወሀብዎ፡ለጎዶልያስ፡ወልደ፡አኪቃም፡
ለአኪቃም፡ልጅ፡ለጎዶልያን፡ሰጡት፤

ወልደ፡ሳፋን፡
የሳፋን፡ልጅ፤

ያውጽኦ፡ኀበ፡ቤት፡
ወደ፡ቤት፡ያወጣው፡ዘንድ፡ሰጡት፤

ወነበረ፡ማዕከለ፡ሕዝብ፡
በሕዝቡ፡መካከል፡ኗረ፤

፲፭፡ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፡
ወደ፡ኤርምያስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ መጣ፤ተነገረ፤

እመ፡ሀሎ፡በዐፀደ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡
በግዞት፡ቤት፡ሳለ፤

እንዘ፡ይብል፡
እንዲህ፡ሲል፤

፲፮፡ ሑር ፡ በሎ ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ኢትዮ ጵያዊ፡
ለኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ሒደህ፡ንገረው፡ሲል፡በግዞት፡ቤት፡ ሳለ፡መጣ፤ተነገረ፤

ወይቤ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባዖት፡ አምላከ፡እስራኤል፡
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡አመጽእ፡ነገርየ፡በዛ፡ሀገር፡
እነሆ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አመጣለሁ፤

ለእኩይ፡ወኢኮነ፡ለሠናይ፡
ለበጎ፡ነገር፡ያይደለ፡ለክፉ፡መከራን፡ አመጣለሁ፡አለ፤

ወይከውን፡በቅድሜከ፡
በፊትህ፡ይደረጋል፤

፲፯፡ ወለከሰ ፡ አድኀነከ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፡
አንተን ፡ ግን ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከመከራ ፡ አድንሃለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወኢይሁበከ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ዕደው ፡ ዘአንተ ፡ ትፈርሆ፡እምገጸሙ፡
አንተ ፡ ከፊታቸው ፡ የተነሣ ፡ በምትፈ ራቸው፡ሰዎች፡እጅ፡አልጥልህም፤

፲፰፡እስመ፡ድኅነ፡አድኀነከ፡
ከመከራ፡አድንሃለሁና፤

ወበኵናት፡ኢትወድቅ፡
በጦር፡አትሞትም፤

ወትከውን፡ነፍስከ፡ምርካበ፡
ሰውነትህ ፡ የተድላ ፡ የደስታ ፡ የሕይወት፡መገኛ፡ትሆናለች፤ለናቡከ ደነፆር ፡ የተገዛ ፡ የሕይወት ፡ መገኛ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ ይናገር ፡ ነበርና ፡ ለኔ ፡ የተናገረልኝ፡መስሎት፤

እስመ፡ተወከልከ፡ብየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ በኔ ፡ አምነሃል ፡ ብሏልና።

## ምዕራፍ፡፵፤

፩፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡የመጣ፡የተነገረ፡የእግዚአ ብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

እምድኅረ ፡ ተፈነወ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ሊቀ ፡ መበስላን፡እምራማ፡
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡ከራማ፡ ከተላከ፡በኋላ፡የመጣ፤

ሶበ፡ነሥአ፡እንዘ፡እሡር፡በማእሠር፡
በሰንሰለት፡ታሥሮ፡ሳለ፡ባመጣው፡ጊዜ፤

www.ethiopianorthodox.org

በማዕከለ ፡ ፈላስያን ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ ወዘይሁዳ፡እለ፡ተዔወዉ፡ውስተ፡ባቢሎን፡
ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ተማርከው ፡ በሔዱ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ባመጣው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ፡የመጣ፡የተነገረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

፪፤ወነሥአ፡ሊቀ፡መበስላን፡ለኤርምያስ፡
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡ኤርምያስን፡አምጥቶ፡

ወይቤሎ፡
እንዲህ፡አለው፤

እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ነበበ ፡ ዘንተ ፡ እኩየ፡በዝንቱ፡መካን፡
ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉውን፡ነገር፡በዚህ፡ቦታ፡ተናገረ፡አለው፤

፫፤ወገብረ፡እግዚአብሔር፡በከመ፡ነበበ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አደረገ፤

እስመ፡አበስክሙ፡ሎቱ፡
ኪያሁ፡ሲል፡ነው፤እሱን፡በድላችሁ ታልና፤

ወኢሰማዕክሙ፡ቃሎ፡
ቃሉንም፡አልሰማችሁምና፤

ወኮነ፡ብክሙ፡ዝንቱ፡ነገር፡
ይህ ፡ ነገር ፡ ተደረገባችሁ ፤ እግዚአብሔር፡በናቡዛርዳን፡አድሮ፡ኤርምያስን፡ከእስራኤል፡አግብቶ፡ይዘልፈዋል፤

፬፤ ወይእዜኒ፡ናሁ፡ፈታሕኩከ፡እምነ፡መዋቅሕቲከ፡ዘእዴከ፡
እነሆ ፡ አሁንም ፡ በእጅህ ፡ ካለ ፡ ሰንሰለት፡ፈታሁህ፤

እመ ፡ ሠናየ ፡ ኮነ ፡ በቅድሜከ ፡ ለመጺእ፡ምስሌየ፡ባቢሎን፡
ከኔ፡ጋራ፡ወደ፡ባቢሎን፡መምጣት፡ከወደድክ፤

ነዓ፡
ና፤

ወእሠይም፡አዕይንትየ፡ኀቤከ፡
በፍቅር፡ዓይኔ፡አይሃለሁ፤

ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ኀቤከ ፡ እኩየ ፡ መጺአ፡ምስሌየ፡ኀቤየ፡ባቢሎን፡
ከኔ፡ጋራ፡ወደ፡ባቢሎን፡መምጣት፡ባትወድ፡ግን፤

ርኢ፡ኵሎ፡ምድረ፡ቅድሜከ፡
ሀገሩ፡ሁሉ፡በፊትህ፡ነው፡እይ፤

ንበር፡ኀበ፡ዘአደመከ፡
ከወደድከው፡ደስ፡ከሚያሰኝህ፡ቦታ፡ኑር፤

፭፤ ወግባእ ፡ ወንበር ፡ ኀበ ፡ ጎዶልያን፡ወልደ፡አኪቃም፡
ሒደህ፡ከአኪቃም፡ልጅ፡ከጎዶልያን፡ዘንድ፡ተቀመጥ፤

ወልደ፡ሳፋን፡
ከሳፋን፡ልጅ፤

ዘረሰዮ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡በምድረ፡ይሁዳ፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በይሁዳ፡ዕፃ፡የሾመው፤

ወንበር፡ምስሌሁ፡ማዕከለ፡ሕዝብ፡
ከእርሱ፡ጋራ፡በሕዝቡ፡መካከል፡ኑር፤

አው ፡ ኀበ ፡ አደመከ ፡ አዕይንቲከ ፡ ለክ ለሐዊር፡
ወይም ፡ ለመኖር ፡ ደስ ፡ ከሚያሰኝህ፡ቦታ፡ኑር፤

ወወሀበ፡ሊቀ፡መበስላን፡አምኃ፡



የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡ እጅ ፡ መንሻውን፤

ወሀብተ፡
ድርጎውን፡ሰጥቶ፤

ወፈነዎ፡
ሸኝቶ፡ሰደደው፤

፮፤ ወሖረ ፡ ኤርምያስ ፡ ኀበ ፡ ጎዶልያን ፡ ወልደ፡አኪቃም፡መሴፋ፡
ኤርምያስ ፡ በመሴፋ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ አኪቃም፡ልጅ፡ወደ፡ጎዶልያን፡ሔደ፤

ወነበረ ፡ ማዕከለ ፡ ሕዝብ ፡ ተራፍያን ፡ በምድር፡
በሀገር ፡ በቀሩ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ኖረ፤

፯፤ወሰምዑ፡ኵሉ፡መሳፍንተ፡ኃይሎሙ፡
በሠራዊቱ ፡ የተሾሙ ፡ መሳፍንቱ ፡ሁሉ፡ሰሙ፤

እለ፡እምገዳም፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ ያሉ ፡ በሠራዊቱ ፡ የተሾሙ፡መሳፍንቱ፡ሰሙ፤

እሙንቱ፡ወዕደዊሆሙ፡
እነሱም፡ሰዎች፡ሰሙ፤

ከመ ፡ ሤሞ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ለጎዶልያን ፡ ወልደ፡አኪቃም፡ውስተ፡ምድር፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የአኪቃም፡ልጅ፡ጎዶልያንን፡በሀገር፡እንደሾመው፡ሰሙ፤

ወከመ፡አዕቀቦ፡ዕደወ፡ወአንስተ፡
ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ እንደ ፡አስጠበቀ፤

ወሕፃናተ፡ወነዳያነ፡ምድር፡እለ፡ኢፈለሱ፡ባቢሎን፡
ሕፃናቱንና፡ወደ፡ባቢሎን፡ተማርከው፡ያልሔዱ ፡ የሀገር ፡ ድሆችን ፡ እንደ ፡አስጠበቀ፡ሰሙ፤

፰፤ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ ጎዶልያን ፡ መሴፋ ፡ እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፡
በመሴፋ፡ወደ፡አለ፡ወደ፡ጎዶልያን፡ሔዱ፤የናታንዩ፡ልጅ፡እስማኤል፤

ወዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፡
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤

ወሶርያልስ፡ወልደ፡ናታናሐሚት፡
የናታናሐሚት፡ልጅ፡ሶርያልስ፡

ወደቂቀ፡ዖፌ፡
የዖፌ፡ልጅ፤

ወልደ፡ኒሙፋጤ፡
የኒሙፋጤ፡ልጅ፤

ወኢያዛንያስ፡ወልደ፡ሞቃጤ፡
የሞቃጤ፡ልጅ፡ኢያዛንያስ፡

እሙንቱ፡ወሰብአሙ፡
እነዚህ፡ሰዎቻቸው፡ወደ፡ጎዶልያን፡ሔዱ፤

፱፤ ወመሐለ ፡ ሎሙ ፡ ጎዶልያን ፡ ወልደ ፡ አኪቃም፡
የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያን ፡ማለላቸው፤

ወልደ፡ሳፋን፡
የሳፋን፡ልጅ፤

በእንቲአሆሙ፡ምስለ፡ሰብአሙ፡
ከሰዎቻቸው፡ጋር፡ለእነሱ፡ማለላቸው፤

ወይቤሎሙ፡
እንዲህ፡አላቸው፤

ኢትፍርሁ፡እምተቀንዮ፡ከለዳውያን፡
ከከለዳውያን ፡ መገዛት ፡ አትፍሩ ፡አላቸው፤

ንበሩ፡ውስተ፡ምድር፡

www.ethiopianorthodox.org

በሀገራችሁ፡ኑሩ፤
ወተቀነዩ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
ለባቢሎን፡ንጉሥ፡ተገዙ፤
ወይኄይሰክሙ፤
ለእርሱ ፡ መገዛት ፡ ይሻላችኋል ፡
አላቸው፤

፲፤ ወአነ ፡ ነየ ፡ እነብር ፡ ማዕከሎሙ ፡
በመሴፋ፤
እኔም ፡ በመሴፋ ፡ በመካከላቸው ፡
እኖራለሁ፤
ወእቀውም፡ቅድመ፡ገጸሙ፡ለከለዳውያን፡
እለ፡ይመጽኡ፡ኀቤነ፤
ወደ፡እኛ፡በሚመጡ፡በከለዳውያን፡
ፊት፡እቀመጣለሁ፤
ወአንትሙሰ፡አስተጋብኡ፡ወይነ፤
እናንተ፡ግን፡ወይኑን፤
ወቀምሐ፤
ፍሬውን፤
ወቅብዓ፤
ዘይቱን፡ሰብስባችሁ፤
ወደዩ፡ውስተ፡ቀሳውቲክሙ፤
በዕቃችሁ፡ጨምሩ፤
ወኅድሩ፡ውስተ፡አህጉር፡ዘአኀዝክሙ፤
በያዛችኋቸው፡አገሮች፡ኑሩ፡አላቸው፤

፲፩፤ ወኵሉ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡
ምድረ፡ሞዓብ፤
በሞዓብ ፡ አውራጃ ፡ የሚኖሩ ፡
አይሁድ፡ሁሉ፤
ወደቂቀ፡አሞን፡ወኤዶም፤
የአሞንና፡የኤዶም፡ልጆች፡ሁሉ፤
ወኵሎሙ፡እለ፡ውስተ፡ምድር፤
በሀገር፡ያሉ፡ሰዎች፡ሁሉ፤
ሰምዑ፡ከመ፡ወሀበ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ተረፈ፡
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ከይሁዳ፡የቀሩትን፡
እንደ፡ሰጠው፡ሰሙ፤
ወከመ ፡ ሤሞ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለጎዶልያን ፡
ወልደ፡አኪቃም፤
የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያንን ፡
በእነርሱ፡ላይ፡እንደ፡ሾመው፡ሰሙ፤
ወልደ፡ሳፋን፤
የሳፋን፡ልጅ፤

፲፪፤ ወተመይጡ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡
እምኵሉ፡መካናት፤
አይሁድ፡ሁሉ፡ከየቦታው፡ተመለሱ፤
እምኀበ፡ተዘርዉ፡ሀየ፤
ከተበተኑበት፡ቦታ፡ተመልሰው፤
ወመጽኡ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ይሁዳ ፡ ኀበ፡
ጎዶልያን፡ውስተ፡መሴፋ፤
በመሴፋ ፡ ያለ ፡ ጎዶልያን ፡ ወደ ፡
አለበት፡ወደ፡ይሁዳ፡ዕፃ፡መጡ፤
ወአስተጋብኡ፡ወይነ፤
ወይኑን፤
ወቀምሐ፡ብዙኀ፡ፈድፋደ፤
እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ ፍሬውን ፡ ይሰበ
ስባሉ፤

፲፫፤ወዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤
ወኵሎሙ፡መሳፍንተ፡ኃይሎሙ፤
በሠራዊቱ፡ላይ፡የተሾሙ፡መሳፍንቱ፤
እለ፡ውስተ፡ገዳም፤
በምድረ፡በዳ፡ያሉ፤
መጽኡ፡ኀበ፡ጎዶልያን፡ውስተ፡መሴፋ፤
በመሴፋ፡ወደ፡አለ፡ወደ፡ጎዶልያን፡
መጡ፤



እመ ፡ አእምሮ ፡ ተአምር ፡ ከመ ፡ በኤላሞን ፡
ንጉሠ ፡ ደቂቀ ፡ አሞን ፡ ፈነወ ፡ እስማኤልሃ ፡
ወልደ ፡ ናታንዩ ፡ ኀቤከ ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡
ነፍሰከ፤
የአሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ በኤላሞን ፡
አንተን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ የናታንዩ ፡
ልጅ፡እስማኤልን፡ወዳንተ፡እንደ፡ላከ፡
ብታውቅስ ፡ ዝም ፡ ባላልህም ፡ ነበር ፤
አንድም ፡ እመ ፡ አእምሮ ፡ አእመርከ ፤
ዕውቀት ፡ ቢኖርህስ ፡ የአሞን ፡ ልጆች ፡
ንጉሥ ፡ በኤላሞን ፡ ሰውነትህን ፡
ይገድል፡ዘንድ፡የናታንዩ፡ልጅ፡እስማ
ኤልን፡ወደ፡አንተ፡ላከ፡አሉት፤
ወኢአምኖሙ፡ጎዶልያን፡ወልደ፡አኪቃም፤
የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያን ፡ አላመና
ቸውም፤

፲፮፤ወዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤
ይቤሎ፡ለጎዶልያን፡በኅቡዕ፡በመሴፋ፤
በኅቡዕ ፡ በቆይታ ፤ አንድም ፡ በኅቡዕ ፡
በመሴፋ፡ጎዶልያንን፡እንዲህ፡አለው፤
እሑር ፡ እቅትሎ ፡ ለእስማኤል ፡ ወልደ ፡
ናታንዩ፤
ሔጄ ፡ የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡
ልግደለው፤
እንዘ፡አልቦ፡ዘየአምር፤
የሚያውቅ፡ሰው፡ሳይኖር፡ልግደለው፡
አለው፤
ከመ፡ኢይቅትል፡ነፍሰከ፤
አንተን፡እንዳይገድል፤
ወይዘረዉ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡
ተጋብኡ፡ኀቤከ፤
ወደ ፡ አንተ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አይሁድ ፡

ወይትኃጐሉ፡እለ፡ተርፉ፡አይሁድ፤
ከሞት ፡ የቀሩ ፡ አይሁድ ፡ ይጠፋሉ ፡
አለው፤

፲፯፤ ወይቤሎ ፡ ጎዶልያን ፡ ወልደ ፡
አኪቃም፡ለዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የአኪቃም፡ልጅ፡ጎዶልያን፡የቃርሔ፡
ልጅ፡ዮሐናንን፡እንዲህ፡አለው፤
ኢትግበር፡ዘንተ፡ነገረ፤
ይህን፡ነገር፡አታድርግ፤
እስመ ፡ ሐሰተ ፡ ትብል ፡ አንተ ፡ ላዕለ ፡
እስማኤል፤
አንተ ፡ በእስማኤል ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡
ነገርን፡ተናግረሃልና።

## ምዕራፍ፡፵፩

### ጉባዔ፤

፩፤ወኮነ፡በሳብዕ፡ወርኅ፤
በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በጥቅምት ፡
እንዲህ፡ሆነ፤
መጽአ፡እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፤
ኮነ ፡ ያለውን ፡ መጽአ ፡ ብሎ ፡ አመ
ጣው ፤ የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል፡
መጣ፤
ወልደ፡ኤልሰማ፤
የኤልሰማ፡ልጅ፤
እምዘመደ፡መንግሥት፤
ከዘመደ፡መንግሥት፡የሚሆን፤
ወመገብተ፡ንጉሥ፤
የንጉሥ፡ሹማምንት፡መጡ፤
ወአሠርቱ፡ሰብእ፡ምስሌሁ፤
አሥር፡ሰዎች፡ከእርሱ፡ጋር፡መጡ፤
ኀበ፡ጎዶልያን፡ወልደ፡አኪቃም፡በመሴፋ፤
በመሴፋ፡ወደ፡አለ፡ወደ፡አኪቃም፡
ልጅ፡ወደ፡ጎዶልያን፡መጡ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበልዐ፡ህየ፡እከለ፡ኅቡረ፡በመሴፋ፡
በመሴፋ፡አንድነት፡እህል፡በሉ፤

፪፤ ወተንሥአ ፡ እስማኤል ፡ ወልደ ፡ ናታንዩ፡
የናታንዩ፡ልጅ፡እስማኤል፡ተነሥቶ፤
ወአሠርቱ፡ዕደው፡እለ፡ምስሌሁ፡
ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው፤
ወቀተልዎ፡ለጎዶልያን፡ወልደ፡አኪቃም፡
የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያንን ፡ ገደሉት፤
ወልደ፡ሳፋን፡በመጥባሕት፡
የሳፋንን፡ልጅ፡ጎዶልያንን፡በሰይፍ፡ ገደሉት፤
ወቀተልዎ፡ለዘሤሞ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ላዕለ፡ምድር፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሾመውን፡ገደሉት፤

፫፤ ወለኵሎሙ፡አይሁድ፡እለ፡ምስሌሁ፡ ለጎዶልያን፡በመሴፋ፡
በመሴፋ ፡ ከጎዶልያን ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ አይሁድን፡ሁሉ፡ገደሏቸው፤
ወለኵሎሙ ፡ ከለዳውያን ፡ እለ ፡ ተረክቡ ፡ በህየ፡
በዚያ፡የተገኙ፡ከለዳውያንን፡ሁሉ፤
ወኵሎ ፡ ዕደወ ፡ መስተቃትላነ ፡ ቀተለ ፡ እስማኤል፤
አርበኞችን፡ሁሉ፡እስማኤል፡ገደለ፤

፬፤ወኮነ፡በሣኒታ፡ዕለት፡
በማግሥቱ፡እንዲህ፡ሆነ፤
እምዘቀተሎ፡ለጎዶልያን፡እስማኤል፡
እስማኤል ፡ ጎዶልያንን ፡ ከገደለው ፡ በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤

ወአልቦ፡ሰብእ፡ዘየአምሮ፡
የሚያውቀው፡ሰው፡አልነበረም፤

፭፤ወመጽኡ፡ዕደው፡እምሴኬም፡
ከሴኬም፡ሰዎች፡መጡ፤
ወእምሴሎ፡
ከሴሎ፤
ወእምሰማርያ፡
ከሰማርያ፤
ሰማንያ፡ዕደው፡
ሰማንያ፡ሰዎች፡መጡ፤
ልጹያን፡አጽሐሚሆሙ፡
በዘመዶቻቸው ፡ ሞት ፡ አዝነዋልና፡ ጢማቸውን፡ተላጭተው፤
ወስጡጥ፡አልባሲሆሙ፡
ልብሳቸውን፡ቀድደው፡አስልበው፤
ወልሕዋን፡
አዝነው፤
ወመሐና፡
እጅ፡መንሻውን፤
ወሊባኖስ፡ውስተ፡እደዊሆሙ፡
ሽቱውን፡በእጃቸው፡ይዘው፡መጡ፤
ከመ፡ያብኡ፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያገቡ፡ ዘንድ፤

፮፤ወወጽአ፡እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፡
ከመ፡ይትቀበሎሙ፡እመሴፋ፡
ከመሴፋ ፡ ይቀበላቸው ፡ ዘንድ፡
የናታንዩ፡ልጅ፡እስማኤል፡ወጣ፤
ወሖረ፡
ሔደ፤
ወይበኪ፡እንዘ፡የሐውር፡
ሲሔድ፡ያለቅስ፡ነበር፤



ወኮነ፡ሶበ፡ቀርቦሙ፡
በቀረባቸው፡ጊዜ፡እንዲህ፡ሆነ፤
ይቤሎሙ፡
እንዲህ፡አላቸው፤
ባኡ ፡ ምስሌየ ፡ ኀበ ፡ ጎዶልያን ፡ ወልደ ፡ አኪቃም፡
ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ፡ጎዶልያን፡ግቡ፡አላቸው፤

፯፤ወኮነ፡ሶበ፡ቦኡ፡ማዕከለ፡ሀገር፡
ወደ ፡ ከተማ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ፤
ቀተሎሙ፡እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፡
የናታንዩ፡ልጅ፡እስማኤል፡አጠፋቸው፤
ወወረውዎሙ፡ውስተ፡ግብ፡
ወደ፡ጕድጓዱ፡ወረወሯቸው፤
ውእቱ፡ወዕደው፡እለ፡ምስሌሁ፡
እርሱና ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ጣሏቸው፤

፰፤ወአሠርቱ፡ሰብእ፡እለ፡ተረክቡ፡በህየ፡
በዚያ፡የተገኙ፡አሥሩ፡ሰዎች፤
ቀርቡ፡ወይቤልዎ፡ለእስማኤል፡
ቀርበው፡እስማኤልን፡እንዲህ፡ አሉት፤
ኢትቅትለነ፡
አትግደለን፡አሉት፤
እስመ፡ብነ፡መዝገብ፡በሐቅል፡
በምድረ፡በዳ፡ድልብ፡አለንና፤
ሥርናይ፡
ስንዴ፤
ወሠገም፡
ገብስ፤
መዓር፡
ማር፤
ወቅብዕ፡
ቅቤ፡አለንና፡አትግደለን፡አሉት፤
ወሐደገ ፡ እንከ ፡ ቀቲሎቶሙ ፡ በማዕከለ ፡ አኃዊሆሙ፡
በወንድሞቻቸው ፡ መሐከል ፡ መግደልን፡ተወ፤

፱፤ ወወገረ ፡ እስማኤል ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ለዕደው ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡ ምስለ ፡ ጎዶልያን ፡ ውስተ፡ግብ፡ዓቢይ፡
እስማኤል ፡ ከጎዶልያን ፡ ጋራ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎችን፡ሬሳቸውን፡በጕድጓድ፡ጣለ፤
ውእቱኬ ፡ ዘገብረ ፡ ንጉሥ ፡ አሣ ፡ ቅድመ ፡ ባኦስ፡ንጉሠ፡እስራኤል፡
ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባኦስ ፡ ፊት ፡ የተነሣ፡ንጉሡ፡አሣ፡የሠራው፡ነው፤
ዘንተ፡ግበ፡መልዓ፡
ይህንን፡ጕድጓድ፡መላ፤
ወፈጸመ ፡ እስማኤል ፡ ወልደ ፡ ናታንዩ ፡ ቅቱላነ፡
የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ የሞቱትን፡ሰዎች፡ሬሳ፡ጥሎ፡ጨረሰ፤

፲፤ ወሜጠ ፡ እስማኤል ፡ ኵሎ ፡ ሕዝበ ፡ ተራፍያነ፡ዘውስተ፡መሴፋ፡
እስማኤል ፡ በመሴፋ ፡ ያሉ ፡ ከሞት ፡ የቀሩ፡ሕዝቡን፡ሁሉ፡መለሰ፤
ወአዋልደ፡ንጉሥ፡
የንጉሡ፡ሴቶች፡ልጆችን፤
ወኵሎ፡እለ፡ተርፉ፡ሕዝበ፡ዘአዕቀቦ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፡ለጎዶልያን፡ወልደ፡ አኪቃም፡
የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያን ፡ በመሴፋ ፡ ያስጠበቀውን ፡ ከሞት ፡ የቀሩ፡ሕዝቡን፡መለሰ፤
ወጌሠ፡እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፡

www.ethiopianorthodox.org

የናታንዩ፡ልጅ፡እስማኤል፡ተነሥቶ፡
ሔደ፤

ወመጽአ፡ለአዲው፡ኀበ፡ደቂቀ፡አሞን፥
ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ተሻግሮ ፡
ለመሔድ፡መጣ፤

፲፩፤ወሰምዐ፡ዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፡ሰማ፤

ወኵሉ፡መላእክተ፡ኃይሎሙ፡እለ፡ምስሌሁ፤
ከእርሱ፡ጋራ፡ያሉ፡በሠራዊቱ፡ላይ፡
የተሾሙ፡አለቆች፡ሁሉ፡ሰሙ፤

ኵሎ ፡ እኩየ ፡ ዘገብረ ፡ እስማኤል ፡ ወልደ ፡
ናታንዩ፤
የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ያደረ
ገውን፡ሁሉ፡ሰሙ፤

፲፪፤ወአስተጋብኡ፡ኵሎ፡ሠራዊተ፤
ሠራዊቱን፡ሁሉ፡ሰብስበው፤

ወሖሩ ፡ ይታቀተሉ ፡ ምስለ ፡ እስማኤል ፡
ወልደ፡ናታንዩ፤
ከናታንዩ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ጋራ ፡
ሊዋጉ፡ሔዱ፤

ወረከቡ፡በኀበ፡ማይ፡ብዙኅ፡በገባዖን፤
ብዙ፡ውሀ፡ባለበት፡በገባዖን፡
አገኘው፤

፲፫፤ ወኮነ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡
ዘምስለ፡እስማኤል፤
ከእስማኤል፡ጋራ፡ያሉ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡
ባዩ፡ጊዜ፤

ዮሐናንሃ፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናንን፡ባዩ፡ጊዜ፡
እንዲህ፡ሆነ፤

ወኵሎ፡ሠራዊተ፡ዘምስሌሁ፤
ከሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡
ባዩ፡ጊዜ፤

ተፈሥሑ፤
ኮነ ፡ ያለውን ፡ ተፈሥሑ ፡ ብሎ ፡
አመጣው፡ደስ፡አላቸው፤

፲፬፤ ወተመይጡ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ዘፄወወ፡
እስማኤል፡እመሴፋ፤
ከመሴፋ ፡ እስማኤል ፡ የማረካቸው፡
ሕዝቡ፡ሁሉ፡ተመለሱ፤

ወገብኡ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ ዮሐናን ፡ ወልደ፡
ቃርሔ፤
ተመልሰው፡ወደ፡ቃርሔ፡ልጅ፡ወደ፡
ዮሐናን፡ሔዱ፤

፲፭፤ ወእስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ፡ድኅነ፡
ምስለ፡፰ቱ፡ዕደው፡እምገጸ፡ዮሐናን፤
የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤልም ፡
ከዮሐናን፡ፊት፡የተነሣ፡ከስምንቱ፡
ሰዎች፡ጋራ፡ዳነ፤

ወዐደወ፡ኀበ፡ደቂቀ፡አሞን፤
ወደ፡አሞን፡ልጆች፡ተሻግሮ፡ሔደ፤

፲፮፤ወነሥአ፡ዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤

ወኵሎ፡ሠራዊተ፡ኃይሎሙ፡እለ፡ምስሌሁ፤
ከሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ፡
ይዞ፤

ኵሎሙ፡እለ፡ተርፉ፡ሕዝበ፤
ከሞት፡የቀሩ፡ሕዝቡን፡ሁሉ፡ይዞ፤

እለ፡ገብኡ፡ኀበ፡እስማኤል፡ወልደ፡ናታንዩ
እመሴፋ፤
ከመሴፋ፡ወደ፡ናታንዩ፡ልጅ፡ወደ፡
እስማኤል፡የተመለሱትን፤

እምድኅረ ፡ ቀተሎ ፡ ለጎዶልያን ፡ ወልደ፡
አኪቃም፤
የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያንን፡
ከገደለው፡በኋላ፤



ዕደወ፡ኃያላነ፡መስተቃትላነ፡
አርበኞችን፤

ወአንስቶሙ፤
ሚስቶቻቸውን፤

ወሕፃናቲሆሙ፤
ልጆቻቸውን፤

ወእለ፡ተርፉ፡ሕፅዋን፤
ከሞት፡የቀሩ፡ባለሟሎቹን፤

እለ፡ገብኡ፡እምገባኦን፤
ከገባኦን፡የተመለሱትን፡ይዞ፤

፲፯፤ወሖሩ፤
ሔዱ፤

ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ቤሮት ፡ ዘቅሩብ ፡
ኀበ፡ቤተ፡ልሔም፤
የቤተ ፡ ልሔም ፡ አቅራቢያ ፡ በም
ትሆን ፡ በግብፅ ፡ አፋፍ ፡ ባለች ፡
በቤሮት፡ተቀመጡ፤

ከመ፡ይሑሩ፡ወይባኡ፡ውስተ፡ግብፅ፤
ሒደው፡በግብፅ፡ይኖሩ፡ዘንድ፤

፲፰፤እምገጸ፡ከለዳውያን፤
ከከላዳውያን፡ፊት፡የተነሣ፤

እስመ፡ፈርሁ፡እምገጾሙ፤
ከፊታቸው፡የተነሣ፡ፈርተዋልና፤

እስመ ፡ ቀተለ ፡ እስማኤል ፡ ወልደ ፡ ናታንዩ ፡
ጎዶልያንሃ፡ወልደ፡አኪቃም፤
የናታንዩ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ የአ
ኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያንን ፡ ስለገ
ደለው፤

ዘሤሞ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡በምድር፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
የሾመውን፡ስለገደለ።

## ምዕራፍ፡፵፪

፩፤ ወመጽኡ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክተ፡
ኃይሎሙ፤
በሠራዊቱ፡የተሾሙ፡አለቆች፡ሁሉ፡
መጡ፤

ወዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤

ወኢያዛንያስ፡ወልደ፡ሐናንያ፤
የሐናንያ፡ልጅ፡ኢያዛንያስ፤

ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ንዑስ ፡ ወዓቢይ ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡
ወደ፡ነቢዩ፡ወደ፡ኤርምያስ፡መጡ፤

፪፤ወይቤሉ፤
እንዲህ፡አሉ፤

ይደቅ፡ምሕረትነ፡ቅድመ፡ገጽከ፤
ልመናችን፡ከፊትህ፡ይድረስ፤

ወጸሊ ፡ በእንቲአነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፤
ስለ፡እኛ፡ወደ፡ፈጣሪያችን፡ወደ፡እግ
ዚአብሔር፡ለምንልን፤

በእንተ፡እሉንቱ፡እለ፡ተርፉ፤
ከሞት፡ስለ፡ቀሩ፡ስለነዚህ፤

እስመ፡ተረፍነ፡ኅዳጣን፡እምብዙኃን፤
ከብዙዎች፡ጥቂቶች፡ቀርተናልና፤

በከመ፡አዕይንቲከ፡ይሬጽራ፤
ዓይኖችህ ፡ እንደሚያዩን ፡ ጥቂቶች ፡
ቀርተናልና፤

፫፤ወያይድዓነ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡
ፍኖተ፡እንተ፡ባቲ፡ነሐውር፤
ፈጣሪያችን፡እግዚአብሔር፡የምንሔ
ድበትን፡ጐዳና፡ይንገረን፤

ወነገረ፡ዘንገብር፤
የምናደርገውን፡ነገር፡ይንገረን፡አሉ፤

፬፤ ወይቤሎሙ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ነቢዩ፡ኤርምያስ፡እንዲህ፡አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

ሰማዕኩክሙ፡
ሰማኋችሁ፤
ናሁ፡አነ፡እጼሊ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡አምላ
ክክሙ፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር፡እለምናለሁ፤
በከመ፡ቃልክሙ፤
እንደ፡ተናገራችሁ፡እለምናለሁ፤
ወዘአውሥአኒ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አየድ
ዓክሙ፤
የነገረኝን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
እነግራችኋለሁ፤
ወኢየኀብዕ፡እምኔክሙ፡ቃለ፡ወኢአሐደ፤
አንድ ፡ ቃልስ ፡ እንኳ ፡ ምንም ፡ ምን ፡
ከእናንተ፡አልሠውርም፤

፭፤ወይቤልዎ፡እሙንቱ፡ለኤርምያስ፤
እነሱ፡ኤርምያስን፡እንዲህ፡አሉት፤
ይኩን፡እግዚአብሔር፡ስምዓ፡ጽድቅ፤
እግዚአብሔር፡የእውነተኛ፡ምስክርን፡
ይሁን፤
ወምዕመነ፤
የታመነን፡ይሁን፤
በከመ፡ኵሉ፡እንተ፡ለአከከ፡እግዚአብሔር፡
አምላክከ፡ነገረ፡ኀቤነ፤
ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
እንደላከህ፡የላከህን፡ሁሉ፤
ከማሁ፡ንገብር፤
እንደዚሁ፡እናደርጋለን፡አሉት፤

፮፤እመሂ፡ሠናየ፡ወእመሂ፡እኩየ፤
ክፉም፡ቢሆን፡በጎም፡ቢሆን፡እናደር
ጋለን ፡ አለ፤ ሠናየ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡
መሔዱን፡ለእነሱ፡በጎ፡መስሎ፡ታይ
ቷቸዋልና፤
ወእኩየ ፡ መቅረቱን ፡ ነው፡ ክፉ ፡
መስሎ ፡ ታይቷቸዋልና ፤ አንድም ፡
ሠናየ፡አለ፡መሔዱ፡ለእነርሱ፡በጎ፡
ነውና፤ወእኩየ፡መሔዱ፡ክፉ፡ነውና፤
ወቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ዘለሊነ፡
ለአክናከ፡ኃቤሁ፡ንሰምዕ፤
እኛ፡ወደእሱ፡የላክንህ፡የፈጣሪያችን፡
የእግዚአብሔርን፡ቃል፡እንሰማለን፤
ከመ፡ይኩን፡ሠናይ፡ላዕሌነ፤
ለኛ፡በጎ፡ነገር፡ይደረግልን፡ዘንድ፤
እስመ ፡ ንሰምዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፤
የፈጣሪያችን፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡
እንሰማለንና፤

፯፤ወኮነ፡እምድኅረ፡ዐሡር፡ዕለት፤
ከአሥር፡ቀን፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤
ኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፡
ወትሮ ፡ ፈጥኖ ፡ ይሰማው ፡ ነበር፤
አሁን፡ ግን ፡ ሕዝቡን ፡ የተጣላበት፡
ወራት፡ነውና፡በዐሥረኛ፡ቀን፡ወደ፡
ኤርምያስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ተነገረ፤

፰፤ወጸውዖ፡ለዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናንን፤
ወለኵሎሙ ፡ መላእክተ ፡ ኃይል ፡ እለ ፡
ምስሌሁ፤
ከሱ፡ጋራ፡ያሉ፡በሠራዊቱ፡የተሾሙ፡
አለቆችንም፡ጠርቶ፤
ወለኵሎሙ፡ሕዝብ፡ንዑስ፡ወዓቢይ፤
ታላቁንም ፡ ታናሹንም ፡ ወገኖች ፡
ጠርቶ፤

፱፤ወይቤሎሙ፤
እንዲህ፡አላቸው፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡
እስራኤል፤



የእስራእል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ፡አለ፤
በእንተ፡ዘፈነውክሙኒ፡ኀቤሁ፡
ወደ፡እሱ፡ስለላካችሁኝ፤
ከመ፡ይደቅ፡ሣህልክሙ፡ቅድሜሁ፡
ልመናችሁ ፡ በፊቱ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡
እንዲህ፡አለ፤

፲፤ እመ ፡ ነቢረ ፡ ነበርክሙ ፡ ውስተ ፡ ዝ ፡
ምድር፤
በዚህ፡ሀገር፡ፀንታችሁ፡ብትኖሩ፤
አሐንፀክሙ፤
በረድዔት፡አንፃችኋለሁ፤
ወኢይነሥተክሙ፤
በሞት፡አላፈርሳችሁም፤
ወእተክለክሙ፤
እተክላችኋለሁ፤ በሀገራችሁ ፡ አፀናች
ኋለሁ፤
ወኢይመልሐክሙ፤
አላስማርካችሁም፤
እስመ ፡ ነሳሕኩ ፡ እምእኩይ ፡ ዘሐለይኩ ፡
እግበር፡ላዕሌክሙ፤
በእናንተ ፡ ላይ ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፤ ከአ
ሰብኩት ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ተመልሼ ያለ
ሁና፤

፲፩፤ኢትፍርሁ፡እምገጸ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ከናቡከደነፆር ፡
ገጸ፡መዓት፡የተነሣ፡አትፍሩ፤
ዘአንትሙ፡ትፈርሁ፡እምቅድሜሁ፤
ከፊቱ፡የተነሣ፡እናንተ፡የምትፈሩት፤
ኢትፍርህዎ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ለትፍሩት፡አለ፡እግዚአብሔር፤
እስመ፡ምስሌክሙ፡አነ፤
እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ በረድኤት ፡
አለሁና፤
ከመ ፡ አድኅንክሙ ፡ ወእባልሕክሙ ፡
እምእዴሁ፤
ከእጁ፡ፈጽሜ፡አድናችሁ፡ዘንድ፤

፲፪፤ወእሁበክሙ፡ሣህለ፤
ይቅርታን፡እሰጣችኋለሁ፤
ወእሠሃለክሙ፤
ይቅር፡እላችኋለሁ፤
ወአነብረክሙ፡ውስተ፡ምድርክሙ፤
ጠላት፡ጠፍቶላችሁ፡ተዘልላችሁ፡በሀ
ገራችሁ፡ፀንታችሁ፡እንድትኖሩ፡አደ
ርጋለሁ፤

፲፫፤ ወእመሰ ፡ ትቤሉ ፡ አንትሙ ፡
ኢንነብር፡ውስተ፡ዛ፡ሀገር፤
እናንተ ፡ በዚች ፡ ሀገር ፡ ጸንተን ፡
አንኖርም፡ብትሉ፤
ከመ ፡ ኢንስማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፡
የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል፡እንዳንሰማ፤

፲፬፤ ዳዕሙ ፡ ንበውእ ፡ ውስተ ፡ ምድረ፡
ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡አገር፡እንገባለን፡እንጂ፤
ወኢንሬኢ፡ቀትለ፤
ሰልፍን፡አናይም፡ብትሉ፤
ወኢንሰምዕ፡ቃለ፡ቀርን፤
የነጋሪቱን፡ድምፅ፡አንሰማም፤
ወኢንፄነስ፡እክለ፤
እህል፡አጥተን፡አንቸገርም፤
ወንነብር፡ህየ፤
በግብፅ፡አገር፡እንኖራለን፡ብትሉ፤

፲፭፤በእንተ፡ዝንቱ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
ተረፈ፡ይሁዳ፤
ስለዚህ፡ነገር፡ከይሁዳ፡የቀራችሁ፡የእ
ግዚአብሔርን፡ቃል፡ስሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡
እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፤
እስመ፡አንትሙ፡ወሀብክሙ፡ገጸክሙ፤
እናንተ ፡ ገጸ ፡ ልቡናችሁን ፡ መልሳች
ኋልና፤
ከመ፡ትባኡ፡ውስተ፡ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡ትገቡ፡ዘንድ፤
ወቦእክሙ፡ከመ፡ትንበሩ፡ህየ፤
በዚያ፡ትኖሩ፡ዘንድ፡ገብታችኋልና፡
ስሙ፤
፲፮፡ ወይከውን ፡ ኵናት ፡ ዘአንትሙ ፡
ትፈርሁ፡እምቅድመ፡ገጹ፤
ከባቢሎን፡ንጉሥ፡ከናቡከደነፆር፡ገጸ፡
መዓት ፡ የተነሣ ፡ እናንተ ፡ የምት
ፈሩት፡ጦር፡ይመጣባችኋል፤
በህየ፡ይረክበክሙ፡በምድረ፡ግብፅ፤
በግብፅ፡ጦር፡ያገኛችኋል፤
ወረሀብኒ፡ዘአንትሙ፡ፈራህክሙ፡እምኔሁ፡
ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ እናንተ ፡ የምት
ፈሩት፡ቀጠናም፤
ህየ፡ይተሉክሙ፡ድኅሬክሙ፡ግብፀ፤
በኋላ ፡ በኋላችሁ ፡ እናንተን ፡ እየተ
ከተለ፡ይመጣል፤
ወበህየ፡ትመውቱ፤
በእዚያ፡ትሞታላችሁ፤
፲፯፡ ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ረሰዩ፡
ገጾሙ፤
ፊታቸውን ፡ የመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ፡
እንዲህ፡ሆኑ፤
ከመ፡ይሑሩ፡ውስተ፡ምድረ፡ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡ይሔዱ፡ዘንድ፤
ይሕድሩ፡ህየ፤
በዚያ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን፡
የመለሱ፡ሰዎች፡ሁሉ፡እንዲህ፡ሆኑ፤
በኵናት፤
በጦር፤

ወበረኃብ፡ወበብድብድ፡የሐልቁ፤
በቀጠና፡በቸነፈር፡ይጠፋሉ፤
ወኢይድኅኑ፤
ከሞት፡አይድኑም፤
ወኢአሐዱ ፡ እምእኩይ ፡ ዘአነ ፡ አመጽእ ፡
ላዕሌሆሙ፤
እኔ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ከማመጣው ፡
ከክፉ፡ነገር፡አንድ፡ሰው፡አይድንም፤
፲፰፡እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ፡ኃያላን፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡የመላእክት፡ጌታ፡
እንዲህ፡ብሏልና፤
በከመ ፡ ወረደ ፡ መዓትየ ፡ ወመቅሠፍትየ ፡
ላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም፡በሚኖሩ፡ሰዎች፡ላይ፡
መዓቴ፡መቅሠፍቴ፡እንደመጣ፤
ከማሁ፡ይወርድ፡ላዕሌክሙ፡መዓትየ፤
እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ መዓቴ ፡ በእናንተ፡
ይመጣባችኋል፤
እምከመ፡ቦእክሙ፡ውስተ፡ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡ከገባችሁ፡በኋላ፡ይመጣባ
ችኋል፤
ወትከውኑ፡ለመሐላ፤
ለመሐላ ፡ ትሆናላችሁ ፤ እስራኤልን፡
ያጠፋ፡ያጥፋህ፤እስራኤልን፡የረገመ፡
ይርገምህ፡እያሉ፤
ወለተነሥቶ፤
ሰጥፋት፤
ወለመርገም፤
ለመርገም፤
ወለፅዕለት፡
ለስድብ፡ትሆናላችሁ፤
ወኢትሬእይዋ፡ለዛቲ፡መካን፤
ዳግመኛ፡ይህቺን፡ቦታ፡አታይዋትም፤
፲፱፡ ከመዝ ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ላዕሌክሙ፤



እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡
እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ፤
እለ፡ተረፍክሙ፡እምነ፡ይሁዳ፤
ከይሁዳ ፡ ከሞት ፡ የቀራችሁ ፡ ሰዎች፡
በእናንተ፡ላይ፡ተናገረ፤
ወኢትባኡ፡ውስተ፡ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡አትግቡ፤
ወይእዜኒ፡አእምሮ፡አእምሩ፤
አሁንም፡ፈጽማችሁ፡ዕወቁ፤
ከመ፡አስማዕኩ፡ለክሙ፡ዮም፤
ዛሬ፡እንደ፡አዳኘሁባችሁ፡እወቁ፤
፳፡እስመ፡ስሕትክሙ፡በነፍስክሙ፤
በሰውነታችሁ፡ስታችኋልና፤
እስመ፡አንትሙኒ፡ፈነውክሙኒ፡ኀበ፡እግዚ
አብሔር፡አምላክክሙ፤
ወደ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እናንተ፡ልካችሁኛልና፤
እንዘ፡ትብሉ፡ጸሊ፡ለነ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
አምላክነ፤
ወደ፡ፈጣሪያችን፡ወደ፡እግዚአብሔር፡
ለምንልን፡ብላችሁ፡ልካችሁኛልና፤
ወበከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘነበበከ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላክነ፡ንግረነ፤
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ፡ ነገ
ረህ፡የነገረህን፡ሁሉ፡ንገረን፡ብላችሁ፤
ከማሁ፡ንገብር፤
እንደዚሁ፡እናደርጋለን፡ብላችሁ፡ልካ
ችሁኛልና፤
፳፩፡ወነገርኩክሙ፡ዮም፡
ዛሬ፡ነገርኋችሁ፤
ወኢሰማዕክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላ
ክክሙ፤
የፈጣሪያችሁ ፡ የእግዚአብሔርን፡
ቃል፡አልሰማችሁም፤
በከመ፡ኵሉ፡ዘለዐከኒ፡ኀቤክሙ፡
ወደ፡እናንተ፡እንደ፡ላከኝ፡የላከኝን፡
አልሰማችሁም፤
፳፪፡ ወ...

አሁንም፡እወቁ፤
ከመ ፡ በኵናት ፡ ወበረኃብ ፡ ወበሞት ፡
ተሐልቁ፤
በጦር፤በቀጠና፤በሞት፤እንድትጠፉ፡
እወቁ፤
በመካን፡ኀበ፡አንትሙ፡መከርክሙ፤
እናንተ፡በመከራችሁበት፡ቦታ፡እንድ
ትጠፉ፡እወቁ፤
ትባኡ፡ወትኅድሩ፡ህየ፤
ገብታችሁ፡በዚያ፡ትኖሩ፡ዘንድ።

## ምዕራፍ፡፵፫፤

### ጉባዔ፤

፩፤ወኮነ፡ሶበ፡አሕለቀ፡ኤርምያስ፡እንዘ፡ይነ
ግር፡ለኵሉ፡ሕዝብ፡ኵሎ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤
ኤርምያስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ሁሉ፡ለሕዝቡ፡ነግሮ፡ከጨረሰ፡በኋላ፡
እንዲህ፡ሆነ፤
በከመ ፡ ፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኮሙ ፡
ኀቤሆሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ቃላተ፤
ፈጣሪያቸው፡እግዚአብሔር፡ይህንን፡
ነገር ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ እንደላከው ፡
ተናግሮ፡ከጨረሰ፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤
፪፤ይቤ፡አዛርያ፡ወልደ፡ኢዮስያስ፤
የኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ አዛርያ ፡ እንዲህ ፡
አለ፤
ወዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤
ወኵሎሙ ፡ ዕደው ፡ ዕቡያን ፡ እለ ፡ ይቤልዎ ፡
ለኤርምያስ፤
ትዕቢተኞች ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ኤርም
ያስን፡እንዲህ፡አሉት፤
ሕስወ፡ተናገርከ፡አንተ፤
አንተ፡ሐሰት፡ነገር፡ተናገርህ፡አሉት፤
ኢፈነወከ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡ኀቤነ፤
ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ፡
እኛ፡አልላከህም፤
እንዘ፡ይብል፤
እንዲህ፡ብሎ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኢትባኡ፡ውስተ፡ግብፅ፡ከመ፡ትኅድሩ፡ህየ፡
በዚያ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡
አትግቡ፡ብሎ፡አልላከህም፤

፫፤ አላ ፡ ባሮክ ፡ ወልደ ፡ ኔርዩ ፡ አስሐተከ፡
በኀቤነ፤
የኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ በኛ ፡ ዘንድ፡
አሳተህ፡እንጂ፡አልላከህም፡አሉት፤
ከመ፡ይመጥወነ፡ውስተ፡እደ፡ከለዳውያን፤
በከለዳውያን፡እጅ፡ይጥለን፡ዘንድ፤
ከመ፡ይቅትሉነ፤
ሊገድሉን፤
ወከመ፡ያፍልሱነ፡ውስተ፡ባቢሎን፤
ወደ፡ባቢሎን፡ማርከው፡ሊወስዱን፤

፬፤ወኢሰምዑ፡ዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤
ወኵሎሙ፡መላእክተ፡ኃይሎሙ፤
በሠራዊቱ፡ላይ፡የተሾሙ፡አለቆችም፤
ወኵሎሙ፡ሕዝብ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤
ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል፡አልሰሙም፤
ከመ፡ይኅድሩ፡ውስተ፡ምድረ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አል
ሰሙም፤

፭፤ወነሥአ፡ዮሐናን፡ወልደ፡ቃርሔ፤
የቃርሔ፡ልጅ፡ዮሐናን፤
ወኵሎሙ፡መላእክተ፡ኃይሎሙ፤
የሠራዊቱ፡አለቆች፡ሁሉ፤
ወኵሎሙ፡ተራፍያነ፡ይሁዳ፤
ከይሁዳ፡የቀሩ፤
እለ ፡ ተጋብኡ ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኀበ ፡
ተዘርዉ፤
ከተበተኑበት፡ከአሕዛብ፡ሀገር፡የተሰ
በሰቡ፡ሰዎች፤
ከመ፡ይኅድሩ፡ውስተ፡ምድረ፡ይሁዳ፤
በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ የተሰ
በሰቡ፡ሰዎች፡ሁሉ፤

፮፤ዕደወ፡ወአንስተ፤
ወንዶችንና፡ሴቶችን፤
ወሕፃናተ፡ወአዋልደ፡ነገሥት፤
ሕፃናቱንና ፡ የነገሥታቱን ፡ ሴቶች ፡
ልጆች፤
ወኵሎ፡ነፍሳተ፡ዘአትረፈ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡
መበስላን፡ምስለ፡ጎዶልያን፡ወልደ፡አኪቃም፤
ከአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ከጎዶልያን ፡ ጋር፤
የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን፡ ያስቀ
ራቸው፡ሰዎችን፡ሁሉ፤
ወልደ፡ሳፋን፤
የሳፋን፡ልጅ፤
ወኤርምያስሃኒ፡ነቢየ፤
ነቢዩ፡ኤርምያስን፤
ወባሮክሃኒ፡ወልደ፡ኔርዩ፤
የኔርዩ፡ልጅ፡ባሮክን፡ይዘው፤

፯፤ወቦኡ፡ውስተ፡ግብፅ፤
ወደ፡ግብፅ፡ገቡ፤
እስመ፡ኢሰምዑ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔርን፡ቃሉ፡አልሰሙም፤
ወበጽሑ፡እስከ፡ጣፍናስ፤
እስከ፡ጣፍናስ፡ደረሱ፤

፰፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ፡
ኤርምያስ፡በጣፍናስ፤
በጣፍናስ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡መጣ፡ተነገረ፤
እንዘ፡ይብል፤
እንዲህ፡ሲል፤

፱፤ንሣእ፡ለከ፡አዕባነ፡ዓበይተ፡በእደዊከ፤
በእጅህ፡እንክብል፡እንክብል፡ደንጊያ
ዎችን፡አምጥተህ፤
ወድፍኖሙ፡ውስተ፡ኖኅተ፡ቤተ፡ፈርዖን፤
በፈርዖን፡ቤት፡ደጃፍ፡ቅበራቸው፤
ውስተ፡ጣፍናስ፤
በጣፍናስ፡ባለ፡በፈርዖን፡ቤት፡ደጃፍ፡
ቅበራቸው፤
በቅድመ፡አዕይንቲሆሙ፡ለዕደወ፡ይሁዳ፤
የይሁዳ፡ሰዎች፡እያዩ፡ቅበራቸው፤

፲፤ ወትብሎሙ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
[illegible]



የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው፤
ናሁ፡አነ፡እፌኑ፡ወአመጽእ፡ለናቡከደነፆር፡
ንጉሠ፡ባቢሎን፡ገብርየ፤
እነሆ፡እኔ፡ልኬ፡አገልጋዩ፡የሚሆን፡
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆርን ፡
አመጣዋለሁ፤
ወያነብር ፡ መንበሮ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ አዕባን፡
ዘኀባዕኩ፤
መጥቶ ፡ በቀበርኋቸው ፡ ደንጊያዎች ፡
ላይ፡ዙፋኑን፡ይዘረጋል፤
ወያነሥእ፡ላዕሌሆሙ፡ወላትዊሆሙ፤
ጋሻዎቹን፡በእነሱ፡ላይ፡ያነሣል፤

፲፩፤ ወይበውዕ ፡ ወይቀትላ ፡ ለምድረ፡
ግብፅ፤
ገብቶ፡ምድረ፡ግብፅን፡ያጠፋታል፤
ወዘሂ፡ለሞት፡ውስተ፡ሞት፤
ለሞት ፡ የታዘዘው ፡ ወደ ፡ ሞት ፡
ይሒድ፤
ወዘሂ፡ለተፄውዎ፡ለተፄውዎ፤
ለምርኮ፡የታዘዘው፡ወደ፡ምርኮ፤
ወዘሂ፡ለኲናት፡ለኲናት፤
ለጦር፡የታዘዘው፡ወደ፡ጦር፡ይሒድ፤

፲፪፤ ወያውዒ ፡ በእሳት ፡ ቤተ ፡ አማልክ
ቲሆሙ፡ለግብፅ፤
የግብፅን ፡ የጣዖታቸውን ፡ ቤት ፡
በእሳት፡ያቃጥላል፤
ወያውዕዮሙ፤
ያቃጥላቸዋል፤
ወያፈልሶሙ፤
ማርኮ፡ይወስዳቸዋል፤
ወይቀምላ፡ለምድረ፡ግብፅ፡ከመ፡ዘይቀምል፡
[illegible]
የበግ፡እረኛ፡ልብሱን፡ለምዱን፡እያገ
ላበጠ፡እንዲቀምል፡ከዱር፡ከገደል፡
አውጥቶ፡ይቀምላታል፤ማለት፡ይማር
ካታል ፤ አንድም ፡ ይከድና ፡ ቢል ፡
እረኛ፡ ምድርን ፡ በለምዱ ፡ እንዲያለ
ብሳት ፡ የናቡከደነፆር ፡ ሠራዊት ፡
ግብፅን ፡ ይሸፍናታል ፤ አንድም ፡
ይቀልማ፡ ቢል፡ እረኛ ፡ ለምዱን ፡
ቀለም፡እንዲያገባ፡በደም፡ያልላታል፤
አንድም ፡ ይቀልባ ፡ ቢል ፡ እረኛ ፡
ለምዱን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያገኑነ ፡ እንዲ
ቀልብ ፡ እየቀለበ ፡ ማርኮ ፡ ባቢሎን ፡
ያወርዳታል፤
ወይወጽእ፡እምህየ፡በሰላም፤
ከዚያ፡በተድላ፡በደስታ፡ይወጣል፤

፲፫፤ ወይቀጠቅጥ ፡ ዓምደ ፡ ሀገረ ፡ ፀሐይ፡
ዘውስተ፡ምድረ፡ግብፅ፤
የግብፅ ፡ ሀገር ፡ ንጉሥን ፡ ያጠፋል፤
ግብፅን ፡ ፀሐይ ፡ አላት፤ ዋዕየ ፡ ፀሐይ፡
ስለፀናባት፤አንድም፡በፀሐይ፡አምና፡
በፀሐይ ፡ አምልካ ፡ ስለኖረች ፡ ሀገረ ፡
ፀሐይ፡አላት፤
ወያውዒ ፡ በእሳት ፡ ቤተ ፡ አማልክቲሆሙ፡
ለግብፅ፤
የግብፅን ፡ የጣዖታቸውን ፡ ቤት ፡
በእሳት፡ያቃጥላል።

## ምዕራፍ ፡ ፵፬ ፤

፩፤ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ ፡ እምኀበ ፡
እግዚአብሔር፤
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ወደ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ፡ ቃል ፡
ይህ፡ነው፤
ወኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስተ፡ግብፅ፤

www.ethiopianorthodox.org

በግብፅ፡ወደሚኖሩ፡ወደ፡አይሁድም፡
ሁሉ፤

ወእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ጣፍናስ፡ወመግደሎ፡
በጣፍናስና፡በመግደሎ፡ወደሚኖሩ፤

ወውስተ፡ሜምፎስ፡
በሜምፎስ፡ወደሚኖሩ፤

ወውስተ፡ምድረ፡ፋቱራ፡
ፋቱራ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ በፋቱራ ፡
ወደ ፡ ሚኖሩ ፤ አንድም፡ ስመ ፡ ሰብእ፡
ነው፤ሚርተኛ፡ነው፤

ወይቤሎሙ፡
እንዲህ፡አላቸው፤

፪፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት ፡
አምላከ፡እስራኤል፡
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ለሊክሙ ፡ ርኢክሙ ፡ ኵሎ ፡ እኩየ ፡ ዘአም
ጻእኩ፡ላዕለ፡ኢየሩሳሌም፡
በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ያመጣሁትን፡
ክፉውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ አይታ
ችኋል፤

ወላዕለ፡አህጉረ፡ይሁዳ፡
በይሁዳም ፡ አውራጃ ፡ ላይ፡ ያመጣ
ሁትን፡ክፉ፡ነገር፡አይታችኋል፤

ዘኮነት፡በድወ፡እስከዛ፡ዕለት፡እምእከዮሙ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ የሆነች ፡ ከክፋታቸው፡
የተነሣ ፡ እስከዚች ፡ ቀን፡ ድረስ ፡
ምድረ፡በዳ፡የሆነች፤

፫፤ ወአልቦ ፡ ዘይነብር ፡ እምገጸ ፡ እከዮሙ ፡
ዘገብሩ፡
ከሠሩት ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ የተነሣ ፡
የሚኖር፡ሰው፡የለም፤

ከመ፡ያምዕዑኒ፡
የሰዝኑኝ፡ዘንድ፤

ወሖሩ፡ከመ፡ይዕጥኑ፡
ለጣዖት፡ያጥኑ፡ዘንድ፡ሔዱ፤

ወይትቀነዩ፡ለአማልክተ፡ነኪር፡
ለከነዓን፡ጣዖት፡ይገዙ፡ዘንድ፤

ዘኢየአምርዎሙ፡እሙንቱ፡
እነሱ፡ለማያውቋቸው፤

ወኢአበዊሆሙ፤
አባቶቻቸውም ፡ ለማያውቋቸው ፡
ጣዖታት፡ይገዙ፡ዘንድ፡ሔዱ፤

፬፤ ወፈነውኩ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኵሎ ፡ አግብ
ርትየ፡ነቢያተ፡በጽባሕ፡
አገልጋዮቼ ፡ ነቢያትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጥኜ፡
ወደ፡እነሱ፡ሰደድሁ፤

እንዘ ፡ ዕብል ፡ ኢትግበሩ ፡ ዘንተ ፡ ምግባረ፡
ርኩሰ፡ዘእጸልእ፡
እኔ፡የምጠላውን፡ይህን፡ክፉ፡ሥራ፡
አትሥሩ፡ስል፡ሰደድሁ፤

፭፤ወኢሰምዑኒ፡
ነገር፡ግን፡አልሰሙኝም፤

ወኢሜጡ፡ዕዝኖሙ፡
ልቡናቸውን፡አልመለሱም፤

ከመ፡ይትመየጡ፡እምእከዮሙ፡
ከክፋታቸው፡ይመለሱ፡ዘንድ፤

ከመ፡ኢይዕጥኑ፡ለአማልክተ፡ነኪር፡
ለከነዓን፡ጣዖት፡እንዳያጥኑ፤

፮፤ወወረደ፡መዓትየ፡ወመቅሠፍትየ፤
መዓቴ ፡ መቅሠፍቴ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
መጣ፤

ወነደ፡በአህጉረ፡ይሁዳ፡ወበአፍአሃ፡ለኢየሩ
ሳሌም፡
በይሁዳ ፡ አውራጃና ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አውራጃ ፡ ነደደ ፤ ነደደም፡ ይላል ፡
ተደረ



ወኮነ፡በድወ፡
ምድረ፡በዳ፡ሆነ፤

ወዓፀ፡እስከ፡ዛ፡ዕለት፡
እስከዚች፡ቀን፡ድረስ፡በረሃ፡ሆነ፤

፯፤ ወይእዜኒ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ፀባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፡
አሁንም ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ለምንት ፡ ትገብሩ ፡ አንትሙ ፡ እኩየ ፡ ዓቢየ ፡
ለነፍስክሙ፡
እናንተ ፡ በሰውነታችሁ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ለምን፡ትሠራላችሁ፤

ከመ፡ትምትሩ፡ብእሴ፡ወብእሲተ፡
ሴትንና፡ወንድን፡ታጠፉ፡ዘንድ፤

ደቂቀ፡ወሕፃናተ፡
ትልልቆችንና፡ሕፃናቱን፤

ወጠባዊተ፡እማዕከለ፡አህጉረ፡ይሁዳ፡
ከይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ መካከል ፡ ጡት፡
የምትጠባውን፡ታጠፉ፡ዘንድ፡በሰው
ነታችሁ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለምን ፡ ትሠራ
ላችሁ፤

ከመ፡ኢታትርፉ፡ወኢአሐደ፡
አንድ፡ሰውስ፡እንኳ፡እንዳታስቀሩ፤

፰፤ ከመ ፡ ያምርሩኒ ፡ በምግባረ ፡
እደዊሆሙ፡
በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ጣዖት ፡ ያሳዝኑኝ፡
ዘንድ፤

ትዕጥኑ ፡ ለአማልክተ ፡ ባዕድ ፡ በምድረ፡
ግብፅ፤
በግብፅ ፡ ምድር ፡ ለከነዓን ፡ ጣዖት ፡
ታጥኑ፡ዘንድ፤

ወቦእክሙ፡አንትሙ፡ትኅድሩ፡ህየ፡
እናንተ ፡ በዚያ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡

ከመ፡ትትመተሩ፡
ትጠፉ፡ዘንድ፤

ወትኩኑ፡ለመርገም፡
ለጥፋት፡ትሆኑ፡ዘንድ፤

ወለፅዕለት፡ውስተ፡ኵሉ፡አሕዛበ፡ምድር፡
በምድር ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡
ለስድብ፡ትሆኑ፡ዘንድ፤

፱፤ ቦኑ ፡ ተረሥአክሙ ፡ እከዮሙ ፡ ለአበ
ዊክሙ፡
በውኑ፡የአባቶቻችሁ፡ክፋት፡ተዘነጋ
ችሁን፤

ወእከየ ፡ ነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡ ወእከየ ፡ መላእክ
ቲሆሙ፤
የይሁዳ፡የነገሥታቱ፡ክፋትና፡የአለቆ
ቻቸው፡ክፋት፡ተዘነጋችሁን፤

ወእከዮን ፡ ለአንስቲያክሙ ፡ ዘገብራ ፡
በምድረ፡ይሁዳ፡ወበአፍአሃ፡ለኢየሩሳሌም፡
በይሁዳ ፡ አውራጃና ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አውራጃ ፡ የሠሩት ፡ የሚስቶቻችሁ ፡
ክፋት፡ተዘነጋችሁን፤

፲፤ወኢያዕረፉ፡እስከ፡ዛቲ፡ዕለት፡
እስከዚች፡ቀን፡ድረስ፡አላረፉም፤

ወኢፈርሁ፡
አልፈሩም፤

ወኢዓቀቡ፡ሕግየ፡
ሕጌን፡አልጠበቁም፤

ወኢሖሩ ፡ በኵነኔየ ፡ ዘወሀብኩ ፡ ቅድመ፡
አበዊክሙ፤
በአባቶቻችሁ ፡ ፊት ፡ በሰጠኋቸው ፡
በሕጌ፡ጸንተው፡አልኖሩም፤

ወቅድሚክሙ፡
በፊታችሁም ፡ በሰጣኋቸው ፡ በሕጌ ፡
ጸንተው፡አልኖሩም፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ ወእንበይነዝ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፤
ስለዚህ፡ነገር፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግ
ዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ናሁ ፡ አነ ፡ አቀውም ፡ ገጽየ ፡ ላዕሌክሙ፡
በእኩይ፤
እነሆ፡እኔ፡በክፉ፡ነገር፡ገጸ፡መዓቴን፡
በእናንተ፡ላይ፡አጸናለሁ፤
ከመ፡እሥርዎሙ፡ለኵሎሙ፡ይሁዳ፡
የይሁዳን፡ሰዎች፡ሁሉ፡አጠፋቸው፡
ዘንድ፤

፲፪፤ ወእነሥአሙ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ፡
እምይሁዳ፤
ከይሁዳ፡ከሞት፡የቀሩትን፡አመጣቸ
ዋለሁ፤
እለ፡ወደዩ፡ገጸሙ፡ከመ፡ይባኡ፡ብሔረ፡
ግብፅ፡
ወደ፡ግብፅ፡ይገቡ፡ዘንድ፡ፊታቸውን፡
የመለሱትን፤
ይኅድሩ፡ህየ፤
በዚያ፡ይኖሩ፡ዘንድ፡የተመለሱትን፡
አመጣቸዋለሁ፤
ከመ፡አኅጕሎሙ፡ለኵሎሙ፡እለ፡ተርፉ፡
እምይሁዳ፡በምድረ፡ግብፅ፡
ከይሁዳ ፡ ከሞት ፡ የቀሩትን ፡ ሁሉ፡
በግብፅ፡አውራጃ፡አጠፋቸው፡ዘንድ፡
አመጣቸዋለሁ፤
ወይወድቁ፡በኲናት፤
በጦር፤
ወበረሀብ፤
በቀጠና፡ይጠፋሉ፤
ወየኅልቁ፡ንዑሶሙ፡ወዓቢዮሙ፤
ታላቁም፡ታናሹም፡ያልቃሉ፤
ወይወድቁ፡በኲናት፤
በጦር፡ይጠፋሉ፤
ወበረሀብ፡ይመውቱ፤
በቀጠና፡ይሞታሉ፤
ወይከውኑ፡ለመሐላ፤
ለመሐላ፡ይሆናሉ፡ማለት፡ይማማሉባ
ቸዋል፤እስራኤልን፡ያስማረከ፡ያስማ
ርከህ፤እስራኤልን፡ያጠፋ፡ያጥፋህ፡
እያሉ፤
ወለሐጕል፤
ለጥፋት፤
ወለመርገም፤
ለመርገም፤
ወለፅዕለት፤
ለስድብ፡ይሆናሉ፤

፲፫፤ ወእዋህዮሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡
ግብፅ፡
በግብፅ፡የሚኖሩትን፡በመዓት፡እጐበ
ኛቸዋለሁ፤
በከመ፡ወሀይክዎሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡
ኢየሩሳሌም፡በኲናት፤
በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ በጦር፡
እንደጐበኘኋቸው፡በመዓት፡እጐበኛ
ቸዋለሁ፤
ወበረሀብ፤
በቀጠና፤
ወበሞት፤
በሞት፡እንደ፡ጐበኘኋቸው፡በመዓት፡
እጐበኛቸዋለሁ፤

፲፬፤ ወአልቦ፡ዘይድኅን፤
የሚድን፡የለም፤
ወይተርፍ፡እምውስቴቶሙ፤
ከውስጣቸው፡የሚቀር፡የለም፤



እለ፡ተርፉ፡እምይሁዳ፤
ከይሁዳ፡ከሞት፡ከቀሩ፤
እለ፡መጽኡ፡ይኅድሩ፡ውስተ፡ግብፅ፡
በግብፅ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ከመጡ ፡
የሚቀር፡የለም፤
ከመ፡ይትመየጡ፡ውስተ፡ምድረ፡ይሁዳ፡
ወደ፡ይሁዳ፡ዕፃ፡ይመለሱ፡ዘንድ፤
እሙንቱ፡ይትዌከሉ፡በነፍሶሙ፤
እነርሱ፡በሰውነታቸው፡ይታመናሉ፤
ከመ፡ይግብኡ፡ህየ፤
ወደ ፡ እዚያ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡
ይታመናሉ፤
ኢይገብኡ፡ዘእንበለ፡እለ፡ጐዩ፤
ከሸሹ፡ሰዎች፡በቀር፡አይመለሱም፤
አንድም፡ከክፉ፡ሰዎች፡ግብር፡ከሸሹ፡
በቀር፡አይመለሱም፤

፲፭፤ ወተሰጥውዎ፡ለኤርምያስ፡ኵሎሙ፡
ዕደው፤
ሰዎች፡ሁሉ፡ለኤርምያስ፡መለሱለት፤
እለ፡የአምሩ፡ከመ፡የዐጥና፡አንስቲያሆሙ፡
ለአማልክተ፡ነኪር፤
ሚስቶቻቸው፡ለከነዓን፡ጣዖት፡እንዲ
ያጥኑ፡የሚያውቁ፤
ወኵሎን፡አንስት፡እለ፡ይቀውማ፡ማኅበረ፡
ዓቢየ፤
በእስራኤል ፡ መሐከል ፡ የሚቆሙ፤
አንድም ፡ አንድነት ፡ የሚቆሙ ፡
ሴቶች፡ሁሉ፤
ወኵሎሙ ፡ ሕ.፡ብ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ፡
ምድ.፡ ‹ብፅ፤
ı‹ግብፅ፡የሚኖሩ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፤
ወውስተ፡ምድረ፡ፋቱራ፤
ፋቱራ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ነው ፤ በፋቱራ ፤
አንድም ፡ ማርተኛ ፡ ነው ፤ ማርተኛ፡
በሚኖርበት፡ሀገር፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡
መለሱለት፤
እንዘ፡ይብሉ፤
እንዲህ፡ብለው፤

፲፮፤ ነገረ ፡ ዘነገርከነ ፡ በስመ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡
የነገርኸንን ፡ አንሰማም ሲሉ ፡ መለ
ሱለት፤

፲፯፤እስመ፡ገቢረ፡ንገብር፡ኵሎ፡ዘወጽአ፡
እምአፉነ፤
ከአንደበታችን፡የወጣውን፡ሁሉ፡እና
ደርጋለንና፤
ወነአጥን፡ለንግሥተ፡ሰማይ፤
ለሰማይ ፡ እመቤት ፤ ለፀሐይ ፤
ለጨረቃ፡እናጥናለን፤
ወሞጻሕተ፡ናወጽሕ፡ላቲ፤
ወይኑንም፡ፍልቅ፡አድርገን፡እናፈስላ
ታለን፤
በከመ፡ገበርነ፡ንሕነ፤
እኛ፡እንዳደረግን፤
ወአበዊነ፤
አባቶቻችንም፡አንዳረጉ፤
ወነገሥትነ፤
ነገሥታቱ፤
ወመላእክቲነ፡በሀገረ፡ይሁዳ፤
አለቆቻችንም፡በይሁዳ፡ሀገር፡እንዳ
ደረጉ፤
ወበአፍአሃ፡ለኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ በአውራጃዋ ፡ እንዳ
ደረጉ፡እናደርጋለንና፤
ወጸገብነ፡እክለ፡ወኮነ፡በሠናይ፤
ለፀሐይ ፡ መሥዋዕቱን ፡ ሠውተን ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ስምዑ፡ቃለ፡እግዚአ
ብሔር፡ኵልክሙ፡አይሁድ፡እለ፡ትነብሩ፡
ውስተ፡ግብፅ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በግብፅ ፡ የምትኖሩ ፡
አይሁድ፡ሁላችሁ፡የእግዚአብሔርን፡
ቃል፡ስሙ፤

ናሁ፡መሐልኩ፡በስምየ፡ዐቢይ፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡
እነሆ፡ሕያው፡አነ፡አማንየ፡በርእስየ፡
ብዬ፤ማልኩ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እመ ፡ ይከውን ፡ እንከ ፡ ስምየ ፡ ለጸውዖ ፡
ውስተ፡አፈ፡ኵሉ፡ይሁዳ፡ዘይቤሉ፡ሕያው፡
እግዚአብሔር፡ዘእምኵሉ፡ምድረ፡ግብፅ፡
ስምየ፡ለተጸውአ፡ሲል፡ነው፤ከግብፅ፡
ያወጣን፡እግዚአብሔር፡ሕያው፡ነው፡
ይሉ ፡ በነበሩ ፡ በይሁዳ ፡ ሰዎች ፡
አንደበት፡ስሜ፡ለመጠራት፡ቢሆን፤
አንድም ፡ ለጸውአ ፡ ስምየ ፡ ውስተ ፡
አፈ፡ ኵሉ፡ ይሁዳ ፡ ይላል ፤ ከግብፅ ፡
ያወጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡
ነው፡ ይሉ፡ የነበሩ ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች፡
ሁሉ፡በቃላቸው፡ስሜን፡ለመጥራት፡
ቢሆኑ፡ሕያው፡ነኝ፡አለ፤

፳፯፤ እስመ ፡ አነ ፡ እተግህ ፡ በእንቲ
አሆሙ፡
በእነርሱ፡መከራ፡ለማምጣት፡እተጋ
ለሁና፡ምንም፡ብተጋ፡ሕያው፡ነኝ፡

ከመ፡እሣቅዮሙ፡
መከራ፡አጸናባቸው፡ዘንድ፡

ወኢያሤኒ፡ላዕሌሆሙ፤
ለእነርሱ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አላደርግላቸ
ውምና፤

ወየሐልቁ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ በምድረ ፡
ግብፅ፤
በግብፅ ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡
ያልቃሉ፤

በኵናት፡
በጦር፡

ወበረሀብ፡እስከ፡የሐልቁ፡
በቀጠና፡እስኪጠፉ፡ድረስ፡ያልቃሉ፤

፳፰፤ ወዘድኅኑ፡እምኲናት፡ይትመየጡ፡
እምግብፅ ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ፡ ሕዳጣን ፡
በኍልቍ፡
ከመ፡ይትመየጡ፡ሲል፡ነው፡ከጦር፡
የዳኑ ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ በቁጥር ፡
ከግብፅ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ይመለሱ፡
ዘንድ፡ ሕያው፡ ነኝ ፡ አለ ፤ አንድም፡
እመ፡ይከውን፡ብለህ፡መልስ፡ከመ፡
ይከውን፡ ሲል ፡ ነው ፤ ስምየ ፡
ለተጸውዖ፡ከግብፅ፡ያወጣን፡እግዚአ
ብሔር፡ሕያው፡ነው፡ይሉ፡በነበሩ፡
በይሁዳ፡ ሰዎች ፡ አንደበት ፡ ስሜ ፡
ለመጠራት ፡ እንዲሆን ፤ አንድም ፡
ለጸውዖ፡ስምየ፡ውስተ፡አፉሁ፡ኵሉ፡
ይሁዳ፡ሲል፡ነው፤ከግብፅ፡ያወጣን፡
እግዚአብሔር፡ሕያው፡ነው፡ይሉ፡
የነበሩ ፡ የይሁዳ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በቃላቸው ፡ ስሜን ፡ ለመጥራት ፡
እንዲሆኑ፡ሕያው፡ ነኝ፡ አለ፤ እስመ፡
አነ፡ በእነርሱ፡ መከራ ፡ ለማምጣት ፡
እተጋለሁና ፡ ምንም ፡ ብተጋ፤ ከመ ፡
እሣቅዮሙ ፤ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡
ዘንድ፤ ወኢያሤኒ፡ ለእነርሱ ፡ በጎ ፡
ነገር፡አላደርግላቸውምና፡ምንም፡ባላ
ደርግላቸው፡ሕያው፡ነኝ፤ወየሐልቁ፤
በግብፅ ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡
ያልቃሉና፤



በኵናት፡ወበረሀብ፡
በጦር ፡ በቀጠና ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡
ያልቃሉና፤ወዘድኅኑ፡
አሁን ፡ ዋዌ፡ ነው ፡ ከጦር ፡ የዳኑት ፡
ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ በቁጥር ፡ ከግብፅ፡
ወደ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመለሳሉ፤
አንድም ፡ እመ ፡ ይከውን ፡ እመ ፡
ኢይከውን፡ ስምየ ፡ ለተጸውአ ፡ ሲል ፡
ነው፤
ከግብፅ ፡ ያወጣን ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ በነበሩ ፡ በይሁዳ፡
ሰዎች ፡ አንደበት ፡ ስሜ ፡ ለመጠራት ፡
ባይሆን ፤ አንድም ፡ ለጸውአ ፡ ስምየ ፡
ሲል ፡ ነው ፤ ከግብፅ፡ ያወጣን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ የነበሩ ፡
የይሁዳ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በቃላቸው ፡
ስሜን ፡ ለመጥራት ፡ ባይሆን ፡ ሕያው ፡
ነኝ ፡ አለ፤ እስመ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ እተግህ ፡
ሲል፡ነው፤
በእነሱ ፡ መከራ ፡ ለማምጣት ፡
እንድተጋ፡ ከመ ፡ እሣቅዮሙ፤ መከራ፡
አፀናባቸው ፡ ዘንድ ፤ ወኢያሤኒ ፤
ለእነሱ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አላደርግላቸ
ውምና፤ ወየሐልቁ ፤ በጦር ፡ በቀጠና ፡
ያልቃሉና ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፤
ወዘድኅኑ፡ እንዳለፈው ፡ አይለወጥም፤
አንድም ፡ እመ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡
ኢይከውን፡ ስምየ፡ ለተጸውዖ ፡ ሲል
ነው፤
ከግብፅ ፡ ያወጣን ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ በነበሩ ፡ በይሁዳ፡
ሰዎች ፡ አንደበት ፡ ስሜ ፡ ለመጠራት ፡
እንዳይሆን፤አንድም፡ለፀውዖ፡ስምየ፡
ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ኵሉ ፡ ይሁዳ ፡ ሲል ፡
ነው ፤ ከግብፅ ፡ ያወጣን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ የነበሩ ፡
የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በቃላቸው ፡
ስሜን ፡ ለመጥራት ፡ እንዳይሆኑ ፡
ሕያው ፡ ነኝ ፡ አለ፤ እስመ ፡ አነ ፤ እኔ ፡
በእነሱ ፡ መከራ ፡ ለማምጣት ፡ እተጋ
ለሁና ፡ ምንም ፡ ብተጋ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡
ከመ ፡ እሣቅዮሙ ፤ መከራ ፡ አጸና
ባቸው፡ ዘንድ ፤ ወኢያሤኒ ፤ ለእነሱ ፡
በጎ፡ ነገር ፡ አላደርግላቸውምና ፤ ወየ
ሐልቁ ፤ በጦር ፡ በቀጠና ፡ እስኪጠፉ ፡
ድረስ ፡ ያልቃሉና ፤ ወዘድኅኑ ፤ ከጦር ፡
የዳኑት ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ በቁጥር ፡
ከግብፅ፡ወደኢየሩሳሌም፡ይመለሳሉ፤

ያእምሩ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ አይሁድ ፡ በምድረ ፡
ግብፅ፡ከመ፡ይንበሩ፡ህየ፡
በግብፅ ፡ ከሞት ፡ የቀሩ ፡ አይሁድ ፡
በዚያ፡ሊኖሩ፡ያውቁ፡ዘንድ፤

ነገረ፡መኑ፡ይቀውም፡
የማን፡ነገር፡ይፀናል፤

ዘዚአየኑ፡
የእኔ፡ነገር፡ነውን፤

ወሚመ፡ዘዚአሆሙ፡
ወይስ፡የእነሱ፡ነገር፡ይፀናልን፤

፳፱፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ትእምርትክሙ ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ምልክታችሁ፡ይህ፡ነው፡አለ፡እግዚአ
ብሔር፤

ከመ፡እሔውጸክሙ፡በዝንቱ፡መካን፡ከመ፡
ታእምሩ ፡ ከመ ፡ ቀዊመ ፡ ይቀውም ፡
ላዕሌክሙ፡ቃልየ፡ለእኩይ፤
በእናንተ ፡ ላይ ፡ የተናገርሁት ፡ ቃሌ ፡
ለክፉ፡ነገር፡እንዲጸና፡ታውቁ፡ዘንድ፡
በዚህ ፡ ቦታ ፡ በመዓት ፡ እንድጐበ
ኛችሁ፡ምልክቱ፡ይህ፡ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ናሁ ፡ አነ ፡ እሜጥዎ ፡ ለፈርዖን ፡ አውፍር ፡ ንጉሠ፡ግብፅ፡ውስተ፡እደ፡ጸላእቱ፡
እነሆ ፡ እኔ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ የሚሆን፡ አውፍር ፡ የሚባል ፡ ፈርዖንን ፡ በጠላቶቹ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠ ዋለሁ፤
ወውስተ፡እደ፡እለ፡የሐሥሥዋ፡ለነፍሱ፡
ሰውነቱን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈልጓት ፡ ሰዎች፡እጅ፡አሳልፌ፡እሰጠዋለሁ፤
ከመ ፡ መጠውክዎ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፡
የይሁዳውን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ እጅ፡አሳልፌ፡እንደሰጠሁት፤
ወውስተ፡እደ፡ጸላእቱ፡
በጠላቶቹ፡እጅ፤
ወውስተ፡እደ፡እለ፡የኀሥሥዋ፡ለነፍሱ፡
ሰውነቱን ፡ ለጥፋት ፡ በሚፈልጓት ፡ ሰዎች ፡ እጅም ፡ አሳልፌ ፡ እንደሰ ጠሁት፡በጠላቶቹ፡እጅ፡እጥለዋለሁ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፭ ፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ነገር ፡ ዘነገሮ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ፡ ለባሮክ፡ ወልደ ፡ ኔርዩ ፡ አመ ፡ ጸሐፈ ፡ ዘንተ፡ ቃላተ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ እምአፈ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ በራብዕት፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ፡ለኢዮአቄም፡ወልደ፡ኢዮስያስ፡ ንጉሠ፡ይሁዳ፡
ነገር ፡ ዘነገሮ ፡ ኤርምያስ ፡ ለባሮክ ፡ በራብዕ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለኢዮ አቄም ፡ ወልደ ፡ ኢዮስያስ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ፡ ብሎ ፡ መግጠም፡ ነው ፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮስያስ፡ ልጅ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዘመን ፡ ኤርምያስ ፡ ለኔርዩ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክ ፡ የነገረው፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው፤
አንድም ፡ አፈ ፡ አመ ፡ ጸሐፈ ፡ ዘንተ፡ ቃላተ፡ በራብዕ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ፡ ለኢዮአቄም፡
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮስያስ ፡ ልጅ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዘመን ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ እየሰማ፡ በጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ኤርምያስ ፡ ለኔርዩ ፡ ልጅ፡ ለባሮክ፡የነገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

፪፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ፡ እስራኤል፡
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡አለ፤
ላዕለ፡ባሮክ፡
በባሮክ፡ላይ፡በመዓት፡አለሁ፡አለ፤

፫፤ትብል፡አሌ፡ሊተ፡
ወዮልኝ፡ትላለህ፤
እስመ፡ወሰከ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡በመከራ፡ላይ፡መከራ፡ ጨምሮብኛልና፤
ወወኀበ፡ስራሐ፡ላዕለ፡ሕማምየ፡
በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አምጥቶብ ኛልና ፤ አንድም ፡ ለማውጣት ፡ ወዮልኝ፡ ትላለህ ፡ በመከራ ፡ ላይ መከራ፡በኃዘን፡ላይ፡ኃዘን፡ጨምሮብ ኛልና፡ወዮልኝ፤
ወሰራሕኩ፡በገዓርየ፡
በጩኸት፡ደከምኩ፤
ወኢረከብኩ፡ዕረፍተ፡ትብል፡
ትብል [illegible]



ዕረፍትን፡አላገኘሁም፡ትላለህ፤

፬፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ናሁ፡ዘሐነፅኩ፡ለልየ፡እነስት፡
እነሆ ፡ እኔ ፡ የሠራሁትን ፡ እኔ ፡ አፈርሰ ዋለሁ፤ በፊት ፡ የጻፈውን ፡ ኤልያቄም፡ አቃጠለበት ፡ ዳግመኛ ፡ ጻፍ ፡ አለው ፤ ባሮክ ፡ አንጐራጐረ ፡ አላስማርክህም ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ አስማርክሃለሁ ፤ አላሳዝ ንህም ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ አሳዝንሃለሁ፤ መከራ ፡ አላመጣብህም፡ ብዬ ፡ ነበር፤ መከራ ፡ አመጣብሃለሁ ፡ አለው፤ ኋላ ፡ ንስሐ፡ገብቶ፡ቀርቶለታል፤
ወዘለልየ፡ተከልኩ፡ለልየ፡እመልኀ፡
እኔ፡የተከልሁትን፡እኔ፡እነቅለዋለሁ፤
ወለኵላ፡ምድር፤
ሀገሪቱን፡ሁሉ፡አጠፋታለሁ፤

፭፤ወአንተ፡ተኀሥሥ፡ዓቢያተ፡
አንተ ፡ ታላላቅ ፡ ነገርን ፡ ትፈልጋለህ፡ አንድም ፡ አብያተ ፡ ቤት ፡ ቤት፡ ንብረት፡ትሠራ፡ዘንድ፡ትፈልጋለህ፤
ኢትኅሥሥ፡
ነገር፡ግን፡አትፈልግ፤
እስመ ፡ አነ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ፡ ዘሥጋ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ አመጣለሁ፡ብሏልና፤
ወእሁብ ፡ ነፍሰከ ፡ ከመ ፡ ትዔወው ፡ በኵሉ ፡ በሐውርት፡ኀበ፡ሖርከ፡ህየ፡
በሔድክበት ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ፡ ትማረክ ፡ ዘንድ ፡ ሰውነትህን ፡ ለምርኮ ፡ እሰጣ ታለሁ፡ብሏልና፤

## ምዕራፍ ፡ ፵፮ ፤

፩፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡ ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡ ነው፤
ላዕለ፡አሕዛበ፡ግብፅ፡
በግብፅ፡አሕዛቦችና፤

፪፤ ወዲበ ፡ ኃይለ ፡ ፈርዖን ፡ ኒካዑ ፡ ንጉሠ፡ ግብፅ፤
በግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖን ፡ ሠራዊት፡ ላይ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአ ብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤
ዘሀሎ፡ኀበ፡ፈለገ፡ኤፍራጥስ፤
በኤፍራጥስ፡ወንዝ፡አጠገብ፡ያለ፤
ውስተ፡ኬርኬማስ፤
በኬርኬማስ ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ በኤፍ ራጥስ፤
ዘቀተላ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ በራብዕ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለኢዮአቄም፡ ወልደ፡ኢዮስያስ፡ንጉሠ፡ይሁዳ፤
የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዘመን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደ ነፆር ፡ በወጋት ፡ በኬርኬማስ ፡ ውስጥ፡ ባለ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ያለ ፡ በግብፅ ፡ ንጉሥ፡ በፈርዖን ፡ ሠራዊት፡ ላይ ፡ የመጣ ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል፡ይህ፡ነው፤

፫፤ንሥኡ፡ንዋየ፡ሐቅል፤
የበዳ፡ፀብታችሁን፡ያዙ፤
ወልበሱ፡ሐፂነ፤
ጥሩር፡ልበሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወጻኡ፡ተቃተሉ፣
ወጥታችሁ፡ተዋጉ፤

፱፤ወረሐኑ፡አፍራስ፣
ፈረሶችን፡ጫኑ፤

ወይፀዓኑ፡መስተፅዕናን፣
በፈረስ፡የሚቀመጡ፡ሰዎች፡በፈረስ፡ይቀመጡ፤

ወይደዩ፡ጌራ፡ውስተ፡ርእሶሙ፣
በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ቦርቦርቴ (የብረት ፡ ቆብ)፡ይድፉ፤

ንሥኡ፡ኲያንዊክሙ፣
ጦራችሁን፡ያዙ፤

ወልበሱ፡ልብሰ፡ሐፂን፣
ጥሩር፡ልበሱ፤

፭፤ለምንት፡ርኢኩ፡እንዘ፡ይጐይዩ፡ወይደነግፁ፡ወይሜምዑ፣
እንዋጋምና ፡ እንዲህ ፡ ትለናለህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ አርበኞች ፡ ደንግጠው፡ሲሸሹ፡ሲሸበሩ፡ለምን፡አያለሁ፤

ወይገብኡ፡ድኅሬሆሙ፣
ወደ፡ኋላቸው፡ሸሽተው፡ሲመለሱ፡ለምን፡አያለሁ፤

ወጽኑአኒሆሙ፡ይነትዑ፡ወይጐይዩ፡ወኢይትቃተሉ፣
አርበኞቻቸው ፡ ሳይዋጉ ፡ ሲሸሹ ፡ ለምን፡አያለሁ፤

ወይሠወጡ፣
ሸሽተው፡ሲመለሱ፤

ወየዓግትዎሙ ፡ ዓውዶሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፣
ከወደ፡ኋላቸው፡ይከብቧቸዋል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፮፤ኢይጐይይ፡ረዋጺ፣
ሩዋጭ፡አይሸሽም፤

ወኢያመስጥ፡ጽኑዕ፡ለመንገለ፡ደቡብ፡ላዕለ፡ፈለገ፡ኤፍራጥስ፣
አርበኛውም ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ፡ወደ፡ግራ፡ወደ፡ግራ፡ቢሮጥ፡ሩጦ፡አያመልጥም፤

ደከሙ፡ሂ፣
በመከራው፡ደከሙ፤

ወወድቁ፣
ድል፡ተነሡ፤

፯፤መኑ፡ዝንቱ፡ዘይመጽእ፡ከመ፡ውኂዝ፣
እንደ፡ፈሳሽ፡ውሀ፡በዝቶ፡የሚመጣ፡ይህ፡ማነው፤

ወማዕበሉ፡ከመ፡ውኂዘ፡ማይ፡ግብፀ፣
ማዕበሉም፡እንደ፡ፈሳሽ፡ውሀ፡በዝቶ፡የሚመጣ ፡ ማነው ፡ ማለት ፡ ጦሩ ፡ በዝቶ፡ ከግብፅ ፡ የሚመጣ ፡ ይህ ፡ ማነው፤

፰፤ወከመ፡ፈለግ፡የዓርግ፣
እንደ፡ፈሳሽ፡በዝቶ፡የሚወጣ፤

ወከመ፡ማዕበል፡ዘይትሀወክ፡እምባሕር፣
ከባሕሩ ፡ ተርፎ ፡ ማዕበሉ ፡ እንዲተዋወክ፡የሚተዋወክ፡ይህ፡ማነው?

ወይቤ፡አዓርግ፡ወእደፍና፡ለምድር፣
ወጥቼ ፡ በብዛት ፡ ምድርን ፡ እሸፍናታለሁ፡አለ፤

ወአጠፍዕ፡ሀገረ፣
ሀገሩን፡አጠፋለሁ፤

ወእለ፡ይነበሩ፡ውስቴታ፣
በውስጧ ፡ የሚኖሩትንም ፡ ሰዎች ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፱፤ተፀዐኑ፡አፍራሰ፣
በፈረስ፡ተቀመጡ፤



ወአስተረስዩ፡ሠረገላተ፣
ሠረገላውን፡አፀርሩ፤

ወይጻኡ ፡ መስተቃትላን ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ወፉጥ፡ወልዳ፣
የልዳና ፡ የፉጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች፡ወጥተው፡ይዋጉ፤

በንዋየ ፡ ሐቅሎሙ ፡ ተወላቲዎሙ ፡ ወይንድፉ፣
በበዳ ፡ ፀብታቸው ፡ ተመካክተው ፡ ይዋጉ፡ይጥፉ፤

፲፤ ወይእቲ ፡ ዕለት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ፡ዕለተ፡በቀል፣
ይህቺም ፡ ቀን ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር፡የሚበቀልባት፡ቀን፡ናትና፤

በዘይትቤቀሎሙ፡ለፀሩ፣
ጠላቶቹን፡ተበቅሎ፡በሚያጠፋቸው፡ገንዘብ፤

ወትበልዕ፡መጥባሕተ፡እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር ፡ ሥልጣኑ ፡ ታጠፋለች፤

ወትጸግብሂ፡ወትሰክር፡እምደሞሙ፣
ከደማቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ትሰክራለች፤

እስመ፡መሥዋዕቱ፡ለእግዚአብሔር፡ፀባዖት፡አምላከ፡እስራኤል፣
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡የአቸናፊ፡የእግዚአብሔር፡መዓቱ፡ይመጣልና፤

በምድረ፡ደቡብ፡ወፈለገ፡ኤፍራጥስ፣
በደቡብ፡ባለ፡ወንዝ፡ማለት፡በግብፅና፡በኤፍራጥስ፡ወንዝ፡ይደረጋልና፣

፲፩፤ዕርጊ፡እስከ፡ገለዓድ፣
እስከ፡ገለዓድ፡ድረስ፡ወጥተሽ፤

ወንሥኢ፡ርጢነ፡ድንግል፡ወለተ፡ግብፅ፤

ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ የምትሆኚ ፡ የግብፅ፡ልጅ፡መድኃኒቱን፡አምጪ፤

በከንቱ፡አብዛኅኪ፡ፈውሰ፡ዘለምንትሂ፡ኢይበቍዓኪ፣
ለምንም፡ለምን፡የማይረባሽ፡የማይጠቅምሽ፡በከንቱ፡ድኅነትን፡አበዛሽ፤

፲፪፤ሰምዑ፡አሕዛብ፡ቃለኪ፣
አሕዛብ፡ቃልሽን፡ሰሙ፤

ወመልአ፡ምድረ፡አውያትኪ፣
ጩኸትሽ፡ምድርን፡መላ፤

እስመ፡ደክሙ፡መስተቃትላን፡ምስለ፡መስተቃትላን፣
የናቡከደነፆር ፡ አርበኞች ፡ ከናቡከደነፆር፡አርበኞች፡ጋር፡ደከመዋልና፣
የናቡከደነፆር ፡ አርበኞችስ ፡ ያቸንፋሉ፡እንጂ፡አይቸነፉም፡ብሎ፡የግብፃውያን ፡ አርበኞች ፡ ከግብፃውያን ፡ አርበኞች፡ጋራ፡ደከመዋልና፤

ኀቡረ፡ወድቁ፡ኵሎሙ፣
ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ድል ፡ ተነሥተዋልና፤

፲፫፤ ቃል፡ዘነበበ፡እግዚአብሔር፡በእደ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፤
በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር፡የተናገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ከመ ፡ ይመጽእ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ እንዲመጣ፤

ወይቀትላ፡ለምድረ፡ግብፅ፣
ግብፅን ፡ እንዲወጋት ፡ የተናገረው ፡ ነገር፡ይህ፡ነው፤

፲፬፤ንግሩ፡በግብፅ፤
በግብፅ፡ተናገሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዜንዉ፡በመግደሎን፤
በመግደሎንም፡አውሩ፤

ወአስምዑ፡በሜምፎስ፡ወበጣፍናስ፡
በሜምፎስና፡በጣፍናስ፡አሰሙ፤

ወበሉ፡ቁሙ፡ወተደለዉ፤
ተዘጋጅታችሁ፡ቁሙ፡በሉ፤

እስመ፡በልዐት፡ኲናት፡ዐውደከ፡
ጦር ፡ ዙሪያህን ፡ አጥፍታለችና ፡ ማለት፡ሠራዊትህን፡አጥፍታለችና፤

፲፭፤ለምንት፡ተኀጥአ፡ኀያላኒከ፡
አንዋጋምና ፡ እንዲህ ፡ ትለናለህ ፡ ትሉኝ፡እንደሆነ፡አርበኞችህ፡ለምን፡ታጡ፤

ወኢሀለዉ፤
አልነበሩም፤

እስመ፡እግዚአብሔር፡አድከሞሙ፤
እግዚአብሔር፡በመከራ፡አድክምዋቸዋልና፤

፲፮፤ወብዙኅ፡ደክሙ፤
በብዙ፡ደክመዋልና፡

ወወድቁ፤
ድል፡ተነሥተዋልና፤

ወአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ይብሎ ፡ ልካልኡ ፡
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል፤

ተንሥእ፡ንግባዕ፡ብሔረነ፡ኀበ፡ሕዝብነ፡
ተነሥ ፡ ከወገኖቻችን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሀገራችን፡እንመለስ፤

ወውስተ ፡ ምድረ ፡ ሙላድነ ፡ እምገጸ ፡ መጥባሕተ፡አረሚ፤
ከአረማዊ፡ጦር፡የተነሣ፡ወደ፡ተወለድንበት፡ሀገር፡እንመለስ፡አለው፤

፲፯፤ ወሰመዩ ፡ ስሞ ፡ ለፈርዖን ፡ ንጉሠ ፡ ግብፅ፡ኒካዑ፡
የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፡ ስሙን ፡ አንካሳ፡አሉት፤

ሳኦን፡
ሳኦን፡ሠባራ፤

ሐኤኬር፤
ሰላላ፤

ሐሙኤድ፤
ደካማ ፡ አሉት ፤ አንድም ፡ ሳኦን ፡ ኀሠር፤ ሐኤኬር ፡ ምቱረ ፡ ሥርው፤ሐሙኤድ፡ ዘበጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ዘበጽሐ፡ ጊዜከ፡ማለት፡ነው፤

፲፰፤ ሕያው ፡ አነ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ፀባዖት፡ስሙ፤
ስሙ ፡ አቸናፊ ፡ የሚባል ፡ እግዚአብሔር፡ሕያው፡ነኝ፡አለ፤

ከመ፡ዕፀ፡ጠርቤንቶስ፡ዘውስተ፡አድባር፤
በደጋ፡ያለ፡ዱር፡ብዙ፡እንደሆነ፤

ወከመ፡ቀርሜሎስ፡ዘውስተ፡ባሕር፤
በደሴትም ፡ ያለ ፡ ተክል ፡ ብዙ ፡ እንደሆነ፤

ይመጽእ፡ንዋይ፡ዘአፍለሱ፡
ማርከው ፡ የወሰዱት ፡ የግብፃውያን፡ ገንዘብ ፡ በዝቶ ፡ ይመጣል ፤ ከዚያ፡ እንዳለ፡ሁኖ፡እንዲህ፡አለ፤አንድም፡ ይወስዱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወያመጽኡ፡ ክብራ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ፡ ወይወስ ድዎሙ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው፤ አንድም ፡ በደጋ ፡ ያለ ፡ ወስፈንጠር፡ እንዲይዝ፡እንዲቆነጥጥ፡ቀርሜሎስ፡ የቆላ ፡ ጋቢሎ ፡ እንዲይዝ ፡ እንዲቆ ነጥጥ ፡ ገንዘቧ ፡ ተይዞ ፡ ይሄዳል፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ጠርቤንቶስ፡

በደጋ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ዱር ፡ ደስ ፡ እንዲ ያሰኝ፡ወከመ፡ቀርሜሎስ፤በደሴትም፡ ያለ ፡ ተክል ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ይመጽእ፡ ንዋይ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ገንዘቧ፡ማርካ፡ያመጣችው፡የግብፅ፡ ከብቷ፡ተማርኮ፡ይሔዳል፤አንድም፡ ከመ፡ዕፀ፡ጠርቤንቶስ፡በደጋ፡ያለ፡ ተክል ፡ እንዲነቀል ፤ ወከመ ፡ ቀርሜሎስ፡በውኃ፡ዳር፡ያለ፡ፊላ፡ ቁጠማ ፡ እንዲነቀል ፤ ይመጽእ ፡ ገንዘቧ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ ተነቅሎ ፡ ይሔዳል፤ጠርቤንቶስ፡ባለው፡ኤጠቢ ርዮን፡ይላል፤

፲፱፤ወግበሪ፡ለኪ፡መካነ፡እንተ፡ትነብሪ፡ ወለተ፡ግብፅ፤
ጠላት ፡ ጠፍቶልሽ ፡ ተዘልለሽ፡ የምትኖሪ፡የግብፅ፡ልጅ፡አንባውን፡ ቆርቍሪ፤

እስመ፡ኖፍ፡መገዘበረ፡ትከውን፤
ኖፍ ፡ ተፈታ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሆና ለችና፤

እስመ፡አልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴታ፡
በውስጧ፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡የሉምና፤

፳፤ ዕጐልት ፡ ሠናይት ፡ ግብፅ ፡ እንተ ፡ ተነሥአት፡እምደቡብ፡
ከባቢሎን፡ተነሥታ፡የሔደች፡ግብፅ፡ ያማረች ፡ የተወደደች ፡ ጊደር ፡ ናት ፤ ያች፡እንድትቀናጣ፡ፈጣሪ፡የለኝም፡ አለች፤

ወአምጽእዋ፤
ማርከው፡የወሰዷት፤

፳፩፤ወአስባቢሃኒ፡ምስሌሃ፡
ከርሷ፡ጋራ፡ያሉ፡አርበኞቿ፤አንድም፡

አሳቢሃ፡ቢል፡በደመወዝ፡ተገዝተው፡ የሚዋጉላት፡ሰዎች፤

ከመ ፡ አልሕምተ ፡ መጋዝእት ፡ እለ ፡ የሐር ስዎሙ፡በውስቴታ፤
በውስጧ ፡ እንደሚያርሱባቸው ፡ ገቾች፡ናቸው፤

እስመ፡እሙንቱኒ፡ጐዩ፤
እነርሱ፡ሸሽተዋልና፤

ወተሰውጡ፡ኅቡረ፤
አንድ፡ሆነው፡ተመልሰዋልና፤

ወኢቆሙ፤
አልቆሙምና፤

እስመ፡በጽሐቶሙ፡ዕለተ፡ሞቶሙ፤
የሚሞቱባት፡ቀን፡ደርሳባቸዋለችና፤

ወዓመተ፡ይትቤቀልዎሙ፤
ተበቅለው፡እነርሱን፡የሚያጠፉባት፡ ቀን፡ደርሳባቸዋለችና፤

፳፪፤ ቃላ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ተሐውር፡በኃይል፤
እንደ፡እባብ፡ቃሏን፡አቀጠነች፡አለ፤ ስትጮህ ፡ ስታለቅስ ፤ አንድም ፡ በተ ድላ፡በደስታ፡የምትኖር፡ግብፅ፡

ተሐውር፡በኃይል፤
በግድ፡ተማርካ፡ትሔዳለች፤

ወይመጽእዋ፡በጕድብ፡ከመ፡ዘይሜፅር፡ዕፀ፤
እንጨት ፡ እንደሚፈልጥ ፡ ሰው ፡ ገጀሞ፡ይዘው፡ይመጡባታል፤

፳፫፤ግዝሙ፡ዖማ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ዛፏን፡ቍረጡ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡ትበዝኅ፡እምአንበጣ፤
ከአንበጣ፡ይልቅ፡ትበዛለችና፤

ወኢትትኌለቍ፤
አትቈጠርምና፤



www.ethiopianorthodox.org

ወአልባ፡አቅም፤
ልክ፡የላትምና፤

፳፬፤ተሐፍረት፡ወለተ፡ግብፅ፤
የግብፅ ፡ ልጅ ፡ መከራ ፡ መጥቶባት ፡
አፈረች፤

ወገብዐት ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡
እምደቡብ፤
ከባቢሎን ፡ በመጡ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡
ወደቀች፤

፳፭፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት ፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እትቤቀሎ፡ለአሞንሜኖን፤
አሞንሜኖን ፡ ንጉሥ ፤ አንድም ፡
ጣዖት፤ አንድም ፡ ካህን ፡ ጣዖት ፡ ነው
እበቀለዋለሁ፤

ወለፈርኦን፤
አሞንሜኖንን፡ንጉሥ፡ብሎ፡ገለጸው፤
ፈርኦንን፡እበቀለዋለሁ፤

ወለግብፅ፤
ግብፃውያንን፡እበቀላቸዋለሁ፤

ወለአማልክቲሃ፤
ካህን ፡ ጣዖት ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡
ገለጠው፤ጣዖቶቿን፡እበቀላቸዋለሁ፤

ወለነገሥታ፤
ነገሥታቷን፤

ወለእለ፡ይትዌከሉ፡ቦቱ፤
የሚታመኑበትን፡ሰዎችም፡እበቀላቸ
ዋለሁ፤

፳፮፤ ወአገብኦሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እለ ፡
የኃሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤
ሰውነታቸውን፡ለጥፋት፡በሚፈልጓት፡
ሰዎች፡እጅ፡አሳልፌ፡እጥላቸዋለሁ፤

ወውስተ ፡ እደ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡
ባቢሎን፤
በባቢሎን፡ንጉሥ፡በናቡከደነፆርም፡
እጅ፡እጥላቸዋለሁ፤

ወውስተ፡እደ፡አግብርቲሁ፤
በባሮቹ፡እጅ፡እጥላቸዋለሁ፤

ወእምድኅረዝ ፡ ትገብዕ ፡ ከመ ፡ መዋዕለ ፡
ቀዲሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደቀደመው ፡ ወደ ፡
መሆን ፡ ትመለሳለች ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

፳፯፤ ወአንተሰ ፡ ገብርየ ፡ ያዕቆብ ፡
ኢትፍራህ፤
ባርያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ አንተ ፡ ግን ፡
አትፍራ፤

ወኢትደንግፅ፡እስራኤል፤
እስራኤልም፡አትደንግጥ፤

እስመ፡ናሁ፡አነ፡አድኅነከ፡እምርኁቅ፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ ከራቀ ፡ ወገን ፡ ከአሕዛብ፡
አድንሃለሁና፤

ወለዘርዕከኒ፡እምኀበ፡ፄወውዎሙ፤
ልጆችህንም፡ከማረኳቸው፡ቦታ፡አድ
ናቸዋለሁና፤

ወይሠወጥ፡ያዕቆብ፤
ያዕቆብ፡ወደ፡ሀገሩ፡ይመለሳል፤

ወየዐርፍ፡ወይነውም፤
ጠላት ፡ ጠፍቶለት ፡ ተዘልሎ ፡
ይኖራል፤

ወአልቦ፡ዘያነጥዮ፤
የሚዘበዝበው፡የለም፤

፳፰፤ኢትፍራህ፡ያዕቆብ፡ገብርየ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፤
ባርያዬ፡ያዕቆብ፡አትፍራ፡አለ፡እግዚ
አብሔር፤



እስመ፡አነ፡ሀሎኩ፡ምስሌከ፤
እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በረድዔት ፡
አለሁና፤

እስመ ፡ እገብር ፡ ማኅለቅተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡
አሕዛብ፡ኀበ፡ወሰድኩከ፡ህየ፤
በዚያ ፡ አስማርኬ ፡ በወሰድኩህ ፡
በአሕዛብ፡ላይ፡የጥፋት፡ፍጻሜን፡አደ
ርጋለሁና፤

ወኪያከሰ፡ኢያሐልቀከ፡በህየ፤
አንተን፡ግን፡በዚያ፡አላጠፋህም፤

እጌሥጸከ፡በጽድቅ፤
በእውነት፡በመከራ፡እገሥጽሃለሁ፤

ወአንጽሖኒ፡ኢያነጽሐከ፤
መከራውን ፡ ሳላቀምስ ፡ ከኃጢአት ፡
አላነፃሕም፤አንድም፡ወአድኅኖ፡ኢያ
ድኅነከ ፡ ይላል ፤ መከራውን ፡
ሳላቀምስ፡ከፍዳ፡አላድንህም።

## ምዕራፍ ፡ ፵፯ ፤

፩፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡በእንተ፡ኢሎፍሊ፤
ኢሎፍላውያን ፡ እንዲጠፉ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ፡የመጣ፡የተነገረ፡የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤አንድም፡በኤ
ርምያስ ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል፡ይህ፡ነው፤

ዘእንበለ፡ይቅትላ፡ፈርዖን፡ለጋዛ፤
ፈርዖን፡ጋዛን፡ሳያጠፋት፤

፪፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤
ናሁ፡ማይ፡የዓርግ፡እምደቡብ፤
ከባቢሎን፡ውሃ፡ይመጣል፤
ወይከውን፡ውኂዝ፡ዘይደፍና፡ወዘየሰጥማ፤
[illegible]

ያሰጥማት ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ጦሩ ፡
ምድርን፡የሚያጠፋት፡ይሆናል፤

ወለሀገርኒ፡በምልዓ፤
አገሪቱንም ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያጠፋት ፡
ይሆናል፤

ወለእለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፤
በውስጧ ፡ የሚኖሩትንም ፡ የሚያጠ
ፋቸው፡ይሆናል፤

ወየአወይዉ ፡ ወይግዕሩ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡
ዘይነብሩ፡ውስተ፡ምድር፤
በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ፈጽመው፡ይጮሃሉ፤

፫፤ እምድምፀ፡መራደ፡ኃያላኒሁ፡ምስለ፡
ንዋየ፡ሐቅሎሙ፤
ከበዳ ፡ ፀብታቸው ፡ ጋራ ፡ ከሚጠ
በጥቡ፡አርበኞች፡ድምፅ፡የተነሣ፤

ወእምድልቅልቀ፡ሠረገላሁ፤
ከሠረገላው፡ንውጽውጽታ፡የተነሣ፤

ወእምድምፀ፡መንኰራኵሩ፤
ከሠረገላው ፡ መንኰራኵር ፡ ድምፅ ፡
የተነሣ፡ይጮሃሉ፤

አበውኒ፡ኢይትመየጡ፡ኀበ፡ውሉዶሙ፤
አባቶችም፡ወደ፡ልጆቻቸው፡አይመ
ለሱም፤

እስመ፡ደክሙ፡እደዊሆሙ፤
እጃቸው ፡ ለመወርወር ፡ ቃላቸው ፡
ለመምከር፡ደክሟልና፤

፬፤ በዕለት፡እንተ፡ትመጽእ፡ታጥፍአሙ፡
ለኢሎፍሊ፤
ኢሎፍላውያንን፡ታጠፋቸው፡ዘንድ፡
ጦር፡በምትመጣበት፡ቀን፡እጃቸው፡
ለመወርወር፡ደክሟልና፤

ወ[illegible]ማስኖን፡ለጢሮስ፡ወለሲዶና፤
ለ[illegible]ሮስንና፡ሲዶናን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለዘርሎሙ፡እለ፡ተርፉ፡ረድኤቶሙ፡
የቀሩ፡ረዳቶቻቸውንም፡ሁሉ፡ያጠፋ
ቸዋል፤

እስመ ፡ ይሤርዎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለኢሎፍሊ፤
እግዚአብሔር፡ኢሎፍልያንን፡ያጠፋ
ቸዋልና፤

ወለእለ፡ተርፉ፡ደስያተ፡ከፍቱር፡
ከፍቱር፡በሚባል፡ደሴት፤አንድም፡
ቈላፍ፡በሚኖርበት፡ደሴት፡የቀሩ
ትንም፡ያጠፋቸዋልና፤

፭፤ምጽአታ፡ብርሃት፡ለጋዛ፡
በጋዛ ፡ ቡሕነት ፡ ወጣባት ፡ አለ ፤
ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ በመሸከም ፤
አንድም ፡ ፍርሀት ፡ ቢል ፡ ፍርሀት ፡
መጣባት፤

ወተገድፈት፡አስቀሎና፡
አስቀሎና፡ጠፋች፤

ወእለሂ፡፩ዱ፡፩ዱ፡ተርፉ፡ውስተ፡ኢማቂም፡
ከዚያ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ በአምባ ፡
የቀሩ፡ሰዎችም፡ጠፉ፤

፮፤ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ትገምዲ ፡ ወይሌ ፡
መጥባሕቱ፡ለእግዚአብሔር፡
የእግዚአብሔር ፡ ሥልጣኑን ፡ እስከ ፡
መቼ፡ድረስ፡ትቆርጫለሽ፡ወዮ፤

ወእስከ፡ምንትኑ፡ኢታረምሚ፡
ዝም ፡ የማትዪ ፡ ምን ፡ እስኪሆን ፡
ድረስ፡ነው፤አንድም፡እስከ፡ማእዜኑ፡
ቢል ፡ ዝም ፡ የማትዪ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡
ድረስ፡ነው፤

ግብኢ፡ውስተ፡ቀቀብኪ፡
[illegible]ቱ፡ተመለሽ፤

፯፤እፎ፡ታረምም፡ዘእግዚአብሔር፡አዘዘ፡
ላዕለ፡አስቀሎና፡
እግዚአብሔር ፡ በአስቀሎና ፡ ላይ ፡
ያዘዛት ፡ መቅሠፍት ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡
አለች፤

ወላዕለ፡ጸራልዩ፡ዘባሕር፡
በጽንፈ፡ባሕር፡ባለ፡በጸራልዩ፡ላይ፡
ትንቢት ፡ ይነገራል ፤ መከራ ፡ ይመ
ጣል፤ በእንተ ፡ ሞዓብ ፡ ማንሻ ፤
አንድም፡ በጽንፈ ፡ ባሕር ፡ ባለች ፡
ጸራልዩ፡ላይ፡የታዘዘውን፡ሳታደርግ፡
መዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡
ዝም፡ትላለች፡ወደ፡ላይ፡ጨርስ፤

ሀየ፡ትትነሣእ፡
ነገር፡ዘበእንተ፡ሞዓብ፡በሞዓብ፡ላይ፡
ትንቢት ፡ ይነገራል ፡ መከራ ፡ ይመ
ጣል።

## ምዕራፍ ፡ ፵፰ ፤

ጉባዔ፤

፩፤ነገር፡ዘበእንተ፡ሞዓብ፡
ሞዓብ ፡ እንድትጠፋ ፡ የተናገረው ፡
ነገር፡ይህ፡ነው፤

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፀባዖት ፡
አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አቸናፊ፡እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ወይሌ፡ላዕለ፡ናባው፡
በናባው፡ልቅሶ፡አለ፤

እስመ፡ጠፍአት፡
ጠፍታ[illegible]



ወተነሥአት፡ቀርያታርም፡
ቀርያታርም፡ተማርካ፡ሔደች፤

ወተኀፍረ፡ፀወና፡ወተመውዐ፡
አምባዋ፡ተፈታ፤አንድም፡ንጉሥዋ፡
ጠፋ፡ድል፡ተነሥቶ፡አፈረ፤

፪፤ አልባ፡እንከ፡ፈውስ፡ለሞዓብ፡
እንግዲህ፡ወዲህ፡ለሞዓብ፡ድኅነት፡
የላትም፤

ላዕለ፡ሐሴቦን፡ሜጡ፡ዘላዕሌሃ፡እኩየ፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ የመጣውን ፡ ወደ ፡
ሐሴቦን፡መለሱ፤

ንዑ፡ንምትራ፡እምውስተ፡አሕዛብ፡
ከአሕዛብ ፡ ለይተን ፡ እናጠፋት ፡
ዘንድ፡ኑ፤

ወሐዲገኒ፡ትትሐደግ፡
ጠፊአ፡ትጠፍዕ፡ተዪውዎ፡ትዪወው፡
ሲል፡ነው፤ትጠፋለች፤

እስመ፡እምድኅሬሃ፡ትመጽእ፡ሠናት፡
ጦር፡እርሷን፡ተከትላ፡ትመጣለችና፤

፫፤ እስመ ፡ ቃለ ፡ እለ ፡ ይዌውዑ ፡
እምውስተ፡አድባር፡
የሚደነፉ ፡ የናቡከደነፆር ፡ ሠራዊ
ት፡ቃል፡ተሰምቷልና፤

ዓቢየ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ትትቀጠቀጥ ፡ ሞአብ ፤
ሞአብ ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡ ትቀጠቀ
ጣለች፤

፬፤ ዜንዉ፡ውስተ፡ጎራ፡
ጥፋቷን፡በጐረቤቿ፡ተናገሩ፤

፭፤ እስመ፡በዝኅ፡ብካያ፡
ለቅሶዋ፡በዝቷልና፤

ወዓርጉ፡እንዘ፡ይበክዩ፡በፍኖተ፡አሮሜንዮ፡
[illegible]

የድንፋታን፡ቃል፡ሰማሁ፤

ወቅጥቃጤ፡
በመከራ፡መቀጥቀጡን፡ሰማሁ፤

፮፤ ጕዩ፡ወአድኅኑ፡ነፍሰክሙ፡
ሽሹታችሁ ፡ ሰውነታችሁን ፡ ከሞት ፡
አድኑ፤

ወንበሩ፡ገዳመ፡ከመ፡ሐለስትዮ፡
እንደ፡በዳ፡አኽያ፡በምድረ፡በዳ፡ኑሩ፤

፯፤ ወይነሥኡኪ፡
ማርከው፡ይወስዱሻል፤

እስመ፡ተወከልኪ፡በምግባርኪ፡
በሠራሽው፡በጣዖትሽ፡አምነሻልና፤

ወበመዛግብትኪ፡
ባደለብሽው፡በድልብሽ፡አምነሻልና፤

ወለኪኒ፡ይእኀዙኪ፡
አንቺንም ፡ ማርከው ፡ ይዘውሽ ፡
ይሔዳሉ ፡ (በመከራ ፡ ይይዙሻል) ፡
ብትልም፤

ወይወጽእ፡ኮሞስ፡ኀበ፡ያፈልስዎ፡
ጣዐቱ ፡ ማርከው ፡ ወደሚወስዱበት ፡
ቦታ፡ይወጣል፤

ወገነውቱኒ፡
ካህናተ፡ጣዖቱም፡ተማርከው፡ወደሚ
ሄዱበት፡ቦታ፡ይወጣሉ፤

ወመላእክቲሁኒ፡ኅቡረ፡
አለቆቹም ፡ አንድነት ፡ ተማርከው ፡
ወደሚሔዱበት፡ቦታ፡ይወጣሉ፤

፰፤ ወይመጽእ ፡ ተሠርዎ ፡ እምላዕለ ፡
ኵሉ፡አህጉር፡
በሀገሩ፡ሁሉ፡ጥፋት፡ይመጣል፤

ወአልቦ፡ዘይድኅን፡
የሚድን፡የለም፤

ወይመውት፡ዘውስተ፡ዝ፡ሀገር፡
[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ወየሐልቅ፡ዘውስተ፡ገዳም፤
በገጠርም፡ያለ፡ሰው፡ያልቃል፤
በከመ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንደተናገረ፤

፱፤ሀቡ፡ጽጌ፡ለሞአብ፤
ለአሞአብ ፡ አበባውን ፡ አምሳል ፡
መርገፍ፡አድርጋችሁ፡ስጡ፡ማለት፡
ያ፡እንዲረግፍ፡ትጠፋለች፡ስትሉ፤
አንድም፡ሰነፍ፡እርቅ፡አድርጋችሁ፡
ሞዓብን፡አጥፏት፤
እስመ፡ወጺአ፡ትወጽእ፤
ተማርካ፡ትሔዳለችና፤
ወይትመዘበር፡ኵሉ፡አህጉሪሃ፤
አገሮቿ፡ሁሉ፡ይጠፋሉና፤
ወአልቦ፡ዘይነብሮን፤
የሚኖርባቸው፡ሰው፡የለምና፡ሀቡ፡
ጽጌ፡ብለህ፡እሥር፤

፲፤ርጉመ፡ለይኩን፡ዘያሰትት፡ነገረ፡እግዚ
አብሔር፤
የሞአብን፡ሰዎች፡አጥፉ፡የሚል፡የእ
ግዚአብሔርን፡ነገር፡የሚንቅ፡የሚያ
ቃልል፡ሰው፡ርጉም፡ይሁን፤
ወርጉም ፡ ውእቱ ፡ ዘይከልእ ፡ መጥባሀተ ፡
እምደም፤
የባቢሎንን፡ሰዎች፡ደም፡ከማፍሰስ፡
ሰይፉን፡የሚመልስ፡ሰው፡ርጉም፡
ነው፤አንድም፡ርጉመ፡ለይኩን፤ከአጋ
ንንቷ፡ጋራ፡ተዋጉ፡የሚለውን፡የእግ
ዚአብሔርን፡ነገር፡የሚንቅ፡የሚያ
ቃልል፡ሰው፡ርጉም፡ይሁን፤
ወርጉም፡ውእቱ፤
አጋንንትን፡ከማጥፋት፡ሥልጣኑን፡

፲፩፤ወአዕረፈት፡ሞአብ፡እምደቂቃ፤
ከልጆቿ፡የተነሣ፡ሞአብ፡ጠላት፡
ጠፍቶላት፡አርፋ፡ኖረች፤
ወተአመነት፡በዓቃቢሃ፤
በጣዖቷ፤አንድም፡በወይን፡ጠባቂዋ፤
አንድም ፡ በንጉሥዋ ፤ አንድም ፡
በዘበኞቿ፡ታመነች፤
ወኢተሠውጠ፡እምጻሕብ፡ውስተ፡ጻሕብ፤
ወይኗ፡ከአንዱ፡ፊቀን፡ወደ፡አንዱ፡
ፊቀን ፡ አልተመለሰም ፤ አልተገለ
በጠም፤
ወኢሖረ፡ወኢፈለሰ፤
ከአንዱ፡አገር፡ወደ፡አንዱ፡አገር፡
አልሔደም፤
በእንተ፡ዝንቱ፡ቆመ፡ጣዕሙ፤
ስለ፡አልተገለበጠ፡ጣዕሙ፡ጸና፤
ወመዓዛሁኒ፡ኢየኀልቅ፤
መዓዛውም፡አይፈጸምም፤አንድም፡
ወኢተሠውጠ ፡ ወኢሖረ ፡ ሰው ፡
ከአንዱ፡ሀገር፡ወደ፡አንዱ፡ሀገር፡
ተማርኮ፡አልሔደም፤በእንተ፡ዝንቱ፡
ስለአልተማረከ፡ ተድላ ፡ ደስታው ፡
ጸና፤ ወመዓዛሁኒ ፡ ተድላ ፡ ደስታው ፡
አይፈጸምም፤

፲፪፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡
መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ስለዚህ፡ነገር፡እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡
ወራት ፡ ይመጣል ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እፌኑ፡ሎቱ፡ጠዋይያነ፤
ጠማሞች፡ሰዎችን፡አመጣበታለሁ፤
ወይጠውይዎ፤
ይጠሙበታ[illegible]



ብርሌውን ፡ ብርጭቆውን ፡ ይሠ
ብራሉ ፤ አንድም ፡ አባለ ፡ ዘሩን ፡
ይሠልባሉ፤
ወይሠብሩ፡አጽሕብቲሁ፤
ፊቀኑን ፡ ይሠብራሉ ፤ አንድም ፡
ሕዋሣቱን፡ያጠፋሉ፤

፲፫፤ወትትኀፈር፡ሞአብ፡እምነ፡ኮሞስ፤
ከጣኦቱ፡የተነሣ፡ሞአብ፡በመከራ፡
ታፍራለች፤
ከመ፡ተኀፍረት፡ቤተ፡እስራኤል፡እምነ፡
ቤቴል፤
ቤተ፡እስራኤል፡በቤቴል፡ከቆመው፡
ጣዖት፡የተነሣ፡በመከራ፡እንደ፡
አፈረች፡ታፍራለች፤
ተስፋሆሙ፡ለእለ፡ተወከሉ፡ቦቱ፤
የሚታመኑበት፡ሰዎች፡ተስፋቸው፡
የሚሆን፡ብሎ፡ለቤቴል፡ቀጠለ፤

፲፬፤ወእፎ፡ትብሉ፡ጽኑዓን፡ንሕነ፤
እኛ ፡ ጽኑዓን ፡ ነን ፡ እንደምን ፡
ትላላችሁ?
ዕደው፡ኃያልን፡በውስተ፡ቀትል፤
በሰልፍ፡አርበኞች፡ነን፡እንደምን፡
ትላላችሁ?

፲፭፤ ወተሐጕለት ፡ ሞዓብ ፡ በውስተ ፡
ቀትል፡ሀገሩ፤
ሀገሩ፡ሞአብ፡በሰልፍ፡ጠፋች፤
ወኅሩያኒሁ፡ወወራዙቲሁ፡ወረዱ፤
አርበኞቹ፡ጐልማሶቹ፡ተማርከው፡
ወደ፡ባቢሎን፡ወረዱ፤
ወተቀትሉ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባኦት፡
ስሙ፤
ስሙ ፡ አቸናፊ ፡ የሚባል ፡ እግዚአ
ብሔር፡ጠፉ፡አለ፤

፲፮ [illegible]

የሞአብ ፡ ጥፋት ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡
ደረሰች፤
ወአፍጠነት፡ጥቀ፡እከዩሂ፤
ክፋቱም፡እጅግ፡ቀረበች፤

፲፯፤ወአንቀልቅሉ፡ሎቱ፡ኵልክሙ፡እለ፡
ዓውዱ፤
በዙሪያው፡ያላችሁ፡ሰዎች፡ሁላችሁ፡
ተነዋወፁለት፤
ወኵልክሙ፡እለ፡ተአምሩ፡ስሞ፤
ስሙን፡የምታውቁ፡ሁላችሁ፡ተነዋወ
ፁለት፤
ወበሉ ፡ እፎ ፡ ተቀጥቀጠት ፡ ቀስታም ፡
ጽንዕት፤
ፅንዕት ፡ የምትሆን ፡ መንደርቶ ፡
ሞአብ፡እንዴት፡ጠፋች፡በሉ፤
ወበትር፡ዐባይ፤
ትልቅ ፡ ብትር ፡ የሆነች ፡ ሞአብ ፡
እንዴት፡ጠፋች፡በሉ፤

፲፰፤ ረዲ ፡ እምነ ፡ ክብርኪ ፡ ወንበሪ ፡
ውስተ፡ርጡብ፡ወለተ፡ዴባን፤
የዴባን፡ልጅ፡ከዙፋንሽ፡ወርደሽ፡
በጭቃ፡ላይ፡ተቀመጪ፡አለ፤መከራ፡
እንዳለባት፡መናገር፡ነው፤አንድም፡
ከክብርሽ ፡ ከመንግሥትሽ ፡ ተዋ
ርደሽ፡በሐሣር፡ቦታ፡ተቀመጪ፤
ተቀጥቀጠት፡ሞአብ፤
ሞአብ፡ጠፋች፤
ዐርገ፡ላዕሌኪ፡ዘየሐሥሮ፡ለአጽዋንኪ፤
አምባዎችሽን ፡ የሚያፈርሰው ፡
ንጉሥ፡ወደ፡አንቺ፡ዘመተ፤አንድም፡
ኃያላኖችሽን፡ያጐሰቍላቸዋል፤

፲፱፤ ቁሚ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ወርእዩያ ፡
ለእንተ፡ትነብር፡ውስተ፡አሮኤል፤
አሮኤል፡በባቢሎን፡የምትኖረውን፡

www.ethiopianorthodox.org

ወተሰአሊዮ፡ለዘአምሰጠ፡እንዘ፡ይጐይይ፡
ሲሸሽ፡ያመለጠውን፡ጠይቂው፤

ወበሊዮ፡ምንተ፡ኮነት፡ሞአብ፡
ሞአብ፡ምን፡ሆነች፡ብለሽ፡ጠይቂው፤

፳፤ ተኀፍረት፡ሞአብ፡
ሞአብ፡መከራ፡መጥቶባት፡አፈረች፡ ይልሻል፤

ወተቀጥቀጠት፡
በጦር፡ጠፋች፤

ዐውይዉ፡ወገአሩ፡
ጩሁ፡አልቅሱ፤

ወዜንዉ፡ውስተ፡አርኖን፡ከመ፡ተኀጕለት፡ ሞአብ፡
ሞአብ ፡ እንደ ፡ ጠፋች ፡ በአርኖን ፡ ተናገሩ፤

፳፩፤ ወይመጽእ፡ኵነኔ፡ውስተ፡ምድረ፡ ሐሜሶር፡ወላዕለ፡ከይሎን፡
በሐሜሶር፡አገርና፡በከይሎን፤

ወኢያሳ፡ወአራባስ፡
በኢያሳ፡በአራባስ፤

፳፪፤ ወዴባን፡ወናባው፡
በዴባንና፡በናባው፤

ወላዕለ፡ዴብላታ፡
በዴብላታ፤

፳፫፤ ወቀርያታርም፡
በቀርያታርም፤

ወቤተ፡ገብአም፡ወቤተ፡ሚኦን፡
በገብአምና፡በሚኦን፤

፳፬፤ ወቀርዮት፡ወባሳን፡
በቀርዮትና፡በባሳን፤

ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አህጉረ ፡ ሞአብ ፡ ዘቅሩብ ወዘርኁቅ፡
በሩቅም ፡ በቅርብም ፡ ባሉ ፡ በሞአብ ፡ አውራጃዎች፡ላይ፡ፍርድ፡ይመጣል፤

፳፭፡ ወተሰብረ፡ቀርነ፡ሞአብ፡
የሞአብ፡ንጉሥ፡ድል፡ተነሣ፡ጠፋ፤

ወተቀጥቀጠ፡እዴሁ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ሥልጣኑም ፡ ጠፋች ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፤ እጁን ፡ ንጉሥ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ቀርነ ፡ ሞአብ ፡ ሥልጣን ፡ ማለት፡ነው፤

፳፮፤አስከርዋ፡
በመከራ፡አረቂ፡አሰከሯት፤

እስመ፡ተአበየት፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፡
በእግዚአብሔር፡ላይ፡ታብያለችና፤

ወዓንኮለላ፡
መከራው፡ራሷን፡አዞራት፤

ወትጠፍህ፡እዴሃ፡
በእጇ ፡ ታጨበጭባለች ፡ ማለት ፡ የብስጭት፤

ወበቂያዓ፡ትከውን፡ሰሐቀ፡
በትፋቷ፡መዘበቻ፡ትሆናለች፤

፳፯፤ወለእመ፡ኢሰሐቅዋ፡ትከውን፡ለከ፡ ከመ፡ሰራቂ፡ዘተረክበ፡
በሞአብ ፡ አሕዛብ ፡ ካልዘበቱባት ፡ እስራኤል ፡ ሲሰርቅ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ እንደ፡ጐረቤት፡ሌባ፡ትሆንብሐለች፤ አንድም ፡ መከራ ፡ አምጥቼ ፡ካላዘበት ኩባት፡እንደ፡ጐረቤት፡ሌባ፡ትሆንብ ሐለች፤

ለእለ፡ተናገርከ፡ትትሐወከ፡ባቲ፡
እየጸለይህባት፤አንድም፡ትንቢት፡እየ ተናገርህባት፤መከራ፡መጥቶ፡ትታወ ካለች፤

፳፰፤ እስመ፡ተኀደጉ፡አህጉር፡
አገሮች፡ተፈትተዋልና፤

ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ሞአብ፡



በሞአብ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በዓለት ፡ ደንጊያ፡በዋሻ፡ኖሩ፤

ወውስተ፡በአታት፡
በጉድጓዱ፡ተቀመጡ፤

ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ እለ ፡ የሐዕና ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ፡
ልጆቻቸውን ፡ በዋሻ ፡ እንደሚያ ሳድጉ፡ርግቦች፡ሆኑ፤

ወውስተ፡አፈ፡ግበብ፡
በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያሳድጉ ፡ ርግቦች፡ሆኑ፤

፳፱፤ሰማዕነ፡ዕዕለተ፡ሞአብ፤
የሞአብን፡ስድብ፡ሰማን፤

ወዓቢየ፡ሐሣረ፡ዘሐሥረ፡
የተዋረደውን ፡ ብዙ ፡ ውርደቱን ፡ ሰማን፤

ወትዕቢቶ፡ዘአዕበየ፡ልቦ፡
ልቡናውን ፡ የሚያስታብይበትን ፡ ትዕቢቱን፡ሰማን፤

፴፤አንሰ፡አእመርኩ፡ምግባሮ፡ይቤ፡እግ ዚአብሔር፡
እኔ፡ሥራውን፡አወቅሁ፡አለ፡እግዚአ ብሔር፤

ወአኮ፡በአምጣነ፡ኃይሉ፡ዘገብረ፡ከማሁ፡
ኃጢአቱ ፡ እንደ ፡ ኃይሉ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ አይደለም ፡ አለ ፤ ኃይሉ ፡ ሲያንስ፡ኃጢአቱ፡ሲበዛ፡ነው፤

፴፩፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አዐወዩ ፡ ላዕለ ፡ ሞአብ፡እንተ፡ኵለሄ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሁልጊዜ ፡ በሞአብ ፡ ላይ፡እጮሀለሁ፤

ወእገዕር፡ላዕለ፡ዕደወ፡ቂራዲስ፡አአወዩ፡
ኖራ፡በሚወቅጡ፡ኖራ፡በሚመርጉ፡ ሰዎች፡ላይ፡እጮሃለሁ፤

፴፪፤ወብካየ፡ኢያዜር፡እበኪ፡ለኪ፡ወይነ፡ ሱባማ፡
የሱባማ፡ወይን፡የሂለይን፡ለቅሶ፡አለ ቅስልሻለሁ፤ሂለይ፡ቃለ፡ቀጭን፡ናት፡ ቃሌን፡አቅጥኜ፡የሰዎችን፡ለወይኑ፡ ሰጥቶ ፡ ተናገረ ፤ አንድም ፡ ወብካየ ፡ ሳይናበብ፡ኢያዜር፡ለቅሶን፡አለቅስል ሻለሁ ፤ ወወይነ ፡ ሱባማ ፡ ይላል ፤ የሱባማም፡ወይን፡አለቅስልሻለሁ፤

እስመ፡አብሩ፡አሕራግኪ፡
ሐረጎችሽ ፡ ደርቀዋልና ፤ አንድም ፡ ወገኖችሽ፡ጠፍተዋልና፤

ዓደዉ፡ባሕረ፡
ወንዙን፡ተሻግረው፡ሔዱ፤

እስከ፡ባሕረ፡ኢያዜር፡
እስከ፡ኢያዜር፡ወንዝ፡ድረስ፡ሔዱ፤

ግዱፋንኪ፡
በየጐዳናው ፡ የወደቁ ፡ ሬሳዎችሽ ፡ በዙ፡ጠፉ፤

ወበጽሑ፡ላዕለ፡ቀምሕኪ፡
በተክልሽ፡ላይ፡ደረሱ፤

ወላዕለ፡ቀሥምኪ፡ወረደ፡ጥፍዓት፡
በአዝመራሽ፡ላይ፡ጥፋት፡መጣበት፤

ወአጥፍዕዎ፡ቀሠምት፡ዘእንበለ፡ይብስል፡
የሚያጠፉ ፡ ሰዎች ፡ ሳይበስል ፡ በጮርቃው ፤ አንድም ፡ ዘእንበለ ፡ ይስብል ፡ ይላል ፤ ሳይዘረዝር ፡ በቡቃያው፡አጠፉት፤

፴፫፤ወኀልቀ፡ትፍሥሕት፡ወኃሤት፡እም ከርሜል፡
ከርሜል፡ስመ፡ሀገር፡ነው፤ከከርሜል፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ጠፋ ፤ አንድም ፡ እምከራሜ፡ከራሚ፡ይላል፡ከወይኑ፡ ጠጅ፡ተድላ፡ደስታ፡ጠፋ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምድረ፡ሞአብ፤
ከሞአብ፡ዕፃ፡ተድላ፡ደስታ፡ጠፋ፤

ወወይንሂ፡እምነ፡ምክያድኪ፡ጠፍአ፤
ወይኑም፡ከአውድማሽ፡ጠፋ፤

ኢበነግህ፡አልቦ፡ዘያከይዱ፤
በነግህ፡የሚያበራዩት፡የለም፤

ወኢበሠርክ፡አልቦ፡ዘይገብሩ፤
በሠርክም፡የሚሠሩት፡የለም፤

፴፬፤እምአውያተ፡ሐሴቦን፡እስከ፡አርያል፤
ከሐሴቦን ፡ ጩኸት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
አርያል፡ድረስ፤

ወእስከ፡ኢያሳ፡ወሀቡ፡ቃሎሙ፤
እስከ፡ኢያሳ፡ድረስ፡ቃላቸውን፡ሰጡ፤

ወእምሴጎር፡እስከ፡ሐሮኒም፤
ከሴጎር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐሮኒም ፡
ድረስ፡ቃላቸውን፡ሰጡ፤

ዕጉልት፡እንተ፡፫ቱ፡ከረምታ፤
ሞአብ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆናት ፡
ጊደር፡ ናት ፤ ያች ፡ እንድትታበይ ፡
ታበየች፤

እስመ፡ማየ፡ኔምሬም፡ኮነ፡በድወ፤
የኔምሬም ፡ ውሀ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ሁኗልና፤

፴፭፤ ወአጠፍአ ፡ ለሞአብ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ሞአብን ፡ አጠፋታለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

ወዘየዓርግ፡ውስተ፡ምሥዋዕ፡ወየአጥን፡ለአ
ማልክቲሁ፤
ለጣዖቱ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያሣርግ ፡
ዕጣን፡የሚያጥን፡ሰው፡ይጠፋል፤

፴፮፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ልብየ ፡ ለሞአብ ፡
ይነቅ፡ከመ፡ዕንዚራ፤

እንደበገና ፡ ይጮሃል ፡ አለ ፤ ነቢይ ፡
ለሁሉ ፡ ያዝናልና ፤ አንድም ፡ ርኅሩኅ ፡
እግዚአብሔር፡አድሮበታልና፤

ወልብየ፡ላዕለ፡ዕደወ፡ቂራዲስ፡ይነቁ፡ከመ፡
ዕንዚራ፤
ልቡናዬም፡ኖራ፡በሚወቅጡ፡ጭቃ፡
በሚመርጉ፡ሰዎች፡ላይእንደ፡በገና፡
ይጨሀል ፡ አለ ፡ ነቢይ ፤ ለሁሉ ፡
ያዝናልና፤

በእንተ፡ዘገብረ፤
ከፉ፡ሥራ፡ስለ፡ሠራ፤

፴፯፤ እስመ ፡ በርእሰ ፡ ሰብእ ፡ ኵሉ ፡
ብርሐት፤
በሰው ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ቡሀነት ፡ ትወጣ
ለችና ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡
በመሸከም፤

ወኵሉ፡በሐውርት፡ይትላፀዩ፤
መንደሮች ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ይላ
ጫሉ፤

ወያአትቱ፡ኵሎ፡ዕሕሞሙ፤
ጢማቸውን፡ሁሉ፡ይነጩሉ፤

ወይትቀጠቀጡ፡ኵሉ፡ዕዳው፤
ትቢያው ፤ ጉድፉ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉ፡
ማለት፡አርበኞች፡ይጠፋሉ፤

ወይቀንቱ፡ሠቀ፡ሐቌ፡ኵሉ፤
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በወገባቸው ፡ ማቅ፡
ይታጠቃሉ፤

፴፰፤ውስተ፡ኵሉ፡አንሕስተ፡ሞአብ፡
በሞአብ፡ሠገነት፡ላይና፤

ወበውስተ፡ኵሉ፡መርሕብ፡ላህ፤
በዓደባባዩ፡ሁሉ፡ለቅሶ፡ይሰማል፤

እስመ [illegible]



እግዚአብሔር፡ለምንም፡ለምን፡እንደ
ማይረባ ፡ እንደማይጠቅም ፡ ድስት ፡
አጠፋኋት፡ብሏልና፤

፴፱፤እፎ፡ተወለጠት፤
ሞአብ ፡ በፍርሐት ፡ እንዴት ፡ ተለ
ወጠች?

ወሜጠት፡ዘባና፡ሞአብ፤
ሞአብ፡ጀርባዋን፡መልሳ፡አንገቷን፡
ቀልሳ፡እንዴት፡ሸሸች?

ወኮነት ፡ ሠሐቀ ፡ ወሥላቀ ፡ ለኵሉ ፡
አድያሚሃ፤
በመወሳሰኛዋ፡ላሉ፡ሁሉ፡መሣቂያ፡
መዘበቻ፡እንደምን፡ሆነች?

፵፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ናሁ፡ከመ፡ንሥር፡ይሠርር፤
እነሆ ፡ እንደ ፡ አሞራ ፡ ፈጥኖ ፡
ይመጣል፤

ወይሰፍሕ፡ክነፊሁ፡ኀበ፡ሞአብ፤
ወደ፡ሞአብ፡ሠራዊቱን፡ይሰዳል፤

፵፩፤ተእኅዘት፡ሐቌርዮት፤
ሐቌርዮት፡በመከራ፡ተያዘች፤

ወተእኅዛ፡አጽዋኒሃ፤
አምባዎቿ ፡ ተፈቱ ፤ አንድም ፡ አር
በኞቿ፡ጠፉ፤

ወኮነ ፡ ልበ ፡ ሠራዊተ ፡ ሞአብ ፡ ውእተ ፡
አሚረ፡ከመ፡ልበ፡ብእሲት፡እንተ፡ውስተ፡
ማሕምም፤
ያን፡ጊዜ፡የሞአብ፡ሠራዊት፡ልቡና፡
በምጥ ፡ እንደተያዘች ፡ ሴት ፡ ልቡና ፡
ሆነ፤

[illegible]

እስመ፡ተአበየት፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፤
በእግዚአብሔር፡ላይ፡ታብያለችና፤

፵፫፤ፍርሀት፤
በቁሙ፡ፍርሀት፤

ወጸድፍ፤
በገደል፡መውደቅ፤

ወመሥገርት፡ላዕሌኪ፤
ወጥመድ፡በአንቺ፡ላይ፡ይመጣል፤

እንተ፡ትነብሪ፡ሞአብ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ጠላት ፡ ጠፍቶልሽ ፡ ተዘልለሽ ፡
የምትኖሪ ፡ ሞአብ ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡
ወጥመድ ፡ ይመጣል ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፤ አንድም ፡ ፍርሃት ፡ የቤት ፡
ጦር፤ወጸድፍ፡የእዳሪ፡ጦር፤
ወመሥገርት ፡ የሜዳ ፡ ጦር ፤ በአንቺ ፡
ላይ፡ይመጣል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፵፬፤ዘጐየ፡እምገጸ፡ፍርሀት፤
ከፍርሀት፡የተነሣ፡የሸሸ፡ሰው፤

ይወድቅ፡ውስተ፡ጸድፍ፤
በገደል፡ይወድቃል፤

ወዘወጽአ፡እምጸድፍ፡ይእኅዞ፡መሥገርት፤
ከገደል ፡ ያመለጠውን ፡ ወጥመድ ፡
ይይዘዋል ፤ አንድም ፡ ዘጐየ ፤ ከቤት ፡
ጦር፡የተነሣ፡የሸሸ፡ይወድቅ፤በእዳሪ፡
ጦር ፡ ይጠፋል ፤ ወዘወጽአ ፡ ከእዳሪ ፡
ጦር ፡ ያመለጠውን ፡ የሜዳ ፡ ጦር ፡
ያጠፋዋል፤

እስመ፡ዘንተ፡አመጽእ፡ላዕለ፡ሞአብ፤
ይህንን፡በሞአብ፡ላይ፡አመጣለሁና፤

በዓመተ፡እዋኅዮሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ በመከራ ፡ በጐበኘ
ኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ አመ

www.ethiopianorthodox.org

፵፭፤ ውስተ ፡ ጽላሎተ ፡ ሐሴቦን ፡ ቆሙ ፡ እለ፡ጐዩ፡እምቀትል፤
ከሰልፍ ፡ ከጦር ፡ የሸሹ ፡ ሰዎች ፡ በሐሴቦን፡ጥላ፡ቆሙ፤

እስመ፡እሳት፡ወጽአት፡እምሐሴቦን፤
ጦር፡ከሐሴቦን፡ወጥታለችና፤

ወነድ፡እምአህጉረ፡ሴዎን፤
ከሴዎንም ፡ አውራጃ ፡ ጦር ፡ ወጥታ ለችና፤

ወበልአት፡ገጸ፡ሞአብ፤
የሞአብን፡አውራጃ፡አጥፍታለችና፤

ወርእሰ፡ደቂቀ፡ሳዖን፤
የሳኦን፡ልጆች፡ንጉሥንም፡አጥፍታ ለችና፤

፵፮፤ አሌ፡ለኪ፡ሞአብ፤
ሞአብ፡ወዮልሽ፤

እስመ፡ተሐጕለ፡ኮሞስ፤
ጣዖቱ፡ጠፍቷልና፤

ወሕዝቡ፤
ወገኖቹም፡ጠፍተዋልና፤

እስመ፡ተንሥኡ፡ደቂቅኪ፡በተፄውዎ፤
ወንዶች ፡ ልጆችሽ ፡ በምርኮ ፡ ተማርከው፡ሒደዋልና፤

ወአዋልድኪ፡ተፄወዋ፤
ሴቶች፡ልጆችሽ፡ተማርከዋልና፤

፵፯፤ ወእመይጥ ፡ ፄዋ ፡ ሞአብ ፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤
በኋላ፡ዘመን፡የሞአብን፡ምርኮ፡እመ ልሳለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስከ፡ዝየ፡ኰነኔ፡ሞአብ፤
የሞአብ ፡ ጥፋት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ አለ፤ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚያ መጣው ፡ የአሞንን ፡ ነውና፤ አንድም ፡
የሞአብ ፡ ጥፋት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ አለ ፤ እንዲህ ፡ እስከመሆን ፡ ድረስ፡ደርሳ፡ነው፤

## ምዕራፍ ፡ ፵፱ ፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ነገር፡በእንተ፡ደቂቀ፡አሞን፤
የአሞን ፡ ልጆች ፡ እንዲጠፉ ፡ የተና ገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

አልቦኑ፡ደቂቅ፡በውስተ፡እስራኤል፤
በእስራኤል፡ልጅ፡የለምን?

ወአልቦኑ ፡ ዘይወርስ ፡ እምኔሆሙ፡ ከመ ፡ ይረሶ፡ሞሎክ፡ለጋድ፤
ሞሎክ፡እስራኤልን፡እንዲወርሰው፡ ከእስራኤል ፡ የሚወርስ ፡ ልጅ ፡ የለምን፤

ወሕዝቡ፡ውስተ፡አህጉሪሁ፡ይንበር፤
ወገኑስ ፡ በሀገሩ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ የሚወርስ፡ልጅ፡የለምን፤

፪፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፤ መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እነሆ ፡ እንዲህ ፡ ያለ፡ ወራት፡ይመጣል፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወአሰምዕ፡ሐከከ፤
ፀብዕ፡ክርክርን፡አሰማለሁ፤

ወውውዓ፡ቀትል፡ላዕለ፡አራቦት፡ዘደቂቀ፡ አሞን፤
የአሞን ፡ ልጆች ፡ ሀገር ፡ በምትሆን፡ በአራቦት፡ላይም፡ሠልፍ፡የሚደረግ በትን፡ድንፋታ፡አሰማለሁ፤

ወይከውኑ፡ለኀጕል፤
ለጥፋት፡ይሆናሉ፤



ወአዋልዲሃ፡ይውዕያ፡በእሳት፤
ወአድዋሊሃም፡ይላል፤ጥቃቅኑ፡አው ራጃዎቿ፡በእሳት፡ይቃጠላሉ፤

ወይወርሶ፡እስራኤል፡ለወራሲሁ፡ይቤ፡እግ ዚአብሔር፤
እስራኤል ፡ ወራሹን ፡ ይወርሰዋል ፡ አለ፡እግዚአብሔር፤

፫፤አውይዊ፡ሐሴቦን፤
ሐሴቦን፡አልቅሺ፤

እስመ፡ኀለፈት፤
ተድላሽ፡ደስታሽ፡ጠፍታለችና፤

ወአውይዋ፡አዋልደ፡አራቦት፤
የአራቦት፡ልጆች፡አልቅሱ፤

ወቅንቱ፡ሠቀ፤
ምንጣፍ፡ማቅ፡ታጠቁ፤

ወብከዩ፡ወአስቆቅዉ፤
ፈጽማችሁ፡አልቅሱ፤

እስመ፡ይሰድድዎ፡ለሞሎክ፡ንጉሥ፤
ንጉሡን፡ሞሎክን፡ማርከው፡ይወስዱ ታልና፤

ወለመላእክቲሁ፡ኅቡረ፤
አለቆቹንም ፡ አንድነት ፡ ማርከው ፡ ይወስዱዋቸዋልና፤

፬፤ምንተ፡ትትኃሠዪ፤
ለምን፡ደስ፡ይልሻል፤

ጠፍዓ፡ቈላትኪ፡ወለት፡ዕሉት፤
ወንጀለኛ ፡ ልጅ ፡ ቈላዎችሽ ፡ ጠፍተ ዋልና፡አልቅሺ፡እንጂ፡ለምን፡ደስ፡ ይልሻል፤

እንተ፡ትትአመን፡በመዛግብቲሃ፤
በድልቦቿ፡የምትታመን፡ወንጀለኛ፤

ወትብል፡አልቦ፡ዘይበውዕ፡ኀቤየ፤
ወደ፡እኔ፡የሚገባ፡የለም፡የምትዪ፡ ለምን፡ደስ፡ይልሻል፤

፭፤ ናሁ፡አነ፡አመጽእ፡ድንጋፄ፡ላዕሌኪ፡ ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባኦት፤
እነሆ፡አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እኔ፡ በአንቺ፡ላይ፡ድንጋፄን፡አመጣለሁ፡ አለ፤

እምኵሉ ፡ ዓውድኪ ፡ ተዘርወ ፡ ብእሲ ፡ ቅድመ፡ገጹ፤
ከዓደባባይሽ፡ሰው፡ጠፋ፤

ወአልቦ፡ዘያስተጋብእ፡ለዘሖረ፤
ሸሽቶ ፡ የሔደውን ፡ የሚመልሰው ፡ የለም፤

፮፤ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡እመይጥ፡ፄዋ፡ ደቂቀ፡አሞን፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአሞንን ፡ ልጆች ፡ ምርኮ፡ እመልሳለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአ ብሔር፤

፯፤ ነገር፡ዘበእንተ፡ኤዶምያስ፤
ኤዶምያስ፡እንድትጠፋ፡የተናገረው፡ ነገር፡ይህ፡ነው፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባኦት፤
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

አልቦ፡እንከ፡ጠቢብ፡ውስተ፡ቴማን፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በቴማን ፡ ብልህ ፡ ሰው፡የለም፤

ወተኃጥአት፡ምክር፡እምደቂቃ፤
ከልጆቿ፡ምክር፡ጠፋች፤

ወጠፍአ፡ጥበቦሙ፤
የጦር፡ጥበብ፡ጠፋባቸው፤

፰፤ ወኬድዎ፡ለብሔሮሙ፤
አገራቸውን ፡ እነናቡከደነፆር ፡ መገሳ ገሻ፡አደረጉት፤

ጕዩ፡ወተመየጡ፤
ሸሽታችሁ፡ተመለሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአዕምቁ፡ለነቢር፡እለ፡ትነብሩ፡ዴዳን፤
በዴዳን ፡ የምትኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡
ለመኖር ፡ ክክር ፡ ቆፍሩ ፡ (ምሽግ ፡
ቆፍሩ)፡አምባውን፡ሥሩ፤

እስመ ፡ ዕፁበ ፡ ግብረ ፡ አምጻእኩ ፡ ላዕሌሁ ፡
በዕለተ፡ዕዋሀዩ፤
በመከራ፡በምጐበኝበት፡ቀን፡ጭንቅ፡
ሥራ፡አመጣበታለሁና፤

፱፤እመ፡መጽኡ፡እለ፡ይቀሥሙ፤
ወይኑን ፡ የሚለቅሙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡
አንተ፡ቢመጡ፤

እምኢያትረፉኑ፡ለከ፡ተቅራመ፤
የሚበቃቸውን ፡ ያህል ፡ ወስደው ፡
ጥቂት፡ባላስቀሩልህ፡ነበር፤

ወእመኒ፡ሰረቅት፡ቦኡ፡በሌሊት፡እምኢያጥ
ፍኡኑ፡ዘየአክሎሙ፡ነሢአሙ፤
ሌቦች ፡ በሌሊት ፡ ቢገቡ ፡ የሚበቃ
ቸውን ፡ ያህል ፡ ወስደው ፡ ባላስቀሩ
ልህም፡ነበር፤

፲፤ እስመ ፡ አነ ፡ ከሠትክዎ ፡ ለኤሳው ፡
ወከሠትኩ፡ኅቡዓቲሁ፤
እኔ ፡ የኤሳውን ፡ በማጀት ፡ የተቀበ
ረውን፡በቆጥ፡የተሰቀለውን፡ገልጬ
በታለሁና ፡ እንዴት ? ለጥፋት ሆነ ?
ይሉታል፤

ወኢይክል፡እንከ፡ተኀብአ፡ግሙራ፤
እንግዲህ፡ወዲህ፡ፈጽሞ፡መሠወር፡
አይቻለውም፤

ተቀጥቀጠ፡እዴሁ፤
ሥልጣኑ፡ጠፋ፤

ወኢሀለዉ፡እኅዊሁ፡ወጎሩ፤
ሞአብ፡አሞን፡አልነበሩም፤

፲፩፤ ወአልቦ ፡ ተረፍ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታኒ ፡
በዘየሐዩ፤

በሚድን፡ገንዘብ፡ልጅህ፡ልጅ፡አይወ
ልድም፤

ወአንሰ፡አሐዩ፤
እኔ፡ግን፡እስራኤልን፡አድናለሁ፤

ወመበለታቲከ ፡ ላዕሌየ ፡ ይትዌከላ ፡ ወይሴ
ፈዋኒ፡ዕቤራቲከ፤
አንተን ፡ ተጠግተው ፡ የሚኖሩ ፡
ዕቤራት፡ዕጓለ፡ማውታ፡እስራኤል፡
በእኔ፡ያምናሉ፤

፲፪፤እስመ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ናሁ፡ዘኢኮነ፡ኵነኔ፡ለሰትየ፡ጽዋዕ፡ሰትየ፡
ይሰትዩ፤
መከራ፡ለመቀበል፡ሊፈረድባቸው፡
የማይገቡ ፡ እስራኤል ፡ የተፈረደ
ባቸው፤

ወአንተኑ፡ነጺሐ፡ትነጽሕ፡ወኢትነጽሕ፡
እንከ፤
መከራውን ፡ ሳትቀምስ ፡ ከኃጢአት፡
ትነጻለህ?አትነጻም፤ድኅነኑ፡ትድኅን፡
ቢል ፡ መከራውን ፡ ሳትቀምስ ፡ ትድ
ናለህ?አትድንም፤

እስመ፡ሰትየ፡ትሰቲ፤
መከራ፡ትቀበላለህና፤

፲፫፤እስመ፡በርእስየ፡መሐልኩ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ሕያው፡አነ፡አማንየ፡
በርእስየ፡ብዬ፡ምያለሁ፡ብሏልና፤

ከመ፡ትከውን፡ዓፀ፤
ኤዶምያስ፡ምድረ፡በዳ፡እንድትሆን፤

ወለፅዕለት፤
ለስድብ፤



ወለመርገም፡ትከውን፡ባሶር፤
ኤዶምያስ ፡ ለመርገም ፡ እንድትሆን ፡
ማልኩ፡ብሏልና፤

ወኵሉ ፡ አህጉሪሃ ፡ ይከውና ፡ መዝበረ ፡
ለዓለም፤
አገሮቿ፡ሁሉ፡ለዘለዓለሙ፡የተፈቱ፡
ይሆናሉ፡እንዲሆኑ፡ብትልም፤

፲፬፤ ሰሚዓ ፡ ሰማዕኩ ፡ በኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
ከአቸናፊ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ሰማሁ፤

ከመ፡ፈነወ፡ሐዋርያተ፡ውስተ፡በሐውርተ፡
አሕዛብ፤
ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሀገሮች ፡ መልእክተ
ኞችን፡እንደ፡ላከ፡ሰማሁ፡አነቃቅቶ፡
ማምጣቱን፡ሲያይ፡ፈነወ፡አለ፤

ይትጋብኡ፡ወይመጽኡ፡ላዕሌሃ፤
በእርሷ፡ላይ፡ተሰብስበው፡ይመጣሉ፤

ወይትነሥኡ፡ወይትቃተልዋ፤
በጠላትነት፡ተነሥተው፡ይወጓታል፤

፲፭፤ ኅዳጠ፡ረሰይኩከ፡ውስተ፡አሕዛብ፡
ከመ፡ይመንኑከ፤
ይንቁሕ ፡ ዘንድ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡
ጥቂት፡አደረግሁህ፤

ወያስተአክዩከ፡ሰብአ፡ተውኔትከ፤
ማርከህ ፡ ወስደህ ፡ ትዘብትባቸው
የነበሩ፡አሕዛብ፡ያክፉፉሃል፤

፲፮፤ ወያስተናሥአከ ፡ ትዕቢተ ፡ ልብከ ፡
ወትዕቢተ፡ልብከ፡አስተናሥአከ፤
የልቡናህ ፡ ትዕቢት ፡ ለምርኮ ፡
አነሳሣህ፤ አንድም ፡ ወያስተአክዩከ ፡
ያክፉፉሃል ፡ ተውኔትከ ፡ ወትዕቢተ ፡
ልብከ፤በሰው፡መዘበትህ፡የልቡናህ፡
ትዕቢት፡አነሳሥተው፡አስማረኩህ፤

ዘየኀድር፡መልዕልተ፡ኰኵሕ፤

በዋሻ፡የሚኖር፡ጥንብ፡አሞራ፡ነህ፤

ወይእኀዝ፡መልዕልተ፡ወግር፡ልዑል፤
ከትልቅ ፡ ገደል ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡
ጥንብ፡አሞራ፡ነህ፤ያ፡ከላይ፡መርግ፡
ከታች፡ቀስት፡ነፍጥ፡እንዳያገኘው፡
በገደል፡መካከል፡ይኖራል፡አንተም፡
እንደዚያ፡ነህ፤

እስመ፡አስረርከ፡ከመ፡ንስር፡እጐሊከ፤
ልጆችህን ፡ እንደ ፡ ንሥር ፡ በአምባ ፡
ብታስጠጋ፡ብታወጣ፤

እምህየ፡አጸድፈከ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከዚያ ፡ አወርድሃለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአ
ብሔር፤

፲፯፤ወትከውን፡ኤዶምያስ፡ከመ፡አፅ፤
ኤዶምያስ፡ምድረ፡በዳ፡ትሆናለች፤

ኵሉ፡ዘየኃልፍ፡ህየ፡ይደነግፅ፤
በእርሷ ፡ የሚያልፍ ፡ ሁሉ ፡ ይደነ
ግጣል፤

ወይትፋጸይ፡በእንተ፡ኵሉ፡መቅሠፍታ፤
መከራ ፡ ስለ ፡ መጣባት ፡ ያፏጫል ፡
ብንጣራ ፡ ሰው ፡ ይሰማናል ፡ ብለው ፤
አንድም፡የፍርሃት፤

፲፰፤ከመ፡ተገፍትዓት፡ሰዶም፤
ሰዶም፡እንደጠፋች፤

ወገሞራ፤
ገሞራም፡እንደ፡ጠፋች፤

ወአድያሚሃ፤
አውራጃዎቿ፡ሁሉ፡እንደ፡ጠፉ፤

ይቤ፡እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፤
ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡
ትጠፋለች፡አለ፤

ወኢይነብር፡ህየ፡ሰብእ፡ወኢየኀድር፡ህየ፡
እጓለ፡እመሕያው፤
በዚያች፡ሰው፡አይኖርባትም፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፤ናሁ፡የዓርግ፡ከመ፡አንበሳ፡እምዕበየ፡ዮርዳኖስ፡ውስተ፡ብሔረ፡ኤታም፤
ከዮርዳኖስ ፡ በላይ ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ወደ ፡ ኤታም ፡ እነሆ ፡ ናቡከደነፆር ፡ እንደ ፡ አንበሳ፡በማስፈራት፡ይመጣል፤

እስመ፡ፍጡነ፡እሰድዶሙ፡እምኔሃ፤
ፈጥኜ ፡ ከእርሷ ፡ አስወጥቼ ፡ እሰዳቸዋለሁና፤

ወወራዙተ፡እሠይም፡ላዕሌሃ፤
በእርሷ ፡ ላይ ፡ ጐልማሶችን ፡ እሾማለሁና፤

መኑ፡ከማየ፤
እንደኔ፡ያለ፡ማነው?

ወመኑ፡ዘይትቃወመኒ፤
የሚከራከረኝ፡ማነው፤

ወመኑ፡ገዘ፡ኖላዊ፡ዘይቀውም፡ቅድመ፡ገጽየ፤
በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ አርበኛ ፡ ማነው ፡ ይላል ፤ ሰብአ ፡ ኤዶምያስ ፤ አንድም ፡ መኑ ፡ ከማየ ፤ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ፈጣሪ ፡ ማነው፡ይላል፡ጌታ፤

ወመኑ፡ዘይትቃወመኒ፤
የሚቀዋወመኝ፡ማነው፤

ወመኑ፡ገዘ፡ኖላዊ፤
በፊቴ ፡ በባለሟልነት ፡ የሚቆም ፡ ማነው፤

፳፤በእንተ፡ዝንቱ፡ስምዑ፡ምክረ፡እግዚአብሔር፡ዘመከረ፡ላዕለ፡ኤዶምያስ፤
የኤዶምያስ ፡ ሰው ፡ የሚከራከረኝ ፡ ማነው፡ስለ፡አለ፤የኤዶምያስ፡ሰዎች፡በኤዶምያስ፡ላይ፡የመከረውን፡የእግዚአብሔርን፡ምክር፡ስሙ፤

ወሕሊናሁ ፡ ዘሐለየ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ቴማን፤
በቴማን ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያሰበውን፡ሐሳቡን፡ስሙ፤

እመ፡ኢሐብለይዎሙ፡ለትሑታን፡አባግዕ፤
ትሑታን ፡ እስራኤልን ፡ ባይዘበዝቧቸው፡(ባይበዘብዟቸው)፤

ወኢረሰይዎ፡ዓፀ፡ለማኅደሮሙ፡ዘውስቴታ፡ይነብሩ፤
በውስጧ፡የሚኖሩባት፡አገራቸውን፡ምድረ፡በዳ፡ባያደርጓት፤

፳፩፤ እምኢደንገጸት ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ድምፀ፡ድቀቶሙ፤
ምድር ፡ ባልደነገጠችም ፡ ነበር ፤ ከግፋቸው፡ድምፅ፡የተነሣ፡ባልደነገጠችም፡ነበር፤

ከመ፡ድምፀ፡ባሕር፡ናሁ፡ተሰምዓ፡ቃላ፤
እነሆ ፡ እንደ ፡ መጣያ ፡ ውሀ ፡ ቃሏ፡ተሰማ፤

፳፪፤ወናሁ፡ከመ፡ንሥር፡ይሠርር፡፤
እነሆ ፡ ናቡከደፆር ፡ እንደ ፡ ንሥር፡ፈጥኖ፡ይመጣል፤

ወይኔጽር፡ወይሰፍሕ፡ክነፊሁ፡ላዕለ፡ባሦር፤
ንሥር ፡ የሚበላውን ፡ ተመልክቶ፡ክንፉን፡በሥጋው፡ላይ፡እንዲዘረጋ፡ናቡከደነፆር ፡ ሠራዊቱን ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ፡ይሰዳል፤

ወይከውን ፡ ልቦሙ ፡ ለጽኑዓነ ፡ ኤዶምያስ፡በይእቲ፡ዕለት፡ከመ፡ልበ፡ብእሲት፡እንተ፡ውስተ፡ማሕምም፤
በዚች፡ቀን፡የኤዶምያስ፡አርበኞች፡ልቡና፡በምጥ፡እንደ፡ተያዘች፡ሴት፡ልቡና፡ይሆናል፤

፳፫፤ነገር፡በእንተ፡ደማስቆ፤
ደማስቆ፡እንድትጠፋ፡አይቶ፡የተናገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ተነፍረ፡ኤማት፡ወአርፋድ፤
ኤማትና ፡ አርፋድ ፡ መከሩ ፡ መጥቶባቸው፡አፈሩ፤



እስመ፡እኩየ፡ነገረ፡ሰምዓ፡ወደንገፃ፤
ክፉ፡ነገር፡ሰምተው፡ደንግጠዋልና፤

ወከመ፡ባሕር፡ተምዕዓ፤
እንደ፡ባሕር፡ተበሣጭተዋልና፤

ወኢይክሉ፡እንከ፡አዕርፎ፤
እንግዲህ፡ወዲህ፡ከመከራው፡ማረፍ፡አይቻላቸውምና ፡ ተነፍረ ፡ ብለህ ፡ እሠር፤

፳፬፤ወተመስወት፡ደማስቆ፤
ደማስቆ፡እንደ፡ሰም፡ቀለጠች፤

ወመምዓት፡ወጕየት፤
ተሸብራ፡ሸሸች፤

ወአኀዛ ፡ ረዓድ ፡ ወማሕምም ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ትወልድ፤
እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ እንቅጥቅጥ ፡ ምጥ፡ያዛት፤

፳፭፤እፎ፡ኢሀደጉ፡ሀገረ፡ላቲ፤
የኤዶምያስ፡ሰዎች፡ሊኖሩባት፡የወደዱዋት ፡ ሀገርን ፤ አንድም ፡ እነናቡከደነፆር ፡ ሊወጓት ፡ የወደዷት ፡ ሀገርን ፡ እንዴት፡አልተዉላት፤

ወዐፀደ፡ዘአፍቀሩ፤
ሀገረና ፡ ዓፀድ ፡ ዘአፍቀሩ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ ነው ፤ የወደድዋት ፡ ሀገርን ፡ እንዴት፡አልተዉላት?

፳፮፤በእንተ፡ዝንቱ፡ይወድቁ፡ወራዙቲሃ፡ውስተ፡መርህባ፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጐልማሶቿ ፡ በዓደባባይዋ፡ይጠፋሉ፤

ወይወድቁ፡ዕደውኒ፡መስተቃትላን፡ውእተ፡አሚረ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
አርበኞች ፡ ሰዎችም ፡ ያንጊዜ ፡ ይጠፋሉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፯፤ወአነድድ፡እሳተ፡ውስተ፡አረፋቲሃ፡ለደማስቆ፤
በደማስቆ ፡ ቅጽር ፡ እሳት ፡ አነዳለሁ ፡ ማለት፡በኃያላኑ፡ጦር፡አመጣለሁ፤

ወትበልዕ፡አብያተ፡ወልደ፡አዴር፤
የወልደ፡አዴርን፡ወገን፡ታጠፋለች፤

፳፰፤ነገር፡ዘበእንተ፡ቄዳር፤
የእስማኤል፡ልጆች፡እንዲጠፉ፡የተናገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ወለነገሥተ፡አዕፃዳት፡እለ፡ቀተለ፡ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የወጋቸው፡ነገሥታቱም፡እንደጠፉ፡የተናገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ተንሥኡ፡ወዕርጉ፡ውስተ፡ቄዳር፤
ተነሥታችሁ ፡ ወደ ፡ እስማኤል ፡ ልጆች፡ዝመቱ፤

ወአጥፍዕዎሙ፡ለደቂቀ፡ቄዴም፤
ለደቂቀ ፡ ጽባሕ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የምሥራቅ ፡ ልጆችን ፡ አጥፏቸው ፤ አንድም ፡ ደቂቀ ፡ ቀደምት ፡ ይላል ፤ የቀደሙ፡ልጆችን፡አጥፏቸው፤

፳፱፤ተዓይኒሆሙ፤
ሠራዊታቸውን፤

አባግዒሆሙኒ፡ይንሥኡ፤
በጎቻቸውንም፡ማርከው፡ይውሰዱ፤

ወመራዕይሆሙ፤
መንጋቸውን፤

ወኵሎ፡ንዋዮሙ፤
ገንዘባቸውን፡ሁሉ፤

ወአግማሊሆሙኒ፡ይንሥኡ፡ለርእሶሙ፤
ግመሎቻቸውን፡ለራሳቸው፡ይውሰዱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወጸውዑ፡ፈላሴእምአድያም፤
ከዳርቻ፡መጻተኛውን፡ጥሩ፤

፴፡ጉዩ፤
ሽሹ፤

ወተሐወኩ፡ጥቀ፤
እጅግ፡ተዋወኩ፤

አዕምቁ ፡ ለነቢር ፡ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ውስተ ፡
አዕፃዳት፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
በአምባዎች ፡ የምትኖሩ ፡ ሰዎች ፡
በዚያ፡ ለመኖር ፡ አምባውን ፡ ጥልቅ ፡
አድርጉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

እስመ ፡ መከረ ፡ ላዕሌክሙ ናቡከደነፆር ፡
ንጉሥ፡ዘባቢሎን፡ምክረ፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
በእናንተ፡ላይ፡ምክርን፡መከሯልና፤

ወሐለየ፡ሕሊና፡እኩየ፤
ክፉ፡ሐሳብንም፡አስቧልና፡በአምባ፡
ለመኖር፡አምባውን፡ጥልቅ፡አድርጉ፤

፴፩፤ ተንሥኡ ፡ ወዕርጉ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብ ፡
ዘሠናየ ፡ ይቀውም ፡ ወዕሩፈ ፡ ይነብር ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ጠላት፡ጠፍቶላቸው፡
ተዘልለው፡በበጎ፡አኗኗር፡ወደሚኖሩ፡
ወገኖች፡ተነሥታችሁ፡ዝመቱ፡አለ፤

እለ፡አልቦሙ፡ማዕፆ፤
ሳንቃ፤

ወኢመንሠግ፤
ቁልፍ፤

ወኢመዝግሀ፤
መዝጊያ ፡ ወደሌላቸው ፡ ወገኖች
ዝመቱ፤

አላ፡ባሕቲቶሙ፡ይነብሩ፤
ጠላት ፡ ጠፍቶላቸው ፡ ብቻቸውን ፡
ይኖራሉ፡እንጂ፤

፴፪፤ወይከውኑ፡አግማሊሆሙ፡ለምህርካ፤
ግመሎቻቸው፡ለምርኮ፡ይሆናሉ፤

ወእንስሳሆሙ፡ለፄዋዌ፤
ከብቶቻቸውም፡ለምርኮ፡ይሆናሉ፤

ወየሐፍሶሙ፡ኵሉ፡ነፋስ፡ለቅሩፃነ፡ገጽ፤
እንደ፡ጉንጋ፡እንደናሪያ፡ፊታቸውን፡
የከተቡ ፡ ሰዎችን ፡ ነፋስ ፡ ይወስዳ
ቸዋል ፡ ማለት ፡ ናቡከደነፆር ፡ ማርኮ ፡
ይወስዳቸዋል፤

ወአመጽእ፡ሐጕሎሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ጥፋታቸውን፡አመጣለሁ፡አለ፡እግዚ
አብሔር፤

፴፫፤ ወይከውን፡አዕፃዳቲሆሙ፡ማኅደረ፡
ለአዕዋፍ፤
ቦታቸው ፡ ለአዕዋፍ ፡ ማደሪያን ፡
ይሆናል፤

ወአፀ፡ዘለዓለመ፡ዓለም፤
ለዘለዓለሙ፡በረሃ፡ይሆናል፤

ወኢይነብር፡ሀየ፡ሰብእ፡ወኢየሐድር፡ሀየ፡
ዕጓለ፡ዕመሕያው፤
በዚያ፡ሰው፡ፈጽሞ፡አይኖርበትም፤

፴፬፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ኀበ ፡
ኤርምያስ፡ነቢይ፤
ፋርስ ፡ እንድትጠፋ ፡ ወደነቢዩ ፡
ኤርምያስ፡የመጣ፡የተነገረ፡የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤

በእንተ፡ዔላም፤
ዔላም ፡ ያላት ፡ ፋርስ ፡ ናት ፤ አንድም፤
በፋርስ ፡ በሜዶን ፡ መካከል ፡ ያለች ፡
ሀገር፡ናት፤

በቀዳሚ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሴዴቅያስ፡
ንጉሠ፡ይሁዳ፤
የይሁዳው ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡
በነገሠ፡ በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡
ኤላም፡እንድትጠፋ፡የተነገረ፡የእግዚ
አብሔር፡ቃል፡ይህ፡ነው፤



፴፭፤ ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ፀባኦት፤
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እሰብር፡ቀስተ፡ኤላም፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ የፋርስን ፡ ቀስት ፡ እሰብ
ራለሁ ፡ ማለት ፡ የፋርስን ፡ ሥልጣን ፡
አጠፋለሁ፤ ቀስተ ፡ ኤላም፡ ባለው ፡
አውኀዝ ፡ ይላል፤ ቀስተ ፡ ዔላም ፡
ማለት፡ነው፤

ቀዳሚተ፡ኃይሎሙ፤
የሠራዊታቸው ፡ መዲና ፡ የምትሆን ፡
የፋርስን፡ሥልጣን፡አጠፋለሁ፤

፴፮፤ ወአመጽእ ፡ ላዕለ ፡ ኤላም ፡
አርባዕተ፡ ነፋሳተ ፡ እምአርባዕቱ ፡ አጽናፈ ፡
ሰማይ፤
በኤላም ፡ ላይ ፡ ከአራቱ ፡ መዓዝን ፡
አራቱን፡ቤተ፡አሕዛብ፡አመጣለሁ፤

ወእዘርዎሙ፡ውስተ፡ኵሉ፡ነፋሳት፤
በአራቱ፡ቤተ፡አሕዛብ፡ሁሉ፡እበትና
ቸዋለሁ፤

ወአልቦ፡ሕዝብ፡ዘኢይመጽእ፡ሀየ፤
ወደዚያ፡የማይመጣ፡ወገን፡የለም፤

ወይወሰድዎሙ፡ለኤላም፤
የፋርስን ፡ ሰዎች ፡ ማርከው ፡ ይወስዱ
ቸዋል፤

፴፯፤ ወአደነግፆሙ ፡ ለኤላም ፡ በቅ
ድመ፡ኵሉ፡ፀሮሙ፤
የኤላምን ፡ ሰዎች ፡ በጠላቶቻቸው ፡
ፊት፡አስደነግጣቸዋለሁ፤

ወበቅድመ፡እለ፡የኃሥሥዋ፡ለነፍሶሙ፤
ሰውነታቸውን ፡ ለጥፋት፡ በሚፈ
ልጓት ፡ ሰዎችም ፡ ፊት ፡ አስደነግጣቸ
ዋለሁ፤

ወአመጽእ ፡ መቅሠፍትየ ፡ ወመዓትየ ፡
ላዕሌሆሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ መዓቴን ፡ መቅሠ
ፍቴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አመጣለሁ ፡
አለ፤

ወአመጽእ ፡ መጥባሕተ ፡ ዲቤሆሙ ፡ እስከ ፡
አኀልቆሙ፤
እስካጠፋቸው፡ድረስ፡በእነርሱ፡ላይ፡
ሾተልን፡ሰይፍን፡አመጣባቸዋለሁ፤

፴፰፤ ወአነብር ፡ መንበርየ ፡ ውስተ ፡
ኤላም፤
በፋርስ፡ዙፋኔን፡እዘረጋለሁ፤

ወአጠፍዕ ፡ እምህየ ፡ ነገሥተ ፡ ወመሳፍንተ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ከዚያ ፡ ነገሥታቱን፤ መሳፍንቱን ፡
አጠፋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፴፱፤ ወይከውን፡በድኃሪ፡መዋዕል፤
በኋላ፡ዘመን፡እንዲህ፡ይሆናል፤

እመይጥ፡ፄዋ፡ኤላም፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡የፋርስን፡ምርኮ፡እመ
ልሳለሁ፡አለ።

## ምዕራፍ ፡ ፶ ፤

፩፤ ቃለ፡እግዚአብሔር፡ዘነበበ፡ላዕለ፡
ባቢሎን፡ኀበ፡ምድረ፡ከላውዴዎን፡በእደ፡
ኤርምያስ፡ነቢይ፤
በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ቃል ፡ በከላው
ዴዎን ፡ አውራጃ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡
የተነገረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህ፡
ነው፤

፪፤ ንግርዎሙ፡ለአሕዛብ፤
ይህንን፡ነገር፡ለአሕዛብ፡ንገሯቸው፤

ወአስምዕዎሙ፤
አዳኙባቸው፤

ወአንሥኡ፡ትእምርተ፤
አላማውን፡አንሡ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢትክብቱ፡
አላማውን፡አትሠውሩ፤
ወበሉ፡ተሠግረት፡ባቢሎን፡
ባቢሎን፡ጠፋች፡በሉ፤
ወተኀፍረ፡ቤል፡
ጣዖቱ፡አፈረ፤
ወፈርሃት፡መሮድህ፤
መሮድህ ፡ በባቢሎን ፡ ፈራች ፤ አንድም፡ መሮድህን ፡ ይ፱ ፡ ሁሉን ፡ የምትፈጭ ፡ የምታጠፋ ፡ ባቢሎን ፈራች፤
ወተሃፍሩ፡ጣዖታቲሃ፡
ይሰግዱላቸው፡የነበሩ፡ጣዖታት፡አላ ድናቸው፡ብለው፡አፈሩ፤
ወደንገፁ፡አማልክቲሃ፡
ካህናቷ፡ደነገጡ፤

፫፤ እስመ፡ዓርጉ፡ላዕሌሃ፡ሕዝብ፡ዘእም ሰሜን፡
ከፋርስ፡የመጡ፡ቂሮስ፡ዳርዮስ፡ዘም ተውባታልና፤
ውእቱ፡ዘይሬስያ፡ለምድር፡ሙስንተ፡
ይህ፡ወገን፡ባቢሎንን፡የጠፋች፡የሚ ያደርጋት፡ነው፤
ወአልቦ፡ዘይተርፍ፡ውስቴታ፡
በውስጧ፡የሚቀር፡የለም፤
ኢሰብእ፡ወኢእንስሳ፡
ሰውም፡ከብቱም፡የሚቀር፡የለም፤
ተሐውኩ፡ወሖሩ፡ውእተ፡አሚረ፡
ያን፡ጊዜ፡ተሸብረው፡ሔዱ፤

፬፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚ አብሔር፡
በዚያ ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ፡አለ፤
ይመጽኡ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል፡ እሙንቱ ፡ ወደቂቀ፡ይሁዳ፡ኅቡረ፡
የእሥሩ ፡ ነገድ ፤ የሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ልጆች፡አንድነት፡ይመጣሉ፡አለ፤
የሐውሩ፡እንዘ፡ይበክዩ፡ኅቡረ፡
አንድነት ፡ እያለቀሱ ፡ ተማርከው ፡ ይሔዳሉ፤
የኀሥሥዎ፡ለእግዚአብሔር፡አምላኮሙ፡
ፈጣሪያቸው፡እግዚአብሔርን፡በሕግ፡ በአምልኮት፡ይሹታል፤

፭፤ ወጽዮንሃ፡የሐትቱ፡ፍኖቶ፡
ወጽዮንሃ ፡ ፍኖቶ ፡ የሐትቱ ፡ ሲል ፡ ነው፤ ሕግጋቱ ፡ የተጻፉባት ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን፡ይመረምራሉ፤
ወገጸሙ፡ለፌ፡ይመይጡ፡
ፊታቸውን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ይመልሳሉ፤
ወይመጽኡ ፡ ወይትመሐፀኑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ ብሔር፡አምላኮሙ፡
መጥተው ፡ በፈጣሪያቸው ፡ በእግዚአ ብሔር፡ያምናሉ(ይማፀናሉ)፤
እስመ፡ኪዳን፡ዘለዓለም፡ኢይትረሣዕ፡
ለዘለዓለም ፡ የማይዘነጋ ፡ መሐላ ፡ ነውና፤

፮፤ አባግዐ፡ግዱፋነ፡ኮኑ፡ሕዝብየ፡
ወገኖቼ ፡ እስራኤል ፡ በመከራ ፡ የተጣሉ፡ሆኑ፤
ኖሎቶሙ፡አንኀገውዎሙ፡ውስተ፡አድባር፡
ነገሥታቱ፡አንሠራ፡አንቀጣ፡ብለው፡ ካህናቱ ፡ አንመክር ፡ አናስተምር ፡ ብለው፡በተራራ፡አስማረኳቸው፤
ወገደፍዎሙ፡
በመከራ፡ጣሏቸው፤
ወአንኀገዉ፡እምደብር፡ውስተ፡ወግር፡ሖሩ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ ወደባቢሎን ፡ ከባቢ ሎን፡ወ[illegible]



ወረስዑ፡ማኅደሮሙ፡
ማደሪያቸውን፡ዘነጉ፤

፯፤ ኵሉ፡ዘረከበ፡ያሐልቆሙ፡
ያገኘ፡ሁሉ፡ይማርካቸዋል፤
ወይቤሉ፡ፀሮሙ፡ኢነአርፎሙ፡
ጠላቶቻቸው ፡ ከመከራ ፡ አናሳርፋ ቸውም፡አሉ፤
እስመ ፡ አበሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምዕራፈ ፡ ጽድቅ፡
የሃይማኖት፡መገኛ፡እግዚአብሔርን፡ ከደዋልና፤
ወትውክልተ፡አበዊሆሙ፡
አባቶቻቸው ፡ የሚታመኑበት ፡ እግዚ አብሔርን፡ከደዋልና፤
ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

፰፤ ጻኡ፡እማዕከለ፡ባቢሎን፡
ከባቢሎን፡መካከል፡ውጡ፤
ወእምድረ፡ፋርስ፡
ከፋርስም፡አውራጃ፡ውጡ፡አለ፤
ይመጽኡ ፡ ወይከውኑ ፡ ከመ ፡ አክይስት ፡ በቅድመ፡ገጸ፡አባግዕ፡
መጥተው ፡ በፍየሎች ፡ ፊት ፡ እንዳሉ ፡ እባቦች ፡ ይሆናሉ ፡ አለ ፤ አሕዛብ ፡ ይጠፋሉ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ በቅድመ ፡ አክይስት ፤ በበጎች ፊት ፡ እንዳሉ ፡ ፍየሎች ፡ ይሆናሉ ፡ አለ፤ እስራኤል ፡ በሚጠት ፡ አጥፊ ፡ ይሆናሉ፤

፱፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ አነሥእ ፡ ወዐዓርግ ፡ ላዕለ፡ባቢሎን፡ሠራዊተ፡አሕዛብ፡አበይተ፡ እምድረ፡ሰሜን፡
እነሆ ፡ ከፋርስ ፡ የመጡ ፡ ታላላቆች ፡ ብዙዎች ፡ ሠራዊትን ፡ አሥነስቼ ፡
[illegible]

ወይትቃተልዋ፡በህየ፡
በዚያ፡ይወጓታል፤
ወይእኀዝዎሙ ፡ ከመ ፡ ሐፀ ፡ መስተቃትላን፡ ነዳፊ፡ዘኢይሰወጥ፡ዕራቆ፡
ሳይወጋ ፡ ባዶውን ፡ እንደማይመለስ ፡ እንደ ፡ አርበኞች ፡ ፍላፃ ፡ አጥብቀው፡ ይይዟቸዋል፤

፲፤ ወይትበረበሩ፡ፋርስ፡
የፋርስ ፡ ሰዎች ፡ ይበዘብዛሉ ፤ ምነው ፡ የፋርስ ፡ ሰዎችማ ፡ አጥፊዎች ፡ አይደሉም ? ቢሉ ፡ ግብር ፡ አበር ፡ የሆኑት ፡ አብረው ፡ ጠፍተዋልና ፤ አንድም ፡ ኋላ ፡ በደበያት ፡ ጠፍተ ዋልና፤
ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ማህረኩኪ ፡ ይጸግቡ ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
አንቺን ፡ የማረኩሽ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብሽን ፡ ይጠግባሉ ፡ አለ ፡ እግዚአ ብሔር፤

፲፩፤ እስመ፡ተፈሣሕኪ፡
ደስ፡ብሎሻልና፤
ወተቈናደይኪ፡
እንደ፡ተልባ፡ተፈናጥረሻልና፤
እስመ፡ሄወውኪዮሙ፡ለርስትየ፡
ማደሪያዎቼ ፡ እስራኤልን ፡ ስለማረክ ሻቸው፤
እስመ ፡ ፈሐልኪ ፡ ከመ ፡ ዕጐልት ፡ በኀበ ፡ ምቅማሕ፡
ጊደር ፡ አበቅ ፡ በምትቅምበት ፡ ቦታ፡ እንድትቀናጣ፡ተቀናጥተሻልና፤
ወወጋዕኪዮሙ፡ከመ፡አሥዋር፡
በሬዎች፡እንዲዋጉ፡ወግተሻቸዋልና፡ ይጸግቡ፡ብለህ፡እሠር፤

፲፪፤ ተኀፍረት፡እምከሙ፡ጥቀ፡ወተኀ ፍረት፡ወላዲትክሙ፡

www.ethiopianorthodox.org

እምክሙ ፡ ወላዲትክሙ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ ይረዳኛል ፡ ብላ ፡ ተስፋ ፡ ያደረ ገችው፡ልጇ፡ተማርኮባት፡እናታችሁ፡ በመከራው ፡ አፈረች ፤ ይረዳኛል ፡ የምትለው፡ወንድ፡ልጇ፡ተማርኮባት፡ ብትልም፤

ናሁ፡ኀሪተ፡አሕዛብ፡ማሰንት፡
እነሆ ፡ ከአሕዛብ ፡ የተመረጠች ፡ ባቢሎን ፡ ጠፋች ፤ አንድም ፡ አሕዛብ፡ ከጠፉ፡በኋላ፡ጠፋች፤

ወበድወት፡
ምድረ፡በዳ፡ሆነች፤

ወተመዝበረት፡እመዓተ፡እግዚአብሔር፡
ከመዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተነሣ ፡ ጠፋች፡(ተፈታች)ብትልም፤

፲፫፤ ወኢትሄሉ፡እንከ፡
እንግዲህ፡ወዲህ፡አትኖርም፤

ወትጠፍዕ፡ኵለንታሃ፡
ሁለንተናዋ፡ትጠፋለች፤

ወኵሉ፡ዘየኀልፍ፡እንተ፡ባቢሎን፡ይቴክዝ፡
ወደ፡ባቢሎን፡የሚሔድ፡ሰው፡ሁሉ፡ ያዝናል፤

ወይትፋፀይ፡በእንተ፡ኵሉ፡መቅሠፍታ፡
መቅሠፍት፡ስለ፡መጣባት፡ያፏጫል፤ ብጣራ ፡ ሰው ፡ ይሰማኛል ፡ ብሎ ፤ አንድም፡ፈርቶ፤

፲፬፤ ተቃተልዋ፡ለባቢሎን፡
ባቢሎንን፡ውጓት፤

ወዕግትዋ፡ኵልክሙ፡
ሁላችሁም፡ክበቧት፤

ወወስቁ፡ቀስተክሙ፡ላዕሌሃ፡
ቀስታችሁን ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ሳቡ ፡ ቀፍሩ፡ብትልም፤

ወንድፍዋ፡
ቀስታችሁን፡ስባችሁ፡ውጓት፤

ወኢትትሐከዩ፡ነዲፎታ፡
እርሷን፡መውጋት፡ቸል፡አትበሉ፤

እስመ፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፡አበሰት፡
እግዚአብሔርን፡በድላለችና፤

፲፭፤ ዕግትዋ፡እስመ፡ደከሙ፡እደዊሃ፡
እጆቿ፡ለመወርወር፤ቃሏ፡ለመምከር፡ ደክሟልና፡ክበቧት፤

ወወድቀ፡ጥቅማ፡
ግምቧ(ቅጥሯ)፡ወደቀ፤

ወንኀለ፡ዓረፋቲሃ፡
ቅጽሯ ፡ ፈረሰ ፤ አንድም ፡ ጥቅማ ፡ ንጉሥዋ ፡ ጠፋ ፡ ወንኀለ ፡ አረፋቲሃ፡ መኳንንቷ፡ኃያላኗ፡ጠፉ፤

እስመ ፡ እምነበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትቤቀልዋ፡በቀለ፡
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡በቀልን፡ተከ ፍለዋታልና፤

ወበከመ፡ገብረት፡ግበርዋ፡
እርሷ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገች ፡ ክፉ ነገር፡አድርጉባት፤

፲፮፤ ወሠርዉ፡ዘርያመ፡ለባቢሎን፡
የባቢሎንን ፡ ልጃቸውን ፡ የልጅ ፡ ልጃ ቸውን፡አጥፉ፤

ወዘይእኀዝ፡ማዕፀደ፡በመዋዕለ፡ማዕረር፡
በመኸር ፡ ጊዜ ፡ ማጭድ ፡ የሚይዝ ፡ ሰው ፡ ይጨድ ፡ አለ ፡ በለው ፤ ሣበው ፡ የሚባል፡መሣሪያ፡የያዘ፡ሰው፡ያጥፋ፤

እምገጸ ፡ መጥባሕተ ፡ የናናዊ ፡ ወይሠወጥ ፡
፩ዱ፡፩ዱ፡ውስተ፡ሕዝቡ፡
ወእምገጸ፡መጥባሕተ፡አረማውያን፡
ይሠወጥ...



ጦር፡የተነሣ፡አንዱም፡አንዱ፡ወደ፡ ወገኑ፡ይመለስ፤

ወ፩ዱ፡ወ፩ዱ፡ይዕቱ፡ብሔሮ፡
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ይመለስ፤

፲፯፤ በግዕ፡ዘተገድፈ፡እስራኤል፡
እስራኤል፡የጠፋ፡በግ፡ነው፤

አናብስት፡ዘረውዎ፡
አንበሳዎች ፡ በተኑት ፡ ማለት ፡ የባቢሎን፡ሰዎች፡ማረኩት፤

መቅድመ፡በልዖ፡ንጉሠ፡አሦር፡
ንጉሠ ፡ አቶርም ፡ ይላል፤ ከዚህ አስቀድሞ ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ስልም ናሶር፡ማርኮ፡አጠፋው፤

ወድኅረ ፡ ውሕጦ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን፡
ኋላ ፡ ግን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደ ነፆር፡በጦር፡ዋጠው፤

፲፰፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚ አብሔር፡ፀባኦት፡አምላከ፡እስራኤል፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡እትቤቀሎ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
እነሆ ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ እበቀለ ዋለሁ፤

ወለምድሩ፤
አገሩንም፡እበቀላታለሁ፤

በከመ፡ተበቀልክዎ፡ለንጉሠ፡ፋርስ፤
የፋርስን፡ንጉሥ፡እንደ፡ተበቀልኩት፡ የባቢሎንን፡ንጉሥ፡እበቀለዋለሁ፤

፲፱፤ ወእሰውጦ ፡ ለእስራኤል ፡ ውስተ ፡ ሊዖቱ፤
እስራኤልን፡ወደርስቱ፡ወደ፡መስኩ፡ ...

ወይትረአይ፡ውስተ፡ቀርሜሎስ፡
ወደ፡ቀርሜሎስ፤

ወባሳን፡
ወደ፡ባሳን፡፤

ውስተ፡ደብረ፡ኤፍሬም፡
ወደ፡ኤፍሬም፡ተራራ፤

ወውስተ፡ገለአድ፡
ወደ፡ገለአድ፡ዕፃ፡ይሠማራል፤

ወትጸግብ፡ነፍሱ፡
ሰውነቱ፡ተድላውን፡ደስታውን፡ትጠ ግባለች፤

፳፤ በእማንቱ፡መዋዕል፡
በዚያ፡ወራት፤

ወበውእቱ፡ጊዜ፡
በዚያን፡ጊዜ፤

ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

የኀሥሥዋ፡ለኃጢአተ፡እስራኤል፡
የእስራኤልን፡ኃጢአት፡ይፈልጓታል፤

ወኢትሄሉ፡
ነገር፡ግን፡አትኖርም፡አለ፤

ወጌጋዩ፡ለይሁዳ፡ኢትትረከብ፡
የይሁዳም፡በደሉ፡አትገኝም፡አለ፤

እስመ ፡ እሠሃሎሙ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ፡ ውስተ ምድር፡
በዚያች ፡ አገር ፡ ከሞት ፡ የቀሩትን ፡ ሰዎች፡ይቅር፡እላቸዋለሁና፤

፳፩፤መሪራን፡የዐርጉ፡ላዕሌሃ፡
ቁጡዎች ፡ የሆኑ ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ በርሷ፡ላይ፡ይዘምታሉ፤

ወላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡
በውስጧ ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ይዘምታሉ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተበቀሊ፡መጥባሕት፤
ጦር ፡ የባቢሎንን ፡ ሰዎች ፡ ተበቅለሽ፡ አጥፊ ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአ ብሔር፡የባቢሎንን፡ሰዎች፡አጥፊ፤

ወአማስኒ፡ደኃሪቶሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ፍጻሜያቸውንም፡አጥፊ፡አለ፡እግዚአ ብሔር፤

ወግበሪ፡ኵሎ፡ዘአዘዝኩኪ፤
የአዘዝኩሽን፡ሁሉ፡አድርጊ፡አለ፤

፳፪፤ውውዓ፡ቀትል፤
የሰልፍ፡ድንፋታ፡ግርግርታ፤

ወቅጥቃጤ፡ዓቢይ፡በምድር፤
ጽኑ፡መከራ፡በምድር፡ይደረጋል፤

፳፫፤እፎ፡ተቀጥቀጠት፤
ባቢሎን፡እንዴት፡ጠፋች፤

ወተሰብረት፡እንተ፡ትፈጽሐ፡ለኵላ፡ምድር፤
ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋት ፡ የነበረች ፡ ባቢሎን፡እንዴትስ፡ድል፡ተነሣች፤

ወእፎ ፡ ኮነት ፡ ሙስንተ ፡ ባቢሎን ፡ በውስተ፡ አሕዛብ፤
በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ባቢሎን ፡ እንዴት፡ የጠፋችን፡ሆነች፤

፳፬፤ተቀጥቀጥኪ፤
በመከራ፡ተቀጠቀጥሽ፤

ወተእኀዝኪ፡ባቢሎን፤
ባቢሎን፡በመከራ፡ተያዝሽ፤

ወአንቲሂ፡ኢያእመርኪ፤
አንቺም ፡ ይህ ፡ እንዲመጣብሽ ፡ አላወ ቅሽም፤

ተረከብኪ፡ወተእኀዝኪ፤
በመከራው፡ተይዘሽ፡ተገኘሽ፤

እስመ፡ለእግዚአብሔር፡ተቃወምኪዮ፤
እግዚአብሔርን፡ተቀዋውመሽዋልና፤

፳፭፤አርኀወ፡እግዚአብሔር፡መዝገቦ፤
አርኀወ፡መዝገቦ፡ግሥ፡ነው፡እግዚአ ብሔር፡ይጥፉ፡ብሎ፡አዘዘ፤

ወአውጽአ፡ንዋየ፡መዓቱ፤
አጠፋቸው፤

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ፀባኦት ፡ ይገብር፡በምድረ፡ፋርስ፤
ፈጣሪ ፡ የሚሆን ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ በፋርስ ፡ ሀገር ፡ የወደደውን ፡ ያደርጋልና፤

፳፮፤እስመ፡በጽሐ፡ዕድሜሁ፤
የሚጠፉበት፡ጊዜው፡ደርሷልና፤

አርኀዉ ፡ መዛግብቲሃ ፡ ወፍትንዋ ፡ ከመ፡ በዓት፤
ሣጥኖቿን ፡ ከፍታችሁ ፡ እንደ ፡ ዋሻ ፡ በርብሯት፤

ወሠርውዋ፤
ጨርሳችሁም፡አጥፏት፤

ወኢታትርፉ፡ላቲ፡ወኢምንተኒ፤
ምንም፡ምን፡አታስቀሩላት፤

፳፯፤ወአይብሱ፡ኵሎ፡ፍሬሃ፤
ፍሬዋን፡ሁሉ፡አጥፉ፤

ወይረዱ፡ወይትቃተሉ፤
ወርደው፡ይዋጉ፤

አሌ፡ሎሙ፡እስመ፡በጽሐት፡ዕለቶሙ፤
የሚጠፉባት ፡ ቀን ፡ ደርሳለችና ፡ ወዮላቸው፤

ወጊዜ፡ይትቤቀልዎሙ፤
የሚበቀሉባቸውም ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ዋልና፡ወዮላቸው፤

፳፰፤ ቃለ ፡ እለ ፡ ይጐይዩ ፡ ወአምሰጡ ፡ እምድረ፡ባቢሎን፤
ይሰማዕ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ ከባቢሎን ፡ አምልጠው ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ይሰማል፤



ከመ ፡ ይዜንዉ ፡ በጽዮን ፡ በቀለ ፡ እግዚአ ብሔር፡አምላክነ፡ወበቀለ፡መቅደሱ፤
የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በቀልና ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ በቀል ፡ በጽዮን፡ይናገሩ፡ዘንድ፤

፳፱፤አስምዑ፡ውስተ፡ባቢሎን፤
በባቢሎን፡አዳኙ፤

ብዙኃን ፡ እንተ ፡ ኵለሂ ፡ ይነድፍዋ ፡ ወየዓ ግትዋ፡ተዓይን፤
በአራቱ፡መዓዝን፡ከበው፡ባቢሎንን፡ የሚወጓት ፡ ሠራዊት፡ ብዙዎች ፡ ናቸው፤

ወአልቦ፡ዘያመሥጥ፡እምኔሃ፤
ከእርሷ፡የሚያመልጥ፡የለም፤

ወተበቀልዋ፡በከመ፡ምግባራ፤
እንደ፡ሥራዋ፡ተበቅለው፡አጠፏት፤

ወኵሎ፡በከመ፡ገብረት፡ይገብርዋ፤
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አደረገች ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያደርጉባታል፤

እስመ ፡ ተቃወመቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላከ፡ቅዱሰ፡እስራኤል፤
ጽንዓ ፡ እስራኤል ፡ ክብረ ፡ እስራኤል፡ እግዚአብሔርን፡ተቀዋውማዋለችና፤

፴፤በእንተ፡ዝንቱ፡ይወድቁ፡ወራዙቲሃ፡ በውስተ፡መርኅባ፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጐልማሶቿ ፡ በዓደባ ባይዋ፡ተደብድበው፡ይወድቃሉ፤

ወኵሎሙ ፡ ዕደዊሃ ፡ መስተቃትላን፡ ይት ገደፉ፡ውእቱ፡አሚረ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ያን፡ጊዜ፡የሚዋጉ፡አርበኞቿ፡ሁሉ፡ ይጠፋሉ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፴፩፤ ናሁ ፡ አነ ፡ ላዕሌኪ ፡ ጽእልት ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡...

የተሰደብሽ ፡ ባቢሎን ፡ እነሆ ፡ እኔ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ በመዓት ፡ አለሁብሽ ፡ አለ፡አቸናፊ፡እግዚአብሔር፤

እስመ፡በጽሐት፡ዕለትኪ፤
የምትጠፊባት፡ቀን፡ደርሳለችና፤

ወጊዜ፡ይትቤቀሉኪ፤
አንቺን ፡ ተበቅለው ፡ የሚያጠፉበ ትም፡ጊዜ፡ደርሷልና፤

፴፪፤ወትደክሚ፡ኀሥርት፤
አንቺ፡ጐስቋላ፡በመከራው፡ትደክሚ ያለሽ፤

ወትወድቂ፤
በመከራ፡ተይዘሽ፡ትወድቂያለሽ፤

ወአልቦ፡ዘያነሥአኪ፤
የሚያድንሽ፡የለም፤

ወአነድድ፡እሳተ፡ውስተ፡ዖምኪ፤
በዛፍሽ፡እሳት፡አነድዳለሁ፤አንድም፡ በኃያላኑ፡ጦር፡አመጣለሁ፤

ወትበልዕ፡ኵሎ፡ዘዓውድኪ፤
በዙሪያሽ፡ያለውን፡ሁሉ፡ታጠፋለች፡ ማለት፡ሠራዊቱን፡ሁሉ፡ታጠፋለች፤

፴፫፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባኦት፤
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ተዓገልዎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወለደቂቀ፡ይሁዳ፡ኅቡረ፤
የእስራኤልን ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳን ፡ ልጆች ፡ አንድነት ፡ ሁነው ፡ ቀሙአቸው፤

ወኵሎሙ፡እለ፡ፄወውዎሙ፡ተኀየልዎሙ፤
የማረኳቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በረቱ ባቸው፤

ወዓበዩ፡ፈንዎቶሙ፤
...ኑን፡ማሰናበት፡እምቢ፡አሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፬፤ ወዘያድኅኖሙሰ ፡ ኃያል ፡ እግዚአ ብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ስሙ፤
ያዳናቸው ፡ ኃያል ፡ የሚሆን ፡ እግዚአ ብሔር፡ግን፡ስሙ፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ ነው ፤ አንድም፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ ያዳናቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ ኃያል፡ነው፤

ቅሥተ፡ይሳነኖሙ፡ለዕድዋኒሁ፡
ቅሥተ ፡ ይትዋቀሰሙ ፡ ተሰናነ ፡ ይሳነኖሙ፡ሲል፡ነው፤ባለጋራዎቹን፡ ይከራከራቸዋል፡ይወቅሳቸዋል፤

ከመ፡ታርምም፡ምድር፡
ምድር፡ከጦር፡ፀጥ፡ትል፡ዘንድ፤

ወያደነግፅዎሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ባቢሎን፡
በባቢሎን፡የሚኖሩትን፡ሰዎች፡ያስደ ነግጧቸዋል፤

፴፭፤ መጥባሕት፡ላዕለ፡ፋርስ፡ይቤ፡እግዚ አብሔር፡
በፋርስ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት፡ ጦር ፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃጥታባቸዋለች ፡ አለ ፡ እግዚአ ብሔር፤

ወላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ባቢሎን፡
በባቢሎን፡በሚኖሩ፡ሰዎች፡ላይ፤

ወላዕለ፡መሳፍንቲሃ፡
በመሳፍንቶቿ፡ላይ፤

ወዲበ፡ጠቢባኒሃ፡
የጦር ፡ ጥበብ ፡ እናውቃለን ፡ በሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ጦር፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ፡ እግዚአብሔር፡ተቃጥታባቸዋለች፤

፴፮፤ መጥባሕት፡ላዕለ፡መስተቃትላኒሃ፡
በአርበኞቿም፡ላይ፡ጦር፡አለ፡ማለት፡ ጦር ፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃጥታባ ቸዋለች፤

ወይደክሙ፡
በመከራ፡ተይዘው፡ይደክማሉ፤

መጥባሕት፡ላዕለ፡ኃያላኒሃ፡
በኃያላኖቿ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት፡ ጦር ፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃጥታባ ቸዋለች፤

ወይደነግፁ፡
በመከራ፡ይደነግጣሉ፤

፴፯፤ መጥባሕት፡ላዕለ፡አፍራሲሃ፡
በፈረሶቿ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት፡ ጦር፡ይመጣባቸዋል፤

ወላዕለ፡ሠረገላቲሃ፡
በሠረገላዎቿም ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት፡ ጦር ፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃጥታባ ቸዋለች፤

ወላዕለ፡እለ፡ይዴመሩ፡ማዕከላ፡
በኃጢአት ፡ በግቢ ፡ አንድ ፡ በሚሆኑ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ አለ፡ ማለት ፡ ጦር፡ ይመጣባቸዋል ፤ አንድም ፡ ሥልጣነ፡ እግዚአብሔር፡ተቃጥታባቸዋለች፤

ወይከውኑ፡ከመ፡አንስት፡
በፍርሃት ፡ ተይዘው ፡ እንደ ፡ሴቶች፡ ይሆናሉ፤

መጥባሕት፡ላዕለ፡መዛግብቲሃ፡
በድልቦቿ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ይማረካሉ፤

ወይዘረዉ፡
ይበተናሉ፤



፴፰፤ መጥባሕት፡ላዕለ፡ማያቲሃ፡
በውሀዎቿ፡ላይ፡ድርቅ፡አለ፤

ወይየብሱ፡
ውሀዎቿ፡ይደርቃሉ፤

እስመ፡ምድረ፡ግልፎዋት፡ይእቲ፡
የጣዖታቱ፡ሀገር፡ናትና፤

ወይትቄናደዩ፡ውስተ፡ደሰያቲሃ፡
በደሴቶቿ፡ላይ፡ይቀናጣሉ፤

፴፱፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይነብሩ ፡ ጺም ፡ ምስለ፡ኢም፡
ፍጥረተ ፡ የማን ፡ ወጺጋም ፤ ፍጥረተ ፡ ባሕር ፡ ወየብስ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ስለዚህ፡ ነገር፡በቀኝ፡በግራ፡በባሕር፡በየብስ፡ ያሉ፡ፍጥረታት፡ይኖሩባታል፤

ወየኀድራሃ፡አዋልደ፡ጼዴናታት፡
እለ፡ሄለይ፡ይኖሩባታል፤

ወኢትሔሉ፡እንከ፡ለዓለም፡
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አትኖርም፤

ወኢይነብርዋ፡ለትውልደ፡ትውልድ፡
ለልጅ፡ልጅ፡ዘመን፡አይኖሩባትም፤

፵፤ በከመ ፡ ገፍትዖን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰዶም፡ወለገሞራ፤
እግዚአብሔር፡ሰዶም፡ገሞራን፡እንዳ ጠፋቸው፤

ወለአድያሚሆን፡
አውራጃቸውን፡ሁሉ፡እንዳጠፋቸው፤

ይቤ፡እግዚአብሔር፤
ትጠፋለች፡አለ፡እግዚአብሔር፤

ወኢይነብር፡እንከ፡ሰብእ፡ህየ፡ወኢየኃድር፡ ባቲ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
እንግዲህ፡ወዲህም፡ሰው፡አይኖርባትም፤

፵፩፤ ናሁ ፡ ሕዝብ ፡ ይመጽእ ፡ እምድረ ፡ ደቡብ፡፤
እነሆ ፡ ከባቢሎን ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ይመጣል፤

ወዓቢይ፡ሠራዊት፡
ብዙ፡ሠራዊት፤

ወነገሥትሂ ፡ ብዙኃን ፡ ይትነሥኡ ፡ እምአ ጽናፈ፡ምድር፡
ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣሉ፤

፵፪፤ወቦሙ፡ቀሥት፡
ቀሥት፡አላቸው፡ይዘዋል፤

ወቢዶን፡
በሎታም ፡ አላቸው ፡ ይዘዋል ፡ ዘይእኀዙ ፡ ማንሻ ፤ አንድም ፡ ወቦሙ፡ ቀሥት ፤ ቀሥት ፡ አላቸው ፡ ይዘዋል፤ ወቢዶነ ፡ ዘይእኀዙ ፡ በሎታንም ፡ የያዙ፡ሰዎች፤

ጥቡዓን፡እሙንቱ፤
ጨካኞች፡ናቸው፤

ወኢይምሕሩ፡
አይራሩም፤

ውውዓሆሙ፡ከመ፡ድምፀ፡ባሕር፡ይደምፁ፡
ድንፋታቸውን፡እንደ፡ባሕር፡ድምፅ፡ ያሰማሉ፤

ወይጼዓኑ፡በአፍራሲሆሙ፡
በፈረሶቻቸው፡ይቀመጣሉ፤

ወይትቃተሉኪ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ወለተ ፡ ባቢሎን፡
የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ በማስ ፈራት፡ይወጉሻል፤

፵፫፤ ወሰምዐ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ውውዓሆሙ፡

www.ethiopianorthodox.org

የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ድንፋታቸውን ፡ ሰምቶ፤

ወተመስዉ፡እደዊሁ፡
እጆቹ፡እንደ፡ሰም፡ቀለጡ፤

ወአኀዞ፡ማሕምም፡ከመ፡እንተ፡ትወልድ፡
ምጥ ፡ እንደያዛት ፡ ሴት ፡ ጭንቅ ፡ ያዘው፤

፵፬፤ናሁ፡የዐርግ፡ከመ፡አንበሳ፡እምዕበየ፡ዮርዳኖስ፡ውስተ፡ምድረ፡ኤታም፡
እነሆ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ በማስፈራት ፡ ወደ ፡ ኤታም ፡ አገር፡ይመጣል፤

እስመ፡ፍጡነ፡እሰድዶሙ፡እምኔሃ፡
ፈጥኜ ፡ ከሷ ፡ አስወጥቼ ፡ እሰዳቸዋለሁና፤

ወአቀውሞሙ፡ላዕሌሃ፡ለኵሉ፡ወራዙት፡
ጎልማሶችን፡ሁሉ፡በእርሷ፡ላይ፡አቆማቸዋለሁ፤

እስመ፡አልቦ፡ከማየ፡
እንደ፡እኔ፡ያለ፡የለም፡ብላለችና፤

ወመኑ፡ዘይትቃወመኒ፡
የሚከራከረኝ፡የለም፤

ወመኑ፡ዝ፡ኖላዊ፡ዘይቀውም፡ቅድመ፡ገጽየ፡
በፊቴም ፡ የሚቆም ፡ አርበኛ ፡ የለም ፡ ብላለችና፡አቀውሞሙ፡ብለህ፡እሥር፤ አንድም ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ከማየ ፡ እንደእኔ፡ያለ፡ፈጣሪ፡ማነው፡ይላል፡ ጌታ፤ወመኑ፡ዘይትቃወመኒ፡የሚቀዋወመኝስ ፡ ማን ፡ ነው ፤ ወመኑ ፡ ዝ ፡ ኖላዊ፡ በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ አርበኛ ፡ ማነው፡ይላል፡ጌታ፤

፵፭፤በእንተ፡ዝንቱ፡ስምዑ፡ምክሮ፡ለእግዚአብሔር፡ዘመከረ፡ላዕለ፡ባቢሎን፡
ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ስለአደረገች ፡ በባቢሎን፡ላይ፡የመከረውን፡የእግዚአብሔር፡ምክሩን፡ስሙ፤

ወሕሊናሁ፡ዘሐለየ፡ላዕለ፡ፋርስ፡
በፋርስ ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ያሰበውን፡ ሐሳቡን፡ስሙ፤

ለእመ፡ኢማሰነ፡መሐስዓ፡አባግዒሆሙ፤
የበጎቻቸው፡ጠቦት፡የጠፋ፡ባይሆን፤

ወእመ፡ኢማሰነ፡መርዔት፡እምኔሆሙ፤
መንጋቸው፡ከእነሱ፡ተለይቶ፡የጠፋ፡ ባይሆን፤

፵፮፤ እስመ ፡ እምውውዓሆሙ ፡ ለእለ፡ ይሴርውዋ፡ለባቢሎን፡
ባቢሎንን ፡ ከሚያጠፏት ፡ ሰዎች፡ ድንፋታ፡የተነሣ፤

እምኢያድለቅለቀት፡ምድር፡
ምድር፡ባልተነዋወጠችም፡ነበር፤

ወተሰምዐ፡ውውዓሆሙ፡ለአሕዛብ፡
የአሕዛብ፡ድንፋታቸው፡ተሰማ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፩ ፤

፩፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ናሁ ፡ አነሥእ ፡ አነ ፡ ነፋሰ ፡ መርቄ ፡ ላዕለ፡ ባቢሎን፡
እነሆ ፡ እኔ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ እጀ፡ መዓቴን፡አነሣለሁ፤

ወላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡
በውስጧም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡ አመጣለሁ፤

ተንሥኢ፡ነፋስ፡ወአማስኒ፡
መቅሠፍት፡ተነሥተሽ፡አጥፊ፤

፪፤ ወእፌኑ ፡ ላዕለ ፡ ባቢሎን ፡ ጸዓልያነ፡ ወጸአልያተ፡



የሚሳደቡ ፡ ሴቶችንና ፡ ወንዶችን ፡ ወደ፡ባቢሎን፡እሰዳለሁ፤

ይጼእልዋ፡
እነርሱም፡ይሰድቡዋታል፤

ወያረኵስዋ፡ለምድራ፡
ምድሯን፡ያረክሷታል፤

እስመ ፡ ሀለዉ ፡ ላዕሌሃ ፡ እምዓውዳ ፡ በዕለተ፡ ምንዳቤሃ፡
በመከራዋ ፡ ቀን ፡ በዙሪያዋ ፡ ከብበው፡ አሉና፤

፫፤ለይስሐብ፡ዘይዌስቅ፡ቀስቶ፡
ቀስቱን ፡ የሚስብ ፡ ሰው ፡ ቀስቱን ፡ ይሳብ፤

ወይትሬሰይ፡በንዋየ፡ሕቅሉ፡
በመሣሪያ፡ዕቃውም፡ይጠረር፤

ወኢትምሐኩ፡ለወራዙቲሃ፡
ለጐልማሶቿ፡አትራሩ፤

ወአማስኑ፡ኵሎ፡ኃይላ፡
ሠራዊቷን፡ሁሉ፡አጥፉ፤

፬፤ወይወድቁ፡ቅቱላኒሃ፡በምድረ፡ፋርስ፡
በፋርስ፡ሀገር፡የሞቱ፡አርበኞቿ፤

ወርጉዛን፡በአፍአሃ፡
በአውራጃዋ ፡ ተወግተው ፡ የቆሰሉት፡ይወድቃሉ፤

፭፤ እስመ ፡ ኢኮነት ፡ መበለተ ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡
ቤተ፡እስራኤል፡ደሀ፡አልሆነችምና፤

ወይሁዳሂ፡ይእዜ፡ኢርኅቀ፡እምአምላኩ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡
ይሁዳም ፡ ፈጣሪው ፡ ከሚሆን ፡ ከአቸናፊ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አልራቀምና፡ይወድቁ፡ብለህ፡እሥር፤

እስመ፡መልአት፡ምድሮሙ፡ዓፀ፡እምቅዱሰ፡እስራኤል፡
ከጽንዓ ፡ እስራኤል ፡ ከክብረ ፡ እስራኤል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ መዓት፡የተነሣ፡አገራቸው፡ምድረ፡በዳ፡ስለሆነች፤

፮፤ጉዩ፡እማዕከለ፡ባቢሎን፡
ፈጥናችሁ ፡ ከባቢሎን ፡ መካከል ፡ ውጡ፡

ወአድኅኑ ፡ ነፍሰክሙ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ከእናንተ ፡ አንዱም፡ አንዱም፡ሰውነታችሁን፡አድኑ፤

ወኢትትገደፉ፡በኃጢአታ፡
በእርሷ፡ኃጢአት፡እናንተ፡አትጥፉ፡

እስመ ፡ መዋዕለ ፡ በቀል ፡ በጽሐ ፡ ላዕሌሃ ፡ እምኀበ፡እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ በቀል፡ የሚደረግበት ፡ ወራት ፡ ደርሷልና፤

ወይፈድያ፡በከመ፡ፍዳሃ፡
እንደ፡ኃጢአቷ፡መጠን፡መከራውን፡ያመጣባታል፤

### ጉባዔ ፤

፯፤ጽዋዓ፡ወርቅ፡ይእቲ፡ባቢሎን፡ውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር፡
በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተያዘች ፡ ባቢሎን፡የወርቅ፡ጽዋ፡ናት፡ማለት፡ ያች፡ደስ፡እንድታሰኝ፡እርሷም፡ሰባ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ኑራለችና ፤ አንድም ፡ በተራ ፡ ይጠጡባታል ፤ እርሷም ፡ በተራ ፡ ሁሉን ፡ አጥፍታ ለችና ፤ አንድም ፡ ያች ፡ ድንገት ፡ ወድቃ፡ እንድትሠበር ፡ ድንገት ፡ ሁሉን፡አጥፍታለችና፤

ወታሠክራ ፡ ለኵላ ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ወይነ ፡ መንሱታ፡

www.ethiopianorthodox.org

በእጇ ፡ በተያዘ ፡ በመቅሠፍቱ ፡ አረቂ፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ አሠከረቻት ፡ ማለት፡ አጠፋቻት፤

ሰትዩ፡አሕዛብ፤
አሕዛብ ፡ የመቅሠፍቱን ፡ አረቄ ፡ ጠጡ፤

በእንተ፡ዝንቱ፡ተንተኑ፡አሕዛብ፤
የመቅሠፍቱን ፡ አረቄ ፡ ስለ ፡ ጠጡ ፡ አሕዛብ ፡ ለመውደቅ ፡ ፍግምግም ፡ አሉ፤

፰፤ወግብተ፡ወድቀት፡ባቢሎን፡ወተቀጥቀጠት፤
ባቢሎን፡ድንገት፡ጠፋች፤

ብክይዋ፤
አልቅሡላት፤

ወንሥኡ ፡ ርጢነ ፡ ለቍስላ ፡ እመቦ ፡ ከመ ፡ ትትፌወስ፤
ምናልባት ፡ ትድን ፡ እንደሆነ ፡ ለቍስለ፡ መከራዋ ፡ መድኃኒት ፡ ፈልጉላት፤

፱፤ፈወስናሃ፡ለባቢሎን፤
ለባቢሎን፡መድኃኒት፡አደረግንላት፤

ወኢሐይወት፤
ነገር ፡ ግን ፡ አልዳነችም ፤ አንድም ፡ ፈወስናሃ ፡ ባቢሎንን ፡ መከርናት ፤ አስተማርናት ፡ ወኢሐይወት ፡ አልተመለሰችም፤

ንኅድጋ፡እንከሰ፡ወንእቱ፡ኵልነ፡ብሔረነ፤
እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ እርሷን ፡ ትተን ፡ ሁላችንም፡ወደ፡ሀገራችን፡እንመለስ፤

እስመ፡በጽሐ፡ውስተ፡ሰማይ፡ኵነኔሃ፤
ግዛቷ፡እስከ፡ሰማይ፡ደርሷልና፤

ወሐረ፡እስከ፡ከዋክብት፤
እስከ ፡ ከዋክብትም ፡ ደርሷልና ፡ ማለት፡ ኃያላኑን ፡ መኳንንቱን ፡ ሠራዊቱን ፡ እስከ ፡ መግዛት ፡ ደርሷልና፤

፲፤ወአውጽአ፡እግዚአብሔር፡ፍትሐነ፤
እግዚአብሔር ፡ ፍርዳችንን ፡ አወጣ ፡ ማለት፡ፈረደልን፤

ንዑ፡ንንግር፡በጽዮን፡ግብረ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፤
የፈጣሪአችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ፡እንናገር፡ዘንድ፡ኑ፤

፲፩፤አስተዳልዉ፡አሕፃክሙ፤
ፍላፃችሁን፡አዘጋጁ፤

ወምልዑ፡ምጕንጳክሙ፤
ጕራንጕሬአችሁንም፡ያዙ፤

እስመ ፡ አንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሰ፡ ንጉሠ፡ሜዶን፤
እግዚአብሔር፡የሜዶንን፡ንጉሥ፡የዳርዮስን፡ልቡና፡አነሣስቷልና፤

እስመ፡ላዕለ፡ባቢሎን፡መዓቱ፤
መዓቱ፡በባቢሎን፡ላይ፡ታዝለችና፤

ከመ፡ይሥርዋ፤
ባቢሎንን፡ያጠፋት፡ዘንድ፤

እስመ፡በቀለ፡እግዚአብሔር፡ይእቲ፤
የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ የሚደረግባት፡ስለሆነ፤

ወበቀለ፡መቅደሱ፤
የቤተ ፡ መቅደስም ፡ በቀል ፡ የሚደረግባት፡ስለሆነ፤

፲፪፤ ንሥኡ ፡ ትእምርተ ፡ ውስተ አረፋቲሃ፡ለባቢሎን፤
በባቢሎን ፡ ቅጽሮች ፡ ላይ ፡ ሰንደቅ ዐላማ ... ፤



ጽንዑ፡ምስለ፡ምጕንጳክሙ፤
ከጕራንጕሬያችሁ፡ጋራ፡ጽኑ፤

ወአንሥኡ፡አስባቢሃ፤
አስባቢሃ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ኃያላኖቿን ፡ አነሳሡ ፤ አንድም ፡ ወሰባቢሃ ፡ ካህናቶቿ ፤ አንድም ፡ አሳቢሃ ፡ ቢል በደመወዝ ፡ ተገዝተው ፡ የሚዋጉላት፡ አርበኞቿን፡አነሣሡ፤

ወአስተዳልዉ፡ንዋየ፡ሐቅልክሙ፤
የበዳ፡ፀብታችሁን፡አዘጋጁ፤

እስመ ፡ አኀዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይግበር ፡ ዘነበበ፡ላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ባቢሎን፤
እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩ፡ ሰዎችና፤

ወእለ፡የኀድሩ፡በማይ፡ብዙኀ፤
ስፉሕ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በሰፊው ፡ ውሀ ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተናገረውን፡ ነገር፡ያደርግ፡ዘንድ፡ጀምሯልና፤

፲፫፤ብዝኀተ፡መዛግብት፤
አንቺ፡ድልበ፡ብዙ፡ባቢሎን፤

በጽሐተኪ፡ደኀሪትኪ፤
ፍጻሜ፡ጥፋትሽ፡ደረሰችብሽ፤

ወዓመተ፡ትዕግልትኪ፤
ደሀውን፡የምትቀሚበት፡ፍዳ፡ዘመን፡ ደረሰችብሽ፤

፲፬፤ እስመ ፡ መሐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በርእሱ፤
እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ እኔ ፡ አማንየ፡ በርእስየ፡ብሎ፡ምሏልና፤

ከመ ፡ ይመልዕ ፡ ላዕሌኪ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ አንበጣ፤
እንደ ፡ አንበጣ ፡ ሰውን ፡ በአንቺ ፡ ላይ፡ አብዝቶ ፡ እንዲመላ ፡ ሕያው ፡ እኔ ፡ ብሎ ...

ወይረውፁ፡ላዕሌኪ፡እንዘ፡ይወርዱ፤
ከብበው፡በአንቺ፡ላይ፡ይሮጣሉ፤

፲፭፤ዘፈጠራ፡ለምድር፡በኃይሉ፤
በከሐሊነቱ ፡ ምድርን ፡ የፈጠራት፡ እርሱ፡ነው፤

ወአጽንዓ፡ለዓለም፡በጥበቡ፤
በባሕርይ ፡ ጥበቡ ፡ ዓለምን ፡ ያጸናት ፡ እርሱ፡ነው፤

ወበምክሩ፡ሰፍሐ፡ለሰማይ፤
በባሕርይ ፡ ምክሩም ፡ ሰማይን ፡ የዘረጋው፡እርሱ፡ነው፤

፲፮፤ ወገብረ ፡ ቃለ ፡ ድምፀ ፡ ማያት ፡ በሰማይ፤
በሰማይም ፡ የውኃዎች ፡ ድምፅ ፡ ቃልን፡እንዲሰማ፡አደረገ፤

ወአዕረገ፡ደመናተ፡እምአጽናፈ፡ምድር፤
ከጽንፈ፡ምድር፡ደመናትን፡አወጣ፤

ወገብረ፡መባርቅተ፡ለጊዜ፡ዝናም፤
በዝናም ፡ ጊዜ ፡ ሊሰሙ ፡ መባርቅትን፡ ፈጠረ፤

ወአውጽአ፡ነፋሰ፡እምነ፡መዛግብቲሁ፤
ነፋሱን፡ከቦታዎቹ፡አወጣ፤

፲፯፤ወለስሐ፡ምክረ፡ኵሉ፡ሰብእ፤
የሰው ፡ ሁሉ ፡ ምክር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ፡ አልጫ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ያ ፡ እንዲናቅ፡ የተናቀ፡ሆነ፤

ወተኃፍረ፡ኵሉ፡ነሐቢ፡በግልፎሁ፤
ጃን፡ሸላሚ፡ሁሉ፡በጣዖቱ፡አፈረ፤

እስመ፡ሐሰተ፡ሰበኩ፤
ሐሰት፡ጣዖትን፡ሠርተዋልና፤

ወአልቦ፡መንፈስ፡ውስቴቶሙ፤
በውስጣቸው፡ዕውቀት፡የለምና፤

፲፰፤ ከንቱ፡ውእቱ፡ግብሮሙ፤
ሥራቸው፡ከንቱ፡ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

የጎሥሩ፡ወይትሐጐሉ፡አመ፡ይሔውጾሙ፡
እግዚአብሔር ፡ በመዓት ፡ በጐበ
ኛቸው፡ጊዜ፡ይጠፋሉ፡ይጐሰቈላሉ፤

፲፱፤አኮ፡ከመዝ፡መክፈልቱ፡ለያዕቆብ፡
የያዕቆብ ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ እግዚአ
ብሔር፡እንደዚህ፡አይደለም፤

እስመ፡ፈጣሬ፡ኵሉ፡ውእቱ፤
የሁሉ፡ፈጣሪ፡ነውና፤

ወእስራኤልሰ፡በትረ፡ርስቱ፡እግዚአ፡ኃይል፡
ስሙ፤
የርስቱ፡ዕድል፡እስራኤል፡የሆነለት፡
የእግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ እግዚአ ፡
ኃይል፡ይባላል፤

፳፤ዘራዊት፡አንቲ፡ሊተ፡ንዋየ፡ሐቅል፡
አንቺ፡ሁሉን፡የምታጠፊ፡ባቢሎን፡
ከዚህ፡ቀድሞ፡የበዳ፡ፀብት፡ነበርሽ፤

ዘረውኩ፡ብኪ፡አሕዛበ፤
ዛሬ፡ግን፡አሕዛብን፡አጠፋሁብሽ፤

ወአአትት፡እምውስቴትኪ፡ነገሥተ፤
ነገሥታቱን ፡ ከአንቺ ፡ ለይቼ ፡
አጠፋለሁ፤

፳፩፤ወእዘሩ፡እምውስቴትኪ፡አፍራሰ፡
ፈረሶችን፤

ወመስተፅዕናነ፤
በፈረስ ፡ የተቀመጡትን ፡ ከአንቺ ፡
አጠፋለሁ፤

ወእዘሩ፡እምውስቴትኪ፡ሠረገላተ፤
ሠረገላዎችን፤

ወዘይጼእኖሙ፤
በሠረገላው ፡ የተቀመጡትን ፡ እበት
ናለሁ፤ማለት፡አጠፋለሁ፤

፳፪፤ ወእዘሩ ፡ እምውስቴትኪ ፡ ብእሴ ፡
ወብእሲተ፤
ሴትንና፡ወንድን፡ከአንቺ፡እበትናለሁ፤

ወእዘሩ፡እምኔኪ፡ወሬዛ፡ወድንግለ፤
ጐልማሳውንና፡ድንግሊቱን፤

ወእዘሩ፡እምኔኪ፡ልሒቀ፡ወሕፃናተ፤
ሽማግሌውንና ፡ ሕፃናቱን ፡ ከአንቺ፡
አጠፋለሁ፤

፳፫፤ወእዘሩ፡እምኔኪ፡ኖላዌ፡ወመርዔቶ፤
እረኛውንና ፡ መንጋውን ፡ ከአንቺ፡
አጠፋለሁ፤

ወእዘሩ፡እምኔኪ፡ሐረሳዌ፡ወወፍሮ፤
በሬውንና፡መሠምሪያውን፡ከአንቺ፡
አጠፋለሁ፤

ወዕዘሩ፡እምኔኪ፡መላእክተ፡ወመሳፍንተ፤
አለቆችንና፡ሹማምንቱን፡ከአንቺ፡
አጠፋቸዋለሁ፤

፳፬፤ወእትቤቀላ፡ለባቢሎን፤
ባቢሎንን፡እበቀላታለሁ፡አለ፤

ወለኵሉ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ከላውዴዎን፤
በከላውዴዎን ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን፡
ሁሉ፤

ኵሎ ፡ እኩየ ፡ ዘገብሩ ፡ በውስተ ፡ ጽዮን፤
በቅድመ ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
በጽዮን፡ክፋውን፡ሥራ፡ሁሉ፡የሠሩ፡
በባቢሎን፡የሚኖሩ፡ሰዎችን፡ሁሉ፡
በዓይኖቻችሁ ፡ እያያችሁ ፡ አጠፋቸ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፳፭፤ ናሁ ፡ አነ ፡ ላዕሌከ ፡ ደብር ፡ ኀሡር፡
ይቤ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘያማስና፡ ለኵላ፡
ምድር፤
ጐስቋላ ፡ ብልጣሶር ፡ ምድርን ፡ ሁሉ፡
የሚያጠፋት ፡ እግዚአብሔር ፡ እነሆ፡
እኔ፡በአንተ፡ላይ፡በመዓት፡አለሁ፡አለ



ወእሰፍሕ፡እዴየ፡ዲቤከ፤
እደ ፡ መዓቴን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡
አመጣለሁ፤

ወእነሥተከ፡እምነ፡ያላዕትከ፤
ከዋሽህ፡አውጥቼ፡አጠፋኃለሁ፤

ወእሬስየከ፡ደብረ፡ሐሩር፤
ድርቅ፡የተመላበት፡ተራራ፡አደርግ
ሃለሁ፤

፳፮፤ ወኢይነሥኡ ፡ እምኔከ ፡ ዕብነ ፡ ለማዕ
ዘንት፤
ከአንተ ፡ ለማዕዝን ፡ ደንጊያውን ፡
አላነሣም፤

ወዕብነ፡ለመሠረት፤
ደንጊያውንም፡ለመሠረት፡ከአንተ፡
አላነሣም ፡ ማለት ፡ ልጅ፡ አልተካ
ልህም፤

እስመ ፡ ለዓለም፡ አማስነከ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አጠፋ
ኀለሁ፤ብሏልና፤

፳፯፤ንሥኡ፡ትእምርተ፡ዲበ፡ምድር፤
በባቢሎን ፡ ሰንደቅ ፡ አላማውን ፡
አንሡ፤

ወንፍሑ፡ቀርነ፡ውስተ፡አሕዛብ፤
በአሕዛብ፡ላይ፡ነጋሪቱን፡ምቱ፤

ቀድሱ፡ላዕሌሃ፡አሕዛበ፤
አሕዛብን፡በእርሷ፡ላይ፡ለዩባት፤

ወአዝዙ፡ዲቤሃ፡ነገሥተ፡ዘእምነ፡ዓራራት፤
ዓራራት፡ስመ፡ሀገር፡ነው፤በዓራራት፡
የሚኖሩ ፡ ነገሥታትን፡ እዘዙ ፤
አንድም፡ ዓራታት ፡ ይላል ፡ በአልጋ ፡
ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚኖሩ፡ ነገሥ
ታቱን፡አዝዙባት፤(እዘዙባት)
ወ[illegible]

እስከ፡ናዜዎንም፡ድረስ፡የሚኖሩትን፡
እዘዙ፤

ወአቅሙ፡ላዕሌሃ፡ነዳፍያነ፤
ፍላፃቸውን፡እየወረወሩ፡የሚዋጉ፡አር
በኞችንም፡በእርሷ፡ላይ፡አጽኑባት፤

ወአዕርጉ፡ዲቤሃ፡አፍራሰ፡ዘከመ፡አንበጣ፡
ብዝኀ፤
ብዛቱ፡እንደ፡አንበጣ፡የሆነ፡ፈረስን፡
ወደ፡እርሷ፡አዝምቱባት፤

፳፰፤ ወቀድሱ ፡ ላዕሌሃ ፡ ሠራዊተ ፡ ንጉሠ፡
ሜዶን፤
የሜዶን፡ንጉሥ፡የዳርዮስን፡ሠራዊት፡
በእርሷ፡ለዩባት፤

ወመሳፍንተ፡ኵሉ፡ምድር፤
የሀገሩን፡ሁሉ፡ሹማምንት፤

ወዘኵሉ፡መላእክቲሁ፤
አለቆቹን፡ሁሉ፤

ወዘኵሉ፡በሐውርቲሁ፤
አውራጃውን፡ሁሉ፡ለዩባት፤

፳፱፤አድለቅለቀት፡ምድር፤
ባቢሎን፡ተነዋወጠች፤

ወሐመት፤
በመከራው፡ተጨነቀች፤

እስመ ፡ ተንሥአት ፡ ምክረ ፡ እግዚአብሔር ፡
ላዕለ፡ባቢሎን፤
የእግዚአብሔር ፡ ምክሩ ፡ በባቢሎን ፡
ላይ፡ጸንታለችና፤

ከመ፡ያማስና፡ለምድር፡ዘባቢሎን፤
ባቢሎንን፡ያጠፋት፡ዘንድ፤

ወአልቦ፡ዘይነብራ፤
የሚኖርባት፡ሰው፡የለም፤

፴፤ ሐልቁ ፡ መስተቃትላን ፡ ዘባቢሎን ፡
ዘይጸብኡ፤
የሚዋጉ፡የባቢሎን፡አርበኞች፡ጠፉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይነብሩ፡ሀየ፡ውስተ፡ጥቅም፤
በቅጽር፡በባቢሎን፡የሚኖሩ፡ጠፉ፤

ወይትቀጠቀጥ፡ኃይሎሙ፤
ኃይላቸው፡ሠራዊታቸው፡ይጠፋል፤

ወይከውኑ፡ከመ፡አንስት፤
በፍርሀት ፡ ተይዘው ፡ እንደ ፡ ሴቶች፡ ይሆናሉ፤

ውዕያ፡አብያቲሃ፤
ቤቶቿ፡ተቃጠሉ፤

ወተቀጥቀጠ፡መናሥግቲሃ፤
ቍልፏ ፡ ተሰበረ ፡ ማለት ፡ ኃያላኖቿ ፡ ጠፉ፤

፴፩፤ ዘይረውፅ ፡ ለተቀብሎ ፡ ረዊፀ ፡ ይረውፅ፤
የፊተኛውን ፡ ጉበኛ ፡ ለመቀበል ፡ የሚሮጥ ፡ የኋለኛው ፡ የብልጣሶር ፡ ጉበኛ ፤ የፊተኛውን ፡ ጉበኛ ፡ ለመቀበል፡ይሮጣል፤

ወዘይዜኑ፡ለተቀብሎ፡ዘይዜኑ፤
የፊተኛውን፡ወሬ፡ነጋሪ፡ለመቀበል፡ የሚሮጥ፡የኋለኛው፡ወሬ፡ነጋሪ፡የፊ ተኛውን ፡ ወሬ ፡ ነጋሪ ፡ ለመቀበል፡ ይሮጣል፤

ከመ፡ይዜንዎ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
ለብልጣሶር፡እለ፡ቂሮስ፡መጡ፡ብሎ፡ ይነግረው፡ዘንድ፤አንድም፡ዘይረውፅ፡ የፊተኛውን ፤ ባለምሥራች ፡ ለመ ቀበል፡የሚሮጥ፡የኋለኛው፡የዳርዮስ፡ ባለምሥራች ፡ የፊተኛውን ፡ ባለም ሥራች ፡ ለመቀበል ፡ ይሮጣል ፤ ወዘይዜኑ ፡ የፊተኛውን ፡ ባለም ሥራች፡ ለመቀበል ፡ የሚሮጥ ፡ የኋለኛው፡የቂሮስ፡ባለምሥራች፡የፊ ተኛውን፡ባለምሥራች፡ለመቀበል፡ ይሮጣል፡ከመ፡ይዜንዎ፤ለቂሮስ፡ብል ጣሶርን፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ይነግረው፡ ዘንድ፡ሞተ፡ብሎ፤

እስመ፡እስተጋብዕዋ፡ለሀገር፤
ከተማይቱን፡እጅ፡አድርገዋታልና፤

ወለማዕዶታሂ፡አኅዝዋ፤
ገጠሯንም፡ይዘዋታልና፤

፴፪፤ወሐፁራሂ፡አውዓዩ፡በእሳት፤
አጥሯን፡በእሳት፡አቃጠሉ፤

ወዔወውዎሙ፡ለዕደው፡መስተቃትላን፤
አርበኞች፡ሰዎችንም፡ማረኳቸው፤

፴፫፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ጸባኦት፡አምላከ፡እስራኤል፤
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አቸናፊ ፡ እግዚአ ብሔር፡እንዲህ፡ብሏልና፤

ቤተ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ከመ ፡ ዓውድ ፡ ዘያከ ይድዎ፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ እህል ፡ እንደ ሚያበራዩበት ፡ ዓውድማ ፡ ይጠፋል፡ ብሏልና፤

ዓዲ፡ኅዳጠ፤
አሁን፡ጥቂት፡ቆይቶ፤

ወበጽሐ፡ጊዜ፡ማዕረሩ፤
የሚጠፋበት፡ጊዜው፡ደርሷልና፤

፴፬፤ በልዓኒ ፡ ወተካፈለኒ ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር፡ ገንዘቤን፡ተካፍሎ፡በላብኝ፤

ወረሰየኒ፡ንዋየ፡ከንቱ፤
እንደተሠበረ፡ዕቃ፡እንደ፡ብርሌ፡እን ደብርጭቆ፡አደረገኝ፤

ወውኅጠኒ፡ከመ፡ከይሲ፤
እ[illegible]



ወፀግበ፡ከርሡ፡እምነ፡ሥጋየ፤
ገንዘቤን ፡ ከመብላቱ ፡ የተነሣ ፡ ሆዱ፡ ጠገበ፤

፴፭፤አርኃወ፡መናሥግትየ፤
ቁልፌን፡ከፈተ፡ማለት፡አርበኞቼን፡ አጠፋ፤

ወአኅሠረኒ፡ውስተ፡ባቢሎን፤
በባቢሎን፡አጐሠቈለኝ፤

ትቤ፡እንተ፡ትነብር፤
ጠላት፡ጠፍቶላት፡በተድላ፡በደስታ፡ የምትኖር፡ጽዮን፡በባቢሎን፡አጐሠ ቈለኝ፡አለች፤

ወደምየኒ፡ላዕለ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ፋርስ፡ ትቤ፡ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌምም፡የደሜ፡ፍዳ፡በፋርስ፡ በሚኖሩ፡ሰዎች፡ላይ፡ነው፡አለች፤

፴፮፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ ብሔር፤
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡አለ፤

ናሁ፡አነ፡እኴንኖ፡ለገፋዒኪ፤
እነሆ ፡ እኔ ፡ የሚገፋሽን ፡ የሚበድ ልሽን፡እፈርድበታለሁ፡ማለት፡አጠ ፋዋለሁ፤

ወእትቤቀል፡በቀለኪ፤
በቀልሽን፡እከፈላለሁ፤

ወአነጽፋ፡ለባሕር፤
ባቢሎንን፡አጠፋታለሁ፤

ወእደመስሶ፡ለምዕላዲሃ፤
ከተማዋን፡አጠፋዋለሁ፤

፴፯፤ወትከውን፡ባቢሎን፡ለጼዋዌ፤
ባቢሎን፡ለምርኮ፡ትሆናለች፤

ወማኅደረ፡አክይስት፤
[illegible]

ወይትፋጸይዋ፡ህየ፤
በዚያ፡ያፏጩባታል፤

ወኢይነብርዋ፡እንከ፡ኅቡረ፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰዎች ፡ አንድነት፡ አይኖሩባትም፤

፴፰፤ ከመ ፡ አናብስት ፡ ይጥሀሩ ፡ ወይት ነሥኡ፤
እንደ ፡ አንበሳዎች ፡ ተነሥተው ፡ ይደነፋሉ፡ያገራሉ፤

ወከመ፡ዕጒለ፡አናብስት፡ይትአረወዩ፤
እንደ ፡ አንበሳዎች ፡ ወይፈን ፡ ይሸበራሉ፤

፴፱፤አሰትዮሙ፡ወአሰክሮሙ፡ከመ፡ይት ቈናደዩ፤
እንደ፡ተልባ፡ፍንጥር፡ፍንጥር፡ይሉ፡ ዘንድ ፡ የመቅሠፍቱን ፡ አረቂ ፡ አጠጥቼ፡አሰክራቸዋለሁ፤

ወይኑሙ፡ንዋመ፡ዘለዓለም፤
የዘለዓለም ፡ እንቅልፍን ፡ ያንቀላፉ ፡ ዘንድ፤

ወኢይነቅሑ፡እንከ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከእንቅልፋቸው ፡ አይነቁም ፡ ማለት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አያገኙም፡አለ፡እግዚአብሔር፤

፵፤ ወአወርዶሙ ፡ ከመ ፡ ይጥብሕዎሙ ፡ ከመ፡አባግዕ፤
እንደ፡በጎች፡ያርዷቸው፡ዘንድ፡አወር ዳቸዋለሁ፤

ወይእኅዝዎሙ፡ከመ፡ሐራጊት፤
እንደ፡ጊደሮች፡ይይዟቸዋል፤

ወከመ፡አባሕዝ፡ወመሐስዕ፤
እንደ ፡ ጠቦት ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ አውራዎች፡ይይዟቸዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፩፤በእፎ፡ተገምረት፡
ባቢሎን፡እንዴት፡ጠፋች፤
ወተእኀዘት፡ምክሐ፡ለኵሉ፡ምድር፡
የሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ መመኪያ ፡ ባቢሎን ፡
እንዴት፡በመከራ፡ተያዘች፤
እፎ ፡ ኮነት ፡ ባቢሎን ፡ ሙስንተ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ፡አሕዛብ፡
በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ባቢሎን ፡
እንዴት፡የጠፋች፡ሆነች፤

፵፪፤ዐርገት፡ባሕር፡ላዕለ፡ባቢሎን፡
ፋርስ፡ወደ፡ባቢሎን፡ዘመተች፤
በድምፀ፡ማዕበላ፡ደፈነታ፡
በኃያላኖቿ፡ሸፈነቻት፤

፵፫፤ወኮነ፡አህጉሪሃ፡ምድረ፡በድው፡
አውራጃዎቿ፡ምድረ፡በዳ፡ሆኑ፤
ወዐፀ፡ዘኢይነብሮ፡መኑሂ፡እምሰብእ፡
ከሰው ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ ማን ፡ የማይኖ
ርበት፡በረሃ፡ሆነ፤
ወኢየሐድሮ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ የማይኖርበት ፡ በረሃ ፡
ሆነ፤

፵፬፤ወእትቤቀል፡ላዕለ፡ኵሉ፡ባቢሎን፡
ባቢሎንን፡ሁሉ፡እበቀላለሁ፤
ወአቀይዓ፡እምአፉሃ፡ዘውኀጠት፡
የዋጠችውን ፡ ከአፏ ፡ አስተፋታለሁ ፡
ማለት፡የቀማችውን፡እንድትመልስ፡
አድርጋታለሁ፤
ወኢይትጋብኡ፡እንከ፡አሕዛብ፡ህየ፡
እንግዲህ፡ወዲህ፡አሕዛብ፡በዚያ፡አይ
ሰበሰቡም፤
ወአረፋተ፡ባቢሎን፡ይወድቁ፡
የባቢሎን ፡ ቅፅሮች ፡ ይወድቃሉ ፡
ማለት ፡ የባቢሎን ፡ አርበኞች ፡

፵፭፤ፃኡ፡እማዕከላ፡ሕዝብየ፡
ወገኖቼ፡ከመካከሏ፡ውጡ፤
ወአድኅኑ ፡ ነፍስክሙ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እመቅ
ሠፍተ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ ከሚያመጣው ፡
መቅሠፍት ፡ የተነሣ ፡ አንዱም ፡
አንዱም፡ሰውነታችሁን፡አድኑ፤

፵፮፤ወከመ፡ኢይድክም፡አልባቢክሙ፤
ልቡናችሁ፡እንዳይደክም፤
ወትፈርሁ ፡ እምሰሚዓ ፡ ዜናሃ ፡ ውስተ ፡
ምድር፡
በምድር ፡ ጥፋቷን ፡ ከመስማታችሁ ፡
የተነሣ ፡ የደስታ ፡ ድንጋፄ ፡ ትደነግጣ
ላችሁ፤
ወይመጽእ፡በዓመተ፡ዜናሃ፡
ዜናሃ ፡ ጥፋቷ ፡ በተደረገበት ፡ ዘመን ፡
ተድላ፡ደስታ፡ይመጣላችኋል፤
ወእምድኅሬሁ፡በዓመተ፡ተሰምዖታ፡
ጥፋቷንም ፡ ከሰማችሁበት ዘመን ፡
በኋላ፡ተድላ፡ደስታ፡ይመጣላችኋል፤
ወአመጽእ፡እምህየ፡ውስተ፡ምድር፡
በባቢሎን፡መከራን፡አመጣለሁ፤
ወዅነኔ፡ዲበ፡ኵነኔ፤
በመከራ፡ላይ፡መከራን፡አመጣለሁ፤

፵፯፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ
መዋዕል፡
እነሆ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ወራት፡ይመጣል፤
ወእትቤቀል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡
ግልፎ፡ባቢሎን፡
እግዚአ[illegible]የባቢሎን[illegible]ሞያት፡
[illegible]



ወኵሉ፡ምድራ፡ይየብስ፡
አገሯ፡ሁሉ፡ይጠፋል፤
ወኵሎሙ፡ቅቱላኒሃ፡ይወድቁ፡በማዕከሌሃ፡
በጦር፡ተወግተው፡የሞቱ፡አርበኞቿ፡
ሁሉ፡በመካከሏ፡ይወድቃሉ፡አለ፤

፵፰፤ ይትፌሥሑ ፡ ላዕለ ፡ ባቢሎን ፡
ሰማያት፡ወምድር፡
ልዑላኑ፡ትሑታኑ፡በባቢሎን፡ጥፋት፡
ደስ፡ይላቸዋል፤
ወኵሎሙ፡እለ፡ይነብርዋ፡
በነሱም፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ደስ፡
ይላቸዋል፤
እስመ ፡ እምሰሜን ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሃ ፡ እለ ፡
ያጠፍኡ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር ፡ የሚያጠፉ ፡ ሰዎች ፡
ከፋርስ ፡ ወደ ፡ እርሷ ፡ ይመጣሉ ፡
ብሏልና፤ምነው፡ፋርስማ፡ጽባሕ፡አይ
ደለችም ፡ ቢሉ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡
የሌለውን ፡ አለ ፤ ለአንዱ ፡ ጽባሕ ፡
ብትሆን፡ለአንዱ፡ሰሜን፡ናትና፤

፵፱፤ ወባቢሎንሂ ፡ ለድቀተ ፡ ቅቱላነ፡
እስራኤል፡
ባቢሎንም ፡ ከእስራኤል ፡ በሞቱ፡
ሰዎችና፤
ወለቅቱላነ፡ኵሉ፡ምድር፡
በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ በጦር ፡ ተወግተው፡
በሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ምክንያት ፡ ለጥፋት ፡
ትሆናለች፤

፶፤እለ ፡ ድኅንክሙ ፡ እመጥባሕት ፡ ፃኡ ፡
ወኢትቁሙ፤
ከሞት ፡ የዳናችሁ ፡ ሰዎች ፡ ውጡ፡
አትቁሙ፤
[illegible]

በሩቅም ፡ ያላችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡
በአምልኮት፡አስቡት፤
ወኢየሩሳሌምሃኒ፡ሐልዩ፡በልብክሙ፤
ኢየሩሳሌምንም፡በልቡናችሁ፡አስቡ፤

፶፩፤እፎ፡ኀሠርነ፡ወተኀፈርነ፤
እንዴት ፡ በመከራው ፡ ጐሰቈልነ ፡
እንዴትስ፡አፈርነ፤
እስመ፡ሰማዕነ፡ጽዕለተነ፡
ስድባችንን፡ሰምተናልና፤
ወከደነነ፡ኃሣር፡ገጸነ፤
ጕስቍልናም ፡ ፊታችንን ፡ ሸፍኖ
ናልና፡እንዴት፡አፈርነ፤
ወቦኡ ፡ ካልዕ ፡ ሕዝብ ፡ ውስተ ፡ መቅደስነ ፡
ቤተ፡እግዚአብሔር፤
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ወደ ፡
ቤተ፡መቅደሳችንም፡ሌሎች፡አሕዛብ፡
ገቡ፡(ገብተዋልና)፡ብትልም፤

፶፪፤በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ፡አለ፤
ናሁ፡ይመጽእ፡መዋዕል፤
እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፡
አለ፤
ወእትቤቀሎሙ፡ለግልፎዋት፤
ጣዖታቱን፡ተበቅዬ፡አጠፋቸዋለሁ፤
ወይወድቁ፡በኵሉ፡ምድር፡ቅቱላን፤
በጦር ፡ ተወግተው ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡
በሀገሩ፡ሁሉ፡ይወድቃሉ፤

፶፫፤ እስመ ፡ ለእመ ፡ ዐርገት ፡ ባቢሎን ፡
[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ባቢሎን ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ብትወጣ፤

ወእመሂ፡አጽንአት፡ነፍሳ፡በኃይል፤
ልቡናዋንም፡በኃይል፡ብታጸና፤

ይመጽኡ፡እምህየ፡እለ፡ይሜርውዋ፡ይቤ፡ እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡የሚያጠፏት፡ሰዎች፡ ከፋርስ፡ይመጣሉ፡ብሏልና፡በጦር፡ የተወጉ ፡ ሰዎች፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ፡ ይወድቃሉ፤

፶፬፤ቃለ፡ውውዓ፡ውስተ፡ባቢሎን፤
በባቢሎን፡የድንፋታ፡ቃል፡ይሰማል፤

ወዓቢይ፡ቅጥቃጤ፡ውስተ፡ምድረ፡ፋርስ፤
በፋርስም ፡ ሀገር ፡ ፅኑዕ ፡ መከራ ፡ ይደረጋል፤

፶፭፤ እስመ ፡ ሠረዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለባቢሎን፤
እግዚአብሔር ፡ ባቢሎንን ፡ አጥፍቷታልና፤

ወአጥፍአ፡እምኔሃ፡ቃለ፡ዓቢየ፤
ከእርሷም፡ የሚሰማ ፡ ቃልን ፡ አጥፍቷልና፤

ወድምፀ፡ማዕበሎሙ፡ከመ፡ማይ፡ብዙኅ፤
የማዕበላቸው ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሀ፡ተሰማ፤

ወሀቡ፡ድምፀ፡ቃሎሙ፡ብዙኅ፤
ብዙ የሆነ ፡ የቃላቸውን ፡ ድምፅ ፡ ሰጡና፡እስመ፡ሠረዋ፡ብለህ፡እሠር፤

፶፮፤መጽአ፡ኃሣር፡ለባቢሎን፤
በባቢሎን፡ጉስቁልና፡መጣባት፤

ተሠግሩ፡መስተቃትላኒሃ፤
አርበኞቿ፡ጠፉ፤

ወተሠብረት፡ቀስቶሙ፤
ቀስታቸው፡ተሠበረች፤

እስመ፡እግዚአብሔር፡ተበቀሎሙ፤
እግዚአብሔር፡ተበቅሏቸዋልና፤

ወእግዚአብሔር፡ፈደዮሙ፤
እግዚአብሔር፡ፍዳውን፡አምጥቶባቸዋልና፡ተሠብረት፡ብለህ፡እሠር፤

፶፯፤ወአሰክሮሙ፡ስካረ፡ለመኳንንቲሃ፤
መኳንንቶቿን፡የመቅሠፍቱን፡አረቄ፡ አጠጥቼ፡አሰክራቸዋለሁ፤

ወለጠቢባኒሃ፤
የጦር ፡ ጥበብ ፡ እናውቃለን ፡ የሚሉትን፤

ወለነገሥታቲሃ፤
ነገሥታቷን፤

ወለዓቃብያኒሃ፤
ዘበኞቿን፤

ወለኃያላኒሃ፤
ኃያላኖቿን ፡ የመቅሠፍቱን ፡ አረቄ፡ አጠጥቼ፡አሠክራቸዋለሁ፤

ወይነውሙ፡ንዋመ፡ዘለዓለም፤
የዘለዓለም፡እንቅልፍን፡ያንቀላፋሉ፤

ወኢይነቅሑ ፡ እንከ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፤
ንጉሥ፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ስሙ፤
ስሙ፡ሁሉን፡የሚገዛ፡ንጉሥ፡እግዚአብሔር ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ፡ እስከ ፡ ዕለተ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ አይነሡም ፡ ብሏልና፤

፶፰፤ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፀባኦት፤
አቸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤

ርኅብት፡አረፍተ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን፡ቅጽር፡ሰፊ፡ነበረች፤

ይነሥእዋ፡ወያንህልዋ፤
ዙሪያዋ...



ወያውዕይዎ፡ለዶዴሃ፡ዓበይት፡በእሳት፤
ታላላቆች፡ሰዎች፡ደጃፏን፡በእሳት፡ ያቃትሉታል፤

ወይፃምዉ፡አሕዛብ፡ለከንቱ፤
አሕዛብ፡ለከንቱ፡ነገር፡ይደክማሉ፤

ወየኃልቁ፡ቀደምቶሙ፡ለአሕዛብ፡በእሳት፤
ከአሕዛብ ፡ አስቀድመው ፡ የነገሡ፡ ነገሥታቱ፡በጦር፡ይጠፋሉ፤

## ጉባዔ፤

፶፱፤ ነገር ፡ ዘአዘዞ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ፡ ለሴርያ፡ወልደ፡ኔርያ፤
ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ሴርያን፡ያዘዘው፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ወልደ፡ማሴው፤
ኔርያን፡የማሴው፡ልጅ፡አለው፤

አመ ፡ ሖረ ፡ እምኀበ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ፡ውስተ፡ባቢሎን፤
ሴዴቅያስን ፡ የግብር ፡ አግቢ ፡ አለቃ፡ አድርጎ፡ለናቡከደነፆር፡ግብር፡አግባ፡ ብሎ ፡ ሰድዶታል ፤ አንድም ፡ ለእለ ፡ ኢኮንያን፡ስንቅ፡ሠጥቶ፡ሰድዶታል፤

አመ ፡ ራብዕ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሴዴቅያስ፤
ዘአዘዞ፡አመ፡ራብዕ፡አመ፡ሖረ፡አመ፡ ራብዕ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ፡በአራተኛው፡ዘመን፡የኔርያ፡ ልጅ ፡ ሴርያን ፡ ነቢዩ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘው ፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው ፤ አንድም ፡ አመ ፡ ሖረ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ ፡ ባራተኛው፡ ዘመን ፡ ከይሁዳው ፡ ንጉሥ፡ ከሴዴቅያስ ፡ ተልኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን፡በሔደ፡ጊዜ፡ያዘዘው፡ነገር፡ ይህ፡ነው፤

ወሴርያ፡መልአ...
...ቢል፡ነው፤

ሴርያም፡የእጅ፡መንሻ፡አለቃ፡ነው፤ አንድም፡መልአከ፡ጋድ፡ቢል፡የነገደ፡ ጋድ፡ቤት፡አለቃ፡ነው፤

፷፤ጸሐፈ፡ኤርምያስ፡መጽሐፈ፡ውስተ፡ መጽሐፍ፡፩ዱ፡ኵሎ፡እኪተ፡ዘይመጽእ፡ ውስተ፡ባቢሎን፤
ኤርምያስ፡በባቢሎን፡የሚመጣውን፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከግብሩ ፡ ዱብዳቤ፡ጋራ፡አንድ፡አድርጎ፡ጻፈው፤ ውስተ፡ፈለገ፡ኤፍራጥስ፡ይለዋል፡ የግብሩንስ፡ዱብዳቤ፡አይጥለውም፡ ብሎ፡አንድ፡አድርጎ፡አይጽፈውም፡ ብትልም፡ውስተ፡መጽሐፈ፡፩ዱ፡ ይላል ፤ በአንድ ፡ በሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈው፤

ወኵሎ፡ዘንተ፡ነገረ፡ዘተጽሕፈ፡በእንተ፡ ባቢሎን፤
ስለ፡ባቢሎን፡የተጻፈውን፡ይህንን፡ ሁሉ፡ነገር፡ጻፈው፤

፷፩፤ወይቤሎ፡ኤርምያስ፡ለሴርያ፤
ኤርምያስ፡ሴርያን፡እንዲህ፡አለው፤

አመ፡ቦእከ፡ባቢሎን፡ወርኢከ፤
ወደ፡ባቢሎን፡ገብተህ፡ባየህ፡ጊዜ፤

አንብብ፡ኵሎ፡ዘንተ፡ነገረ፤
ይህንን፡ሁሉ፡ነገር፡አንብብ፤

፷፪፤ወበል፡አንተ፡እግዚአ፡ትቤ፡ከመ፡ ትሥርዎሙ ፡ ለኵሉ ፡ በሐውርት፡ ከመ ፡ ኢይንበሮ፡ሰብእ፡ትሠርዎሙ፤
ሰዎች ፡ እንዳይኖሩባት፡ እንድታጠፋቸው፡ተናግረሃልና፤

ወኢእንስሳ፤
ከብት ፡ እንዳይኖርባት ፡ ሀገሮችን ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ አቤቱ ፡ ...ጥፋቸው፡አልክ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይማስኑ፡ለዓለም፤
ለዘለዓለሙ፡ይጠፋሉ፡ብለሃልና፤

፷፫፤ወአንቢበከ፡ውእተ፡መጽሐፈ፤
ይህንን፡ደብዳቤ፡ካነበብክ፡በኋላ፤

ተአሥር፡ዕብነ፡ውስቴታ፤
ደንጊያ፡ጨምረህ፡አሥረህ፤

ወትዌርዋ፡ውስተ፡ፈለገ፡ኤፍራጥስ፤
በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ወርውረህ ፡ ጣላት፤

፷፬፤ወትብል፡ከመዝ፡ትሰጠም፡ባቢሎን፤
ያች ፡ ስትጠፋ ፡ ባቢሎን ፡ ትጠፋለች፡ ብለህ፡ተናገር፤አንድም፡ትጥፋ፤

ወኢትትነሣእ፡እንከ፡እምገጸ፡እኩይ፡ዘአነ፡ አመጽእ፡ላዕሌሃ፤
እኔ ፡ ከማመጣው ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ የተነሣ፡እንግዲህ፡ወዲህ፡አትድንም፤

እስከ፡ዝየ፡ነገረ፡ኤርምያስ፤
ኤርምያስ፡እስከዚህ፡አንቀጽ፡ድረስ፡ የባቢሎንን፡ጥፋት፡ተናገረ፤አንድም፡ እስከ፡ዝ፡ቢል፡እስከ፡እንደዚህ፡ያለ፡ ጥፋት፡ተናገረ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፪ ፡

፩፡ወልደ፡፳፡ወ፩ዱ፡ዓመት፡ሴዴቅያስ፡ አመ፡ነግሠ፤
ሴዴቅያስ፡በነገሠ፡ጊዜ፡የሀያ፡አንድ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ሴዴቅያስን ፡ ኤርምያስ ፡ ቢመክረው፡ ቢያስተ ምረው ፡ ያልሰማ ፤ አልሰማም፡ ያለ ፡ ሕፃን፡ ሆኖ ፡ አደለም ፤ በእምቢታው ፡ ነው፡ለማለት፡ዘመን፡ቆጠረ፤

ወ፲ቱ፡ወ፩ደ፡ዓመተ፡ነግሠ፡በኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት፡ነገሠ፤

ወስማ፡ለእሙ፡አሚጠል፡ወለተ፡ኤርምያስ፡ እምሎምና፤
ከሎምና ፡ ወገን ፡ የተወለደ ፡ የኤር ምያስ፡ልጅ፤ሌላ፡ኤርምያስ፡ነው፤

፪፤ወገብረ፡እኩየ፡በቅድመ፡አዕይንቲሁ፡ ለእግዚአብሔር፤
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገርን፡ አደረገ፤

ከመ፡ኵሉ፡ዘገብረ፡ኢዮአቄም፤
ኢዮአቄም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደሠራ ፡ ክፉ፡ሥራ፡ሠራ፤

፫፤ እስመ ፡ መዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ፡ በኢየሩሳሌም፡ወበይሁዳ፤
በኢየሩሳሌምና፡በይሁዳ፡መዓተ፡እግ ዚአብሔር፡ታዝዞአልና፤

እስከ፡ገደፎሙ፡እምቅድመ፡ገጹ፤
ከባለሟልነቱ፡እስኪለያቸው፡ድረስ፤

ወዓለዎ፡ሴዴቅያስ፡ለንጉሠ፡ባቢሎን፤
ሴዴቅያስ ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ከዳው፤

፬፤ ወኮነ፡በታስዕ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፤
ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ ፡ በዘጠነኛው፡ ዓመት፤

በአሥር፡ወርኅ፤
በአሥረኛው፡ወር፡በጥር፤

ወበአሥር፡ሠርቅ፤
ጥር፡በባተ፡በአሥር፡ቀን፤

በጽሐ፡ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ደረሰ፤

ውእቱ፤
እርሱ፤



ወኵሉ፡ኃይሉ፡ላዕለ፡ኢየሩሳሌም፤
ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ፡ ደረሱባት፡ማለት፡ዘመቱባት፤

ወተዓየነ፡ላዕሌሃ፤
በእርሷ፡ላይ፡ሠፈረባት፤

ወሐፀራ፤
በጦር፡አጠራት፤

ወነደቀ፡ተባዕተ፡በዓውዳ፤
በኃያላኑ ፡ ከበባት ፤ አንድም ፡ መንገኒቀ፡ይላል፤በነፍጥ፡ከበባት፤

፭፤ ወተፀወነት ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡ አሥሩ፡ ወአሐዱ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለሴዴቅያስ፤
ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ነገሠበት ፡ እስከ ፡ አሥራ፡አንድ፡ዘመን፡ድረስ፡ሀገሪቱ፡ በጦር፡ተከበበች፤

፮፤በራብዕ፡ወርኅ፤
ባራተኛው፡ወር፡በሐምሌ፤

አመ፡ተሱዑ፡ለሠርቅ፤
ሐምሌ፡በባተ፡በዘጠነኛው፡ቀን፤

ጸንዓ፡ረሀብ፡በሀገር፤
በከተማ፡ረሀብ፡ጸና፤

ወአልቦ፡እክል፡ለሕዝበ፡ምድር፤
ለሕዝቡ ፡ የሚመገቡት ፡ እህል ፡ አልነ በራቸውም፤

፯፤ወተገፍትዓት፡ሀገር፤
እኩሉ ፡ እንሸሽ ፤ እኩሉ ፡ እንዋጋ ፤ እኩሉ ፡ እንግባ ፤ እኩሉ ፡ አንዋጋ ፡ በማለት፡ተለያዩ፤

ወኵሉ፡ሰብእ፡መስተቃትላን፡ጐዩ፤
አርበኞች፡ሰዎች፡ሁሉ፡ሸሹ፤

ወወጽኡ ፡ እምሀገር ፡ በሌሊት ፡ ፍኖተ ፡ አንቀጽ፡ማዕከለ፡ጥቅም፡ዘማዕከለ፡አረፍተ፡ ገነተ፡ንጉሥ፤
የንጉሡ ፡ ተክል ፡ ባለበት ፡ ቅጽር ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ በግንቡ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በር ፡ በሌሊት ፡ ከከተማው ፡ ሸሹ ፤ እንደ ፡ ዓሄ ፡ ቢትና ፡ እንደ ፡ ዓደባባይ፡ኢየሱስ፤

ወከለዳውያን፡አገቱ፡ሀገረ፤
የከለዳውያን ፡ ሰዎችም ፡ አገሪቱን ፡ ከበቡ፤

ወሖሩ፡ፍኖተ፡ዐረብ፤
በምዕራብ ፡ የሚወስደውን ፡ ጐዳና ፡ ይዘው፡ሔዱ፤

፰፤ ወዴገንዎ ፡ ኃይለ ፡ ከለዳውያን ፡ ድኅሬሁ፡ለንጉሥ፤
የከለዳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ንጉሡን ፡ በኋላው፡በኋላው፡ተከተሉት፤

ወረከብዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በዐራቦት፡ ዘኢያሪኮ፤
ዐራቦት ፡ ዘደቂቀ ፡ አሞን ፡ አለና ፡ ዘኢያሪኮ ፡ አለ ፤ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስን፡ በዐራቦት፡ዘኢያሪኮ፡አገኙት፤

ወኵሎሙ፡ኃይሉ፡ተዘርዉ፡እምኔሁ፤
ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ተለይተው፡ ተበተኑ፤

፱፤ወአኀዝዎ፡ለንጉሥ፤
ንጉሡን፡ይዘው፤

ወወሰድዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ውስተ ፡ ዴብላታ፡በምድረ፡ኤማት፤
በኤማት ፡ ዕፃ ፡ በዴብላታ ፡ ወደ ፡ አለ፡ ወደ፡ባቢሎን፡ንጉሥ፡ወሰዱት፤

ወተናገሮ፡ኵነኔ፤
እችላለሁ ፡ አትል ፡ አትዋጋ ፤ አልችልም፡አትል፡አትገብር፡አለው፤ ይህስ ፡ ባልችል ፡ ይለዋል ፡ ብሎ ፡ ፍትሐ፡ ይላል ፤ ከሰው ፡ መርጦ ፡ ለሹመት ፡ ከዕንጨት ፡ መርጦ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለታቦት፡እንዲሉ፡መርጬ፡ብሾምህ፡
ምነው፡ከዳኸኝ፡ተፋረደኝ፡አለው።

፲፤ ወረገዞሙ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ለደቂቀ፡
በቅድመ፡አዕይንቲሁ፤
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ልጆቹን፡በፊቱ፡
እየወጋ፡ጣላቸው።
ወለኵሎሙ፡መላእክተ፡ይሁዳ፡ቀተሎሙ፡
በዴብላታ፤
የይሁዳን፡አለቆች፡ሁሉ፡በዴብላታ፡
ገደላቸው።

፲፩፤ወአውጽአ፡አዕይንቲሁ፡ለሴዴቅያስ፡
ክፉ፡ባየበት፡አይኑ፡በጎ፡አይይበት፡
ብሎ፡ዓይኑን፡አጠፋው።
ወአሠሮ፡በመዋቅሕት፤
በእግር ፡ ብረት ፤ አንድም ፡ በድን
ብኩል፡ ይላል ፤ በእግር ፡ ብረት ፡
አሠረው ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ የፈረስ ፡
ጭራ፤ በአንድ ፡ እጁ ፡ ቅል ፡
አስጨብጦ፡ራቁቱን፡አድርጎ፡ፋርስ፡
አውርዶታል ፤ ከዚያም፡ ባቁላ፡
እየፈጨ ፡ ሙቷል ፤ በሞተም ፡ ጊዜ ፡
ከወፍጮ፡ሥር፡ተቀብሯል።
ወወሰዶ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ውስተ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ወሰደው።
ወወሀቦ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡እስከ፡አመ፡
ሞተ፤
እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡
አኖረው።

፲፪፤ ወበኃምስ፡ወርኅ፤
በአምስተኛው፡ወር፡በነሐሴ።
አመ፡አሡሩ፡ለሠርቅ፤
ነሐሴ፡በባተ፡በአሥር፡ቀን።
ወይእቲ፡ዓመት፡፲ቱወ፱ቱ፡ዓመት፡ዘነግሠ፡
ናቡከደነፆር፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ይህቺውም ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡
ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር ፡ የነገሠባት ፡
አሥራ፡ዘጠነኛዪቱ፡ዘመን፡ናት።
መጽአ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፤
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርድን፡መጣ።
ዘይቀውም፡ቅድመ፡ገጸ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡
ውስተ፡ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡
ፊት ፡ በባለሟልነት ፡ የሚቆም ፡
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡መጣ።

፲፫፤ ወአውዓየ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፤
ቤተ፡መቅደስን፡በእሳት፡አቃጠለ።
ወቤተ፡ንጉሥ፤
የንጉሡንም፡ቤት።
ወኵሎ፡አብያተ፡ኢየሩሳሌም፤
የኢየሩሳሌምን፡ቤቶች፡ሁሉ።
ወኵሎ፡አብያተ፡ዓበይት፡አውዓየ፡በእሳት፤
የመኳንንቱን፡ቤቶች፡ሁሉ፡በእሳት፡
አቃጠለ።

፲፬፤ ወኵሎ፡ዐረፍተ፡ኢየሩሳሌም፤
የኢየሩሳሌምን፡ቅጽር፡ሁሉ፡በእሳት፡
አቃጠለ።
ወነሠቱ፡ጥቅማ፡ኃይለ፡ከለዳውያን፡ዘሊቀ፡
መበስላን፤
ያዛገሮች ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ ናቡዛር
ዳንን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ የከለዳ
ውያን ፡ ሠራዊትም ፡ ግምቧን ፤
አፈረሱ።

፲፭፤ ወአምጽአ፡ሊቀ፡መበስላን፡እምነ
ዳያን፡ሕዝብ፤
የአዛገሮች፡አለቃ፡ከድሆች፡ወገኖች፤
አመጣ።
ወተረፈ፡ሕዝብ፡እለ፡ተርፉ፡ውስተ፡ሀገር፤
በከተማ፡ከቀሩ፡ወገኖች፡አመጣ።



ወእለ፡ገብኡ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
ወደ፡ባቢሎን፡ንጉሥ፡የተመለሱትን።
ወእለ፡ተርፉ፡ሕዝብ፡እምዘ፡አፍለሰ፡ናቡዛ
ርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፤
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡ከማረ
ካቸው፡የቀሩትን፡አመጣ።

፲፮፤ ወእምነዳያነ፡ምድር፡አትረፈ፡ናቡ
ዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፤
የአዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡
ከምድር፡ድሆች፡አስቀረ።
ለሐረስት፤
አራሾች፡ሊሆኑ።
ወለዐቀብተ፡ወይን
ወይን፡ሊያርሙ፡ሊኮተኩቱ።

፲፯፤ ወአዕማደ፡ብርት፡ዘቤተ፡እግዚአ
ብሔር፤
የቤተ፡እግዚአብሔርን፡የብርቱን፡
አዕማድ።
ወድዶነሂ፤
ድፍን፡ገበታውን።
ወባሕረሂ፡ዘብርት፡ዘቤተ፡እግዚአብሔር፡
ቀጥቀጡ፡ፋርስ፤
በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡
ባሕረ፡ ብርትን ፡ የፋርስ ፡ ሰዎች ፡
ሠብረው።
ወነሥኡ፡ኵሎ፡ብርተ፡ወወሰዱ፡ባቢሎን፤
ብርቱን፡ሁሉ፡ይዘው፡ወደ፡ባቢሎን
ወሰዱ።

፲፰፤ ወጽሕርታተ፤
ጋኖችን፤
ወኮኮማተ፤
አመድ፡የሚያፈሱባቸው፡እንቅቦችን።
ወፍያላተ፤
ጣሳዎችን፤
ወአጽሕልተ፤
ሥልስ፡የሚሰሉባቸው፡ወጭቶችን።
ወኵሎ፡ንዋየ፡ብርት፡እለ፡ይትለአኩ፡ቦሙ፤
የሚያገለግሉባቸው፡የብርቱን፡ዕቃ
ዎች፡ሁሉ።
ነሥኡ፤
ማርከው፡ወሰዱ።

፲፱፤ መናብርተ፤
ማዕጠንቶችን፤
ወመሳውደ፤
መጫሪያውን።
ወፍያላተ፤
ጣሳ፤
ወጽሕርታተ፤
ጋን፤
ወመራናተ፤
መቅረዞችን፡ተቅዋምን፡ብትልም።
ወአጽሕልተ፤
ሥልስ፡የሚሠልሱበትን፡ወጭት።
ወመዳምሃ፡ዘወርቅ፡ወዘብሩር፡ነሥአ፡ሊቀ፡
መበስላን፤
የወርቅ፤የብር፡የሚሆነውን፡ማንካ፡
የወርቅ፡ዕቃ፡የሚሆነውን፡ወርቁን፡
የብር፡ዕቃ፡የሚሆነውን፡ብሩን፡
ብትልም፤የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛ
ርዳን፡ማርኮ፡ወሰደ።

፳፤አዕማደ፡ክልዔተ፤
ሁለቱን፡አዕማድ፤
ወባሕረ፡አሐተ፤
አንዲቱን፡ባሕረ፡ብርትን፤
ወአልሕምተ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡ ዘብርት ፡
ዘመትሕተ፡ሜኮኖት፤
ከጋኑ፡በታች፡ያሉ፡የብርት፡የሚሆኑ፡
አሥራ፡ሁለቱን፡አልሕምት።
ዘገብረ፡ንጉሥ፡ሰሎሞን፡ለቤተ፡እግዚአ
ብሔር፤

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ለቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡የሠራው፤
ወአልቦ፡መድሎት፡ለእሉ፡ንዋያተ፡ብርት፤
የብርት ፡ ለሚሆኑ ፡ ለነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡
ሚዛን፡አልነበራቸውም፤

፳፩ ወአዕማድ ፡ ፲ቱወ፰ቱ ዕመት ፡
ቆሙ፡ለ፩ዱ፡ዓምድ፡
ቢያሳዝነው ፡ ይሠራል ፤ አዕማድም ፡
የአንዱ ፡ ዓምድ ፡ ቁመቱ ፡ አሥራ ፡
ስምንት፡ክንድ፡ነው፤
ወአምጣን፡ዘየዓውዶ፡፲ቱ፡ወ፪ቱ፡እመት፤
ዙሪያው፡አሥራ፡ሁለት፡ክንድ፡ነው፤
ወግዘፉ፡አርባዕ፡አፃብዕ፡ዘከርካዕ፤
የለውዝ ፡ የገውዝ ፡ አበባ ፡ የመሰለ ፡
ያለበት ፡ ግዘፉ ፡ ድንዳኔው ፡ ብትልም ፡
ጋት ፡ ነው ፡ አራት ፡ ጣት ፡ ነው ፡
ብትልም፡ይሆናል፤

፳፪ ወኮታሪት፡ላዕሌሁ፡ዘብርት፤
በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ድፍን ፡ ገበታ ፡
የብርት፡ነው፤
ወቆሙ፡ለኮታሪት፡፩ዱ፡
የአንዱ፡ድፍን፡ገበታ፡ቁመቱ፡
ኃምስ፡በዕመት፤
አምስት፡ክንድ፡ነው፤
ወመሥገርት፤
የተበሳሳ፡ሐብል፤
ወሮማናት፡ላዕለ፡ኮታሪት፡የዓውድ፤
በድፍኑ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡
ሮማናቶች፡ሻኩራዎች፡አሉ፤
ወኵሉ፡ዘብርት፤
ሁሉም፡የብርት፡ናቸው፤
ወከማሁ፡ለዓምድ፡ካልዕ፤
የሁለተኛውም ፡ ዓምድ ፡ ቁመቱ ፡
አሥራ፡ስምንት፡ክንድ፡ነው፤
ወሮማናት፤
ዑመአ ፡ የማየሰሙ ፡ ሮማኖቶችም ፡

፳፫ ወኮኑ ፡ ሮማናት ፡ ፺ወ፮ቱ ፡ እለ ፡
ይነፍሑ፡በንፍሐተ፡ነፋሳት፤
ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ ድምፅ ፡
የሚያሰሙ ፡ ሮማናቶች ፡ ዘጠና ፡
ስድስት ፡ ናቸው ፤ መላው ፡ ሁለት ፡
መቶ፡ ናቸው ፤ ኃምሳውን ፡ ድፍን ፡
ኃምሳውን ፡ የሚጮኽ ፡ አድርጎ ፡
በአንዱ ፡ መርገፍ ፡ አድርጎበታል ፡
ዝቅ፡ ብሎ ፡ እንደዚሁ ፡ አንድ ፡
መርገፍ፡ አድርጓል ፤ መቶ ፡ ነው ፤
አራቱን ፡ አጉደለ ፡ ሁለቱን ፡
በኃምሳው ፤ ሁለቱን ፡ በኃምሳው ፡
እያካፈለ ፡ እንደመቁጠሪያ ፡ አድርጎ
ታልና፡እንዲህ፡አለ፤
ወኵሉ ፡ ሮማናት ፡ ፻ ት ፡ ላዕለ ፡ መሥገርት፡
ዘየዓውድ፤
በተበሳሳው ፡ ገበታ ፡ የሚዞሩ ፡
ሮማናት፡ ሻኩራዎች ፡ መቶ ፡ ናቸው፤
አራት፡መቶም፡ይላሉ፤

፳፬ ወነሥአ፡ሊቀ፡መበስላን፡ለሴርያ፡
ዓቢይ፡ካህን፤
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡ደጉን፡
ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሴርያን ፡ ማርኮ ፡
ወሰደው፤
ወለሶፎንያስ ፡ ካህን ፡ ዘእምታሕቴሁ ፤
ከእርሱ፡በታች፡የሚያገለግል፡ሶፍንያ
ስንም፡ወሰደው፤
ወለ፫ቱ፡አቀብተ፡አናቅጽ፤
ሦስቱን ፡ በር ፡ ጠባቆችም ፡ ማርኮ ፡
ወሰዳቸው፤

፳፭ ወእምሀገር፡ነሥአ፡አሐደ፡ሕፅወ፤
ከከተማ፡አንድ፡ባለሟል፡ወሰደ፤
ዘኮነ፡ጸሐፌ፡ለዕለ፡ዕደው፡ፀብእ፤
ሰልፍ ፡ በ...



ወ፯ተ፡ዕደወ፡እለ፡ይሬእዩ፡ገጸ፡ንጉሥ፤
የንጉሡን ፡ ፊት ፡ የሚያዩ ፡ ሰባቱን ፡
ሰዎች፡ማርኮ፡ወሰደ፤
እለ፡ተረክቡ፡ውስተ፡ሀገር፤
በከተማ፡የተገኙ፤
ወጸሐፌ ፡ መልአከ ፡ ኃይሎሙ ፡ ለሕዝበ ፡
ምድር፤
በሀገሩ፡ሕዝብ፡ላይ፡ባሉ፡በሠራዊቱ፡
ላይ ፡ የተሾመ ፡ የቢትወደዱን ፡
ጸሐፊም፡ወሰደ፤
ወ፷፡ዕደወ፡እምሕዝበ፡ምድር፤
በሀገር ፡ ካሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ ለይቶ ፡ ስሳ ፡
ሰዎችን፡ወሰደ፤
እለ፡ተረክቡ፡ውስተ፡ሀገር፤
በከተማ፡የተገኙትን፤

፳፮ ወነሥአሙ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ሊቀ ፡
መበስላን፤
ያዛገሮች ፡ አለቃ ፡ ናቡዛርዳን ፡ ማርኮ ፡
ወሰዳቸው፤
ወነሥአሙ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘባቢሎን ፡
ዴብላታ፤
በዴብላታ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ንጉሥ፡ወሰዳቸው፤

፳፯ ወቀተሎሙ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፤
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ገደላቸው፤
ወሞቱ፡በዴብላታ፡በምድረ፡ኤማት፤
በኤማት ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡
በዴብላታ፡ሞቱ፤
ወአፍለሶ፡ለይሁዳ፡እምነ፡ምድሩ፤
ይሁዳንም፡ከሀገሩ፡ማረከው፤

፳፰ ዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ ዘአፍለሰ ፡ ናቡከደ
ነፆር፡በሳብዕ፡ዓመተ፡አይሁድ፤
አይሁድ ፡ አንድ ፡ ዓመተ ፡ ኀድገት ፡
በጀመሩ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ናቡከ
ደነፆር ፡ የማረከው ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ ነው ፤
የማረከው ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብትል ፤
... ነው ...

ሠላሳ፡ምእት፡እሥራ፡ወሠለስቱ፤
አንድ ፡ ዓመተ ፡ ኀድገት ፡ በተጀመረ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ናቡከደነፆር ፡
የማረካቸው ፡ አይሁድ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡
ከሃያ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፤ ሳብዕ ፡ ያለው ፡
ወአመ ፡ ራብዕ ፡ ዓመተ መንግሥቱ ፡
ለኢዮአቄም ፡ ይእቲኬ ፡ ቀዳሚተ ፡
መንግሥቱ፡ለናቡከደናፆር፡ይለዋል፤
የኤልያቄም ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ይቀረዋል ፤ ሰባቱ ፡ ሲፈጸም ፡ በኢኮ
ንያን ፡ ተማርከዋልና ፤ አንድም ፡
በሳምን ፡ ቢል ፡ የኢኮንያን ፡ ሦስቱ ፡
ወር፡ተጀምሯልና፤

፳፱ በዓመት፡፲ወ፰ቱ፡ዘናቡከደነፆር፤
ናቡከደነፆር፡በነገሠ፡በአሥራ፡ስምን
ተኛው፡ዘመን፤
እምኢየሩሳሌም ፡ ነፍሰ ፡ አይሁድ ፰ቱ ፡
፻፴ወ፪ቱ፤
ከኢየሩሳሌም ፡ የተማረኩ ፡ አይሁድ ፡
ስምንት፡መቶ፡ሠላሳ፡ሁለት፡ናቸው፤
አሥራ፡ስምንት፡ያለው፡የኤልያቄም፡
ሰባት፡ዓመት፤የሴዴቅያስን፡አሥራ፡
አንድ፡ቢገጥሙት፡አሥራ፡ስምንት፡
ይሆናል ፤ አንድም ፲ወ፱ቱ ፡ ቢል ፡
በሐምሌ ፡ ነው ፡ የማረከው ፤ ዘመነ ፡
መንግሥቱ ፡ የነገሠበት ፡ ንጉሠ ፡
ነገሥት ፡ የሆነበት ፡ በነሐሴ ፡ ነው ፤
ቤተ፡ መቅደስ ፡ የተቃጠለበት ፤
የእርሱ፡ መንግሥት ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡
ይሆናልና ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ቢል ፡ እነርሱን ፡
ማርኮ ፡ ከሀገሩ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡
ተቀምጦ፡ኑሮ፡መጥቷልና፤

፴ በዓመት፡እሠርቱ፡ወተሥአቱ፡ዘናቡ
ከደነፆር፤
ናቡከደነፆር ፡ በነገሠ ፡ በአሥራ ፡
ዘጠኝ፡ዘመን፤

www.ethiopianorthodox.org

አፍለሰ፡ናቡዛርዳን፡ሊቀ፡መበስላን፡ነፍሰ፡ አይሁድ፡
የአዛገሮች፡አለቃ፡ናቡዛርዳን፡የአይ ሁድን፡ወገኖች፡ማረከ፤

፯፻፡፵ወ፭፡
የተማረኩትም፡ሰባት፡መቶ፡አርባ፡ አምስት፡ናቸው፤

ወኵሉ፡ነፍስ፡፵፻ወ፮፻፡
መላው፡አራት፡ሺህ፡ከስድስት፡መቶ፡ ናቸው፤

፴፩፤ ወኮነ፡በ፴ወ፯ቱ፡ዓመት፡እምዘ ፈለሰ፡ኢኮንያን፡ንጉሠ፡ይሁዳ፡
የይሁዳው፡ንጉሥ፡ኢኮንያን፡በነገሠ፡ በሠላሳ፡ስድስት፡ዘመን፡እንዲህ፡ ሆነ፤ ሠላሳ፡ወስድስቱ፡ያለው፡ናቡከ ደነፆር፡ንጉሠ፡ነገሥት፡የሆነበት፡ ሀያ፡ አምስት፡ዘመን፡የሴዴቅያስ፡ አሥራ፡አንድ፡ይህንን፡ቢገጥሙት፡ (ቢደምሩት)፡ሠላሳ፡ስድስት፡ያለው፡ ይህንን፡ነው፤ ሠላሳ ወ፯ቱ፡ቢል፡የዮ ልማሮዴቅ፡ተጀምሯልና፤

በ፲ወ፪ቱ፡ወርኅ፡
በአሥራ፡ሁለተኛው፡ወር፡ በመጋቢት፡

አመ፡፳ወ፭፡ለወርኅ፡
መጋቢት፡በባተ፡በሀያ፡አምስተኛው፡ ቀን፤

ነሥአ፡ኢዮልማሮዴቅ፡ንጉሠ፡ባቢሎን በዓመተ፡መንግሥቱ፡ለኢኮንያን፡ንጉሠ፡ ይሁዳ፡
ኢዮልማሮዴቅ፡በነገሠ፡በመጀመ ሪያው፡ዘመን፡የይሁዳው፡ንጉሥ፡ኢኮ ንያንን፡አመጣው፤ናቡከደነፆር፡ሰባት፡ ዓመት፡እሪያ፡ሆኖ፡ኖረ፡ሆኖ፡ሳለ፡ ብትልም፡ኢዮልማሮዴቅ፡ምስለኔ፡ ሁኖ፡ሲገዛ፡ኖረ፡ከተመለሰ፡በኋላ፡ እንግዲህ፡ወዲህ፡መንግሥት፡ቀም ሲልና፡መንግሥት፡ያፋልሳል፡ብሎ፡ ብትልም፡ያውከኛል፡ብሎ፡አሥሮት፡ ሳለ፡ኢኮንያንን፡ያጫውተው፡ነበር፤ ፈጣሪያችንን፡በድለን፡ቀረብን፡ እንጂ፡መንግሥት፡ክህነት፡ሰጥቶን፡ ነበር፡እያለ፡ኋላ፡ሲነግሥ፡ ለሥልጣን፡አብቅቶታል፤

ወአውጽኦ፡እምቤተ፡ሞቅሕ፡
ከግዞት፡ቤት፡አወጣው፤

፴፪፤ ወተናገሮ፡ሠናየ፡
በጎ፡ነገር፡ተናገረው፤

ወረሰዮ፡መንበሮ፡መልዕልተ፡መንበረ፡ መንግሥት፡እለ፡ምስሌሁ፡
ዙፋኑንም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ ከሚቀመጡ፡ ነገሥታት፡ዙፋን፡ በላይ፡አደረገው፤

፴፫፤ ወወለጠ፡ልብሰ፡ተሞቅሖቱ፡
የግዞት፡ቤት፡ልብሱን፡ለወጠለት፤

ወበልዓ፡በቅድሜሁ፡ኅብስተ፡ዘልፈ፡በኵሉ መዋዕለ፡ሕይወቱ፡
ባለ፡በዘመኑ፡ሁሉ፡ዘወትር፡በፊቱ፡ ግብር፡ይበላ፡ነበር፤

፴፬፤ ወፈተቶ፡ሎቱ፡ፍተ፡ዘዘልፍ፡
የዘወትር፡ድርጎ፡ዳረገው፤

ወተውህበ፡ሎቱ፡እምኀበ፡ንጉሠ፡ባቢሎን፡ እንተ፡ጸብሖት፡
እየነጋ፡እየመሸ፡ከባቢሎን፡ንጉሥ፡ ድርጎ፡ተሰጠው፤

እስከ፡እለ፡ሞቱ፡በኵሉ፡መዋዕለ፡ሕይወቱ፡
ባለ፡በዘመኑ፡ሁሉ፡እስኪሞት፡ ድረስ፡ድርጎ፡ተሰጠው፤

ተፈጸመ፡ዘኤርምያስ፡ነቢይ።



# መጽሐፈ ፡ ባሮክ ፤

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ዝንቱ፡ነገረ፡መጽሐፍ፡ዘጸሐፈ፡ ባሮክ፡ወልደ፡ኔርዩ፡
የኔርዩ፡ልጅ፡ባሮክ፡የጻፈው፡ የመጽሐፍ፡ነገር፡ይህ፡ነው፤

ወልደ፡ማሴው፡
ኔርዩን፡የማሴው፡ልጅ፡አለው፤

ወልደ፡ሴዴቅዩ፡
ማሴውን፡የሴዴቅዩ፡ልጅ፡አለው፤

ወልደ፡ኬልቅዩ፡
ሴዴቅዩን፡የኬልቅዩ፡ልጅ፡አለው፤

ባቢሎን፤
ወደ፡ባቢሎን፡የመጣ፡የኔርዩ፡ልጅ ባሮክ፡የጻፈው፡የመጽሐፍ፡ነገር፡ ይህ፡ነው፤

፪፤ በኃምስ፡ዓመት፡
ሴዴቅያስ፡በነገሠ፡በአምስተኛው፡ ዘመን፤ አንድም፡ወተቀንየ፡ ኤልያቄም፡ሠለስተ፡ዓመተ፡ይላልና፡ ከኤልያቄም፡ሁለት፡ዓመት፤ የሴዴ ቅያስ፡ሦስት፡አምስት፡ያለው፡ ይህንን፡ነው፤

በሰቡዓ፡ሠርክ፡
ሠርቀ፡ወርኅ፡በባተ፡በሰባተኛው፡ ቀን፡ያልታወቀ፡ወርኅ፡ነው፤

አመ፡ነሥእዋ፡ፋርስ፡ለኢየሩሳሌም፡
ከመ፡ነሥእዋ፡ሲል፡ነው፤ የፋርስ፡ ሰዎች፡ኢየሩሳሌምን፡እንዲማርኳት፤

ወአውዓይዋ፡በእሳት፡
በእሳትም፡እንዲያቃጥሏት፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ቢል፡የፋርስ፡ሰዎች፡ኢየ ሩሳሌምን፡ከማረኳት፡በኋላ፡ወአው አይዋ፡በእሳትም፡ካቃጠልዋት፡ በኋላ፡ በኢኮንያን፡ጊዜ፤ አንድም፡ እምቅድመ፡ይንሥእዋ፡ቢል፡የፋርስ፡ ሰዎች፡ኢየሩሳሌምን፡ሳይማርኳት፡ በእሳትም፡ሳያቃጥሏት፡በሴዴቅያስ፡ ጊዜ፡የመጣ፡የመጽሐፍ፡ነገር፡ይህ፡ ነው፤

፫፤ወአንበበ፡ባሮክ፡ዘ፡መጽሐፈ፡ ዘተጽሕፈ፡
ባሮክ፡የተጻፈውን፡ይህን፡መጽሐፍ፡ አነበበ፤ ጸሐፊ፡የጻፈውን፡የጐደ ለውን፡ ለመምላት፡የጠመመውን፡ ለማቅናት፡መልሶ፡እንዲያነብብ፡ አነበበ፤

ኀበ፡ኢኮንያን፡ወልደ፡ኢዮአቄም፡ንጉሠ፡ ይሁዳ፤
ወደ፡ይሁዳው፡ንጉሥ፡ወደ፡ ኢዮአቄም፡ልጅ፡ወደ፡ኢኮንያን፡ የሚሰደውን፤አንድም፡እርሱ፡የሚል ከውን፤

ወኵሉ፡ሕዝብ፡ዘመጽአ፡
ወደ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡የሚሰደውን፤

፬፤ ወለአከ፡ኢየሩሳሌም፡ኀበ፡ካህናት፡
በኢየሩሳሌም፡ወደ፡አሉ፡ካህናትም፡ የሚልከውን፡አነበበ፤አንድም፡ኀበ፡ ኢኮንያን፤ከይሁዳው፡ንጉሥ፡ከኢዮ አቄም፡ልጅ፡ከኢኮንያን፡ዘንድ፡ የመጣውን፤ ወኵሉ፡ሕዝብ፡ከሕ ዝቡም፡ዘንድ፡የመጣውን፡ወለአከ፡ ኢየሩሳሌም፤በኢየሩሳሌም፡ካሉ፡ከካ ህናቱም፡ዘንድ፡የሚልከውን፡ይህን፡ መጽሐፍ፡አነበበ፤

www.ethiopianorthodox.org